| ፫፻፴፬ | ሕክምናና የመፈወስ ሙያዎችንና ሆስፒታሎችን መቆጣጠር | 521 |
| ፫፻፴፭ | የማስታወቅ ግዴታን አለመፈፀም | 522 |
| ፫፻፴፮ | የማከምን ተግባር አለመፈፀም | 522 |
| ፫፻፴፯ | ሬሳን ስለመቅበርና ስለማቃጠል የወጣውን ደንብ መጣስ | 523 |
| | ርዕስ ሁለት | |
| | በሰዎችና በንብረቶች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች | |
| | ምዕራፍ አንድ | |
| ፫፻፴፰ | በዚህ ርእስ ሥር ባልተሸፈኑ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ያለውን ተካፋይነት የሚመለከት ጠቅላላ ድንጋጌ | 523 |
| ፫፻፴፱ | የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ርዕስ ስር በተመለከቱት የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ያለው ተካፋይነት | 524 |
| | ምዕራፍ ሁለት | |
| | በሰዎች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች | |
| | ክፍል አንድ | |
| | ለሰውነት ጥበቃ የወጡ ደንቦችን መተላለፍ | |
| ፫፻፵ | የእጅ እልፊትና ቀላል የኃይል ድርጊት | 524 |
| ፫፻፵፩ | ሬሣን ወይም ቁስለኛን አለማስታወቅ | 525 |
| ፫፻፵፪ | በግል ነፃነት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች | 525 |
| ፫፻፵፫ | የግል ምስጢር የመጠበቅ መብትን መንካት | 526 |
| ፫፻፵፬ | በክብር ላይ የሚፈጸሙ ቀላል ጥፋቶች | 526 |
| | ክፍል ሁለት | |
| | በመልካም ጠባይ /ሞራሊቲ/ ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች | |
| ፫፻፵፭ | በመልካም ሥነ ምግባርና መልካም ጠባይ /ሞራሊቲ/ ላይ የሚፈፀሙ ጥፋቶች | 527 |
| ፫፻፵፮ | አስነዋሪ የዝሙት ጥያቄ እና የብልግና ተግባር | 527 |
| ፫፻፵፯ | ለብልግና ተግባር የሚያነሳሳ ማስታወቂያና መግለጫ ማውጣት | 528 |
| ፫፻፵፰ | የማስወረጃ ዘዴዎችን ማስተዋወቅ | 528 |
| | ምዕራፍ አራት | |

| አንቀጽ ቁጥር | የአንቀጽ ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| | በንብረት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች | |
| | ክፍል አንድ | |
| | ብሔራዊ ሀብቶችን መጠበቅ | |
| ፰፻፺፱ | ታሪካዊ፣ ኪነ-ጥበባዊ እና የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅ | 528 |
| ፰፻፲ | እፅዋትንና እንስሳትን መጠበቅ | 529 |
| | ክፍል ሁለት | |
| | ሌሎች ንብረቶችን መጠበቅ | |
| ፰፻፲፩ | የመንግሥት እና የግል ንብረቶችን መጠበቅ | 529 |
| ፰፻፲፪ | ቀላል ስርቆት | 530 |
| ፰፻፲፫ | እሸት መቅጠፍና ከማሣ መቃረም | 531 |
| ፰፻፲፬ | አጠራጣሪ የሆኑትን አንዳንድ ዕቃዎች ያለምክንያት መያዝ | 531 |
| ፰፻፲፭ | ንብረቶችን መሰወርና አግባብ ላለው ባለሥልጣን አለማስታወቅ | 532 |
| ፰፻፲፮ | የሌላ ሰውን ንብረት ማበላሸት ወይም ዋጋው እንዲቀንስ ማድረግ | 532 |
| ፰፻፲፯ | በሕዝብ ሀውልቶች ላይ ጉዳት ማድረስ | 533 |
| | ክፍል ሦስት | |
| | በንብረት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች በጠቅላላው | |
| ፰፻፲፰ | የሌላውን ሰው ጥቅም በተንኰል መጉዳት | 533 |
| ፰፻፲፱ | ወስላታነት | 534 |
| ፰፻፳ | ሌሎች ጥቅሞችን በማጭበርበር ማግኘት | 534 |
| ፰፻፳፩ | አውቃለሁ ባይነት | 534 |
| ፰፻፳፪ | ያለፈቃድ ገንዘብ መሰብሰብ | 535 |
| | ምዕራፍ አራት | |
| | በኢኮኖሚ፣ ንግድና የባሕር አስተዳደር ጉዳዮች ላይ የሚፈጸሙ | |
| | የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች | |
| ፰፻፳፫ | የንግድና የሂሳብ መዛግብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መተላለፍ | 535 |
| ፰፻፳፬ | በግዴታ የፍርድ አፈጻጸም ሥርዓት ላይ እምቢተኛ መሆን | 536 |
| ፰፻፳፭ | ስለንግድ መርከቦች የወጡትን ደንቦች መጣስ | 537 |

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የወንጀል ሕግ

## ፩፱፻፺፮ ዓ.ም.

# አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፬/፲፱፻፺፮
# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ

## መግቢያ

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሥራ ላይ ከዋለ ወደ ግማሽ ምዕት ዓመት ተጠግቷል:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ሥር ነቀል የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች በኢትዮጵያ ተካሂደዋል:: ከነዚህም ውስጥ የሃይማኖቶች፣ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የህዝቦች እኩልነት፣ የዜጐችና የነዋሪዎች ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች፣ እንዲሁም ሰብአዊ መብቶች፣ ይልቁንም እንደ ህፃናትና ሴቶች የመሳሰሉ የህብረተሰቡ ክፍሎች መብቶች፣ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በህገ-መንግሥቱ ዕውቅና ማግኘታቸው በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ:: ከዚህ ሁሉ ለውጥ በኋላ የ፲፱፻፵፱ኙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አፈፃፀም እንዲቀጥል ማድረጉ አግባብነት አይኖረውም::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የሚታየው ሌላ ክፍተት፣ የቴክኖሎጂ ዕድገትና የዘመናዊ ኑሮ ውስብስብነት የወለዳቸውን ወንጀሎች በተገቢው ሁኔታ አለማካተቱ ነው:: እንደ አይሮፕላን ጠለፋ፣ የኮምፒዩተር ወንጀሎችና በወንጀል አማካይነት የተገኘን ገንዘብና ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ (ማኒ ሎንደሪንግ) የመሳሰሉት ወንጀሎች የወንጀለኛ ምቀአ ሕጉ ያልዳሰሳቸው ናቸው:: ከዚህም ሌላ ከኖሰየመ ሆነ ከአደገኛ አደንዛዥ ዕጾች ጋር ተያይዘው የሚደረጉ ወንጀሎችን በተመለከተ፣ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ቅወሰ በማስከተላቸው ከአገርም አልፎ በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሕግ

አወጣጥም ሆነ በክትትል ረገድ ትኩረት ሲሰቡ ቢታይም እነዚህ ወንጀሎች አሳሳቢ በሆኑበት ደረጃ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በብቃት አልታቀፉም::

በዝምታ ሊታለፍ የማይገባው አንድ ሌላ ጉዳይ፣ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በሕፃናትና በሴቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳትና ሥቃይ የሚያስከትሉ መሆኑን የወንጀለኛ መቀጫ ሕጉ እውቅና አለመስጠቱ ነው:: እርግጥ ነው፣ የሕዝቦች ባህል እንዲከበር ሕገ መንግሥቱ ይደነግጋል፤ ጐጂነታቸው በሣይንስ የተረጋገጠውን ልማዶች ግን ሕገ-መንግሥቱ አይደግፍም:: እንዲሁም ሕዝቦች የማያምኑበትና የማይደግፉት ሕግ ብዙውን ጊዜ ተግባራዊ ስለማይሆን የዚህ ዓይነቱን ሕግ ማውጣቱ ጥቅም እንደሌለው እውነት ነው:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ሕግ አውጭው ዘመናዊ ሕግ በማውጣት ኅብረተሰቡን በማስተማርና በመምራት ከጐጂ ባሕሎች እራሱን እንዲያላቅቅ ማድረግ እንደሚገባው በወንጀል ሕግ አወጣጥ ፍልስፍና የሚደገፍ ጉዳይ ነው::

ከዚህም ሌላ በነጋሪት ጋዜጣ በልዩ ልዩ ሕጐች ተበታትነው የሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች የተቻለውን ያህል በአንድነት አካትቶ አንድ አጠቃላይ (ኮምፕረሄንሲቭ) ሕግ ማውጣቱ ይደገፋል:: እንዲሁም መደበኛ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ እና የተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ጎን ለጎን እንዲሰሩ ማድረጉ የዜጐችን እኩልነት ያላገናዘበ በመሆኑ አንድ አጠቃላይ የወንጀል ሕግ መኖሩ የዚህ አይነቱ አሰራር እንዲያከትም ያደርገዋል::

ከላይ የተጠቀሱትን ጉድለቶች አስወግዶ የተሟላ የወንጀል ሕግ ለማውጣት ከፍተኛ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ ክፍሎች በሙሉ ተደርጓል:: በፍትሕ ሚኒስቴርና በፍትሕና ሕግ

ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት የተዘጋጁ ረቂቅ የወንጀል ሕጎች ውይይት ተካሂዶባቸዋል:: የሕግና የሕክምና ባለሙያዎች፣ የአእምሮ ስነጠበብት፣ ልዩ ልዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የሙያ ማህበሮች አስተያየት በመስጠት ለሕጉ አወጣጥ አብይ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ሕዝቦች በአዲስ አበባና በክልሎች ከየሥራ ዘርፉና ከየማህበሩ ወኪሎቻቸውን በመላክ በየአካባቢው በተደረጉ ስብሰባዎች በረቂቅ ሕጉቹ ላይ ጠቃሚ አሳቦችን ሊያቀርቡ ችለዋል:: እንደ ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈርና እንደ ከባድ ስርቆት ባሉት ወንጀሎች ላይ ትጣቱ የከበደውም በዋነኛነት የሕዝብን ሐሳብ መሰረት በማድረግ ነው:: ከዚህም ሌላ፣ የወንጀል ሕጉን ይዘት ለማዳበር የሕግ ምሁራን አስተያየቶችና የውጭ አገር ሕግጋትም ሆኑ ልምዶች ተቃኝተዋል::

በመጨረሻም ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነጥብ የቅጣት አወሳሰን ጉዳይ ነው:: ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ጉዳዩች ላይ ተመሣሣይ ቅጣት የሚወሰኑበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ በሕጉ ድንጋጌዎች ላይ አንዳንድ አበይት ለውጦች ተካሂደዋል:: የቅጣት አወሳሰንን ውስብስብና አስቸጋሪ የሚያደርጉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች እንዲሻሻሉ ተደርጓል:: ፍርድ ቤቶች ቀላል ከሆነው አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ በጥንቃቄ መርምረው ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት መወሰን የሚያስችላቸው ድንጋጌ ተካቷል:: የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥም ሆነ ለመቆጣጠር የሚያስችል የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (ማንዋል) እንዲወጣ ይደረጋል::

ከቅጣት አወሳሰን ጋር ተያይዞ መነሣት ያለበት ነጥብ የወንጀል ሕግ ዓላማ የኅብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ መሆኑ ነው። ኅብረተሰቡን የሚጠብቀውም ወንጀል እንዳይፈፀም በመከላከል ሲሆን ይህንን ግብ የሚመታበት አንዱ ዋናው መንገድ ቅጣት ነው። ወንጀል አድራጊዎች መቀጣታቸው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ ያደርጋል፤ ለወደፊቱም ወንጀል ለሚፈጽሙ ሰዎችም ማስጠንቀቂያ ይሆናል። በተወሰኑ ወንጀሎች ረገድ የእስራት ወይም የሞት ቅጣት ተፈፃሚ ቢሆንም ዋናው አስተሳሰብ ጥፋተኞቹ ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው በኅብረተሰቡ ላይ ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈጽሙበት ለመከልከል ነው። እንዲህ በሆነ ጊዜም ከሞት ቅጣት በቀር የዕድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው ጥፋተኞች እንኳ ቅጣታቸውን ሳይጨርሱ በአመክሮ ሊለቀቁ ይችላሉ፤ በአንዳንድ ወንጀሎች ረገድም የቅጣት ውሳኔ ሳይሰጥ ወይም ቅጣቱ ቢወሰንም ተፈፃሚ ሳይሆን ጥፋተኞች በገደብ ሊለቀቁ ይችላሉ። ይህም ጥፋተኞች ሰላማዊ ኑሮ እንዲመሩ የሚያደርግ ሲሆን የወንጀል ሕጉ ለጥፋተኞች መታረም የሰጠውን ከፍተኛ ስፍራ ያሳያል። ጥፋተኞች በማረሚያ ቤት ባሉበት ጊዜ እንኳ ታስረው እንዲማቅቁ በማድረግ ፈንታ ከማረሚያ ቤት ሲወጡ በሚጠቅማቸው ልዩ ልዩ የሙያ ሥራ እንዲሰለጥኑና የቀለም ትምህርት እንዲማሩ መደረጉ ለጥፋተኞች ተሃድሶ የወንጀል ሕጉ ያለውን ከፍተኛ ግምት ያረጋግጣል።

የወንጀል ሕጉ ስለነዚህ ጉዳዮች በግልጽ መደንገጉ ፍርድ ቤቶች ቅጣት ሲወስኑ የሕጉን ዓላማና የቅጣትን ልዩ ልዩ ግቦች ከግምት እንዲያስገቡ በማቀድ እንደሆነ መታወቅ ይገባዋል።

ይህ ሁሉ ያላሰለሰ ጥረት ተደርጎ የተሻሻለው የወንጀል ሕግ፣ የሀገሪቱ መንግሥትና የሕዝቦቹ ስርዓት፣ ሰላምና ደህንነት እንዲሁም የዜጎቹ እና የነዋሪዎቹ መብቶችና ነፃነቶች መከበራቸውን እንደሚያረጋግጥ ይታመንበታል።

የወንጀል ሕጉ የሀሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ለማፋጠን የሚያስችልና የተረጋጋ የነፃ ገበያ ስርዓት እንዲጐለብት የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገር በሀገራችን ትክክለኛ የፍትሕ ስርዓት ለማስፈን እንደሚረዳ በመታመኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፭) መሰረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል።

## ፩ <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የ፲፱፻፺፮ ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪ <u>የተሻሩ ሕጐች</u>

የሚከተሉት አዋጆች:-

ሀ/ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣

ለ/ በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም የወጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፬/፲፱፻፸፬፣

ከግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጀምሮ የተሻሩ ናቸው

## ፭ ልዩ ሁኔታ

በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፫ ላይ እንደተደነገገው፣ የተለዩ ሕጎችና የልዩ ልዩ ደንቦች አፈፃፀም እንደተጠበቀ ነው።

## ፮ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የወንጀል ሕግ ልዩ መጽሐፍ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር ፩፻፷፭/፲፱፻፶፪ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ . . .. . . . . ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ.ም

ግርማ ወ/ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

BACK

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የወንጀል ሕግ

## መጀመሪያ ታላቅ ክፍል
## ጠቅላላ ክፍል

## አንደኛ መጽሐፍ
## ወንጀሎችና ወንጀል አድራጊው

## ርዕስ አንድ
## የወንጀል ሕግና የአፈፃፀሙ ወሰን

### ምዕራፍ አንድ
### የሕጉ ተፈፃሚነት ወሰን

አንቀጽ ፩ ዓላማና ግብ

የወንጀል ሕግ ዓላማ፣ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግሥት፣ የሕዝቦቿን፣ የነዋሪዎቿን፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፅሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው።

አንቀጽ ፪ የሕጋዊነት መርህ

፩ የወንጀል ሕግ ስለ ልዩ ልዩ ወንጀሎችና በወንጀል አድራጊዎች ላይ ስለሚፈፀሙት ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች በዝርዝር ይደነግጋል።

BACK



፪ ፍርድ ቤት ሕገወጥነቱ በሕግ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደወንጀል ሊቆጥረው እና ቅጣት ሊወስንበት አይችልም::

ፍርድ ቤቱ በሕግ ከተደነገጉት በቀር ሌሎች ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን አይችልም::

፫ በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሰላል በማለት ወንጀልነቱ በግልፅ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት ፍርድ ቤት እንደወንጀል ሊቆጥረው አይችልም::

፬ ከላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች፣ ፍርድ ቤት ሕጉን እንዳይተረጉም አያግዱትም:: የሕጉ አነጋገር አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ ሕጉ ሊደርስበት ያሰበውን ግብ ለማረጋገጥ እንዲቻል ሕግ አውጪው ባቀደው ትርጉምና በሕጉ መንፈስ መሠረት ፍርድ ቤቱ መተርጐም አለበት::

፭ ማንም ሰው በሕግ መሠረት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከዚህ ቀደም በተቀጣበት ወይም ሌላ ሕጋዊ እርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም::

<u>አንቀጽ ፫ ሌሎች የሚያስቀጡ ሕጐች</u>

ይህ የወንጀል ሕግ ቢኖርም ቅጣት የሚደነግጉ ደንቦችና ልዩ ሕጐች የተጠበቁ ናቸው::

በእነዚህ ደንቦችና ሕጐች ላይ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር የዚህ ሕግ መርሆች ለእነርሱም ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## ንቀጽ ፬ በሕግ ፊት እኩል መሆን

የወንጀል ሕግ የሰውን፣ የማህበራዊ ኑሮ ደረጃን፣ የዘርን፣ የብሔርን፣ የብሔረ ሰብን፣ የቀለምን፣ የጾታን፣ የቋንቋን፣ የሃይማኖትን፣ የፖለቲካን ወይም የሌላ አስተሳሰብን፣ የሀብትን፣ የትውልድን ወይም የሌላ አቋምን ልዩነት ሳያደርግ በሁሉም ላይ በእኩልነት ተፈጻሚ ይሆናል።

በወንጀል አድራጊዎች መሐከል ልዩነት የሚደረገው ምንጩ የዓለም አቀፍ ሕግ ወይም ሕገመንግሥት ሆኖ በዚህ ሕግ የተደነገገ መሠረታዊ መብት ሲኖር፣ ወይም የወንጀሉ ከባድነት፣ የጥፋቱ ደረጃ ወይም የአድራጊው ዕድሜ፣ ሁኔታዎች ወይም ልዩ ግላዊ ጠባዩ ወይም ወንጀሉ በሕብረተሰቡ ላይ ያስከተለው አደጋ ከግምት ውስጥ እንዲገባ ይህ ሕግ ሲደነግግ ነው።

### ምዕራፍ ሁለት
### የሕጉ አፈፃፀም ወሰን
### ክፍል አንድ
### ጊዜን የሚመለከቱ ሁኔታዎች

## አንቀጽ ፭ የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሠራ መሆኑ

፩ በዚህና በተሻረው የወንጀል ሕግ እንደወንጀል የተቆጠ ረ ድርጊት የተፈፀመው ይህ ሕግ ከመፅናቱ በፊት ከሆነ፣ ጉዳዩ የሚታየው በተሻረው የወንጀል ሕግ መሠረት ነው።

፪ ድርጊቱ በዚህ ሕግ መሠረት ወንጀል ሆኖ በተሻረው የወንጀል ሕግ ግን እንደወንጀል ካልተቆጠረና የተፈፀመው ይህ ሕግ ከመፅናቱ በፊት ከሆነ ሊያስቀጣ አይችልም።

፫ የተሻረው ሕግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈፀመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ሕግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከስስም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም፤ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ ይቋረጣል።

<u>አንቀጽ ፮ የተለየ ሁኔታ፤ የተሻለውን ሕግ ተፈፃሚ ማድረግ</u>

ይህ ሕግ እንዲፀና ከተደረገ በኋላ አድራጊው ሕጉ ከመፅናቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት፣ ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ በሥራ ላይ ከነበረው ሕግ ይልቅ ይሄኛው ሕግ ቅጣት የሚያቃልልት ሲሆን በዚህ ሕግ ላይ የተመለከተው ቅጣት ይፈፀምበታል።

ፍርድ ቤቱ ይህ ሕግ የተሻለ መሆኑን የሚወስነው በእያንዳንዱ ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በማመዛዘን ነው።

<u>አንቀጽ ፯ የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈፃፀም</u>

የተሻረው ሕግ በሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ በተፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ይህ ሕግ ከፀና በኋላ በሚሰጡ ፍርዶች ላይ የጥንቃቄ እርምጃዎችን አወሳሰን በሚመለከት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች (አንቀጽ ፻፹፬-፻፺፭) ተፈፃሚ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ ፰ የይርጋ ዘመን አፈፃፀም</u>

፩ የተሻረው ሕግ በሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ በተፈፀሙ ወንጀሎች ረገድ፣ የክስ አቀራረብና የቅጣት አፈፃፀም የይርጋ ዘመን ይህ ሕግ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ ሕግ መሠረት ይመራል።

ቢሆንም ይህ ሕግ ከመፅናቱ በፊት ያለፈው ጊዜ ለይርጋ ዘመን መታሰብ አለበት።

፪ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ ያስቀጣ የነበረ ወንጀል በዚህ ሕግ መሠረት ያለግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ሲሆን፣ ይህ ሕግ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ አቤቱታ አቅራቢው የግል አቤቱታ የማቅረብ መብቱን ካልተጠቀመበት ቀሪ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፱ በተሻረው ሕግ መሠረት የተሰጡ ፍርዶች አፈፃፀም</u>

ፍርዱ በተሻረው የወንጀል ሕግ መሠረት ተሰጥቶ እንደሆነ፣ አፈፃፀሙ የሚመራው ከዚህ በታች ባሉት መርሆች ነው።

፩ ቀድሞ ቅጣት ተወስኖበት የነበረው ድርጊት በአዲሱ ሕግ የማያስቀጣ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ሊፈፀም አይችልም፤ የተጀመረው ቅጣትም ወዲያውኑ ይቋረጣል።

፪ ለአንድ ለተወሰነ ጊዜና አላፊ ለሆኑ ምክንያቶች ሕግ የደነገገውን ግዴታ በመጣስ የወንጀል ፍርድ ተሰጥቶ እንደሆነ፣ የተባለው ጊዜ ማለፍ ምክንያት ሆኖ የተወሰነውን ቅጣት ሊያቆመው አይችልም፤ የተባለው ጊዜ ማለፉ ክስ ማቅረብንም አያግድም።

፫ ይህ ሕግ ከመፅናቱ በፊትም ሆነ በኋላ በተሰጠ ወይም በሚሰጡ ፍርዶች የተወሰኑ ቅጣቶች አፈፃፀም፣ በዚሁ ሕግ በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ይሆናል። እንዲሁም የተጣለውን መቀጮ ስለማስገባት፣ አስቀድሞ በገደብ ስለመልቀቅ እና ስለአመክሮ የሚደረገው የሥርዓቱ አፈፃፀም በዚህ ሕግ እንደተመለከተው ነው።

፬ ይህ ሕግ በፀናበት ጊዜ፣ የተወሰነበትን ቅጣት በመፈፀም ላይ የሚገኝ እስረኛ ቀደም ሲል ነፃነትን በማሳጣት የሚያስቀጣ ሌላ ወንጀል ፈፅሞ ሳይደረስበት የቀረ መሆኑ ሲታወቅ፣ ፍርዱን የሚወስንበት ፍርድ ቤት ለተቀጪው የተሻለውን የሕግ ድንጋጌ /አንቀጽ ፮/ መሠረት አድርጉ በመያዝ፣ ስለተደራራቢ ወንጀሎች

በተወሰኑ ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፲፫፯/ መሠረት ይወሰናል።

ቢሆንም በቀድሞ ፍርድ መሠረት የፈፀመው የእስራት ቅጣት ጊዜ ይቀነስለታል።

<u>አንቀጽ ፲ የወንጀለኞች ሪኮርድ መሰረዝንና መሰየምን በሚመለከት የዚህ ሕግ አፈፃፀም</u>

በተሻረው ሕግ በተሰጡ ፍርዶች መሠረት የተመዘገበ የወንጀለኞች ሪኮርድ መዝገብ የሚሰረዝበትና ወንጀለኞች የሚሰየሙበት ሁኔታ በዚህ ሕግ መሠረት ይመራል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>በቦታን የሚመለከቱ ሁኔታዎች</u>

<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

<u>ዋና አፈፃፀም</u>

<u>አንቀጽ ፲፩ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚደረጉ ወንጀሎች፣ መደበኛ ሁኔታ</u>

፩ አንድ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በዚህ ሕግ ከተመለከቱት ወንጀሎች ማናቸውንም ቢያደርግ ይህ ሕግ ተፈፃሚ ይሆንበታል።

የኢትዮጵያ ግዛት የብሱን፣ አየሩንና የውኃ አካላቱን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ የግዛቱም ስፋት በሕገ መንግስቱ እንደተወሰነው ነው።

፪ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ቢኖርም፣ በዓለም አቀፍ ሕግ የማይደፈሩ መብቶች ስላሏቸው ሰዎች የተደነገጉት የተጠበቁ ናቸው።

፫ ወንጀል አድራጊው በሌላ አገር ተሸሽጐ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት በራሱ ሕግ መሠረት ጉዳዩ እንዲታይ ለማድረግ ተላልፎ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል::

## አንቀጽ ፲፪ ልዩ ሁኔታ፣ ውክልና መስጠት

፩ የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወንጀል አድርጐ ወደ ውጭ አገር በመሸሹ ምክንያት ሳይከሰስ ወይም ሳይቀጣ የቀረ እንደሆነና ከሸሸበት አገርም ተላልፎ ሊሰጥ ያልተቻለ እንደሆነ፤ በዚያው አገር ጉዳዩ እንዲታይ የኢትዮጵያ መንግሥት ሊጠይቅ ይችላል::

፪ የውጭ አገር ዜጋው ባደረገው ወንጀል በውጭ አገር ተከስሶ በጉዳዩ በተሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ነፃ የወጣ እንደሆነ፤ ተፈርዶበት ይቅርታ ወይም ምህረት አግኝቶ እንደሆነ፤ ክሱ ወይም ቅጣቱ በይርጋ ቀርቶለት እንደሆነ፤ በዚህ ወንጀል እንደገና አይከሰስም::

፫ ወንጀለኛው በውጭ አገር የተወሰነበትን ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ሳይፈፅም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ቢገኝ እና የቅጣቱ አፈፃፀም በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በይርጋ ያልታገደ ከሆነ፣ ሳይፈፅም የቀረው ቅጣት እዚሁ ይፈፀምበታል::

በቅጣቱ ዓይነት ወይም በአፈፃፀሙ ልዩነት የተገኘ እንደሆነ፣ በውጭ አገር ከተፈረደበት ቅጣት ጋር ይበልጥ ተመሳሳይ ሆኖ በሚገኘው ዓይነት ይፈፀምበታል::

<u>አንቀጽ ፲፫ በኢትዮጵያ ላይ ከግዛቷ ውጭ የሚደረግ ወንጀል</u>

ከኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል በሦስተኛ መጽሐፍ፣ አንደኛ ርዕስ፣ አንደኛ ምዕራፍና በዚሁ መጽሐፍ በአምስተኛው ርዕስ /አንቀጽ ፪፻፴፰ - ፪፻፷፣ አንቀጽ ፫፻፶፭ - ፫፻፸፬/ የተደነገጉትን በመጣስ በኢትዮጵያ መንግሥት በደህንነቱ ወይም አንድነቱ ላይ፣ በሕጋዊ ተቋማቱ ወይም ዋና ዋና ጥቅሞቹ ወይም በገንዘቡ ላይ ወንጀል ባደረገ በማናቸውም ሰው ላይ ይህ ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፲፬ የማይደፈር መብት ያለው ኢትዮጵያዊ በውጭ አገር ሆኖ የሚያደርጋቸው ወንጀሎች</u>

፩ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፲፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በውጭ አገር ያለ የኢትዮጵያ መንግሥት የዲፕሎማቲክ ወይም የቆንሲል አባል፣ የመንግሥት መልእክተኛ ወይም ወኪል በውጭ አገር ወንጀል አድርጎ ስለማይደፈር መብት ዓለም አቀፍ በሆነው ልማድ መሠረት ወንጀሉን ባደረገበት አገር ሊከሰስ የማይችል እንደሆነ፣ ይህ ሕግ ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያና በተባለው አገር ሕግ መሠረት ድርጊቱ እንደወንጀል ተቆጥሮ የሚያስቀጣ ሲሆን ነው።

፪ በኢትዮጵያ ወይም ድርጊቱ በተፈፀመበት አገር ሕግ መሠረት ወንጀሉ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጣ ሲሆን፣ አቤቱታ ካልቀረበ በስተቀር ክሱ ሊቀርብ አይችልም።

<u>አንቀጽ ፲፭ የኢትዮጵያ መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት አባል በውጭ አገር ሆኖ የሚያደርገው ወንጀል</u>

፩ ማንም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባል በዚሁ ሁኔታ ሳለ በውጭ አገር መደበኛ ሕግን በመጣስ

ወንጀል በማድረጉ ሕጉን በጣሰበት ቦታ ቢያዝና ቢከሰስ፣ በዚያው አገር ሕግና በግዛቱ ባለው የዳኝነት ሥልጣን መሠረት ይዳኛል።

ሸሽቶ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የገባ እንደሆነ፣ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፫፩(፪) መሠረት ይከሰሳል።

፪ የተፈፀመው ወንጀል በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፪፻፷፱ - ፫፻፳፪ ከተዘረዘሩት፣ በዓለም አቀፍ ሕግ ወይም በወታደራዊ ተግባር ላይ ከሚደረጉት ወንጀሎች አንዱ ከሆነ የመከላከያ ሠራዊቱ አባል የሚዳኘው በዚህ ሕግና በኢትዮጵያ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ነው።

## አንቀጽ ፲፯ በውጭ አገር የተሰጡ ፍርዶች ውጤት

፩ ማንም ወንጀል አድራጊ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፲፩፣ ፲፫፣ ፲፬(፩) እና ፲፭(፪) መሠረት በኢትዮጵያ ዋና የዳኝነት ሥልጣን ሥር ተጠያቂ ሲሆን በውጭ አገር የተፈረደበት ቢሆንም እንኳ በኢትዮጵያ ከተገኘ ወይም ተላልፎ ከተሰጠ በዚያው ጉዳይ ላይ እንደገና ሊከሰስና ሊፈረድበት ይችላል።

፪ በውጭ አገር ፍርድ ከክስ ውጭ መሆኑ ወይም በነፃ መለቀቁ በዚህ ሕግ መሠረት እንደገና ከመከሰስ ወይም ከመቀጣት አያድነውም።

፫ ተከሳሹ ባደረገው ወንጀል በውጭ አገር ተፈርዶበት ቅጣቱን በሙሉም ሆነ በከፊል ፈፅሞ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ አዲስ ቅጣትን በሚወስንበት ጊዜ ቀድሞ የፈፀመውን ቅጣት አስቦ ይቀንስለታል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ምትክ አፈፃፀም

### አንቀጽ ፲፯ በዓለም አቀፍ ሕግና ሥርዓት ላይ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ወንጀሎች

፩ ማንም ሰው ከኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ:-

ሀ/ ኢትዮጵያ ተስማምታ በተቀበለችው ዓለም አቀፍ ውል ወይም ስምምነት፣ ወይም ሕግ ውስጥ እንደ ዓለም አቀፍ ወንጀል ሆኖ የተቆጠረውን ድርጊት በመፈፀም፤ ወይም

ለ/ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፭፻፳፭፣ ፭፻፺፱፣ ፮፻፴፭፣ ፮፻፴፮፣ ፮፻፵ ወይም ፮፻፵፩ የተመለከተውን ተላልፎ፣ የሕዝብን ጤንነት ወይም የሕዝብን ሞራል በመጉዳት፤

ወንጀል ያደረገ እንደሆነ፤ በውጭ አገር ተከስሶ የመጨረሻ ውሳኔ ካልተሰጠ በቀር በዚሁ ሕግ ድንጋጌዎችና ከዚህ በታች በተመለከቱት ጠቅላላ ሁኔታዎች (አንቀጽ ፲፱ እና ፳(፪)) መሠረት ክሱ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ይታያል።

፪ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፬ እና ፲፮(፪) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው።

### አንቀጽ ፲፰ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ሌሎች ወንጀሎች

፩ ማንም ሰው ከኢትዮጵያ ውጭ በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ ወይም ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ከኢትዮጵያ ውጭ ከዚህ በላይ በተመለከቱት አንቀጾች ከተገለጹት ወንጀሎች ሌላ የፈፀመ እንደሆነ፤ አድራጊው በዚሁ ወንጀሉ በውጭ አገር ሳይከሰስ ከቀረ ይህ የወንጀል ሕግ በምትክነት ተፈጻሚ የሚሆነው:-

BACK



ሀ/ ድርጊቱ በተፈፀመበት አገር ሕግና በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጎ እንደሆነ፤ እና

ለ/ የተፈፀመው ወንጀል ከባድነት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ተከሳሹ ተይዞ ተላልፎ እንዲሰጥ ለማድረግ በቂ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፤

ነው::

፪ ማንም የውጭ አገር ሰው ከኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ ሌላ ወንጀል ፈፅሞ ወደ ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ በዚህ ሕግ እጁ ተላልፎ ካልተሰጠ ወይም በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ኢትዮጵያ ውስጥ ሊከሰስና ጉዳዩ ሊታይ የሚችለው በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረት ወንጀሉ ከአስር ዓመት ባላነሰ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን ነው::

## አንቀጽ ፲፪ ይህ ሕግ በምትክነት የሚፈፀምበት ሁኔታ

፩ ይህ ሕግ በምትክነት ተፈፃሚ የሚሆነው:-

ሀ/ ወንጀሉ በተደረገበት አገር ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ወንጀሉ የሚያስከስሰው በግል አቤቱታ ብቻ ሲሆን አቤቱታው ቀርቦ እንደሆነ፤

ለ/ አድራጊው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተገኘ እንደሆነና ተላልፎ ያልተሰጠ እንደሆነ፤ ወይም በዚሁ ባደረገው ወንጀል ተላልፎ ለኢትዮጵያ ተሰጥቶ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን በፈፀመበት አገር አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ይቅርታ ያላገኘ እንደሆነ ወይም ወንጀሉ በተደረገበት አገር ሕግ

ወይም በኢትዮጵያ ሕግ በይርጋ ያልታገደ እንደሆነ፤

ነው::

፪ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፲፯ እና በአንቀጽ ፲፰(፪) የተደነገጉትን የወንጀል ዓይነቶች በሚመለከት፣ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በፊደል "ሀ" እና "ሐ" የተዘረዘሩት ሁኔታዎች የግዴታ መሟላት አይኖርባቸውም::

፫ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ከማቅረቡ በፊት የፍትህ ሚኒስትሩን ማማከር ይኖርበታል::

፬ የውጭ አገሩና የኢትዮጵያ የወንጀል ሕጎች ለተፈፀመው ወንጀል በሚደነግጉት ቅጣት መካከል ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሹን በሚጠቅመው ሕግ ላይ የተደነገገው ቅጣት ነው::

<u>አንቀጽ ፳ በውጭ አገር የተሰጠ የፍርድ ውጤት</u>

፩ የኢትዮጵያ ሕግ በሌላ አገር ሕግ ምትክነት ብቻ በተከሳሹ ላይ በሚፀናበት ጊዜ ሁሉ /አንቀጽ ፲፭(፩)፣ ፲፯ እና ፲፰/ ወንጀል አድራጊው በዚሁ ጉዳይ በውጭ አገር ተከስሶ በሚገባ ነፃ ወጥቶ እንደሆነ ወይም የማያስከስሰው ነው ተብሎ ተለቆ እንደሆነ፤ የኢትዮጵያ ሕግ ተፈፃሚ አይሆንበትም::

፪ በውጭ አገር ክሱ ታይቶ ቅጣት የተወሰነበት ወንጀለኛ ቅጣቱን ያልፈፀመ ወይም ከፊሉን ብቻ የፈፀመ እንደሆነ፤ ጠቅላላው ወይም ቀሪው ቅጣት በኢትዮጵያ ሕግ ወይም ጉዳዩን አይቶ በወሰነው አገር ሕግ መሠረት በይርጋ ካልታገደ በስተቀር በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል:: የአንቀጽ ፲፪(፫)

BACK



ድንጋጌ እንደአስፈላጊነቱ ለዚህ አንቀጽ ተፈፃሚ ይሆናል::

ስክፍል ሦስት
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ ፳፩ አሳልፎ መስጠት

፩ ማንም የውጭ አገር ሰው ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ ሆኖ መደበኛ የወንጀል ሕግን በመተላለፍ ላደረገው ወንጀል የተከሰሰ ወይም የቅጣት ፍርድ የተፈረደበት እንደሆነና ወደ ኢትዮጵያ የገባ እንደሆነ፤ ሕጉ እንደሚያዘው በመንግሥታት መካከል በተደረገ ውል ወይም በዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ መሠረት ወንጀለኛው ያደረገው ወንጀል የኢትዮጵያን መንግሥት በቀጥታና በዋና ባለጉዳይነት የማያገባው ሆኖ ሲገኝና ወንጀሉን ያደረገበት አገር መንግሥትም በግዛቱ ሕግ መሠረት እንዲፈረድበት ወይም ቅጣቱን እንዲፈፅም አግባብ ያለው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፤ ተይዞ ለፍርድ ወደሚቀርብበት ወይም ቅጣቱን ወደሚፈጽምበት አገር ተላልፎ ሊሰጥ ይቻላል /አንቀጽ ፲፫/::

፪ ወንጀሉ በተደረገ ጊዜም ሆነ ወይም የአድራጊው እጅ ተላልፎ እንዲሰጥ የሚያሳስብ ጥያቄ በቀረበበት ጊዜ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነውን ማንኛውንም ሰው ለሌላ አገር መንግሥት አሳልፎ መስጠት አይቻልም:: ሆኖም አድራጊው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ይዳኛል::

፫ አሳልፎ የመስጠትን ነገር የሚያመጡ ወንጀሎች በተደረጉ ጊዜ ሁሉ ጥያቄው በኢትዮጵያ መንግሥት ሕጐችና በሚሰራባቸው ዓለም አቀፍ ውሎች መሠረት ይፈፀማል::

BACK



## አንቀጽ ፳፪ ለውጭ አገር ፍርዶች እውቅና መስጠት

፩ የተከሳሹን ያለፈ የሕይወት ታሪክና ቅጣት የሚያከብዱ ምክንያቶችን፣ አመክሮ መስጠትንና ማስቀረትን፣ ደጋጋሚነትና የሚያስከትለውን ቅጣት፣ የደህንነት ማረጋገጫ እርምጃዎችን፣ ተከሳሽ በሕግ ፊት ችሎታ የሌለው መሆኑንና ከማዕረግ መሻርን፣ መሰየምን፣ የካሣ አከፋፈልን፣ የተወሰዱ ዕቃዎችን መመለስን እና ሌሎች የፍትሐብሔር ነክነት ያላቸውን ነገሮች እንዲሁም በዚህ ሕግ ላይ የተደነገጉ ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት በውጭ አገር ለተሰጠ ፍርድ እውቅናን መስጠት ይቻላል::

፪ ለውጭ አገር ፍርድ እውቅና መስጠት የሚቻለው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት እንደወንጀል በተቆጠረ ድርጊት ላይ በልዩ ፍርድ ቤት ሳይሆን በመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ፍርድ፣ አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ባለሥልጣን የተረጋገጠ ሲሆን ነው::

በውጭ አገር የተሰጠውን ፍርድ አውቆ መቀበል የሚቻለው ትክክለኛነቱ በተመሰከረለት የወንጀለኞች የሪኮርድ ወይም የፍርድ ቅጅ፣ የዳኝነት ወይም የአስተዳደር ሥልጣን ባለው የውጭ አገር መሥሪያ ቤት ትክክለኛነቱ በተረጋገጠ ማስረጃ፤ ወይም እምነት ሊጣልበት በሚገባ በማናቸውም ሌላ ዓይነት ማስረጃ መሠረት ነው::

### ርዕስ ሁለት

### ወንጀልና አፈፃጸሙ

### ምዕራፍ አንድ

### የወንጀል ድርጊት

## አንቀጽ ፳፫ የሚያስቀጣ ወንጀል

፩ ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገውን ድርጊት መፈፀም ወንጀል ነው::

BACK



በዚህ ሕግ ውስጥ ድርጊት ማለት በሕግ የተከለከለውን ማድረግ ወይም በሕግ የታዘዘውን አለማድረግ ነው::

፪ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው::

፫ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ ቢኖርም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፴፬ በተደነገጉት ሁኔታዎች መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል::

፬ አንድ ወንጀል ማስቀጣት የሚችለው ፍርድ ቤት ወንጀሉ መፈፀሙን ሲያረጋግጥና ቅጣት የሚጣልበት ሆኖ ሲያገኘው ነው::

<u>አንቀጽ ፳፬ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት</u>

፩ የአንድ ወንጀል አፈፃፀም አንድ የተወሰነ ውጤት እንደሚያመጣ የታወቀ በሆነበት ጊዜ ሁሉ፣ ውጤቱን ያስገኘው ተከሳሽ የተከሰሰበት ድርጊት መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ወንጀሉ እንደተደረገ አይቆጠርም::

በምክንያቱና በውጤቱ መካከል ግንኙነት አለ የሚባለውም በነገሮች የታወቀ ወይም የተለመደ ሂደት የተከሳሽ ድርጊት ውጤቱን ለማስገኘት የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው::

፪ ለተከሳሹ እንግዳ ከሆነ የሌላ ሰው አድራጎት፣ ፍጥረታዊ ነገር ወይም አጋጣሚ ሁኔታ የተነሳ አስቀድሞ የደረሰ፣ የተደረበ ወይም ጣልቃ የገባ ምክንያት በተገኘ ጊዜ ይህ እንግዳ ምክንያት ራሱን ችሎ አንድን ውጤት ያስከተለ ሲሆን በተከሳሹ ድርጊትና በውጤቱ መካከል ሊኖር ይችል የነበረው ግንኙነት ይቋረጣል::

የተቋረጠው ድርጊት ራሱን የቻለ ወንጀል ሆኖ ሲገኝ የዚሁ ወንጀል ቅጣት ይፈፀምበታል::

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው ውጤት ማስከተል ባይችሉም ተጣምረው ውጤትን በሚያስከትሉበት ጊዜ በእያንዳንዱ ምክንያት እና በተገኘው ውጤት መካከል ግንኙነት እንዳለ ይቆጠራል::

## አንቀጽ ፳፭ ወንጀል የተደረገበት ጊዜና ቦታ

፩ ወንጀል እንደተደረገ የሚቆጠርበት ሥፍራና ጊዜ ወንጀለኛው የወንጀል ድርጊቱን ያደረገበት ወይም ሕጉ የሚያስገድደውን ተግባር ሳይፈፅም የቀረበት ሥፍራና ጊዜ ነው::

የወንጀል ሙከራ እንደተደረገ የሚቆጠርበት ጊዜና ቦታ፣ አድራጊው የወንጀሉን ሙከራ የሚያቋቁሙትን የመጀመሪያ ድርጊቶች ያደረገበት ወይም ሳያደርግ የቀረበት ጊዜና ቦታ ነው::

፪ ወንጀሉ በአንድ ጊዜ የማይደረግ በመሆኑ ድርጊቱና ውጤቱ በአንድ ቦታ ላይ በማይገኙበት ጊዜ ወንጀሉ እንደተደረገ የሚቆጠረው፣ ድርጊቱ በተደረገበት ወይም ውጤቱ በተገኘበት ቦታ ነው::

እንዲሁም የወንጀል ሙከራ እንደተደረገ የሚቆጠረው አድራጊው ወንጀሉን ለማድረግ በሞከረበት ወይም ውጤቱ ይገኝበታል ብሎ ባሰበው ቦታ ነው::

የክስ አቀራረቡን በሚመለከት፣ ወንጀሉ ውጤት ያገኘበት ሥፍራ ፍርድ ቤት፣ ወንጀሉ ለተደረገበት ቦታ ፍርድ ቤት ምትኩ ነው::

፫ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፳፭ ላይ እንደተደነገገው፣ የወንጀል ድርጊቶች መቀላቀል ወይም መደጋገም ለአንድ ተራ ወይም ቅጣት ለሚያከብድ ወንጀል ማቋቋሚያ ሲሆን ወይም የወንጀሉ ድርጊት ተራዝሞ ሲቆይ፣ ከተቀላቀሉት ወይም ከተደጋገሙት ድርጊቶች አንዱ ወይም ተራዝሞ ከቆየው የወንጀል ድርጊት ከፊሉ የተደረገበት ቦታና ጊዜ፣ ወንጀሉ እንደተደረገበት ቦታና ጊዜ ይቆጠራል።

## ምዕራፍ ሁለት

## የወንጀል አፈፃፀም ደረጃ

### አንቀጽ ፳፯ የማሰናዳት ተግባሮች

የወንጀልን ድርጊት ለማሰናዳት ወይም ለማመቻቸት በተለይም መሣሪያዎችን በማሰባሰብ ወይም ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የተደረጉ ድርጊቶች አያስቀጡም፤ ሆኖም ድርጊቶቹ:-

ሀ/ ራሳቸው ወንጀል ሆነው የሚያስቀጡ መሆናቸው በሕግ የተደነገገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ከወንጀሎቹ ከባድነትና በአጠቃላይ ከሚያደርሱት አደጋ መጠን የተነሳ ልዩ ወንጀል መሆናቸው በሕግ በግልፅ የተደነገገ እንደሆነ፤

ያስቀጣሉ።

### አንቀጽ ፳፯ ሙከራ

፩ ማንም ሰው አስቦ ወንጀልን ለማድረግ ጀምሮ የወንጀሉን ድርጊት እስከ መጨረሻው ያልተከታተለ ወይም ለመከታተል ያልቻለ ወይም የወንጀሉ ድርጊት እንዲፈጸም እስከ መጨረሻው ተከታትሎ አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላገኘ ቢሆንም በመሞከሩ ብቻ ጥፋተኛ ይሆናል።

BACK



ወንጀሉ እንደተጀመረ የሚቆጠረው የተደረገው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደ ታሰበበት ግብ ለማድረስ የተደረገ በሆነበት ጊዜ ነው፡፡

፪ በሕጉ ላይ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር የወንጀል ሙከራ ሁልጊዜ የሚያስቀጣ ነው፡፡

ለወንጀል ድርጊት የማነሳሳት ወይም የአባሪነት ሙከራ በሕግ ተገልጾ ያስቀጣል ተብሎ ካልተደነገገ በቀር አያስቀጣም፡፡

፫ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፻፲፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የወንጀልን ድርጊት በመሞከሩ አድራጊው በመደቡ ለመፈጸም በፈለገው ወንጀል በተደነገገው ቅጣት ይቀጣል፡፡

የነገሩ ሁኔታዎች የሚገቡ ምክንያቶችን ሲያስገኙ ግን ፍርድ ቤቱ በመደበኛ የቅጣት ማቅለል ደንብ መሠረት /አንቀጽ ፻፸፱/ ቅጣቱን ለማቃለል ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ ፳፰ መተውና መፀፀት</u>

፩ አድራጊው ሊፈጽመው የነበረውን የወንጀል ድርጊት በገዛ ፈቃዱ የተወ እንደሆነ፤ የነገሩ ሁኔታዎች የሚገቡ ምክንያቶችን ሲያስገኙ ፍርድ ቤቱ በሕግ በተፈቀደው ወሰን መሠረት /አንቀጽ ፻፸፱/ ወይም እንደመሰለው /አንቀጽ ፻፹/ ቅጣቱን ያቃልልለታል፡፡ የወንጀል ድርጊቱን የተወው በሐቀኝነት ወይም ከፍ ባለ የሕሊና ስሜት በመነሳሳት ምክንያት እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ ከቅጣት ነፃ ያደርገዋል፡፡

፪ አድራጊው የወንጀሉን ድርጊት እስከ መጨረሻው አድርሶ በራሱ ፈቃድ ውጤቱ እንዳይደርስ የከለከለ ወይም ያደረገው አስተዋጽኦ መልካም ፍሬ ያስገኘ

እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን እንደመሰለው ያቃልልለታል /አንቀጽ ፸፱/።

፫ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ድንጋጌ የወንጀሉን ሥራ በፈቃዱ ለተወ ወይም ወንጀሉ ውጤት እንዳያገኝ ለማገድ በበኩሉ የተቻለውን ሁሉ ላደረገ አነሳሽ ወይም አባሪ /አንቀጽ ፴፮ እና ፴፯/ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፳፱ ሊፈፀም የማይቻል ወንጀል</u>

በማናቸውም ዘዴና መሣሪያ ወይም በማናቸውም ነገር ላይ ምንም ቢሆን ሊፈፀም የማይቻል ወንጀልን ለማድረግ ለሞከረ ሰው ፍርድ ቤቱ እንደመሰለው ቅጣቱን ያቃልልለታል /አንቀጽ ፸፱/።

አድራጊው ጉዳት ለማድረስ በማይችል በማናቸውም ዘዴ ወይም መሣሪያ፣ በአምልኮ ሥራ፣ በሞኝነት ወይም በመንፈስ ልልነት የወንጀል ድርጊት ሙከራ ባደረገ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከቅጣቱ ነፃ ያደርገዋል።

ከዚህ በላይ የተመለከቱት የአንቀጹ ድንጋጌዎች ለወንጀል አነሳሽ ወይም አባሪ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፴ ከሙከራ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች</u>

በወንጀል ሙከራ ሂደት ውስጥ የሚደረግ ድርጊት ራሱን የቻለ ሌላ ወንጀል የሚያቋቁም ሆኖ ሲገኝ፣ ለዚሁ የተወሰነው ቅጣት በአድራጊው ላይ ተፈጻሚ ይሆንበታል።

<u>አንቀጽ ፴፩ የዳኛ አስተያየት</u>

በተተወ ወይም ሳይደረግ በቀረ በልዩ ልዩ የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ሙከራ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት

BACK



ቅጣትን ለመወሰን ወይም አስፈላጊ ሲሆን ቅጣትን ለማቃለል ወይም በተለይ አንድ ቅጣት መወሰንን ጨርሶ ለመተው ፍርድ ቤቱ የነገሩን ሁኔታ ማየትና መመዘን ይገባዋል:: በተለይም የወንጀሉን ሙከራ እርምጃ መጠንና የተደረገው ሙከራ የሚያደርሰውን የአደጋ ከባድነት ደረጃ፣ ሙከራው ከፍጻሜ ሳይደርስ የቀረበትን ምክንያት፣ አድራጊው ወንጀሉን ማድረግ የተወበትንና የተጸጸተበትን ምክንያት፣ እንዲሁም ደግሞ የጥፋተኛውን ያለፈ ጊዜ የሕይወት ታሪክና የጠባዩን አደገኛነት መመርመርና መመዘን አለበት::

## ምዕራፍ ሦስት

## በወንጀል አፈፃፀም ላይ ተካፋይ መሆን

### አንቀጽ ፴፪ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ መሆን

፩ ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው:-

ሀ/ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር በተለይም በእንስሳ ወይም በተፈጥሮ ኃይል አማካይነት በእርግጥ ወንጀሉን አድርጎ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ ሲሆን፤ ወይም

ሐ/ ሕፃንን ወይም አእምሮው ያልተስተካከለውን ወይም ሁኔታውን ያልተገነዘበውን ሰው ወንጀል ለማድረግ መሣሪያ ያደረገ፣ ወይም ሌላውን ሰው ወንጀል እንዲያደርግ ያስገደደ ሲሆን፤ ነው::

BACK



፪ የተደረገው ወንጀል ከአድራጊው አሳብ በላይ ያለፈ እንደሆነ፤ ጉዳዩ የሚታየው በአንቀጽ ፶፰/፫/ በተመለከተው መሠረት ነው።

፫ በአንድ ወንጀል አደራረግ በዋና ወንጀል አድራጊነት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ተካፋይ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በመደቡ በተወሰነው መሠረት ይቀጣሉ።

ፍርድ ቤቱ የግል ሁኔታዎች /አንቀጽ ፹፩/፣ እንዲሁም እንደየጥፋታቸው መጠን የቅጣት ውሳኔ የሚመለከቱትን ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፹፰/ መከተል አለበት።

## አንቀጽ ፴፫ በልዩ ወንጀል ተካፋይ መሆን

የተለዩ ሰዎች ብቻ ሊፈፅሙት የሚቻል ወንጀል ሲያጋጥም፣ በተለይም ወታደራዊ ወንጀሎችን በሚመለከት ወታደር፣ ከመንግሥት ሥራ ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን በሚመለከት የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ሴትን አስገድዶ ለመድፈር ወንድ መሆን የሚያሻ ሲሆን ወንጀል አድራጊው የተባለው ልዩነት ባይኖረውም፣ በሙሉ ፈቃዱና ዕውቀቱ የወንጀሉ ሙሉ ተካፋይ እንደሆነ፤ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተጠያቂ ከመሆን አይድንም።

## አንቀጽ ፴፬ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት

፩ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የመንግሥት አስተዳደር አካላትን ሳይጨምር በሕግ ላይ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት በወንጀል ሊቀጣ ይችላል።

BACK



አንድ ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣውም ከኃላፊዎቹ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ፣ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ ወይም ድርጅቱን በመሣሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሣሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ነው።

፪ ድርጅቱ የሚቀጣው በአንቀጽ ፺(፫) እና (፬) መሠረት በመቀጮ ነው፤ ሲያስፈልግም ድርጅቱ እንዲታገድ፣ እንዲዘጋ ወይም እንዲፈርስ ተጨማሪ ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል።

፫ የድርጅቱ መቀጣት የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በየግላቸው ላደረጉት ወንጀል ሊወሰንባቸው የሚገባውን ቅጣት አያስቀርም።

፬ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ፣ "ድርጅት" ማለት መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ ወይም ሕዝባዊም ሆነ ግላዊ መዋቅር ያለው አካል ሲሆን፣ ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለፖለቲካ፣ ለሃይማኖት ወይም ለሌላ ሕጋዊ ዓላማ የተቋቋመንና በመንግስት እውቅና ያገኘን ማናቸውንም ማህበር ያጠቃልላል።

<u>አንቀጽ ፴፫ በሕብረት የተፈፀመ ወንጀል</u>

አንድ ወንጀል ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች በሕብረት በተደረገ ጊዜ፣ የወንጀሉ ተካፋይ መሆኑ ያልተረጋገጠበት ሰው አይቀጣም።

ሆኖም በአንድ ክፍል በተመደቡ ሰዎች እንደ አድማና እንደ አምባጓሮ የመሳሰሉ ወንጀሎች በተደረጉ ጊዜ፣

በሕብረቱ ውስጥ መገኘቱ የተረጋገጠበት ሰው የማይቀጣው፣ በወንጀሉ ተካፋይ አለመሆኑን ሲያስረዳ ነው::

<u>አንቀጽ ፴፮ ማነሳሳት</u>

፩ ማንም ሰው ወንጀል እንዲደረግ አነሳሳ የሚባለው አስቦ ሌላውን ሰው በመጐትጐት፣ ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ፣ በስጦታ፣ በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲያደርግ ያግባባ እንደሆነ ነው::

፪ አነሳሹ የሚቀጣው ወንጀሉ ቢያንስ ተሞክሮ እንደሆነ ነው::

፫ የሚወሰንበትም ቅጣት ሊደረግ ለታሰበው ወንጀል ሕጉ በደነገገው ቅጣት ልክ ነው:: የነገሩም ሁኔታዎች የሚገቡ ምክንያቶችን ሲያስገኙ ሕግ በወሰነው መጠን ቅጣቱ ሊቃለል ይችላል /አንቀጽ ፻፸፱/::

፬ ዋና ወንጀል አድራጊው ያደረገው ወንጀል፣ አነሳሹ ከፈለገው በላይ በሆነ ጊዜ አነሳሹ የሚቀጣው እርሱ በፈለገው ወይም ይሆናል ብሎ ሊገምተው በሚችለው ወንጀል ብቻ ነው /አንቀጽ ፶፰(፫)/::

ይህም በሚሆንበት ጊዜ ዋና ወንጀል አድራጊው ላደረገው ከባድ ወንጀል እራሱ ብቻ ኃላፊ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፴፯ አባሪነት</u>

፩ ማንም ሰው በወንጀል ድርጊት አባሪ ነው ተብሎ የሚቆጠረው ዋና ወንጀል አድራጊው ወንጀል ከማድረጉ በፊትም ሆነ ወይም በሚያደርግበት ጊዜ፣ ወሬ በማቀበል፣ በመምከር፣ ወንጀል የሚያደርግበትን ዘዴ ወይም መሣሪያ ወይም ግዙፋዊ እርዳታ

BACK



በመስጠት ወይም ለወንጀሉ አፈፃፀም በሚጠቅም በማናቸውም ሌላ ዓይነት መንገድ እስቦ የረዳው እንደሆነ ነው::

፪ ታስቦ ለሚደረግ ወንጀል አባሪ መሆን ሁልጊዜም የሚያስቀጣ ነው::

፫ አባሪው የሚቀጣው ወንጀሉ ቢያንስ የተሞከረ እንደሆነ ነው::

፬ አባሪው የሚወሰንበት ቅጣት ሊደረግ ለታሰበው ወንጀል ሕጉ በደነገገው ቅጣት ልክ ነው:: ፍርድ ቤቱ የነገሩን ሁኔታ በማመዛዘን ሕጉ ከደነገገው ውሳኔ መስመር ሳያልፍ አባሪውን በሚመለከት ቅጣቱን ሊያቀልለት ይችላል /አንቀጽ ፻፸፱/::

፭ ዋና ወንጀል አድራጊው ያደረገው ወንጀል አባሪው ከፈለገው በላይ በሆነ ጊዜ አባሪው የሚቀጣው እርሱ በፈለገው ወይም ይሆናል ብሎ ሊገምተው በሚችለው ወንጀል ብቻ ነው /አንቀጽ ፶፰(፫)/::

ይህም በሚሆንበት ጊዜ ዋና ወንጀል አድራጊው ላደረገው ከባድ ወንጀል እርሱ ብቻ ኃላፊ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፴፰ ወንጀል ለማድረግ ማደም</u>

፩ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ ሰዎች አንድን ወንጀል ለማድረግ የተስማሙ እንደሆነ፤ ስለወንጀል ተካፋይነት እና ቅጣትን ስለማከበድ የተፃፉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑባቸዋል /አንቀጽ ፹፬(፩)(መ)/::

፪ ሆኖም በመንግሥት ዋና ዋና ጥቅሞችና በመከላከያ ኃይሉ ላይ ስለማደም፣ ሕገወጥ የሆኑ ማህበሮች ስለማቋቋምና በነዚሁ ማህበሮች ውስጥ ስለመግባት፣ ስለክፉ አድራጊ ማህበርተኞች ወይም ስለወንበዴዎች

ድርጅቶችና ስለመሳሰሉት በዚህ ሕግ በልዩ ክፍል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ናቸው /አንቀጽ ፪፻፶፯፣ ፪፻፷፬፣ ፫፻ እና ፬፻፷፰/::

## አንቀጽ ፴፱ ወንጀልን አለማስታወቅ

፩ በሕግ ላይ በግልፅ ካልተደነገገ በቀር /አንቀጽ ፪፻፶፬ እና ፫፻፴፰/ ወንጀልን ለመፈፀም የተደረገውን መሰናዳት ወይም ሙከራ፣ ፍጻሜ ያገኘ ወንጀልን ወይም ወንጀል አድራጊውን አለማሳወቅ፣ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ወንጀል አድራጊውን መርዳት ወይም አባሪነት ነው ተብሎ አያስቀጣም::

፪ ለፍርድ ባለሥልጣን ስለአለማስታወቅ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፵፫ የተደነገገው የተጠበቀ ነው::

፫ ከላይ የተመለከቱት ግዴታዎች በጠባቡ መተርጎም ይኖርባቸዋል::

## አንቀጽ ፵ ወንጀል ከተደረገ በኋላ ወንጀል አድራጊውን መርዳት

ማንም ሰው ወንጀል ከተደረገ በኋላ አስቦ ወንጀል አድራጊው ከመከሰስና ከመቀጣት እንዲያመልጥ በመደበቅ ወይም በሌላ መንገድ የረዳው እንደሆነ፣ ወይም በወንጀል የተገኘውን ዕቃ የሸሸገ እንደሆነ፣ ለእነዚህ ድርጊቶች በሕጉ ልዩ ክፍል በተደነገገው ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል /አንቀጽ ፬፻፵፰፣ ፬፻፷ እና ፮፻፹፪/::

## አንቀጽ ፵፩ የግል ምክንያቶች ለሌላ የማይተላለፉ መሆናቸው

ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም በሁለተኛ ደረጃ ተካፋይነት ወንጀል አድርገው ሲገኙ እያንዳንዱ በተካፋይነቱ ደረጃ፣ በጥፋቱ

BACK



መጠን፣ ራሱና ድርጊቱ ሊያስከትለው በሚችለው የአደጋ ከባድነት መጠን እራሱ ባደረገው ወንጀል ብቻ ይቀጣል::

ከቅጣት ለማዳን፣ ቅጣትን ለማቃለል ወይም ለማክበድ ምክንያት የሚሆኑት የነገሩ አካባቢ ሁኔታዎች፣ የጥፋተኛው ልዩ ጠባዮች፣ ወይም የግል ግንኙነቶች ለራሱ ነው እንጂ ለሌላ ሰው የሚተላለፉ አይደሉም:: እንዲሁም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው ሰው ካልሆነ በቀር ሌላውን ሰው ሊጐዳ ወይም ሊጠቅም አይችልም::

## ምዕራፍ አራት

## በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በሚደረጉ ወንጀሎች ተካፋይ መሆን

### አንቀጽ ፵፪ መርህ

፩ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፴፪ - ፵፩ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ቢኖሩም የአሳብ መግለፅን ነፃነት ለመጠበቅና ይህም ነፃነት ከመጠን እንዳያልፍ ለማገድ በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በሚደረግ ወንጀል ተካፋይ የመሆን ሁኔታ ሲያጋጥም የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፪ በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት የሚደረጉ ወንጀሎች፣ በጋዜጦች፣ በመጻሕፍት፣ በበራሪ ጽሁፎች፣ በመጽሔቶች፣ በሚለጠፉ ወረቀቶች፣ በስዕሎች፣ በሲኒማ፣ በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ስርጭት ወይም በማናቸውም ሌላ የሕዝብ መገናኛ በሆነ ዘዴ የሚደረጉ ናቸው::

፫ ወንጀሉ የተደረገው በነዚሁ በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ከሆነ የሰውን ክብር በመንካት ብቻ ሳይሆን የግልን ወይም የጋራ ደህንነትን በማደፍረስና በወንጀል ሕግ ተከብሮ የሚኖረውን ማናቸውንም ሕጋዊ መብት መንካትን ይጨምራል፤ ወንጀሉ

BACK



ተፈፀመ የሚባለውም በነዚሁ ዘዴዎች ለሕዝብ በተገለፀ ጊዜ ነው::

## አንቀጽ ፵፫ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት በሚፈጸሙ ወንጀሎች ያለው ኃላፊነት

፩ በየጊዜው በሚወጣ ህትመት አማካይነት የሚፈጸም ወንጀል የሚያስከትለው ኃላፊነት እንደሚከተለው ይሆናል::

ሀ/ የፕሬስ ውጤቱ ሲታተም በዋና አዘጋጅነት ወይም በምክትል አዘጋጅነት የተመዘገበው ሰው፣

ለ/ ህትመቱ በወጣበት ግዜ ፕሬሱ ፈቃድ የሌለው ከሆነ ወይም በንኡስ አንቀጽ ፩ /ሀ/ መሠረት ኃላፊ የሆነው ሰው ዋና አዘጋጅ ለመሆን የሚያበቁ ሁኔታዎችን የማያሟላ ሆኖ ከተገኘ ወይም በዋና አዘጋጅነት መስራቱን ያቆመ ከሆነ የፕሬሱ አሳታሚ ኃላፊ ይሆናል፣

ሐ/ የዋና አዘጋጁ ኃላፊነት የይስሙላ ከሆነ ወይም የፕሬስ ውጤቱ በወጣበት ጊዜ ዋና አዘጋጁ በስልጣኑ ለመገልገል እንደማይችል በግልጽ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ካሉ የፕሬሱ አሳታሚ ኃላፊ ይሆናል፣

መ/ እንደ ዋና አዘጋጅ እንዲሰራ በዋና አዘጋጁ የተወከለው አዘጋጅ የፕሬስ ውጤቱ በወጣበት ጊዜ እንደ ዋና አዘጋጅ ለመስራት የሚያበቁትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ወይም የተሾመበት ጊዜ ያለፈ ከሆነ ወይም ስልጣኑን ሊገለግልበት እንደማይችል በግልጽ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ካሉ የፕሬሱ ዋና አዘጋጅ ኃላፊ ይሆናል፣

ሠ/ የፕሬስ ውጤቱ በተሰራጨበት ወቅት የፕሬሱን አሳታሚ ለማወቅ ካልተቻለ በአሳታሚው ምትክ ኃላፊ የሚሆነው አታሚው ይሆናል፣

ረ/ የአታሚውን ማንነት ለማወቅ ባልተቻለ ጊዜ በአታሚው ምትክ ኃላፊ የሚሆነው የፕሬስ ውጤቱ ላይ የአታሚው ስም ያልተገለጸ መሆኑን ወይም አታሚ ያልሆነው ሰው ስም በሀሰት መገለጹን እያወቀ የፕሬስ ውጤቱን ያሰራጨ ማንኛውም ሰው ይሆናል፣

ሰ/ ከሀገር ውጭ የታተመ ሕትመትን በሚመለከት ኃላፊ የሚሆነው፣ በውጤቱ በግል ለመጠቀም ከሚያስገባው ሰው ውጭ የሆነ አስመጪ ወይም የፕሬስ ውጤቱን ያሰራጨው ማንኛውም ሰው ይሆናል።

፪ የፕሬስ ውጤቱ በየጊዜው ከሚወጣ ሕትመት ውጭ የሆነ ሌላ የሕትመት ስራ ሲሆን፣

ሀ/ የደራሲው ስም በሕትመቱ ላይ የተገለጸ ከሆነ ደራሲው ኃላፊ ይሆናል። ሆኖም የፕሬስ ውጤቱ የተሰራጨው ከደራሲው ፈቃድ ውጭ ከሆነ፣ ወይም ስሙ የብዕር ስሙ ወይም እውነተኛ ስሙ ያልሆነ ስሙ በፕሬስ ውጤቱ ላይ የተገለጸው ከፈቃዱ ውጭ መሆኑ ከተረጋገጠ ደራሲው ኃላፊ አይሆንም። በየጊዜው የሚወጡ ሕትመቶች ውስጥ የማይካተቱ የሕትመት ውጤቶችን አስመልክቶ በሚደረግ ማንኛውም የፍርድ ምርመራ የደራሲው ማንነት ሊጣራ ይችላል፣

ለ/ ሕትመቱ ከአንድ በላይ በሆኑ ደራሲዎች የተውጣጡ ጽሁፎችን እንዲይዝ የታቀደ በመሆኑ ወይም የያዘ በመሆኑ ደራሲው በንዑስ አንቀጽ ፪(ሀ) መሠረት ኃላፊ ሊሆን ካልቻለ እና በሕግ መሠረት የሕትመቱ ዋና አዘጋጅ የተሾመ ከሆነ አዘጋጁ ኃላፊ ይሆናል፣

ሐ/ በንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) ከተመለከተው የሕትመት ስራ ውጭ በሆነ ሌላ የህትመት ስራ ዋና አዘጋጁ ኃላፊ የሚሆነው ሕትመቱ ታትሞ በወጣበት ጊዜ ደራሲው በሕይወት የሌለ ከሆነ ብቻ ነው። ሆኖም የአዘጋጁ ስም፣ የብዕር ስሙ ወይም እውነተኛ ያልሆነ ስሙ፣ ከአዘጋጁ ፈቃድ ውጭ በፕሬስ ውጤቱ ላይ መገለጹ ከተረጋገጠ አዘጋጁ ኃላፊ አይሆንም፣

መ/ በየጊዜው ከሚወጣ ህትመት ውጭ ሌላ የህትመት ስራን በተመለከተ እንደ ሕትመቱ አዘጋጅ የሚቆጠረው የሕትመቱ ደራሲ ባይሆንም ሕትመቱ እንዲታተምና እንዲሰራጭ ያደረገ ማንኛውም ሰው ነው፣

ሠ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፪(ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) መሠረት ለፕሬሱ ህትመትና ስርጭት ደራሲው ወይም አዘጋጁ ኃላፊ ካልሆነ ወይም በሞት ከተለየ አሳታሚው ኃላፊ ይሆናል፣ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል እንደ አሳታሚ የሚቆጠረው የሌሎችን የሕትመት ስራዎች እየተቀበለ ለሕትመትና ለስርጭት ለማብቃት የሚሰራ ማንኛውም ሰው ነው፣

ረ/ የአሳታሚውን ማንነት ለማረጋገጥ ካልተቻለ ወይም አሳታሚ ከሌለ አታሚው ኃላፊ ይሆናል፣

ሰ/ በየጊዜው በሚወጣ ህትመት ውስጥ የማይካተት የህትመት ስራ ሲሆን የንዑስ አንቀጽ ፩ (ሠ) ድንጋጌ፣

ህትመቱን በሚያሰራጨው ሰው ላይ በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፫ የመገናኛ ብዙሃን ውጤቱ በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ወይም ይህን በመሳሰሉ የመገናኛ ዘዴዎች የሚሰራጭ ሲሆን የፕሮግራሙ ኃላፊ እርሱ ከሌለ ባለፈቃዱ ኃላፊ ይሆናል።

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (፪) ወይም (፫) በተመለከተው መሠረት ለመገናኛ ብዙኃኑ ውጤት በመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊ የሆነው ሰው በሀገር ውስጥ የመኖሪያ ስፍራው ካልታወቀ ወይም የመኖሪያ አድራሻውን ለማረጋገጥ ካልተቻለ ከእርሱ ቀጥሎ የተመለከተው ሰው በኃላፊነት ይጠየቃል።

፭ በዚህ አንቀጽ በመገናኛ ብዙኃን ውጤቶች አማካይነት በተፈጸመ ወንጀል ኃላፊነትን ለመወሰን ሲባል የውጤቱ ይዘት ኃላፊነት ባለበት ሰው ሙሉ ዕውቀትና ፈቃደኛነት እንደገባ እንደታተመ ወይም እንደተሰራጨ ይቆጠራል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ተቃራኒ ማስረጃ እንዲቀርብ አይፈቀድም።

<u>አንቀጽ ፴፬ የደራሲው፣ የአመንጪው ወይም የአሳታሚው ልዩ የወንጀል ኃላፊነት</u>

፩ የአንቀጽ ፴፫ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤ የጦር መሣሪያ ይዞ በማመጽ ወይም የእርስ በርስ ጦርነት በማስነሳት በመንግስት ላይ በሚደረግ ወንጀል (አንቀጽ ፪፻፵)፣ በክዳት (አንቀጽ ፪፻፵፰-፪፻፶)፣ በስለላ (አንቀጽ ፪፻፶፪)፣ ለወንጀል ድርጊት በማነሳሳትና በአባሪነት፣ በማነሳሳትና በአባሪነት ሙከራ (አንቀጽ ፪፻፶፭)፣ በመገፋፋትና ግዙፍ ባልሆነ የማሰናዳት ተግባር (አንቀጽ ፪፻፶፯)፣ በሰብዓዊነት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች (አንቀጽ ፪፻፷፱ - ፪፻፸፬)፣ ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዲጣሱ ለማድረግ ሌላውን ሰው በማነሳሳት (አንቀጽ ፫፻፴፪)፣ ወታደራዊ ሚስጢርን በመግለጽ (አንቀጽ ፫፻፴፮)፣ ወታደራዊና መንግሥታዊ ሚስጢርን በመግለጽ (አንቀጽ ፫፻፲፮ እና ፫፻፲፯)፣ የሀሰት ወሬዎችን ነዝቶ ህዝብን በማነሳሳት (አንቀጽ ፬፻፹፮(ለ)) ወይም በህግ የታዘዘ ሚስጢር የመጠበቅ ኃላፊነትን ሆን ብሎ በመተላለፍ በመገናኛ ብዙኃን በተገለፀው ወይም

BACK



በተሰራጨው ውጤት በደራሲነት፣ በአመንጪነት ወይም በአሳታሚነት በመሳተፍ በወንጀሉ አፈፃፀም ተካፋይ የሆነ ማንኛውም ሰው ለወንጀሉ ኃላፊ ይሆናል።

፪ እንዲህ በሆነ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀሉን ባደረጉ ሰዎች ላይ ስለወንጀል ተካፋይነት የተመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ ፵፫ የመረጃ ምንጭን በምሲጢር ስለመጠበቅ</u>

፩ በየጊዜው የሚወጣ ፕሬስ ያልሆነ ማናቸውም የፕሬስ ሕትመት አሳታሚ ወይም አዘጋጅ የደራሲውን ስም ወይም የብዕር ስም በፕሬሱ ውጤት ላይ እንዲገልጽ ማስገደድ የተከለከለ ነው።

፪ ማንኛውም የፕሬስ አሳታሚ ወይም አዘጋጅ የተጠቀመበትን የዜና ወይም የመረጃ ምንጭ እንዲገልጽ አይገደድም።

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም፣

ሀ/ በዚህ ህግ ህገ መንግሥታዊውን አስተዳደር፣ የአገር መከላከያ ሀይልን፣ የመንግሥት ጸጥታና ብሔራዊ ደህንነትን ለመጠበቅ የወጡትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የተፈጸሙ ወንጀሎችን በሚመለከት ግልጽና የቅርብ ጊዜ አደጋ የሚያስከትል ሲሆን፣

ለ/ ከባድ የወንጀል ክስ ሲያጋጥምና የመረጃ ምንጩን ማወቅ አማራጭ የሌለውና ወሳኝ ሆኖ ሲገኝ፣

የፕሬስ አሳታሚው ወይም አዘጋጁ የመረጃ ምንጩን እንዲገልጽ በፍርድ ቤት ሊታዘዝ ይችላል።

**አንቀጽ ፴፮ ድርብ ኃላፊነትን ማስቀረት**

በሕግ ላይ በተደነገገው ቅደምተከተል መሠረት ከኃላፊዎቹ አንዱ ከተቀጣ በዚሁ ድርጊት ምክንያት ሌሎች ከኃላፊነት ውጪ ሆነው ከቅጣት ይድናሉ::

ቢሆንም ማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን ድርጅት በየትኛውም ቅደም ተከተል ከተመለከተው ወንጀል አድራጊ ጋር በተደራቢነት ወይም በተናጠል በወንጀል ተጠያቂ ከመሆን አይድንም::

**አንቀጽ ፴፯ የማይደፈር መብት**

በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች እንዳይገለፅ በሕግ ወይም በግልፅ በተሰጠ ውሳኔ የተከለከለ ካልሆነ በቀር የሕግ አውጭ፣ የአስተዳደር ወይም የፍርድ ባለሥልጣኖች የእውነተኛና የትክክለኛ ክርክሮች ወይም ውሳኔዎች ፀሐፊ፣ አሳታሚ ወይም በሕዝብ መገናኛ ዘዴ አቅራቢ የሆነው ሰው በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም::

## ርዕስ ሦስት

## ወንጀል አድራጊውን የሚያስቀጡ ሁኔታዎች

## ምዕራፍ አንድ

## የወንጀል ኃላፊነት

## ክፍል አንድ

## መደበኛ ኃላፊነት

**አንቀጽ ፴፰ የወንጀል ኃላፊነትና ፍፁም ኢ-ኃላፊነት**

፩ በወንጀል ሕግ መደበኛ ድንጋጌዎች መሠረት የሚቀጣው፣ ላደረገው ድርጊት ኃላፊ የሆነው ወንጀል አድራጊ ብቻ ነው::

፪ ማንም ሰው በዕድሜ፣ በሕመም፣ ባልተለመደ የዕድገት መዘግየት፣ ወይም ጥልቅ በሆነ የአእምሮ የመገንዘብ ወይም የማመዛዘን ችሎታ መቃወስ ወይም ከዚህ በታች በአንቀጽ ፵፱ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ስነ-ህይወታዊ ምክንያት የወንጀል ድርጊት በሚፈፅምበት ጊዜ የድርጊቱን ዓይነት ወይም ውጤት ለመገንዘብ ወይም በዚህ ግንዛቤ መሠረት ራሱን ለመቆጣጠር በፍፁም ያልቻለ ሲሆን ለፈፀመው ድርጊት ፍፁም ኢ-ኃላፊ ስለሚሆን አይቀጣም።

፫ ፍርድ ቤት ኃላፊ ላልሆነ ወንጀል አድራጊ በሕግ የተደነገጉ ተስማሚ የሆኑ የሕክምና ወይም የጥበቃ ጥንቃቄዎች እንዲደረጉለት ያዝዛል /አንቀጽ ፻፳፱-፻፴፩/።

<u>አንቀጽ ፵፱ ከፊል ኃላፊነት</u>

፩ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ወይም በአእምሮ ሕመም ምክንያት በተስተካከለ አኳኋን ማመዛዘን ወይም መገንዘብ ባለመቻል፣ በአእምሮ ዕድገት መገታት ወይም ባልተለመደ ወይም ባልተሟላ ሁኔታ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ስነ-ሕይወታዊ ምክንያት የሚገኝ ሰው የወንጀል ድርጊት በሚፈጽምበት ጊዜ የተግባሩን ዓይነት ወይም ውጤት ለመገንዘብ ወይም በዚህ ግንዛቤ መሠረት ራሱን ለመቆጣጠር ያለው ችሎታ <u>ከፊል</u> እንደሆነ ላደረገው ወንጀል ከተደነገገው ቅጣት ውስጥ ከፊሉ ተፈፃሚ ይሆንበታል። ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ በመሰለው የሚወስነው በአንቀጽ ፻ ፹ መሠረት ነው።

፪ ፍርድ ቤቱ ከቅጣቱ በተጨማሪ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት /አንቀጽ ፻፳፱ እስከ ፻፴፩/ ሕክምና ወይም

BACK



ጥበቃ እንዲደረግለት ወይም ጠባዩ እንዲታረም አስፈላጊውን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል::

## አንቀጽ ፶ በስካር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ በተፈጠረ ኢ-ኃላፊነት የሚደረጉ ወንጀሎች

፩ ማንም ሰው አንድን ወንጀል ለመፈፀም በማቀድ ወይም ሊፈፅም እንደሚችል እያወቀ በአልኮል መጠጥ ወይም አእምሮን በሚያደነዝዝ ነገር ወይም በሌላ ዓይነት ዘዴ አስቦ ራሱን ወደ ፍፁም ኢ-ኃላፊነት ወይም ወደ ከፊል ኃላፊነት በማስገባት ወንጀሉን ያደረገ እንደሆነ፤ ነፃ የሚያወጡ ወይም ቅጣትን የሚቀንሱ ድንጋጌዎች አይፀኑለትም::

በእንደዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ላይ ጠቅላላዎቹ የወንጀል ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፪ አድራጊው ወንጀል ለመፈፀም ራሱን እንደሚያጋልጥ እያወቀ ወይም ለማወቅ እየቻለ ወይም ማወቅ እያለበት በራሱ ጥፋት ወደ ፍፁም ኢ-ኃላፊነት ወይም ወደ ከፊል ኃላፊነት ራሱን ካስገባ በኋላ በዚሁ ሁኔታ እያለ ወንጀል ያደረገ እንደሆነ፤ ወንጀሉ በቸልተኛነት መሠረት የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ አድራጊው ስለቸልተኛነት በተደነገጉት በመደበኛዎቹ ድንጋጌዎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል /አንቀጽ ፶፱/::

፫ አድራጊው በገዛ ጥፋቱ ወደ ፍፁም ኢ-ኃላፊነት ራሱን ካስገባ በኋላ ሊያደርግ ያልፈቀደውን ወይም ያላሰበውን ወንጀል አድርጎ ሲገኝ፣ በሕዝብ ደህንነት ላይ ጉዳትን ስለማድረስ በሕጉ ልዩ ክፍል የተመለከተው ድንጋጌ /አንቀጽ ፬፻፺፩/ ተፈፃሚ ይሆናል::

፩ ምንም ጥፋት ሳይኖረው ወይም በሌላ ሰው ተገዶ በፍፁም የኢ-ኃላፊነት ሁኔታ ውስጥ ባለበት ጊዜ ወንጀል ያደረገ ሰው በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም::

<u>አንቀጽ ፶፩ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚደረግ የልዩ አዋቂ ምርመራ</u>

፩ የተከሳሹ ፍጹም ወይም <u>ከፊል</u> ኃላፊነት አጠራጣሪ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ ስለዚሁ ነገር ልዩ ዕውቀት ያለውን የአዋቂ አሳብ መጠየቅ አለበት፤ ቢያስፈልግም በተከሳሹ ጠባይ ባለፈ ሕይወት ታሪኩና በሁኔታዎቹ ላይ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል::

በተለይ ተከሳሹ የአእምሮ በሽታ ያለበት ወይም በሚጥል በሽታ የሚታወክ ለመሆኑ፣ ወይም መስማትና መናገር የሚሣነው ለመሆኑ ወይም አእምሮን በሚያደነዝዝ ነገር ወይም በመጠጥ አዘውታሪነት በሽታ የተለከፈ ለመሆኑ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ ለዚሁ ልዩ ዕውቀት ያለውን የአዋቂ ሰው አሳብ መጠየቅ ግዴታ ነው::

፪ ፍርድ ቤቱ በተለመደው ሥነ ሥርዓት መሠረት ልዩ ችሎታ ያለውን አዋቂ ወይም አዋቂዎች ይመርጣል:: እንዲሁም ተግባራቸውንና የሚያጣሩትንም ጉዳዮች ገልጾ ያስታውቃቸዋል::

ተከሳሹ ወንጀሉን ባደረገበት ጊዜና ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ፣ በማመዛዘንና በመወሰን ችሎታው ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ውጤት ምርመራው ማረጋገጥ አለበት:: ከዚህም በተጨማሪ ጠቃሚ ስለሆኑት የሕክምና ዓይነቶች ወይም የደህንነት ማረጋገጫ እርምጃዎች ለፍርድ ቤቱ መግለፅ አለበት::

፫ ፍርድ ቤቱ በዚሁ በተገኘው መግለጫ መሠረት ስለተከሳሹ ኃላፊነት ተገቢ የሆነውን ሕጋዊ ውሳኔ ይሰጣል። ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ መሠረት አድርጎ መያዝ የሚገባው ልዩ አዋቂው በሕግ ረገድ የሚያቀርብለትን አሳብ ሳይሆን በሳይንስ ረገድ በትክክል ተጠንቶ የሚቀርብለትን በአስረጂው ውጤት መሠረት ላይ የተገኘውን ነው።

## ክፍል ሁለት
## ህፃናትና ለአካለመጠን ያልደረሱ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች

### አንቀጽ ፶፪ በህፃናት ላይ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚ አለመሆን

ዕድሜያቸው ዘጠኝ ዓመት ያልሞላ ህፃናት በወንጀል ሕግ ኃላፊዎች ሆነው አይቆጠሩም። በእነዚህም ላይ የዚህ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆኑም።

ህፃናት ወንጀል በፈፀሙ ጊዜ ቤተዘመዶቻቸው፣ አስተማሪዎቻቸው፣ አሳዳሪዎቻቸው ወይም ሌሎች አካላት ተገቢ የሆኑትን ጥንቃቄዎች ያደርጉላቸዋል።

### አንቀጽ ፶፫ በወጣት ወንጀል አድራጊዎች ላይ የሚፈፀሙ ልዩ ድንጋጌዎች

፩ ዕድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አሥራ አምስት ዓመት የሞላቸው ወንጀል ያደረጉ ወጣቶች የሚወሰኑባቸው ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ከአንቀጽ ፻፶፯ እስከ ፻፷፰ የተደነገጉት ብቻ ናቸው።

ለአዋቂ ጥፋተኞች የተደነገጉት መደበኛ ቅጣቶች ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤ ከአዋቂዎችም ጋር አይታሰሩም።

፪ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ላደረጉት ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ካልተገኙ በቀር ከአንቀጽ ፻፶፰ እስከ

፻፷፰ የተደነገጉት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆኑም።

ሆኖም ወጣቱ አላፊነት የሌለው በሆነ ጊዜ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፱ -፻፸፫ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

<u>አንቀጽ ፻፸ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማጣራት</u>

፩ ፍርድ ቤቱ ለሚሰጠው ውሳኔ አስፈላጊ ሆኖ በታየው ጊዜ ለአካለመጠን ስላልደረሰ ወጣት ጠባይ፣ ስለአስተዳደጉ፣ ስለኑሮውና ስለሕይወቱ ሁኔታ ሊያውቅ የሚፈልገውን መረጃ ይጠይቃል። የወላጆቹን፣ የአስተማሪዎቹን፣ የአሳዳሪዎቹን እና የሚመለከታቸውን ተቋማት አሳብ መቀበል ይችላል።

ከላይ የተጠቀሱት ሰዎችና ድርጅቶች ለአካለመጠን ያልደረሰውን ወጣት እንዲሁም ቤተዘመዶቹን፣ የሚመለከቱና በእጃቸው የሚገኙትን የግል መዝገቦች፣ በተለይም ስለጤንነቱና ስለ-ኅብረተሰባዊ ኑሮው ዝርዝር ነገር የያዙ የጽሁፍ መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ ሊያዝዝ ይችላል።

፪ ፍርድ ቤት ቅጣቱን ወይም የጥንቃቄ እርምጃውን ከመወሰኑ በፊት ለአካለመጠን ያልደረሰው ወጣት በአንድ የጤና ወይም የትምህርት ማዕከል፣ በቤት ውስጥ ወይም በሌላ ተስማሚ ሥፍራ ክትትል እየተደረገበት እንዲቆይ ሊያዝ ይችላል።

ፍርድ ቤቱ የወጣት ጥፋተኛውን የአካልና የአእምሮ ሁኔታ በተመለከተ የባለሙያ ማስረጃ ሊጠይቅ ይችላል። እንዲሁም የወጣት ጥፋተኛውን የአካልና የአእምሮ ሁኔታ ለማወቅና ተስማሚ የሆነውን የትምህርት፣ የእርምትና የጥበቃ እርምጃ ለመወሰን ይረዳው ዘንድ

ለባለሙያው አስፈላጊ የሆኑትን ጥያቄዎች ሊያቀርብ ይችላል::

፫ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ መሠረት አድርጐ መያዝ የሚገባው ልዩ አዋቂው በሕግ ረገድ የሚያቀርብለትን አሳብ ሳይሆን በሳይንስ ረገድ በትክክል ተጠንቶ የሚቀርብለትን ውጤት ነው::

## አንቀጽ ፶፭ የቅጣቱ ወይም ጥንቃቄ እርምጃው አወሳሰን

ፍርድ ቤት በወጣት ጥፋተኛው ላይ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ በሚወስንበት ጊዜ ዕድሜውን፣ ጠባዩን፣ የአእምሮና የሞራል ዕድገቱን ሁኔታ እንዲሁም ቅጣቱ ወይም የጥንቃቄ እርምጃው በጥፋተኛው ላይ ሊያመጣ የሚችለውን መልካም ለውጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው::

ፍርድ ቤቱ የተሻለ ውጤት ያስገኛል ብሎ ባመነ ጊዜ ትዕዛዙን ሊለዋውጥ ይችላል /አንቀጽ ፻፷፬/::

## አንቀጽ ፶፮ ከ፲፭ ዓመት በላይ፣ ከ፲፰ ዓመት በታች ያሉ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች

፩ አድራጊው ወንጀል ባደረገበት ጊዜ ከአስራ አምስት ዓመት የበለጠ ዕድሜ ኖሮት ነገር ግን አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው እንደሆነ፣ ጉዳዩ የሚታየው በሕጉ ላይ በተመለከቱት መደበኛ ድንጋጌዎች መሠረት ነው::

፪ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነው የነገሩን ሁኔታ በማመዛዘን በተለይም የተከሳሹን ወጣትነት ዕድሜ መጠን፣ ሊታረም አለመቻሉንና አደገኛነቱን፣ አመሉ ሊሻሻል የሚችል ዕድል የሚያጋጥመው መሆን አለመሆኑን በመገንዘብ መደበኞቹን የቅጣት ማቅለያ ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፻፸፱/ መሠረት አድርጐ በመያዝ

ወይም የተሻለ መስሎ ሲታየው ለአካለመጠን ላልደረሱት ወንጀለኞች የተመደበውን የልዩ ቅጣት አወሳሰን /ከአንቀጽ ፻፷፮ እስከ ፻፷፰/ በመከተል ነው።

## ምዕራፍ ሁለት
## በወንጀል ጥፋተኛ መሆን

### ክፍል አንድ
### አሳብ፣ ችልተኛነትና ድንገተኛ ነገር

#### አንቀጽ ፶፯ መርህ፣ የወንጀል ጥፋትና ድንገተኛ ነገር

፩ በሕጉ መሠረት ጥፋተኛነቱ ካልተረጋገጠ በቀር ማንም ሰው ሊቀጣ አይችልም።

ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኛነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም።

፪ ማንም ሰው የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም።

### ንዑስ ክፍል አንድ
### በነጠላ ወንጀል ጥፋተኛ መሆን

#### አንቀጽ ፶፰ አስቦ ወንጀል ማድረግ

፩ ማንም ሰው አስቦ ወንጀል አደረገ የሚባለው፦

ሀ/ አንድ የተወሰነን ውጤት ለማግኘት ብሎ ሕገወጥና የሚያስቀጣን ድርጊት እያወቀ በራሱ ፍላጎት ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ ድርጊቱ ሕገወጥና የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ የሆነው ይሁን ብሎ ውጤቱን በመቀበል ድርጊቱን ያደረገ እንደሆነ፤ ነው።

፪ ታስቦ የተደረገ የወንጀል ተግባር በሕግ መሠረት /አንቀጽ ፳፫ እስከ ፻፮/ የማያስቀጣ ወይም ይቅርታ የሚያሰጥ ካልሆነ በቀር ምንጊዜም ያስቀጣል።

፫ ስለቸልተኛነት የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ማንም ሰው ባላወቀው፣ ባልፈለገው ወይም በቀጥታ ወይም በአጋጣሚ ከአሳቡ በላይ በሆነው ነገር ሊፈረድበት አይቻልም።

## አንቀጽ ፶፱ በቸልተኛነት ወንጀል ማድረግ

፩ ማንም ሰው በቸልተኛነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው፦

ሀ/ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን፤ ወይም

ለ/ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ፣ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ፤

ድርጊቱን የፈጸመ እንደሆነ ነው።

የወንጀል ቸልተኛነት አለ የሚባለውም የአድራጊው የግል ሁኔታ፣ በተለይም ዕድሜው፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራው እና የማኅበራዊ ኑሮ ደረጃው ሲመዘን በጉዳዩ ሁኔታዎች

BACK



ሊደረጉ ይገባል ተብሎ በአግባቡ የሚጠበቁትን ጥንቃቄዎች ያላደረገ እንደሆነ ነው።

፪ በተደረገው ጥፋት ዓይነት ወይም ከባድነት ወይም በሕብረተሰቡ ላይ ሊያደርስ በሚችለው አደጋ ምክንያት በሕጉ ላይ በተለይ ያስቀጣል ተብሎ ካልተደነገገ በቀር በቸልተኛነት የተፈፀመ ድርጊት አያስቀጣም።

ፍርድ ቤቱ በወንጀል አድራጊው ላይ ቅጣት የሚወስነው፣ ድርጊቱ ሊያስከትል የሚችለውን ውጠ ት፣ አድራጊው በኅሊናው እየተረዳው ወይም መረዳት ሲገባው ካለማመዛዘኑ የተነሳ ያደረገውን የጥፋት ደረጃና የአደገኛነት ባሕሪውን በመመርመር ነው።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## በተደራራቢ ወንጀሎች እና በደጋጋሚነት ረገድ ጥፋተኛ መሆን

### አንቀጽ ፷ ተደራራቢ ወንጀሎች

ማንም ሰው ተደራራቢ ወንጀሎችን አድርጓል የሚባለው:-

ሀ/ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ማናቸውንም ዓይነት ግዙፍ ወንጀሎችን አከታትሎ ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ወይም በአንድ ድርጊት ልዩ ልዩ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን በመፈፀም ጣምራ ወንጀሎችን ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

BACK



ሐ/ በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት ያደረገው ወንጀል አንድን የሕግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ፤ ነው።

## አንቀጽ ፷፩ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መሆኑ

፩ በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሲሆን፣ አድራጊው ተመሳሳይ ባህርይ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም።

፪ በሕግ በተጠበቀ በዚያው በአንድ መብት ላይ ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተደረጉ የወንጀል ተግባሮች በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት በተደረጉ ጊዜ እንደ አንድ ወንጀል ይቆጠራሉ። ወንጀል አድራጊው ለዚሁ እንደ አንድ ወንጀል ለተቆጠረው እንጂ ተደጋግሞ ወይም ተከታትሎ ለተፈፀመው ለእያንዳንዱ ድርጊት አይቀጣም።

እንዲሁም ወንጀል አድራጊው የወንጀል ተግባሮችን ደጋግሞ ወይም አከታትሎ ማድረጉ፣ ወይም ወንጀልን እንደልማድ ወይም ሙያ አድርጎ መያዙ ለአንድ ተራ ወይም ለአንድ ቅጣትን ለሚያከብድ ወንጀል ማቋቋሚያ መሆኑ ወይም የወንጀሉ ድርጊት ለተወሰነ ጊዜ ተራዝሞ ሲቆይ አንድ ነጠላ ወንጀል እንጂ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎችን እንዳደረገ አይቆጠርም።

፫ አድራጊው የተወሰነ ወንጀል ለማድረግ አሳብ አለው ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ፣ በተለይም የማይገባውን

BACK


ብልፅግና ለማግኘት በንብረት ላይ ወንጀል አድርጐ እንደሆነ ወይም የሐሰት ገንዘብ ሠርቶ እንደሆነ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጐ እንደሆነ ወይም ሐሰተኛ ሰነድ ሠርቶ ወይም ተጠቅሞበት እንደሆነ፤ የመጀመሪያውን የጥፋት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ሲል መሠረታዊ ከሆነው ወንጀል በኋላ አከታትሎ ያደረገው ድርጊት ከቀድሞ አሳቡና ሊደርስበት ካቀደው ግቡ ጋር የተያያዘ ሆኖ በዋናው ወንጀል ይጠቃለላል፡፡

<u>አንቀጽ ፷፪ አዲስ ቅጣት የሚያስከትል ወንጀልን መደጋገም</u>

አድራጊው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፷፩ የተመለከተውን ጠ ባይ የያዘ ወንጀል ካደረገ በኋላ ቀድሞ አድርጐት ከነበረው ወንጀል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሌላ ወንጀል በአዲስ አሳብ ወይም ቸልተኛነት እንደገና ቢያደርግ፣ ወንጀሉን ያደረገው ቀድሞ በድሎት በነበረው ሰው ወይም በሕግ በተጠበቀው በዚያው መብት ላይ ቢሆንም እንኳ፣ ይህ አዲስ ወንጀል ስለሆነ ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ ፻፹፬ ስለተደራራቢ ወንጀሎች በተደነገገው መሠረት ቅጣቱን ያከብዳል፡፡

<u>አንቀጽ ፷፫ የተዛመዱ ወንጀሎች በተደረጉ ጊዜ ያለው ጥፋተኛነት</u>

አድራጊው ሌላ ወንጀል ለማድረግ እንዲመቸው ወይም ቀደም ሲል ላደረገው ወንጀል ከለላ እንዲሆነው ሌላ ወንጀል ያደረገ እንደሆነ እና ይህንን ሊፈፅም ያሰበውን ዋና ወንጀል ቢያንስ ሞክሮ እንደሆነ፤ ሕጉ እንደ አንድ ከባድ ወንጀል የሚቆጥረው ካልሆነ በቀር በተደራረቡ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ስለማክበድ (አንቀጽ ፻፹፭) የተደነገገው የቅጣት አወሳሰን ደንብ ይፈፀምበታል፡፡

## አንቀጽ ፷፬ ሌሎች ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ሲደረጉ ያለው ጥፋተኛነት

በአንቀጽ ፷፪ ወይም ፷፫ ከተመለከተው ውጭ ተመሳሳይ ወይም ልዩ ልዩ ወንጀሎችን ወንጀል አድራጊው አከታትሎ ያደረገ እንደሆነ፣ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎችን በማድረጉ የአንቀጽ ፻፹፬ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆንበታል።

## አንቀጽ ፷፭ የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ በሚደረጉ ጣምራ ወንጀሎች ያለው ጥፋተኛነት

ወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የሕግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ፣ ተደራራቢ ወንጀሎችን በማድረጉ ቅጣቱ የሚወሰነው በአንቀጽ ፻፹፯(፩) መሠረት ነው።

## አንቀጽ ፷፮ ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎችን በማመልከት ያለው ጥፋተኛነት

፩ በጦር መሣሪያ፣ በአደገኛ መሣሪያ፣ በእሳት፣ በሚፈነዳ ነገር፣ በመርዝ ወይም በሚያፈዝ መድኃኒት በመገልገል ወይም በሰው ወይም በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ አንድ የተወሰነ ወንጀል ሲደረግ የሰውን ሕይወት እንደማሳለፍ ወይም በሰው አካል ወይም በሰው ንብረት ላይ ጉዳት እንደማድረስ የመሳሰለ ሌላ ወንጀል ተደርጐ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ የወንጀል አድራጊውን ጥፋተኛነትና ቅጣት የሚወስነው በሚከተሉት መርሆች መሠረት ነው፤

ሀ/ አድራጊው የመጀመሪያውን ወንጀል ያደረገው፣ ወንጀሉ የሚያስገኘውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በማቀድ ወይም ቀድሞውኑ አውቆ በመቀበል ከሆነ (አንቀጽ ፶፰(፩))፣ አስበ

ላደረጋቸው ከአንድ በላይ ለሆኑት ወንጀሎች ማቋቋሚያ የሚሆኗቸው ሁኔታዎች መሟላ ታቸውን በማረጋገጥ ጉዳዩን በሚመ ለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት (አንቀጽ ፻፹፬ እና ፻፹፯ (፪)(ሀ)) ፍርድ ቤቱ ለተደራራቢዎቹ ወንጀሎች ቅጣቱን በማክበድ ይወስናል።

ለ/ አድራጊው አስቦ ያደረገው ወንጀል በቸልተኛነት የሚያስቀጣ ወንጀል ባስከተለ ጊዜ (አንቀጽ ፶፱(፩)) አስቦና በቸልተኛነት ያደረጋቸው ወንጀሎች ተደራራቢ ስለሚሆኑ ፍርድ ቤቱ በዚሁ መሠረት ቅጣቱን ያከብዳል (አንቀጽ ፻፹፯(፪)(ሀ))።

ሐ/ አድራጊው በቸልተኛነት ያደረገው የመጀመሪያው ወንጀል በቸልተኛነት የሚያስቀጣ ሌላ ወንጀል ባስከተለ ጊዜ በቸልተኛነት የተደረጉት ወንጀሎች ተደራራቢ ስለሚሆኑ ፍርድ ቤቱ በዚሁ መሠረት ቅጣቱን ያከብዳል (አንቀጽ ፻፹፯ (፪)(ለ))።

፪ ይልቁንም በሕዝብ ደህንነት ላይ አደጋን በሚያደርሱ፣ እንደእሳት አደጋ ባሉ፣ በሚፈነዱ ነገሮች በመገልገል፣ በሕዝብ መገናኛ ላይ ወይም በሕዝብ ጤንነት ላይ አደጋን የሚያደርስ እንዲሁም ሰዎችን ለአደጋ የማጋለጥ፣ የማጉላላት፣ አምባጓሮ፣ እርጉዝ ሴትን የማስወረድ፣ ወይም አስገድዶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀምን የሚመለከት ዋና ወንጀል ሲደረግና ተደራቢው ወንጀል የዚሁ ምክንያት ውጤት ሲሆን የቅጣት ማክበድ ደንብ ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል (አንቀጽ ፻፹፯ (፪)(ሐ) እና አንቀጽ ፻፹፬)።

<u>አንቀጽ ፷፯ ደጋጋሚነትን በማመለከት ያለው ጥፋተኛነት</u>

ወንጀል አድራጊው በደጋጋሚነት ወንጀል አድርጓል ብሎ ፍርድ ቤት ቅጣት የሚያከብደው (አንቀጽ ፻፹፰) የተወሰነበትን የእሥራት ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል

BACK



ከፈፀመበት ወይም ይህ ቅጣት በይቅርታ ከቀረለት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ መነሻ ቅጣቱ ስድስት ወር የሆነ ቀላል እሥራት ማስቀጣት የሚችል አዲስ ወንጀል አስቦ ያደረገ እንደሆነ ነው።

## ክፍል ሁለት

## በሕግ የተፈቀዱ ድርጊቶች፣ የማያስቀጡና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### በሕግ የተፈቀዱ ድርጊቶች

#### አንቀጽ ፷፰ በሕግ የታዘዙ ወይም የተፈቀዱ ድርጊቶች

በሕግ የታዘዙ ወይም የተፈቀዱ ድርጊቶች በተለይም:-

ሀ/ ከሕግ ወሰን ሳያልፍ የተፈፀመውን የሕዝብ አገልግሎት ሥራ ወይም የመንግሥት ወይም የወታደርን የሥራ አፈፃፀም የሚመለከቱ ድርጊቶች ሲሆኑ፤

ለ/ ከደንበኛው ሕሊናዊ ልምድ ወሰን ያልወጡ የጠባይ ማረምን መብት ወይም የሥነ ሥርዓት ማስፈፀምን ሥልጣናዊ መብት ተግባራዊ የሚያደርጉ ድርጊቶች ሲሆኑ፤ ወይም

ሐ/ በሕግ እውቅና የተሰጠውን የግል መብትን ሥራ ላይ ለማዋል የተፈፀሙ ድርጊቶች ሲሆኑና አፈፃፀማቸው ከሕግ ወሰን ያላለፈ ሲሆን፤

እንደ ወንጀል የማይቆጠሩና የማያስቀጡ ናቸው።

#### አንቀጽ ፷፱ የሙያ ሥራ ግዴታ

የሙያ ሥራ ግዴታን ለመወጣት የተፈፀሙ ድርጊቶች ከሙያው ደንብና አሠራር ልማድ ውጭ ካልሆኑና በከባድ የሙያ ጥፋት ካልተፈፀሙ በቀር አያስቀጡም።

BACK


## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የማያስቀጡና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች

### አንቀጽ ፸ የተበዳይ ፈቃድ

፩ አድራጊው የፈጸመው ወንጀል በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጣና ተበዳዩ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ የፈቀደው ድርጊት ከሆነ አያስቀጣም::

፪ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፭፻፷፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንም ሰው የንግድ አላማ ሳይኖረው በራሱ ነፃ ፈቃድ በሚያደርገው ውል፣ ሌላ ሰው ለግል ጥቅሙ እንዲያውለው ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ተገቢና አስፈላጊ የሆነ ሳይንሳዊ ምርምር ወይም ሙከራ እንዲያካሄድበት፣ አካሉን፣ የአካሉን ክፍል ወይም ከብልቶቹ አንዱን በሕይወቱ እያለ በሚሰጥበት ወይም ከሞቱ በኋላ እንዲሰጥ በሚያደርግበት ጊዜ ተቀባዩ፣ በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም::

### አንቀጽ ፸፩ ፍጹም የሆነ መገደድ

ሊቋቋመው በማይችለው መንገድ ፍጹም ተገድዶ ሊደርስበት ከነበረው ጉዳት በማይበልጥ ሁኔታ ወንጀል ያደረገ ሰው ተገድዶ ባደረገው ወንጀል አይቀጣም (አንቀጽ ፴፪(፩)(ሐ))::

ፍርድ ቤቱ ፍጹም የመገደድ ሁኔታ መኖሩን የሚወስነው የነገሩን አኳኋን ይልቁንም የመገደዱን ዓይነት የከፍተኛነቱንም መጠን እንዲሁም የተገዳጁን የግል ኑሮ ደረጃ ሁኔታና የእድሜውን በተለይም የሁለቱን የጉልበታቸውን መጠንና በተገዳጁና በአስገዳጁ መካከል

BACK



ያለውን የበታችነትና የበላይነት አኳኋን ከግምት በማስገባት ነው::

<u>አንቀጽ ፸፪ ለማሸነፍ የሚቻል መገደድ</u>

የደረሰበት መገደድ ሊታገድ የሚቻል ሆኖ ለማሸነፍ ወይም ድርጊቱን ከመፈጸም ለማምለጥ ችሎታ እያለው ወንጀል ባደረገ ሰው ላይ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን በመሰለው ያቃልላል ( አንቀጽ ፻፹):

<u>አንቀጽ ፸፫ የትዕዛዝ ሰጪ ተጠያቂነት</u>

የበታች የሆነ ሰው የማዘዝ መብት ካለው የበላይ የአስተዳደር ወይም የወታደር ሹም በተሰጠው ግልጽ ትዕዛዝ አንድን ድርጊት በሚፈፅምበት ጊዜ፣ ድርጊቱ ወንጀል ከሆነና ከተሰጠው ትዕዛዝ ውጪ ካልሆነ (አንቀጽ፺፰(፫)) በተደረገው ወንጀል ኃላፊ የሚሆነውና የሚቀጣው ትዕዛዙን የሰጠው ሰው ነው::

<u>አንቀጽ ፸፬ የትዕዛዝ ፈፃሚው ተጠያቂነት</u>

፩ ትዕዛዝ ፈፃሚው ትዕዛዙ ከሕግ ውጭ መሆኑን፣ በተለይም አዛዡ ለማዘዝ ሥልጣን የሌለው ወይም ድርጊቱ ወንጀል መሆኑን እያወቀ፣ የፈፀመውም ድርጊት የነፍስ መግደል ወይም የቃጠሎ ወይም በሰዎች ላይ ወይም በንብረት ወይም ደግሞ በአገር ደህንነትና በኅብረተሰብ ዋና ዋና ጥቅሞች ላይ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ ላይ የደረሰ ከባድ አደጋ ሲሆን በጥፋቱ ኃላፊ ሆኖ ይቀጣል::

፪ ትዕዛዝ ፈጻሚው ሥነ ሥርዓትን የመጠበቅ ወይም የመታዘዝ ስሜት አድሮበት ትዕዛዙን ያደረገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በመሰለው ቅጣቱን ሊያቃልልለት ይችላል፤ በተለይም ትዕዛዙ አስገዳጅ ሲሆን ፍርድ

BACK



ቤቱ እንደመሰለው ቅጣቱን ያቃልልለታል (አንቀጽ ፻፹)፡፡

ትዕዛዝ ፈፃሚው ጥፋት ያደረገው በመንግስት ሥራ ወይም የወታደር ሥርዓት አፈፃፀም ሥነ ሥርዓት በሚያስገድደው ተግባር ሆኖ ትዕዛዙን ለመቃወምና ለመከራከር ባለመቻሉ በቀጥታ ከመፈፀም በቀር ሌላ የተሻለ መንገድ ለማግኘት ባለመቻሉ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በግልፅ በተረዳ ጊዜ ቅጣቱን በሙሉ ሊያስቀርለት ይችላል፡፡

፫ ትዕዛዝ ፈጻሚው ከትዕዛዝ ውጭ አልፎ አስቦ ላደረገው ወንጀል እርሱ ብቻ ኃላፊ ሆኖ ይቀጣል፡፡

<u>አንቀጽ ፸፰ አስገዳጅ ሁኔታ</u>

የራስን ወይም የሌላ ሰውን መብት በቅርብ ከሚደርስ ከባድ ከሆነ አደጋ ለማዳን የተፈፀመ ድርጊት፣ አደጋውን በሌላ መንገድ ማስወገድ የማይቻል ከሆነና አድራጊው ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ዘዴዎችን የተጠቀመ ከሆነ አያስቀጣም፡፡

የሰውን ሕይወት ወይም ደህንነት የመጠበቅ ልዩ የሙያ ግዴታ ያለበት ሰው የሚፈፅመው ተመሳሳይ ድርጊት በዚህ አንቀጽ ሥር ከቅጣት አያድንም፤ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመሠለው ቅጣቱን ያቃልልለታል (አንቀጽ ፻፹)፡፡

<u>አንቀጽ ፸፱ የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን መተላለፍ</u>

በነገሮቹ አካባቢ ሁኔታዎች መሠረት በአደጋ ላይ የሚገኘውን መብት መስዋዕት ማድረግ ተገቢ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ወይም በሌላው ሰው መብት ላይ የተደረገው ጉዳት ካስፈላጊው መጠን በላይ እንደሆነ፤ ወይም አድራጊው የተገኘበት አስገዳጅ ሁኔታ ወይም የአደጋ ሁኔታ በራሱ ጥፋት የመጣ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ እንደመሰለው ቅጣቱን ያቀልለታል (አንቀጽ ፻፹)፡፡

BACK



## አንቀጽ ፸፯ ወታደራዊ አስገዳጅ ሁኔታ

፩ በወታደራዊ አደጋ ጊዜ በተለይም የአድማ ግርግር ሲሆን ወይም በጦር ግንባር ላይ አንድ የወታደር አዛዥ ወይም የበላይ ሹም የሆነ በአገልግሎት ሥራው ላይ በሚገኝበት ጊዜ ሥነ ሥርዓትን ለማስከበር ወይም ተገቢውን የታዛዥነት ተግባር ለማጽናት በነዚህ በተዘረዘሩት ጊዜያት አስፈላጊውን ፀጥታ ለማስገኘት ሌላ ዘዴ ባለመገኘቱ የፈጸመው ድርጊት አያስቀጣም።

፪ አድራጊው የነገሩ ሁኔታ ከሚያስገድደው በላይ አልፎ ሠርቶ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን በመሰለው ያቀልለታል (አንቀጽ ፻፹)፣ ወይም የነገሩ ሁኔታ በተለይ የሚያስገድደው ሆኖ ሲገኝ ከቅጣቱ ነፃ ሊያደርገው ይችላል።

## አንቀጽ ፸፰ ሕጋዊ መከላከል

የራሱን ወይም የሌላውን ሰው መብት ሕገወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ሕገወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈፀመ ድርጊት አያስቀጣም።

## አንቀጽ ፸፱ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን ማሳለፍ

፩ ተመጣጣኝ ባልሆነ ዘዴ ወይም መሣሪያ በመገልገል ወይም ሕገወጡን ጥቃት ወይም በቅርብ መድረሱ የማይቀረውን ሕገወጥ የሆነ ጥቃት ለመከላከል አስፈላጊ ከሆነ ድርጊት አልፎ በመፈፀም ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን ባሳለፈ ሰው ላይ ፍርድ ቤቱ በመሰለው ቅጣቱን ያቃልለታል (አንቀጽ ፻፹)።

፪ ጥቃትን ለመከላከል ሲል ያደረሰው ጥፋት ከመጠኑ ያለፈበት ጥቃቱ ባስከተለበት ይቅርታ ሊያስገኝ በሚችል ፍርሃት ፣ ድንገተኛ ድንጋጤ ወይም

BACK



በደምፍላት ምክንያት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከቅጣቱ ሙሉ በሙሉ ነፃ እስከመሆን ሊያደርሰው ይችላል::

<u>አንቀጽ ፹ በፍሬ ነገር መሳሳት</u>

፩ በትክክለኛ ፍሬ ነገሩ ሁኔታ የተሳሳተ ግንዛቤ ይዞ አንድ ሰው የወንጀል ድርጊት ያደረገ እንደሆነ ጉዳዩ የአድራጊውን የተሳሳተ ግንዛቤ መሠረት በማድረግ ይታያል::

ወንጀል ለመስራት አስቦ ያላደረገው መሆኑ የተገለጸ እንደሆነ ቅጣት አይደርስበትም:: ቢሆንም አድራጊው በቸልተኛነት የሚያስቀጣው ሲሆን፣ በአንቀጽ ፶፱ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል::

፪ በፍሬ ነገር መሳሳት ወንጀልን ያደረገ ሰው ይህ የፈፀመው የስህተት ድርጊት ሌላ የሚያስቀጣ ወንጀል አስከትሎ እንደሆነ በዚህ ጥፋቱ ከመቀጣት አይድንም::

፫ በተጐጂው ማንነት ወይም ወንጀሉ በተፈፀመበት ነገር ላይ የተፈፀመ ስህተት ወንጀል መሆኑን አያስቀርም::

<u>አንቀጽ ፹፩ በሕግ ላይ መሳሳትና ሕግን አለማወቅ</u>

፩ ሕግን አለማወቅ ወይም በሕግ ላይ መሳሳት መከላከያ ሊሆን አይችልም::

፪ ድርጊቱን ለመፈፀም መብት ያለው መሆኑን በቅን ልቦና ለማመንና እንደዚህ ባለ በተሳሳተ እምነት ላይ ለመገኘትም በቂና እርግጠኛ ምክንያት ያለው ሆኖ ለተገኘ ወንጀለኛ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን በመሰለው ያቃልልለታል (አንቀጽ ፻፹)::

ፍርድ ቤቱ ቅጣትን የሚወስነው ከስህተት የደረሰበትን ምክንያት በተለይም የስህተቱንና የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በመገመት ነው::

፫ በቂ ምክንያት ሊገኝበት በሚችልና ፍፁም በሆነ አለማወቅና ቅን ልቦና እንዲሁም ወንጀሉን በማድረግ አሳብ መኖሩ በግልጽ በማይታይባቸው የተለዩ

BACK



ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱ ከቅጣት ነፃ ለማድረግ ይችላል።

## ክፍል ሦስት
## የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች

### አንቀጽ ፹፪ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች

፩ ፍርድ ቤቱ በሕጉ ከተደነገገው ውሳኔ ሳያልፍ ቅጣትን የሚያቃልለው (አንቀጽ ፻፹፱):-

ሀ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የዘወትር ጠባዩ መልካም እንደሆነና ያጠፋውም በዕውቀት ማነስ፣ ባለማወቅ፣ በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ፤

ለ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በተከበረና በግል ጥቅም ላይ ባልተመሠረተ ፍላጐት ወይም ከፍ ባለ ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ ወይም ማሕበራዊ እምነት ተነሳስቶ እንደሆነ፤

ሐ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው ከፍተኛ የቁሳዊ እጦት ወይም የሕሊና ስቃይ ደርሶበት፣ ከፍ ያለ አደጋ የሚያመጣ ነገር የተቃጣበት መስሎት፣ መሠረት ያለው ፍርሃት አድሮበት ወይም ደግሞ ሊታዘዝለት በሚገባው ወይም በሥልጣኑ ሥር በሚያስተዳድረው ሰው ተፅእኖ ምክንያት እንደሆነ፤

መ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው የተበደለው ሰው ጠባይ ከብርቱ ፈተና ላይ ጥሎት፣ በከባድ ፀብ ቀስቃሽነት ወይም በአፀያፊ ስድብ ምክንያት ወይም ደም ከሚያፈላ ንዴት፣ ስቃይ ወይም ብስጭት ላይ ጥሎት እንደሆነ፤ ወይም ከፍ ያለ አስገዳጅነት ባለው ስሜትን በሚለውጥ ሁኔታ ወይም ምክንያት ባለው የመንፈስ ሁከት ላይ ሆኖ እንደሆነ፤ ወይም

BACK



ሠ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን ካደረገ በኋላ በእውነት የተፀፀተ መሆኑን፣ በተለይም በደል ላደረሰበት ሰው አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ፣ ወይም ጥፋቱን በመገንዘብ ራሱን ለፍትህ አካላት በማቅረብ ወይም የወንጀሉ ጥፋት ላደረሰው ጉዳት በተቻለ መጠን በመካስ መፀፀቱን በተግባር አሳይቶ እንደሆነ ወይም ተከሰሶ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ያመነ እንደሆነ፣ ነው፡፡

፪ በሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ በተለየ ድንጋጌ እነዚህ ሁኔታዎች ወይም ምክንያቶች በማቅለያነት በተመለከቱ ጊዜ ፍርድ ቤቱ እነዚሁኑ ምክንያቶች ቅጣቱን ለማቅለል በድጋሚ ሊጠቀምባቸው አይችልም፡፡

## አንቀጽ ፹፪ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች፣ ዝምድናና የጠበቀ ወዳጅነት

፩ በአንቀጽ ፳፱ መሠረት ልዩ ቅጣት ማቅለያ ምክንያት መሆናቸው በዚህ ሕግ በልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በተጨማሪ ወንጀለኛው ሕግን የሚቃረን ተግባር ያደረገው፣ በተለይም ወንጀል ማድረጉንና ወንጀለኛውን እያወቀ ለፍርድ ባለሥልጣን የማስታወቅ ግዴታውን ያልፈፀመው ወይም መስጠት የሚገባውን እርዳታ ያልሰጠው፣ ሐሰተኛ መግለጫ፣ ምስክርነት ወይም መረጃ የሰጠው ወይም ወንጀለኛው ከክስ ወይም ከቅጣት አፈፃፀም እንዲያመልጥ የረዳው ራሱን፣ የቅርብ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዱን ወይም በተለይ ጥብቅ በሆነ ወዳጅነት የተሳሰረውን ሰው ለቅጣት፣ ለውርደት ወይም ለከባድ አደጋ ላለማጋለጥ

ሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በመሰለው ቅጣቱን ያቀልለታል (አንቀጽ ፻፹)::

ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ወይም ጥብቅ የሆነ ወዳጅነት ግንኙነት ምክንያት በቂ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት::

፪ ወንጀለኛው የሚጠየቅበት ጥፋት በጣም ከባድ ያልሆነና ይህ የተባለው ዝምድና ወይም በወዳጅነት የተሳሰረ ግንኙነት እጅግ ጥብቅ በመሆኑ የነገሩ ሁኔታ የሚያስጨንቅ ስሜት ያሳደረበት በመሆኑ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ወንጀለኛውን በማስጠንቀቅ ወይም በወቀሳ ብቻ በማለፍ ሊወሰን ከሚችለው ሌላ ቅጣት ነፃ ሊያደርገው ይችላል (አንቀጽ ፻፹፪)::

፫ ከባድና ከፍ ያለ አደጋ የሚያደርሱ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው (አንቀጽ ፪፻፶፩(፩))፣ ፫፻፴፭(፫) እና ፮፻፹፪(፩)::

<u>አንቀጽ፹፬ ቅጣትን የሚያከብዱ ጠቅላላ ምክንያቶች</u>

፩ ፍርድ ቤቱ በሕግ ከተደነገገው ውሳኔ ሳያልፍ ቅጣቶችን የሚያከብደው (አንቀጽ ፻፹፫):-

ሀ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በከሐዲነት ወይም በወስላታነት፣ ወራዳነትን ወይም መጥፎ አመልን በሚያሳይ ምቀኝነት፣ ጥላቻ፣ ስግብግብነት፣ መጥፎ ነገርን ለመሥራት ወይም ሰውን ለመጉዳት ፍጹም ፈቃደኛ በመሆን፣ ወይም በተለየ ክፋት ወይም ጨካኝነት እንደሆነ፣

ለ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው ሥልጣኑን፣ ተግባሩን ወይም የተጣለበትን እምነት ወይም ኃላፊነት ያለአግባብ በመገልገል እንደሆነ፣

ሐ/ ወንጀለኛው በቀድሞ ጥፋተኛነቱ፣ ወንጀልን ማድረግ ሙያ ወይም ልማድ አድርጐ መያዙ፣ ወይም የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፣ ጊዜ፣ ቦታና የአፈጻጸሙ አኳኋን፣ በተለይም በሌሊት ወይም በሽብር ወይም በሁከት ለአደጋ ሽፋን ወይም በጦር መሣሪያ ወይም በሌላ አደገኛ መሣሪያ ወንጀሉን በማድረግ የተለየ አደገኛነቱን አሳይቶ እንደሆነ፤

መ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው ወንጀል ለመፈፀም በተደረገ ስምምነት መሠረት ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ወይም ወንጀል ለመፈፀም ከተቋቋመ ቡድን ጋር በመስማማት ወይም አባል በመሆን ይልቁንም እንደወንጀል ቡድን ሹም፣ አደራጅ ወይም መሪ በመሆን እንደሆነ፤ ወይም

ሠ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በዕድሜው፣ በጤንነቱ፣ በኑሮው ወይም በሥራው ሁኔታ ልዩ ጥበቃ በሚያሻው ሰው ላይ በተለይም ለመከላከል አቅም በሌለው፣ መንፈሰ ደካማ፣ በሽተኛ ወይም የአካል ጉዳተኛ፣ እሥረኛ ወይም በቅርብ ዘመዱ ላይ ወይም የበላዩ ወይም የበታቹ በሆነ ሰው ላይ፣ በሕግ በተቋቋመ ባለሥልጣን ወይም የሥራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ በአንድ የሕዝብ አገልጋይ በሆነ ሠራተኛ ላይ እንደሆነ፤ ነው::

፪ እነዚህ ሁኔታዎች በሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀል ማቋቋሚያ ወይም ለቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች እንደሚሆኑ በተደነገገ ጊዜ የወንጀሉን ቅጣት ለማክበድ ሲል ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ሁኔታ ዳግመኛ ምክንያት ሊያደርገው አይችልም::

## አንቀጽ ፹፭ ልዩ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች፤ የወንጀሎች መደራረብና ደጋጋሚነት

ተደራራቢ ወንጀሎችና ደጋጋሚነት በሚያጋጥሙበት ጊዜ ቅጣቱ የሚከብደው በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፻፹፬ እስከ ፻፹፰ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ፹፮ ሌሎች ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች

ቅጣትን ለማቅለል (አንቀጽ ፻፸፱) ወይም ለማክበድ (አንቀጽ ፻፹፫) የሚያስችል፣ በሕግ በግልጽ ያልተጻፈ ሌላ በቂ ምክንያት ሲገኝና ይህንኑ ፍርድ ቤቱ የሚቀበለው ሲሆን ለምን እንደተቀበለው ገልጾ መጻፍ አለበት፡፡

## ሁለተኛ መጽሐፍ

## የወንጀል ቅጣትና አፈፃፀሙ

## ርዕስ አንድ

## ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች፣ እንዲሁም አፈፃፀማቸው

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ፹፯ መርህ

በዚህ ሕግ የተመለከቱት ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ሕጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም አለባቸው (አንቀጽ ፩)፡፡

ቅጣቶቹና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምንጊዜም ሰብአዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡

BACK



## አንቀጽ ፹፰ የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰን

፩ ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የዚህን ሕግ ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎች፣ እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው።

፪ ቅጣቱ ሊወሰን የሚገባው፣ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣ ያለፈ የሕይወት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የአሳቡን ዓላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን ነው።

፫ የዚህ ሕግ የልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት ይወስናል።

፬ የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (Manual) ያወጣል።

## አንቀጽ ፹፱ በጣም ቀላል የሆኑ ወንጀሎች

በጣም ቀላል የሆኑ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ ስለማስጠንቀቂያ ወይም ስለተግሳጽ (አንቀጽ ፻፳፪) ወይም ስለደንብ መተላለፍ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመከተል ሊወስን ይችላል።

በጣም ቀላል የሆኑ ወንጀሎች የሚባሉት ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ናቸው።

BACK



## ምዕራፍ ሁለት

## ለአካለመጠን በደረሱ ሰዎች ላይ የሚፈፀሙ መደበኛ ቅጣቶች

## ክፍል አንድ

## ዋና ቅጣቶች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የገንዘብ ቅጣቶች

### ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል አንድ

### መቀጮ፣ ንብረትን መውረስና መያዝ

#### አንቀጽ ፺ መቀጮ፣ የመቀጮ አወሳሰን መርሆች

፩ በወንጀል ምክንያት መቀጮ የሚከፈለው በገንዘብ ነው፤ ገቢነቱም ለመንግሥት ነው:: ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር መቀጮው ከብር አሥር እስከ ብር አስር ሺህ ሊደርስ ይችላል:: ሆኖም ተቀጪው ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት በሆነ ጊዜ፤ መቀጮው ከአንድ መቶ ብር እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ ይሆናል::

፪ ፍርድ ቤቱ በተፈረደበት ሰው ላይ የመቀጮውን ልክ የሚወስነው የወንጀሉን ክብደት፣ የአደገኛነቱን መጠን፤ የሀብቱን ሁኔታ፣ የገቢ ምንጩን፣ ስለቤተሰቦቹ አስተዳደር ያለበትን ሸክም፣ የሙያ ሥራውንና ከሥራው የሚያገኘውን ገቢ መጠን፣ ዕድሜውንና የጠ ንነቱን ሁኔታ በማመዛዘን ነው::

፫ በሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ የእሥራት ቅጣት ብቻ በተደነገገ ጊዜና ተቀጪው የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በሆነ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት ቀላል እሥራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር አስር ሺህ፣ እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እሥራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር ሃያ ሺህ፣ እስከ አስር ዓመት ፅኑ እሥራት ለሚያስቀጣ እስከ ብር ሃምሳ ሺህ፣ ከአሥር ዓመት በላይ ፅኑ እሥራት የሚያስቀጣ ወንጀል ሲሆን በዚህ

BACK



አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) እስከ ተመለከተው ከፍተኛ ወሰን ለመድረስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል::

፬ በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል ውስጥ ወይም በሌላ ሕግ ላይ መቀጮ ብቻ በተደነገገ ጊዜ እና ተቀጪው የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በሆነ ጊዜ መቀጮው አምስት እጥፍ ይሆናል::

## አንቀጽ ፺፩ መቀጮን ከእስራት ጋር ማጣመር

የዚህ ሕግ ልዩ ክፍል መቀጮንና እሥራትን በአማራጭ የደነገገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የወንጀሉን ክብደትና የወንጀለኛውን ሁኔታ በማመዛዘን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ሁለቱንም አጣምሮ ሊወስን ይችላል::

## አንቀጽ ፺፪ አፍቅሮ ንዋይ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መሆኑ

፩ በተለይ ከፍ ያለ ቅጣት የሚወስኑት የልዩ ድንጋጌ ደንቦች እንደተጠበቁ ሆነው ወንጀለኛው ወንጀል ያደረገው የአፍቅሮ ንዋይ ስሜት አነሳስቶት ወይም ወንጀለኛነትን እንደሙያ ሥራ በመቁጠር በዚሁ ሥራው ጥቅም ሊያገኝ የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ባጋጠመው ቁጥር በእንደዚህ ያለ ተግባሩ መጠቀምንና ይህንኑ እንደጥቅም ማግኛ የመደበው ሆኖ የኑሮውም ሁኔታና በወንጀሉ ያገኘው ጥቅም ይህንኑ ተግባሩን በግልጽ የሚያሳይ በቂ ምክንያት መሆኑ የተገመተ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ቅጣቱን በማሳደግ እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ የሚደርስ መቀጮ ሊወስንበት ይችላል::

ምንጊዜም ቢሆን መቀጮው በወንጀሉ ድርጊት ምክንያት የተገኘውን ጥቅም ከመውረስ በተጨማሪ የሚወሰን ይሆናል::

BACK



፪ የወንጀሉን ድርጊት ለመፈጸም ያነሳሳው የአፍቅሮ ንዋይ ምክንያት ሆኖ ይህ የአፍቅሮ ንዋይ መነሾ የተደረገውን ወንጀል የማያቋቁም ቢሆንም ስለእንደዚህ ያለው ጥፋት የሚገባውን ቅጣት በሚወስኑት በሕጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች ላይ መቀጮ ተገልጾ ያልተመለከተ ቢሆንም እንኳ ፍርድ ቤቱ ከሚወስነው የእሥራት ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ጋር መቀጮንም አጣምሮ ሊፈርድ ይችላል።

<u>አንቀጽ ፺፫ መቀጮን ማስገባት</u>

፩ ተቀጪው መቀጮውን ወዲያውኑ መክፈል አለበት።

፪ ተቀጪው መቀጮውን ወዲያውኑ ለመክፈል የማይችል ሲሆን ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ለገንዘቡ መክፈያ ጊዜ ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር ጊዜ ይሰጠዋል።

፫ እንዲሁም የተቀጪው የኑሮ ሁኔታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምንበት መቀጮውን ጥቂት በጥቂት እንዲከፍል ሊፈቅድለት ይችላል። እርግጠኛ የሆነ ችሎታውንም በመገመት የመክፈያውን ጊዜና የገንዘቡን ልክ ፍርድ ቤቱ ይወስናል። የገንዘብ መክፈያው ጊዜ ከሦስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም።

<u>አንቀጽ ፺፬ ወዲያውኑ መቀጮ በማይከፈልበት ጊዜ ፍርድ ቤት የሚወስደው እርምጃ</u>

፩ የተወሰነው መቀጮ ወዲያውኑ በማይከፈልበት ጊዜ ሁሉ ተቀጪው የተወሰነበትን መቀጮ በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ ለመክፈል የሚችል መሆኑ እንዲረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ተስማሚ የሆነ የሰው ዋስትና ወይም ግዙፍ መያዣ እንዲሰጥ ያዝዛል።

ተቀጪው ሊሰጥ የሚገባውን የማረጋገጫ ዋስትና መጠን ፍርድ ቤቱ የሚወስነው የነገሩን ሁኔታና፣ የተቀጪውን የኑሮ ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባትና ፍትህንም መሠረት በማድረግ ነው።

፪ ተቀጪው በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መቀጮውን ያልከፈለ እንደሆነ ዋስትና የተገባበት ገንዘብ ወይም በግዙፍ መያዣነት የተሰጠው ንብረት ገቢ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ በያዘው የወንጀል መዝገብ አስፈላጊውን ይወስናል።

፫ ተቀጪው የዋስትና ግዴታ ለመግባት ወይም መያዣ ለማቅረብ ባልቻለ ወይም ባልፈቀደ ጊዜ ንብረቱ በሕጉ አግባብ ተይዞ እንዲሸጥና ገንዘቡም ገቢ እንዲሆን ይወሰናል። የንብረቱም ሽያጭ ሲፈፀም በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺፰(፫) የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፺፮ መቀጮውን በሥራ መለወጥ</u>

ከላይ በአንቀጽ ፺፫ እና ፺፬ መሠረት መቀጮው ገቢ ያልሆነ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ለመንግሥት ወይም ለሕዝብ አገልግሎት ድርጅት በሥራ በማገልገል እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ያዝዛል።

ፍርድ ቤቱ የመቀጮውን መጠን ከግምት በማስገባት መቀጮው ተከፍሎ የሚያልቅበትን ጊዜ ይወስናል። ሆኖም የሚወሰነው ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊበልጥ አይችልም።

<u>አንቀጽ ፺፯ መቀጮውን በግዴታ ሥራ መለወጥ</u>

ተቀጪው ከዚህ በላይ ከአንቀጽ ፺፫ እስከ ፺፮ በተደነገገው መሠረት መፈፀም ያልቻለ እንደሆነ፣ የግዴታ ሥራ እንዲሠራ ፍርድ ቤት መወሰን አለበት።

በዚህ አንቀጽ መሠረት የግዴታ ሥራ እንዲሠራ ፍርድ ቤት የሚወስነው ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊበልጥ አይችልም።

## አንቀጽ ፺፯ የግዴታ ሥራ የቅጣት አፈፃፀምን ማቆም

መቀጮው በግዴታ ሥራ በተለወጠ ጊዜ፣ ጥፋተኛው የዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፭ ከተገለፀው ሁኔታ በተጨማሪ በድህነቱ፣ ስለቤተሰቦቹ አስተዳደር ባለበት ኃላፊነት፣ በጤንነቱ ወይም ተገቢ በሆነ በማናቸውም ምክንያት የግዴታ ሥራውን ለመሥራት የማይችል ከሆነ የግዴታ ሥራው የቅጣት አፈፃፀም እንዲቋረጥ ፍርድ ቤቱ ሊያዝዝ ይችላል።

## አንቀጽ ፺፰ ንብረት መውረስ

፩ በሕጉ ላይ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች የተመለከቱትን የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በመከተል የወንጀለኛው ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲወረስ ሊፈርድ ይችላል።

፪ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ሥራ ወንጀለኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘው ንብረት ይወረሳል።

እንዲሁም የውርሱ ትዕዛዝ በሕጋዊ መንገድ የተገኘውን ንብረትም ይጨምራል።

፫ ውርሱ ሊፈጸም የማይቻለው:-

ሀ/ ለተቀጪውና ለቤተሰቡ መተዳደሪያ አስፈላጊ የሆኑ ለዘወትር የቤት አገልግሎት የሚጠቅሙ የሥራ ማከናወኛ ቁሳቁሶች፣ የጥበብ ወይም የእርሻ ሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎች ሲሆኑ፤

ለ/ ቢያንስ ለስድስት ወር ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ልዩ ሁኔታዎችን አይቶ ይገባል ብሎ

BACK



በሚገምተው ምክንያት ለተገለጸና በቂ አስተያየት ሊሰጠው ተገቢ በሆነ ውሳኔ ከዚህ ለሚበልጥ ጊዜ ለተቀጪው ቤተሰብ ሕይወትና ለመተዳደሪያቸው ወይም አስፈላጊ የሆኑት የዕለት ምግብና ለኑሮዋቸው መደገፊያ የሆኑ ለልዩ ልዩ ገቢዎች ሲሆኑ፤

ሐ/ ከዘር በውርስ የወረደ ማናቸውም ንብረት ሆኖ ተቀጪው በስጦታ፣ በኑዛዜ ወይም በሌላው ዓይነት መንገድ ሊያዝበት የማይችልበት ሲሆን፤

መ/ ከወንጀሉ ንፁህ የሆነ የወንጀለኛውን ባለቤት በሚመለከት፣ ከጋራ ንብረታቸው ግማሹ እንዲሁም ንፁህን የሆኑ የወንጀል አድራጊው ባለቤት ወይም ልጆች ወይም የሌሎች የግል ንብረት ሆኖ በሕግ አግባብ ወይም በልማዳዊ ሥርዓት መሠረት በግል በባለአደራነትና በአስተዳዳሪነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ወይም በሙሉ አዛዥነት ምክንያት በተቀጪው ይዞታ ሥር የሚገኙ ሀብቶች ሁሉ ሲሆኑ፤ ነው::

<u>አንቀጽ ፺፱ ንብረትን መያዝ</u>

ማንም ሰው በአገሪቱ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ወይም በውስጥና በውጭ ደህንነት ላይ አድማ በማድረጉ ወይም ጉዳት የሚያደርስ ተግባር በመፈጸሙ ምክንያት በሌለበት በተፈረደበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከሚወስንበት ከማንኛውም ቅጣት ጋር አጣምሮ ንብረቱ እንዲያዝ ለማዘዝ ይችላል::

የንብረት መያዝ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ በአንቀጽ ፺፰(፫) የተመለከቱት የአወሳሰን ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ::

BACK



## ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል ሁለት
## ወንጀሉ የሚያስከትላቸው ሌሎች የገንዘብ ውጤቶች

### አንቀጽ ፻ ለመንግሥት ገቢ ሊሆን የሚገባው ሀብት

፩ አንድ ሰው ለወንጀል ሥራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመሥራት እንዲረዳው ወይም ወንጀሉን ለፈጸመበት ዋጋ እንዲሆነው የተሰጠው ወይም ሊሰጠው የታቀደው ማናቸውም ጥቅም ሁሉ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል።

የተባሉት ንብረቶች በዓይነት ያልተገኙ እንደሆነ ተቀባዩ ዋጋቸውን ለመንግሥት ማስገባት አለበት።

፪ ማናቸውም በወንጀል የተገኘ ንብረት በተለመዱት ደንቦች መሠረት ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ባለንብረቱ ወይም ባለመብቱ ያልተገኘ እንደሆነ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል።

ሆኖም ንብረቱ የሚበላሽ፣ ወይም ከጥቅም ውጭ ይሆናል ተብሎ የሚገመት ከሆነ በደንቡ መሠረት ተሸጦ ገንዘቡ ሥልጣን በተሰጠው መሥሪያ ቤት እስከ አምስት ዓመት ድረስ በአደራ ሊቀመጥ ይችላል።

### አንቀጽ ፻፩ ንብረትን መተካት ወይም የጉዳት ካሣና ኪሣራን መክፈል

ወንጀሉ በተበዳዩ ወይም በተበዳይ ባለመብቶች ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ባደረሰባቸው ጊዜ ተበዳዩ ወይም ስለተበዳዩ መብት ያላቸው ሰዎች በዳዩ ያደረሰባቸውን ጉዳት እንዲከሳቸው፣ ያጠፋውን ወይም ያፈረሰውን እንደነበረ እንዲመልስ እንዲሁም ለደረሰባቸው ጉዳት ተመዛዛኝነት ያለው ካሣ በኪሣራ ስም እንዲከፈላቸው እንዲፈረድበት ሊጠይቁ ይችላሉ።

BACK



ይህንን ለማድረግ የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ክሱ ጋር አጣምረው ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይህም በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል።

አንቀጽ ፻፪ ለተበዳይ የሚሰጠው ካሣ

፩ ወንጀለኛው ወይም ስለእርሱ ተጠያቂ የሆኑት እንደነገሩ ሁኔታና ወይም በኑሮአቸው ምክንያት በተበዳዩ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሊከሱ የማይችሉ መሆናቸው በታወቀ ጊዜ ከወንጀለኛው ላይ ከተያዘው ዕቃ ከሚገኘው ገንዘብ ውስጥ ወይም በዋስትና መያዣ ስም ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ ወይም ከመቀጮው ውስጥ ወይም በጉልበት ሥራ ተለውጦ ከሚያገኘው የገቢ ሂሣብ ውስጥ ወይም ከተወረሰው ንብረት ሂሣብ ውስጥ ለተበዳዩ እንዲከፈል ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል።

፪ መንግሥት ለተበዳዩ በከፈለው የካሣ ገንዘብ ልክ በተበዳዩ መብት ተተክቶ ጉዳቱን ባደረሰው ወንጀለኛ ላይ በቀጥታ ሊጠይቅና ሊቀበል ይችላል።

ንዑስ ክፍል ሁለት
የግዴታ ሥራ እና ነፃነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች
ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል አንድ
የግዴታ ሥራ

አንቀጽ ፻፫ ከግዴታ ሥራ ከሚገኘው ገቢ ተቀንሶ ለመንግሥት የሚከፈል ገንዘብ

፩ ወንጀሉ ከባድነት የሌለው ሆኖ የሚያስከትለውም ቅጣት ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት እንደሆነ ጥፋተኛውም መስራት የሚችል ሆኖ ለኅብረተሰቡ አደገኛ የማይመስል ሲሆን የግል ነፃነቱ ሳይገደብ ቁጥጥር እየተደረገበት የግዴታ ሥራ ቅጣትን እንዲፈፅም ፍርድ ቤቱ ሊወስንበት ይችላል።

BACK



ይህ ቅጣት ከአንድ ቀን እስከ ስድስት ወር ሊደርስ ይችላል::

፪ ቅጣቱም የሚፈጸመው ተቀጪው ዘወትር በሚሰራበት ወይም በተቀጠረበት ቦታ ወይም በሕዝባዊ ተቋም ወይም ሕዝባዊ ሥራ በሚካሄድበት ሥፍራ ይሆናል::

ከተቀጪው የድካም ዋጋ ወይም በሥራ ፍሬው ከሚያገኘው ጥቅም እስከ አንድ ሦስተኛ /ሲሶ/ በማይበልጥ ሂሣብ እየተቀነሰ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል::

፫ ከተቀጪው ጥቅም ላይ ሊቀነስ የሚገባው የገንዘብ ልክ፣ ቅጣቱ የሚፈጸምበት ሥፍራና ቅጣቱ የሚቆይበት ጊዜ እንዲሁም ተገቢ የሆነው የቁጥጥሩ ዓይነት በፍርድ ላይ ይወሰናል::

<u>አንቀጽ ፻፬ የግል ነፃነትን ከመገደብ ጋር የሚወሰን የግዴታ ሥራ</u>

፩ የነገሩ ሁኔታ ተገቢ ወይም አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ በሆነ ጊዜ በተለይም ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፻፫(፩) መሠረት የተጣለበትን ግዴታ ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፤ ወይም ተቀጪውን ከጐጂ አካባቢ ወይም መጥፎ ጠባይ ካላቸው ሰዎች ማግለል ሲያስፈልግ የግዴታ ሥራው ቅጣት የግል ነፃነቱን ከመገደብ ጋር እንዲፈፀምበት ፍርድ ቤቱ ሊያዝ ይችላል::

፪ ፍርድ ቤቱ የነገሩን ሁኔታ መሰረት በማድረግ ነፃነት የመቀነሱን የቅጣት ዓይነትና ቅጣቱ የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል::

ይህም ቅጣት ተቀጪውን ከአንድ የሥራ ቦታ ወይም ከአንድ አሠሪ ዘንድ ወይም ከአንድ የሥራ ተቋም ሳይለቅ ወይም ከመኖሪያ ሥፍራው ሳይወጣ ወይም

በመንግሥት ባለሥልጣኖች ተቆጣጣሪነት ከሚጠበቅ ከአንድ ከተወሰነ ሥፍራ ሳይለይ የግዴታ ሥራውን እንዲያከናውን የሚያደርገው ሊሆን ይችላል::

፫ ተቀጪው የተሰጠውን የግዴታ ውሳኔ ጥሶ የተገኘ እንደሆነ ቅጣቱ በዚያው በቀረው ጊዜ ልክ ወደ ቀላል እሥራት ይለወጣል::

<u>አንቀጽ ፻፭ በሕመም ጊዜ የግዴታ ሥራ ቅጣት የሚታገድበት ሁኔታ</u>

የግዴታ ሥራ የተፈረደበት ሰው የግዴታ ሥራውን በሚፈጽምበት ጊዜ የታመመ እንደሆነ፣ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺፯ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ፤ ከሕመሙ እስከሚድን ድረስ የግዴታ ሥራውን እንዲሰራ አይደረግም::

ከሕመሙ ሲድን የግዴታ ሥራውን እንዲቀጥል ይደረጋል፤ የግዴታ ሥራውን መቀጠል ካልቻለ ግን ከግል ጤንነቱና ሁኔታው ጋር ተስማሚ የሆነ ሌላ ሥራ እንዲሠራ ይታዘዛል:: የዚህ ዓይነቱን ትዕዛዝ መስጠት ወይም ተግባራዊ ማድረግ ካልተቻለ ፍርድ ቤቱ በተቀጪው ላይ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ቅጣት አይወስንም::

<u>ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
<u>የግል ነፃነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች</u>

<u>አንቀጽ ፻፮ ቀላል እሥራት</u>

፩ ቀላል እሥራት ከባድነቱ መካከለኛ የሆነ ወንጀልን ባደረገና ጥፋተኛውም ለኅብረተሰቡ እጅግ አደገኛ መስሎ ባልታየ ጊዜ የሚወሰን የነፃነት ማሳጣት ቅጣት ነው::

ስለአመክሮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀላል እሥራት ከአሥር ቀን እስከ ሶስት ዓመት ሊደርስ ይችላል::

ሆኖም ከወንጀሉ ከባድነት የተነሳ በህጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ ወይም በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ ወይም ወንጀለኛው በተደጋጋሚ ሲቀጣ የቀላል እሥራቱ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ ይችላል:: ፍርድ ቤቱ እሥራቱ የሚቆይበትን ጊዜ በፍርዱ ላይ ይወስናል::

፪ እሥራቱም በተለይ ለዚሁ ብቻ ተብለው በተቋቋሙ ማረሚያ ቤቶች ወይም የማረሚያ ቤት ክፍሎች ውስጥ ይፈፀማል::

## አንቀጽ ፻፺ ቀላል እሥራትን በግዴታ ሥራ መተካት

እስከ ስድስት ወር የሚደርስ የቀላል እሥራት ቅጣት በሕጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቶ በሚያጋጥምበት ጊዜ ሁሉ የዚህን የግል ነፃነት የማሳጣት ቅጣት ለማስፈፀም ወይም በእሥር ቤቱ መልካም አካሄድ ላይ ችግር የሚፈጥር ሆኖ የተገመተ እንደሆነ ወይም የተቀጪውንም ጠባይ ለማሻሻል ወይም ወደ ማህበራዊ ኑሮው መልሶ ለማግባት የማይስማማ ሆኖ የታየ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በእሥራቱ ምትክ የግዴታ ሥራን ሊወስን ይችላል (አንቀጽ ፻፫፣ ፻፬)::

በሕጉ ልዩ ክፍል በቀላል እሥራት ምትክ የግዴታ ሥራ ቅጣትን ስለመተካት የተደነገገ ባይኖርም በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል::

## አንቀጽ ፻፺፩ ጽኑ እሥራት

፩ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚወሰነው ከባድ ወንጀል ባደረጉና በተለይም ለኅብረተሰቡ አደገኛ በሆኑ ወንጀለኞች ላይ ነው::

የጽኑ እሥራት ቅጣት ግቡ ተቀጪው እንዲታረምና ወደ ማህበራዊ ኑሮ እንዲመለስ ከማድረግ በተጨማሪ በተለይ ለኅብረተሰቡ ደህንነት በጥብቅ ቁጥጥር ሥር እንዲቆይ ለማድረግ ነው።

ይህ ቅጣት የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ሊደርስ ይችላል። በሕጉም ተገልጾ የተደነገገ ሲሆን የዕድሜ ልክ እሥራት ሊወሰን ይችላል። ቢሆንም ስለአመክሮ የተወሰኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው።

፪ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈጸመው በተለይ ለዚህ ቅጣት መፈጸሚያ እንዲሆኑ ታስበው በተሰሩና ለዚሁ በተሰናዱ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ብቻ ነው።

የጽኑ እሥራት ቅጣት የአፈጻጸም ሁኔታ ከቀላል እሥራት የአፈጻጸም ሁኔታ በይበልጥ ይከብዳል።

<u>አንቀጽ ፻፱ የወል ድንጋጌዎች</u>

ከዚህ የሚከተሉት የአፈፃፀም መሠረታውያን ደንቦች ነፃነትን ለሚያሳጡ ለሁለቱም ዓይነት ቅጣቶች ተፈፃሚዎች ይሆናሉ። የደንቦቹም ዓላማ የቅጣቶቹ አወሳሰን ሊደርስበት የፈለገውን ውጤት ማስገኘት ነው።

ስለቅጣቶች አፈጻጸም በጠቅላላው፣ ወደ እሥራት ቦታ ስለማስገባት፣ እሥረኞችን ስለመለያየት፣ እሥረኞች ከውጭ ሰዎች (ጠያቂዎች) ጋር ስለሚያደርጉት ግንኙነት፣ ስለውስጣዊ ሥነ ሥርዓትና በሥነ ሥርዓት ጉድለት ስለሚወሰዱት እርምጃዎች አወሳሰን፣ እንዲሁም ስለእሥረኞች ትምህርትና መንፈሳዊ ደህንነት ስለሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ጉዳይ፤ በቅጣቶች አፈጻጸም ሕግና በማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ደንቦች ውስጥ ተለይተው ይገለጻሉ።

BACK



## አንቀጽ ፻፲ እሥረኞችን መለያየት

፩ ጾታቸው የተለያዩ ወንጀለኞች ቅጣታቸውን የሚፈጽሙት በተለያዩ እሥር ቤቶች ውስጥ ነው:: ለዚሁም ጉዳይ የተለያዩ እሥር ቤቶች ያልተዘጋጁ ሲሆን ባለው እሥር ቤት ውስጥ የተለያየ ክፍል እንዲኖር ተደርጐ ሴቶችና ወንዶች እንዳይገናኙ ይደረጋሉ::

፪ በጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ወይም በልዩ ክፍል ተለይተው እንዲታሠሩ የተፈረደባቸው ጥፋተኞች በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ለአካለመጠን ካልደረሱ እሥረኞች ወይም በቀላል እሥራት ከተቀጡ ለአካለመጠን ከደረሱ እስረኞች ጋር በፍፁም እንዳይገናኙ ይደረጋል::

፫ ውሳኔ ያላገኙ እሥረኞች ወይም በዕዳ ምክንያት ተይዘው የታሰሩ ወይም ከመንግሥት ሥራ ግዴታቸው የተነሳ ከእሥረኞች ጋር ግንኙነት የነበራቸው ሆነው በወንጀል ወይም በዕዳ ምክንያት የታሰሩ ሰዎች ከሌሎች እሥረኞች ጋር አይቀላቀሉም::

## አንቀጽ ፻፲፩ የመስራት ግዴታና የሥራው ዋጋ

፩ በአንድ ወንጀለኛ ላይ ነፃነትን የማሳጣት ቅጣት በተፈረደበት ጊዜ ሁሉ ተቀጪው በግዴታ እንዲሰራ ማድረግ የቅጣቱ አፈጻጸም አካል ነው::

ማንኛውም ጤናማ የሆነ ተቀጪ ከማረሚያ ቤቱ አስተዳደር የታዘዘውን ሥራ መቀበል አለበት:: ይህም ሥራ በተቻለ መጠን ሁሉ ከተቀጪው ችሎታ ጋር የሚስማማና ጤንነቱን የማይጐዳ፣ ጠባይ ለማረምና በሥራ ልምድ ትምህርትም አእምሮውን ለማጐልመስ የሚረዳው ሆኖ ወንጀለኛው የቅጣቱን ጊዜ ሲጨርስ ተመልሶ ተፈላጊውን የማህበራዊ ኑሮ ለመያዝ

BACK



ወደሚያስችለው ግብ ሊያደርሰው የሚችል መሆን አለበት፡፡

፪ ይህን የግዴታ ሥራ እንዲፈጽም የተገደደ ማንኛውም እሥረኛ ሁሉ ለሥራው ተገቢ ከሆነና ጠባዩም መልካም ከሆነ ለሥራ ችሎታውና ለሚሰጠውም አገልግሎት ተመዛዛኝ የሆነ የቀን ክፍያ ይታሰብለታል፡፡

ሊታሰብለት የሚገባው የገንዘብ ልክ፣ ታስሮ በሚቆይበት ጊዜ የገንዘቡ ሂሣብ አያያዝና ከእሥራት ነፃ በሚለቀቅበት ጊዜ የሚደረገው የገንዘብ አሰጣጥ ሥርዓት በማረሚያ ቤት የውስጥ ደንቦች ላይ በተመለከተው መሠረት ይፈጸማል፡፡

<u>አንቀጽ ፻፲፪ የእሥራቱን ሁኔታ መለዋወጥ</u>

ቅጣቱ በተቀጪው ላይ ያደረሰውን የጠባይ ማረም ስሜትና በሚፈታበት ጊዜ ደንበኛውን የማህበራዊ ኑሮ ሕይወት ለመያዝ ተገቢ ለመሆን መቻሉን በማረጋገጥ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን መሠረታውያን ሃሣቦች በመከተል የተቀጪው የእሥራት ቅጣት አፈጻጸም ሁኔታ በየጊዜው እየተለዋወጠለት እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ የዚህም አፈጻጸምና አሠራር በቅጣት አፈጻጸም ሕግና በማረሚያ ቤቱ የውስጥ ደንብ ላይ ይገለጻል፡፡

፩ የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር አስፈላጊ ሆኖ ሲታየው ተቀጪው እሥር ቤት እንደገባ ወዲያውኑ ወይም ቅጣቱን በመፈፀም ላይ እንዳለ፣ እጅግ ቢበዛ ከሦስት ወር ለማያልፍ ጊዜ ለብቻው ተለይቶ እንዲታሰር ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር እስረኛው ተለይቶ እንዲታሰር ከማድረጉ በፊት የሕክምና ባለሙያ፣

BACK



አስፈላጊ ሲሆንም የስነ አእምሮ ሐኪም በማማከር የጥንቃቄውንና የጊዜውን ልክ ይወስናል::

፪ ዋናው የቅጣት ጊዜ የሚፈጸመው እንደአስፈላጊነቱና እንደጠቃሚነቱ እንደጊዜውም ሁኔታ መጠን፣ በሕብረት ወይም ለብቻ የሚሰራ የግዴታ ሥራን በመሥራት ነው::

ከሥራ ውጭና እንዲሁም ሌሊት እሥረኛውን ለብቻው የመለየት ጉዳይ በተቻለ መጠን ይከናወናል::

፫ እሥረኞች ጠባያቸውን በተሻሻለ ሁኔታ በማረማቸውና የተሻሻሉ በመሆናቸው መጠን ከእሥራትም የመፈቻቸው ጊዜ በመቃረቡ መጠን የተሻለ ምግብ የማግኘት፣ የጠያቂ አለመከልከል፣ የተቃለለ ሥራ የመሥራት፣ የዕረፍት ጊዜ የመስጠትና በሌላም ይህን በመሳሰለ ነገር የመጠቀም ሁኔታ የእሥራቱንም ሁኔታ የማቃለልና የማሻሻል ጥቅም በማረሚያ ቤቱ ሥራ መሪ ሊፈቀድላቸው ይችላል::

ከመጠን ያለፉ ወይም ጠባያቸው ደስ ያላሰኘ በሆነ ጊዜ ግን የተሰጧቸው ጥቅሞች እንዲቀሩባቸው ለማድረግ፣ ወይም የተቀጪዎቹ እልከኛነት ይህ እንዲደረግ አስፈላጊ መሆኑን ሲያሳይ፣ ላልተወሰነ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ጥቅሞቹን ማስቀረት ይቻላል::

## አንቀጽ ፻፲፫ በተወሰነ ገደብ በአመክሮ መፈታት

፩ የተቀጪው ጠባይ አጥጋቢ እንደሆነና በሕግ የተደነገጉት ሁኔታዎች ተሟልተው የተገኙ እንደሆነ (አንቀጽ ፪፻፪)፣ ተቀጪው የተወሰነበት የእሥራት ጊዜ ከማለቁ በፊት ለአመክሮ ቀደም ብሎ ሊፈታ ይችላል::

በአመክሮ ከመለቀቁ በፊት በአንድ በተወሰነ የቅጣት ወይም የሥራ ቦታ ወይም ይህን በመሳሰለ በማናቸውም የሥራ ድርጅት ውስጥ የፈተና ጊዜ እንዲያሳልፍ ለማድረግ ይቻላል::

፪ የቅጣቶችን አፈጻጸም የሚመለከተው ሕግና የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ደንቦች፣ የአመክሮውን አፈጻጸም፣ አሠራርና ዝርዝር ሁኔታዎች ይወስናሉ::

## አንቀጽ ፻፲፩ በወታደሮች ላይ የሚወሰን የቅጣት አፈፃፀም

ነፃነትን የማሳጣት ቅጣት በወታደሮች ላይ በተወሰነባቸው ጊዜ በወታደር እሥር ቤት ውስጥ፣ በወታደር ሠፈር ወይም የጦር ምሽግ በሚገኝበት ሥፍራ፣ በወታደር አስተዳደርና ሥነሥርዓት አፈጻጸም የተወሰነባቸውን ቅጣት የመፈጸም ደንብ እንደተጠበቀ ነው::

የአሠራሩም አፈጻጸም በውስጥ ደንብ የተወሰነው ይሆናል::

## አንቀጽ ፻፲፪ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የተያዘበትን ጊዜ መቁጠር

፩ ነፃነትን የማሳጣት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የቅጣቱ ፍርድ ከመወሰኑ አስቀድሞ ተቀጪው በወንጀሉ ምክንያት እጁ ተይዞ የቆየበትን ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ ከዋናው ቅጣት ጋር ይቆጥርለታል::

ቢሆንም ጥፋተኛው በገዛ ጥፋቱ በጥበቃ እንዲታሰር ወይም የእሥራቱ ጊዜ እንዲረዝምበት አድርጎ እንደሆነ ፍርድ ሳይወስንበት ለመጠበቂያ እጁ ተይዞ የቆየበት ጊዜ አይቆጠርለትም::

BACK



፪ ለመጠበቂያ እጁ ተይዞ የመቆየት ጉዳይ፣ ሁኔታ፣ አሠራርና አፈጻጸም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ በተደነገገው መሠረት ይፈጸማል።

## አንቀጽ ፻፲፮ የታመመ እሥረኛ ወደ ሐኪም ቤት ሲገባ ሆስፒታል የቆየበትን ጊዜ መቁጠር

፩ አንድ ወንጀለኛ የተወሰነበትን ቅጣት በመፈፀም ላይ እያለ በመታመሙ ለመታከም እንዲችል ወደ ሆስፒታል የተዛወረ እንደሆነ በመታመሚያ ቦታ የቆየበት ጊዜ ሊፈጽመው ከሚገባው ቅጣት ጋር ይታሰብለታል።

እንዲሁም ወደ ሆስፒታል እንዲዛወር ያስፈለገበት ከመታሰሩ በፊት በደረሰበት ሕመም ወይም ሌላ ምክንያት ሲሆን፣ የዚህ አንቀጽ የንኡስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቆየበት ጊዜ በሙሉ በቅጣት ከሚፈጽመው ጊዜ ጋር ይቆጠርለታል።

፪ ተቀጪው አስቦ ሕመሙን በራሱ ላይ እንዲደርስ በማድረግ ወይም በማታለል ሆስፒታል ገብቶ ተኝቶ እንደሆነ በዚህ አኳኋን ሆስፒታል ተኝቶ ያሳለፈው ጊዜ ሊፈጽመው ከሚገባው ቅጣት ጋር አይታሰብለትም።

፫ ወንጀለኛው ቅጣቱን በመፈጸም ላይ እያለ አእምሮው በመታወኩ ምክንያት ለድርጊቱ ሃላፊ ሊሆን አለመቻሉ ልዩ አዋቂዎች ያረጋገጡ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ለጊዜው እንዲቋረጥ ተደርጐ ወደ መታከሚያ ቤት ወይም ለዚሁ ተገቢ ወደሆነ የማስታመሚያ ቦታ ይዛወራል።

ሕመሙ የማይድን የአእምሮ በሽታ ሲሆን ቀሪው የቅጣት ጊዜ አይፈፀምበትም።

BACK



## ንዑስ ክፍል ሦስት
## የሞት ቅጣት

**አንቀጽ ፻፲፯ መርህ**

፩ የሞት ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ፍፃሜ ያገኘ ሆኖ እጅግ በጣም ከባድ በመሆኑና ወንጀለኛውም በተለይ አደገኛ በመሆኑ ለወንጀሉ ቅጣት እንዲሆን በሕጉ በግልፅ ተደንግጉ በተገኘ ጊዜ እንዲሁም ለወንጀለኛው ቅጣትን የሚያቃልልለት ምክንያት በታጣ ጊዜ እና ወንጀለኛው ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ዕድሜው ቢያንስ አስራ ስምንት ዓመት የሞላው ሲሆን ብቻ ነው::

፪ የሞት ቅጣት በአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ፍርዱ ካልጸና በቀር ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም:: በይቅርታ ወይም በምህረት ያልተሻረ ወይም ያልተለወጠ መሆኑ አስቀድሞ ከመመር መሩና ከመታወቁ በፊት ተፈጻሚነት አይኖረውም::

፫ የሞት ቅጣት በሕዝብ ፊት፣ በአደባባይ በስቅላት ወይም በሌላ በማናቸውም ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ አይፈጸምም:: ቅጣቱ በሰብአዊ ሁኔታ በማረሚያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲፈጸም ይታዘዛል:: የአፈፃፀሙ ዘዴም ጉዳዩን በሚመለከተው የፌዴራል ወይም የክልል ማረሚያ ቤት አስተዳደር የበላይ ሕግ አስፈፃሚ አካል ይወሰናል::

የሞት ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት በተቀጪው ላይ ማናቸውንም የስቃይ፣ የበቀል እርምጃ ወይም የአካል ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ የተከለከለ ነው::

፬ የሞት ቅጣት ከተፈጸመ በኋላ አስከሬኑን ቤተሰቡ ከጠየቀ ይሰጠዋል:: ጠያቂ ቤተሰብ ካልተገኘ ግን አስከሬኑ በተገቢው ሥነ ሥርዓት ይቀበራል::

**አንቀጽ ፻፲፰ የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሰው ቅጣቱ እስከሚፈፀም የሚቆይበት ሁኔታ**

የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሰው ቅጣቱ እስከሚጸናና እስከሚፈጸም ድረስ ጽኑ እሥራት የተፈረደበት እስረኛ ቅጣቱን በሚፈጽምበት ሁኔታ ታስሮ ይቆያል፡፡

የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ለእስረኛው ደህንነት አስፈላጊ የሆነውን የጥንቃቄ ጥበቃ ያደርግለታል፡፡

እስረኛው ሲፈልግና ከተቻለ በታሰረበት ክፍል ውስጥ ሥራ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ ፻፲፱ የሞት ቅጣት አፈፃፀም ታግዶ የሚቆይበት ሁኔታ**

በፍጹም ኢ-ኃላፊነት ወይም ከፊል ኃላፊነት ላይ በሚገኝ ወይም በጽኑ በታመመ ሰው ወይም ባረገዘች ሴት ላይ በዚሁ ሁኔታ ላይ እስከሚገኙበት ጊዜ ድረስ የተወሰነባቸው የሞት ቅጣት ታግዶ ይቆያል፡፡

**አንቀጽ ፻፳ የሞት ቅጣትን መለወጥ**

፩ ያረገዘች ሴት ሕይወት ያለው ልጅ የወለደች ስትሆንና ይህንኑም ልጅ መመገብና ማሳደግ ሲኖርባት የሞት ቅጣቱ በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ይለወጥላታል፡፡

፪ በዚህ ሕግ ውስጥ በተመለከቱት ድንጋጌዎች (አንቀጽ ፪፻፳፱ እና ፪፻፴) መሠረት የሞት ቅጣት በይቅርታ ወይም በምህረት ሊለወጥ ወይም ቀሪ ሊሆን ይችላል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ተጨማሪ ቅጣቶች**

**አንቀጽ ፻፳፩ መርህ**

ተጨማሪ ቅጣቶቹ የሚወሰኑት ለዋነኛው ቅጣት ተደራቢ ወይም ማሟያ በመሆን ነው፡፡ እነዚህ ቅጣቶች ተፈጻሚ

BACK



የሚሆኑት ፍርድ ቤቱ በፍርዱ ላይ በግልጽ ሲያዝዝ ብቻ ነው።

ተጨማሪ ቅጣቶች ለእያንዳንዱ ወንጀል ተደንግገው ባይገኙም በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው በተገኙ ጊዜ ሁሉ ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ቅጣቶችን የሚወስነው የቅጣትን ዓላማና በተለይም በተቀጪው ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን የጥበቃና የጠባይ ማረም ዝንባሌ በመከተልና በዚሁ አሳብ በመመራት ነው።

<u>አንቀጽ ፻፳፪ በጥፋተኛው ላይ የሚደረግ ማስጠንቀቂያ፣ ወቀሳ፣ ተግሣፅ፣ ጥፋተኛው የሚጠይቀው ይቅርታ</u>

፩ የጥፋተኛውን ክብር ጠቅሶ በማስገንዘብ በጥፋተኛው ላይ ወይም በኅብረተሰቡ ዘንድ መልካም ውጤት የሚያስገኝ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በገመተ ጊዜ ከዋናው ቅጣት በተጨማሪ በችሎት ወይም በፍርዱ ላይ ጠበቅ ያለ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ የመውቀስ፣ ወይም የመገሰፅ ፍርድ በግልፅ ሊወስን ይችላል። እንዲሁም ጥፋተኛው ጥፋቱን አምኖ ተበዳዩን ወይም ስለእርሱ ባለመብቶች የሆኑትን በግልፅ ይቅርታ እንዲጠይቅ ሊያዘው ይችላል።

፪ ወንጀሉ በጣም ቀላል መሆኑን ሕጉ በግልፅ በደነገገ ጊዜ ወይም ቅጣትን የሚያቃልሉ ምክንያቶች ሲገኙ (አንቀጽ ፹፪ እና ፹፫)፣ ወይም በልዩ ሁኔታ ቅጣትን ለማቃለል ሲቻል (አንቀጽ ፻፹)፣ ወይም ቅጣቱ ሳይፈፀም እንዲቆይ በተደረገ ጊዜ (አንቀጽ ፻፺፪)

BACK



ፍርድ ቤቱ ይህንን ቅጣት ለዋናው ቅጣት ምትክ አድርጎ ለመወሰን ይችላል።

## አንቀጽ ፻፳፫ ከሙያ መሻር

የጥፋቱ ዓይነትና ሁኔታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ ሲሆንና ወንጀለኛው በሙያዎቹ ሊሰራባቸው ያልተገባ ሰው መሆኑ ሲታወቅ ፍርድ ቤቱ፤

ሀ/ ከሕዝባዊ ሙያዎቹ በተለይም ከመራጭነት መብቱ፣ በአንድ ምርጫ ተካፋይ ከመሆንና ለሕዝብ አገልግሎት ሥራ ከመመረጥ፣ ወይም ለማዕረግ ከመመረጥ፣ በሰነድ ወይም የውል ስምምነት ላይ ምስክር ወይም ዋስ ከመሆን፣ ለፍርድ ሥራ ልዩ አዋቂ ወይም ነባሪ ሆኖ ከመስራት መብት፤ ወይም

ለ/ በቤተዘመድ ላይ ካለው መብት፣ በተለይም የወላጅነት ሥልጣን ከመያዝ ችሎታ፣ሞግዚትነት ወይም አስተዳዳሪ (ጠባቂ) ከመሆን መብት፤ ወይም

ሐ/ የሥራ ወይም የንግድ ፈቃድ የሚያስፈልገውን የሙያ፣ የኢንዱስትሪ ወይም የንግድ ሥራ ከመስራት መብት፤

ሊሽረው ይችላል።

## አንቀጽ ፻፳፬ ቅጣቱ የሚቆይበት ዘመንና አወሳሰኑ

፩ ማናቸውም ከሙያ የመሻር ቅጣት (አንቀጽ ፻፳፫) ለጊዜው ወይም ለዘወትር ሊሆን ይችላል። ለጊዜው ብቻ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር አያንስም፣ ከአምስት ዓመት አይበልጥም።

ጥፋተኛው የፈፀመውን ወንጀል ከባድነት፣ የቀድሞ ጥፋተኛነቱን፣ የጠባዩን አደገኛነት ወይም መጥፎነት፣ ወንጀሉን ይደጋግማል ተብሎ የሚያሰጋ መሆን

BACK


አለመሆኑን፣ ከመብት የመሻሩ ቅጣት ተፈላጊነትና ጠቃሚነት፣ ወይም ቅጣቱ በተቀጪው ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ውጤት እንዲሁም ማህበራዊ ኑሮውን ለመጠበቅ አስፈላጊነቱን በመገመትና መሠረት አድርጐ በመያዝ ፍርድ ቤቱ በእያንዳንዱ ጉዳይ ከመብቱ የመሻሩ ቅጣት የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል::

፪ የሞት ወይም የፅኑ እሥራት ቅጣት ፍርድ ከሕዝባዊ መብት የመሻርን ጉዳይ በግድ ማስከተል አለበት:: የፅኑ እሥራት ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ የመብቱ የመሻር ውጤት የሚቆይበትን ጊዜ ፍርድ ቤት ይወስናል:: የሞት ፍርድ ወይም የዕድሜ ልክ እሥራት ቅጣት በተወሰነ ጊዜ ስለይቅርታ (አንቀጽ ፪፻፴፱)፣ ስለምህረት (አንቀጽ ፪፻፵) እና ስለመሰየም (አንቀጽ ፪፻፵፪ እስከ ፪፻፵፯) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመብት የመሻሩ ቅጣት ለዘወትር ፀንቶ ይቆያል::

<u>አንቀጽ ፻፳፭ ከመብት የመሻሩ ቅጣት የሚፀናበት ጊዜ</u>

፩ ከመብት የመሻር ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው::

፪ ከመብት የመሻሩ ቅጣት የተሰጠው ለጊዜው እንደሆነ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ቅጣቱ ተፈጻሚ የመሆኑ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የተወሰነው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ዋናው ቅጣት ከተፈጸመበት ወይም ቅጣቱ በይቅርታ ከተሻረበት ወይም በይርጋ ቀሪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ነው::

በወንጀለኛው ላይ ነፃነትን የማሳጣት ቅጣት ተፈርዶበት በአመክሮ ከተለቀቀ በኋላ፣ በአመክሮ ተፈትቶ በቆየበት ጊዜ ሁሉ መልካም ጠባይ አሳይቶ እንደሆነ ከመብት የመሻር ቅጣት የሚቆይበት ጊዜ የሚታሰበው በአመክሮ ከእስራቱ ከተፈታበት ቀን ጀምሮ ነው::

የሙያ ሥራውን የመስራት መብቱ በፍርድ የተሻረበት ወንጀለኛ (አንቀጽ ፻፳፫(ሐ)) በአመክሮ እንዲፈታ ሲደረግ (አንቀጽ ፪፻፮) ለፈተና ያህል የሙያ ሥራውን በአመክሮው ጊዜ እንዲቀጥል ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድለት ይችላል::

<u>አንቀጽ ፻፳፪</u> <u>መብትንና ክብርን መመለስና መሰየም</u>

እንደነገሩ ሁኔታ በሕጉ ላይ በተመለከተው መሠረት በቅጣት ተሰርዞ የነበረውን ማናቸውም መብት ጥፋተኛው በወንጀል ሥራው ከመቀጣቱ በፊት እንደነበረው ሁኔታ ሊመለስለትና ሊሰየም ይችላል (አንቀጽ ፪፻፴፪- ፪፻፴፯)::

<u>አንቀጽ ፻፳፫</u> <u>ከመከላከያ ሠራዊት ማስወገድ፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ</u>

፩ በወታደራዊ ጉዳይ ጥፋተኛው በፈፀመው ወንጀል ወራዳ፣ መጥፎ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያሳይ ወታደራዊ ፍርድ ቤቱ ከሚፈርድበት ከዋነኛው ቅጣት ጋር ከደረጃው ዝቅ እንዲል ወይም ከመከላከያ ሠራዊት አባልነት እንዲወገድ ሊፈርድበት ይችላል::

እነዚህም ቅጣቶች የሚወሰኑት አግባብ ካለው የመከላከያ ባለሥልጣን ጋር አስቀድሞ በመመካከርና የሚሰጠውንም ተቀዳሚ ሃሣብ በመረዳት ነው::

፪ የነዚህ ቅጣቶች መወሰን ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ሌሎች ተጨማሪ ቅጣቶች መወሰንን አያግድም::

<u>አንቀጽ ፻፳፬</u> <u>ውሳኔው የሚጸናበት ሁኔታ</u>

ከመከላከያ ኃይል አባልነት የመወገድ ወይም ከደረጃ ዝቅ የመደረግ ቅጣት ውሳኔ የሚጸናው በወታደራዊ አስተዳደር ደንብ በተመለከተው መሠረት ነው::

## ምዕራፍ ሦስት

## ለአካለመጠን በደረሱ ጥፋተኞች ላይ የሚፈጸሙ የጥንቃቄ እርምጃዎች

## ክፍል አንድ

## ኃላፊነት በሌላቸውና ከፊል ኃላፊነት ባላቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ በተለየ ሁኔታ የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎች

### አንቀጽ ፻፳፱ መርህ

ፍርድ ቤቱ መደበኛውን ምርመራና የልዩ አዋቂውን ምርመራ መሠረት በማድረግ (አንቀጽ ፶፩) ወንጀል አድራጊው ኃላፊነት እንደሌለበት (አንቀጽ ፵፰) ወይም ከፊል ኃላፊነቱ (አንቀጽ ፵፱) መሆኑን ሲያረጋግጥ እንደነገሩ ሁኔታ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይወስናል።

### አንቀጽ ፻፴ ለጥንቃቄ በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥና እንዲታከም ማድረግ

፩ ወንጀል አድራጊው ካለበት ሁኔታ የተነሳ በሕዝብ ሠላምና ሥርዓት ላይ ችግር የሚያደርስ ወይም አብረውት በሚኖሩት ሰዎች ላይ አደጋ ያደርሳል ተብሎ ሲታመን ፍርድ ቤቱ ተስማሚ በሆነ ተቋም ውስጥ ተለይቶ እንዲቀመጥ ማዘዝ አለበት።

፪ ወንጀል አድራጊው ሕክምና የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ባለበት ተቋም እንዲታከም፣ ይህም ካልተቻለ በአንቀጽ ፻፴፩ በተደነገገው መሠረት ተገቢ ሕክምና ወደሚያገኝበት ተቋም ተዛውሮ እንዲታከም ያዝዛል።

ስለመልካም አጠባበቁም ተገቢ የሆኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች ይፈፀማሉ።

BACK



## አንቀጽ ፻፴፩ ሕክምና

፩ አድራጊው የአእምሮ ሕመም ወይም ጉድለት ወይም መስማትና መናገር የተሳነው የሆነ እንደሆነ ወይም የሚጥል በሽታ ያለበት ወይም በአልኰል መጠጥ ሱሰኝነት ወይም በአደገኛ መድኃኒቶች ወይም በአደንዛዥ ዕጾች የተመረዘ ወይም ይህን በመሳሰለ በማናቸውም በሽታ አእምሮው የተነካ ሆኖ እንዲታከም ወይም ተገቢውን ሌላ እርዳታ እንዲያገኝ የሚያስፈልግ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ተገቢ በሆነ ሐኪም ቤት ወይም ተቋም ገብቶ እንዲታከም ያዝዛል::

፪ ልዩ አዋቂው እንደሚያቀርበው ሃሣብ አድራጊው አደገኛ እንዳልሆነና በሆስፒታል ውስጥ ሆኖ መታከሙ አላስፈላጊ መሆኑ የታወቀ እንደሆነ በተመላላሽነት ብቻ እንዲታከም ፍርድ ቤቱ ያዝዛል::

በዚህን ጊዜ ሪፖርት ሊያቀርብለት በሚችል የሕክምና አዋቂ ወይም ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል ጥበቃና ቁጥጥር እንዲደረግበት ፍርድ ቤቱ ያዝዛል:: ይኸው አጠባበቅ አስተማማኝ ካልሆነና መልካም ውጤት የማያስገኝ መሆኑ ከተረጋገጠ ምንጊዜም ቢሆን ሊሻር ይችላል::

ፍርድ ቤቱ የጥበቃ ትዕዛዙን ከመሻሩ ወይም ሌላ ተገቢ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት አስፈላጊ ነው የሚለውን ሪፖርት እንዲያቀርብለት የህክምና አዋቂን ወይም ስልጣን የተሰጠውን አካል ሊያዝዝ ይችላል::

## አንቀጽ ፻፴፪ የሕክምናው እና የጥበቃው ውሳኔ የሚቆይበት ጊዜ

፩ አድራጊው እንዲታከም ወይም በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር ባለሥልጣን ያስፈፅማል::

BACK



አድራጊው የሚታከመው ወይም በተወሰነ ቦታ የሚቀመጠው ላልተወሰነ ጊዜ ነው:: ነገር ግን ፍርድ ቤቱ በየሁለቱ ዓመት ውሳኔውን እንደገና ይመረምራል::

ውሳኔው የተሰጠበት ምክንያት መጥፋቱን ልዩ አዋቂው ባረጋገጠ ጊዜ የአስተዳደሩ ባለሥልጣን ይህንኑ ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ሲያመለክት በተቀጪው ላይ እንዲፈፀምበት ታዞ የነበረው የጥንቃቄ እርምጃ እንዲቀር ፍርድ ቤቱ ያዝዛል::

፪ የጥንቃቄ እርምጃው የተደረገበት ምክንያት በመላ ያልጠፋ ቢሆንም ለጊዜው ብቻ እንዲለቀቅ የሚገባ መሆኑን ልዩ አዋቂው ያረጋገጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር ባለሥልጣን ያቀረበለትን ሪፖርት በመከተል አድራጊው እንዲታከም ወይም በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ታግዶ እንዲቆይ ያዝዛል::

የጥንቃቄ እርምጃው የታገደለት ሰው ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ በአንድ የጥበቃ ባልደረባ ቁጥጥር እንዲደረግበትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በአንቀጽ ፪፻፫ መሠረት የጠባይ አመራር እርምጃዎች እንዲወሰዱበት ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ይሰጣል::

፫ ለጠቅላላው ደህንነት አጠባበቅ ወይም ለተለቀቀው ሰው መልካም ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥፋተኛው እንዲለቀቅ ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ይሻራል::

የፈተናውን ጊዜ በሚገባ የፈፀመ እንደሆነ፣ የጥንቃቄ እርምጃው ይቀርለታል::

<u>አንቀጽ ፻፴፫ ከፊል ኃላፊነት በቅጣት ላይ ያለው ውጤት</u>

፩ <u>ከፊል</u> ኃላፊነት ስላላቸው ሰዎች የቅጣት አወሳሰን የተደነገገው እንደተጠቀበ ሆኖ (አንቀጽ ፶፱) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ለጊዜው አግዶ አድራጊው በጥንቃቄ መፈፀሚያ ቦታ ተወስኖ እንዲቆይ (አንቀጽ ፻፴) ወይም ሆስፒታል እንዲገባ (አንቀጽ ፻፴፩) ያዝዛል።

፪ የታዘዘው የጥንቃቄ እርምጃ ሲፈፀም የተቋሙ አስተዳደር ወይም ኃላፊነት የተሰጠው የጥበቃ ባልደረባ ያቀረበው ሪፖርት በጥፋተኛው ላይ ተወስኖ የነበረው ቅጣት አሁንም እንዲፈፀም አስፈላጊ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለጥበቃ በአንድ ቦታ ተወስኖ የቆየበት ወይም በሕክምና ያሳለፈው ጊዜ ለጊዜው ታግዶለት ከነበረው ቅጣት ላይ ሊቀነስለት የሚገባ ወይም የማይገባ መሆኑን በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፻፲፯ መሠረት ይወስናል።

ይህንንም ውሳኔ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ መሠረት አድርጐ የሚከተለው አድራጊው የፈፀመውን ወንጀል ከባድነት፣ የቀድሞ ታሪኩንና የጠባዩን ሁኔታ፣ በአንድ ሥፍራ ተወስኖ መቆየቱ ወይም የተደረገለት ሕክምና ያስገኘውን ውጤት፣ እንዲሁም ለወደፊቱ ጠባዩን ለማሻሻል የሚችል መሆኑን ወይም ሰላማዊ ሰው ለመሆን የሚያሳየውን አዝማሚያ በማመዛዘን ነው።

፫ ወንጀል አድራጊው ቀሪውን ቅጣት እንዲፈፀም ማድረጉ ጠቃሚ አለመሆኑን ፍርድ ቤት ሲያምንበት የቅጣቱን መፈፀም ያስቀርለታል።

BACK



## ክፍል ሁለት

## የመከላከልና የአጠባበቅ አጠቃላይ የጥንቃቄ እርምጃዎች

### አንቀጽ ፻፴፩ መርህ

በዚህ ምዕራፍ የተደነገጉት የመከላከልና የመጠበቅ አጠቃላይ የጥንቃቄ እርምጃዎች ለነገሩ አካባቢ ሁኔታ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆናቸውን ፍርድ ቤቱ ባመነበት ጊዜ ከዋናው ቅጣት ጋር በማጣመር ወይም ዋናው ቅጣት ከተፈፀመ በኋላ ተጨማሪ ሆነው እንዲፈፀሙ ሊወሰኑ ይቻላል::

እንዲህ ያሉት የመከላከልና የመጠበቅ የጥንቃቄ እርምጃዎች ለእያንዳንዱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግገው ባይገኙም በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው በተገኙ ጊዜ ሁሉ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ በግልጽ ማዘዝ አለበት::

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ንብረት ነክ የጥንቃቄ እርምጃዎች

### አንቀጽ ፻፴፪ የመልካም ጠባይ ዋስትና፣ መርህ

፩ የተፈረደበት ሰው እንደገና ወንጀል ለመስራት ማሰቡን ሲገልጽ ወይም አዲስ ወንጀል እንደሚሰራ በእርግጥ የሚያሰጋ ሆኖ ሲገኝ፣ በተለይም እንደገና ወንጀል ለመስራት የሚያስበው በግልጽ ጠላትነት ወይም በዛቻ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ይህ ወንጀለኛ በመልካም ጠባይ እንዲመራ ማረጋገጫ ቃል እንዲገባና በቂ የሆነ ዋስትና እንዲሰጥ ሊያስገድደው ይችላል::

፪ ይህም በመልካም ጠባይ እንዲመራ የገባው የማረጋገጫ ቃል ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ድረስ ይሆናል::

ዋስትናው የሚሰጠው እንደነገሩ ሁኔታ በራስ ወይም በሰው ዋስትና ወይም በመያዣ ነው::

፫ ፍርድ ቤቱ የማረጋገጫው ቃል የሚቆይበትን ጊዜና የመያዣውን ወይም የዋስትናውን መጠን የሚወስነው የዛቻውን ዓይነት፣ ከባድነትና የአደገኛነቱን እንዲሁም የአድራጊውንና የዋሶቹን የግል ኑሮ ደረጃና የሀብት ሁኔታ መሠረት በማድረግ ነው::
የተገባው የማረጋገጫ ቃልና የተሰጠው ዋስትና በፍርዱ ላይ ተገልጾ ይጻፋል::

<u>አንቀጽ ፻፴፮</u> <u>የማረጋገጫ ቃል ወይም ዋስትና መስጠትን እንቢ ማለት</u>

፩ ወንጀል ይሰራል ተብሎ አስጊ የሆነው ሰው እንዲሰጥ የተጠየቀውን የማረጋገጫ ግዴታ ለመስጠት ያልፈለገ እንደሆነ ወይም በመጥፎ ሃሳብና በክፉ ልቦና ላይ በመመስረት የራስ ወይም የሰው ዋስትና ያልሰጠ እንደሆነ ወይም ለተወሰነበት ጊዜ አስፈላጊውን የማረጋገጫ ዋስትና ያላስቀመጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተለመደው የፖሊስ ማረፊያ ቤት ተይዞ እንዲቆይ ሊያስገድደው ይችላል::

፪ ፍርድ ቤቱ ይህ ጥፋተኛ በማረፊያ ቤት የሚቆይበትን ጊዜ ወዲያውኑ ይወስናል:: ጥፋተኛው ዛቻውን በመደጋገም ካላደሰና እንደገና ጠባዩንም የማያሻሽል ካልሆነ ወይም መጥፎ ሃሳቡን ካልቀጠለና ይህንንም የመሳሰለ ልዩ አጋጣሚ ሁኔታ ካላደረሰ በቀር በማረፊያ ቤት ተይዞ የሚቆይበት ጊዜ ከሦስት ወር ሊበልጥ አይችልም::

ፍርድ ቤቱ ጥያቄ ሲቀርብለት በቂ በሆኑ ምክንያቶች የጊዜውን ውሳኔ ሊያራዝም ይቻላል:: በጥያቄውም መሠረት ወንጀለኛው ተፈትቶ ቁጥጥር እንዲደረግበት (አንቀጽ ፻፵፰) ወይም የመከላከልና የመጠበቅን ጉዳይ

ማጠንከር የሚያስፈልግ ሆኖ ሲታየው እጅግ ቢበዛ እስከ ሦስት ወር ድረስ የእሥራቱ ውሳኔ ታድሶ እንዲፈፀም ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል። ሆኖም በማረፊያ ቤት ተይዞ የሚቆይበት ጊዜ በድምሩ ከስድስት ወር ሊያልፍ አይችልም።

፫ በዚሁ መካከል ጥፋተኛው የተጠየቀውን ማረጋገጫ የሰጠ ወይም በቂ የሆነ ዋስትና ያቀረበ እንደሆነ ይለቀቃል።

## አንቀጽ ፻፴፯ የውሳኔው ውጤት

ለፈተና በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ጥፋተኛው ወንጀል ያላደረገ እንደሆነ የገባበት ማረጋገጫ ቃል ይቀርለታል። የራሱና የዋሶቹም ዋስትና ይወርድላቸዋል። ስለዋስትና ያስቀመጠው መያዣ ወይም ገንዘብ ይመለስለታል። ለፈተና በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ወንጀል ያደረገ እንደሆነ ግን የዋስትናው መያዣ ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል፤ ወይም ዋሱ ይገደዳል። ለፈፀመውም ወንጀል መደበኞቹ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ናቸው።

## አንቀጽ ፻፴፰ ዋስትና ወይም መያዣ ለመስጠት አለመቻል

ወንጀል ይፈጽማል ተብሎ አስጊ የሆነው ሰው ለመተማመኛ እንዲያሲዝ የሚጠየቀውን መያዣ ወይም ዋስትና በራሱ ባልሆነ ምክንያት ለማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ወንጀለኛው ከማረፊያ ቤት ተለቅቆ ወይም በማረፊያ ቤት መቆየቱ ቀርቶለት ቁጥጥር እንዲደረግበት (አንቀጽ ፻፵፰) ፍርድ ቤቱ ያዝዛል።

## አንቀጽ ፻፴፱ የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔን መደጋገም

፩ አንድ ሰው የመልካም ጠባይ ዋስትና እንዲሰጥ ከተደረገ በኋላ በአካባቢ ሁኔታዎች በተለይም እንደገና

በመዛቱ ወይም የአደገኛነት ዝንባሌ በማሳየቱ ምክንያት ተገቢ መስሎ ሲታይ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛውን እንደገና የማረጋገጫ ቃል እንዲገባና ዋስትና እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል (አንቀጽ ፻፴፭)።

፪ ቢሆንም ይህ የተባለው ሰው በአንቀጽ ፻፴፮(፪) ሁለተኛ ፓራግራፍ የተመለ ከተውን ከፍተኛ የሆነውን የስድስት ወር የማረፊያ ቤት እሥራት ጊዜ አስቀድሞ የፈፀመ ሲሆን ለወደፊቱ የማረጋገጫ ቃል እንዲገባ ወይም ዋስትና እንዲሰጥ ተጠይቆ በመጥፎ ሃሳብ እንቢ ያለ እንደሆነ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሳይደረግ ቁጥጥር እንዲደረግበት ፍርድ ቤቱ ማዘዝ አለበት (አንቀጽ ፻፴፰)።

የዛቻው አይነት በአንቀጽ ፭፻፹ ስር የሚመጣ ከሆነ አድራጊው በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ከመከሰስ አይድንም።

<u>አንቀጽ ፻፵ አደገኛ የሆኑ ነገሮችን መውረስ</u>

፩ ወንጀልን ለመፈፀም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም ለወንጀል ተግባር ያገለገሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች የሕዝብን ሰላማዊ ኑሮን፣ ሥርዓትን፣ ጤናን ወይም መልካም ጠባይን ሊጐዱ የሚችሉ ሲሆኑ ፍርድ ቤቱ እንዲወረሱ ያዝዛል።

የተወረሱት ነገሮች እንዲጠፉ፣ ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑ ወይም ፖሊስ ወይም ለወንጀል ምርመራ ክፍል እንዲሰጡ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል።

፪ ማንኛውም ነገሮች ወይም መሣሪያዎች አደገኛነት የሌላቸው ወይም በሕግ ያልተከለከሉ የንፁህ ሦስተኛ ወገኖች ንብረት ሲሆኑ የእነዚህ ሰዎች መብት የተጠበቀ ነው።

## አንቀጽ ፻፵፩ የወል ድንጋጌ፣ ለጥንቃቄ የሚደረግ ጠቅላላ አፈፃፀም

ማንም ሰው ከመከሰሱ በፊት ወይም ተከስሶ ጉዳዩ በፍርድ ቤት በሚታይበት ጊዜ በጋራ ወይም በግል ፀጥታ ላይ አደጋ ለማድረስ ዝቶ በተገኘ ጊዜ የመልካም ጠባይ ማረጋገጫ ዋስትና ግዴታ እንዲገባ ሊደረግ ይቻላል::

አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ማንም ሰው ሊከሰስ ወይም ሊፈረድበት ባይችልም እንኳ በእጁ የተገኘ አደገኛ ነገር ሁሉ እንዲወረስ በአንቀጽ ፻፵ በተመለከተው መሠረት ፍርድ ቤት ሊያዝዝ ይችላል::

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የሥራ እንቅስቃሴን በመገደብ የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎች

## አንቀጽ ፻፵፪ ፈቃድን ማገድና መልሶ መውሰድ

ልዩ ልዩ ሥራ ወይም ተግባር እንዲያከናውን በግልፅ በተሰጠው ፈቃድ የሚጠቀም ማንም ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በዚሁ ሥራው ከፍ ያለ አደጋ የሚያደርስ ወይም የተደጋገመ ከባድ ወንጀል የሰራ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ በዋነኛው ወንጀሉ ምክንያት ከሚወስንበት ቅጣት ጋር ተጨማሪ በማድረግ ይህ የተሰጠ ው ፈቃድ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ እንዲያዝበት ለመወሰን ይችላል::

ወንጀለኛው ብዙ ጊዜ የተደጋገመ ወይም በተለይ ከባድ የሆነ ወንጀል ሠርቶ እንደሆነ ፈቃዱ እስከ ጭራሹ እንዲወሰድበት ለማድረግ ይቻላል::

አንድ ሥራን ከማከናወን መብት የመሻር ቅጣትም እንደተጠበቀ ነው (አንቀጽ ፻፳፫(ሐ))::

BACK



## አንቀጽ ፻፵፫ ድርጅትን መከልከልና መዝጋት

አንድ የንግድ፣ የኢንዱስትሪ፣ የሃይማኖት ወይም የፖለቲካ ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጅት ወንጀል ለመፈፀም ወይም ለማራመድ ጥቅም ላይ ከዋለና ወንጀሉም በሕዝብ ፀጥታ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ በወንጀለኛው ላይ ከተወሰነው ቅጣት በተጨማሪ ይኸው ድርጅት ሥራ እንዲያቆምና እንዲዘጋ ፍርድ ቤቱ መወሰን ይችላል::

እንዲሁም የተፈፀመው ወንጀል ከአንድ ዓመት በበለጠ ፅኑ እሥራት የሚያስቀጣ ሲሆን ድርጅቱ እንዲፈርስ ንብረቱም እንዲጣራ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል::

## አንቀጽ ፻፵፬ ውሳኔውን አለማክበር የሚያስከትለው ውጤት

፩ የማገዱ፣ የመከልከሉ ወይም የመዝጋቱ ትዕዛዝ ጠቅላላና የመጨረሻ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥፍራ ወይም ለተለየ አንድ ክፍል ሆኖ በፍርዱ ውስጥ ሊወሰን ይችላል::

ውሳኔው በወንጀለኛው በራሱ ወይም በሌላ ሰው ስም ቢሆንም ወይም ድርጅቱን በሌላ ዓይነት አመራር በማካሄድ ዘዴም ቢሆን ወይም በማናቸውም አኳኋን የተከለከለውን ሥራ እንዳይቀጥል ያደርገዋል::

፪ የክልከላውን ውሳኔ መተላለፍ በሕጉ መሠረት ያስቀጣል (አንቀጽ ፬፻፶፱)::

የተከለከለውም ድርጅት ተመልሶ ተከፍቶ እንደሆነ እንደገና ይዘጋል፤ አዲሱ ድርጅት ይፈርሳል፤ ንብረቱም በሕጉ መሠረት ይጣራል::

BACK



## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የግል ነፃነትን በመገደብ የሚፈፀሙ የጥንቃቄ እርምጃዎች

### አንቀጽ ፻፵፩ ጥፋተኛው በአንዳንድ ሥፍራ እንዳይደርስ መከልከል

፩ ከዋናው ቅጣት በተጨማሪ አንድ ወንጀለኛ ለጥፋቱ መፈፀሚያ ምክንያት ከሆነው ወይም አዲስ ጥፋት ለመሥራት ከሚረዳው ከአንዳንድ ሥፍራ በተለይም ከመሸታ ቤት፣ ከሆቴል ቤት፣ ከመዝናኛ ሥፍራዎች፣ ከመገበያያ ወይም የሕዝብ መሰብሰቢያ ከሆኑ ከማናቸውም ሥፍራዎች እንዳይደርስ ፍርድ ቤቱ ሊወስንበት ይችላል::

፪ ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ፍርድ ላይ የተከለከለውን ሥፍራ ከልልና ክልከላው የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል:: ይህም የክልከላ ጊዜ ከሦስት ወር እስከ አንድ ዓመት ሊደርስ ይችላል::

### አንቀጽ ፻፵፪ በአንድ በተወሰነ ቦታ ከመኖር ወይም ውሎ ከማደር መከልከል

፩ በአንቀጽ ፻፵፩ ላይ እንደተገለፀው ለጥበቃው ፍፁም አስፈላጊ የሆነ ተመሳሳይ ምክንያት ሲገኝ ይህ የመከልከል ጉዳይ ወንጀለኛው በአንድ ከተማ፣ መንደር ወይም በአንድ በተወሰነ አካባቢ እንዳይኖር ወይም ውሎ እንዳያድር የማገድን ውሳኔ ሊያስከትል ይችላል::

፪ ይህም ውሳኔ ለተወሰነ ጊዜ ይሆናል:: ጊዜውም እንደወንጀሉ ከባድነት፣ እንደወንጀለኛው ጠባይና እንደነገሩ አካባቢ ሁኔታ ከአንድ ዓመት እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ ይችላል::

BACK

ፍርድ ቤቱ የከልከላውን ምክንያት መግለፅ አለበት፣ የተከለከለውን ቦታ ክልልና ክልከላውም የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል::

## አንቀጽ ፻፵፯ በአንድ ቦታ ወይም አካባቢ ተወስኖ የመኖር ግዴታ

፩ ወንጀለኛው ተጨማሪ ሁከት እንደሚፈጥር ወይም ወደፊት በወንጀለኛነት የሚቀጥል መስሎ ሲታይ ወንጀል የመፈፀም ዕድሉን በሚቀንስ አንድ የተወሰነ ቦታ ወይም ክልል ተወስኖ እንዲኖር ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል::

፪ ወንጀለኛው የሚኖርበትን ቦታ ወይም አካባቢ እንዲሁም በዚሁ አኳኋን ተወስኖ የመኖሩ ግዴታ የሚቆይበትን ጊዜ ፍርድ ቤቱ ይወስናል:: ጊዜውም ከአንድ ዓመት ሊያንስ ከአምስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም::

፫ በአንቀጽ ፻፴፩ የተደነገገው የመልካም ጠባይ ዋስትና በወንጀለኛው ላይ ከተወሰነበትና ለጉዳዩ በቂ የጥንቃቄ እርምጃ ከሆነ ይኸው የተወሰነበት የጥንቃቄ እርምጃ ብቻ እንዲፈፀምበት ፍርድ ቤቱ ያዝዛል::

## አንቀጽ ፻፵፰ ጥፋተኛው ላይ ቁጥጥር ማድረግ

፩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተለቀቀው እሥረኛ በፖሊስ ቁጥጥር እየተደረገበት እንዲጠበቅ ፍርድ ቤቱ ሊያዝዝ ይችላል::

በሕጉ ላይ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ፣ በተለይም በአንቀጽ ፻፴፰ በተመለከተው ጉዳይ ካልሆነ በቀር ጥፋተኛው መላልሶ በሰራቸው ወንጀሎች ወይም በሰራው ወንጀል ከባድነት በተለይም አደገኛ መሆኑ ካልተረጋገጠና በዚሁ ምክንያት ቢያንስ የአንድ ዓመት

ቀላል እሥራት የተፈረደበት ካልሆነ፣ በቀር ይህ ውሳኔ አይፈጸምበትም::

፪ የቁጥጥሩ ጊዜ ከአንድ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ ይችላል:: ፍርድ ቤቱ የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል::

ቁጥጥሩም፣ ተጠባቂው ወደሚፈልገው ማህበራዊ ኑሮ ለመመለስ በሚከተለው የሥራ አፈጻጸምና ሊከተለው በሚገባ ደንበኛ ኑሮ ላይ ችግር በማያደርስ አኳኋን መፈፀም አለበት::

ቁጥጥር የሚደረግበት ሰው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወይም በተጠራ ቁጥር ከአንድ ባለሥልጣን ዘንድ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ ሊያዝዝ ይችላል::

፫ የነገሩን ሁኔታና የጥፋተኛውን የጠባይ ሁኔታ በመገንዘብ በተቀጪው ላይ የሚደረገው ቁጥጥር በአንድ የጥበቃ ባልደረባ ብቻ ቢፈፀም የሚበቃ መሆኑ በታመነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ይህንን ብቻ ሊወስን ይችላል /አንቀጽ ፪፻፳/::

## <u>አንቀጽ ፻፵፱ ተፈቅደው የተሰጡትን ወረቀቶች ለጊዜው መልሶ መውሰድ</u>

ለቁጥጥርና ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ከዚህ በላይ የግል ነፃነትን ስለመቀነስ ለተደነገጉት ውሳኔዎች ተጨማሪ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ለተቀጪው ተፈቅደው የተሰጡ ወረቀቶች ወይም ጠ ስፖርቶች ለጊዜው እንዲያዙበት ለማዘዝ ይችላል::

የፍርዱም ውሳኔ ይህ ቅጣት የተበየነበትን ምክንያትና ቅጣቱም ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ገልጾ ማመልከት አለበት::

<u>አንቀጽ ፻፶ ወንጀለኛውን ከአገር ማስወጣት</u>

፩ ተቀጪው የውጭ አገር ዜጋ እንደሆነና በተለይም በአገር ውስጥ እንዲኖር የማያስፈልግ ወይም በተለይ አደገኛ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ለጊዜው ወይም እስከ ጭራሹ ከኢትዮጵያ ግዛት እንዲወጣ ሊያዝዝ ይችላል::

ይህ የጥንቃቄ እርምጃ ለሦስት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በእሥራት በተቀጣ ወይም በልዩ አዋቂ አስተያየት ለሕዝብ ደህንነት አደገኛ መሆኑ በተረጋገጠበት ወይም ኃላፊነት በሌለው ወይም ኃላፊነቱ በተቀነሰ ሰው ላይ ሊታዘዝ ይችላል::

ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በፍርዱ ላይ መግለፅ አለበት::

፪ ፍርድ ቤቱ ይህን ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት ጉዳዩ የሚመለከተውን የመንግሥት አካል ማማከር አለበት::

አግባብ ያላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተጠበቁ ናቸው::

፫ ማናቸውም ሌላ የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔ ከአገር የማስወጣትን ትዕዛዝ አያስቀርም::

<u>አንቀጽ ፻፶፩ አፈፃፀሙ</u>

፩ ከአገር የማስወጣቱ ውሳኔ የሚፈፀመው ጉዳዩ በሚመለከተው የመንግሥት ባለሥልጣን አማካይነትና በአስተዳደር ደንብ በተመለከተው መሠረት ነው::

፪ በወንጀለኛው ላይ ነፃነትን የሚያሳጣ ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ ከአገር የመውጣቱ ውሳኔ የሚፈፀምበት

BACK



የተወሰነበትን ቅጣት ከፈፀመ ወይም ቅጣቱ በይቅርታ ወይም በምህረት ከቀረለት በኋላ ነው።

፫ ይህ ውሳኔ የሚመለከተው ከፊል ኃላፊነት ያለውን ጥፋተኛ ሲሆንና የነገሩ ሁኔታዎች በቂ ምክንያት የሚያስገኙ ሲሆን አስቀድሞ ቅጣቱ ሊፈፀምበት ይችላል፤ ከዚያም ለጥንቃቄ በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ /አንቀጽ ፻፴/ ወይም እንዲታከም /አንቀጽ ፻፴፩/ የማድረጉ የጥንቃቄ እርምጃ ከአገር በማስወጣት ውሳኔ ሊተካ ይችላል።

አድራጊው ኃላፊነት የሌለው ሲሆን ለጥንቃቄ በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ ወይም እንዲታከም የማድረጉ የጥንቃቄ እርምጃ፣ የነገሩ ሁኔታ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ፣ ከአገር በማስወጣት ውሳኔ ሊተካ ይችላል።

## <u>አንቀጽ ፻፶፪ የጥንቃቄ እርምጃን ለሙከራ ለጊዜው ማገድ</u>

ወንጀለኛው የግል ነጻነት የማሳጣት ቅጣት ተወስኖበት እንደሆነና በአመክሮ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ተሰጥቶ እንደሆነ በአንዳንድ ሥፍራ ከመድረስ፣ ከመኖር ወይም ውሎ ከማደር የመከልከል፣ በአንድ ቦታ ወይም አካባቢ ተወስኖ የመኖር፣ ወይም ከአገር የማስወጣት ውሳኔ ለሙከራና ውሳኔውንም የመሻር መብት ሳይነካ በሕግ በተፈቀዱ ጠቅላላ ሁኔታዎችና ዋስትናዎች መሠረት ታግዶ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ሊያዝዝ ይችላል /አንቀጽ ፪፻፺/።

## <u>አንቀጽ ፻፶፫ የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔዎች ሲጣሱ የሚወሰን ቅጣት</u>

በአንዳንድ ቦታ እንዳይደርስ፣ በአንዳንድ በተወሰነ ቦታ እንዳይኖር ወይም ውሎ እንዳያድር፣ በአንድ በተወሰነ ቦታ ወይም አካባቢ በግዴታ እንዲኖር ወይም ቁጥጥር እንዲደረግበት የተወሰነውን የግዴታ ትዕዛዝ በመጣስ፣ እንዲሁም ከአገር እንዲወጣ ተወስኖበት ከወጣ በኋላ ወደ

ኢትዮጵያ ግዛት እንዳይገባ የተወሰነበትን የክልከላ ፍርድ በመጣስ የገባ ሰው በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፩፻፶፱ እና ፩፻፷፩ መሠረት ይቀጣል::

## ንዑስ ክፍል አራት

## የማሳወቅ እርምጃዎች

### አንቀጽ ፻፶፩ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ማሳወቅ

ባለፉት ክፍሎች በተደነገገው መሠረት ፍርድ ቤቱ አንድ ተጨማሪ ቅጣት ወይም ተቀዳሚ ጥንቃቄ ወይም የአጠ ባበቅን ጉዳይ የሚመለከት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ጉዳዩ የሚመለከተው ባለሥልጣን ውሳኔውን እንዲያውቀው፣ እንዲያስፈፅም፣ ወይም እንዲቆጣጠር አስፈላጊ ሲሆን የተሰጠው ፍርድ ተፈጻሚነት እንዲያገኝና መጠበቁን ለመቆጣጠር እንዲቻል ለሚመለከተው የአስተዳደር፣ የወታደራዊ፣ የፖሊስ ባለሥልጣን ወይም አግባብ ላለው ሌላ አካል ሳይዘገይ ያስታውቃል::

በእያንዳንዱ ጉዳይ ውሳኔው ፍሬ ማግኘቱን ለማረጋገጥ እንዲቻል ፍርድ ቤቱ ለሕዝብ የሚገለጽበትን ሁኔታ ያዝዛል::

### አንቀጽ ፻፶፪ ፍርድን ለሕዝብ መግለጽ

፩ ለሕዝብ፣ ለተከሳሹ ወይም ለተበዳዩ የሚጠቅም መሆኑ በታመነ ጊዜ ፍርዱ በሙሉ ወይም በከፊል ለሕዝብ እንዲገለጽ ፍርድ ቤቱ ያዝዛል::

የፍርዱ መገለጽ ለሕዝብ ጠቃሚ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች እንዲገለጽ ያዝዛል:: ጠ ቃሚነቱ ለግል ባለጉዳይ በሆነ ጊዜ ግን ባለጉዳዩ በጽሁፍ ካላመለከተ በቀር እንዲገለጽ አይደረግም::

፪ ፍርድ ቤቱ የተለመደውን የማስታወቂያ አወጣጥ ሥርዓት በመከተል እንደነገሩ ሁኔታና እንደአስፈላጊነቱ መጠን የፍርዱ ውሣኔ ለሕዝብ የሚገለጽበትን ዘዴና የመግለጫውንም ይዘትና ብዛት ይወስናል::

ማስታወቂያውንም ሕዝብ በሚሰበሰብበት አደባባይ በመለጠፍ፣ ወይም በሌላ በማናቸውም የመገናኛ ብዙኃን ዘዴ በማሰራጨት ለመፈፀም ይቻላል::

<u>አንቀጽ ፻፶፮ በፍርድ መመዝገቢያ ላይ መመዝገብ</u>

፩ በፍርድ የተሰጡ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ሕጉ በሚያዘው መሠረትና የወንጀለኞች ሪከርድን በሚመለከተው ደንብ መሠረት በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ይመዘገባል::

ፍርዱ ተመግዝቦ የሚቆይበትን ጊዜና የአመዘጋገቡን መጠን፣ ባለመብት ለሆነውም የሚገለጽበትን ልክ እንዲሁም የወንጀሉን መሰረዝ የወንጀለኛውን መሰየም ሁኔታና ውጤት የደንቡ ድንጋጌዎች ይወስናሉ::

፪ በአጠቃላይ የወንጀል ቅጣቶች በወንጀለኞች መዝገብ ላይ የሚመዘገቡት የተቀጪውን የቀድሞ ጥፋተኛነት አግባብ ያላቸው የፍርድ ባለሥልጣኖች እንዲያ ውቁት ነው:: ተቀጪው ተሰይሞ እንደገና ወደማህበራዊ ኑሮው ሊመለስ የሚችልበትን ቀና መንገድ እንዳያሰናክሉበት በማሰብ ለሦስተኛ ወገኖች ወይም ጉዳዩ ለማይመለከታቸው ሰዎች አይገለጽም::

## ምዕራፍ አራት

## ለአካለመጠን ባልደረሱ ሰዎች ላይ የሚፈፀሙ የጥንቃቄ እርምጃዎችና ቅጣቶች

## ክፍል አንድ

## በዘጠኝ እና በአሥራ አምስት ዓመት መካከል ያለው የዕድሜ ዘመን

### ንዑስ ክፍል አንድ

### መደበኛ የጥንቃቄ እርምጃዎች

**አንቀጽ ፻፷፪ መርህ**

ዕድሜው ከዘጠኝ እስከ አሥራ አምስት ዓመት የሆነ ወጣት በወንጀል ሕግ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱን ፈፅሞ በተገኘ ጊዜ /አንቀጽ ፶፪/ ፍርድ ቤቱ የሕጉን ጠ ቅላላ ድንጋጌዎች በመከተልና ከነገሩም ልዩ ግብ ለመድረስ /አንቀጽ ፶፫/ አስፈላጊም ሲሆን ነገሩን ለመረዳት ተገቢ የሆነው ምርመራ እንዲደረግ ካዘዘ በኋላ /አንቀጽ ፶፬/ ከዚህ በታች ከተመለከቱት የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱን ያዝዛል::

**አንቀጽ ፻፷፫ ሕክምና ወደሚደረግበት ተቋም መላክ**

ለአካለመጠን ያልደረሰው ወንጀል አድራጊ ሕክምና የሚያስፈልገው ሲሆን በተለይም የአእምሮ ደካማ፣ የአእምሮ ዕድገቱ የዘገየ፣ አእምሮው የታመመ፣ የሚጥል በሽታ ያለበት፣ በአልኮል መጠጥ ሱሰኝነት የተጠመደ ወይም በናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ ነገሮች ወይም በሌሎች በሚያፈዙ ዕፅዋት የተመረዘ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ተገቢ በሆነው የሕክምና ተቋም እንዲታከም ያዝዛል::

የሚቻል በሆነ ጊዜ ሕክምናው ትምህርትና ሥልጠናን ያካተተ መሆን ይኖርበታል::

## አንቀጽ ፻፶፱ ቁጥጥር በማድረግ የሚሰጥ ትምህርት

፩ ለአካለመጠን ያልደረሰው ወንጀል አድራጊ በበጐ አስተዳደግ ያላደገ ወይም በንዝህላልነት የተተወ ወይም ጠባዩ ወደ መጥፎ ሥራ ያዘነበለ ወይም የሚያዘነብል ሲሆን በጠባቂ ሥር ሆኖ ቁጥጥር እየተደረገበት ትምህርትና አስተዳደግ እንዲያገኝ ይታዘዝለታል።

ጠባቂ የሚሆኑ ዘመዶች ከሌሉት ወይም ቢኖሩትም ችሎታ የሌላቸው ሲሆን ብቁ ለሆነ ሰው ወይም ሕፃናትን ለመጠበቅና ለማስተማር ለተቋቋመ ድርጅት እንዲሰጥ ይታዘዛል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጠባቂዎች በአደራ የተሰጣቸውን ለአካለመጠን ያልደረሰውን ወጣት መልካም ጠባይ የሚከታተሉ ለመሆናቸው ፍርድ ቤት ቀርበው ኃላፊነታቸውን በጽሑፍ ያረጋግጣሉ።

ጠባቂዎቹ በአደራ የተሰጣቸውን ወጣት መልካም ሁኔታ ስለመከታተላቸው በአቅራቢያቸው የሚገኙ የጥበቃ ባልደረቦች /አንቀጽ ፻፷፫/ ይቆጣጠራሉ።

፪ ወደ ትምህርት ቤት አዘውትሮ እንዲሄድ፣ ወይም የሙያ ሥራን እንዲለምድ፣ ከአንዳንድ ሰዎች ከመገናኘት ወይም በአንዳንድ ሥፍራ ከመድረስ እንዲከለከል፣ በተወሰኑ ጊዜያት ከጥበቃ ባለሥልጣኖች ፊት እንዲቀርብ ወይም ሪፖርት እንዲያቀርብ፣ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ግዴታዎች ሊታዘዙበት ይቻላል።

እንደነገሩ አኳኋንና ግብ ለአካለመጠን ባልደረሰው ወንጀል አድራጊ ወይም ለጠባዩ ጠባቂ በሆኑት ሰዎች ላይ እነዚህ ገደቦች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ሊታዘዝ ይችላል።

BACK



፫ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ወይም የጥበቃ ባልደረባው ስለወጣቱ ጠባይ ጠባቂ የሆኑትን ሰዎች ወይም ድርጅቶች ሊያስገነዝባቸውና ሊወቅሳቸው ይችላል::

ጠባቂዎቹ በማናቸውም ምክንያት የማሳደግና የማስተማር ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ካልቻሉ ፍርድ ቤቱ የጠባቂነት ሥልጣናቸውን ሊወስድባቸው ይችላል::

<u>አንቀጽ ፻፷ ተግሳፅና ወቀሳ</u>

፩ ተገቢና መልካም ውጤት የሚሰጥ መስሎ በታየው ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለአካለመጠን ያልደረሰውን ወንጀል አድራጊ ይገስፀዋል ወይም ይወቅሰዋል::

ወቀሳው ለአካለመጠን ያልደረሰው ወንጀል አድራጊ የድርጊቱን ውጤት እንዲረዳውና ለወደፊቱም የበጐ ተግባር ስሜትና መልካም ጠባይ እንዲኖረው የሚያደርግ ሊሆን ይገባል::

፪ ለአካለመጠን ያልደረሰውን ወንጀል አድራጊ የመረዳት ችሎታ እና የፈፀመውን ወንጀል ቀላልነት ወይም የአፈፃፀሙን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ፍርድ ቤቱ ወጣቱን ለማረም በቂ ነው ብሎ ሲያምንበት በወቀሳ ወይም በተግሳፅ ብቻ ሊያልፈው ይችላል::

ጠቃሚ በሚሆንበት ጊዜ ከማናቸውም ሌላ የጥንቃቄ እርምጃ ወይም ቅጣት ጋር ወቀሳው ሊጣመር ይችላል::

<u>አንቀጽ ፻፷፩ በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ እንዲቆይ ማድረግ</u>

ጥፋቱ ከባድ ባልሆነ ጊዜና ለአካለመጠን ያልደረሰውም ወንጀል አድራጊ በቀላሉ የሚታረም መስሎ ሲታይ ወጣቱ በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤቱ ተወስኖ ሳይወጣ በዕረፍት ሰዓቱ ወይም በዕረፍት ቀኖቹ ለዕድሜው

BACK



በሚስማማና በተወሰነ ሥፍራ እንዲሰራ ፍርድ ቤቱ ያዝዛል::

እንደነገሩ አኳኋንና እንደጥፋቱ ከባድነት ለአካለመጠን ያልደረሰው ወንጀል አድራጊ በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ የሚቆይበትን ጊዜ ፍርድ ቤቱ ይወስናል::

ወንጀል አድራጊው በጠባቂው ሥር ሆኖ ውሳኔው በትክክል መፈፀሙን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ፍርድ ቤቱ ያዝዛል::

## አንቀጽ ፻፷፪ ወደ ጠባይ ማረሚያ ተቋም መላክ

ፍርድ ቤቱ የወጣት ወንጀል አድራጊውን ፀባይ ወይም የቀድሞ ታሪኩን መጥፎነት እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና አፈፃፀሙን ግምት ውስጥ በማስገባት ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ማረሚያና ማስተማሪያ ወደ ተቋቋመ ልዩ ተቋም እንዲገባ ሊያዝዝ ይችላል::

በዚህም ወጣቱ ተገቢ በሆነ ሥነ ሥርዓት እየተጠበቀ ጠቅላላ ትምህርትን፣ ግብረ-ገብነትን /ሞራልን/ እና የመተዳደሪያ ልዩ ልዩ ሙያ የሚያገኝበትን ትምህርት /የሥራ መልመጃ/፣ እንዲሁም ወደማህበራዊ ኑሮ እንዲመለስና በቅንነት እየሰራ እንዲኖር አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ እንዲማር ይደረጋል::

## አንቀጽ ፻፷፫ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚቆዩበት ጊዜ

፩ በመሠረቱ የሕክምናና /አንቀጽ ፻፶፰/ እየተጠበቁ የመማር የጥንቃቄ እርምጃዎች /አንቀጽ ፻፶፱/ ፀንተው የሚቆዩት የሕክምናው ባለሥልጣን ወይም የጥበቃው ባልደረባ ያስፈልጋል በማለት ወስኖ ባቀረበው ጊዜ ልክ ሲሆን ወንጀል አድራጊው ለአካለመጠን እስከሚደርስበት ጊዜም ሊቀጥሉ ይችላሉ::

BACK



የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ዓላማቸውን ከግብ ያደረሱ መሆናቸውን በመግለፅ ኃላፊነት የተሰጣቸው ባለሥልጣኖች የሚያቀርቡትን አስተያየት ፍርድ ቤቱ ሲያምንበት የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ቀሪ እንዲሆኑ ይወሰናል።

፪ ወደ ጠባይ ማረሚያ ተቋም የመላክ ውሳኔ /አንቀጽ ፻፷፪/ የሚታዘዘው በመሠረቱ ቢያንስ አንድ ዓመት ቢበዛ አምስት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ነው። በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ወጣቱ በሕግ ከተወሰነለት ለአካለመጠን ከሚደርስበት ዘመን በላይ አያልፍም።

የዚህ ዓይነት ውሳኔ በተሰጠ ቁጥር ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ በፍርድ ላይ መገለፅ አለበት።

ወጣቱ ከዚህ በላይ የተመለከተውን የአንድ ዓመት ጊዜ ከፈፀመ በኋላ በሕጉ ላይ በተመለከቱት ጠቅላላ ግዴታዎች መሠረት /አንቀጽ ፪፻፩/ በፍርድ የተወሰነበት የሙከራ ጊዜ እስኪያልቅ ድረስ ሊከተላቸውና ሊፈጽማቸው የሚገባውን የመልካም ጠባይ አመራር ደንቦች እንዲጠብቅና በጥበቃ ባልደረባ ጥገኛነት ውስጥ እንዲቆይ ተደርጐ /አንቀጽ ፪፻፫/ የተወሰነበትን ጊዜ በሙሉ ከመፈጸሙ በፊት ለፈተና በአመክሮ ሊለቀቅ ይቻላል።

<u>አንቀጽ ፻፷፬ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መለወጥ</u>

ፍርድ ቤቱ ለወጣት ወንጀል አድራጊው ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኘው የተቋሙ አስተዳደር በሚያቀርበው አስተያየት መነሻ ከላይ በተጠቀሱት አንቀጾች መሠረት የተሰጠውን ትዕዛዝ መለወጥ ይችላል።

<u>አንቀጽ ፻፷፭ የጥንቃቄ እርምጃዎች ሕጋዊ ውጤት</u>

ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የሕክምና፣ የትምህርት ወይም የማረም የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱ የተወሰነበት ወጣት ወንጀል አድራጊ በወንጀል እንደተቀጣ አይቆጠርም።

BACK



## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ቅጣቶች

### አንቀጽ ፻፷፯ መርህ

ከአንቀጽ ፻፶፫ - ፻፷፪ የተደነገጉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ፍሬ ሳያስገኙ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ለአካለመጠን ያልደረሰው ወንጀል አድራጊ የፈፀመውን ጥፋት በማመዛዘን አስፈላጊ ከሆነም የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ምርመራዎች እንዲደረጉ ካዘዘ በኋላ /አንቀጽ ፶፬/ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ቅጣቶች አንዱን ሊወስንበት ይችላል።

### አንቀጽ ፻፷፰ መቀጮ

፩ ለአካለመጠን ያልደረሰው ወንጀል አድራጊ መቀጮ መክፈሉ ቅጣት ሆኖ የሚሰማው፣ የሚያስተምረውና ከጥፋቱ የሚመልሰው መስሎ ሲታየውና ራሱ መቀጮውን ለመክፈል የሚችል መሆኑን ሲረዳው ፍርድ ቤቱ እንደጥፋቱ ከባድነትና እንደገንዘብ አቅሙ መቀጮ እንዲከፍል ሊፈርድበት ይችላል።

መቀጮውም ከሌላ ቅጣት በተጨማሪ ሊወሰን ይችላል።

፪ መቀጮን ስለመክፈልና መቀጮውን በሌላ ዓይነት ቅጣት ስለመለወጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፺፬ እና ፺፭/ ለአካለመጠን ባልደረሱ ጥፋተኞች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

ለአካለመጠን ያልደረሰው ወንጀል አድራጊው አስቦ መቀጮውን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ያልከፈለ እንደሆነ በመቀጮው ምትክ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው የጊዜ ልክ በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ እንዲቆይ ለማድረግ ይቻላል /አንቀጽ ፻፷፩/።

BACK



## አንቀጽ ፻፷፰ እሥራት

፩ ለአካለመጠን ያልደረሰ ወንጀል አድራጊ እንደደንቡ አሥር ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የፅኑ እሥራት ቅጣት ወይም የሞት ቅጣት የሚያስከትል ከባድ ወንጀል ያደረገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ:-

ሀ/ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የደህንነት ማረጋገጫ፣ ከሰው ተለይቶ የመኖር ወይም ልዩ የሆነ የሥነሥርዓት ጥበቃ ማስፈፀሚያ የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲፈፀሙበት ወደ ጠባይ ማረሚያ ተቋም እንዲላክ ያዝዛል /አንቀጽ ፻፷፪/፤ ወይም

ለ/ ጥፋተኛው አደገኛና ሰላምን የሚያውክ ወይም ፀጥታን የሚያደፈርስና ለሌሎችም መጥፎ ምሳሌ መሆኑን በተረዳው ጊዜ እንደዚህ ስላለው ጉዳይ ከሰው ለይቶ የማኖርን መሠረታዊ ደንብ በመያዝ በቀጥታ የቅጣት መፈጸሚያ ወደሆነ እሥር ቤት እንዲላክ ያዝዛል /አንቀጽ ፻፲(፪)/::

፪ ወጣቱ የፈፀመውን ወንጀል ከባድነትና ጥፋቱንም በፈፀመበት ጊዜ የነበረውን የዕድሜ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ታስሮ የሚቆይበትን የጊዜ ልክ ፍርድ ቤቱ ይወስናል:: ጊዜውም ከአንድ ዓመት ሳያንስ እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ ይችላል::

ወጣቱ ወደጠባይ ማረሚያ ተቋም ከተላከ በኋላ በጠባዩ ሁኔታ ወይም ሊያደርስ በሚችለው አደጋ ምክንያት ወደ እሥር ቤት መላኩ የሚያስፈልግ መሆኑ የታመነ እንደሆነ ወይም ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት የሞላው ሆኖ ሲገኝና የተወሰነበት ቅጣትም ከዚህ ለአካለመጠን ከመድረሻው ጊዜ በመብለጥ የሚያሳስር እንደሆነ ወደ እሥር ቤት ይላካል::

እንዲህም በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ወጣቱ ታስሮ የሚቆይበትን ጊዜ ለመወሰን፣ ጥፋተኛው በጠባይ ማረሚያ ተቋም የቆየበትን ጊዜና ቆይታውም ያስከተለውን የማሻሻል ውጤት ከግምት ያስገባል።

፫ በእሥር ቤት ተይዞ የመቆየቱ ቅጣት የሚፈጸመው በቀላል እሥራት /አንቀጽ ፻፮/ አፈጻጸም ደንብ ዓይነት ነው። እንዲሁም የወጣቱ ጠባይ የተሻሻለ መሆኑ በተገመተ ጊዜ በተለመደውና በሕጉ ላይ በተደነገገው መሠረት ለአመክሮ አስቀድሞ የመፈታት ደንብ ተፈጻሚ ይሆናል /አንቀጽ ፻፲፫/።

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የወል ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፻፷፱ ቀላል ሁኔታዎች፣ በበቂ ምክንያት ቅጣትን ማስቀረት

ወንጀሉ ቀላል ሆኖ ከተፈፀመ ቢያንስ ስድስት ወር ካለፈ በኋላ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ መስሎ ያልታየው እንደሆነ የጥንቃቄ እርምጃ ወይም ቅጣት አይወስንበትም።

እንዲሁም የማስተማርና የጠባይ ማረም የጥንቃቄ እርምጃዎች ወይም ቅጣት በወላጅ ወይም በቤተዘመድ አስቀድሞ የተፈፀመበት ሲሆን ወይም አካለመጠን ያላደረሰው ወጣት መልካም ጠባይን የያዘና የታረመ መስሎ ሲታይና ወንጀልን የመደጋገም ዝንባሌ የማያሳይ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ የጥንቃቄ እርምጃውን ወይም ቅጣቱን አይወስንበትም።

### አንቀጽ ፻፸ ልዩ የይርጋ ደንብ

፩ ወንጀሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ስለወንጀል ክስ አቀራረብ የተወሰነው መደበኛ ወይም ልዩ የይርጋ ዘመን አጋማሽ ካለፈ /አንቀጽ ፪፻፲፯፣ ፪፻፲፰/ የነገሩ

አካባቢ ሁኔታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑ የታመነበት እንደሆነ በአንቀጽ ፻፷፰ ላይ ለተመለከቱት ከባድ ወንጀሎች ካልሆኑ በቀር ፍርድ ቤቱ ማናቸውንም የጥንቃቄ አፈፃፀም ተግባርና ማናቸውንም ቅጣት ቀሪ ያደርጋል::

፪ በአንቀጽ ፻፷፰ የተገለፁትን ከባድ ወንጀሎች በሚመለከት ስለክስ አቀራረብና ስለቅጣት የተደነገገው ጠቅላላ የይርጋ ዘመን ተፈፃሚ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፻፸፩ ውሳኔውን በገደብ ማገድ</u>

በአንቀጽ ፻፷፰ ላይ ስለከባድ ወንጀሎች የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው መልካም ውጤት የሚያስገኙ ሁኔታዎች ተፈጽመው ሲገኙ በጥበቃ ባልደረባ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ በፈተና ቆይቶ የቅጣቱን ፍርድ መስጠት ወይም መፈፀም ለማገድ የተደነገጉት /አንቀጽ ፻፺-፪፻/ በመሠረቱ አካለመጠን ባላደረሱ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ሁልጊዜ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

የፈተናው ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፻፸፪ የጥንቃቄ እርምጃው እና ቅጣቱ በሕዝባዊ መብት ላይ የሚያስከትለው ውጤት</u>

ወንጀል አድራጊው የፈፀመው ወንጀል ከባድነት በአንቀጽ ፻፷፰ ሥር በሚመጣበት ጊዜ ከሕዝባዊ መብት መሻር ፍፁም አስፈላጊ መሆኑን በተለየ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ካልተገነዘበ በስተቀር ለአካለመጠን ባልደረሰ ጥፋተኛ ላይ የተወሰነው ማናቸውም የጥንቃቄ እርምጃና ቅጣት

በወጣቱ ላይ የሕዝባዊ መብት የማጣት ውጤት ሊያስከትል አይችልም::

## <u>አንቀጽ ፻፸፫ ጠቅላላ የሆኑ የመከላከልና የመጠበቅ እርምጃዎች</u>

ለመንግሥት ገቢ መሆን ስለሚገባው ሀብት /አንቀጽ ፻/ እና አደገኛ ነገሮችን ስለመውረስ /አንቀጽ ፻፵/ እንዲሁም አንዳንድ ሥፍራዎችን ከማዘውተር ስለመከልከል /አንቀጽ ፻፵፫/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለአካለመጠን ባልደረሱ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ተፈጻሚዎች ይሆናሉ::

እንዲሁም ጠባዩን ለማሻሻል የማይቻልና ለሕብረተሰቡ አደገኛ መስሎ የሚታየው ለአካለመጠን ያልደረሰ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ወንጀል አድራጊ የተወሰነበትን የጠባይ ማረም ወይም በእሥራት የመቆየትን ቅጣት ከፈፀመ በኋላ ከአገር እንዲወጣ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል /አንቀጽ ፻፶/::

ለአካለመጠን ባልደረሱ ወንጀል አድራጊዎች ላይ የተወሰነውን ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ የማስፈጸም ጉዳይ ለሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የሞግዚትነት ሥልጣን ለተሰጣቸው ሰዎች ወይም ተቋሞች /አንቀጽ ፻፶፬/ መገለጽ አለበት::

## <u>አንቀጽ ፻፸፬ የፍርድ ውሳኔን መግለፅና በፍርድ መዝገብ ላይ መመዝገብ</u>

ለአካለመጠን ያልደረሰውን ወንጀል አድራጊ የሚመለከት የፍርድ ውሳኔ ምንጊዜም በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አይገለጽም /አንቀጽ ፻፶፫/::

የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ የሚመዘገበው /አንቀጽ ፻፸፭/ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ለመንግሥት የአስተዳደርና የፍርድ ባለሥልጣኖች አስፈላጊውን መረጃ ለመስጠት እንዲያገለግል ብቻ ስለሆነ በማናቸውም ምክንያት የዚህን የመዝገብ ቅጂ ለነገሩ ባዕድ ለሆኑ ሌሎች ሰዎች መግለጽ በፍጹም የተከለከለ ነው::

## አንቀጽ ፻፸፮ ፍርድን መሰረዝና መሰየም

ለአካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወይም በእርሱ ላይ በሕግ መሠረት ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ሲጠይቁ ከእሥራት ቅጣቱ በስተቀር ለአካለመጠን ባልደረሰው ወንጀል አድራጊ ላይ የተወሰኑት የጥንቃቄ እርምጃዎችና ሌሎች ቅጣቶች በተፈፀሙ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለመሰየም የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች የተሟሉ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ውሳኔዎቹ ከወንጀለኞች መዝገብ ላይ እንዲሰረዙ ያዝዛል /አንቀጽ ፪፻፴፪ - ፪፻፴፯/::

## ክፍል ሁለት

## ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ፣ ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች ያለ ወጣት ወንጀል አድራጊ

## አንቀጽ ፻፸፯ መደበኛ ሁኔታ

ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ፣ ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ወጣት ወንጀል አድራጊ ወንጀል በሰራ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በመደበኛው የሕግ ድንጋጌ /አንቀጽ ፶፮/ መሠረት ሲወስን የነገሩ አካባቢ ሁኔታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑን የገመተ እንደሆነ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት /አንቀጽ ፸፱/ ቅጣትን ሊያቃልልለት ይችላል::

አድራጊው አስራ ስምንት ዓመት ሳይሞላው በፈፀመው በማናቸውም አይነት ወንጀል ምክንያት የሞት ቅጣት ሊወሰንበት አይችልም/አንቀጽ ፻፲፮/::

BACK



ነፃነትን የማሳጣት ቅጣት በሚፈፀምበት ጊዜ ለአካለመጠን ከደረሱ ወንጀለኞች ተለይቶ የመታሰር ደንብ ለአካለመጠን እስከሚደርስ ድረስ በጥብቅ መፈፀም አለበት /አንቀጽ ፻፲(፪)/::

አንቀጽ ፻፷፯ ልዩ ሁኔታ

፩ ጥፋተኛው በአካሉ ወይም በአእምሮው መጐልመስ ገና ከአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ በታች እንዳለ ወጣት ሆኖ ሲገመት ወይም የፈፀመው ወንጀል ከባድ ባልሆነበት ጊዜና ልዩ አዋቂው እንዳቀረበው ሃሳብ ዕድሜአቸው ከዘጠኝ እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለሆኑት ወጣት ጥፋተኞች በዚህ ምዕራፍ በክፍል አንድ የተወሰኑት የሕክምና፣ የትምህርት ወይም የጠባይ ማረም እርምጃዎች ሊፈጸሙበት ተገቢ ሆኖ ሲገኝ፣ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በተደነገገው መሠረት ቅጣቱን በማቃለል ፈንታ ከእነዚህ የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱ እንዲፈፀምበት በተለይም ወደ ሕክምና ወይም ወደ ጠባይ ማረሚያ ተቋም እንዲላክ ግልጽና ተገቢ በሆነ ምክንያት ለማዘዝ ይቻላል::

፪ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የማሳከሙ፣ በትምህርት የማሰልጠኑ ወይም በጠባይ ማረሚያ ቦታ የማቆየቱ ጊዜ ሕጋዊ ከሆነው ለአካለመጠን ከመድረሻ ጊዜ ለማለፍ አይችልም /አንቀጽ ፻፷፫/::
ይህ ጊዜ ከማለፉ በፊት ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ መስሎ የታየው እንደሆነና ይልቁንም ወጣቱ ከጠባይ ማረሚያው ሲለቀቅ በእሥር ቤት እንዲቆይ /አንቀጽ ፻፷፰(፪)/ ማዘዝ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ፣ በጠባይ ማረሚያው ተቋም ከቆየበት ጊዜ ውስጥ ምን ያህሉ ለሚወሰንበት የእሥራት ቅጣት መቆጠር እንዳለበት ለመወሰን አስቀድሞ በወጣቱ ላይ አስተላልፎት የነበረውን የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔ ሊመረምረው ይችላል::

## ርዕስ ሁለት

## ቅጣትን መወሰንና ማገድ፣ ክስንና ቅጣትን ማቋረጥና ማስቀረት

### ምዕራፍ አንድ

### ቅጣትን መወሰንና ማገድ

### ክፍል አንድ

### ቅጣትን መወሰን

#### አንቀጽ ፻፸፰ ቅጣትን የማቅለል ወይም የማክበድ አወሳሰን

ስለቅጣት አወሳሰን የተደነገጉት ጠቅላላ መርሆች /አንቀጽ ፹፰/ እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ ቅጣቱን ለማቅለል ወይም ለማክበድ ሕጉ በፈቀደ ወይም ግዴታ ባደረገ ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመከተል ይወስናል።

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ቅጣትን የማቅለልና ከቅጣት ነፃ የማድረግ ደንብ

#### አንቀጽ ፻፸፱ መደበኛ የቅጣት ማቅለያ ደንብ

ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቅጣትን ለማቅለል እንደሚችል በሕግ በተደነገገ ጊዜ ሁሉ ቅጣትን ማቅለል የሚገባ ሆኖ ሲያገኘው፣

ሀ/ በሞት ቅጣት ምትክ፣ ከሃያ ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ የሚደርስ ጽኑ እሥራት፤

ለ/ በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ምትክ፣ ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የጽኑ እሥራት ቅጣት፤

ሐ/ የፅኑ እሥራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ በዚህ ቅጣት ምትክ በሕጉ ጠ

ጠቅላላ ክፍል መነሻ ሆኖ ከተደነገገው ከአንድ ዓመት ጀምሮ የፅኑ እስራት ቅጣት፤

መ/ መነሻው አንድ ዓመት በሆነ ፅኑ እስራት ምትክ፣ ከስድስት ወር እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ የቀላል እስራት ቅጣት፤

ሠ/ የቀላል እስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጐ ሲገኝ በዚህ ቅጣት ምትክ፣ ከአስር ቀን የማያንስ የቀላል እስራት ቅጣት፤

ረ/ ከአስር ቀን በማያንስ የቀላል እስራት ቅጣት ምትክ የግዳጅ ሥራ ወይም መቀጮ፣

ይወሰናል።

## <u>አንቀጽ ፻፹ በመሰለው ቅጣትን ማቅለል</u>

ፍርድ ቤቱ በመሰለው ቅጣትን ማቅለል አለበት ወይም ይችላል ተብሎ በሕግ ተደንግጐ በሚገኝበት ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ቅጣትን ለመወሰን ሥልጣን አለው።

ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቅጣትን ማቅለል አለበት ወይም ይችላል ተብሎ በሕግ በተደነገገ ጊዜ የዚህ ሕግ ልዩ ክፍል በሚደነግገው የቅጣት ዓይነት ወይም መነሻ ቅጣት ሳይወሰን መነሻ ከሆነው ቅጣት ዝቅ አድርጐ ወይም ቀለል ያለ ሌላ ዓይነት ቅጣት ተክቶ ለመወሰን ሥልጣን አለው። ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የሚወስነው ማናቸውም ዓይነት ቅጣት በዚህ ሕግ ጠቅላላ ክፍል ለየቅጣቱ ዓይነት ከተደነገገው መነሻ ዝቅ ሊል አይችልም /አንቀጽ ፺፣ ፻፯ እና ፻፹/።

## <u>አንቀጽ ፻፹፩ የወል ድንጋጌዎች</u>

ሕጉ በሚፈቅድበት መጠን ፍርድ ቤቱ ቅጣትን በማቅለል በሚወስንበት ጊዜ ስለጥፋተኛነት በጠቅላላው የተመለከተውን መርህ መሠረት በማድረግ የቅጣቱን ልክ ይወስናል /አንቀጽ ፹፯/።

ፍርድ ቤቱ ቅጣትን /በአንቀጽ ፻፸፱ ወይም በአንቀጽ ፻፹/ በሚያቃልልበት ጊዜ ሁሉ ካሣ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል /አንቀጽ ፻፩/:: አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተጨማሪ ቅጣቶችን /አንቀጽ ፻፳፩-፻፳፫/ እና ስለመከላከልና ስለመጠበቅ የተደነገጉትን አጠቃላይ የጥንቃቄ እርምጃዎች /አንቀጽ ፻፴፬-፻፵፫/ አጣምሮ መወሰን ይችላል::

<u>አንቀጽ ፻፹፪ ከቅጣት ነፃ ማድረግና ቅጣትን መተው</u>

ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛውን ከማናቸውም ቅጣት ነፃ ማድረግና በሙሉ ወይም በከፊል ቅጣትን መተው የሚችለው በሕጉ ላይ በግልፅ ተደንግጐ ሲገኝ ብቻ ነው::

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

<u>የቅጣት ማክበጃ ደንብ</u>

<u>አንቀጽ ፻፹፫ መደበኛ የቅጣት ማክበጃ ደንብ</u>

ቅጣቱ እንዲከብድ ሕጉ በደነገገ ጊዜ (አንቀጽ ፹፬) ለቅጣቱ ማክበጃ የሆኑትን ምክንያቶች ዓይነትና ብዛት እንዲሁም ወንጀለኛው የፈጸመውን ጥፋት ከባድነት በማመዛዘን ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል በተመለከተው አግባብነት ባለው ድንጋጌ ከተወሰነው ቅጣት ጣራ ሳያልፍ ቅጣቱን ይወስናል::

<u>አንቀጽ፻፹፬ ግዙፍ ወንጀሎች በተደራረቡ ጊዜ ቅጣትን ማክበድ</u>

፩ ግዙፍ የሆነ የወንጀል መደራረብ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ (አንቀጽ ፹፭) ፍርድ ቤቱ የወንጀለኛውን ጥፋት ከባድነት በማመዛዘን ከዚህ በሚከተሉት ደንቦች መሠረት ቅጣቱን አክብዶ ይወስናል፤

ሀ/ ነፃነትን ወይም ሕይወትን በማሳጣት ከሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በአንደኛው ምክንያት

BACK



የሞት ወይም የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት /አንቀጽ ፻፮ እና ፻፰/ ሲወሰን በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) እና (ሠ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ውሳኔ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ቅጣት ሁለ አጠቃሎ /ደርቦ/ ይይዛል::

ቢሆንም በከባዱ ወንጀል ምክንያት ከላይ ከተመለከቱት ቅጣቶች አንዱ መወሰኑ ቀርቶ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ዝቅ ተደርጐ የእስራት ቅጣት የተወሰነ እንደሆነ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት ፍርድ ቤቱ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) መሠረት ቅጣቱን ያሳድጋል::

ለ/ ከሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡና ነፃነትን የሚያሳጡ ቅጣቶችን የሚያስከትሉ ተደራራቢ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም ይደመራል:: ቢሆንም ለቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት መብለጥ አይችልም::

በፅኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የሁለት ዓመት ቀላል እስራት ቅጣት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት ይቆጠራል::

ሐ/ በእስራትና በመቀጮ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው ባጋጠሙ ጊዜ ሁለቱም ቅጣቶች ተጣምረው ይወሰናሉ:: አወሳሰኑም፣ እስራትን

BACK



በሚመለከት የዚህ ንዑስ አንቀጽ የፊደል (፩)(ለ) ድንጋጌን፣ መቀጮን ብሚመለከት ደግሞ የዚህ ንዑስ አንቀጽ የፊደል (፩)(መ) ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ነው።

መ/ ከሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ የገንዘብ ቅጣትን የሚያስከትሉ ተደራራቢ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ በተደራራቢ ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም ይደመራል። ወንጀለኛው በአፍቅሮ ንዋይ ስሜት ተነሳስቶ የፈጸመው ካልሆነ /አንቀጽ ፺፪/ በቀር የመቀጮውን ቅጣት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተመለከተው ከፍተኛው የገንዘብ ቅጣት ወሰን ለማሳለፍ አይቻልም።

ሠ/ ፍርድ ቤቱ ከተደራራቢዎቹ ወንጀሎች በአንዱ ምክንያት የተቀጪው ንብረት እንዲወረስ ወስኖ እንደሆነ፣ በሌላው ወንጀል ምክንያት መቀጮ በተጨማሪ ሊወስን አይችልም።

፪ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፷(ሐ) በተደነገገው መሠረት የወንጀሎች መደራረብ ባጋጠመ ጊዜ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር፣ ቅጣቱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይወሰናል።

፫ ማናቸውም ተጨማሪ ቅጣት ወይም የመከላከልና የመጠበቅ ወይም የጠባይ ማረም ወይም የደህንነት ጥንቃቄ እርምጃ አግባብ ባለው በአንድ ድንጋጌ ላይ ወይም ተደራርበው ከተፈጸሙት ወንጀሎች ውስጥ ለአንዱ ወንጀል ብቻ ተወስኖ ቢገኝም እንኳ ከጠ ቅላላው ቅጣት ጋር ተፈጻሚ ማድረግ ይቻላል።

<u>አንቀጽ ፻፹፮ ልዩ ሁኔታ</u>

፩ የተዛመዱ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ ከነርሱ አንዱ የተደረገው ሌላው ወንጀል እንዲፈጸም ለማድረግ፣ ወይም ለማመቻቸት ወይም ለሌላው ከለላ እንዲሆን

BACK



ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን እስከ ከፍተኛ መደብ ድረስ አክብዶ መወሰን አለበት::

፪ የተዛመዱ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች እንደከባድ ግድያ ወይም ከባድ ውንብድና የመሳሰሉ ቅጣት የሚያከብድ አንድ ልዩ ወንጀልን የሚያቋቁሙ መሆናቸው በሕጉ ልዩ ክፍል በተደነገገ ጊዜ ስለእነዚሁ ወንጀሎች የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ::

<u>አንቀጽ ፻፹፯ ባለፈ ጊዜ የተፈፀመ ተደራራቢ ወንጀል ከፍርድ በኋላ መታወቁ</u>

፩ ጥፋተኛው በወንጀል ተፈርዶበት ቅጣቱን በመፈፀም ላይ ሳለ ወይም ከፈፀመ በኋላ፣ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት የፈፀመው ሌላ ተደራራቢ ወንጀል መኖሩ ሲደረስበት ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ ይወስናል::

፪ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የተወሰነውን ቅጣት ከግምት በማስገባት ከዚህ በላይ በተመለከቱት አንቀጾች መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል::

፫ በአንድ ላይ ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ የጠቅላላ ቅጣቱ አወሳሰን ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፻፹፰ በአንድ ድርጊት ግምራ ወንጀሎች ሲፈፀሙ ቅጣት የሚከብድበት ሁኔታ</u>

፩ ወንጀለኛው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የሕግ ድንጋጌዎችን ጥሶ የተገኘ እንደሆነ (አንቀጽ ፷፫) ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን አካባቢ ሁኔታዎች

BACK



ሲመረምር በተለይም ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ሕግ መጣሱን ወይም ግልፅ የሆነ መጥፎ ጠባይ ማሳየቱን ባመነ ጊዜ በአንቀጽ ፻፹፬ በተመለከተው መሠረት ቅጣቱን አክብዶ መወሰን ይችላል::

በሌላ ሁኔታ ግን አግባብ ባለው የሕግ ድንጋጌ ለከባዱ ወንጀል የተደነገገውን ከፍተኛ የቅጣት ወሰን ሣያልፍ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ይወስናል::

፪ ልዩ ልዩ ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን እንደሚከተለው ያከብዳል::

ሀ/ ጥፋተኛው ከተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች ውስጥ ቢያንስ አንዱን አስቦ ያደረገ እንደሆነ፣ አንቀጽ ፷፯(፩)(ሀ) እና (ለ) በአንቀጽ ፻፹፬ በተመለከተው መሠረት ቅጣት ይወስንበታል::

ለ/ ጣምራ ወንጀሎቹ የተፈፀሙት በቸልተኛነት ሲሆን፣ አንቀጽ ፷፯(፩)(ሐ) በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ሳይታለፍ ቅጣት ይወስንበታል::

ሐ/ ጥፋተኛው አስቦ የፈፀማቸው ወንጀሎች የሕዝብን ደህንነትና ጥቅም የሚጎዱ ሆነው በተገኙ ጊዜ አንቀጽ ፷፯(፪) ፍርድ ቤት ቅጣቱን በአንቀጽ ፻፹፬ መሠረት ያከብዳል::

<u>አንቀጽ ፻፹፷ በተደጋገመ ጥፋት ቅጣትን ማክበድ</u>

፩ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፷፯ በተገለፁት ሁኔታዎች አንድ አዲስ ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ፣ ፍርድ ቤት ቅጣቱን ማክበድ ያለበት ሲሆን ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት በማለፍ መወሰን ይችላል:: ፍርድ ቤቱ በሕጉ ልዩ ክፍል ለአዲሱ

ወንጀል ወይም ከአዲሶቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ከባድ ለሆነው ወንጀል የተደነገገውን ጣራ ቅጣት እጥፍ እስኪሆን ቅጣቱን ሊያከብድ ይችላል።

፪ በተደጋገሙት የወንጀሎች ዓይነትና ብዛት እንዲሁም በወንጀለኛው ጥፋተኛነትና በድርጊቱ አደገኛነት መጠን ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ከፍተኛ ቅጣት ሳይከተል ለቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ሊያሳድግ ይችላል።

ወንጀለኛው ልማደኛ ደጋጋሚ ከሆነ ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት እጥፍ በማለፍ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ማሳደግ አለበት።

፫ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚወሰነው ቅጣት ምንጊዜም ቢሆን ለቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት መብለጥ አይችልም (አንቀጽ ፻፮ እና ፻፰)።

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች መደራረብ

### አንቀጽ ፻፹፬ የልዩ ልዩ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች መደራረብ

ልዩ ልዩ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች ሲገኙ ፍርድ ቤቱ ቅጣት የሚወስነው ከዚህ በታች በተደነገገው መሠረት ነው።

፩ በአንድ ወንጀል ላይ ቅጣት የሚያከብዱና የሚያቃልሉ ጠቅላላ ምክንያቶች በተደራረቡ ጊዜ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማክበጃ ምክንያቶችን ከግምት በማስ ገባት ቅጣቱን ያከብድና /አንቀጽ ፹፫/፣ ቀጥሎ

የሚያቃልሉትን ምክንያቶች መሠረት አድርጎ ቅጣቱን ይቀንሳል /አንቀጽ ፻፹፱፣ ፻፹/።

፪ ጥፋተኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሆኖ በተደራረቡ ወንጀሎች ጥፋተኛ የሆነ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ለተደራረቡት ወንጀሎች ቅጣትን ይወስናል፤ ቀጥሎም ደጋጋሚ ወንጀለኛነቱን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳል።

፫ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱት ልዩ ልዩ ቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ በማክበጃ ምክንያቶቹ መሠረት ቅጣቱን ካከበደ በኋላ ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶቹን መሠረት አድርጎ ቅጣቱን ይቀንሳል።

## ክፍል ሁለት

## ቅጣትን መገደብ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ቅጣትን በገደብ ማቆም

**አንቀጽ ፻፺ መርህ**

ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ ማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል፣ ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ ሊሆን የሚችል መሆኑን ፍርድ ቤቱ ያረጋገጠ እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ሊወሰን ይችላል።

በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጡት ውሳኔዎች የወንጀለኛውን የመታረም መልካም ፈቃድና እርዳታ የሚፈልጉ ስለሆነ መልካም ውጤትን ለመስጠት አለመቻላቸው ሲታወቅ በማናቸውም ጊዜ የሚሻሩ ናቸው።

## አንቀጽ ፻፺፭ ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት፣ የጥፋተኛነት ውሳኔውን መሰረዝ

ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ ጥፋቱ በመቀጮ /አንቀጽ ፺/፣ በግዴታ ሥራ /አንቀጽ ፻፫ እና ፻፬/ ወይም ከሦስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት በሚያስቀጣ እንደሆነ /አንቀጽ ፻፮/ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊቱ ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑንና በዚሁ ውሳኔ ብቻ እስከመጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ያመነበት እንደሆነ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ቅጣት ሳይወስን የተወሰነ የፈተና ጊዜ ሊሰጠው ይችላል።

ፈተናው መልካም ፍሬ ያስገኘ እንደሆነ ፍርዱ እንዳልነበረ ይቆጠራል።

## አንቀጽ ፻፺፮ ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ

ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም (አንቀጽ ፻፺፭) የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱን ከወሰነ በኋላ የተወሰነ የፈተና ጊዜ በመስጠት የቅጣቱ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝዝ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የወሰናቸው የጥንቃቄ እርምጃዎችን ግን (ከአንቀጽ ፻፷፯ እስከ ፻፸፱) አያግድለትም።

ፈተናው መልካም ፍሬ ያስገኘ እንደሆነ ጥፋተኛው የተወሰነበትን ቅጣት መፈፀም የለበትም፣ የፍርዱ ውሳኔ ግን በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ፣ ከሌላው ውጤት ጋር ነዋሪ ይሆናል።

BACK


## አንቀጽ ፻፺፫ የተደራረቡ የቅጣት ውሳኔዎች ሲኖሩ ለአፈፃፀ ማቸው ጊዜ መስጠትንና መከፋፈል

የተደራረቡ ቅጣቶች በሚኖሩበት በተለይም ተጨማሪ ቅጣቶች በሚወሰኑበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለኅብረተሰቡ ደህንነትና ጠቅላላ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአንዳንዶቹን ቅጣቶች መታገድና የጊዜ መስጠትን ጉዳይ መተው ይችላል፡

## አንቀጽ ፻፺፬ የቅጣት ገደብ የሚከለከልበትና የሚሻርበት ሁኔታ

፩ የቅጣት አፈጻጸምን መገደብ የማይቻለው:-

ሀ/ ስለደጋጋሚነት የተፃፉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ /አንቀጽ ፷፯ እና ፻፹፷/፣ ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የጽኑ እስራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ የቀላል እስራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም፣

ለ/ ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ የፅኑ እስራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነው።

፪ እንዲሁም:-

ሀ/ የቅጣቱ አፈጻጸም ከመታገዱ በፊት ጥፋተኛው ሌላ ወንጀል ፈጽሞ እንደነበረ የተደረሰበት ሲሆንና በዚሁ ወንጀል ምክንያት የሚፈረድበት የቅጣት ዓይነትና መጠን ከፍ ብሎ በንዑስ አንቀጽ ፩ በፊደል (ሀ) የተመለከተውን ሁኔታ የሚያሟላ ሲሆን፤ ወይም

BACK



ለ/ ወንጀለኛው ቅጣቱ ታግዶለት ለፈተና በተለ ቀቀበት ጊዜ ውስጥ አስቦ አንድን ወንጀል ያደረገ እንደሆነ / አንቀጽ ፪፻(፪)/፤ ወይም

ሐ/ የቅጣት አፈጻጸሙ በታገደለት ጉዳይ የተሰጠው የፈተና ጊዜ መልካም ፍሬ የሚያስገኝ አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲረዳው፤

የቅጣት ማገዱን ውሳኔ ሊሽረው ይችላል::

<u>አንቀጽ ፻፺፫ ማጣራት / ምርመራ</u>

ፍርድ ቤቱ ለውሳኔው አስቀድሞ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ባመነ ጊዜ ሁሉ ፍርዱ እንዲታገድለት የሚጠይቀውን ተከሳሽ የቀድሞ ታሪኩ፣ የነበረው ጠባይ፣ የአኗኗሩና የሥራው ሁኔታ ምን ዓይነት እንደነበረ ምርመራ ተደርጐ የተረጋገጠ መረጃ እንዲቀርብለት ማዘዝ አለበት::

ይህም መረጃ ከአንድ የጥበቃ ባልደረባ ወይም እምነት ከሚጣልበት የማህበራዊ ሠራተኛ ወይም አግባብ ካለው ማናቸውም ሌላ አካል ወይም ተቋም ሊቀርብ ይችላል::

<u>አንቀጽ ፻፺፬ የወል ድንጋጌዎች፤ ለፈተና የሚሰጥ ጊዜ</u>

፩ ፍርድ ቤቱ ከሁለቱ የዕግድ አይነቶች /አንቀጽ ፻፺፩ እና ፻፺፪/ አንዱን ሲመርጥ ምክንያቱን በውሳኔው ላይ መግለጽ አለበት::

የተከሳሹ የቀድሞ ታሪኩ፣ የጠባዩና የዓመሉ አካሄድ ሲመዘን ጊዜ መስጠቱ መልካም ውጤት የሚያስገኝ መስሎ ካልታየ ፍርድ ቤት የማገጃ ትዕዛዝ ለመስጠት አይችልም::

፪ ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው የሚሰጠውን የፈተና ጊዜ የሚወስነው የወንጀሉን ከባድነት፣ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እና

BACK



በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚቻለውን እምነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው::

የፈተናውም ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊያንስ ከአምስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም:: የሚታሰበውም የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው::

## አንቀጽ ፻፺፯ ፈተና የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች

፩ ፍርድ ቤቱ በወንጀል አድራጊው ላይ የተወሰነበት ቅጣት እንዳይፈፀምበት የሚያግድለት ጥፋተኛው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ፣ እንዲፈጽም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል፣ እንዲሁም በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍልና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ከሰጠ በኋላ ነው /አንቀጽ ፻፩/::

፪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈጻጸም አንድ መተማመኛ ዋስትና እንዲሰጥ ያስገድደዋል:: ይህም መተማመኛ በሰው ዋስትና ወይም በንብረትና በገንዘብ መያዣ ልክ ፍርድ ቤቱ የሚወስነው እንደነገሩ ሁኔታና እንደ ጥፋተኛው ችሎታ መጠን ነው::

## አንቀጽ ፻፺፰ በጥፋተኛው ላይ የሚወሰን የጠባይ አመራር ደንብ

፩ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታዩትን የጠባይ አመራር፣ የአጠባበቅና የመቆጣጠር ደንቦች በፍርዱ ላይ ይወስናል::

እነዚህ ደንቦች በተለይ በአንድ የጥበብ መስክ ሙያ መማርን፣ በተወሰነ ሥፍራ የመቀመጥን፣ የመሥራትን ወይም የመኖርን ግዴታ፣ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር እንዳይገናኝ የመከልከልን ወይም በአንዳንድ በተወሰኑ

BACK



ሥፍራዎች ከመድረስ መታገድን፣ አልኮል ከመጠጣት የመከልከልን፣ በሥራው ከሚያገኘው ገቢ በሙሉ ወይም በከፊል ለቤተሰቡ፣ ለሞግዚቱ ወይም ለአሳዳሪው መስጠትን፣ አስፈላጊ የሆነውን ሕክምና መፈጸምን ወይም የሙከራውን ውጤት ፍሬ ለማስገኘት የሚችል ለዚሁ ተገቢ የሆነውንና ይህን የመሳሰለውን ሌላ የአመራር ደንብ የመፈጸም ግዴታን የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ::

፪ በጥፋተኛው ላይ የሚወሰኑት የጠባይ አመራር ደንቦች የጥፋተኛውን አቅምና ፍላጐት፣ የነገሩን ሁኔታና ጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት መሠረት በማድረግ የጥፋተኛውን ጠባይ በማሻሻል ወደታሰበው ግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው::

የጠባይ አመራር ደንቡ ግብ ከፍርድ ማገድ ግብ ልዩ ሊሆንና ከሕጉም ጋር የማይስማሙ ግዴታዎችን ሊያስከትል አይችልም::

፫ አዲስ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርዱ በታገደለት ሰው፣ በባልደረባው፣ በሞግዚቱ ወይም በዋሱ አመልካችነት ወይም በዐቃቤ ሕግ ጠ ያቂነት የተወሰኑት የጠባይ አመራር ደንቦች ሊለወጡ ይቻላል::

<u>አንቀጽ ፻፺፱ በጥፋተኛው ላይ ቁጥጥር ማድረግ</u>

፩ ፍርድ ቤቱ በአንድ ጥፋተኛ ላይ የተወሰነው የቅጣት ፍርድ እንዲታገድ ሲያደርግ፣ ፍርዱ የታገደለት ጥፋተኛ በአንድ አሳዳሪ፣ ሞግዚት፣ በጠባይ መሻሻል ጥበቃ ኃላፊ ወይም በጠቅላላው የጠባቂነት ሥልጣን በተሰጠው የጥበቃ ባልደረባ ሥር ሆኖ ቁጥጥር እንዲደረግበት ያዝዛል /አንቀጽ ፪፻፰/::

BACK



አሳዳሪው ወይም የጥበቃው ባልደረባ ፍርድ ከታገደለት ጥፋተኛ ጋር ግንኙነት እያደረገ በቤቱ ውስጥ ወይም በሥራው ላይ ሊጎበኘው፣ የእረፍቱንም ጊዜ ሊቆጣጠረው፣ በተቻለ መጠን ሁሉ አኗኗሩን እንዲያስተካክልና ጠባዩንም እንዲያሻሽል አስፈላጊውን የአመራር እርዳታ ሊያደርግለት ይገባዋል::

አሳዳሪው ወይም የጥበቃው ባልደረባ ፍርዱ በታገደለት ጥፋተኛ ላይ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ስውር የሆነ ቁጥጥር ያደርግበታል:: ለሚመለከተው የጠባይ መሻሻል ጥበቃ ኮሚሽን ቢያንስ በየሦስት ወር ወይም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሪፖርት ያቀርባል::

፪ የጠባይ መሻሻል ጥበቃ ኃላፊዎች እና የኮሚሽኖች አቋምና ተግባር በሚወጣ ሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ ፪፻ የፈተናው ፍሬ አለማስገኘት የሚያስከትለው ውጤት

፩ ፍርዱ የታገደለት ጥፋተኛ ለፈተና በተሰጠው ጊዜ ውስጥ በግዴታ እንዲከተላቸው ከተሰጡት የጠባይ አመራር ደንቦች አንዱን የጣሰ፣ ከአሳዳሪው ጥበቃ ወይም ከቁጥጥር ለማምለጥ የሞከረ፣ በቸልተኛነት ወንጀል ያደረገ ወይም የተጣለበትን እምነት ያጓደለ እንደሆነ፣ በቸልተኛነት ላደረገው ወንጀል መከሰሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል::

አስፈላጊም ሲሆን በሕጉ ዕቅድና ወሰን ውስጥ እንደተመለከተው በፊት ተወስኖ የነበረውን የፈተና ጊዜ ለማራዘም ወይም አዲስ የጠባይ አመራር ደንብ እንዲከተል ለማስገደድ ይቻላል::

፪ ጥፋተኛው ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ በመጥፎ የጠባይ አመራር የቀጠለ እንደሆነ ወይም ለፈተና በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ አስቦ አዲስ ወንጀል

ያደረገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የፍርዱን ማገድ ትዕዛዝ ይሽርበታል። ሆኖም ጥፋተኛው የሚያቀርበው ሃሳብ በቅድሚያ መሰማት አለበት።

ጥፋተኛው ለፈተና በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስቦ አዲስ ወንጀል ሠርቶ የተፈረደበት እንደሆነ ዳግመኛ የፍርድ ማገድ ትዕዛዝ ሊሰጠው አይችልም።

፫ በእንደዚህ ያለ ጊዜ ፍርድ ቤት አግዶት የነበረውን የቅጣት መወሰን በመሻር ቅጣት ወስኖ እንዲፈጸም ያዝዛል፤ ወይም ተወስኖ የነበረው ቅጣት እንዲፈጸምበት ያደርጋል።

የቅጣቱ ማገድ የሚሻረው አዲስ ታስቦ ወንጀል በመደረጉ ምክንያት እንደሆነ ስለደጋጋሚነት የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ አስቀድሞ ለተፈረደበት ወንጀል ከተወሰነው ወይም ከሚወሰነው ቅጣት ጋር የአዲሱ ወንጀል ቅጣት ተደምሮ ተፈፃሚ ይሆናል /አንቀጽ ፲፻፳/።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## በተወሰነ ገደብ በአመክሮ መፈታት

### አንቀጽ ፪፻፩ መርህ

በዚህ የወንጀል ሕግ ውስጥ የተደነገገው ነጻነትን የሚያሳጣ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ በተወሰነ ጊዜ ሁሉ በሕጉ የተወሰነው የቅጣት አፈጻጸም ጊዜ ሲደርስና ጠቅላላውም ሁኔታ ተሟልቶ ሲገኝ ተቀጪውን ለአመክሮ አስቀድሞ መልቀቅ ይቻላል /አንቀጽ ፪፻፪/።

ለአመክሮ በተወሰነ ገደብ መፈታት የተቀጪውን ጠባይ ማሻሻያና ወደ ደንበኛው ማህበራዊ ኑሮ መመለሻ ሆኖ መቆጠር ይገባዋል። ተቀጪው ለዚሁ ተገቢ ካልሆነና

በተወሰነ ገደብ መፈታቱ ተፈላጊውን ውጤት የሚያስገኝ መሆኑ ካልታመነበት በቀር ሊፈቀድ አይቻልም::

<u>አንቀጽ ፪፻፪ ለመለቀቅ የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

፩ ተቀጪው ከተወሰነበት የእሥራት ጊዜ ከሦስት እጅ ሁለቱን እጅ ወይም ፍርዱ የዕድሜ ልክ እሥራት ሲሆን ሃያ ዓመት በፈፀመ ጊዜ አግባብ ባለው አካል ወይም በጥፋተኛው አሳሳቢነት ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በአመክሮ እንዲፈታ መወሰን የሚችለው ጥፋተኛው:-

ሀ/ አስፈላጊ የሆነውን ነፃነት የሚያሳጣ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ በመፈጸም ላይ ሳለ በሥራውና በጠባዩ የተረጋገጠ መሻሻል አሳይቶ እንደሆነ፤

ለ/ ለደረሰው ጉዳት በተቻለ መጠን ሊከፍል የሚጠበቅበትን በፍርድ ቤት በተወሰነው መሠረት ወይም ከተበዳዩ ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ካሣ ለመክፈሉ ማረጋገጫ አቅርቦ እንደሆነ፤ እና

ሐ/ አመሉና ጠባዩ በመልካም አኗኗር ለመኖር የሚያስችለው እና በአመክሮ መፈታቱ መልካም ውጤት ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ የታመነ እንደሆነ፤ ነው::

፪ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ቢኖሩም በአመክሮ መፈታት በልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ተፈፃሚ አይሆኑም::

BACK



## አንቀጽ ፪፻፫ በአመክሮ የመፈታትን ጉዳይ ማሳወቅ

፩ ጥፋተኛው በሚፈረድበት ጊዜና ወደሚላክበት ተቋም በሚገባበት ጊዜ የተወሰነበት ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት ቀደም ብሎ በአመክሮ ሊለቀቅ የሚችል መሆኑን፣ ይህንንም እድል ለማግኘት ምን ዓይነት ግዴታ መፈጸም እንደሚገባው /እንዲያውቀው/ ይገለፅለታል፡፡

፪ በአመክሮ ለመፈታት የሚያበቁ ሁኔታዎች የተሟሉ መስለው በታዩ ጊዜ አግባብ ያለው አካል እስረኛው በአመክሮ እንዲለቀቅ ራሱ ሃሳብ በማቅረብ ወይም እስረኛው በአመክሮ ልለቀቅ ብሎ ያቀረበውን ማመልከቻ ተቀብሎ ከነአስተያየቱ ለፍርድ ቤት ያስተላልፋል፡፡

## አንቀጽ ፪፻፬ የፈተናው ጊዜ

ፍርድ ቤቱ በአመክሮ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ሲሰጥ ወዲያው ተፈቺው በአመክሮ የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል፡፡ ይህም የአመክሮ ጊዜ የሚቆየው በሌላ ሁኔታ ካልታዘዘ በስተቀር በመሠረቱ ሳይፈጸም የቀረው ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ እስኪፈጸም ድረስ ነው፡፡

የዚህም ጊዜ ልክ በማናቸውም ሁኔታ ከሁለት ዓመት ሊያንስ፣ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለም ከአምስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡ የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተወሰነበት ጥፋተኛ ሲሆን ግን የፈተናው ጊዜ ከአምስት ዓመት ሊያንስ ከሰባት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡

## አንቀጽ ፪፻፭ የጠባይ አመራርና የቁጥጥር ደንብ

፩ ከዚህ በላይ በተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች መሠረት የተለቀቀው ጥፋተኛ ለፈተና በተወሰነለት ጊዜ ተገቢ የሆነውን የጠባይ አመራር ደንብ /አንቀጽ ፻፺፰/ እንዲከተል ይወሰንበታል፡፡

BACK



የተለቀቀው ጥፋተኛ ሊከተላቸው የሚገቡ የጠባይ አመራር ደንቦች የሚወሰኑት በተለይ የተለቃቂውን እድሜና ጠባዩን፣ ከተፈታ በኋላ ሊደርስበት የሚችለውን ለወንጀል የመጋለጥ ዕድል፣ የቤተሰቡን አስተማማኝነት፣ የሙያ ሥራውንና የማህበራዊ ኑሮውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ነው::
የሚቻልም ሲሆን ለተለቃቂው መተዳደሪያ የሚሆኑት ሁኔታዎች ተቀጪው ከመለቀቁ በፊት በሚመለከተው ተቋም ወይም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን በተሰጣቸው የጥበቃ ባልደረቦች ወይም አግባብ ባለው መንግሥታዊ አካል ድጋፍ መዘጋጀት አለባቸው::

፪ በመሠረቱ በሌላ ሁኔታ ካልታዘዘ በስተቀር ተለቃቂው በአንድ አሳዳሪ ወይም በአንድ የጠባቂነት ሥልጣን በተሰጠው ባልደረባ ተቆጣጣሪነትና መሪነት ሥር እንዲኖር ይደረጋል /አንቀጽ ፪፻፰/:: ይህም የጥንቃቄ ሥርዓት ሊፈጸም የማይቻልበት ሁኔታ ካጋጠመና ጠቃሚነት የሌለው መሆኑ ከታወቀ በተለቃቂው ላይ ተፈጻሚ ላይሆን ይችላል::

## አንቀጽ ፪፻፺ የፈተናው ውጤት

፩ የፈተናው ሁኔታና በአመክሮ የመፈታት ትዕዛዝ መሻር የሚመራው ከዚህ በላይ በተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች መሠረት ነው /አንቀጽ ፪፻/::

፪ በአመክሮ የመፈታት ትዕዛዝ ሲሻር ተለቅቆ የነበረው ጥፋተኛ ወደነበረበት ተቋም ተመልሶ እንዲገባ ይደረጋል::

በአመክሮ ተፈትቶ ያሳለፈው ጊዜ ሊፈጽም ከሚገባው ቀሪ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ጊዜ ላይ አይታሰብለትም::

አዲስ ወንጀል በመካከሉ ተደርጐ እንደሆነ ስለደጋጋሚነት የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆኖ (አንቀጽ ፷፯ እና ፻፹፰) ለአዲሱ ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት ከቀሪው ቅጣት ጋር ተደምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

፪ ተለቃቂው የፈተናውን ጊዜ በተወሰነለት የጠባይ አመራር ደንብ መሠረት የፈጸመ እንደሆነ መለቀቁ እስከመጨረሻው ይሆንና ቅጣቱ በሙሉ ይቀርለታል።

አንቀጽ ፩፻፪ <u>የክልከላዎችና የሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎች ውሳኔ ውጤት</u>

፩ ነፃነትን ከሚያሳጣ ቅጣት ጋር የሙያ ሥራ ከማከናወን የመታገድ /አንቀጽ ፻፳፫(ሐ)/፣ በአንዳንድ ሥፍራ ከመድረስ ወይም ውሎ ከማደር የመከልከል ወይም በተወሰነ ሥፍራ ታግዶ የመኖር ተጨማሪ ቅጣት ወይም ከአገር የመውጣት የጥንቃቄ እርምጃ /አንቀጽ ፻፴፫ - ፻፶/ በተጨማሪነት ተወስኖ እንደሆነና በአመክሮ የመለቀቅም ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ ከነገሩ ጠ ቅላላ ሁኔታ የተነሳ ውሳኔው ጠቃሚና የሚገባ ሆኖ ሲታየው ፍርድ ቤቱ አፈጻጸሙን ለሙከራ እንዲታገድ ለማድረግ ይችላል /አንቀጽ ፻፶፪/።

ይህ ውሳኔ የሚሰጠው በተለይ የተለቃቂውን የመሻሻል ሁኔታ ደረጃ፣ የአደገኛ ጠባዩን መጥፋት ወይም መቀነስ ሁኔታ፣ የተጨማሪ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ አፈጻጸም ለጊዜው የማገድ ጉዳይ ወደ ደንበኛው ማህበራዊ ኑሮ ለመመለስ ሊያስገኝ የሚችለውን መልካም ውጤት በማመዛዘን ነው።

፪ ፍርድ ቤቱ ይህን የሚወስነው አስፈላጊውን ማጣራት ካደረገ በኋላና ከማረሚያ ቤቱ አስተዳደርና ጉዳይ ከሚመለከታቸው የጥበቃ ባልደረቦች አስተያየቶችን በቅድሚያ ከተቀበለ በኋላ ነው።

በዚህም ጊዜ ለፈተና በመለቀቁ ጉዳይ ላይ ተለቃቂው ሊፈጽም የሚገባውን ግዴታ፣ መከልከል ያለበትን ወይም ሊሰጥ የሚገባውን የዋስትና ማረጋገጫ ሊደረግበት የሚገባውን ቁጥጥርና ሌሎችንም ይህን የመሳሰሉ ነገሮች ፍርድ ቤቱ ይወስናል::

፫ በአመክሮ የተለቀቀው ተቀጪ በፈተናው ጊዜ ውስጥ ሁሉ በተወሰነለት የጠባይ አመራር ደንብ ተመርቶ ከፍተኛ ወቀሳ ያላገኘው እንደሆነ ጠባዩም የተሻሻለ መስሎ ሲታይ ነጻነትን የመቀነስ ወይም ከአገር የመውጣት ቅጣት ያስከተለውን ጥፋት ዳግመኛ እንደማይሰራ ያመነበት እንደሆነ ተወስኖበት የነበረው ተጨማሪ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ አይፈጸምበትም::

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የጥበቃ ባልደረብነት

### አንቀጽ ፪፻፲ መርህ

የጥበቃ ባልደረብነት ማለት የቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች፣ የእነዚሁም አፈጻጸም የጥበቃ ባልደረብነት ሥልጣን በተሰጠው ባለሥልጣን አማካይነት ፍሬ እንዲያስገኝ የሚደረግበት ሥርዓት ነው::

በሕጉ ተደንግጎ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ አንድ ጥፋተኛ በጥበቃ ባልደረባ ሥልጣን ሥር ሆኖ እንዲጠብቅ መደረግ አለበት:: እንዲሁም በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በገደብ የተለቀቀ ወይም ቅጣቱን ፈጽሞ የተለቀቀ ጥፋተኛ ለጠባዩ መልካም አመራር የጥበቃ ባልደረብነት ድጋፍና እርዳታ እንዲያገኝ ለመጠየቅ ይችላል:: በጥያቄው መሠረትም የጥበቃ ባልደረባ ድርጅቶች ለጥፋተኛው የእርዳታ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው::

አንቀጽ ፻፻፱ የጥበቃ ባልደረብነት ዓላማና ተግባር

፩ የጥበቃ ባልደረባ ዋና ተግባር ማህበራዊ ኑሮ እንደገና እንዲለምዱ የሚያስፈልጋቸውን ጥፋተኞች ቅጣታቸው በታገደላቸው ጊዜም ሆነ በአመክሮ ወይም ቅጣታቸውን ፈጽመው ከተፈቱ በኋላ ወደ ደንበኛው ማህበራዊ ኑሮ እንዲመለሱና ደጋግመው ወንጀል እንዳያደርጉ ምክር መስጠት፣ ወደ ቀና መንገድ መምራትና የመልካም ጠባይ እና የተጨበጠ እርዳታ ማድረግ ነው::

የጥበቃ ባልደረብነት ሥልጣን የተሰጠው ድርጅት በተቻለ መጠን ተጠባቂዎቹን በሥራ ላይ ሊያውላቸው፣ ሥራ ሊሰጣቸው፣ ሥራ ወይም መኖሪያ ወይም እርዳታ እንዲያገኙ ሊያግዛቸው፣ ወይም በሥራቸው የሚያገኙትን ደመወዝና ጥቅም ለተገቢ ጉዳያቸው እንዲያውሉትና በጠቅላላውም በደንበኛው ማህበራዊ ኑሮ ለመኖር የሚችሉበትን ማናቸውንም ድጋፍና እርዳታ ያደርግላቸዋል::

፪ የጥበቃ ባልደረባው ዘወትር ቁጥጥር ያደርግባቸዋል:: የመቆጣጠሩ ተግባር መሻሻላቸውን እንዳያሰናክል በስውር ሊፈጸም ይገባል:: አስፈላጊ ሲሆንም ለፍርድ ቤቱና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል::

አንቀጽ ፻፻፲ አደረጃጀት

፩ ከዚህ በላይ የተገለጸው የባልደረብነቱ ሥራ የሚካሄደው በመንግሥት ተቆጣጣሪነት ሆኖ ለዚሁ ተግባር በተቋቋሙ መንግሥታዊ ወይም ግላዊ ባህርይ ባላቸው ማህበራት ወይም ቡድኖች ነው::

ይህ የባልደረብነት ሥራ በየጊዜው ለሚመረጥ ጠባዩም ለፈተናና ለዚሁ ኃላፊነት ብቁ ለሆነ ግለሰብም ሊሰጥ ይችላል::

በጠቅላላው ይህን ሥራ በሌላ ሁኔታ ለማካሄድ እስከተቻለ ድረስ የጥበቃ ባልደረብነት ለፖሊስ መሥሪያ ቤቶች አይሰጥም::

፪ የሥራው አፈጻጸም ዝርዝር ስለቅጣት አፈጻጸምና ጉዳዩን በሚመለከት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል::

## ምዕራፍ ሁለት

## ክስንና ቅጣትን ማቋረጥና ማስቀረት

### ክፍል አንድ

### የከሳሽ ወይም የተከሳሽ አለመኖር

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ አለመኖር

**አንቀጽ ፪፻፲፩ የግል አቤቱታ ወይም የወንጀል ክስ የማቅረብ መብት በጠቅላላው**

፩ በሕጉ በተለየ ሁኔታ በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር በማናቸውም ጉዳይ ላይ ፍርዱ እንዲሰጥና ቅጣት እንዲወሰን ለማድረግ ክስ የሚቀርበው በዐቃቤ ሕግ ነው::

፪ በዐቃቤ ሕግ አማካይነት ክስ መቅረቡ፣ አግባብነት ላላቸው የመንግስት ባለስልጣኖች የግል አቤቱታ ወይም የወንጀል ክስ የማቅረብ መብትን አያስቀርም::

## አንቀጽ ፪፻፲፪ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች

ወንጀሉ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጣ መሆኑ በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል ወይም በሌላ ማሟያ የወንጀል ሕግ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ በግል ተበዳይ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ የግል አቤቱታ ካልቀረበ በቀር የወንጀል ክስ ማቅረብ አይቻልም።

## አንቀጽ ፪፻፲፫ የግል አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ

የግል አቤቱታ መቅረብ ያለበት ተበዳዩ የወንጀሉን ድርጊት ወይም የወንጀል አድራጊውን ማንነት ካወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሦስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

ተበዳዩ የግል አቤቱታውን ለማቅረብ ያልቻለው የግል አቤቱታ ለማቅረብ በማያስችል ጉልህ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር ይህ ጊዜ ካለፈ የግል አቤቱታ ለማቅረብ እንዳልፈለገ ይቆጠራል። የግል አቤቱታውንም ለመቀበል አይቻልም።

የግል አቤቱታ ማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት ከሆነ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ያጋጠመው ችግር ከተወገደበት ቀን ጀምሮ ነው።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የተከሳሽ ወይም የተፈረደበት ሰው መሞት

## አንቀጽ ፪፻፲፬ ከፍርድ በፊት የተከሳሽ መሞት

አንድ ተከሳሽ በፍርድ ቤት ከመከሰሱ ወይም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት የሞተ እንደሆነ ክሱ ሊቀርብ ወይም ሊቀጥል ወይም ፍርድ ሊሰጥ አይችልም።

BACK



## አንቀጽ ፪፻፲፰ የተፈረደበት ሰው መሞት

ጥፋተኛው ከተፈረደበት በኋላ የሞተ እንደሆነ የቅጣቱና የጥንቃቄ እርምጃው ውሳኔ ቀሪ ይሆናል::

## ክፍል ሁለት

## የክስና የቅጣት ይርጋ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የክስ ይርጋ

## አንቀጽ ፪፻፲፱ መርህ እና ውጤቱ

፩ በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ከዚህ በታች የተመለከተው የይርጋ ዘመን ካለፈ በኋላ በማናቸውም ወንጀል የግል አቤቱታን ወይም የወንጀል ክስን መቀበልና ጉዳዩን በዳኝነት ማየት አይቻልም::

የይርጋ ዘመኑ ማለፍ ለማናቸውም የወንጀል ተካፋይ ቅጣትን ያስቀራል:: ለይርጋ የተወሰነም ጊዜ ካለፈ የጥፋተኛነት ውሳኔ ወይም ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ሊወሰን አይቻልም::

፪ ክሱ በይርጋ ስለመታገዱና ክሱን ለመቀበል የማይገባ ስለመሆኑ ተከሳሹ ባያመለክትም ዐቃቤ ሕጉ ወይም ፍርድ ቤት በማናቸውም ጊዜ ማንሳት አለበት::

## አንቀጽ ፪፻፳ መደበኛ የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን

፩ በወንጀል ተግባር ክስ የማቅረብ የይርጋ ዘመን የሚፀናው ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ነው:-

ሀ/ የሞት ፍርድ ወይም የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል ሃያ አምስት ዓመት፣

BACK



ለ/ ከአሥር ዓመት በላይ እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ሃያ ዓመት፣

ሐ/ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ አሥራ አምስት ዓመት፣

መ/ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል አሥር ዓመት፣

ሠ/ ከአንድ ዓመት በላይ በቀላል እሥራት ለሚያስቀጣ ወንጀል አምስት ዓመት፣

ረ/ እስከ አንድ ዓመት በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወይም በመቀጮ ብቻ ለሚያስቀጣ ወንጀል ሦስት ዓመት::

፪ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ:-

ሀ/ የወንጀሎቹ ከፍተኛ ቅጣቶች ተመሳሳይ በሚሆኑበት ጊዜ የአንዱ ወንጀል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን በሁሉም ወንጀሎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

ለ/ የወጀሉቹ ከፍተኛ ቅጣቶች የተለያዩ በሚሆንበት ጊዜ ከሁሉም ከባድ የሆነው ወንጀል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን በሌሎች ወንጀሎች ላይም ተፈፃሚ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፪፻፲፰</u> <u>ልዩ የግል አቤቱታ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን</u>

የአንቀጽ ፪፻፲፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ የማናቸውም የወንጀል ክስ የይርጋ ዘመን ሁለት ዓመት ነው::

BACK



## አንቀጽ ፪፻፲፱ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር

፩ የይርጋ ዘመን የሚታሰበው የቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ሳይገቡ በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት መሠረት በማድረግ ነው።

የተፈፀመው ወንጀል በተለዋጭ ወይም በተደራራቢ ተፈፃሚነት በሚኖራቸው ቅጣቶች የሚያስቀጣ ሲሆን የይርጋ ዘመኑ የሚታሰበው ከሁሉም ከባድ ለሆነው ወንጀል በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት መሠረት በማድረግ ነው።

፪ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው ጥፋተኛው የወንጀሉን ድርጊት ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ነው።

የወንጀሉ ድርጊት እየተደጋገመ ተፈፅሞ እንደሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የወንጀል ድርጊት ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ነው። እንዲሁም የወንጀሉ ድርጊት ለረጅም ጊዜ ሲፈፀም የቆየ እንደሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የወንጀሉ ድርጊት ካቆመበት ቀን ጀምሮ ነው።

ወንጀሉ ተደርጓል ለማለት የሚቻለው ከጠባዮቹ አንዱ የወንጀሉ ውጤት የሆነ እንደሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀመረው የወንጀሉ ውጤት ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

## አንቀጽ ፪፻፳ የይርጋ ዘመን መታገድ

፩ በሕጉ ወይም በፍሬ ነገር ክሱ እንዳይጀመር ወይም እንዳይቀጥል የሚያግድ መሰናክል እስካለ ድረስ የይርጋ ዘመን መቆጠሩ ታግዶ ይቆያል።

BACK


እንዲሁም ክስ ቀርቦ ነገሩ በዳኝነት በመታየት ላይ እንደሆነ ወይም በሌላው ችሎት የቀረበው ክስ ሳይፈፀም ተከሣሹ በተከሰሰበት የወንጀል ክስ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የማይገባ እንደሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር ታግዶ ይቆያል::

መሰናክሉም እንደተወገደ ወዲያውኑ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር ይቀጥላል::

፪ ስለክሱ መከታተል አቤቱታ እንዲቀርብ ማስፈለጉ በሕግ ተመልክቶ በተገኘ ጊዜ አቤቱታ አለማቅረቡ የይርጋውን መቆጠር አያግደውም::

እንዲሁም ክሱ እንዳይጀምር ወይም እንዳይቀጥል ጥፋተኛው በራሱ ፍላጐት የሚፈፅመው ተግባር የይርጋ ጊዜውን መቆጠር አያግደውም::

<u>አንቀጽ ፪፻፳፭ የይርጋ ዘመን መቋረጥ</u>

ከወንጀሉ ወይም ከወንጀለኞቹ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ምርመራ እንዲካሄድ፣ ብርበራ እንዲደረግ፣ መጥሪያ እንዲሰጥ ወይም ክስ እንዲቀርብ የሚሰጥ ትዕዛዝ፣ የሚፈፀም ድርጊት ወይም የሚሰጥ ውሳኔ የይርጋ ዘመኑን መቆጠር ያቋርጣል::

የይርጋ ዘመን በተቋረጠ ቁጥር እንደገና እንደ አዲስ መቆጠር ይጀምራል::

የይርጋ ዘመኑ መቋረጥ ፍጽም የሆነ ውጤት አለው፤ በወንጀሉ ተካፋይ መሆናቸው ለታወቀውም ሆነ ላልታወቀው ሁሉ መቋረጡ ይፀናባቸዋል::

## አንቀጽ ፪፻፷፪ ፍፁም የሆነ የይርጋ ዘመን

በማናቸውም ምክንያት መደበኛ የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን /አንቀጽ ፪፻፲፯/ አጠፌታ ጊዜ ካለፈ ወይም ልዩ የግል አቤቱታ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን ሲሆን /አንቀጽ ፪፻፲፰/ ከዚሁ ዘመን በግማሽ የሚበልጥ ጊዜ አልፎ እንደሆነ በወንጀሉ ላይ የሚቀርበው ክስ ወይም የሚደረገው መከታተል በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች ይርጋ

## አንቀጽ ፪፻፷፫ መርህ እና ውጤቱ

፩ በሕግ በሌላ አኳኋን በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር በተቀጪው ላይ የተወሰነው ቅጣት በማናቸውም ምክንያት ከዚህ በታች ከአንቀጽ ፪፻፷፬ - ፪፻፷፰ በተመለከቱት ጊዜያት ውስጥ ሳይፈጸም የቆየ እንደሆነ ቅጣቱን የማስፈጸም መብት ቀሪ ይሆናል፤ የተወሰነውም ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ሊፈጸም አይችልም፡፡

የዋነኛው ቅጣት የይርጋ ዘመን የተጨማሪ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች መፈፀምንም ያስቀራል፡፡ እንዲሁም የዋናው ቅጣት የይርጋ ዘመን ከቅጣቱ ጋር ለተያያዘ የንብረት መውረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም የጥንቃቄ እርምጃዎች ያለዋነኛ ቅጣት በሚወሰኑበት ጊዜ የአንቀጽ ፪፻፷፬(፩)(መ) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፪ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዳኝነት ወይም የአስተዳደር ባለሥልጣኖች በራሳቸው ተነሳሽነት የቅጣት የይርጋ ደንብን አክብሮ የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፫ የተወሰነው ቅጣት በይርጋ ዘመኑ መታገድ ምክንያት ሳይፈፀም ቢቀርም በወንጀለኞች መዝገብ ውስጥ እንደተመዘገበ ይቆያል::

## አንቀጽ ፪፻፰ መደበኛ የቅጣት ይርጋ ዘመን

፩ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች ይርጋ ዘመን የሚፀናው በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል፣

ሀ/ ለሞት ፍርድ፣ ወይም ለዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሠላሳ ዓመት

ለ/ ከአሥር ዓመት በላይ ለሆነ ነፃነትን የማሳጣት ቅጣት ሃያ ዓመት

ሐ/ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ነፃነትን የማሳጣት ቅጣት አሥር ዓመት

መ/ ለማናቸውም ሌላ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔ አምስት ዓመት

፪ ተደራራቢ ቅጣቶች ተወስነው እንደሆነ ቀላል የሆኑት ቅጣቶች በይርጋ ቀሪ የሚሆኑት ከሁሉም ከባድ የሆነው ቅጣት በይርጋ ቀሪ በሚሆንበት ጊዜ ነው::

## አንቀጽ ፪፻፱ የቅጣት ይርጋ ዘመን አቆጣጠር

፩ የቅጣት ይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው፣ ፍርዱ የመጨረሻ ሆኖ ተፈፃሚ መሆን ይችል ከነበረበት ቀን ወይም ፍርዱ መፈፀም ጀምሮ እንደሆነ ተቀጪው ይኸው ፍርድ እንዳይፈፀምበት ካመለጠበት ቀን ጀምሮ ነው::

ተቀጪው ፍርዱ ከታገደለት በኋላ የፍርድ መታገድ ትዕዛዝ የተሻረ እንደሆነ የይርጋው ጊዜ የሚቆጠረው

የቅጣቱ አፈፃፀም እንዲቀጥል ከታዘዘበት ቀን ጀምሮ ነው::

፪ ተደራራቢ ቅጣቶች ተወስነው እንደሆነ ለይርጋው ጊዜ አቆጣጠር መሠረት የሚሆነው ከሁሉም ከባድ የሆነው የቅጣት የይርጋ ጊዜ ነው::

<u>አንቀጽ ፪፻፳፮ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ የይርጋ ዘመን መታገድ</u>

የቅጣት ይርጋ ዘመን ታግዶ የሚቆየው:-

ሀ/ የቅጣቱ ወይም የጥንቃቄ እርምጃው አፈፃፀም እንደ ሕጉ ሊፈፀም ወይም አፈፃፀሙ ሊቀጥል ባልቻለ ጊዜ፣ ይህ መሰናክል እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ፣

ለ/ ተቀጪው ፍርዱ ታግዶለት፣ በአመክሮ ተፈትቶ ወይም የዕዳ መክፈያ ጊዜ ተሰጥቶ እንደሆነ የተወሰነው ጊዜ እስካላለቀ ድረስ፣

ሐ/ ነጻነትን በማሳጣት ቅጣት ወይም በሌላ የጥንቃቄ እርምጃ ለማስፈጸም ታስሮ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ፣ ነው::

<u>አንቀጽ ፪፻፳፯ የቅጣት የይርጋ ዘመን መቋረጥ</u>

የቅጣት ይርጋ ዘመን የሚቋረጠው የማስፈፀም ኃላፊነት በተሰጠው ባለሥልጣን ቅጣቱን ለማስፈፀም የሚደረግ ወይም ወደ ቅጣቱ አፈፃፀም የሚያመራ ተግባር በሥራ ላይ እንዲውል ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ነው::

<u>አንቀጽ ፪፻፳፰ ፍፁም የሆነ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ፣ ይርጋ ዘመን</u>

ለመደበኛ ሕጋዊ ቅጣት ከተወሰነው የይርጋ ዘመን /አንቀጽ ፪፻፳፬/ በግማሽ የሚበልጥ ጊዜ ካለፈ ጥፋተኛው በዚህ ጊዜ ውስጥ ቢያንስ በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል አስቦ በመፈፀም አደገኛ መሆኑን ካላሣየ በቀር

BACK



የቅጣት ወይም የጥንቃቄ ተግባር አፈፃጸም ውሣኔ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ቀሪ ይሆናል::

## ክፍል ሦስት

## ይቅርታና ምህረት

### አንቀጽ ፪፻፳፱ ይቅርታ

፩ በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር በፍርድ የተወሰነ ቅጣት ሥልጣን በተሰጠው አካል በሙሉ ወይም በከፊል በይቅርታ ሊቀር ወይም ዓይነቱ አነስተኛ በሆነ ቅጣት ሊለወጥ ይችላል::

የከባድነታቸው ደረጃ ማናቸውም ቢሆን በዋነኛነትም ሆነ ወይም በተጨማሪ ተፈጻሚ ለሚሆኑ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ይቅርታ ሊሰጥ ይችላል::

፪ የይቅርታ አሰጣጡ ሁኔታ በሕግ እንደተደነገገው ይሆናል፤ ይቅርታን የሚሰጠው ሁኔታና ገደብ ይወስናል::

ይቅርታ ሲሰጥ በተቀጪው ላይ የተወሰነው ፍርድ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ይኖራል::

### አንቀጽ ፪፻፴ ምህረት

፩ በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር ሁኔታዎች ሲገመገሙ የእርምጃው አስፈላጊነት ጠቃሚ መሆኑን በሚያመለክቱበት ጊዜ ለአንድ ዓይነት ወንጀሎች ወይም በአንድ ደረጃ ለሚገኙ ወንጀለኞች ያለምንም ገደብ ወይም በአንዳንድ ገደቦች ወይም ግዴታዎች አግባብ ባለው አካል ጠቅላላ ምህረት ሊሰጥ ይችላል::

የምህረት አሰጣጡም ሁኔታ በሕግ እንደተደነገገው ይሆናል፡፡ ሕጉ ዓላማውን፣ የተጠቃሚዎቹን ማንነትና የተፈጻሚነቱን ወሰን በግልጽ መወሰን አለበት፡፡

፪ ምህረት ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ፣ ማናቸውም የወንጀል ክስ እንዳይጀመር ወይም እንዳይቀጥል ያግዳል፡፡

ምህረት በሚሰጥበት ጉዳይ ቅጣት ተወስኖ እንደሆነ ምህረቱ ቅጣቱንና ቅጣቱ የሚያስከትለውን ማንኛዎቹንም ሌሎች የወንጀል ውጤቶች ያስቀራል፡፡ የጥፋተኛነት ውሳኔም እንዳልነበረ ተቆጥሮ ከወንጀለኞች መዝገብ ላይ ይሰረዛል፡፡

## አንቀጽ ፪፻፴፩ በፍትሐብሔር በኩል የሚከፈል ካሣና ወጪ

፩ ይቅርታና ምህረት በፍትሐ ብሔር በኩል፣ የጠፋውን እንደነበረ የመመለስና በተበዳዩ ላይ ለደረሰው ጉዳት የሚከፈለውን ካሣና ኪሣራ አያስቀረውም፡፡

፪ ይቅርታን ወይም ምህረትን በሚሠጠው ትዕዛዝ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ለመንግሥት ሊከፈል የሚገባውና ገና ያልተከፈለ ኪሣራ በይቅርታ ወይም በምህረት ይሰረዛል፡፡

## ክፍል አራት

## መሠየም

## አንቀጽ ፪፻፴፪ መርህ

፩ የተወሰነበትን ቅጣት የፈፀመ ወይም ቅጣቱ በይርጋ ወይም በይቅርታ የቀረለት ወይም ፍርዱ ወይም የቅጣቱ አፈፃፀም የታገደለት ወይም በአመክሮ የተለቀቀ ማንኛውም ጥፋተኛ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሕጋውያን ግዴታዎች ከፈፀመ፣ ከመቀጣቱ በፊት የነበረው ንፁህ ስም ተመልሶለት

እንዲሰየምና የተወሰነበትም ፍርድ እንዲሰረዝለት መጠየቅ ይችላል::

መሰየም የሚገኘው በመልካም ሥራ ነው እንጂ በይገባኛል አይደለም::

፪ ወንጀለኛው ከመቀጣቱ በፊት ወደነበረው ንፁህ ስም ተመልሶ ለመሰየም ጥያቄ ለማቅረብ ችሎታ ያጣ ወይም የሞተ እንደሆነ ሕጋዊ ወኪሉ ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ አንዱ ጥያቄውን ለማቅረብ ይችላል::

<u>አንቀጽ ፪፻፴፫ ለመሰየም የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች</u>

ፍርድ ቤቱ መሰየምን የሚፈቅደው:-

ሀ/ ቅጣቱ ፅኑ እስራት፣ እስከ መጨረሻው ከአገር መውጣት ወይም የንብረት መወረስ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከተፈፀመበት ወይም በይርጋ ከታገደበት ቀን አንስቶ፤ ወይም ቅጣቱ በይቅርታ በመሻሩ ምክያት ተቀጪው ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ወይም ተቀጪው ቅጣቱ ታግዶለት ወይም በአመክሮ ተፈትቶ የፈተናውን ጊዜ በሰላም ጨርሶ እንደሆነ ቅጣቱ ከታገደለት ወይም በአመክሮ ከተፈታበት ቀን አንስቶ ቢያንስ የአምስት ዓመት ጊዜ ያለፈ እንደሆነ፣ በሌላ ሁኔታ ግን ያለፈው ጊዜ ቢያንስ ሁለት ዓመት የሆነ እንደሆነ፤

ለ/ የተወሰነ ተጨማሪ ቅጣት ካለ ይኸው ቅጣት ተፈፅሞ እንደሆነ፤ እና

ሐ/ የተለቀቀው ተቀጪ የራሱ ችሎታና የጊዜው ሁኔታ በሚፈቅድለት መጠንና ራሱም ሊፈጽመው ይገባዋል ተብሎ በሚገመትበት ሁኔታ በፍርድ የተወሰ ነበትን ካሣ፣ የዳኝነትና ማናቸውንም ሌላ ኪሣራ በሚገባ አጠናቅቆ ከፍሎ እንደሆነ፤

መ/ የተለቀቀው ተቀጪ በፊደል (ሀ) በተገለፀው ጊዜ ውስጥ በመልካም ጠባይ ተመርቶ እንደሆነና በማናቸውም በእስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ጥፋተኛ ሳይሆን ቆይቶ እንደሆነ፣ ነው::

ከላይ በፊደል (ሀ) የተገለፀው ለመሠየም የሚያበቃው አነስተኛ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው፣ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፷፯ ስለደጋጋሚነት የተደነገገውን የጊዜ ገደብ እስካልነካ ድረስ ነው::

## አንቀጽ ፪፻፴፬ ልዩ ሁኔታዎች

፩ ቅጣቱ በይርጋ የታገደለት ሰው ሲሆን ቅጣቱ ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ይህ ቅጣት ያበቃ የነበረበት ጊዜ ከማለፉ በፊት የመሰየም ትዕዛዝ ሊሰጥ አይቻልም::

፪ ስሙ እንዲታደስለት የሚጠይቀው ተቀጪ በሕዝባዊ፣ በወታደራዊ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት መስክ የሚያስመሰግን ልዩ አስተዋጽኦ አበርክቶ ከተገኘ የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት መሰየሙ ሊፈቀድለት ይቻላል::

## አንቀጽ ፪፻፴፭ የመሰየም ውጤቶች

መሰየም ፍርዱን የሚሰርዘው ስለሆነ ከዚህ የሚከተሉትን ውጤቶች ያስከትላል:-

፩ ተቀጥቶ የነበረው ሰው ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ተወስኖበት የነበረው የመብት፣ የማዕረግ፣ ወይም የችሎታ ማጣት ለወደፊቱ ቀሪ ሆኖለት ሕዝባዊ መብቱንና ቤተሰብ የማስተዳደርና የሙያ ሥራ

የመሥራት መብቱን እንደገና ለመያዝ ችሎታ ይኖረዋል፤

፪ የቅጣቱ ፍርድ ከወንጀለኞች መዝገብ ላይ ይፋቅለታል፣ ወደፊትም እንዳልተፈረደበት ይቆጠራል፤

፫ በጠላትነት ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ቢሆን ያለፈውን ጥፋት አንስቶ መውቀስ፣ ወቃሹን በስም ማጥፋት ወንጀል ያስቀጣል፣ ለሕዝብ ጥቅም የተደረገ ነው ብሎ መከላከልም አይቻልም::

አንቀጽ ፪፻፴፮ ለመሰየም የሚቀርበውን ጥያቄ አለመቀበልና ጥያቄውን እንደገና ማቅረብ

ለመሠየም የቀረበውን ጥያቄ በቂ አይደለም በማለት ፍርድ ቤቱ ሳይቀበለው የቀረ እንደሆነ ሁለት ዓመት ከማለፉ በፊት እንደገና ጥያቄ ለማቅረብ አይቻልም::

አንቀጽ ፪፻፴፯ የተሰጠውን ውሳኔ መሻር

እንዲሠየም ከተፈቀደለት በኋላ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደገና በሞት ወይም በፅኑ እስራት እንዲቀጣ የመጨረሻ ፍርድ ተወስኖበት እንደሆነ የተፈቀደለት መሠየም ይሠረዛል፤ እንዲሁም ዳግመኛ እንዲሠየም ሊፈቀድለት አይቻልም::

ሁለተኛ ታላቅ ክፍል

ልዩ ክፍል

ሦስተኛ መጽሐፍ

በመንግሥት፣ በአገርና በዓለም አቀፍ ጥቅሞች ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

ርዕስ አንድ

በመንግሥት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

BACK



## ምዕራፍ አንድ

## በአገር ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

## ክፍል አንድ

## በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትና በአገር የውስጥ ደህንነት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

## ንዑስ ክፍል አንድ

## በሕገ መንግሥቱና በመንግሥት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፪፻፴፰ በሕገ መንግሥትና በሕገ መንግሥት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ወንጀል

፩ ማንም ሰው በኃይል፣ በዛቻ፣ በአድማ ወይም ሕገወጥ በሆነ በማናቸውም መንገድ አስቦ:-

ሀ/ የፌዴራሉን ወይም የክልልን ሕገ መንግሥት ያፈረሰ፣ የለወጠ ወይም ያገደ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በፌዴራሉ ወይም በክልል ሕገ መንግሥት የተቋቋመውን ሥርዓት ያፈረሰ ወይም የለወጠ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ ሲፈፀም በሕዝብ ደህንነት ወይም ኑሮ ላይ ከፍተኛ ቀውስ ደርሶ እንደሆነ፤ አድራጊው በዕድሜ ልክ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል::

### አንቀጽ ፪፻፴፱ የሕገ መንግሥታዊ ሥልጣንን ተግባራዊነት ማሰናከል

ማንም ሰው በኃይል ሥራ፣ በዛቻ ወይም ሕገወጥ በሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ በፌዴራል ወይም በክልል ሕገ መንግሥት ሥልጣን የተሰጠው አካል ወይም ባለሥልጣን

BACK



ተግባሩን እንዳያከናውን ያደናቀፈ፣ የከለከለ ወይም አስገድዶ ውሣኔ እንዲሰጥ ያደረገ እንደሆነ፣

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፪፻፴ የጦር መሣሪያ ይዞ በማመፅ፣ ወይም የእርስ በርስ ጦርነት በማስነሣት በመንግሥት ላይ የሚደረግ ወንጀል</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ በሕገ መንግሥት በተቋቋሙት አካላት ወይም ባለሥልጣኖች ላይ ሕዝብ፣ ወታደሮች ወይም ሽፍቶች የትጥቅ አመፅ እንዲያነሱ ያደራጀ ወይም የመራ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ ዜጐችን ወይም በአገር ነዋሪ የሆኑትን በማስታጠቅ ወይም አንዱ ወገን በሌላው ላይ የጦር መሣሪያ እንዲያነሳ በማነሳሳት የእርስ በእርስ ጦርነት እንዲነሳ ያደረገ እንደሆነ፣

ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት ይቀጣል::

፪ ድርጊቱ በሕዝብ ደህንነት ወይም ኑሮ ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከተለ እንደሆነ፣ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ያስቀጣል::

፫ ማንም ሰው በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ሁኔታ በተደራጀ ወይም በተነሳሳ እንቅስቃሴ በራሱ ፈቃድ ተካፋይ እንደሆነ፣

ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት ይቀጣል::

BACK



፬ አደራጁ ወይም ተካፋዩ በሰው ሕይወት፣ ነፃነት፣ አካል፣ ጤና ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱ ወይም ሌላ ወንጀል መፈፀሙ የተረጋገጠበት ሲሆን ለዚሁ ወንጀል አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት በተጨማሪ ተጠያቂ ይሆናል::

## አንቀጽ ፪፻፵፩ የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል

ማንም ሰው በኃይል ወይም በሌላ ማናቸውም ሕገ መንግሥትን የሚፃረር መንገድ፣ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር፣ ያገሪቱ ሕዝቦች አንድነት እንዲፈርስ ወይም ፌዴሬሽኑ እንዲከፋፈል፣ ወይም ከፌዴሬሽኑ ግዛት ወይም ሕዝብ ከፊሉ እንዲገነጠል የሚያደርግ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፵፪ የአገሪቱን የግዛት ወይም የፖለቲካ ሉአላዊነት በመጣስ የሚደረግ ወንጀል

ማንም ሰው የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆችን፣ ደንቦችን ወይም ስምምነቶችን ወይም የአገሪቱን ሕግ በመጣስ:-

ሀ/ ለሕዝብ ደህንነት አስጊ የሆነ ተግባር ለመፈፀም ወደ አገሪቱ ግዛት የገባ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የኢትዮጵያ ሥልጣን በሆነው ተግባር ውስጥ በተለይም የምርመራ፣ የብርበራ ወይም የፍርድ አሠራር በሆነው ሥራ ውስጥ ገብቶ ለውጭ አገር መንግሥት ወይም ድርጅት ሲሠራ የተገኘ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፵፫ በሕገወጥ መንገድ ከአገር መውጣት፣ ወደአገር መግባት ወይም በአገሪቱ ውስጥ መኖር

፩ ማንም ሰው እስበ:-

ሀ/ የመንግሥቱን ሕግ በመጣስ ከአገር የወጣ፣ ወደአገሪቱ ግዛት የገባ ወይም በአገሪቱ ውስጥ የኖረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ከላይ በፊደል (ሀ) ከተዘረዘሩት ድርጊቶች አንዱ እንዲፈፀም ያደረገ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሕገ ወጥ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ ነዋሪ ያልሆነን ወይም ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለውን ሰው ወደ ሌላ አገር ግዛት እንዲገባ ያደረገ ከሆነ፣ ወይም በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የሚያስችል የተጭበረበረ የጉዞ ሰነድ ወይም መታወቂያ እንዲዘጋጅ ያደረገ፣ ያቀረበ ወይም ይዞ የተገኘ እንደሆነ፤ ወይም ግለሰቡ ሕግ የሚጠይቀውን ሥርዓት ሳያሟላ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ ማናቸውንም ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል:

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተፈጸመ ወንጀል የስደተኛው ሕይወት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ

ወድቆ እንደሆነ ወይም ኢ-ሠብአዊና ጭካኔ ለተሞላበት አያያዝ ተዳርጐ እንደሆነ፣ ወንጀሉን ያደረገው ሰው ከአምስት ዓመት እስከ አሥር አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

፬ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) ከተዘረዘሩት ድርጊቶች አንዱ እንዲፈፀም የረዳው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ፤ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል::

፭ ድርጊቱ ግልፅ የሆነ የደንብ እልፌት ተግባር ሲሆን ስለዚሁ ጉዳይ የተደነገገው ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል::

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## አገርን መድፈር

### አንቀጽ ፪፻፵፬ የአገሪቱን መንግሥት እንዲሁም ያገሪቱን ምልክቶችና በመንግሥት የታወቁ ሌሎች ምልክቶችን መድፈር

፩ ማንም ሰው በንግግር ወይም በአድራጐት ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን በአደባባይ የአገሪቱን መንግሥት ያዋረደ፣ የሰደበ፣ ስሙን ያጠፋ ወይም በሀሰት የወነጀለ እንደሆነ፤

ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማያንስ መቀጮ ይቀጣል::

የስም ማጥፋት፣ በሀሰት የመወንጀል፣ የማዋረድ ወይም የመስደብ ድርጊት ተፈፅሟል የሚባለው በአንቀጽ ፮፻፲፫ እና በአንቀጽ ፮፻፲፭ መሠረት ነው::

፪ ማንም ሰው በተንኮል፣ በንቀት ወይም ይህን በመሳሰለ በማናቸውም አሳብ በግልጽ የታወቀውን አንድ የአገር ምልክት ማለትም የፌዴራላዊት ኢትዮጵያ ሰንደቅ

BACK


ዓላማን ወይም አርማን እንዲሁም የክልላዊ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማን ወይም አርማን በአደባባይ የቀደደ፣ ያቃጠለ፣ ያጠፋ፣ የደፈረ፣ ያበላሸ፣ የሰደበ ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያዋረደ እንደሆነ፤

ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፵፭ በታወቁ ምልክቶች ያለአግባብ መገልገል

ማንም ሰው ለማናቸውም አገልግሎት ጉዳይ ቢሆን በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፪፻፵፬ በተገለጹት ሰንደቅ ዓላማዎች ወይም ምልክቶች በሕግ ከተፈቀደው ውጭ የተገለገለ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

## ክፍል ሁለት

## በመንግሥት የውጭ ደህንነት እና በመከላከያ ኃይል ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

## አንቀጽ ፪፻፵፮ በአገር ነፃነት ላይ የሚደረግ ወንጀል

ማንም ሰው:-

ሀ/ የአገሪቱን ነፃነት አደጋ ላይ ለመጣል ወይም አገሪቱ ሉአላዊነቷን እንድታጣ፤

ለ/ የአገሪቱን ነፃነት አደጋ ላይ ለመጣል የውጭ መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ለመገፋፋት፤ ወይም

ሐ/ የውጭ መንግሥት የጠላትነት ድርጊት በአገሪቱ ላይ እንዲፈጽም ወይም አገሪቱ ከውጭ አገር መንግሥት ጋር ጦርነት እንድትዋጋ ወይም የጠላትነት ድርጊት እንዲፈፀምባት፣ በጠላትነት እንድትከበብ ወይም እንድትያዝ፣

BACK



በማሰብ ማናቸውንም ድርጊት ያደረገ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፵፯ የአገር መከላከያ ኃይልን መጉዳት

ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ ወታደራዊ ጠባይ ያለውን ወይም ለአገር መከላከያ እንዲሆን የታቀደውን ማናቸውንም የኢኮኖሚ ድርጅት፣ የመከላከያ ሥራ ተቋም ወይም ሥፍራ፣ የመገናኛ ወይም የመጓጓዣ ዘዴ፣ ሥራ፣ ማከማቻ፣ የጦር መሣሪያ ወይም ቁሳቁስ ያለአግባብ አሳልፎ በመስጠት፣ በማፍረስ፣ የተንኮል ሥራ በመፈጸም ወይም ለአገልግሎት እንዳይውል በማድረግ፣

ለ/ ጠላት ለሆነ ለውጭ አገር መንግሥት ወታደሮች በማቅረብ፣ ወይም የኢትዮጵያ ዜጐች ለዚሁ ለጠላት አገር በወታደርነት እንዲያገለግሉ በመመልመል ወይም በማግባባት፣ ወይም ራሱ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለዚሁ ዓይነት የጠላት አገር መንግሥት በመሰለፍ፣

ሐ/ የጦር ወታደሩ የጦር አገልግሎቱን ከመፈጸም እምቢተኛ እንዲሆን፣ ወታደራዊ አመጽ እንዲያስነሳ ወይም እንዲከዳ በግልጽ በማነሳሳት፣ ወይም የጦር ወታደርነት ግዴታ ያለበት ሰው ከነዚህ ወንጀሎች አንደኛውን እንዲፈጽም በማደፋፈር ወይም እንዲነሳሳ በማድረግ፣ ወይም

BACK



መ/ ለአገር መከላከያ የሚያገለግሉትን ወታደራዊ የጥንቃቄ እርምጃዎችን በማሰናከል፣ በማበላሸት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ የተንኮል ድርጊት በመፈጸም፣

በኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ በሆነ ጊዜ፣ በተለይም በጦርነት ወይም ጦር አስጊ በሆነበት ጊዜ እንደሆነ፤ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል::

አንቀጽ ፪፻፵፰ ከፍ ያለ ክዳት

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ወይም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም እንዲያስከብር በግልጽ አደራ የተጣለበት ሰው:-

ሀ/ የጦር መሣሪያ በመያዝ ወይም በጸብ ድርጊት ኢትዮጵያን የተቃወመ እንደሆነ፤

ለ/ ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት ከሚያደርግ ኃይል ጋር ወይም ለዚሁ ኃይል ጥቅም ከሚሠራ ሰው ወይም ድርጅት ጋር በመተባበር ወይም ምስጢራዊ ግንኙነት በማድረግ ይኸው ኃይል እንዲመቸውና እንዲቀናው በማናቸውም አኳኋን የረዳ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ዕቃዎችን፣ የጦር መሣሪያዎችን፣ ፕላኖችን፣ ማስረጃ የሚሆኑ ጽሁፎችን ወይም ለአገሩ መከላከያ የሚያገለግሉትን ማንኛዎቹንም ነገሮች በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ለጠላት አሳልፎ በመስጠት ወይም በአገልግሎቶችና ይህን የመሳሰሉ ዕቃዎችን ለጠላት በማቅረብ ጠላትን የደገፈ እንደሆነ፤

BACK



ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፪፻፵፱ ክዳት

፩ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ወይም የኢትዮጵያን ጥቅም እንዲያስከብር በግልጽ አደራ የተጣለበት ሰው አስቦ:-

ሀ/ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ በምስጢር እንዲጠበቅና እንዳይገለጽ የተደረገውን ምስጢር፣ ሰነድ፣ የመላላክ ጉዳይ ወይም አንድ ውሣኔ ለሕዝብ ወይም ለውጭ አገር መንግሥት፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ሌላ ድርጅት ወይም ወኪል የገለጸ፣ አሳልፎ የሰጠ፣ ወሬውን ያስተላለፈ፣ ወይም በግልጽ እንዲነገር ያደረገ እንደሆነ፤

ለ/ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ወይም መልዕክተኛ ሆኖ ከውጭ አገር መንግሥት ጋር እንዲፈጽም የተላከበትን ወይም ለኢትዮጵያ ጥቅም ሊከራከርበትና ሊፈጽም የሚገባውን ጉዳይ ግልጽ በሆነ ዓይነት እንዲሰናከል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ የኢትዮጵያን ደህንነት፣ ነፃነት ወይም ዋነኛ ጥቅሞች የሚመለከቱትን ሰነዶች፣ ጽሁፎች፣ ወይም ማስረጃዎች ያበላሸ፣ ያጠፋ፣ የደበቀ፣ እንዲጠፉ ያደረገ፣ ወይም ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪ አድራጎቱ የኢትዮጵያን ሕልውና ወይም ነፃነት በቀጥታ ከባድ አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ፍርድ ቤቱ

BACK



ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ሊወሰን ይችላል::

፫ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈጸመው በቸልተኛነት ከሆነ ቅጣቱ ከስድስት ወር ያላነሰ ቀላል እስራት ሆኖ እንደነገሩ ከባድነት እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ከፍ ሊል ይችላል::

<u>አንቀጽ ፪፻፶ የኢኮኖሚ ክዳት</u>

፩ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም የኢትዮጵያን ጥቅም እንዲያስከብር በግልጽ አደራ የተጣለበት ሰው አስቦ:-

ሀ/ ስለኢትዮጵያ ወይም ስለመከላከያ ኃይል ከፍተኛ ጥቅም ሲባል በምስጢር የሚጠበቀውን ኢኮኖሚያዊ ጠባይ ያለውን የመላላክ ግንኙነት፣ ውሣኔ፣ የተደረገ ነገር ወይም ሰነድ ለሕዝብ ወይም ለውጭ አገር ሰው የገለጸ፣ አሳልፎ የሰጠ፣ ይዘቱን ያስተላለፈ፣ ወይም እነዚሁ እንዲያገኙት ያደረገ እንደሆነ፤

ለ/ እንዲጠብቃቸው በኃላፊነት የተሰጡትን ዕቃዎች፣ መሣሪያዎች ወይም እነዚህን የመሳሰሉትን ሌሎች ነገሮች የገለጸ ወይም አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት የሚያደርግ መንግሥት ባወጣው ብድር ጉዳይ የተካፈለ ወይም ለብድሩ የሚውል ገንዘብ ወይም ንብረት ያዋጣ እንደሆነ፤

ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል:: ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ጽኑ እስራቱ እስከ ሃያ ዓመት ሊደርስ ይችላል::

፪ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈጸመው በቸልተኛነት ከሆነ ከሶስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፪፻፵፰ ከጠላት ጋር መተባበር

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ወይም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም እንዲያስከብር በግልጽ አደራ የተጣለበት ሰው ኢትዮጵያ በጦርነት ላይ በምትገኝበት ጊዜ ወይም ግዛቷ በሙሉ ወይም በከፊል በጠላት በተወረረበት ጊዜ የጠላትን ዓላማ ለማሳካት በማሰብ በምክርም ሆነ በተግባር ጠላትን የደገፈ እንደሆነ፣ በተለይም፡-

ሀ/ በጠላት ስም የሲቪል ወይም የአስተዳደር ሥራ በፍርድ፣ በፖሊስ፣ በእሥር ቤት፣ በዘብ ጥበቃ፣ በትራንስፖርት ወይም በሌላ እነዚህን በመሳሰሉ ክፍሎች ያከናወነ፣ ወይም

ለ/ ከጠላት ቁጥጥር ለማምለጥ የሚፈልጉትን የወገን ተዋጊዎች ወይም ስደተኞች ለጠላት ያጋለጠ ወይም አሳልፎ የሰጠ፣ ወይም

ሐ/ የጠላትን ወይም የወራሪን ጥቅም በሚያራምድ ፕሮፖጋንዳ፣ የፕሬስ ወይም ሌላ የመገናኛ ዘዴ ሥራ ውስጥ የተሳተፈ፣ ወይም

መ/ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በኢኮኖሚ ረገድ አብሮ የሠራ፣

እንደሆነ፣ ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል።

አንቀጽ ፪፻፶፪ ስለላ

፩ ማንም ሰው ለአንድ የውጭ አገር መንግሥት ወይም ለአንድ የውጭ አገር የፖለቲካ ድርጅት ወይም ለማናቸውም ሌላ የውጭ አገር ድርጅት ጥቅም ሲል በኢትዮጵያ፣ በተቋሞቿ፣ በድርጅቶቿ ወይም በዜጐቿ ላይ ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ፤

ሀ/ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲ፣ የወታደራዊ ወይም የኢኮኖሚ ስለላ ሥራ አገልግሎት ያደራጀ፣ በዚሁ ሥራ ተካፋይ የሆነ ወይም የደገፈ ወይም ለዚሁ አገልግሎት ሌላውን የመለመለ ወይም የቀጠረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ለዚሁ ስለላ የሚያገለግል መረጃ የሰበሰበ፣ ያስተላለፈ፣ ወይም እንዲገኝ ያደረገ ወይም በምስጢር የሚጠበቀውንና በሕዝብ በይፋ የማይታወቀውን መረጃ በመንግሥት ወይም በግል ለተቋቋሙ መሥሪያ ቤቶች ወይም ወኪሎቻቸው እንዲገለጽ ያደረገ እንደሆነ፤

ስለላው የተደረገው በመንግሥት ላይ ወይም በሕዝብ ጥቅም ላይ ጉዳት በሚያመጣ ሁኔታ እንደሆነ፤ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል:: ስለላው ጉዳት ያደረሰው የግል በሆነ ሰው ወይም በግል ማህበር ላይ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

፪ የመንግሥቱን የውስጥና የውጭ ጸጥታ በቀጥታ በመጉዳት የተደረገ ስለላ በሆነ ጊዜ፤ ቅጣቱ ከሃያ ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል:: ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜና ይልቁንም በጦርነት ጊዜ ወይም ጦርነት በሚያስጋበት ጊዜ፣ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማቲክ ወይም የወታደር ስለላ ተደርጐ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ሊወስን ይችላል:: ስለላው

BACK



የተደረገው የኢትዮጵያ ሕልውና በአስጊ ሁኔታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ፣ የሞት ቅጣት ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ ፪፻፶፫ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ለጦር ጓደኞች መንግሥታት ተፈፃሚ መሆናቸው

በዚህ ክፍል ውስጥ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንደኛው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የጦር ጓደኛ በሆኑ ወይም በሚተባበሩ መንግሥታት ላይ ጉዳት ለማድረስ ተደርጎ እንደሆነ በዚህ ክፍል የተመለከቱት ቅጣቶች ይፈጸማሉ፡፡ ይህም የሚፈጸመው ተመሳሳይ ድንጋጌ ላለው መንግሥት ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## የወል ድንጋጌዎች

## አንቀጽ ፪፻፶፬ በተዘዋዋሪ መንገድ መርዳትና ማበረታታት

፩ ማንም ሰው በአገሪቱ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት፣ የፖለቲካና የግዛት ሉዓላዊነት፣ የመከላከያ ኃይል ወይም የውስጥና የውጭ ደህንነት ላይ ወንጀል የተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የተሞከረ መሆኑን ወይም ወንጀል እንዲፈፀም የመሠናዳት ተግባር መከናወኑን እያወቀ ለባለሥልጣን ሳያስታውቅ የቀረ ወይም አደጋው እንዳይደርስ ወይም አድራጊው እንዲያዝ የሚቻለውን ያላደረገ እንደሆነ፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም ግልፅ በሆነ ምክንያት ለማስታወቅ አለመቻሉን ካላስረዳ በስተቀር፣

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የአገሪቱ የውስጥ ወይም የውጭ ደህንነት በአስጊ ሁኔታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ፣

ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ነው፡፡

፫ እነዚህ ሁኔታዎች ባጋጠሙ ጊዜ ለባለሥልጣን ማስታወቅ ካለበት ግዴታ ውጭ ለመሆን ሲል አድራጊው የሠራውን ወይም የሙያውን ምስጢር ምክንያት ለማድረግ አይችልም::

፬ ከጥፋተኛው ጋር ያለው የዝምድና ወይም የጠበቀ የወዳጅነት ግንኙነት ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ጉዳዮች እንደመከላከያ ምክንያት ሊሆን አይችልም /አንቀጽ ፲፫ ::

## <u>አንቀጽ ፪፻፶፮ ለወንጀል ስራ ማነሣሣትና አባሪነት፣ የማነሳሳትና የአባሪነት ሙከራ</u>

ከዚህ በላይ ከአንቀጽ ፪፻፴፰ እስከ ፪፻፵፪፣ ከአንቀጽ ፪፻፵፮ እስከ ፪፻፶፪ ድረስ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱ ሳይሞከር በቀረበት ጊዜ ወንጀሉ እንዲፈፀም የተደረገ የወንጀል ሥራ ማነሳሳት ሙከራ /አንቀጽ ፴፮/፪/፣ አባሪነት /አንቀጽ ፴፯/፫/፣ የአባሪነት ወይም የማነሣሣት ሙከራ /አንቀጽ ፳፯/፪/፣

ከአንድ ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እስራት፤ ወይም ይህ አድራጐት ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ በተለይ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ፤ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ያስቀጣል::

## <u>አንቀጽ ፪፻፶፯ የተንኰል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ ዓይነት ማሰናዳት</u>

ማንም ሰው ከዚህ በላይ ከአንቀጽ ፪፻፴፰ እስከ ፪፻፵፪፣ ከአንቀጽ ፪፻፵፮ እስከ ፪፻፶፪ ድረስ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱን ለመፈፀም:-

ሀ/ ወታደሮችን፣ የሽምቅ ተዋጊዎችን፣ ሽፍቶችን ወይም ቅጥረኞችን የመለመለ፣

ያቋቋመ ወይም ወደ አገር ውስጥ ያስገባ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ የጦር መሣሪያዎችን፣ ጥይቶችን፣ ስንቅን፣ ገንዘብን ወይም እነዚህን የመሳሰሉትን ግዙፍ የሆኑ ነገሮችን ያዘጋጀ፣ ያከማቸ ወይም ወደ አገር ያስገባ እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፪፻፶፯ መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር</u>

ማንም ሰው ከዚህ በላይ ከአንቀጽ ፪፻፴፰ እስከ ፪፻፵፪፣ ከአንቀጽ ፪፻፵፬ እስከ ፪፻፶፪ ድረስ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱ እንዲፈጸም ለማድረግ ወይም ለመደገፍ:-

ሀ/ በንግግር፣ በሥዕል ወይም በጽሁፍ አማካይነት በግልፅ የቀሰቀሰ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ሽፍቶች በአገር ውስጥ ወይም ከአገር ውጭም ቢሆን እንዲቋቋሙ ያደመ፣ እቅድ ያወጣ ወይም የገፋፋ እንደሆነ ፤ ወይም

ሐ/ እንደዚህ በመሳሰሉት ሽፍቶች ቡድን የገባ፣ በእቅዱም የተባበረ፣ ወይም ትዕዛዙን የተከተለ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ ከውጭ አገር መንግሥታት፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ ድርጅት ወይም ከእነዚሁ ወኪሎች ጋር ግንኙነት ያደረገ ወይም በምስጢር ግንኙነት የተባበረ እንደሆነ፤ ወይም

ሠ/ የሕዝቡን ሞራል ዝቅ ለማድረግና እምነቱን ወይም የመቋቋም ኃይሉን ለማፍረስ በማቀድ በተቀናጀ ዘዴ

BACK



ትክክለኛ ያልሆነ፣ ጥላቻ የተሞላበት ወይም ያለውን አቋም የሚያፈርስ መረጃ በንግግር፣ በጽሁፍ ወይም በስዕል የበተነ ወይም ያስታወቀ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት፤ ወይም ይህ አድራጎት ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ በተለይ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፪፻፶፰ ከባድ ሁኔታ</u>

በዚህ ምዕራፍ ወንጀሉ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት እንደሚያስቀጣ ሕጉ በደነገገባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ፍርድ ቤቱ የሞት ቅጣትን የሚወስነው:-

ሀ/ ወንጀሉ የተፈጸመው በአገሩ ላይ ሁከት በደረሰ ጊዜ ወይም ይኸው ሁከት ወይም የእርስ በርስ ጦርነት ወይም ከውጭ አገር ጋር የሚደረግ ጦርነት በሚያሠጋበት ጊዜ፣ ወይም የውጭ መንግሥት ጣልቃ ገብነት በሚኖርበት ጊዜ፣ ወይም በጸጥታ መታወክ የአስቸኳይ ሁኔታ አዋጅ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ፣ ወይም ልዩ ሁኔታዎች መኖራቸው በግልጽ በተነገረ ጊዜ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ አድራጎቶቹ የታቀዱትና የተፈጸሙት ከአድማ የተነሳ እንደሆነ ወይም የጦር መሣሪያ በያዙ ክፍሎች እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ወንጀለኛው ከውጭ አገር ወይም ከውጭ መንግሥት የፖለቲካ ወይም ሌላ ድርጅት ባገኘው ሀብት፣ የጦር መሣሪያ ወይም በማናቸውም አኳኋን በሚያገኘው ዕርዳታ ወይም ድጋፍ ወንጀሉን ፈጽሞ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ በቦንብ፣ በድማሚት ወይም በሌላ በማናቸውም በሚፈነዳ መሣሪያ ወይም በብዙ ሰው ላይ አደጋ

BACK



ሊያደርስ በሚችል ይህንኑ በመሰለ የማሸበሪያ መሣሪያ ወይም ዘዴ ወንጀሉን ሰርቶት እንደሆነ፣ ነው::

## አንቀጽ ፪፻፶፱ ተጨማሪ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች

፩ በዚህ ምዕራፍ የተመለከተው ማናቸውም በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል የተፈጸመው በተሾመ ወይም የመሪነት ሥልጣን በተሰጠው ሰው ወይም የግል ጥቅም ለማግኘት በመፈለግ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ከዚሁ ቅጣት ጋር በማጣመር ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ሊወስን ይችላል::

፪ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ጥፋተኛ አምስት ዓመት ወይም ከዛ በላይ የሆነ ጽኑ እስራት ከተፈረደበት፣ ቅጣቱን ከጨረሰ በኋላ ካገር እንዲወጣ ይወሰንበታል::

፫ የከዳት፣ የስለላ ወይም ምስጢር አሳልፎ የመስጠት ወንጀል ተፈጽሞ በተገኘ ጊዜ ሁሉ የወንጀሉ መፈጸሚያ የሆኑት ወይም ይህንኑ ጉዳይ የሚመለከቱት መሣሪያዎች፣ ዕቃዎች፣ የመልእክት ደብዳቤዎች ወይም ማስረጃዎች ሁሉ ይወረሳሉ::

## አንቀጽ ፪፻፷ ንብረትን መውረስ

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም እንዲያስከብር በግልፅ አደራ የተጣለበት ሰው በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፪፻፴፷፣ ፪፻፴ እና ፪፻፴፩፣ ፪፻፴፯ እስከ ፪፻፶፩ እና ፪፻፶፪(፪) ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱን በመፈፀም ጥፋተኛ ሆኖ የተፈረደበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከሚፈርደው ከዋናው ቅጣት ጋር አጣምሮ የተፈረደበት ሰው ንብረት በሕግ መሠረት እንዲወረስ ለማዘዝ ይችላል /አንቀጽ ፺፰/::

## ምዕራፍ ሁለት

## በውጭ አገር መንግሥት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፪፻፷፩ በውጭ አገር መንግሥት ላይ የሚደረግ የተቃዋሚነት ድርጊት

ማንም ሰው በኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ውስጥ ሆኖ የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ አገር መንግሥት ጋር ያለውን ሰላማዊ ግንኙነት ለማበላሸት በሚችል አኳኋን፡-

ሀ/ በተንኮል ሥራ፣ በሐሰት ውንጀላ፣ በጥላቻ ስብከት፣ ወይም በኃይል ሥራ የውጭ አገር መንግሥት ውስጣዊ የፖለቲካ ሥራ ወይም የውስጥ ፀጥታ እንዲናወጥ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሚዋጉ በውጭ አገር መንግሥታት ጦርነት ውስጥ ኢትዮጵያ የማትገባ ስለመሆኑዋ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ በሚገባ የታወጀውን ወይም በሌላ ዓይነት ውሣኔ በመንግሥት የተገለጸውን ድንጋጌ የጣሰ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ጦርነት በሚያደርግ የውጭ አገር መንግሥት ላይ የጠላትነት ድርጊት የገፋፋ፣ እንዲፈፀም የተስማማ ወይም ያበረታታ እንደሆነ፤

ቢያንስ በሦስት ወር ቀላል እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ እንደሆነ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

### አንቀጽ ፪፻፷፪ በውጭ አገር መንግሥታት መሪዎች፣ መልዕክተኞች እና ሌሎች በአለም አቀፍ ሕግ ጥበቃ ባገኙ ሰዎች ላይ የሚፈጸም ወንጀል

፩ ማንም ሰው በኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ውስጥ በአንድ አገር መንግሥት ርዕሰ ብሔር፣ የመንግሥት መሪ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ መልዕክተኛ ወይም

BACK



ቤተሰቡ ወይም ተከታዩ ወይም በዓለም አቀፍ ድርጅት ተወካይ ወይም በዓለም አቀፍ ጥበቃ ባገኘ ሌላ ሰው አካል፣ ነፃነት ወይም ደህንነት ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም አደጋ የጣለ ወይም በሚሰራበት ተቋም፣ የግል ቤቱ ወይም ተሽከርካሪው ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም ከላይ የተመለከቱትን ተግባራት ለመፈጸም የዛተ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ ሲፈፀም ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ሰዎች የአንዱ ሕይወት አልፎ እንደሆነ ስለሰው መግደል የተደነገጉት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## አንቀጽ ፪፻፷፫ የውጭ አገር መንግሥትን ግዛት መጣስ

ማንም ሰው የዓለም አቀፍ ሕግን፣ በመጣስ ሕገወጥ ድርጊት ለመፈፀም፣ ሁከት ለማስነሳት ወይም አደገኛ የሆነ ድርጊት ለመፈፀም ሲል:-

ሀ/ ወደ ውጭ አገር መንግሥት ግዛት ውስጥ የገባ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በዚሁ መንግሥት ግዛት ውስጥ ሆኖ በዚሁ መንግሥት የሥልጣን ክልል ውስጥ የሚገኝ ተግባርን ያለአግባብ የፈፀመ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፷፬ የውጭ አገር መንግሥታትን ማዋረድ

፩ ማንም ሰው አንድን የውጭ አገር መንግሥት በቀጥታ ወይም መሪውን ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን

የዚህን የውጭ አገር መንግሥት የዲፕሎማቲክ አባል፣ ተጠሪ ወይም መልዕክተኛ የሆነውን በአደባባይ በንግግር ወይም በአድራጐት ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያዋረደ፣ የሰደበ፣ ስም ያጠፋ፣ ወይም በሐሰት የወነጀለ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በተለይም በሐሰት የመወንጀል ድርጊት ሲሆን እስራቱ ቢያንስ ሦስት ወር ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፪፻፷፬ የታወቁ የውጭ አገር ምልክቶችን ማዋረድ</u>

ማንም ሰው ከኢትዮጵያ ጋር ሰላማዊ የወዳጅነት ግንኙነት ያለውን የውጭ አገር መንግሥት የታወቁ የሉዓላዊነት ምልክቶች ይልቁንም የዚሁ አገር መንግሥት እንደራሴ የሚያውለበልበውን አርማ ወይም ሰንደቅ ዓላማ በፀብ ስሜት፣ በጥላቻ መንፈስ፣ በንቀት፣ ወይም ይህን በመሳሰለ በማናቸውም ስሜት የቀደደ፣ ያቃጠለ፣ ያጠፋ፣ ያበላሸ፣ የሰደበ ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያዋረደ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፪፻፷፭ በመንግሥታት መካከል የተቋቋሙ ድርጅቶችን ማዋረድ</u>

ማንም ሰው በመንግሥታት መካከል የተቋቋመውንና ኢትዮጵያ አባል የሆነችበትን ተቋም ወይም ድርጅት ወኪል ወይም የታወቀውን ምልክቱን በአደባባይ ያዋረደ እንደሆነ፤ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፪፻፷፬ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፷፯ የውለታ መመለስ ሁኔታ

በዚህ ምዕራፍ በውጭ አገር መንግሥታት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎችን በተመለከተ የተደነገጉት በጠቅላላ ተፈጻሚ የሚሆኑት በሕጎቻቸው ለኢትዮጵያ ተመሣሣይ ጥበቃ ለሚሰጡ መንግሥታት ብቻ ነው::

ከላይ የተፃፈው ድንጋጌ ቢኖርም የአንቀጽ ፪፻፶፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ነው::

## አንቀጽ ፪፻፷፰ የክስ አቀራረብ

በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት ወንጀሎች ክስ የሚቀርበው ተበደልኩ የሚለው መንግሥት ወይም ድርጅት ወንጀለኛው እንዲቀጣለት ሲጠይቅና የፌዴራሉ የፍትህ ሚኒስትር ወይም ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሲፈቅድ ብቻ ነው::

## ርዕስ ሁለት

## ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ምዕራፍ አንድ

## መሠረታውያን ወንጀሎች

## አንቀጽ ፪፻፷፱ ዘርን ማጥፋት

ማንም ሰው በሠላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጐሣ፣ በዘር፣ በዜግነት፣ በቀለም፣ በሃይማኖት ወይም በፖለቲካ አንድ የሆነን ቡድን በሙላ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ የጥፋቱን ድርጊት በማደራጀት፣ ትዕዛዝ በመስጠት ወይም ድርጊቱን በመፈፀም:-

ሀ/ በማናቸውም ሁኔታ የማኅበረሰቡን አባሎች የገደለ፣ አካላዊ ወይም ኅሊናዊ ጤንነት የጐዳ፣ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፤ ወይም

BACK



ለ/ የማኅበረሰቡ አባላት በዘር እንዳይራቡ ወይም በሕይወት እንዳይኖሩ ለማድረግ ማናቸውንም ዘዴ በሥራ ላይ ያዋለ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ የማህበረሰቡን አባላት ወይም ሕፃናት በግዴታ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ያዛወረ ወይም የበተነ ወይም ሊሞቱ ወይም ሊጠፉ በሚችሉበት የኑሮ ሁኔታ እንዲኖሩ ያደረገ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት፤ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፸ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የሚፈፀም የጦርነት ወንጀል

ማንም ሰው በጦርነት፣ በጦርነት ግጭት፣ ወይም በጠላት ወረራ ጊዜ የዓለም አቀፍ ሕግ ድንጋጌዎችንና የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕጋጋትን በመጣስ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ጉዳት ለማድረስ በማደራጀት፣ በማዘዝ ወይም ድርጊቱን በመፈጸም፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ:-

ሀ/ ሰውን የገደለ፣ ያሰቃየ፣ ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ ያጉላላ፣ ስነ-ሕይወታዊ ሙከራዎችን ያደረገ፣ በሰው አካል፣ አእምሮ ወይም ጤንነት ላይ ከባድ ስቃይ ወይም ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ሌሎች ድርጊቶችን ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ገንዘብ ዋጋ እንዳያገኝ ዋጋውን ዝቅ አድርጎ በማክሰር፣ ሐሰተኛ ገንዘብ በማተም፣ ወይም በተደራጀ ዕቅድ ገንዘብን በማዋረድ ወይም በማናቸውም ሁኔታ አስቦ ሕዝብን ለረሀብ የዳረገ፣ በችግር ላይ የጣለ ወይም በአጠቃላይ የሕዝቡን ኑሮ ያናጋ እንደሆነ፤ ወይም

BACK



ሐ/ ሕዝብን በኃይል ከሥፍራው እንዲፈናቀል ወይም እንዲበተን ያደረገ፣ በተደራጀ ዕቅድ ከአገር ያስወጣ፣ ወይም ወደ አንድ የግዞት ሥፍራ ወይም የግዴታ ሥራ ማከናወኛ ሥፍራ በመላክ እንዲታሰር ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ በጠላት የስለላ አገልግሎት፣ የጦር ኃይል ወይም የአስተዳደር ሥራ ውስጥ ተመልምሎ እንዲያገለግል ያስገደደ እንደሆነ፤ ወይም

ሠ/ በግዴታ ዜግነቱን እንዲያጣ ወይም ኃይማኖቱን እንዲለውጥ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ረ/ የዝሙት አዳሪነት፣ የብልግና ድርጊት ወይም የግብረ ሥጋ ድፍረት ተግባር እንዲፈጸም ያስገደደ እንደሆነ፤ ወይም

ሰ/ የማስፈራራት ወይም የማሸበር ድርጊት ያደረገ፣ በወጀ /በመያዣነት/ ያገተ ወይም የጅምላ ቅጣት የጣለ ወይም የበቀል ድርጊት ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ሸ/ ንብረትን የወረሰ፣ ያወደመ ወይም ለራሱ ያደረገ፣ ሕገወጥ ወይም ተገቢ ያልሆነ ግብር ወይም ቀረጥ የጣለ እንደሆነ፤ ወይም ለወታደራዊ አገልግሎት ፍጹም አስፈላጊ ከሆነው በላይ ቀረጥና ግብር እንዲከፈል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ቀ/ ምግብን፣ ለምግብ ማምረቻ የሚውሉ የእርሻ ቦታዎችን፣ ሰብልን፣ የቤት እንስሳትን፣ የመጠጥ ውሃ አገልግሎቶችን፣ የመስኖ ሥራዎችን፣ የጤና ተቋማትን፣ ወይም ትምህርት ቤቶችን የወረሰ፣

BACK



ያፈረሰ፣ ያጠፋ፣ ከጥቅም ውጭ እንዲሆኑ ያደረገ ወይም ለእራሱ እንዲሆኑ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

በ/ ታሪካዊ ሀውልቶችን፣ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን ወይም የማምለኪያ ቦታዎችን ያወደመ፣ የወሰደ፣ ከጥቅም ውጭ ያደረገ፣ ለእራሱ ያደረገ ወይም በእነዚህ ላይ የኃይል ተግባር ያደረገ ወይም እነዚህን ነገሮች ለወታደራዊ ዓላማ ያዋለ እንደሆነ፤ ወይም

ተ/ አንደኛው ወገን በተቆጣጠረው ሥፍራ ላይ ለሚኖሩ ሰላማዊ ሰዎች አልባሣትን፣ መኝታ፣ መጠለያ፣ የሕክምና መድኃኒትና መገልገያ ወይም ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ያላቀረበ፤ እንዲቀርብላቸው ያላደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ቸ/ ግጭት ከመፈጠሩ በፊት በተሰደዱበት ወይም ኗሪ በሆኑበት አገር ሕግ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት እንደ ስደተኛ ወይም ዜግነት እንደሌላቸው የሚታወቁ ሰዎችን ያጠቃ፣ ያፈናቀለ፣ እንዲጠፉ ያደረገ ወይም በአግባቡ ያልያዘ እንደሆነ፤ ወይም

ኀ/ ዕድሜያቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን በጦርነት ውስጥ እንዲሣተፉ ለማድረግ ለወታደራዊ አገልግሎት አባልነት የመለመለ እንደሆነ፤ ወይም

ነ/ በተፈጥሮ አካባቢ ላይ የተስፋፋ እና ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ በሚችል መሣሪያ ወይም የውጊያ ስልት የተጠቀመ፣ በዚሁም ምክንያት የአካባቢውን ነዋሪ ጤና እንዲታወክ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ኘ/ አደገኛ የሆነ ኃይል እንዲለቀቅ በሚያደርግና በዚሁም የተነሳ በሰላማዊ ነዋሪ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ በሚችል ሁኔታ ግድቦችን እና

BACK



የኒውክሊየር የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ ጣቢያዎችን ያጠፋ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሕግ ከተቋቋሙና ለፍርድ ሂደት ዋስትና ከሚሰጡ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ ቅጣትን የወሰነ እና ያስፈፀመ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፪፻፸፩ በቁስለኞች፣ በበሽተኞች፣ በባሕር ወይም በአየር አደጋ ላይ ባሉ ሰዎች ወይም በጤና አገልግሎት ላይ የሚፈፀም የጦርነት ወንጀል</u>

፩ ማንም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ:-

ሀ/ በቁስለኞች፣ በህመምተኞች፣ በባህር ወይም በአየር አደጋ ላይ ባሉ በህክምና ወይም በመጀመሪያ እርዳታ ሠራተኞች ላይ የግድያ፣ የማሰቃየት፣ በሁኔታዎች አስፈላጊ የሆነውን የጤና እርዳታን የመከልከል፣ ርህራሄ በሌለው ሁኔታ ሰውን የመበደል ድርጊት የፈፀመ፣ ወይም ማናቸውንም ሌላ የአካል ወይም የሕሊና ስቃይ እንዲደርስባቸው ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ለጤና ጥበቃ፣ ለእርዳታ መስጫ ክፍል ወይም ለመጓጓዣ የሚያገለግሉትን ዕቃዎች፣ መሥሪያ ቤት ወይም ግምጃ ቤት ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ወይም ያለአግባብ ወይም ለወታደራዊ አገልግሎት ፍፁም አስፈላጊ ሆኖ ከሚገኘው ውጭ ያፈረሰ፣ ከአገልግሎት ውጭ ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ፤ ወይም

BACK



ሐ/ የጤና አገልግሎት ሠራተኞች፣ የሀይማኖት አገልግሎት ሰጪዎችና ጋዜጠኞች የሞያ ሥነ ምግባር እና መመሪያ ከሚያዘው ውጭ እንዲሠሩ ወይም የሞያ ሥነ ምግባር እና መመሪያ በሚያዘው መሠረት እንዳይሠሩ ወይም ቁስለኞችን፣ በሽተኞችን፣ ወይም ሠላማዊ ሰዎችን ለመጠበቅ የወጡ ሌሎች መመሪያዎችን ወይም ደንቦችን ተላልፈው እንዲሠሩ ያስገደደ እንደሆነ፤

በአንቀጽ ፪፻፸ እንደተመለከተው ይቀጣል::

፪ በንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ:-

ሀ/ "ቁስለኛ" እና "ህመምተኛ" ማለት የመከላከያ ሠራዊት አባልም ይሁን ወይም ሰላማዊ ሰው በደረሰበት የመቁሰል አደጋ፣ በበሽታ ወይም በሌላ አካሉ ላይ በደረሰበት ጉዳት ወይም በአእምሮው ላይ በደረሰበት መረበሽና አለመረጋጋት ምክንያት ህክምና የሚያስፈልገው ሰው ሲሆን፣ አራሶችን፣ አዲስ የተወለዱ ህፃናትን እና እንደእርጉዝ ሴቶች የመሳሰሉትን አስቸኳይ የሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸውንና ከማናቸውም ዓይነት የጠላትነት እንቅስቃሴ ታቅበው የሚገኙትን ያጠቃልላል::

ለ/ "በባህር ወይም በአየር አደጋ ላይ ያለ" ማለት ወታደርም ሆነ ወይም ሰላማዊ ሰው በባህር ላይ ወይም በሌላ ውሀ ውስጥ ወይም በአየር ላይ ባጋጠመው ችግር ወይም አደጋ ምክንያት ህይወቱ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ያለና ከማናቸውም ዓይነት የጠላትነት እንቅስቃሴ የታቀበ ሰውን ሁሉ ያጠቃልላል::

## አንቀጽ ፪፻፸፪ በታሰሩ የጦር ምርኮኞች እና በተጋዙ ሰዎች ላይ የሚፈፀሙ የጦርነት ወንጀሎች

ማንም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ:-

ሀ/ በታሰሩ የጦር ምርኮኞች ወይም በተጋዙ ሰዎች ላይ የመግደል፣ የማሰቃየት ተግባር ወይም ከሰብዓዊ ርህራሄ ውጭ የሆነ የማጉላላት በደል እንዲፈጸምባቸው ያደራጀ፣ ያዘዘ ወይም ድርጊቱን የፈጸመ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በዚህ ሁኔታ የሚገኙ ሰዎች በጠላት የስለላ፣ የወታደራዊ ወይም የአስተዳደር ሥራ እንዲያገለግሉ ያስገደደ እንደሆነ፣

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪፻፸ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፸፫ በጦርነት ጊዜ የሚደረግ ገፈፋ፣ ዘረፋና የባህር ውንብድና

ማንም ሰው በጦርነት ጊዜ ለወታደራዊ አገልግሎት አስፈላጊ ነው በሚል ሰበብ የባሕር ወንበዴነትን፣ የዘረፋን፣ የገፋፊነትን ወይም ሕገ ወጥ የሆነ የንብረት ማፍረስን ወይም የመውሰድን ተግባር ያዘጋጀ፣ እንዲዘጋጅ ያዘዘ፣ ወይም ይህንኑ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፣

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪፻፸ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፸፬ መገፋፋትና ማሰናዳት

ማንም ሰው ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱን ለመፈጸም፣ እንዲፈጸም ለማድረግ ወይም አፈጻጸሙን ለመርዳት በማሰብ:-

BACK



ሀ/ በንግግር፣ በሥዕል፣ ወይም በጽሁፍ በአደባባይ የገፋፋ ወይም ያደፋፈረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ አንድ የወንበዴ ማህበር ወይም ቡድን እንዲቋቋም ከሌሎች ጋር
ያደመ፣ ዕቅድ ያወጣ ወይም እንዲቋቋም የገፋፋ ወይም ራሱ ያቋቋመ፣ በዚሁ ማህበር ወይም ቡድን ውስጥ የገባ፣ ዓላማውን የተከተለ ወይም ትዕዛዙን የፈፀመ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፪፻፰፰ ለጠላት ሊደረግ የሚገባውን ተግባር መጣስ</u>

ማንም ሰው በጦርነት ጊዜ ዓለም አቀፍ ሕጐችንና የሰብአዊነት አጠባበቅ ስምምነቶችን ተቃዋሚ በሆነ መንገድ:-

ሀ/ የተማረከውን፣ መሣሪያውን ለምርኮ ያስረከበውን ወይም በማናቸውም ዓይነት ለመከላከል የተሳነውን ወይም የመከላከል ተግባሩን የተወውን ጠላት የገደለ ወይም ያቆሰለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የሙት አካል ያጐደለ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በጦር ሜዳ ላይ በአንድ የጠላት ቁስለኛ፣ በሽተኛ፣ ወይም ሬሳ ላይ ስርቆት የፈፀመ ወይም ኃይልን ተጠቅሞ ገፈፋ የፈፀመ እንደሆነ፣ ወይም ከነዚህ ተግባሮች አንዱን ለመፈፀም በማሰብ ቁስለኛውን፣ በሽተኛውን ወይም ሬሳውን የበረበረ፤ የያዘ ወይም የኃይል ተግባር የፈፀመበት እንደሆነ፤ ወይም

መ/ ከእነዚህ ተግባራት አንዱ እንዲፈጸም ያዘዘ እንደሆነ፤

BACK



በጽኑ እስራት፣ ወይም ወንጀሉ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፸፯ ሕገወጥ በሆኑ የጦር መሣሪያዎች መገልገል

ማንም ሰው ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም በኢትዮጵያ ሕግ በግልፅ በተከለከሉ የጦር መሣሪያዎች ወይም የውጊያ ዘዴዎች ጠላትን የወጋ ወይም በእነዚህ መሣሪያዎች ወይም የውጊያ ዘዴዎች ጠላት እንዲወጋ ትዕዛዝ የሰጠ እንደሆነ፤

ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል:: ነገሩ ከባድ ከሆነ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት፤ ወይም የወንጀሉ አፈፃፀም በጣም ከባድ እንደሆነ፤ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፸፰ የጦርነት ማቆም ውልን ወይም የሰላም ስምምነትን ማፍረስ

ማንም ሰው የጦርነት ማቆም ውል ወይም የሰላም ስምምነት መፈረሙን በግልፅ እያወቀና ትዕዛዝ ከተሰጠው በኋላ ውጊያው እንዲቀጥል ያደረገ ወይም በማናቸውም ሌላ አድራጎት ከውሉ ወይም ከስምምነቱ ግዴታዎች አንዱን አስቦ ያፈረሰ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፪፻፸፱ ፋኖ በመሆን በጦርነት ጊዜ የሚደረግ ወንጀል

ማንም ሰው በጦርነት ጊዜ ዓለም አቀፍ ሕግን በሚቃወም ሁኔታ በኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣኖች የታወቀ የመከላከያ ሠራዊት አባል ወይም የድጋፍ ሰጪ ኃይል

አባል ሳይሆን በኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ላይ ተቃዋሚ የሆነ ተግባር በመፈጸም በአገልግሎቶቹ፣ በማመላለሻ መሣሪያዎቹ፣ በመገናኛ ወይም በማጓጓዥ ዘዴዎቹ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ በጣም ከባድ እንደሆነ፤ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፪፻፸፱ በቁስለኞች፣ በበሽተኞችና በእሥረኞች ላይ መጨከን ወይም የሚገባቸውን ማጓደል

ማንም ሰው ዓለም አቀፍ ሕግጋትን በመጣስ ቁስለኛን፣ በሽተኛን፣ ወይም በእስራት ወይም በግዞት ላይ የሚገኘውን የጦር ምርኮኛ በጨካኝነት ያሰቃየ ወይም የኃይል ድርጊት የፈጸመበት እንደሆነ ወይም በእነዚሁ ሕግጋት የተረጋገጡለትን መብቶች እንዳይጠቀምባቸው የከለከለ ወይም በእነዚሁ መብቶች መጠቀም እንዳይችል ያዘዘ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፪፻፹ ፍትህን መከልከል

ማንም ሰው በጦርነት ወይም በወረራ ጊዜ ዓለም አቀፍ ሕግን በመጣስ ሰላማዊ ሰው፣ ቁስለኛ፣ እሥረኛ ወይም የጦር ግዞተኛ ሰብአዊነቱን የሚያረጋግጥለትን በሕግ መሠረት የመዳኘት መብቱን እንዲሁም በነፃነት ራሱን የመከላከል መብቱን እንዲያጣ ያደረገ ወይም እንዲከለከል ያዘዘ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እስራት ይቀጣል::

## ምዕራፍ ሁለት

## በሰብአዊ ድርጅቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፪፻፸፩ በዓለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች ላይ የሚፈፀም የጠላትነት ድርጊት

፩ ማንም ሰው በሰላም ጊዜ አስቦ:-

ሀ/ በቀይ መስቀል ወይም በቀይ ጨረቃ ማህበር ወይም እነዚህን በመሳሰሉ ሌሎች ሰብዓዊ ድርጅቶች ሠራተኞች፣ ወኪሎች ወይም ባልደረቦች ወይም በነዚሁ ድርጅቶች ጥበቃ ሥር በሚገኙ ሰዎች ላይ የፀብ ሥራ ወይም የኃይል ድርጊት የፈጸመ፣ የዛተ ወይም ያዋረደ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የነዚህን ድርጅቶች ዕቃዎች፣ ግዙፍ ሥራዎች ወይም ማከማቻዎች ያፈረሰ ወይም ጉዳት ያደረሰባቸው እንደሆነ፤

በቀላል እስራት፤ የተፈጸመው ወንጀል ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ይሆናል::

### አንቀጽ ፪፻፸፪ በዓለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች አርማዎችና መለያ ምልክቶች ያለአግባብ መገልገል

ማንም ሰው አስቦ:-

BACK



ሀ/ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶችን አርማዎች ወይም መለያ ምልክቶች ያለፈቃድ የያዘ፣ የሰቀለ ወይም በእነዚሁ የተገለገለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የፀብ ድርጊት ለማዘጋጀት ወይም ለመፈጸም በማቀድ በዚህ ዓይነት አርማ ወይም መለያ ምልክት ወይም በማናቸውም በዓለም አቀፍ ሕግ በታወቀ የደህንነት ምልክት በተለይም በነጭ ሰንደቅ ዓላማ ያለአግባብ የተገለገለ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት፣ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

**አንቀጽ ፪፻፹፫ ዕርቅ መልእክተኛ ላይ የጠላትነት ድርጊት መፈፀም**

ማንም ሰው ከጠላት ወገን የእርቅ መልዕክተኛ ወይም የዕርቅ ድርድር አሳብ አቅራቢ ሆኖ የሚመጣውን ወይም ከእርሱ ጋር ያለውን ሰው ያጉላላ፣ ያስፈራራ፣ ያዋረደ ወይም ያለአግባብ የያዘ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ይቀጣል::

## ርዕስ ሦስት

## ወታደራዊ ወንጀሎች እና በመከላከያ ሠራዊት እንዲሁም በፖሊስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ምዕራፍ አንድ

## ወታደራዊ ወንጀሎች

### ክፍል አንድ

### የአገልግሎት ግዴታን በመጣስ የሚደረጉ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፪፻፹፬ ወታደራዊ አገልግሎትን እንቢ ማለት**

፩ ማንም ሰው በውትድርና የመቀጠር ወይም በወታደርነት የማገልገል ሕጋዊ ግዴታውን ከመፈጸም ለማምለጥ በማሰብ በወታደርነት እንዲመዘገብ ወይም

በክተት አዋጅ መሠረት በየግንባሩ ቀርቦ እንዲያገለግል በግል በተደረገለት ጥሪ፣ በአደባባይ በተለጠፈ ማስታወቂያ ወይም በመገናኛ ብዙኃን በተነገረ ማስታወቂያ የተላለፈውን ትዕዛዝ ያልፈጸመ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠ በት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፪፻፹፮ የጥሪ ትዕዛዝን አለማክበር</u>

፩ ማንም ሰው በወታደርነት መመልመልን ወይም ማገልገልን ባለመፈለግ ሳይሆን፣ የጥሪ ትዕዛዝን ያልፈፀመ እንደሆነ በተለይም ለወታደራዊ ምልመላ የሚደረገውን ምርመራ፣ ፍተሻ፣ የልምምድ ትምህርት ወይም ማናቸውንም ወታደራዊ ግዴታ እንዲፈፅም የተደረገለትን ጥሪ ያላከበረ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ፣ ወይም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ወይም ከፍተኛ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ አደጋ ወይም የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ በተከሰተ ጊዜ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፪፻፹፯ ከአገልግሎት ግዴታ ለማምለጥ ታስቦ የሚደረግ የችሎታ ማጣት</u>

፩ ማንም ሰው በራሱ ወይም በሌላ ሰው አድራጐት አካሉን በሙሉ ወይም በከፊል በማጉደል በሰውነቱ ወይም በጤንነቱ ላይ ጉዳት በማድረስ ወይም ፈቅዶ በሚፈጽመው በሰውነቱ ወይም በጤንነቱ ላይ ጉዳት

BACK



በሚያደርስ በማናቸውም ሌላ ዘዴ በመጠቀም አካሉን በሙሉ ወይም በከፊል በማጉደል ለጊዜው ወይም ለዘወትር ለአገልግሎት ብቁ ሆኖ እንዳይገኝ ያደረገ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ከዚህ በላይ ለተመለከተው ዓላማ በማናቸውም አድራጐት በባለጉዳዩ ፈቃድ ባለጉዳዩን በከፊል ወይም በሙሉ አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ያደረገ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠ በት፣ የጦር ክተት አዋጅ በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፪፻፹፯ ከወታደራዊ አገልግሎት ለማምለጥ የሚፈፀም ማጭበርበር</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ለዘወትር ወይም ለጊዜው ከወታደራዊ አገልግሎት ግዴታው ለማምለጥ አግባብ ያላቸውን የሲቪል ወይም ወታደራዊ ባለሥልጣኖችን ለማታለል በታቀዱ ዘዴዎች የተጠቀመ እንደሆነ በተለይም ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት በማቅረብ፣ ሐሰተኛ በሆነ ቃል ወይም ሰነድ በመታገዝ ወይም በሽተኛ ወይም አካለ ጉዱሎ በመምሰል ያታለለ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ይሆናል፡፡

## <u>አንቀጽ ፪፻፹፰ ኩብለላ</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከወታደራዊ አገልግሎት ግዴታው ለማምለጥ በማሰብ የጦር ክፍሉን ወይም የወታደራዊ ነክነት ያለውን የአገልግሎት ተግባሩን ትቶ የሄደ ወይም በፈቃድ ከሄደ በኋላ ወደ ክፍሉ ወይም ወደ አገልግሎት ተግባሩ ሳይመለስ የቀረ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ያስቀጣል፡፡

## <u>አንቀጽ ፪፻፹፱ ያለአግባብ መቅረት</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከወታደራዊ አገልግሎት ለማምለጥ በማቀድ ሳይሆን፡-

ሀ/ ያለፈቃድ ወይም ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ወታደራዊ ክፍሉን ትቶ የሄደ እንደሆነ ወይም ወታደራዊ ተግባሩን ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ከተሰጠው ፈቃድ ወይም የዕረፍት ጊዜ ያሳለፈ እንደሆነ፤

BACK



ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት ይሆናል::

አንቀጽ ፪፻፺ አስቦ ወደ ጦር ክፍሉ ተመልሶ አለመምጣት

ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በጦርነት ጊዜ:-

ሀ/ ከክፍሉ ጦር ተቋርጦ ከተለየ በኋላ ወደክፍሉ ወይም በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው የወገን ጦር ሳይቀላቀል የቀረ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ ከተማረከ በኋላ ነፃነቱን እንዳገኘ ወዲያውኑ ለአንድ የጦር ክፍል ወይም ወታደራዊ ባለሥልጣን ቀርቦ ሳያመለክት ወይም ወደ ምድቡ ሳይመለስ የቀረ እንደሆነ፣

በቀላል እስራት፣ ወይም ወንጀሉን የፈጸመው አስቦ ለዘለቄታው ከወታደራዊ ግዴታው ለመሸሽ እንደሆነ፣ ከሶስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት ይቀጣል::

ክፍል ሁለት

በወታደራዊ ሥልጣን ያለአግባብ መገልገል

አንቀጽ ፪፻፺፩ ከአገልግሎት ግዴታ ያለአግባብ ነፃ ማድረግ

፩ ማንም ሰው የተሰጠውን የሥራ ወይም ወታደራዊ ሥልጣን ከመጠን በላይ በማሳለፍ ወይም በዚሁ ሥልጣኑ ያለአግባብ በመገልገል ሌላውን ሰው ከወታደራዊ አገልግሎት ግዴታው ነፃ ያደረገው እንደሆነ፣

እጅግ ቢያንስ በስድስት ወር ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦርነት አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፪፻፺፪ በበታች ላይ የሚፈፀም ዛቻና የኃይል ድርጊት</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በትእዛዙ ወይም በስሩ ባለ ሰው ላይ የዛተበት፣ የእጅ እልፊት የፈፀመበት፣ ወይም ከዚሁ ሰው ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ያዋረደው እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በጭካኔ ወይም በኃይል ተግባር፣ በጦር መሣሪያ ወይም በሌላ አደገኛ መሣሪያ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል::

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>የወታደራዊ አገልግሎት ተግባሮችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

<u>መልካም ሥርዓቶችንና ዲስፕሊንን ለአደጋ በሚያጋልጥ</u>

<u>ሁኔታ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

<u>አንቀጽ ፪፻፺፫ ጠቅላላ የአገልግሎት ደንቦችን መጣስ</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከሥነ-ሥርዓት ደንብ መተላለፍ /አንቀጽ ፯፻፺፪/ ውጭ የሆኑትን ጠቅላላ የመከላከያ ኃይሎችን የአገልግሎት ሥራ ትዕዛዞች ወይም ደንቦች አስበ የጣሰ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ከተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል።

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት ሆኖ፣ በሰላም ጊዜ ከሆነ ቅጣቱ የሥነ ሥርዓት /ዲስፕሊን/ ቅጣት ይሆናል፤ በጦርነት ጊዜ ወይም በሌላ ከባድ ሁኔታ ከሆነ ግን ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፪፻፺፬ ያልተሟላ ወይም ትክክል ያልሆነ መረጃን መስጠት</u>

፩ ሥልጣኑ ወይም ወታደራዊ ተግባሩ አፊሴላዊ የሆነ ሪፖርት ወይም መግለጫ ማዘጋጀት ወይም የአገልግሎት ሰነድ ቅጽ መሙላት የሆነ ማንም ሰው፡-

ሀ/ አስቦ ፍሬ ነገርን ወይም እውነተኛውን ነገር የለወጠ ወይም የደበቀ ወይም በፎርማው ሊረጋገጥ በሚገባው ሰነድ ላይ ማናቸውንም ዝርዝር ወይም አሀዝ ሳይሞላ የተወ እንደሆነ፤ ከሁለት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ይቀጣል።

ለ/ የሥራ ግዴታው ሆኖ እያለ በእንቢተኝነት ቃለጉባኤ፣ ሪፖርት ወይም መግለጫ ሳያዘጋጅ ወይም ሳይልክ የቀረ እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተደረገው በቸልተኛነት ከሆነ፤ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል።

፫ የዕረፍት ፈቃድን ለማግኘት ወይም ጊዜውን ለማራዘም በማሰብ አግባብ ካለው ባለሥልጣን እውነቱን የደበቀ ወይም ለዚሁ ባለሥልጣን ሐሰተኛ ማረጋገጫ ያቀረበ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል፣ በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፬ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፤ ወይም ወንጀሉ ከባድ የሆነ አደጋ ሊያስከትል የሚችል እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፪፻፺፩ ሰክሮ መገኘት</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል:-

ሀ/ በወታደራዊ ሥራ ላይ በሚገኝበት ጊዜ እየደጋገመ የሰከረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ሰክሮ ስነሥርዓትን የጣሰ ወይም ህዝብን የረበሸ እንደሆነ፤

ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ የሰከረው ሰው በሌላ ሰው ላይ በመሣሪያ የዛተ ወይም አደገኛ ሆኖ የታየ
እንደሆነ፤ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፪፻፺፪ ከሥነ ሥርዓት /ዲስፕሊን/ ውጭ መሆን</u>

ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል:-

BACK



ሀ/ ያለፈቃድ ከጦር ሠፈሩ፣ ከወታደራዊ መኖሪያ ቤቱ ወይም ከወታደራዊ ምሽግ የሄደ፣ ወይም ያለትዕዛዝ ወይም ያለፈቃድ እንዳይደርስ ከተከለከለ ሥፍራ ወይም ከተፈቀደለት ሰፈር ውጭ የተገኘ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በጹብ፣ በአምባጓሮ ወይም በሁከት ተካፋይ የሆነ ወይም ይህንን አድራጐት እንዲተው አንድ የበላይ አለቃ የሰጠውን ትዕዛዝ በእንቢተኝነት የተቃወመ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በሆስፒታል ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት ሲታከም ለበሽተኞች ማረፊያ ሆኖ ወይም በማናቸውም ሌላ ሥፍራ የራሱን ሁኔታ ይበልጥ የተወሳሰበ ሊያደርግ ወይም ሊያባብስ ወይም የመታከሚያውን ጊዜ ሊያራዝም በሚችል አኳኋን ከሥነ-ሥርዓት ውጭ የሆነ ወይም ትዕዛዝን ያላከበረ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ በማናቸውም ሌላ ሁኔታ በንግግር፣ በአኳኋን ወይም በአድራጐት መልካም ሥርዓትን ወይም ወታደራዊ ሥነ ሥርዓትን ያወከ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፪፻፺፯ በበላይ አለቃ ወይም በማዕረግ እኩያ በሆነ አባል ላይ የሚፈፀም ስድብ፣ ዛቻና የእጅ እልፊት</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል አንድን የበላይ አለቃ ወይም በማዕረግ እኩያው የሆነውን አባል የሰደበ፣ የዛተበት፣ ያወከው ወይም የእጅ እልፊት የፈጸመበት እንደሆነ፤
በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ድርጊቱ የተፈፀመው በኃይል ተግባር ወይም በጦር መሣሪያ፣ አደገኛ በሆነ ነገር ወይም በማናቸውም ዓይነት መሣሪያ አማካይነት እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል።

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠ በት፣ የጦርነት ከተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፤ ቅጣቱ በንዑስ አንቀጽ/፩/ ለተመለከተው ወንጀል ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት፤ በንዑስ አንቀጽ /፪/ ለተመለከተው ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፪፻፺፫ ለበላይ አለመታዘዝ</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል አስቦ በበላይ አዛዡ ወይም አግባብ ባለው ወታደራዊ ባለሥልጣን ተግባሩን በሚመለከት፤ በቃል፣ በፅሑፍ፣ በምልክት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ ለራሱ ወይም እርሱ ለሚገኝበት የጦር ክፍል የተሰጠውን ማናቸውንም ትዕዛዝ ሳይፈጽም የቀረ ወይም ለመፈጸም እንቢተኛ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠ በት፣ የጦርነት ከተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ እና እንቢተኛነቱም ቁርጠኛ የሆነ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል።

፫ ወንጀሉ በተለይ ከባድ ሆኖ እንቢተኛነቱም የተፈጸመው በጠላት ፊት እንደሆነ፤ ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም ሞት ይሆናል።

BACK



## አንቀጽ ፪፻፺፱ ወታደራዊ አመፅ

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከሌሎች ወታደሮች ጋር በመተባበር ሕጋዊ ባልሆነ ስብሰባ በመካፈል ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ በበላይ አለቃ ወይም ወታደራዊ ባለሥልጣን ላይ፣ ወይም የበላይ አለቃን ወይም ወታደራዊ ባለሥልጣንን በመቃወም በተፈጸመ ያለመታዘዝ፣ የተቃውሞ፣ የዛቻ፣ የኃይል ድርጊት ወይም የእጅ እልፊት እንቅስቃሴ ውስጥ ተካፋይ እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠ በት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ፣ የዕድሜ ልክ እሥራት ወይም ሞት ይሆናል::

፫ የአመፁ መሪዎች ወይም አደራጆች ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የቅጣት ወሰኖች ሳይታለፍ ለመቀጣጫ በተለይ በጽኑ አኳኋን /አንቀጽ ፹፪(፩) (መ)/ ይቀጣሉ::

## አንቀጽ ፫፻ ወታደራዊ አመፅ ለማስነሣት የሚደረግ አድማ ወይም መተባበር

፩ ማንም ሰው ወታደራዊ አመጽ ወይም ሕገወጥ ንቅናቄ እንዲነሳ ለማዘጋጀት ከሌሎች ጋር ያደመ ወይም የተባበረ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ

እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

**አንቀጽ ፫፻፩ ወታደራዊ አመፅ እንዲደረግ ማነሣሣትና የማነሳሳት ሙከራ፣ አባሪነትና የአባሪነት ሙከራ**

የጦርነት አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም ጦርነት ባለበት ጊዜ ወታደራዊ አመፅ እንዲደረግ ማነሳሳት ወይም የማነሳሳት ሙከራ፣ አባሪነት ወይም የአባሪነት ሙከራ በቀላል እሥራት ያስቀጣል /አንቀጽ ፳፯(፪)፣ ፴፮(፪)፣ ፴፯(፫)/::

**አንቀጽ ፫፻፪ በዘብ፣ በዘብ ጠባቂ እና በቃኚ ዘብ ላይ የሚፈፀም ወንጀል**

ሥራውን በመፈጸም ላይ በሚገኝ ዘብ፣ በዘብ ጠባቂ ወይም በቃኚ ዘብ ላይ የሚፈጸም ስድብ፣ ዛቻ፣ የእጅ እልፊት፣ የኃይል ተግባር፣ አለመታዘዝ ወይም አመፅ፣ በአንቀጽ ፪፻፺፰ በተደነገገው መሠረት ያስቀጣል::

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የጥበቃ ግዴታን ወይም ትዕዛዞችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፫፻፫ የጥበቃ ግዴታን መጣስ**

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል:-

ሀ/ እስቦ ወይም በቸልተኛነት፣ በስካር ወይም በሌላ ምክንያት የዘብ ሥራውን ለመፈጸም በማያስችለው ሁኔታ የተገኘ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የዘብ ሥራውን ያለፈቃድ የተወ ወይም ሌላ ተረኛ ሳይተካለት ከሥራው ላይ የታጣ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠ በት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት

ጊዜ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው ታስቦ በጠላት ፊት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ፣ የዕድሜ ልክ እሥራት ወይም ሞት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፫፻፩ ወታደራዊ ትዕዛዝን መጣስ</u>

፩ ማንም ሰው ለመደበኛ ዘብ፣ ዘብ ለቆመ ወታደር፣ ለቃኚ ዘብ፣ ለአጃቢ ወታደር፣ ወይም ይህን የመሳሰለ ተግባር ለሚያከናውን ለማንም ሰው የተሰጠውን ትዕዛዝ ተቃራኒ የሆነ ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው:-

ሀ/ የኤሌክትሪክ ኃይል ወይም መብራት ሰጪ ድርጅት ያለበት ቦታን፣ ግድብን፣ የውሃ ማገጃን፣ የውሀ መከተሪያን፣ የመርከብ መጠጊያን፣ የወደብ ድርጅቶችን፣ ወይም የመጠበቂያ ድርጅቶችን፣ ድልድዮችን፣ የሸለቆ መሸጋገሪያዎችን፣ ከፍ ያለ ጥቅም ያላቸው መተላለፊያዎችን፣ ወይም

ለ/ መሣሪያዎች፣ የባቡር ተጐታቾች፣ ወይም በሞተር የሚንቀሳቀሱ መሣሪ ያዎች የሚገኙበትን፣ መርከቦች መልሕቅ ጥለው የሚቆሙበትን ቦታ፣ መሣሪያዎች የተከማቹበትን ግምጃ ቤት ወይም ሌላ ቦታ፣ የጦር መሣሪያዎች፣ ጥይት፣ የሚፈነዱ ነገሮች፣ ነዳጆች ወይም የስንቅ ዕቃዎች የሚከማቹበትን ቦታ፣ ወይም

ሐ/ ጠረፍን ወይም አደገኛ የሆነ ቦታን፣

መጠበቅን የሚመለከት ልዩ ትዕዛዝን በመቃወም እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠ በት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፫፻፳ ትዕዛዝን ያለአግባብ መግለፅ ወይም መለዋወጥ ወይም በአግባቡ አለማስተላለፍ</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በአገልግሎት ሥራው ላይ ሆኖ ነገር ግን በክዳት ሳይሆን:-

ሀ/ የማረጋገጫ ቃልን፣ የይለፍ ቃልን ወይም ምስጢራዊ ትዕዛዝ ሊነገረው ለማይገባ ሰው የገለጸ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ ምስጢሩ ሊገለፅለት ለሚገባው ሰው ቢሆንም ከተቀበለው ማረጋገጫ ቃል፣ የይለፍ ቃል ወይም ምስጢራዊ ትዕዛዝ ጋር የማይመሳሰል ሌላ ዓይነት ቃል አውቆ ያስተላለፈ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ ማስተላለፍ የሚገባውን መልዕክት ሳያስተላልፍ የቀረ እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነና አፈፃፀሙ:-

BACK



ሀ/ በቸልተኛነት ሲሆን፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት ይሆናል፤

ለ/ ታስቦ ሲሆን፣ ቅጣቱ ከሃያ ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

ንዑስ ክፍል ሦስት

ታማኝነትን በማጓደል የሚፈፀሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፫፻፺፮ በዕቃዎች ያለአግባብ መገልገል ወይም ማባከን

፩ ማንም ሰው በጦር መሣሪያዎች፣ በጥይቶች፣ በወታደራዊ ትጥቆች፣ በመሣሪያዎች፣ በተሽከር ካሪዎች፣ በእንስሳት፣ ወይም በሌሎች በአደራ በተሰጠ ት ወይም በተረከባቸው፣ ወይም በሥራው ወይም በወታደርነቱ ምክንያት ባገኛቸው ማናቸውም እነዚህን በመሣሰሉ ዕቃዎች ያለአግባብ የተገለገለ፣ ያዋሰ ወይም በዋስትና ያስያዘ እንደሆነ፤

ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ወይም ወንጀሉ ቀላል ከሆነ ከሶስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተዘረዘሩትን ዕቃዎች የሸጠ፣ ያጠፋ፣ የጣለ፣ ያበላሸ፣ ያባከነ፣ ወይም ያወደመ እንደሆነ፤ በዚህ ሕግ በሌላ ድንጋጌ የሚቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣ ወታደራዊ አገልግሎቱ ወይም ወታደርነቱ ካበቃ በኋላ እንኳ ቢሆን፤ ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፫ ወንጀል የተፈፀመበት መሣሪያ ወይም ዕቃ ለአገር ደህንነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሃያ አምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

BACK



፬ ወንጀሉ የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት፣ ነገሩ ከባድ እንደሆነ የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ ፫፻፺ የማይገባ ጥቅምን ማግኘት ወይም ያለአግባብ ማጥፋት</u>

፩ ማንም ሰው የወታደር ስንቅን፣ ገንዘብን፣ ዕቃን፣ ነዳጅን ወይም ማናቸውንም ሌላ ንብረት የመጠበቅ፣ የመቆጣጠር፣ ሥራውን የመምራት፣ የመግዛት ወይም የማከፋፈል ኃላፊነት ተሰጥቶት፡-

ሀ/ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የተጠቀመበት ወይም በማናቸውም ሁኔታ
ዋጋው ዝቅ እንዲል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በንብረቱ ምክንያት ማናቸውንም ጥቅም የተቀበለ ወይም እንዲሰጠው ያግባባ፣ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን በአንድ ወታደራዊ ዕቃ ቤት፣ ሰፈር፣ የጦር ሰፈር፣ ሆቴል፣ መሰብሰቢያ፣ ወይም ማናቸውም ቤት ውስጥ የተቀመጠውን ምግብ፣ ስንቅ፣ የወታደር ትጥቅ፣ የተገዛ ዕቃ ወይም ሌላ ዕቃ በመግዛት፣ በመሸጥ ወይም በማከፋፈል ሥራው ላይ የማይገባ ጥቅም የተቀበለ ወይም እንዲሰጠው የገፋፋ እንደሆነ፤

አድራጐቱ እንደ እምነት ማጉደል፣ የተንኮል ሥራ አመራር፣ ጉቦ፣ በመንግሥት ሥራ ላይ ማስገደድ ወይም የመሳሰሉት ሆኖ በነዚሁ ወንጀሎች የማያስቀጣ ከሆነ፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

BACK


፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፣ ቅጣቱ ከሃያ ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል።

## ክፍል አራት

## በመከላከያ ሠራዊት ደህንነት፣ ሞራል ወይም ኃይል ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፫፻፳ አደጋን አለማስታወቅ

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ወዲያውኑ ወታደራዊ እርምጃ ሊወሰድበት የሚገባ ሁኔታ መኖሩን እያወቀ ለአዛዡ፣ ለወታደራዊ ባለሥልጣን ወይም ለጦሩ እዝ ሳያስታውቅ የቀረ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

፫ ወታደራዊ አመጽን ወይም የኩብለላን አደጋ ወይም ዕቅድ አለማስታወቅ አግባብ ባለው ድንጋጌ መሠረት ያስቀጣል /አንቀጽ ፫፻፴፮/።

### አንቀጽ ፫፻፱ አስፈላጊ የሆነውን የደህንነት ጥንቃቄ አለማድረግ

፩ አንድ አዛዥ መኮንን ወይም በመከላከያ ሠራዊት አገልግሎት ውስጥ የሚገኝ ሌላ ማንም ሰው አስቦ በወታደራዊ ልምምድ ወይም የአገልግሎት ጉዳይን በሚመለከት በማናቸውም አጋጣሚ ጊዜ የሰዎችን

ወይም የእንስሳትን ሕይወት ወይም ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉትን የጥንቃቄ ወይም የደህንነት እርምጃዎች በራሱ አነሳሽነት ባለማዘጋጀቱ፤ ወይም በኃላፊነቱ ሥራ የሚጠበቁትን የዕቃ ማከማቻዎች፣ የጦር ሠፈሮች፣ ግዙፍ ሥራዎች፣ የሥራ መሣሪያዎች ወይም ሌሎች ዕቃዎች በሚገባ እንዲጠበቁ ወይም ደህንነታቸው እንዲረጋገጥ ባለማድረጉ አደጋ እንዲደርስባቸው ሆነው በአስጊ ሁኔታ ላይ እንዲገኙ ያደረገ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት፣ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ ተግባሩ የሥነ ሥርዓት ቅጣት ብቻ የማይበቃው ሆኖ ሲገኝ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ሆኖ:-

ሀ/ ታስቦ ሲሆን፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት፣ ወይም ጥፋቱ ከባድ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል፤

ለ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ ቅጣቱ ከሶስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል::

## አንቀጽ ፫፻፲ ሐሰተኛ የአደጋ ምልክት መስጠት

፩ ማንም ሰው አስቦ በወታደራዊ ጉዞ ወይም ዕረፍት ጊዜ፣ በጦር ሜዳ ወይም ሠፈር፣ በአንድ የጦር መርከብ ላይ፣ በአውሮፕላን ማረፊያ ቦታ ላይ ወይም

BACK



በማናቸውም በሌላ ሥፍራ በተለይም የጦር መሣሪያ በመምዘዝ፣ በመተኮስ፣ ከበሮ በመምታት፣ ጥሩንባ በመንፋት፣ በምልክት፣ በጩኸት፣ በአካል ንቅናቄ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ በመገልገል ሐሰተኛ የአደጋ ምልክት የሰጠ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ እና በዚህ ሕግ በሌላ ድንጋጌ በተለይ ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ፤ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት ሲሆን ቅጣቱ በንዑስ አንቀጽ /፩/ ለተመለ ከተው ድርጊት ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት፤ በንዑስ አንቀጽ /፪/ ለተመለከተው ድርጊት ደግሞ ከሁለት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፫፻፲፩ የመከላከያ ሠራዊቱን ተስፋ ማስቆረጥ</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ወይም የጦር አዛዥ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተመለከተው ጊዜ ውጭ በሚያሳየው ጠባይ በተለይም የተሰጠውን ትዕዛዝ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ግንባሩን በማጠፍ /በመሸሽ/ የጦር መሣሪያውን፣ ትጥቁን ወይም ጥይቶቹን በመጣል፣ በተዋጊው ጦር መካከል ፍርሀትን በማሰራጨት፣ በሥርዓት አልበኝነት ወይም ለመደናገር ምክንያት በመሆን ወይም እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ ወይም እንዲወገዱ ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለመፈጸም የወታደሮችን ሞራል የነካ እንደሆነ፤

BACK


ከሃያ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በውጊያ ጊዜ ወይም ከውጊያ በፊት ጥቂት ቀደም ብሎ ወይም ውጊያው እንዳበቃ ወዲያውኑ ከሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማያንስ ጽኑ እስራት ይሆናል::

፫ ወንጀሉና የሚያስከትለው ውጤት ከባድ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ፣ ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ሞት ሊሆን ይችላል::

## አንቀጽ ፫፻፲፪ ፈሪነት

ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በጠላት ፊት ሆኖ በፍርሀት:-

ሀ/ የጦር መሣሪያውን ለማንሳት ወይም ለመጠቀም እንቢተኛ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ሳይታዘዝ የተደበቀ፣ የሸሸ፣ ወይም የተሰጠውን የውጊያ ቦታ የለቀቀ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ጓደኞቹ ወይም ጭፍራዎቹ ሳይታዘዙ እንዲደበቁ፣ እንዲሸሹ፣ ወይም የተሰጣቸውን የውጊያ ቦታ እንዲለቁ ያነሳሳ እንደሆነ፤

እጅግ ቢያንስ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራት፣ ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ እንደሆነ በዕድሜ ልክ እሥራት ወይም በሞት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፲፫ ለጠላት እጅን መስጠት

ማንኛውም የጦር አዛዥ ወይም የመከላከያ ሠራዊት አባል:-

BACK



ሀ/ በውጊያ ላይ ወይም በጠላት ፊት በወታደርነቱ ሊፈጽመው የሚገባውን ከሁኔታው የሚጠበቅበትን ሁሉ ሳያደርግ ውጊያ ያቆመ፣ የእርቅ ሰንደቅ ዓላማ ያነሳ፣ መልዕክተኛ የላከ፣ ወይም ሰንደቅ ዓላማውን ያወረደ ወይም ከጭፍሮቹ ጋር በመሆን ለጠላት እጁን የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ሊድን የሚችልበትን መንገድ ፈልጐ የተቻለውን ሁሉ ሳይፈጽም በኃላፊነቱ ሥር ያለውን የጦር መርከብ፣ አውሮፕላን፣ ታንክ ወይም ማናቸውንም የጦር መሣሪያ ትቶ የሄደ፣ የለቀቀ፣ ያበላሸ፣ ወይም ለጠላት አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ለመከላከል ሊፈጽም የሚገባውን ሁሉ ሳያደርግ ትልቅ ምሽግ፣ ከተማ፣ ወደብ፣ ወይም የአውሮፕላን ማረፊያ፣ እርድ /የጦር ሠፈር/ ወይም የምሽግ ሥፍራ ለጠላት የለቀቀ እንደሆነ፤

በእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፲፩ የጦር መሣሪያዎችን እንደተሟሉ መተው</u>

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ወይም የጦር አዛዥ መኮንን በጦርነት ጊዜ ከጥቅም ውጭ ለማድረግ፣ ለማበላሸት፣ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ ሳይፈጽም ወታደራዊ ዒላማዎችን፣ ሠፈሮችን፣ ማረፊያ ቤቶችን፣ ጥይቶችን፣ የጦር መሣሪያዎችን፣ ለጦርነት የሚያገለግሉ ሌሎች ዕቃዎችን፣ ድልድዮችን፣ የሽለቆ መሸጋገሪያ መንገዶችን፣ ሃዲዶችን፣ ወይም ለአገር መከላከያ ከፍተኛ ግምት ያላቸውን ዕቃዎች ለጠላት የተወ እንደሆነ፤
ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት፣ ወይም ጥፋቱ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

BACK



፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከስድስት ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት ይሆናል።

## አንቀጽ ፫፻፲፭ በጠላት የደንብ ልብስ ወይም የጦር መሣሪያ ያለአግባብ መገልገል

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል የጠላትን የደንብ ልብስ፣ ዓርማ ወይም የጦር መሣሪያ በሚያሳስት ወይም ጉዳት በሚያስከትል ሁኔታ ለብሶ ወይም ሲገለገል የተገኘ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በተለይ በጦርነት ጊዜ ሆኖ ድርጊቱ ከፍተኛ ማሳሳትን ወይም ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል።

## አንቀጽ ፫፻፲፮ የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባልን ትቶ መሄድ

፩ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በጦር ሜዳ የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባልን ሳያነሳ ወይም ትቶ በመሄድ በጠላት እጅ እንዲወድቅ ያደረገ እንደሆነ፣

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ማንኛውም የወታደር ሐኪም ግዴታውን ወይም ተግባሩን ባለመፈጸም ለአንድ በጦር ሜዳ ለቆሰለ አባል ተገቢውን ሕክምና ባለማድረጉ ቁስለኛው የሞት ወይም ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ፣ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው ቅጣት ይቀጣል።

፫. ወንጀሉ በአገር ጥቅም ወይም በሠራዊቱ ሞራል ላይ ከፍተኛ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ፣ ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ወይም ሞት ይሆናል::

**<u>አንቀጽ ፫፻፲፯ የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባል በያዘው ንብረት ላይ የሚፈፀም ወንጀል</u>**

ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት አስቦ በጦር ሜዳ ከቆሰለ ወይም ከተሰዋ አባል ላይ የመንግሥትን ወይም ማናቸውንም ሌላ ንብረት የወሰደ እንደሆነ፣

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የወል ድንጋጌዎች</u>

**<u>አንቀጽ ፫፻፲፰ ሲቪሎች ወይም ሚሊሺያዎች የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች</u>**

በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ የሚገኝ ሲቪል ወይም የሚሊሺያ አባል ከዚህ በፊት ባለው ርዕስ ሁለት (ከአንቀጽ ፪፻፷፱-፪፻፹፫) በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመጣስ በሚፈፅማቸው ወንጀሎች ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንቀጽ ፪፻፹፬ - ፫፻፲፯ ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል::

ሆኖም በተመሳሳይ ሁኔታ ለተፈፀሙ አንድ ዓይነት ወንጀሎች የመከላከያ ሠራዊት አባልን ያህል ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን አያከብድበትም::

**<u>አንቀጽ ፫፻፲፱ የጦር ምርኮኞችና የወታደር ግዞተኞች የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች</u>**

፩. በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወይም በኢትዮጵያ የወታደራዊ ወይም የሲቪል ባለሥልጣን ሥር የሚገኝ የጦር ምርኮኛ ወይም የወታደር ግዞተኛ ከዚህ በፊት

BACK



ባለው ርዕስ ሁለት በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ዓለም አቀፍ ሕጐችን በመጣስ በሚፈጽማቸው ወንጀሎች ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚፈፅመው ማናቸውም ወታደራዊ ወንጀል ከገንዘብ ነክ ወይም ከዲስፕሊን ቅጣቶች በስተቀር የዚህ ርዕስ መደበኛ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል።

፪ ጥፋተኛው ወታደራዊ ያልሆኑትን ወንጀሎች የፈጸመ እንደሆነ በዚህ ሕግ ለመደበኛ ወንጀሎች የተደነገጉት ቅጣቶች ተፈፃሚ ይሆኑበታል።

## አንቀጽ ፫፻፳ ወታደራዊ ግዴታን በመጣስ መኮንኖችና አዛዥ መኮንኖች የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች

ወታደራዊ አገልግሎትን፣ ሥርዓትን ወይም ግዴታን፣ ሥነሥርዓትን ወይም በጠቅላላው ወታደራዊ አገልግሎቶችን ወይም ግዴታዎችን በመጣስ አንድ መኮንን ወይም አዛዥ መኮንን ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ፤ በማዕረጉ ደረጃ ምልክት ልዩነት ሳይደረግ አርአያነት እንዲኖረው በአጠፋው ጥፋት መጠን በዚህ የወንጀል ሕግ ከተደነገጉት ከፍተኛ የቅጣት ጣራዎች ሳይታለፍ በከባድ ቅጣት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፫፻፳፩ ለከባድ ሁኔታዎች ተጨማሪ የሚሆኑ ቅጣቶች

በፅኑ እሥራት ወይም በሞት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ አድራጊው ወንጀሉን የፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ እንደሆነ፤ የጦር አዛዥ መኮንን ከሆነ ከሃምሣ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ፤ አዛዥ መኮንን ካልሆነ ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ፍርድ ቤቱ በተጨማሪ ሊቀጣው ይችላል።

ጥፋተኛው አገልግሎቱን ለመቀጠል ወይም ማዕረጉን እንደያዘ ለመኖር የማይገባው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ

ከማዕረጉ ዝቅ እንዲል ወይም ከመከላከያ ሠራዊት አባልነቱ እንዲወገድ በተጨማሪ ሊወሰንበት ይችላል::

## አንቀጽ ፫፻፳፪ የሥነ-ሥርዓት ቅጣቶች የተጠበቁ መሆናቸው

ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በወታደራዊ ሕጎች፣ ደንቦች ወይም መመሪያዎችና ቋሚ ትዕዛዞች ውስጥ የተመለከቱትን የተላለፈ እንደሆነና ጥፋቱ አነስተኛ በመሆኑ በወንጀል የማያስጠይቀው በሚሆንበት ጊዜ፣ በሠራዊቱ የዲስፕሊን መመሪያ መሠረት የሥነ ሥርዓት ቅጣት ይወሰንበታል /አንቀጽ ፯፻፺፪/::

## ምዕራፍ ሁለት

## በመከላከያ ሠራዊትና በአባሎቻቸው ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ክፍል አንድ

## ሥራቸውን በማከናወን ላይ በሚገኙ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## አንቀጽ ፫፻፳፫ የሥራ ግዴታ በማይገባ ሁኔታ እንዲፈፀም ወይም እንዲጣስ ማስገደድ

ማንም ሰው በዛቻ ወይም በኃይል አንድ የመከላከያ ሠራዊት አባል የአገልግሎት ተግባሩን ያለአግባብ እንዲፈጽም ወይም ሊያከናውን የሚገባውን አገልግሎት እንዳይፈጽም ያስገደደ ወይም ያገደ እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፳፬ ሥራውን በማከናወን ላይ ባለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ላይ የሚፈፀም ጥቃት

፩ ማንኛውም ሰው ሥራውን በመፈጸም ላይ የሚገኘውን የመከላከያ ሠራዊት አባል ሳይደርስበት የዛተበት፣ ያጠ ቃው ወይም የእጅ እልፊት ያደረሰበት እንደሆነ፣

BACK



ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው በያዘው መሣሪያ ተበዳዩን ያስፈራራው እንደሆነ ወይም የኃይል ተግባር የፈጸመበት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ቀላል እሥራት ይሆናል::

ድርጊቱ ከባድ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን አስከትሎ እንደሆነ አግባብነት ያላቸው የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ (አንቀጽ ፷፯)::

<u>አንቀጽ ፫፻፳፫ ከባድ ሁኔታዎች</u>

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፳፫ ወይም ፫፻፳፬ የተመለከቱት ወንጀሎች የተፈፀሙት:-

ሀ/ ሥራውን በማከናወን ላይ ባለ ዘብ፣ በወታደር ዘብ፣ በቃኚ ወታደር፣ የወታደራዊ ፖሊስ ወይም በሌላ ወታደራዊ ባለሥልጣን ላይ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሥራው ወይም በማዕረጉ ምልክት ሊለይ በሚችል ወታደራዊ መኮንን ወይም አዛዥ መኮንን ላይ እንደሆነ፤

ዛቻው ወይም ያለጦር መሣሪያ የተፈፀመው ጥቃት በተፈጸመበት ሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ ጉዳት ባላደረሰ ጊዜ ጥፋተኛው ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፤ በኃይል ወይም በጦር መሣሪያ የተፈጸመ ጥቃት ሲሆን ጥፋተኛው ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በመከላከያ ሠራዊትና በድጋፍ ሰጪ የአገልግሎት ክፍሎቻቸው ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

<u>አንቀጽ ፫፻፳፮ የሕግ ወይም የውል ግዴታዎችን መጣስ</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ ለወታደራዊ አገልግሎት ወይም ለመከላከያ ሠራዊት የሚያስፈልጉትን እንስሳት፣ ተሽከርካሪዎች፣

BACK



ምግቦች ወይም ማናቸውንም ሌሎች ዕቃዎች የማስረከብ ወይም የማቅረብ ሕጋዊ ግዴታ እያለበት ይህንን ግዴታውን ተገቢ ባልሆነ ምክንያት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በገባው የውል ግዴታ መሠረት ለወታደራዊ አገልግሎት ወይም ለመከላከያ ሠራዊት ሊያስረክብ ወይም ሊያቀርብ የተስማማውን ስንቅ፣ መሣሪያ፣ ዕቃ ወይም ማናቸውንም ሌሎች ዕቃዎች ወይም ለግዙፍ ሥራዎች፣ ለሕንፃዎች ወይም ለሕዝባዊ /Public/ ሥራዎች አገልግሎት የሚውል ማናቸውንም ነገር የማስረከብ ወይም የማቅረብ ግዴታውን ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በአጠቃላይ ሊያከናውናቸው የሚገባውን ሥራዎች፣ አገልግሎቶች፣ የማስረከብ ወይም የመረከብ ግዴታዎችን የተቆጣጠረው ወይም የተረከበው ወይም ያስረከበው የውል ግዴታዎችን ሳይከተል ወይም ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርግ በመቅረቱ በመከላከያ ሠራዊት ላይ ጉዳት በሚያደርስ አኳኋን ዘግይቶ ወይም ተግባሩን ሳይፈጽም ቀርቶ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል:: ወንጀሉ በጣም ከባድ እንደሆነ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ ቅጣቱ እንደነገሩ ሁኔታ ቀላል እስራት ወይም መቀጮ ይሆናል::

፫ ወንጀሉን የፈፀመው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፺ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል::

## አንቀጽ ፫፻፳፮ የተንኰል ሥራ /አሻጥር/

፩ ማንም ሰው እስቦ:-

ሀ/ ለመከላከያ ሠራዊት የሚያገለግሉ የተቋቋሙ ግዙፍ ሥራዎችን፣ ዕቃዎችን፣ መሣሪያዎችን፣ ወይም ማናቸውንም ሌላ ነገር ያፈረሰ፣ ያበላሸ፣ ወይም ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ አንድ ሹም ወይም ባለሥልጣን ለመከላከያ ሠራዊት የሚሰጠውን አገልግሎት እንዳይፈጽም የከለከለ፣ ወይም አገልግሎቱን ያወከ ወይም አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል::

፫ በመንግሥት የመከላከያ ኃይል ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በአንቀጽ ፪፻፵፯ መሠረት የሚያስቀጡ ይሆናሉ::

## አንቀጽ ፫፻፳፯ በወታደራዊ ዕቃዎች መነገድ

፩ ማንኛውም ሰው እስቦ፣ በመከላከያ ሠራዊት የአስተዳደር አካላት ተወርሰው፣ ወይም ለመከላከያ ሠራዊት እንዲያገለግሉ በሕግ አግባብ ከሕዝብ ተወስደው በአገልግሎት ላይ የሚገኙትን ዕቃዎች ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ያዋሰ፣ በዕዳ ያስያዘ፣ በተውሶ ወይም በመያዣነት የተቀበለ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

BACK



፪ ማንም ሰው ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን ዕቃዎች የሸጠ፣ የገዛ፣ ወይም ሙሉ በሙሉ ለጥቅሙ ያዋለ ወይም ያጠፋ፣ ያፈረሰ፣ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ያደረገ እንደሆነ፤

ቢያንስ በስድስት ወር ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

፫ ነገሩ ከባድ በሚሆንበት ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ያስቀጣል፡፡

፬ ወንጀሉን የፈፀመው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፺ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል፡፡

<u>አንቀጽ ፫፻፳፱ የመከላከያ ሠራዊት የደንብ ልብስን፣ ምልክትንና ሽልማትን ያለአግባብ ማምረትና ለንግድ ማዘዋወር</u>

፩ ማንም ሰው ሳይፈቀድለት ወታደራዊ የደንብ ልብሶችን፣ ምልክቶችን ወይም ሽልማቶችን የሠራ፣ ያከማቸ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ፣ የገዛ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በእጅ ያስገባ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉን የፈፀመው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፺ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል፡፡

<u>አንቀጽ ፫፻፴ የመከላከያ ሠራዊት የደንብ ልብስን፣ ምልክትንና ሽልማትን በማይገባ መልበስ</u>

ማንም ሰው ሳይፈቀድለት ወታደራዊ የደንብ ልብሶችን፣ ምልክቶችን ወይም ሽልማቶችን ለብሶ ወይም አድርጎ የተገኘ እንደሆነ፤

BACK



ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፴፩ ወታደራዊ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መጣስ

፩ ማንም ሰው ለመከላከያ ሠራዊት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ወይም ወታደራዊ ጥቅምን ለመጠበቅ መንግሥት ወይም የሚመለከተው የሲቪል ወይም ወታደራዊ ባለሥልጣን ያወጣውን ደንብ፣ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በዚህ ሕግ በሌላ ድንጋጌ በተለይ የሚቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፴፪ ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዲጣሱ ለማድረግ ሌላውን ሰው ማነሣሣት

፩ ማንም ሰው ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዳይፈጸሙ፣ ሥነ ሥርዓት እንዳይከበር ወይም ወታደራዊ ግዴታ እንዲጣስ በአደባባይ ቢሆንም ባይሆንም ያነሳሳ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ይህንኑ ወንጀል ለመፈጸም ቡድን፣ ንቅናቄ፣ ወይም ሕገወጥ ስብሰባ ያደራጀ ወይም በቡድኑ፣ በንቅናቄው ወይም በሕገወጥ ስብሰባው ተካፋይ እንደሆነ፤ ወይም በሥራው ዕቅድ ውስጥ የገባ ወይም ማህበርተኛ በመሆን ተካፋይ የሆነ ወይም ለዚህ አይነት ድርጊት አስተዋፅኦ ያደረገ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም ይህ አድራጐት ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ በተለይ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፫ ወንጀሉን የፈፀመው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፺ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል።

## <u>አንቀጽ ፫፻፵፫ የተወሰኑ ወታደራዊ ሥፍራዎችን እና ዕቃዎችን ለመጠበቅ የወጡ ክልከላዎችን መጣስ</u>

ማንም ሰው ያለፈቃድ ወይም ሕገወጥ በሆነ መንገድ፡-

፩ በወታደራዊ ባለሥልጣኖች ወይም ወታደራዊ በሆኑ ምክንያቶች ሰው እንዳይደርስበት በተከለከለ ወታደራዊ ሥፍራ፣ የሥራ ቦታ ወይም በማናቸውም ሌላ ሥፍራ ገብቶ የተገኘ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ይህንን የመሳሰለ ወታደራዊ ሥፍራ፣ የሥራ ቦታ ወይም ማናቸውም ሌላ ሥፍራ ወይም ይህን በመሰለ ሥፍራ የሚገኝ የሥራ ቦታን ወይም የመሣሪያን ወይም የሌላ ዕቃ መግለጫን፣ ፕላንን፣ ንድፍን፣ ፎቶግራፍን ወይም ማናቸውም ሌላ ምስልን የሠራ፣ የወሰደ፣ ያዘጋጀ፣ ያባዛ፣ የገለጸ ወይም ለሌላ ሰው አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

## <u>አንቀጽ ፫፻፵፬ ጠቅላላ ትዕዛዞችን ወይም መመሪያዎችን ወደሐሰት መለወጥ ወይም ማጥፋት</u>

፩ የአንቀጽ ፫፻፴፱ እና ፫፻፹፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰው አስቦ፡-

ሀ/ ወታደራዊ ምልመላ ወይም ወታደራዊ አገልግሎት የሚመለከታቸው ዜጎችን ወይም የመከላከያ ኃይሎችን ጥቅም ወይም ፍላጐት በሚመለከት የተደረገ ማናቸውንም ዓይነት ትዕዛዝን ወይም ለወታደራዊ አገልግሎት ዕቃ እንዲቀርብ የተሰጠ ትዕዛዝን አስመስሎ የሠራ ወይም ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ፣ ያጠፋ ወይም እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ይህን አስመስሎ የተሠራውን ወይም ወደ ሐሰት የተለወጠውን ትዕዛዝ ወይም መመሪያ የተገለገለበት እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም እንደነገሩ ከባድነት ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፫፻፴፫ በመከላከያ ሠራዊት እና በወታደራዊ ግዴታዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን አለማስታወቅ

፩ ማንኛውም ሰው ወታደራዊ ኩብለላ ወይም የወታደራዊ አመፅ ወንጀል መዘጋጀቱን ወይም መፈጸሙን እያወቀ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖር ለባለሥልጣን ሳያስታውቅ የቀረ ወይም እንዳይፈጸም ለማገድ ወይም ወንጀለኛው እንዲያዝ የሚቻለውን ያላደረገ እንደሆነ፤

የኩብለላ ወይም የአመጹ ወንጀል ቢያንስ የተሞከረ እንደሆነ፤ በቀላል እሥራት፣ ነገሩ ከባድ ሲሆን ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀልን ለባለሥልጣን የማስታወቅ ግዴታን ባለመፈጸም ለተደረገ ወንጀል የሞያ ወይም የሥልጣንን ምስጢር መብት እንደመከላከያ አድርጐ ለማቅረብ አይቻልም። ወንጀሉ የተፈጸመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ የስጋ ዝምድናንና በፍቅር ወዳጅነት የተሳሰረ ግንኙነትን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አድርጐ ለማቅረብ አይቻልም /አንቀጽ ፹፫/።

፫ የከዳትና የስለላ ወንጀሎችን አለማስታወቅ፣ ስለአገር ደህንነትና ስለአገር መከላከያ ኃይሎች አጠባበቅ በዚህ ሕግ በተደነገገው ድንጋጌ መሠረት ያስቀጣል /አንቀጽ ፪፻፶፬/።

<u>አንቀጽ ፫፻፺፯ ወታደራዊ ምስጢርን መግለፅ</u>

፩ ማንኛውም ሰው በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፪፻፵፰-፪፻፶፪ ከተደነገጉትና በተለይ ከፍ ያለ ቅጣት ከሚያስከትሉት የከዳትና የስለላ ወንጀሎች ውጭ በሆነ ሁኔታ በጠ ቅላላው በሕዝብ ዘንድ በግልፅ ያልታወቁትንና በጠ ባያቸው ከፍተኛ ቁም ነገር በመያዛቸው ምክንያት ላልተፈቀደለት ሰው ወይም ለሕዝብ እንዳይገለጹ በምስጢር የሚጠበቁትን ወታደራዊ ምስጢርነት ያላቸውን ማናቸውንም ዓይነት ሰነዶች ወይም መረጃዎች ላልተፈቀደለት ሰው ወይም ለሕዝብ የገለጸ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የሚመለከተው በተለይ የተጠበቁትን ሰነዶች ወይም መረጃዎች እንደሆነ፤ ወይም ወንጀለኛው እነዚህን ሰነዶች በሚገባ የሚያውቃቸው ወይም እንዲጠብቃቸው የተመደበ ወይም አደራ የተቀበለ ሠራተኛ እንደሆነ፤ ወይም ወንጀሉ ከባድ ወይም የተለየ አደጋ ሊያስከትል የሚችል እንደሆነ፤

BACK



ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማያንስ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ በንዑስ አንቀጽ /፩/ ለተመለከተው ድርጊት ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት፤ በንዑስ አንቀጽ /፪/ ለተመለከተው ደግሞ ከሶስት ዓመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፫፻፴፯ የሀሰት ወይም የሚያደናግር መረጃ</u>

ማንም ሰው ወታደሮች በእንቅስቃሴ ላይ ሆነው ወይም ተግባራቸውን በመፈጸም ላይ እያሉ ለወታደራዊ ጥቅም ተብሎ የታዘዘውን የጥንቃቄ እርምጃ ለማሰናከል ወይም ለማገድ ወይም የመከላከያ ሠራዊት እንቅስቃሴዎችን ወይም የውጊያ ዕቅዶችን ለማሰናከል ወይም የሚያሰናክል አደጋ እንዲደርስባቸው ለማድረግ፤ ወይም ወታደሮች ከሥነ ሥርዓት ውጭ እንዲሆኑ ወይም እንዳይታዘዙ ለማነሳሳት ወይም በህዝቡ መካከል አለመረጋጋትና ሁከት እንዲነሳ ለማበረታታት፤ ትክክል አለመሆናቸውን እያወቀ አስቦ የሐሰት ወሬዎችን የነዛ ወይም ያሰራጨ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት፣ ወይም ወንጀሉ ከባድ ሲሆን እስከ ዕድሜ ልክ ሊደርስ በሚችል ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>የወል ድንጋጌዎች</u>

<u>አንቀጽ ፫፻፴፰ በአደጋ ወይም በጦርነት ጊዜ ቅጣት የሚከብድበት ሁኔታ</u>

፩ ከዚህ በላይ ባሉት ሁለት ክፍሎች ውስጥ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱ የተፈጸመው በሥራው ላይ ባለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ላይ ወይም በመከላከያ ኃይል ወይም በአጋዥ ኃይል ላይ ወይም በወታደራዊ ጥቅሞች

BACK



ላይ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ ጠቅላላ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነና ቅጣቱን የሚያከብድ ሌላ ልዩ ድንጋጌ ከሌለ ፍርድ ቤቱ:-

ሀ/ በቀላል እሥራት ምትክ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት፣

ለ/ ቅጣቱ ጽኑ እሥራት በሆነ ጊዜ በዚህ ሕግ ጠቅላላ ክፍል ስለጽኑ እሥራት የተደነገገው ከፍተኛ የቅጣት ጣራ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት አጠፌታ ድረስ ከፍ በማድረግ፣

ለመወሰን ይችላል:: ቢሆንም የኩብለላ ወይም የአመጽ ወንጀልን ወይም ዕቅድን አለማስታወቅ /አንቀጽ ፫፻፴፰/ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ያስቀጣል::

፪ ወንጀሉ በቸልተኛነት ሲፈጸምና እንደሚያስቀጣ በሕጉ ላይ ተደንግጉ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ:-

ሀ/ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ምትክ ከሶስት ዓመት የማይበልጥ የፅኑ እሥራት ቅጣት፣

ለ/ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ምትክ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ የፅኑ እሥራት ቅጣት፣

ለመወሰን ይችላል::

፫ ፍርድ ቤቱ መቀጮ በሚወስንበት ጊዜ፣ ተፈጻሚ በሆነው ድንጋጌ መሠረት ሕጉ የደነገገውን የመቀጮ መጠን አጠፌታ ድረስ ለመወሰን ይችላል::

<u>አንቀጽ ፫፻፴፱ በአፍቅሮ ንዋይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

የጽኑ እሥራት ቅጣትን የሚያስከትሉ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ ሁሉ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ ምክንያት እንደሆነ እንደነገሩ ከባድነትና እንደወንጀለኛው

የሀብት መጠን ፍርድ ቤቱ ከእሥራት ቅጣቱ ጋር ከመቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ አጣምሮ ሊወስን ይችላል።

## ምዕራፍ ሦስት

## ከአንቀጽ ፪፻፹፩ - ፫፻፴፱ የተደነገጉት ሁኔታዎች በፖሊስ ላይም ተፈፃሚ መሆናቸው

### አንቀጽ ፫፻፵ የአፈፃፀም መርህ

ከዚህ በላይ ባሉት ሁለት ምዕራፎች ውስጥ ቅጣትን ያስከትላሉ ተብለው ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱን የፈፀመው የፖሊስ አባል እንደሆነ ወይም ወንጀሉ የተፈፀመው በሥራ ላይ ባለ የፖሊስ አባል ላይ እንደሆነ፣ ይህ ወንጀል በሌላ ድንጋጌ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣ ከዚህ በላይ ባሉት ሁለት ምዕራፎች ውስጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ /አንቀጽ ፪፻፹፩ - ፫፻፴፱/።

### አንቀጽ ፫፻፵፩ ልዩ ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ ከአንቀጽ ፪፻፹፩ - ፫፻፴፱ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፖሊስ አባላት ላይ ተፈፃሚ በሚሆኑበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ የፖሊስን ልዩ ተግባርና አቋም ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

### አንቀጽ ፫፻፵፪ የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በፖሊስ ላይ ተፈፃሚ መሆናቸው

፩ በፖሊስ ተቋም፣ በአገልግሎት ግዴታና ደህንነት ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ከዚህ በላይ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በተጨማሪ በዚህ ሕግ የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፬፻፪ እስከ ፬፻፳፮/ በፖሊስ አባሎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፪ የወንጀሉ ድርጊት በዚህ ርዕስ ወይም በአራተኛው መጽሐፍ በርዕስ ሦስት ድንጋጌዎች ሥር በተለይም የአገልግሎት ግዴታዎችን ስለመጣስ /አንቀጽ ፪፻፺፫ ወይም ፬፻፳/፣ ያለአግባብ ጥቅምን ስለማግኘት፣ ያለአግባብ ስለማጥፋት ወይም ሥራዎችን በማያመች አኳኋን ስለመምራት /አንቀጽ ፫፻፮ እና ፫፻፯ ወይም ከአንቀጽ ፬፻፯ እስከ ፬፻፲፱/፤ እንዲሁም የሥራ ምስጢርን ስለመግለጽ /አንቀጽ ፫፻፴፮ ወይም አንቀጽ ፫፻፺፮ እና ፫፻፺፯/ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ሊያስቀጣ የሚችል ሆኖ ሲገኝ፣ ፍርድ ቤቱ ወንጀሉ ወታደራዊ ጠባይ የያዘ ወይም የመንግሥት ሠራተኛን የሚመለከት መሆኑን በመመርመር ተገቢ ሆኖ የሚያገኘውን ድንጋጌ ተፈጻሚ ያደርጋል::

<u>ርዕስ አራት</u>

<u>በመንግሥት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

<u>አንቀጽ ፫፻፵፫ ልዩ ሕጎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

፩ በሕግ መሠረት ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል በአገር የገንዘብ ወይም የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የሚፈጸም ማናቸውንም ጉዳት ለመቆጣጠር ወይም ለመከላከል በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ወይም በክልል መንግሥታት የሕግ ጋዜጣ ላይ የሚወጣን ሕግ በመጣስ ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ፤ ቅጣቱ በዚህ የወንጀል ሕግ በተመለከቱት መርሆች መሠረት ይወሰናል::

፪ በደንብ መተላለፍ የተደነገጉትን ወይም በዚህ ዓይነት ያልተመለከቱ የደንብ መተላለፍ ጠባይ ያላቸውን የሚያዙ ወይም የሚከለክሉ ድንጋጌዎችን በመጣስ ወንጀል በሚፈጸምበት በማናቸውም ጊዜ የወንጀሉ መፈፀም ያስከተለው ጉዳት ከአስር ሺህ ብር ያልበለጠ

እንደሆነ፣ የሚወሰነው ቅጣት በዚህ ሕግ ስለደንብ መተላለፍ በተደነገጉት አንቀጾች መሠረት ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ ፫፻፹፩ የወንጀል ቅጣቶች ዓይነታቸውና መጠናቸው</u>

፩ ጉዳዩን የሚመለከቱት ሕጎች በዚህ የወንጀል ሕግ ወደተደነገገ ወንጀል በግልጽ የማይመሩ ሆነው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በዚህ የወንጀል ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎችና መደበኛ የቅጣት ወሰን መሠረት ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይወስናል /አንቀጽ ፺ - ፺፪፣ ፩፻፮ እና ፩፻፯/፡፡

፪ ጥፋቱ ከባድ ሆኖ ወንጀሉም የተፈጸመው በብዙ ገንዘብ ወይም ከፍ ያለ ግምት ባለው ዕቃ ላይ እንደሆነ ወይም በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺፪ እንደተደነገገው ወንጀለኛው ወንጀሉን እንደዋና ሥራው አድርጐ የሚጠቀምበት ሆኖ ሲገኝ፣ ፍርድ ቤቱ በወንጀሉ ሥራ የተገኘው ጥቅም እንዲወረስ ከማድረግ በተጨማሪ ጥፋተኛው ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ እንዲከፍል ለመወሰን ይችላል፡፡

፫ ስለመከላከል፣ ስለመጠበቅና ስለማገድ እንዲሁም በተጨማሪነት ስለሚወሰኑት የመግለጫና የማስታወቂያ እርምጃዎች የተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች የሚጠቅሙ መሆናቸውን ፍርድ ቤቱ ባመነ ጊዜ ተጨማሪ አድርጐ ሊወስን ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ ፫፻፹፪ ተደራቢ የቀረጥና የግብር ቅጣቶች</u>

በቀረጥና በግብር ላይ ስለሚደርሰው ጥፋት በወንጀል በኩል የሚወሰነው ማናቸውም ቅጣት፣ ቀረጥና ግብር

በጊዜው ባለመከፈሉ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሚወሰኑትን ቅጣቶች አያስቀርም::

## ምዕራፍ ሁለት

## ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፫፻፵፮ በወርቅ፣ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ መነገድ

ማንም ሰው በገንዘብ ላይ ጥፋት የሚፈፅመውን ወንጀለኛ ስለመቅጣት በወንጀል ሕጉ ድንጋጌ /ከዚህ በታች ባለው በአምስተኛው ርዕስ/ ላይ ከተመለከተው ውጭ በአንድ በተወሰነ ሁኔታ፣ በገደብ፣ በቁጥጥር ወይም በልዩ ጥበቃ፣ ንግድ ወይም የምንዛሪ ሥራ የሚካሄድበትንና የአገር ወይም የውጭ አገር ሀብት የሆነውን ወርቅ ወይም ማናቸውንም የውጭ አገር ገንዘብ፣ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ሕግን በመጣስ የገዛ፣ ከውጭ አገር ያስመጣ ወይም ወደ ውጭ አገር የላከ፣ በአደራ አስቀማጭነት የተቀበለ፣ ያስቀመጠ፣ የመነዘረ፣ የሸጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ፣

ይህን ወንጀል የፈፀመበትን ሀብት የመውረስ ደንብ የሚጸናበት መሆኑ ሳይቀር ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከሃምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

### አንቀጽ ፫፻፵፯ በከበሩ ማዕድናት ሕገወጥ በሆነ መንገድ መነገድ

ከዚህ በላይ ባለው አንቀጽ በተመለከተው አኳኋን ማንም ሰው ሕገወጥ በሆነ መንገድ የከበሩ ማዕድናት እንደወርቅ፣ ፕላቲንም፣ ዩራኒየም እና ሌሎችንም እነዚህን የመሳሰሉ ማዕድናት እንዲሁም የከበሩ ድንጋዮችን ለመጠበቅ ወይም ሕገወጥ ዝውውርን

ለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ በመጣስ ወንጀል ያደረገ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፵፮ የተወሰነው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

## አንቀጽ ፫፻፵፯ በመንግሥት ገንዘብ አስተማማኝነት ላይ የሚደረግ የተንኮል ድርጊት

ማንም ሰው በመንግሥት ፋይናንስ አስተማማኝነት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማቀድ ወይም ድርጊቱ ጉዳት ለማድረስ እንደሚችል እያወቀ፡-

ሀ/ ያገሪቱ የገንዘብ ምንዛሪ እንዲረክስ ለማድረግ ከባንክ ወይም ወደ ባንክ ለማስገባት በሕግ ግዴታ ከተጣለባቸው ሌሎች ድርጅቶች ገንዘብ እንዲወጣ ያደረገ ወይም ያነሳሳ ወይም የዋስትና ሰነዶች ወይም የግዴታ ሰነዶች በጅምላ በመሸጥ ዋጋቸው ዝቅ እንዲል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ እነዚህን ገንዘቦች፣ የዋስትና ሰነዶች ወይም የግዴታ ሰነዶች ሌላ ሰው እንዳያወጣ ወይም እነዚህኑ እንዳይገዛቸው ያሰናከለ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሀምሳ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤ ወይም ወንጀሉ ከባድ ውጤት ያስከተለ ወይም የሚያስከትል እንደሆነ ከሀያ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

## አንቀጽ ፫፻፵፱ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የመንግሥትን ቀረጥ ወይም ግብር የመክፈል እንቢተኛነት

፩ ማንም ሰው በሕግ የተደነገገውንና በሚመለከተው ባለሥልጣን በአግባቡ የተወሰነውን ከመሬት፣ ከንብረት ወይም ከልዩ ልዩ ገቢ በዓይነትም ሆነ በገንዘብ ሊከፍለው የሚገባውን ግብር ወይም ማናቸውንም

ዓይነት ቀረጥ ወይም ታክስ እንዲከፍል በሕግ አግባብ ሲጠየቅ፣ ለመክፈል እንቢተኛ የሆነ እንደሆነ፤

ግብሩን ወይም ማናቸውንም ዓይነት ቀረጥ ወይም ታክስ የመክፈል ግዴታው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ እንቢተኛነቱ ዛቻን፣ የኃይል ሥራን፣ የእጅ እልፊትን ወይም በጦር መሣሪያ የመገልገልንና መሣሪያ አንስቶ የመቃጣትን ወይም ሁከትን ወይም አመጽን አስከትሎ እንደሆነ ጉዳዩን በሚመለከተው ድንጋጌ መሠረት የተደነገገው ቅጣት ተጣምሮ ይፈጸምበታል /አንቀጽ ፹፯/::

## አንቀጽ ፫፻፱ ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት

፩ ማንም ሰው በአድራጐት፣ በስጦታ፣ በንግግር፣ በዛቻ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ ሌላውን ሰው በሕግ የተደነገገውን ቀረጥ ወይም ግብር እንዳይከፍል ያነሣሣ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ በወንጀሉ ድርጊት መስፋፋት ምክንያት ሁኔታው ከባድ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሶስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራትና መቀጮ ይሆናል::

ወንጀሉ አመጽን ለመቀስቀስ ወይም ባለሥልጣንን ለማስወገድ ማነሳሳትን ወይም የመሣሰሉትን በሚመለከቱ ከባድ ድንጋጌዎች የሚያስጠይቅ ከሆነ የወንጀሎች መደራረብን በሚመለከት አግባብነት ባለው ድንጋጌ ቅጣቱ ይከብዳል /አንቀጽ፹፮/::

## አንቀጽ ፫፻፶፩ በመንግሥት የገቢ ምንጮች ላይ ጉዳት ማድረስ

፩ ማንም ሰው በሕግ የተወሰነውንና ለመንግሥት ግምጃ ቤት ገቢ ሊሆን የሚገባውን ማናቸውንም ዓይነት ግብር፣ ቀረጥ ወይም ሌላ ክፍያ በከፊል ወይም በሙሉ እንዳይከፍል ራሱን ወይም ሌላ ግለሰብን ወይም የሕግ ሰውነት ያለውን ድርጅት ለማዳን አስቦ:-

ሀ/ ቀረጥ ወይም ግብር ሊወሰንበት የሚገባውን ዕቃ ወይም ካፒታል ወይም ገቢን በሚመለከት ወይም ቀረጡን ወይም ግብሩን ለመወሰን አግባብነት ባላቸው በማናቸውም ሁኔታ ላይ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እያወቀ ሐሰተኛ መረጃ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በማናቸውም ሌላ ዓይነት ዘዴ ለዚሁ ጉዳይ ስልጣን የተሰጣቸውን የመንግሥት አካላት ከስህተት ላይ እንዲወድቁ እያወቀ ዕውነቱን ወደሐሰት በመለወጥ፣ ነገሩን በመሰወር ወይም ሐሰተኛ ገቢ ወይም የፈጠራ ሂሳብ በማዘጋጀት ወይም በማናቸውም ይህን በመሳሰለ አድራጎት ያሳሳተ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ ማንኛውም ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ተገቢ ባልሆነ መንገድ፣ ግብር ወይም ቀረጥ እንዳይከፈል ወይም እንዲቀነስ ያደረገ እንደሆነ፤ በሥልጣን ያለአግባብ በመገልገል (አንቀጽ ፬፻፯) ተጠያቂ ይሆናል።

፫ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው ሌሎች ወንጀሎችን በተለይም የማታለል ወንጀልን ወይም ሐሰተኛ ሰነድ የመፍጠር ወንጀልን በሚያቋቁሙ ሁኔታዎች እንደሆነ እነዚህን ወንጀሎች የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ተጣምረው ይፈፀሙበታል /አንቀጽ ፷[illegible]/።

BACK



## አንቀጽ ፫፻፶፪ ኬላ መስበር /ኮንትሮባንድ/

፩ ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ በሕግ የተወሰነው ቀረጥ ወይም ግብር ያልተከፈለበትን ማናቸውንም ዓይነት የንግድ ዕቃ፣ ንብረት፣ ልዩ ልዩ ዕቃ ወይም የፋብሪካ ወይም የእጅ ጥበብ ሥራ የሚያፈራውን ማናቸውንም ዓይነት ነገር ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ያስወጣ ወይም ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ ያስገባ እንደሆነ፤

ለ/ ከላይ በፊደል (ሀ) በተመለከተው ሕገወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ መግባቱን እያወቀ፣ ይህንኑ ዕቃ ወይም ንብረት ያከማቸ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በአገር ውስጥ ተመርተው ቀረጥ ሳይከፈልባቸው እንዳይዘዋወሩ የተከለከሉ ዕቃዎችን ወይም ምርቶችን ያዘዋወረ እንደሆነ፤

በቅን ልቡና ለወንጀሉ ባዕድ የሆኑት ሰዎች መብት ሳይነካ፣ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ዕቃ፣ መጓጓዣ እና የወንጀሉን ፍሬ ስለመውረስ የተደነገገው ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም በቀላል እሥራት ይቀጣል /አንቀጽ ፩፻፵/::

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በኃይል፣ በዛቻ፣ በማጭበርበር ወይም በቡድን ከሆነ፤ ዕቃው ውርስ ሆኖ፣ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ያስቀጣል::

BACK



፫ በጉምሩክ ውስጥ ለጊዜው ብቻ በድንገት በሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ተግባሮች ላይ የሚወሰነው ቅጣት ስለደንብ ተላላፊዎች በተደነገገው መሠረት ይሆናል /አንቀጽ ፯፻፹፩/::

## አንቀጽ ፫፻፶፫ በአገር ኢኮኖሚና በመንግሥት ሞኖፖል ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

፩ ማንም ሰው ከዚህ በላይ በተለይ ከተመለከቱት ወይም በደንብ መተላለፍ ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ /አንቀጽ ፯፻፹፩ - ፯፻፺/:-

ሀ/ የተከለከሉትን ወይም ፈቃድ ወይም ቁጥጥር ወይም ቀረጥ መክፈል የሚያስፈ ልጋቸውን ዕቃዎች፣ ምርቶች ወይም ቁሳቁሶች ከውጭ አገር ማስመጣትን ወይም ወደ ውጭ አገር መላክን፣ ማስቀመጥን፣ ማመላለስን፤ ወይም

ለ/ ከአገሩ መሬት ላይ ወይም ከመሬት ውስጥ ሀብት በሚገኘው ፍሬ መጠቀምን፣ በኤሌክትሪክ ኃይል መገልገልን፣ በውሃዎች፣ በደኖች ወይም በማዕድናት ሀብትና በሚሰጡት ፍሬ መጠቀምን፤ ወይም

ሐ/ በዱር እንስሳት ወይም በፍሬአቸው መጠቀምን ወይም እነዚህኑ እንስሳት ማደንን ወይም መግደልን፣ ወይም

መ/ በተከለሉ ደኖች፣ ፓርኮች ወይም በጥብቅ በታዎች መስፈርን ወይም ሌሎች ተግባራት ማከናወንን፣ ወይም

ሠ/ በመንግሥት ፈቃድ ብቻ የተቋቋመውን ወይም መንግሥት በሞኖፖል የሚቆጣጠረውን ሥራ፤ ወይም

BACK



ረ/ የመንግስት ባንክ ወይም የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን አቋም ወይም የኮንሴሽን አሰጣጥን ወይም የባንክ፣ የንግድም ሆነ የኢንዱስትሪ ድርጅቶችን፣ ፋብሪካዎችን፣ የእህል ወፍጮዎችን ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉ ሆቴሎችን ወይም የማናቸውንም ተቋማት አሠራርና ቁጥጥርን፤

አስመልክቶ የወጡ ድንጋጌዎችን አስቦ የጣሰ እንደሆነ፤

ተግባሩ ከፍ ያለ ቅጣት በሚያስወስን ልዩ ድንጋጌ ውስጥ ያልተመለከተ ሲሆን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ወንጀሎች አድርጎ በመገኘቱ ወንጀል የተፈፀመበት ንብረት የሚወረስበት፣ የንግድ ፈቃዱና የሥራ ምስክር ወረቀቶች የሚወሰድበት፣ የኢንስዱስትሪ ሥራውን እንዳይቀጥል የሚታገድበት፣ ወይም የንግድ ቤቱ የሚዘጋበት መሆኑ ሳይቀር፣ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው የጄኔቲክ ሀብት መሰብሰብን፣ ማጓጓዝን፣ ማስተላለፍን፣ ከአገር ማስወጣትን ወይም ወደ አገር ማስገባትን ወይም መጠቀምን አስመልክቶ የወጣን ሕግ የጣሰ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከብር አሥር ሺህ እስከ ሰላሳ ሺህ ለመድረስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል::

፫ ማንም ሰው ሕግን በሚቃረን መንገድ ብርቅዬ እንስሳትን ያደነ ወይም የገደለ እንደሆነ፤ ወይም ብርቅዬ እንስሳትን ወይም እፅዋትን ወይም

BACK



ውጤታቸውን ይዞ የተገኘ፣ የሰበሰበ፣ ያጓጓዘ፣ ያስተላለፈ፣ ወይም ከአገር ያስወጣ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት፤ ወይም ከአስራ ሁለት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከሃምሣ ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል::

፬ በዚህ አንቀጽ ከተመለከቱት ድርጊቶች አንዱ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ወይም እንደነገሩ ሁኔታና እንደወንጀሉ ከባድነት ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፫፻፵፬ ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች</u>

፩ የተከለከለ ዕቃ የማስተላለፍ፣ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት የተደረገ ሕገወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ ወይም ከፍ ያለ ግምት ባለው ገንዘብ ላይ የተፈጸመ ወንጀል በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀለኛው ይህን የመሳሰለውን የማስተላለፍና በሕግ የተከለከለ ነገር መሥራትን የዘወትር የሞያ ሥራው ያደረገ እንደሆነ፤ የሚወሰንበት ቅጣት ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ እና ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፪ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ወንጀል የተደረገው የሕግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት እንደሆነ፤ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺ የተመለከተው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል::

BACK



## ርዕስ አምስት

## በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ማህተሞች፣ ቴምብሮች ወይም መሣሪያዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፫፻፶፰ የሕግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት የሚመለከት ጠቅላላ ድንጋጌ

በዚህ ርዕስ ስር ከአንቀጽ ፫፻፶፯ እስከ ፫፻፸፬ ባሉት ድንጋጌዎች በተመለከቱት ወንጀሎች ላይ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፴፬ ሁኔታዎች ተሟልተው በሚገኙበት ጊዜ ግለሰቦች ብቻ ሣይሆኑ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅትም በወንጀል ይቀጣል::

## ምዕራፍ አንድ

## የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች

### አንቀጽ ፫፻፶፯ መሥራት

ማንም ሰው በኢትዮጵያ ወይም በውጭ አገር እንደእውነተኛ አድርጐ ለማዘዋወር በማሰብ ሕጋዊ መገበያያ የሆኑትን ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ያለፈቃድ የሰራ ወይም አስመስሎ የሰራ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

### አንቀጽ ፫፻፶፯ ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ

ማንም ሰው ሕጋዊ መገበያያ የሆኑትን ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ከእርግጠኛ ዋጋቸው በላይ በሆነ ዋጋ እንዲዘዋወሩ ለማድረግ በማሰብ መልካቸውን በመለዋወጥ፣ እውነተኛ መልካቸው ላይ ሌላ ነገርን በመጨመር ፣ ቀለማቸውን በመለዋወጥ ወይም በሌላ

ዓይነት ዘዴ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ አገር ወደ ሐሰተኛነት የለወጣቸው እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፶፫ ዋጋውን ዝቅ ማድረግ

ማንም ሰው በኢትዮጵያ ወይም በውጭ አገር ሙሉ ዋጋውን እንደያዘ መገበያያ እንዲሆኑ በማሰብ በሜካኒካል፣ በፊዚካል ወይም በኬሚካል ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ ተጠቅሞ ሕጋዊ የሆኑትን ገንዘቦች ዋጋቸው ዝቅ እንዲል ያደረገ እንደሆነ፤
ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፶፬ ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ እና ማቅረብ

ማንም ሰው ሐሰተኛ የሆኑ ወይም ዋጋቸው ዝቅ እንዲል የተደረጉ ገንዘቦችን፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን እውነተኛ ወይም ሙሉ ዋጋቸውን እንደያዙ አስመስሎ ራሱ እንዲገበያይባቸው ወይም እንዲዘዋወሩ ለማድረግ በማሰብ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ ከአገር ያስወጣ ወይም የያዘ ወይም ያስቀመጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፶፭ የማዘዋወር አሳብ ግምት

ከአንቀጽ ፫፻፶፪ እስከ አንቀጽ ፫፻፶፬ የተገለፁትን ወንጀሎች በሚመለከት ድርጊቶቹ የተፈፀሙት ለማዘዋወር በማሰብ እንደሆነ ይገመታል::

<u>አንቀጽ ፫፻፷፩ ማዘዋወር</u>

፩ ማንም ሰው እስቦ:-

ሀ/ ሐሰተኛ የሆኑትን ወይም ወደ ሐሰተኛነት የተለወጡትን ገንዘቦች የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች እውነተኛ አስመስሎ ወይም ከተወሰነው የበለጠ ዋጋ እንዳላቸው አስመስሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከአገር ውጭ ያዘዋወረ እንደሆነ፤ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

ለ/ ዋጋቸው የተቀነሰውን ገንዘቦች ሙሉ ዋጋ እንደያዙ አስመስሎ እንዲዘዋወሩ ያደረገ እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው ገንዘቡን፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዱን እውነተኛ ነው በሚል እምነት ወይም በትክክለኛ ዋጋው ከተቀበለ በኋላ ሐሰተኛ መሆኑን ወይም ዋጋው መቀነሱን እያወቀ ከኪሣራ ለመዳን:-

ሀ/ ሐሰተኛ ወይም ወደ ሐሰተኛነት የተለወጠውን ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነድ እውነተኛ በማስመሰል ያዘዋወረ እንደሆነ፤
በቀላል እሥራት ይቀጣል፤

ለ/ ዋጋው የተቀነሰውን ገንዘብ ሙሉ ዋጋ እንዳለው በማስመሰል ያዘዋወረ እንደሆነ፤
በመቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፫፻፷፪ ቀላል ሁኔታ</u>

ከአንቀጽ ፫፻፶፮ እስከ አንቀጽ ፫፻፷፩ ያሉትን ወንጀሎች በሚመለከት የገንዘቡ መጠን አነስተኛ ግምት

የሚሰጠው በመሆኑ ወንጀሉ ቀላል በሚሆንበት ጊዜ ቅጣቱ ቀላል እሥራት ይሆናል።

## ምዕራፍ ሁለት

## የታወቁ ማህተሞችን፣ ቴምብሮችን፣ ምልክቶችን፣ ሚዛኖችንና መለኪያዎችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ

### አንቀጽ ፫፻፷፫ የመንግሥት ማህተሞችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ ወይም በማህተሞች ያለአግባብ መገልገል

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ ለመንግሥት ሥራ ጉዳይ ብቻ የሚታተምበትን የመንግሥትን ወይም ከመንግሥታዊ አካላት የአንዱን ማህተም ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሠራ፣ወይም ወደ ሐሰተኛነት በተለወጠ ው ወይም መስሎ በተሠራው ማህተም የተገለገለበት እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በእውነተኛው ማህተም ያለአግባብ የሠራበት እንደሆነ፣

ከሶስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ በአገር ጥቅም ወይም መብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ፣

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

### አንቀጽ ፫፻፷፬ የሌሎች የሕዝብ አገልግሎት ወይም የግል ድርጅቶችን ማህተም ወደ ሐሰት መለወጥና በማህተሞቹ ያለአግባብ መሥራት

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ የሕዝብ አገልግሎት ወይም የግል ድርጅትን ማህተም ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ ወይም ወደ ሐሰተኛነት በተለወጠው ማህተም የተገለገለ፣ ወይም

ለ/ እውነተኛ በሆነው ማህተም ያለአግባብ የሠራበት እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ፤ ከሶስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ያስቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፷፮ የታወቁ ምልክቶችን ወደሐሰት መለወጥ</u>

ማንም ሰው:-

ሀ/ እንደእውነተኛ ወይም እንዳልተሠራባቸው አድርጎ ያለአግባብ ሊሠራባቸው ወይም ሌሎች እንዲሠሩባቸው በማሰብ ያመጣጣቸውን ሥረ መሠረት ምልክት ወይም በግልጽ የታወቀውን መለያ ምልክት ወይም የጥራት ወይም የዋስትና ማረጋገጫ ምልክት፣ በተለይም የጉምሩክን ወይም የዕቃ ማመሳለስ ጉዳይን፣ ወይም የወርቅን፣ የብርን ወይም የሌሎች የከበሩ ማዕድናትን፣ ወይም የእንጨትን፣ የቆዳን ወይም የሌሎች ምርት ውጤቶችን፣ የምግብ ዕቃዎችን፣ የመድሃኒቶችን ወይም ለሕዝብ ጤና ጥበቃ ጠቃሚ የሚሆኑ ዕቃዎችን የሚመለከቱ ሲሆን ማህተሞች፣ በመሰርሰሪያ ማህተም የሚሠሩ ምልክቶች ወይም ማናቸውም ሌሎች መለያ መልክቶች ቢሆኑም እንኳ፤ ሕጋዊ ሥልጣን ሳይኖረው የሠራ፣ ወደሐሰተኛነት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ እንደነዚህ ያሉትን ወደ ሐሰተኛነት የተለወጡትን ወይም መስለው የተሠሩትን ምልክቶች እያወቀ እንደ እውነተኛ ወይም እንዳልተሠራባቸው በማስመሰል የሠራባቸው እንደሆነ፤

ከሶስት ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፷፯ ዋጋ ያላቸውን የታወቁ ቴምብሮች ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ እንደ እውነተኛ ወይም እንዳልተሠራባቸው በማድረግ ሊሠራባቸው ወይም ሌሎች እንዲሠሩባቸው በማሰብ ዋጋ ያላቸውን የታወቁ ቴምብሮች በተለይም ቴምብርነት ያላቸውን ወረቀቶች፣ የፖስታ ቴምብሮች፣ የገንዘብ መክፈያ ምልክት የሆኑ የታተሙ ቴምብሮች ሕጋዊ ሥልጣን ሳይኖረው የሠራ፣ ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ቴምብሮቹ ከተሠራባቸው ወይም ከተሰረዙ በኋላ እንደገና ሊሠራባቸው በማሰብ ገና ዋጋ እንዳላቸው አድርጐ የማስመሰል መልክ የሰጣቸው እንደሆነ፤

እጅግ ቢያንስ በሶስት ወር ቀላል እሥራት ወይም ጥፋቱ ከፍ ያለ ሆኖ ሲገመት ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ጥፋቱ ቀላል በሆነ ጊዜ በተለይም ቀድሞ በተሠራባቸው፣ ወደሐሰት በተለወጡ፣ ሐሰተኛ በሆኑ ወይም በተሰረዙ የፖስታ ወይም የቀረጥ ቴምብሮች በድንገት ተገልግሎ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መቀጮ ብቻ ለመወሰን ይችላል::

## አንቀጽ ፫፻፷፯ የመመዘኛ ክብደቶችንና መለኪያዎችን ወደሐሰት መለወጥ

፩ ማንም ሰው ሌላውን ሰው ለማታለል በማሰብ:-

ሀ/ የመመዘኛ ክብደቶችን ፣ ሚዛኖችን፣ መለኪያዎችን ወይም ለንግድ ወይም

BACK



ለመለዋወጫ የተመደቡትን ሌሎች መሣሪያዎችን ሐሰተኛ በማድረግ የለወጠ እንደሆነ፤

ለ/ ሕግ ከሚፈቅደው ውጭ የታወቁ የመቆጣጠሪያ የማረጋገጫ ዋስትናነት ያላቸውን መለያ ምልክቶችን ወይም ልዩ ልዩ ምልክቶችን በነዚህ መሣሪያዎች ላይ ያተመ ወይም እነዚህን የመለያ ምልክቶች አስመስሎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በነዚህ ሐሰተኛ ወይም ወደ ሐሰተኛነት በተለወጡት መሣሪያዎች አስቦ የሠራባቸው እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ጥፋቱ ቀላል በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከሶስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ለመወሰን ይችላል።

## አንቀጽ ፫፻፷፰ ከአገር ማስወጣት፣ ወደአገር ውስጥ ማስገባት፣ መግዛት፣ በአደራ ማስቀመጥና ማቅረብ

ማንም ሰው ሐሰተኛ መሆናቸውን ወይም ወደ ሐሰተኛነት መለወጣቸውን አስቦ ማህተሞችን፣ ቴምብሮችን፣ ቴምብርነት ያላቸውን ወረቀቶች፣ ምልክቶችን፣ በግልጽ የታወቁ መመዘኛ ክብደቶችን ወይም መለኪያዎችን ከአገር ያስወጣ፣ ወደአገር ውስጥ ያስገባ፣ የገዛ፣ በእጁ ያስገባ ወይም በባለአደራነት ለማስቀመጥ የተቀበለ፣ የሸጠ ወይም ለሽያጭ ወይም ለስጦታ ያቀረበ እንደሆነ ፤

BACK



በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

## ምዕራፍ ሶስት

## የወል ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፫፻፷፱ የማታለል አሳብ ሳይኖረው አስመስሎ መሥራት

፩ ማንም ሰው የማታለል አሳብ ሳይኖረው:-

ሀ/ ገንዘቦችን፣ የባንክ ኖቶችን፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን የታወቁ ባለዋጋ ቴምብሮችን ወይም የፖስታ ቴምብሮችን በማስመሰል የሠራ፣ በተለይም በማስታወቂያነት አስመስሎ ያወጣ ወይም አምሳያ አድርጐ እንዲዘዋወሩ ለማድረግ በማሰብ የማሳሳት አደጋ የሚፈጥር ወይም ለመፍጠር የሚችል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ እንደዚህ ያሉትን መስለው ወይም በአምሣያ የተሰሩትን ነገሮች ወደ አገር ያስገባ፣ ወደ ውጭ አገር ያስወጣ፣ በአደራ የተቀበለ፣ ለሽያጭ ወይም ለስጦታ ያቀረበ ወይም እንዲዘዋወሩ ያደረገ እንደሆነ፤

በመቀጮ፣ ወይም ሁኔታው ለማሳሳት ወይም ለማታለል በተለይ የሚያሰጋ በሆነ ጊዜ ከሶስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ማባዛቱ ለታወቀ ሳይንሳዊ ተግባር ወይም ለመረጃ አላማ ተደርጐ እንደሆነ ወንጀል አይሆንም::

### አንቀጽ ፫፻፸ በገንዘብ፣ በግዴታ ወይም በዋስትና ሰነዶች ወይም በታወቁ ምልክቶች፣ ቴምብሮች ወይም ማህተሞች ላይ አደጋ ማድረስ

ማንም ሰው አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወይም ተቋም በግልጽ ሳያዘው ወይም ሳይፈቀድለት:-

BACK



ሀ/ ለገንዘብ፣ ለግዴታ ወይም ለዋስትና ሰነዶች፣ ለታወቁ መለያ ምልክቶች፣ ለቴምብሮች፣ ለባለሥልጣን ማህተሞች /ቲተሮች/ ወይም ለማህተሞች ማተሚያ ወይም መሥሪያ የሚያገለግሉትን መሣሪያዎች፣ ፎርሞች፣ ከውሮች፣ ወረቀቶች፣ ሞዴሎች፣ ወይም ማናቸውንም ሌሎች ዓይነት ዕቃዎችን ወይም መሣሪያዎችን የሠራ፣ በእጁ እንዲገባ ያደረገ፣ ወደ አገር ያስገባ፣ ወደ ውጭ አገር ያስወጣ፣ ለሌላ ሰው ያቀረበ ወይም አሣልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች የታወቁ ምልክቶች፣ ቴምብሮች፣ የባለሥልጣን ማህተሞች /ቲተሮች/ ወይም ማህተሞች እንዲሠሩ ወይም እንዲታተሙ የሚሰጡትን ትዕዛዞች የተቀበለ፣ የፈፀመ፣ ያስፈፀመ፣ ያስረከበ ወይም ሌላው ሰው እንዲያስረክብ ያደረገ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

## <u>አንቀጽ ፫፻፴፮ ሐሰተኛ ነገሮችን ለመሥራት የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና መሥሪያዎች</u>

፩ ማንም ሰው በህገወጥ መንገድ ሊሠራበት በማሰብ ገንዘቦችን፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን፣ የታወቁ ምልክቶችን፣ ቴምብሮችን፣ የባለሥልጣን ማህተሞችን /ቲተሮችን/ ወይም ማህተሞችን ወደ ሐሰተኛነት ለመለወጥ ወይም አስመስሎ ለመሥራት የሚያገለግሉትን መሣሪያዎች፣ ፎርሞች፣ ከውሮች፣ ወረቀቶች፣ ማዕድኖች፣ ወይም ሌሎች ነገሮችን የሠራ፣ በእጁ ያስገባ፣ የያዘ ወይም ለሌላ የሰጠ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር ባላነሰ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ሆኖም መሣሪያዎቹና መሥሪያዎቹ ብሔራዊ ገንዘቦችን፣ የመንግሥትን ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን ማህተሞችን ሐሰተኛ አድርጐ ወይም አስመስሎ ለመሥራት የሚያገለግሉ ሆነው በተገኙ ጊዜ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፫፻፷፪ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች</u>

፩ በዚህ ርዕስ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንደኛውን በፈፀመ ሰው ላይ ፍርድ ቤቱ በልዩ ሁኔታ ቅጣትን ለማቃለል /አንቀጽ ፻፹/ የሚችለው ወይም የተለዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ከማናቸውም ቅጣት ነፃ ለማድረግ የሚችለው:-

ሀ/ ወደሀሰተኛነት ለመለወጥ የሚያገለግሉትን መሣሪ ዎች ወይም መሥሪያዎች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በራሱ ፈቃድ ያጠፋቸው እንደሆነ፤

ለ/ ወንጀሉ በባለሥልጣኖች ከመታወቁ በፊት በሕዝብ እጅ እንዳይዘዋወሩ፣ እንዳያ ገለግሉ ወይም አደጋ እንዳያደርሱ ያገደ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ የወንጀሉን መፈጸም ወይም መዘጋጀት የገለጸ ወይም ጥፋተኛው ለፍትሕ እንዲ ቀርብ ያደረገ እንደሆነ፤

ነው::

፪ ጥፋተኛው ከዚህ በላይ በተመለከቱት አድራጐቶች ምክንያት ቅጣት ቢወሰንበትም ባይወሰንበትም ለወደፊቱ አደጋ ሊያደርስ ይችላል ተብሎ የሚጠረጠር እንደሆነ የመልካም ጠባይ ማረጋገጫ ዋስትና እንዲሰጥ /አንቀጽ

፪፻፴፮/ወይም እንደአስፈላጊነቱ የግል ነፃነቱ እንዲቀነስ /ከአንቀጽ ፪፻፵፮-፪፻፶/ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል።

፫ ከዚህ በላይ ባሉት ሁለት ምዕራፎች እንደተመለከተው ሐሰተኛ ነገር የመስራቱ፣ ወደ ሐሰተኛነት የመለወጡ፣ ዋጋውን ዝቅ የማድረጉ ወይም ሐሰተኛ ገንዘብ የመሥራቱ ወንጀል እጅግ ቀላል እንደሆነ ወይም በመንግሥት ወይም በጠቅላላው ጥቅም ላይ አንዳች ከፍ ያለ ጉዳት የማያደርስ መሆኑ የተገመተ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በመደበኛ የቅጣት ማቅለያ /አንቀጽ ፻፸፱/ መሠረት ቅጣቱን ያቀልለታል።

## አንቀጽ ፫፻፸፫ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች

በዚህ ሕግ ጠቅላላ ክፍል የተመለከቱት የቅጣት ማክበጃ ደንቦች /አንቀጽ ፹፬/፩/መ// እና የመውረስ ደንቦች /አንቀጽ ፻፵/ እንደተጠበቁ ሆነው ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ ስሜት በተፈጸመ ጊዜ መቀጮው ከብር አንድ መቶ ሺህ የማይበልጥ ይሆናል።

ሐሰተኛ ገንዘብ የመሥራት ወንጀል ተፈጽሞ እንደሆነ መቀጮው ከብር አምስት መቶ ሃምሳ ሺህ የማይበልጥ ይሆናል።

## አንቀጽ ፫፻፸፬ የውጭ አገር መንግሥታትን ጥቅሞች መጠበቅ

የታወቁ የውጭ አገር ገንዘቦችን፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን፣ የባንክ ኖቶችን፣ ማህተሞችን፣ ቴምብሮችን፣ ምልክቶችን፣ የክብደት መመዘኛዎችን ወይም መለኪያዎችን፣ በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ በተደረጉ ልዩ ልዩ ወንጀሎች ላይ የዚህ ርዕስ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት ስለእንደዚህ ያለው ጉዳይ የተደረገ የዓለም አቀፍ ስምምነት ሲኖር ወይም በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ የውለታ መመላለስ ባለ ጊዜ ነው።

BACK



## አራተኛ መጽሐፍ

## በሕዝብ ጥቅሞችና በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ርዕስ አንድ

## በሕዝብ አመኔታ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ምዕራፍ አንድ

## ሐሰተኛ ሰነዶችን መፍጠር፣ ሰነዶችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥና ማጥፋት

### አንቀጽ ፫፻፸፮ በግዙፍ የሚፈፀም ሐሰት

ማንም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት፣ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፡-

ሀ/ ሕጋዊ ክርክሮች ሲካሄዱ በማስረጃነት የሚቀርቡ፣ አንድን ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ወይም የሚያረጋግጡ የሚመስሉ እንደ ጽሁፍ፣ ሌሎች ሰነዶች ወይም ግዙፍ ነገሮች የመሳሰሉትን የፈጠረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ሐሰተኛ ሰነድ ለማዘጋጀት በሌላ ሰው የጣት ፊርማ፣ ፊርማ፣ ምልክት ወይም ማህተም የተጠቀመ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ እውነተኛውን ጽሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ በሐሰተኛ ፊርማ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ አንድን ሰነድ፤ በተለይም የፈራሚውን ስም ወይም ፊርማ ወይም የሰነዱን ይዘት፣ አህዝ፣ ፍሬ ነገር ወይም ዝርዝር መግለጫ በሙሉ ወይም በከፊል

በመለወጥ፣ በማሻሻል፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም በማጥፋት፤ ወደሐሰተኛነት የለወጠ እንደሆነ፤

ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፸፮ ረቂቅ በሆነ መንገድ የሚፈፀም ሐሰት</u>

ማንም ሰው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፸፭ በተመለከተው የወንጀል አሳብ በመነሣት አንድ ሰነድ በሚዘጋጅበት ጊዜ ሕጋዊ ውጤት ያለውን ወይም ሊኖረው የሚችለውን ማናቸውንም ሐሰተኛ ፍሬ ነገር ያስገባ ወይም እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ፤
ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፸፭ በተደነገገው መሠረት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፸፯ ልዩ ሁኔታዎች</u>

ማንም ሰው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፸፭ በተመለከተው የወንጀል አሳብ በመነሳት:-

ሀ/ የአንድን ሰነድ ይዘት በተመለከተ በማሳሳት ሌላ ሰው ሌላ ሰነድ ወይም የተለየ ይዘት ያለው ሰነድ ላይ የፈረመ መስሎት እንዲሳሳት ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ፈቃዱ ባልሆነ ወይም በሌለ ሰው ስም ሰነድ የሰጠ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፸፭ በተደነገገው ቅጣት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፸፰ በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል</u>

ማንም ሰው በሐሰት በተዘጋጀ ወይም ወደሐሰት በተለወጠ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፸፭ በተደነገገው ቅጣት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፸፱ መንግሥታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም ወደ ሐሰት መለወጥ</u>

፩ በዚህ ምዕራፍ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱ የተፈፀመው:-

BACK



ሀ/ በአንድ የመንግሥት መዝገብ፣ በታወቀ ሰነድ ወይም የሕዝብን ጥቅም በሚመለከት ሰነድ ላይ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በመንግሥት ወይም በሕዝብ መዝገብ በገባ ሰነድ ወይም ሟች እራሱ በእጁ በጻፈው ኑዛዜ ላይ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ የአገር መከላከያን፣ የመከላከያ ሰራዊት አቋምን፣ ድርጅትን፣ የሥራ
ተግባርን ወይም ጉዳይ በሚመለከት ሰነድ ላይ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው እነዚህን የመሳሰሉትን መዝገቦች፣ ጽሁፎች፣ የታወቁ ሰነዶች ወይም ሌሎች ሰነዶችን እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ፣ እንዲጠብቅ ወይም ከነዚሁ ውስጥ ቅጂዎች እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

የወንጀሉ አፈጻጸም በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ የእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፫፻፹ ሰነዶችን ማጥፋት</u>

፩ ማንም ሰው በአንቀጽ ፫፻፸፭ በተመለከተው የወንጀል አሳብ በመነሳት ሊያዝበት መብት በሌለው በሌላ ሰው ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ፤

ነገሩ ቀላል ሲሆን ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት፤ ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው በቤተሰቡ አባል፣ በቅርብ ዘመዱ ወይም ከርሱ ጋር በጥቅም ወይም በፍቅር በተሳሰረ ወይም አብሮት በሚኖር ሰው ላይ እንደሆነ፤ ሊቀጣ የሚችለው በግል አቤቱታ አቅራቢነት ነው::

<u>አንቀጽ ፫፻፸፩ መንግሥታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን ማጥፋት</u>

፩ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፸ የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው በመንግሥት ወይም በሕዝብ ወይም በወታደራዊ ሰነዶች ላይ እንደሆነ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ነው::

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው እንደዚህ ያለውን ሰነድ እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ፣ እንዲጠብቅ ወይም እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሃያ አምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ነው::

የወንጀሉ አፈፃፀም በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ ቅጣቱ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ነው::

<u>አንቀጽ ፫፻፸፪ የንግድ ወይም ተላላፊ የዋስትና ሰነዶችን ወደ ሐሰት መለወጥና ማጥፋት</u>

፩ ሰነድን ወደሐሰት የመለወጠ ወይም በዚሁ የመገልገሉ ወይም ሌላው እንዲገለገልበት የማድረጉ ወንጀል

የተፈጸመው በሐዋላ ወረቀት፣ በቼክ፣ በተስፋ ሰነድ፣ በባንክ ደብተር፣ ወይም ለባንክ ማስረከቢያ በሆነ ሰነድ፣ የመገበያያ ካርድ ወይም በገንዘብ ማስቀመጫ ወይም ማበደሪያ ድርጅት ውስጥ በሚገኝ ሰነድ ወይም በአክሲዮን ሰነድ ላይ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

፪ በአንቀጽ ፫፻፹የተመለከተው ድርጊት በእነዚህ ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች ላይ የተፈፀመ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

፫ በአንቀጽ ፫፻፹የተመለከተው ድርጊት በነዚህ ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች ላይ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ነው::

## አንቀጽ ፫፻፹፫ እንደዋና የሚቆጠር ጽሁፍ ወይም ትክክለኛ ግልባጭ

በሕጉ መሠረት የዋናው ሰነድ ምትክ በሆኑ ትክክለኛ ግልባጮች ወይም እንደዋናው ሰነድ እንደሚቆጠሩ በተመሰከረላቸው ትክክለኛ ግልባጮች ላይ የሚፈጸም ወደሐሰተኛነት የመለወጥ ወይም የማጥፋት ድርጊት አግባብ ባላቸው በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች ያስቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፹፬ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ወረቀቶችንና የማጓጓዣ ወረቀቶችን ወደሐሰት መለወጥና በነዚሁ መገልገል

፩ ማንም ሰው በሌላ ሰው መብት ወይም የገንዘብ ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፡-

ሀ/ በየብስ፣ በባህር፣ ወይም በአየር ለሰዎች፣ ለእንስሳት ወይም ለዕቃዎች ወይም ለሸቀጦች

BACK



መመሳለሻ የሆኑትን የትራንስፖርት ወረቀቶች፣ ቲኬቶች ወይም የማጓጓዣ ሰነዶች ሕጋዊ ሥልጣን ሳይኖረው የሠራ ወይም ወደሐሰት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ እውነተኛ የሆኑትን እነዚህኑ ቲኬቶች፣ ደረሰኞች ወይም የማጓጓዣ ሰነዶች ካገለገሉ፣ ከተሰረዙ ወይም ከተበሱ በኋላ እንደገና ሊገለገልባቸው ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልባቸው ለማድረግ የዕውነተኛውን ቲኬት፣ ደረሰኝ ወይም የማጓጓዣ ሰነድ መልክ የሰጣቸው እንደሆነ፤

በቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው እያወቀ እነዚህኑ ወደሐሰት የተለወጡትን ወይም ያገለገሉትን ቲኬቶች፣ ደረሰኞች ወይም የማጓጓዣ ሰነዶች እንደእውነተኛ አድርጐ የተገለገለባቸው እንደሆነ፤

በመቀጮ፣ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

## ምዕራፍ ሁለት

## በምስክር ወረቀቶች ላይ የሚደረግ ሐሰት

### አንቀጽ ፫፻፹፮ ሐሰተኛ ምስክር ወረቀቶች

፩ ማንም ሰው ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ:-

ሀ/ ተገቢ መብት ለማስገኘት የሚችሉ ጽሑፎችን፣ ግላዊ ሁኔታን የሚገልፁ ማስረጃዎችን ወይም የምስክርነት ማስረጃዎችን ወይም ማናቸውንም ዓይነት ጉዳይ የሚመለከቱ የምስክርነት ማረጋገጫ ሰነዶችን ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ ወይም

BACK



አስመስሎ የሠራ ወይም እያወቀ ይህን የመሳሰለውን ሰነድ እንዲገለገልበት ለሌላ ሰው የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ወደሐሰት የተለወጠውን ወይም መስሎ የተሠራውን ሰነድ ወይም ለእርሱ አገልግሎት ያልታሰበውን ወይም እርሱን የማይመለከተውን ትክክለኛ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

ይህ ሰነድ የግል ጉዳይን የያዘ እንደሆነ፤ ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ቀላል እሥራት ያስቀጣል፤ ወይም ሰነዱ ሕዝባዊ ባሕርይ ያለው ሆኖ እንደመታወቂያ ወረቀት ወይም የልደት ምስክር ወረቀት ወይም የችግረኛነት፣ የመልካም ጠባይ፣ የብቁነት ወይም ብቁ አለመሆን ማረጋገጫ ምስክርነት፣ ወይም የሕዝብ መዝገብ ወይም መቆጣጠሪያ ቅጂ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሦስት ወር ያላነሰ ቀላል እሥራት ይሆናል።

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው እነዚህን የመሳሰሉትን ሰነዶች እንዲያዘጋጅ፣ እንዲ ያስቀምጥ፣ እንዲጠብቅ ወይም እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ እንደሆነ እና ይህንንም ወንጀል ያደረገው በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ ሳያስብ እንደሆነ /አንቀጽ ፫፻፹፭/፤ ቅጣቱ ከስድስት ወር እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ፤ ወይም ሁለቱም ነው።

፫ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ነው።

<u>አንቀጽ ፫፻፹፮ ሐሰተኛ የሆነ ኦፊሴላዊ ምስክርነት በማጭበርበር ማግኘት</u>

ማንም ሰው ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፡-

BACK



ሀ/ የመንግሥት ሠራተኛን ወይም ሕጋዊ ውጤት ያለውን ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ ወይም ለማቋቋም ሥልጣን የተሰጠውን ማንኛውንም ሰው በማታለል፤ ቀንና ዘመንን፤ የአንድ ማስረጃን፣ ፊርማን ወይም ግልባጭን ትክክለኛነት ወይም ማናቸውንም ይህን የመሳሰለውን ፍሬ ነገር በሐሰት እንዲያረጋግጥ ያግባባው እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ሌላውን ሰው ለማሳሳት በእንደዚህ ያለው ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፫፻፹፯ ሐሰተኛ የሕክምና ምስክር ወረቀት</u>

፩ ማንኛውም ሐኪም፣ የጥርስ ሐኪም፣ የመድሀኒት ቅመማ ባለሙያ /ፋርማሲስት/፣ የእንስሳት ሐኪም፣ አዋላጅ ወይም በሕክምና ሙያው ሕክምናን በሚመለከት የምስክር ወረቀት ለመስጠት መብት ያለው ማንኛውም ሌላ ሰው የምስክር ወረቀት ስራ ላይ እንደሚውል እያወቀ፣ ለተበቀባዩ ሰው የማይገባ ጥቅም ለማስገኘት የሚችል ወይም የሌላውን ሰው ሕጋዊ ጥቅም የሚጐዳ ሐሰተኛ የሕክምና የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ጽፎ የሰጠ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል:: ወንጀሉ በተደጋገመ ጊዜ የሞያውን ሥራ በሚመለከት የሚወሰነው ተጨማሪ ቅጣት የፀና ይሆናል /አንቀጽ ፻፳፫(ሐ)/::

፪ ሐሰተኛ የሕክምና ምስክር ወረቀት መስጠቱ የተከናወነው በስጦታ፣ በስጦታ ተስፋ ወይም በሌላ ጥቅም እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራትና ከሃምሣ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ ሐሰተኛውን የሕክምና የምስክር ወረቀት ያዘጋጀው የመንግሥት ሠራተኛ ሆኖ ወንጀሉን የፈጸመው በዚሁ በኦፊሴላዊ ሥልጣኑ እንደሆነ፤ ቅጣቱ በንዑስ አንቀጽ (፩) ለተመለከተው ወንጀል ከሦስት ዓመት ያላነሰ ቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአስር ዓመት ያልበለጠ ፅኑ እሥራት፤ በንዑስ አንቀጽ (፪) ለተመለከተው ወንጀል ከአሥራ አምስት ዓመት ያልበለጠ ፅኑ እሥራትና ከመቶ ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል።

፬ ማንም ሰው በሐሰት የተዘጋጀ የምስክር ወረቀት መሆኑን እያወቀ ሌላውን ሰው ለማታለል የተገለገለበት እንደሆነ፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው ቅጣት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፹፫ ተደራራቢ ወንጀሎች</u>

ማንም ሰው ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት፣ ሐሰተኛ የምስክርነት ማስረጃ ወይም እርሱን የማይመለከተውን ወይም እንዲገለገልበት ያልታሰበውን ትክክለኛ የምስክር ወረቀት አግኝቶ በዚሁ አስቦ በመጠቀም ተጨማሪ ወንጀል ለመፈጸም የተገለገለበት እንደሆነ፤ በተለይም የእምነት ማጉደል ወይም የማታለል ወንጀል ሆኖ ወንጀሉ ቢያንስ ተሞክሮ እንደሆነ፤

ፍርድ ቤቱ ስለወንጀል መደራረብ የቅጣት ማክበጃ ድንጋጌዎችን /አንቀጽ ፹፪/ በመከተል ቅጣቱን ይወስናል።

<u>አንቀጽ ፫፻፹፬ ሐሰተኛ የቃል አሰጣጥና ምዝገባ</u>

፩ ማንኛውም አሠሪ፣ የሆቴል ወይም የማደሪያ ቤት ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ፣ ወይም በሕግ መሠረት ለባለሥልጣኖች መቆጣጠሪያ እንዲሆን ፤

፪ የግለሰቦችን ወይም የድርጊቶችን ዝርዝር እንዲመዘግብ ግዴታ የተጣለበት ማንኛውም ሌላ ሰው አስቦ:-

ሀ/ እውነተኛ ያልሆነውን የሰው ስም፣ ቀንና ዘመን፣ ወይም የሰው ወይም የዕቃ መግለጫዎችን የመዘገበ፣ ያስመዘገበ ወይም እንዲመዘገብ የፈቀደ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በእውነተኛ ሁኔታው መሠረት ሳይመዘግብ ወይም እንዲመዘገብ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፫ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው በጥቅም ፍላጐት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት ያላነሰ ቀላል እሥራትና መቀጮ ይሆናል::

## አንቀጽ ፫፻፺ የሐሰት ሥራ ለመፈፀም የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና መሥሪያዎች

፩ ማንም ሰው ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ሊገለገልባቸው በማሰብ ኦፊሴላዊ ጽሁፎችን፣ የምስክር ወረቀቶችን፣ ዲፕሎማዎችን ወይም ሰነዶችን ወደ ሐሰተኛነት ለመለወጥ ወይም በሐሰት ለመፍጠር የሚያገለግሉ መሣሪያዎችንና መሥሪያዎችን ወይም ቁሳዊ ነገሮችን የሠራ፣ በእጁ ያስገባ፣ የያዘ፣ የሰጠ፣ ወይም ለሽያጭ ወይም ለስጦታ ያቀረበ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው እንደነዚህ ዓይነቶቹን መሣሪያዎች፣ መሥሪያዎች ወይም ቁሳዊ ነገሮች ለማናቸውም ዓይነት አገልግሎት ከመዋላቸው በፊት በራሱ ነፃ ፈቃድ ያጠፋቸው እንደሆነ ከማናቸውም ቅጣት ነፃ ይሆናል::

BACK



## ምዕራፍ ሦስት

## ዕቃዎችን ወደ ሐሰት መለወጥ

### አንቀጽ ፫፻፺፩ ዕቃዎችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥና ጥራታ ቸውን ማርከስ

ማንም ሰው ሌላውን ሰው ለማታለል በማሰብ የንግድ ዕቃዎችን ወደሐሰተኛነት የለወጠ፣ አስመስሎ የሠራ ወይም ጥራታቸውን ያረከሰ ወይም ወደሌላ የለወጠ እንደሆነ፤

ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

### አንቀጽ ፫፻፺፪ ማዘዋወር

፩ ማንም ሰው ሌላውን ሰው ለማታለል አስቦ ወደ ሐሰተኛነት የተለወጡትን፣ መስሎ የተሠሩትን ወይም ጥራታቸው የረከሰውን ወይም ወደ ሌላ የተለወጡትን የንግድ ዕቃዎች እንደ እውነተኛ፣ እንዳልተለወጡ፣ ወይም ምንም ጉድለት እንደሌለባቸው በማስመሰል ለሽያጭ ያቀረበ፣ የሸጠ፣ በሕዝብ እጅ እንዲዘዋወሩ ያደረገ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፺፩ በተደነገገው ቅጣት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ በቸልተኛነት ሲፈፀም ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣው ሁኔታው በጣም ከባድ ሆኖ አድራጊውም ልዩ የሆነ ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን በተለይም በነጋዴነቱ ምክንያት የዚህ ዓይነቱን ጥንቃቄ መፈፀም የሚገባው ሆኖ ሲገኝ ነው።

### አንቀጽ ፫፻፺፫ ዕቃዎችን ወደአገር ማስገባት፣ ወደውጭ መላክ፣ በእጅ ማድረግና ማከማቸት

ማንም ሰው ሌላውን ሰው ለማታለል በማሰብ ወይም ለማታለያ የታሰበ መሆኑን እያወቀ ወደ ሐሰተኛነት

የተለወጡትን ወይም ሐሰተኛ የሆኑትን ወይም የተበላሹትን ወይም ጥራታቸው የረከሰውን የንግድ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ ወደውጭ አገር የላከ፣ በእጅ ያደረገ ወይም ያከማቸ እንደሆነ፤

ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

**<u>አንቀጽ ፭፻፺፬ ቅጣትን ማክበድና ተጨማሪ ቅጣቶች</u>**

፩ አድራጊው ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ወንጀሎች ሙያው አድርጐ ይዞ እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራትና እንደነገሩ ከባድነት ከብር አምስት ሺህ ባላነሰ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ዕቃዎቹን የመውረስና ፍርድን የመግለፅ ድንጋጌዎች በማናቸውም ጊዜ የተጠበቁ ናቸው::

**<u>አንቀጽ ፭፻፺፭ ጤናን በሚጐዳ አኳኋን የንግድ ዕቃን ወደ ሐሰት መለወጥና ጥራቱን ማርከስ</u>**

ጤናን ለመጉዳት የሚችሉ ምግቦችን፣ ሸቀጦችን እና ለጤንነት ጠንቅ የሆኑ ወይም የተበላሹ የንግድ ዕቃዎችን ስለመሥራት፣ ጥራታቸውን ስለማርከስና ስለመሸጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብነት ሲኖራቸው ተፈጻሚ መሆናቸው እንደተጠበቀ ነው /አንቀጽ ፰፻፹፺/::

## <u>ትርዕስ ሁለ</u>

## <u>የሕዝብ ጥቅምን የሚመለከት ምስጢርን መግለፅ</u>

**<u>አንቀጽ ፭፻፺፮ ወታደራዊ ምስጢርን መግለፅ</u>**

፩ ማንኛውም ወታደር ወይም በመከላከያ ኃይል አገልግሎት ውስጥ የሚገኝ ሰው ክዳትንና ስለላን በሚመለከት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች /አንቀጽ ፪፻፵፰-፪፻፶፪/ ውጭ ፣ በሥራው ወይም በወታደራዊ

ግዳጅ ምክንያት ያወቀው ሆኖ በጠባዩ ምስጢር የሆነውን ወይም ምስጢር ሆኖ እንዲጠበቅ የታዘዘውን ወይም ለሕዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለውን መረጃ፣ ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር የገለፀ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤

ሥራው ወይም ግዳጁ ከተፈፀመ በኋላ ቢሆንም እንኳን ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ቅጣቱ ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት የሚሆነው:-

ሀ/ ወንጀሉ የሚመለከተው በምስጢር ኮድ /አሀዝ/ የተያዘ መረጃን ወይም ሰነድን እንደሆነ፣ ወይም አድራጊው ምስጢሩን እንዲጠብቅ በግልፅ አደራ የተጣለበት ወይም ምስጢሩን እንዳይገልፅ የመሐላ ቃሉን የሰጠበት እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ወንጀሉ ልዩ በሆነ ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ፤

ነው።

፫ ወንጀሉ በቸልተኛነት ተፈጽሞ እንደሆነ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ለተመለ ከተው ቀላል ወንጀል ቅጣቱ ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ፤ በንዑስ አንቀጽ (፪) ለተመለከተው ከባድ ወንጀል ደግሞ ከሦስት ዓመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፫፻፺፯</u> <u>የሥራ ምስጢርን መግለፅ</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ /አንቀጽ ፬፻፪/ በአንቀጽ ፫፻፺፮ በተመለከተው ድንጋጌ በተገለፀው መሠረት ምስጢር ሆኖ ሊጠበቅ የሚገባውን እና በሥራው ምክንያት ያወቀውን ማናቸውንም ዓይነት

BACK



ሰነድ፣ መረጃ ወይም ፍሬ ነገር ሥራውን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው የተለየ ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ ወይም እምነት የተጣለበት ወይም ወንጀሉ በተለይ ከፍ ያለ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት ሲሆን ቅጣቱ በንዑስ አንቀጽ (፩) ለተመለከተው ቀላል ወንጀል ከብር አንድ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት፤ በንዑስ አንቀጽ (፪) ለተመለከተው ወንጀል ደግሞ ከሦስት ዓመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፫፻፺፰ እንዲገለፅ የተፈቀደ ምስጢር</u>

ለህዝብ ጥቅም ሲባል አግባብ ባለው የሲቪል፣ አስተዳደራዊ ወይም ወታደራዊ ባለሥልጣን የጽሁፍ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ በፍርድ ቤት ወይም ሥልጣን ባለው በማናቸውም ምርመራ በሚያደርግ ፍርድ ቤት ፊት የተደረገ የምስጢር መግለፅ አያስቀጣም::

<u>አንቀጽ ፫፻፺፱ በሞያ ወይም በሥራ ምክንያት የታወቀ ምስጢርን መግለፅ</u>

፩ የማናቸውም እምነት አገልጋይ፣ የሕግ አማካሪ፣ ጠበቃ፣ ነገረ ፈጅ፣ የሽምግልና ዳኛ፣ አስታራቂ ሽማግሌ፣ ልዩ አዋቂ/ኤክስፐርት/፣ ነባሪ፣ አስተርጓሚ፣ ውል አዋዋይ፣ የግል ድርጅት ዳይሬክተር፣ የሥራ መሪ፣ ተቆጣጣሪ ወይም በፍትሐብሔር ወይም በንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ምስጢር መጠበቅ የሚገባው ማንኛውም ሠራተኛ ፣ ሐኪም ፣ የጥርስ ሐኪም ፣

BACK



የመድሀኒት ቅመማ ባለሙያ /ፋርማሲስት/፣ አዋላጅ፣ ነርስ ወይም ሌላ ረዳት የህክምና ሠራተኛ ወይም ሌላ በሙያው ወይም በሥራው ምክንያት የተገለጠ ለትን ምስጢር በሙያ ሥራው ላይ ሳለም ሆነ ሥራውን ከለቀቀ በኋላ የገለጸ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ በሞያ ሥራ መለማመድ ትምህርት ምክንያት ሊያውቅ የቻለውን ምስጢር የገለጸ ተማሪ፣ በሙከራ ላይ ያለ ሠራተኛ ወይም ተለማማጅ ሠራተኛ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

፫ ምስጢር የመግለፁ ወንጀል የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ የግል አቤቱታ ሲቀርብ ቅጣቱ ከብር አንድ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፬፻</u> <u>እንዲገለፅ የተፈቀደ ምስጢር</u>

፩ ምስጢር መግለፅ የማያስቀጣው:-

ሀ/ ምስጢሩ ሊጠበቅለት የሚገባው ሰው በግልፅ ፈቃድ ከሰጠ በኋላ እንደሆነ፤

ለ/ ምስጢሩን በያዘው ሰው አሳሳቢነት ወይም ጠያቂነት አግባብ ያለው የበላይ የሙያ ወይም የቁጥጥር አካል የጽሁፍ ፈቃድ ሰጥቶ እንደሆነ፤

ሐ/ በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ የተሰጠን ግልፅ የፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት በማድረግ ተገልጸ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ ለሕዝባዊ ተግባር ሲባል በፍርድ ችሎት እንዲመሰክር ወይም ላንዱ ባለሥልጣን

መግለጫ እንዲሰጥ የሕጉ ልዩ ድንጋጌ የሚፈቅድ ወይም የሚያዝዝ እንደሆነ፤

ነው::

በሕግ፣ በፍርድ ቤት ወይም በሚመለከተው ባለሥልጣን ምስጢር እንዲገልጽ የታዘዘ ሰው የሚስጢር መጠበቅ ግዴታውን ምክንያት በማድረግ ምስጢሩን ለመግለጽ እንቢተኛ ለመሆን አይችልም::

በማናቸውም ምክንያት ሀይማኖታዊ ኑዛዜ እንዲገለፅ ለማስገደድ አይቻልም::

## <u>አንቀጽ ፬፻፩ የሳይንስ፣ የኢንዱስትሪ ወይም የንግድ ምስ ጢርን መግለፅ</u>

፩ ማንም ሰው ባለቤቱን ወይም ባለይዞታውን ለመጉዳት ወይም ጥቅም ለማግኘትም ሆነ ለማስገኘት በማሰብ በሕግ ወይም በውል ወይም በሥራው ኃላፊነት ምክንያት ያለበትን ግዴታ በመጣስ በምስጢር መጠበቅ የሚገባውን ማናቸውንም የኢኮኖሚ፣ የሳይንስ፣ ወይም የቴክኖሎጂ ግንባታ ዘዴ ወይም መረጃ፤ የኢንዱስትሪን ወይም የንግድን፣ የሳይንስን /ሥነ ጥበብ/ ምስጢር ወይም በሥራ ላይ የሚውልበትን ጥበባዊ ዘዴ ሊገለፅለት ለማይገባ ሰው የገለፀ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ለአገር መከላከያ ጠቃሚ የሆነ የሳይንስ ወይም የስነጥበብ ምስጢር የተገለጸ እንደሆነ፤ በአንቀጽ ፫፻፺፯ የተመለከተው ልዩ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል::

## ርዕስ ሦስት
## በመንግሥት ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች
## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ፬፻፪ ትርጓሜ**

፩ "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግሥት ልማት ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ፣ ተሹሞ፣ ተመድቦ፣ ወይም በሕዝብ ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሥራን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ነው።

፪ "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደር እና የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት ስራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መሥሪያ ቤት ነው።

፫ "የመንግሥት ልማት ድርጅት" ማለት የመንግሥት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የአክስዮን ማህበር ነው።

፬ በዚህ ርዕስ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በቀር "ጥቅም" ማለት:-

ሀ/ በገንዘብ ወይም በማናቸውም ዋጋ ባለው መያዣ ወይም በሌላ ንብረት ወይም በንብረት ላይ ባለ ጥቅም (መብት) የሚተመን ማናቸውም ስጦታ፣ ብድር፣ ክፍያ፣ ወሮታ ወይም ኮሚሽን፤

ለ/ ማናቸውም ሹመት፣ ቅጥር ወይም ውል፤

BACK



ሐ/ ብድርን፣ ግዴታን ወይም ማናቸውንም ዕዳ በሙሉም ሆነ በከፊል መክፈል፣ ማስቀረት፣ ማወራረድ ወይም ከነዚህ ነገሮች ነፃ ማድረግ፤

መ/ ከተመሰረተ ወይም ካልተመሰረተ የአስተዳደር፣ የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ክስ፣ ወይም ካስከተለው ወይም ከሚያስከትለው ማናቸውም ቅጣት ወይም የችሎታ ማጣት በማዳን ወይም ይህን በመሰለ ዘዴ የሚደረግ አገልግሎት ወይም ውለታ፤

ሠ/ ማናቸውንም መብት፣ ተግባር ወይም ግዴታ መፈጸም ወይም ከመፈጸም መታቀብ፤

ረ/ ከላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጭ በገንዘብ የማይተመን ማናቸውም ሌላ ጥቅም ወይም አገልግሎት፤ እና

ሰ/ ከዚህ በላይ ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ረ" ከተጠቀሱት ጥቅሞች አንዱን ማቅረብ፣ ጥቅሙ የሚገኝበትን መንገድ ማመቻቸት ወይም ይህንኑ በሚመለከት የተስፋ ቃል መግባት ወይም መቀበል፤

ነው::

፫ "የማይገባ ጥቅም" ማለት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ጥቅም ነው::

## አንቀጽ ፬፻፫ ጥቅም የማግኘት ወይም የመጉዳት ሐሳብ ግምት

ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር፣ የሙስና ወንጀሎቹ የተፈፀሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በአንቀጹ ውስጥ የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር (ድርጊት) እንደተፈፀመ

BACK



ከተረጋገጠ፣ ድርጊቱ የተፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሦስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል።

<u>አንቀጽ ፬፻፬</u> <u>መርህ</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ ርዕስ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱን ባደረገ ጊዜ ከዚህ በታች የተፃፉት የቅጣት ድንጋጌዎች ይፈፀሙበታል።

፪ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የተከሰሰበት፣ በወንጀለኛነት የፈጸመው ወይም ሳይፈጽም በግድፈት የተወው ተግባር የተሠጠውን ሥራ በሚሠራበት ጊዜ የተፈፀመ እንደሆነና ተግባሩም መደበኛ ሕግ የሚፈጸምበት ሆኖ ነገር ግን በመንግሥት ሥራ ላይ በመሆኑና በእርሱ ላይ ከተጣለው እምነት የተነሣ ያለበትን ግዴታ በመጣሱ ቅጣቱ የሚከብድ ሲሆን በዚህ የወንጀል ሕግ በሌሎች ርዕሶች የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፫ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ፣ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የሕዝብ አደራ ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ ወይም

ማንኛውም ሰው ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት

እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፣ ለመንግሥት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ፣ ያቀረበ፣ የሰጠ፣ ወይም ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ፤ ወይም

በአግባቡ ለተፈፀመ ወይም በአግባቡ ለወደፊቱ ለሚፈፀም የመንግሥት ሥራ የማይገባ ጥቅምን ማንኛውም ሰው የሰጠ ወይም ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የተቀበለ እንደሆነ፤

በዚህ ርዕስ የተመለከቱትን የሙስና ወንጀሎች አድርጓል ተብሎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች የተመለከተው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል።

፬ የሙስና ወንጀሎች በዚህ ርዕስ በምዕራፍ ሁለት በክፍል አንድ እና በምዕራፍ ሶስት በክፍል አንድ ስር ከተመለከቱት ወንጀሎች በተጨማሪ እና በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያን (አንቀጽ ፬፻፷፰)፣ መንግስታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀትን ወይም ወደ ሐሰት መለወጥን (አንቀጽ ፫፻፹፱)፣ ከባድ የእምነት ማጉደልን (አንቀጽ ፬፻፹፬(፩))፣ በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና በወንጀሉ መርዳትን (አንቀጽ ፬፻፹፩)፣ በመንግሥት ሠራተኛ የሚፈጸም ከባድ አታላይነትን (አንቀጽ ፬፻፺፮ (ሀ)) ያጠቃልላሉ።

፭ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በተጣሰው የሕግ ድንጋጌ ከሚወሰንበት ቅጣት በተጨማሪ በሕገወጥ መንገድ ያገኘው ጥቅም፣ ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲወረስ ወይም ጥቅሙም ሆነ ንብረቱ ካልተገኘ ተመጣጣኝ ዋጋውን እንዲከፍል ይደረጋል።

<u>አንቀጽ ፬፻፭ የአስተዳደር ቅጣትና የፍትሐብሔር ኀላፊነት በተደራራቢነት ተፈፃሚ መሆናቸው</u>

በዚህ በምዕራፍ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በወንጀል ተከስሶ መቀጣት ወይም በነፃ መለቀቅ

በአስተዳደርም ሆነ ወይም በፍትሐብሔር ተጠያቂ መሆንን አያስቀርም::

## አንቀጽ ፬፻፮ ከክስ ነፃ ማድረግ

፩ ማንም ሰው ከሙስና ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ ከሆነ በኋላ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈጸመው ድርጊትና ስለተካፋዮቹ ሚና ጠቃሚ መረጃ ከሰጠ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል በዚህ የወንጀል ሕግ መሠረት እንዳይከሰስ ሊደረግ ይችላል::

፪ ስለ ማስረጃው ጠቃሚነት አወሳሰንና ድርጊቱን ያጋለጠ ሰው እንዳይከሰስ ስለሚደረግበት ሁኔታ ዝርዝር አፈፃፀሙን በሚመለከት አግባብ ባለው የስነ-ስርዓት ሕግ ይደነገጋል::

፫ ሕጋዊ በሆነ መልኩ ላገኘው ወይም ሊያገኘው ለሚገባ አገልግሎት የሰጠውን ማናቸውንም ጥቅም እንደሰጥ ላጋለጠ ሰው፣ የሰጠውጉቦ ወይም ስጦታ ወይም ዋጋ ያለው ነገር በወንጀሉ ምክንያት ከተወረሰው ንብረት ላይ ይመለስለታል::

## ምዕራፍ ሁለት

## የመንግስት ሠራተኞች በመንግሥት ሥራ ላይ የሚፈጽሙአቸው ወንጀሎች

## ክፍል አንድ

## ቅንነትንና ታማኝነትን በማጓደል የመንግሥት ሠራተኞች የሚፈጽሟቸው የሙስና ወንጀሎች

## አንቀጽ ፬፻፯ በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፦

BACK



ሀ/ የተሰጠውን ሹመት ወይም ሥልጣን በግልፅ ተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤

ለ/ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን አልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ሥልጣኑ የማይፈቅድለትን ጉዳይ፣ በተለይም ሥልጣን ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ፤

በሕጉ ላይ ጉዳዩን በግልጽ የሚመለከት ድንጋጌ ከሌለ በቀር እንደ ነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅሙ ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የሀላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት የወንጀሉን አፈፃፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ፣ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፬፻፳ ጉቦ መቀበል</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ በቀጥታም

ሆነ በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ሃያ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የሀላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት የወንጀሉን አፈፃፀም ከባድ አድርጉት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ፣ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፬ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለፀው መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከዓለም አቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ የሥራ ግዴታ ድንበር ዘለል ኮርፖሬሽንን ጨምሮ ከማንኛውም የሌላ አገር መንግሥት፣ ሰው ወይም ድርጅት ጥቅም ወይም ስጦታ የጠየቀ፣ የተቀበለ፣ ለመቀበል የተስማማ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ ባሉት ሦስት ንዑስ አንቀጾች ስር ከተመለከቱት ቅጣቶች በአንዱ እንደነገሩ ሁኔታ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፱ የማይገባ ጥቅም መቀበል</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል፤ ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር አስር ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም የጥፋተኛው የሀላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ የወንጀሉ አፈፃፀም ከባድ አድርጉት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራትና ከብር ሰላሣ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈፀመው ከዓለም አቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ የሥራ ኃላፊነት ወይም ግዴታ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች መሠረት ያስቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፲ አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈጽሙት የጉቦ መቀበል ወንጀል</u>

፩ ማንኛውም አስታራቂ ሽማግሌ፣ የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ፣ ንብረት ጠባቂ ወይም አጣሪ፣ ሥራውን ለማካሄድ በባለሥልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክነት በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያው ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ

ማንኛውም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከተው ሰው ላይ ጥቅም ወይም ስጦታ እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፤

በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፬፻፰ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ንዑስ አንቀጾች ስር ከተመለከቱት ቅጣቶች ባንዱ እንደነገሩ ሁኔታ ይቀጣል::

፪ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ሰዎች አንዱ በተሰጠው ሥልጣን ወይም ተግባር መሠረት ማድረግ የሚገባውን ከመፈፀሙ በፊት ወይም በኋላ ጥቅም ወይም ስጦታ እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፤ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፬፻፱ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ንዑስ አንቀጾች ላይ ከተመለከቱት ቅጣቶች በአንዱ እንደነገሩ ሁኔታ ይቀጣል::

## <u>አንቀጽ ፬፻፲፩ የመንግሥት ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፣ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ:-

ሀ/ በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ፣ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ለግል ጥቅሙ ማናቸውንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

ለ/ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣ የሥራ መቋረጥ ውል

ወይም ማናቸውንም የሥራ ውል የተዋዋለ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በጠቅላላው በሥራው ሥልጣን መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የሕዝብ ወይም የመንግሥት ጥቅም የሚጐዳ ተግባር በማናቸውም ዘዴ የፈጸመ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከሃምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የሀላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት የወንጀሉን አፈፃፀም ከባድ አድርጐት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከመቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ፣ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፬ አድራጊው ጥቅም የማግኘት ወይም የማስገኘት አሳብ ሣይኖረው:-

ሀ/ እራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ወይም ወዳጁ ባለጥቅም ወይም ባለአክሲዮን በሆነበት ድርጅት ወይም መስራች ወይም አባል በሆነበት የበጎ

BACK


አድራጎት ድርጅት እና በእርሱ መሥሪያ ቤት መካከል በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ፣ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ውል እንዲፈፀም ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የተወሰኑ ንብረቶችን እንዳይገዛ ወይም እንዳይጫረት በሕግ ወይም በደንብ ተከልክሎ እያለ በስሙ ወይም በሌላ ሰው ስም ወይም ከሌላ ሰው ጋር ንብረት የገዛ ወይም የተጫረተ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::
"ዘመድ" ማለት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ከተከሳሹ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ሰው ነው::

<u>አንቀጽ ፬፻፲፪ አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለት፣ ሆኖም ለግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን:-

ሀ/ ታሽጎ የተረከበውን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገሮች ወይም በአደራ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ፣ወይም ወሬውን የገለጸ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ እንደነዚህ ባሉ ዕቃዎች የተገለገለ ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልባቸው የፈቀደ እንደሆነ፤

ድርጊቱ ከባድ ቅጣት በሚወስን ሌላ ድንጋጌ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ፣ ከሰባት ሺህ ብር

BACK



በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው ጥቅም ለማግኘት በማቀድ ስሜት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራትና መቀጮ ይሆናል::

፫ ድርጊቱ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአንድ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

አንቀጽ ፬፻፲፫ በሥራ ተግባር ላይ የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ:-

ሀ/ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሀራጅ ሽያጭ፣ በሕግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረት ላይ እንዲፈጸም በመወሰኑ፣ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንቀሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በሥራው አጋጣሚ ምክንያት ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም በእጁ ሊገቡ የቻሉትን እነዚህን የመሳሰሉትን ዕቃዎች ወይም ባለዋጋ ነገሮች የሰወረ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የሀላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት

ከፍተኛነት የወንጀሉን አፈፃፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከሠላሣ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ፣ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከብር ሃምሳ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

## አንቀጽ ፬፻፲፩ በሥልጣን መነገድ

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት:-

ሀ/ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተወስኖ የሚሠጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

ለ/ በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለሥልጣኖች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ውል፣ የንግድ ስምምነት፣ የሥራ ጨረታ፣ የዕቃ ማቅረብ ውል፣ ወይም ሌላ ጥቅም፤ ወይም

ሐ/ በአጠቃላይ ከአንድ ባለሥልጣን ወይም የአስ ተዳደር ክፍል የሚሰጠውን ጥቅም ወይም የሚረዳ ውሳኔ፤

ለሌላ ሰው ለማስገኘት፣ ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ

BACK



እሥራትና ከሰላሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የሀላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት የወንጀሉን አፈፃፀም ከባድ አድርጐት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፫ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ፣ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፬፻፲፩</u> <u>በሕገወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የማይገባውን ጥቅም ለራሱ ለማግኘት አስቦ:-

ሀ/ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በሕግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሣ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤

ለ/ ማንኛውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና እስከ አሥራ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው ከዚህ በላይ አንቀጽ ፬፻፲፬ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በአንዱ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከሠላሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፫ ወንጀሉ የተፈፀመው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፬፻፲፬(፫) በተመለከቱት ሁኔታዎች እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፬ ወንጀሉ የተደረገው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ በቀላል እሥራትና በመቀጮ ያስቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፲፯</u> <u>ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት</u>

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራው ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለውን ማንኛውንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከሕግ ወይም ከሥራ ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ከተለመደው አሠራር ውጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ወይም ያዘገየ ወይም ባለጉዳይን ያጉላላ እንደሆነ፤

በደንብ መተላለፍ ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ በሆነ ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ በመቀጮ ፣ ወይም በቀላል

BACK



እሥራት፣ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፲፯ ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት</u>

፩ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን ወይም ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ እንደሚገባ በሕግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ ወይም አለማስመዝገብ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሰረት ያስቀጣል::

፫ በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ስጦታ መቀበል ወይም ከቅርብ የስጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ ወይም ከቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው ወንጀል ማቋቋሚያ አይሆንም::

<u>አንቀጽ ፬፻፲፰ ያለአግባብ ፈቃድ መስጠት እና ማፅደቅ</u>

ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ አስቦ ብቁ ላልሆነ ወይም በሕግ ሊሰጠው ለማይገባው ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያጸደቀ እንደሆነ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት፣ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፲፱ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ</u>

፩ የመንግሥት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ማንም ሰው:-

ሀ/ የኑሮ ደረጃው፣ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ

ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፤

የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በቀር እንደሁኔታው የንብረቱ መወረስ ወይም ለባለቤቱ መመለስ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩(ለ ) የተጠቀሰው ወንጀል በፍርድ ቤት እየታየ ባለበት ጊዜ አንድ ሰው ከተከሳሽ ጋር ካለው ቅርበት ወይም ሌሎች ሁኔታዎች የተነሳ ለተከሳሹ ባለአደራ በመሆን አንድን ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ እንደያዘ ወይም ከተከሣሹ በስጦታ እንዳገኘ ፍርድ ቤት ካመነበት ጉዳዩን በሌላ ማስረጃ ካላፈረሰ በስተቀር ንብረቱ ወይም የገንዘብ ምንጩ በተካሣሹ ይዞታ ሥር እንደሆነ ይቆጠራል::

## ክፍል ሁለት

## የሥራ ግዴታን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፬፻፲ የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈፀም ወንጀል

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ ግዴታ ተግባሩን በአግባቡ ሳይፈጽም በመቅረቱ በመንግሥት፤

BACK



በሕብረተሰቡ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ፣

ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ በወንጀሉ ምክንያት ከባድ ጉዳት ደርሶ እንደሆነ ቀላል እሥራቱና መቀጮው በሕግ እስከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት ሊደርስ ይችላል::

<u>አንቀጽ ፬፻፳፩</u> <u>ህገወጥ የሥራ ማቆም አድማ</u>

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሕግን ወይም ሙያውን በሚቃረን ሁኔታ በፈቃዱ የሥራ ማቆም አድማ ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም የሥራ ማቆም አድማ እንዲደረግ ሌሎችን የገፋፋ እንደሆነ፣
በአንቀጽ ፬፻፳ የተመለከተው ቅጣት ይፈጸምበታል::

<u>አንቀጽ ፬፻፳፪</u> <u>የሰውን ንብረት የመበርበር ወይም የመያዝ ሥልጣንን ያለአግባብ መገልገል</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ ስልጣን ሳይኖረው የሰውን ንብረት የበረበረ፣ የያዘ ወይም ንብረቱን የወሰደ እንደሆነ፣

ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ለመበርበር ወይም ለመያዝ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ቢሆንም ተገቢ ከሆነው ኃይል በላይ ተጠቅሞ ወደሌላ ሰው ቤት ወይም ግቢ የገባ እንደሆነ ወይም በሕግ ከታዘዘው ወይም ከተፈቀደው ሥርዓት ውጭ የሰውን ንብረት የበረበረ፣ የያዘ ወይም የወሰደ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፳፫ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ሰውን መያዝ ወይም ማሰር

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ ከተመለከተው ውጭ ወይም ሕጋዊ ሥርዓትና ጥንቃቄ ሳይከተል ሌላውን ሰው በመያዝ፣ በማሠር፣ ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ነፃነቱን ያሳጣው እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፳፬ በማይገባ የአሠራር ዘዴ መጠቀም

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የመያዝ፣ የመጠበቅ፣ የመቆጣጠር፣ የማጀብ ወይም የመመርመር ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የተጠረጠረን፣ የተያዘን፣ በምስክርነት የቀረበን፣ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የተጠራን፣ ተይዞ በማረፊያ ቤት ወይም በእሥር ቤት የተቀመጠን ወይም የእሥራት ቅጣት በመፈጸም ላይ የሚገኝን ሰው አንድ መግለጫ እንዲሰጠውም ሆነ ጥፋቱን እንዲያምን ወይም ይህን የመሳሰለ ነገር እንዲገልጽለት ወይም በሌላው መንገድ የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ የደለለው፣ የተስፋ ቃል የሰጠው፤ ያስፈራራው ወይም በዚህ ሰው ላይ አግባብነት የሌለው ወይም ከሰብዓዊ ርህራሄ ውጭ የሆነ ወይም ለሰው ልጅ ክብር ወይም ለተሰጠው የሥራ ሥልጣን ተቃራኒ የሆነ ድርጊት የፈጸመበት እንደሆነ፤ በተለይም ድብደባ፣ የጭካኔ ተግባር፣ ወይም የአካል ወይም የመንፈስ ስቃይ ያደረሰበት እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም በመቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

ድርጊቱ ተጨማሪ ወንጀል ባስከተለ ጊዜ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በተደራቢነት እንዳይፈፀም የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ አያግድም።

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በባለሥልጣን ትዕዛዝ እንደሆነ፤ ይኸው ባለሥልጣን ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፷፭ እሥረኛን ህገወጥ በሆነ መንገድ መፍታትና እንዲያመልጥ መርዳት</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ:-

ሀ/ ሕግን ወይም የተሰጠውን ትዕዛዝ ተቃራኒ በሆነ መንገድ በሕግ አግባብ የታሰረውን ወይም የተያዘውንና እንዲጠብቀው የተሰጠውን ሰው የፈታ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የዚሁ ዓይነት ሰው እንዲያመልጥ ያደረገ፣ የፈቀደ ወይም እንዲያመልጥ የረዳው እንደሆነ፤

ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራትና ከብር ሶስት ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ ሕገወጥ አፈታቱ ወይም ማምለጡ የተፈጸመበት ዘዴ ወይም ሁኔታ፣ ያደረሰው ጉዳት፣ እንዲያዝ የታዘዘበት ምክንያት ክብደት፣ ወይም የተያዘው ሰው አደገኛነት ሲታይ ሁኔታው በተለይ ከባድ እንደሆነ፤

BACK



ቅጣቱ እስከ መደበኛው ከፍተኛ ጣራ ለመድረስ የሚችል መቀጮ እና ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል፡፡

፫ ወንጀሉ በቸልተኛነት የተፈጸመ ሲሆን፣ ቅጣቱ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር የማይበልጥ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ ፬፻፳፮ የጦር ምርኮኞችንና የወታደር ግዞተኞችን መፍታትና</u>

<u>እንዲያመልጡ መርዳት</u>

፩ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በጥበቃው ሥር ያሉትን የጦር ምርኮኞች ወይም የወታደር ግዞተኞች ሕግን ወይም ትዕዛዝን በመቃረን የፈታ ወይም እንዲያመልጡ የረዳ እንደሆነ፣

ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት ከሆነ፣ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል፡፡

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>

<u>ሌሎች ሰዎች በመንግሥት ሥራ ላይ የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች</u>

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ሌሎች ሰዎች ከመንግሥት ሥራ ጋር</u>

<u>በተያያዘ መንገድ የሚፈጽሟቸው የሙስና ወንጀሎች</u>

<u>አንቀጽ ፬፻፳፯ ጉቦ መስጠት</u>

፩ ማንም ሰው አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ፣ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት፣ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከብር አስራ አምስት ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ከዓለም አቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ ጉዳይ ለማንኛውም የሌላ አገር መንግሥት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤

በንዑስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው መሠረት ይቀጣል::

፫ ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ጥቅም ወይም ስጦታ ከፍተኛ እንደሆነ፤ ወይም ድርጊቱ በመንግሥት፣ በሕዝብ ወይም በግለሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና ከብር ሃምሳ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፬ አንድ የመንግስት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር እንዲያከናውን ሲል፣ ይህንን ተግባሩን ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ለዚሁ ሠራተኛ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ ማንኛውም ሰው፤ እንደነገሩ ሁኔታ በመቀጮ ወይም በቀላል እሥራት፣ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፭ ከላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች የተገለፀው ወንጀል የተፈፀመው የሕግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት ከሆነ በአንቀጽ ፺(፫) መሠረት በመቀጮ ይቀጣል::

፮ በዚህ አንቀጽ ከተቀመጠው ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ከመንግሥት ጋር ማናቸውንም ዓይነት

BACK



ውል ወይም ግብይት በጨረታቂነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ እንዳይፈጽም የሚከለክል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል::

## አንቀጽ ፬፻፵፫ ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት

ማንኛውም ሰው በአንቀጽ ፬፻፲፯ በተመለከቱት ሁኔታዎች ለማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለው ማንኛውም ሌላ ሰው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለው ነገር ያቀረበ፣ የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፵፬ ማቀባበል

ማንኛውም ሰው ለራሱ ማናቸውንም አይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ስራን ለሚያከናውን ሰው ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለው ነገር፣ አገልግሎት ወይም ሌላ አይነት ጥቅም ከሌላ ሰው የተቀበለ እንደሆነ፣ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ አይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት፣ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፵፭ በሌለው ስልጣን መጠቀም

ማንም ሰው:-

ሀ/ ከመንግስት ስራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በስራው ላይ ያለ በማስመሰል፣

BACK



ለ/ ለወደፊቱ የመንግስት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማመን፣ ወይም

ሐ/ የመንግሥት ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፣

ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ስጦታ ከሌላ ሰው ላይ የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት፣ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፴፭ በግል ተሰሚነት መነገድ</u>

ማንም ሰው የመንግሥት ሠራተኛ ባለመሆኑ ለመንግሥት ሠራተኛ የተደነገገው /አንቀጽ ፬፻፲፬/ የማይመለከተው ቢሆንም፣ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግሥት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ከሌላው ሰው ገንዘብ፣ ስጦታ፣ እጅ መንሻ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም እነዚህን በተመለከተ የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፣

ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከሁለት ሺህ ብር በማያንስ መቀጮ ይቀጣል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ሌሎች ሰዎች በመንግሥት ሥራ ላይ የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች</u>

<u>አንቀጽ ፬፻፴፮ መንግሥታዊ የሆኑ ማስታወቂያዎችንና ሕጉችን መድፈር</u>

ማንም ሰው ሥልጣን ወይም መብት ሳይኖረው አስቦ ባለሥልጣኖች በአደባባይ የለጠፏቸውን ማስታወቂያዎች፣

ሕጐች ወይም ውሣኔዎች ከሥፍራቸው ያነሳ፣ ያበላሸ፣ የቀደደ ወይም እንዳይነበቡ ያደረጋቸው እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከብር አንድ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፴፫ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ መሥራት</u>

ማንኛውም ሰው በሕግ ወይም በደንብ መሠረት ፈቃድ ሊሰጥበት የሚገባውን ማናቸውም ሥራ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ የሰራ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ወይም እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፴፬ የማስመዝገብ ግዴታን የሚመለከቱ ድንጋጌ ዎችን መጣስ</u>

፩ ማንም ሰው በመንግሥት መዛግብት ውስጥ መመዝገብ ያለባቸውን ጋብቻ፣ ሞት፣ ንብረት፣ የንግድ ወይም ሌሎች ሥራዎች ወይም የግለሰቦችን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን፣ የኩባንያዎችን መቋቋም ወይም አሠራር ወይም ተመሳሳይ ድርጊቶችን የሚመለከቱ ፍሬነገሮችን ወይም ማረጋገጫዎችን በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ለሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ሳያስታውቅ የቀረ ወይም እነዚህኑ በሀሰት ያስመዘገበ እንደሆነ፤

ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ የዚህ ዓይነቱ አለማስታወቅ ወይም በሐሰት የማስመዝገቡ ሥራ ተደጋግሞ የተፈጸመ ወይም

እንደልማድ ሆኖ የተያዘ እንደሆነ፤ ወይም የሚመለከተው ባለሥልጣን በተለይ የሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መጥሪያ በመቃወም እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከስድስት ወር ያልበለጠ ቀላል እሥራት ወይም ከብር ሁለት ሺህ ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል።

፫ ልጅ መውለድን ስለ አለማስታወቅ የሚመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ነው /አንቀጽ ፯፻፶፯/።

<u>አንቀጽ ፬፻፹፭ እንዳይገለፁ የተከለከሉ መንግሥታዊ ውይይቶችን ወይም ሰነዶችን መግለፅ</u>

ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ወይም በግልጽ ሳይፈቀድለት በሕጉ መሠረት ወይም ከሚመለከተው መንግሥታዊ ባለሥልጣን በተሰጠው ግልጽ ውሣኔ መሠረት ምስጢር ሆኖ ሊጠበቅ የሚገባውን ሰነድ፣ ሪፖርት፣ መመሪያ፣ ቃለ ጉባኤ ወይም ውሣኔ በሙሉ ወይም በከፊል ለመገናኛ ብዙሃን የገለፀ እንደሆነ፤

ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፹፮ ሕገወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር</u>

ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ፦

ሀ/ በመያዣ ወይም በዋስትና ያስረከበውን ዕቃ ተረካቢው ሳይፈቅድለት ወይም በዚሁ ዕቃ ምክንያት ክስ ቀርቦ በክርክር ላይ እያለ የወሰደ እንደሆነ፤

ለ/ ሊከፈለው የሚገባውን ክፍያ ለማግኘት ሲል የባለዕዳው ንብረት የሆነውን ማናቸውንም ተንቀሳቃሽ ዕቃ የወሰደበት እንደሆነ፤ ወይም

BACK

ሐ/ በጠቅላላው የሌለውን ወይም በሕጉ መሠረት ሊሰራበት የማይችለውን መብት የተጠቀመበት እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

**አንቀጽ ፬፻፴፯ ሥልጣንን በማይገባ መያዝ**

፩ ማንም ሰው ህገወጥ ለሆነ ዓላማ፣ ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ያንድ ባለሥልጣን ወይም ኮሚሽን ሥልጣንን፣ መለያ ምልክትን፣ ማዕረግን ወይም ኦፊሴላዊ የሆኑ ማናቸውንም ትዕዛዞችን የመስጠት ሥልጣንን የራሱ በማድረግ የተገለገለበት እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው ሌላውን ሰው ለመበደል ወይም ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ እንደሆነ ቅጣቱ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል::

**አንቀጽ ፬፻፴፰ የመንግሥት ሥራን ማሰናከልና የመተባበር ግዴታን መጣስ**

ማንም ሰው ከመንግሥት ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሕግ በተፈቀደው ወይም ከፍርድ ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት በመንግሥት ሠራተኛ ሲጠየቅ ቀርቦ ለማስረዳት፣ ተገቢውን መልስ ለመስጠት፣ ሰነዶችን ለማቅረብ ወይም ለማስመርመር ወይም ልዩ ልዩ ቤቶችን፣ ቦታዎችን ወይም ነገሮችን ለማስፈተሽ እምቢተኛ ከሆነ፤ በጠቅላላው ለምርመራ ያልተባበረ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የመንግሥትን ሥራ ያደናቀፈ እንደሆነ፤

BACK



ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፴፱ እሽጉችን መቅደድ፣ መስበርና ዕቃዎችን መውሰድ</u>

ማንም ሰው ሕጋዊ ሥልጣን ሳይኖረው አስቦ:-

ሀ/ አንድን ዕቃ፣ ጽሁፍ ወይም ሰነድ ለመጠበቅ፣ ለማስቀመጥ፣ ለመለየት ወይም ለመሸፈን ወይም ወደማናቸውም ሥፍራ መግባትን ለመከልከል የተደረገውን ኦፊሴላዊ ማህተም፣ ምልክት ወይም መለያ ያነሳ፣ ያበላሸ ወይም የሰበረ ወይም በማናቸውም መንገድ እንደነዚህ ዓይነቱ ማህተም፣ ምልክት ወይም መለያ ውጤት እንዳያገኝ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የተያዘ፣ የተወረሰ ወይም በማናቸውም ምክንያት በአንድ ባለሥልጣን ወይም በሌላ ሰው በጥንቃቄ እንዲያዝ ወይም እንዲጠበቅ የተሰጠ ዕቃን፣ ጽሁፍን ወይም ሰነድን የሰረቀ፣ ለግል ጥቅሙ ያዋለ፣ ያበላሸ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ወይም ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፵ መቃወምና አለመታዘዝ</u>

፩ ማንም ሰው በቂ ምክንያት ሳይኖረው:-

ሀ/ ኦፊሴላዊ የሆነ የሥራ ግዴታውን የሚፈጽመውን የመንግሥት ሠራተኛ ሥራውን እንዳይፈጽም የተቃወመ እንደሆነ፤

ለ/ ሕገወጥ ከሆነ ስብሰባ እንዲበተን ወይም ከአንድ ከተከለከለ ሥፍራ እንዲለቅ፣ ወይም በቃጠሎ፣ በማዕበል ወይም ይህን በመሰለ ሌላ ክስተት ምክንያት በሕዝብ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ለመከላከል በሚወሰድ እርምጃ እንዲካፈል ሥራውን በማከናወን ላይ የሚገኝ የመንግሥት ሠራተኛ ሲጠይቀው አልታዘዝም ያለ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በሚመለከተው ባለሥልጣን በሕጉ አግባብ በተሰጠ ውሣኔ መሠረት ካልፈጸመ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቅጣት እንደሚወሰንበት ተገቢ ማስጠ ንቀቂያ ተሰጥቶት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ መቃወሙ ወይም አለመታዘዙ ኃይልን፣ ዛቻን፣ የኃይል ሥራን ወይም የእጅ እልፊትን አስከትሎ እንደሆነ በአንቀጽ ፬፻፷፩ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፬፻፷፩</u> <u>የኃይልና የማስገደድ ድርጊት</u>

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ ግዴታው የሆነውን ተግባር እንዳያከናውን በዛቻ፣ በማስገደድ ወይም በኃይል ድርጊት ያሰናከለ ወይም ይህን ግዴታውን እንዲያከናውን ወይም ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ ያስገደደ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የመንግሥት ሠራተኛን ወይም በስራው የሚረዳውን ሰው የደበደበ ወይም የኃይል ወይም

BACK



የማስገደድ ድርጊት ወይም ማናቸውንም ሌላ የማስገደድ ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፤

ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ እንደጥፋቱ ከባድነት መጠንና እንደ ተበዳዩም የሥራ ደረጃ ተበዳዩ በጦር መሣሪያ ወይም በሌላ መሣሪያ አማካይነት ተዝቶበት፣ ተገድዶ ወይም ተደብድቦ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፫ የእጅ እልፊቱ ወይም የኃይል ተግባሩ በተበዳዩ ላይ የአካል ጉዳት ወይም የጤንነት ጉድለት ያስከተለ እንደሆነ፤ ስለወንጀሎች መደራረብ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፬፻፴፪ በሕብረት የሚፈፀም ድርጊት</u>

ዛቻው፣ ማስገደዱ፣ ወይም የኃይል ድርጊቱ በተከለከለ የአደባባይ ስብሰባ ወይም በረብሻ የተፈፀመ እንደሆነ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራራቢነት ይፈጸማሉ /አንቀጽ ፬፻፹፬ እና ፬፻፹፰/::

## ርዕስ አራት

## በፍትሕ አስተዳደር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### ምዕራፍ አንድ

### በዳኝነት ሥራ አካሄድ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

<u>አንቀጽ ፬፻፴፫ ወንጀልን አለማስታወቅ</u>

፩ ማንም ሰው በቂ ምክንያት ሳይኖረው:-

ሀ/ በሞት ወይም በዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት የሚያስቀጣ ወንጀል መፈፀሙን ወይም የወንጀለኛውን ማንነት እያወቀ ለሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ሳያስታውቅ የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሕግ ወይም በሙያው ደንቦች ለህዝብ ደህንነት ወይም ሰላምና ሥርዓት ሲባል አንዳንድ ወንጀሎችን ወይም አንዳንድ ከባድ ሁኔታዎችን ለሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች የማስታወቅ ግዴታ እያለበት ይህን ግዴታውን ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ፤

ከብር አንድ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፪፻፵፬ እና ፫፻፴፰ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ናቸው::

<u>አንቀጽ ፬፻፵፬ በጠቋሚዎች እና በምስክሮች ላይ የሚፈጸም ወንጀል</u>

፩ ማንም ሰው ወንጀልን በሚመለከት ለፍትሕ አካላት ጥቆማ ወይም መረጃ የሰጠ ሰው ላይ ወይም በምስክርነት በቀረበ ሰው ላይ ማናቸውንም ጥቃት፣ ተጽዕኖ ወይም ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤
በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የጤና ጉዳትን ወይም ሞትን አስከትሎ እንደሆነ፤ እነዚህኑ በሚመለከት የተደነገጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ::

BACK



ማንም ሰው እያወቀ በወንጀል የሚከሰስን ሰው አስቀድሞ በማስጠንቀቅም ሆነ በመደበቅ ወይም ወንጀሉን የፈፀመበትን መሣሪያ ወይም ዱካውን በመሸሸግ ወይም በማጥፋት፣ የሚደረግ ምርመራን በማሳሳት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ተከሰሶ እንዳይቀርብ የረዳ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፵፯ የፍትሕን ሥራ ማሳሳት

ማንም ሰው:-

ሀ/ ያልተደረገ መሆኑን እያወቀ አንድ ወንጀል ተደርጓል ብሎ ለባለሥልጣኖች በሐሰት ያስታወቀ ወይም በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ራሱ ያላደረገውን ወንጀል ፈፅሜአለሁ በማለት ራሱን የከሰሰ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የወንጀል ምርመራን ወይም የክስ ሂደትን በሚመለከት እያወቀ ትክክል ያልሆነ መረጃ ለባለሥልጣኖች የሰጠ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፵፰ በሐሰት መወንጀል ወይም መከሰስ

ማንም ሰው:-

ሀ/ የሌላውን ሰው ንጽህና እያወቀ ባልፈፀመው ወንጀል በባለሥልጣን ዘንድ የወነጀለው እንደሆነ፤ ወይም

BACK



ለ/ በማናቸውም ሌላ ዘዴ በተለይም፣ ንፁህ የሆነውን ሰው ባልፈፀመው ወንጀል እንዲከሰስ አቅዶ ወንጀል የተፈፀመ በማስመሰል ወይም ስሙን ሳይገልጽ ትክክለኛ ባልሆነ ውንጀላ ሌላውን ሰው የከሰሰ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት እና በመቀጮ ይቀጣል:: ሆኖም በሐሰት የቀረበው ውንጀላ በተወንጃዩ ላይ ከዚህ በላይ ከተመለከተው ቅጣት የበለጠ ቅጣትን አስከትሎ እንደሆነ በንፁሁ ሰው ላይ በተወሰነው ቅጣት ልክ ይቀጣል::

አንቀጽ ፬፻፵፫ ለፍትህ እርዳታ መስጠትን እንቢ ማለት

፩ ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያለው አካል በያዘው ጉዳይ ላይ በተከሳሽነት፣ በምስክርነት ወይም በልዩ አዋቂ ምስክርነት ወይም በአስተር ጓሚነት፣ በነባሪነት ወይም በተቺነት እንዲረዳ በሕግ መሠረት የተጠራ ወይም ተከሳሽን ወይም ማስረጃን እንዲያቀርብ ወይም እንዲልክ የታዘዘ ማንም ሰው:-

ሀ/ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ሳይቀርብ የቀረ ወይም ለመቅረብ እምቢተኛ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ተከሳሽን ወይም ማስረጃን ያላቀረበ ወይም ያልላከ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ቀርቦ ሕግን በሚቃረን አኳኋን ለተጠየቀው መልስ ለመስጠት ወይም እንደታዘዘው ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ፤

ከሁለት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፲ ጥፋተኛው በንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ በተገለፀው ዓይነት ስለፈፀመው ወንጀል ያቀረበው ምክንያት ሐሰተኛ

BACK



ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ይኸው ሰው ሐሰተኛ ምክንያት በማቅረብ ከግዴታው የዳነ እንደሆነ በፈጸመው የአጭበርባሪነት ወንጀል ሊደርስበት የሚገባው የቀላል እሥራት ቅጣት እስከ መደበኛው የቅጣት ጣራ ለመድረስ የሚችል ሲሆን፣ በተለይም ሐሰተኛ በሆነ ሰነድ ወይም የምስክር ወረቀት በተገለገለ ጊዜ የሚወሰነው የቅጣት ደንብ እንደተጠበቀ ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል ፊት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወይም የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው ሌላው አካል ቀጠሮ ሳያደርግ ወዲያውኑ ከዚህ በላይ የተደነገገውን ቅጣት ለመወሰን ይችላል::

## አንቀጽ ፬፻፵፱ ፍርድ ቤትን መድፈር

፩ ማንም ሰው በፍርድ ቤት ምርመራ በሚደረግበት ወይም የፍርድ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ:-

ሀ/ ፍርድ ቤቱን ወይም የዳኝነት ሥራ በማከናወን ላይ ያለውን ዳኛ በማናቸውም መንገድ የሰደበ፣ ያወከ ወይም በነዚሁ ላይ ያፌዘ ወይም የዛተ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ የፍርድ ቤቱን ሥራ በማናቸውም ሌላ መንገድ ያወከ እንደሆነ፣

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ሳያደርግ ወዲያውኑ በጥፋተኛው ላይ ቅጣት ሊወስን ይችላል::

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው ከችሎት ውጭ ሆኖ ዳኛው ሥራውን እያከናወነ ባለበት ጊዜ ከሆነ፣ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በችሎት ወይም በማናቸውም ቦታ የዳኝነት ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ሆኖ በኃይል ወይም በማስገደድ እንደሆነ፣ አግባብ ያለው ድንጋጌ /አንቀጽ ፬፻፴፩/ በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፬፻፵</u> <u>የፍርድ ሂደትን ምስጢር መግለፅ</u>

፩ ማንም ሰው ሕጋዊ ፈቃድ ወይም ይቅርታ የሚያስጥ ምክንያት ሳይኖረው በሁኔታው ምስጢር የሆነውን ወይም ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ምስጢር ሆኖ እንዲጠበቅ የወሰነውን እና በፍርድ ሂደቱ ላይ በመገኘቱ ምክንያት ያወቀውን ማናቸውንም ፍሬ ነገር የገለጸ እንደሆነ፣

ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው በግል የሙያ ሥራው ወይም በሠራተኛነቱ ምክንያት ያገኘውን ምስጢር በመግለፅ እንደሆነ፣ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፫፻፺፯፣ ፫፻፺፱/ ተፈጻሚ ይሆናሉ::

<u>አንቀጽ ፬፻፵፩</u> <u>የፍርድ ሂደትን በተመለከተ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተከለከለ ዘገባን መግለፅ</u>

፩ ማንም ሰው በቀጠሮ ወይም በመሰማት ላይ ስላሉ ወይም ውሳኔ ስላላገኙ የዳኝነት ጉዳዮች ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተዛባ መረጃን፣ ማስታወቂያን፣ ፍሬ አሳብን ወይም ዘገባን የገለፀ እንደሆነ፣

ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በተለይም የኅብረተሰቡ አስተሳሰብ እንዲታወክ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ የሚችል በሆነ ጊዜ፣ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከለከለ ጉዳይን መግለፅ የሚያስቀጣው አግባብ ባለው ድንጋጌ ነው /አንቀጽ ፬፻፴፮/::

የተደረገው አገላለፅ ሕገ ወጥና የተሳሳተ እንደሆነና ድርጊቱም ታስቦ የተፈፀመ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ስለወንጀሎች መደራረብ በተደነገገው መሠረት ቅጣቱን ያከብዳል /አንቀጽ ፻፹፬/:

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>በፍትሕ ሥራ ላይ ሊደረግ በሚገባው በእውነተኛነትና</u>

<u>በታማኝነት ተግባር ላይ የሚፈፀም ወንጀል</u>

<u>አንቀጽ ፬፻፶፪ አንድ ተከራካሪ ወገን የሚሰጠው ሐሰተኛ ቃል</u>

፩ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል ዘንድ ቀርቦ እውነት እንዲናገር ታዞ በፍርድ ቤቱ ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል በሚወሰን ጭብጥ ላይ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች በሚመለከት እያወቀ ሐሰተኛ ቃል የሰጠ እንደሆነ፤

የፈለገው ውጤት ሳይገኝ ቢቀርም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት፤ ወይም ሐሰተኛውን ቃል የሰጠው የወንጀል ክስ ሂደት ላይ ሆኖ ኢ-ፍትሐዊ

BACK



ውሳኔ ሊያስከትል የሚችል እንደሆነ፣ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ተከራካሪው ወገን እውነቱን ለመናገር ምሎ ወይም ማረጋገጫ ሰጥቶ እንደሆነ በተለይም የተፈለገው ውጤት በከፊል ወይም በሙሉ ተገኝቶ እንደሆነ፣

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ተከራካሪው ወገን ጥቅሙን ለማስከበር ሲል ለሚያቀርበው ትክክለኛ ያልሆነ ክርክር የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ አይሆኑም::

**አንቀጽ ፬፻፶፫ ሐሰተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም**

፩ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሰው ማንኛውንም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሐሰተኛ ምስክርነት ወይም የልዩ አዋቂነት አስተያየት የሰጠ እንደሆነ ወይም እውነቱን የደበቀ እንደሆነ፣

ያቀደው አሳቡ ከግቡ ባይደርስለትም እንኳ በቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ምስክሩ እውነቱን ለመናገር ምሎ ወይም ማረጋገጫ ሰጥቶ እንደሆነ በተለይም የተፈለገው ውጤት በከፊል ወይም በሙሉ ተገኝቶ እንደሆነ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ነው::
ሆኖም በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በመስካሪው ድርጊት ምክንያት የጥፋተኛነት ውሳኔ ተላልፎበት እንደሆነ

ወይም ከአሥር ዓመት ፅኑ እሥራት በላይ ተፈርዶበት እንደሆነ የተመሰከረበት ሰው በስህተት በተወሰነበት ቅጣት ልክ ሀሰተኛ መስካሪው ሊወሰንበት ይችላል።

፫ በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክነት ሥልጣን ባለው አካል በሚወሰን ጭብጥ አግባብነት ባለው ፍሬነገር ሐሰተኛ ትርጉም የሚሰጥ ማንኛውም ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ እንደአግባቡ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩)/ ወይም (፪) ላይ የተመለከተው ቅጣት ይወሰንበታል።

፬ ሐሰተኛ ምስክርነቱ ወይም ልዩ አስተያየቱ፣ በሀሰት መተርጐሙ ወይም ማስተርጐሙ ተደርሶበት ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያለው አካል በሚሰጠው ፍርድ ላይ ተፅዕኖ ሊያደርግ የማይችል እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሁለት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ነው።

<u>አንቀጽ ፬፻፶፬</u> <u>ቃልን ማቃናት ወይም መለወጥ</u>

ሐሰተኛ ምስክርነቱ ወይም ልዩ አስተያየቱ፣ በሐሰት መተርጐሙ ወይም ማስተርጐሙ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ከማድረሱና የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጥፋተኛው በገዛ ነፃ ፈቃዱ ቃሉን አቃንቶ ወይም ለውጦ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን በተለየ ሁኔታ /አንቀጽ ፻፹/ ያቃልልለታል።

ወንጀሉ ወይም ወንጀሉ የሚያስከትለው አደጋ ቀላል ሆኖ የማቃናቱ ወይም የመለወጡ ተግባር የተፈጸመው በሐቀኛነት እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ጥፋተኛውን በመገሰጽና ማስጠንቀቂያ በመስጠት ፍርድ ቤቱ ከማናቸውም ሌላ ቅጣት ነፃ ሊያደርገው ይችላል።

BACK



## አንቀጽ ፬፻፵፭ መገፋፋትና ማግባባት

፩ ማንም ሰው በስጦታ፣ በተስፋ፣ በዛቻ፣ በተንኮል ወይም በማታለል፣ በተሰሚነቱ በማግባባት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ ሌላውን ሰው አግባብ ባለው አካል ፊት፣ በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ ሂደት ላይ በሐሰት እንዲወነጅል፣ እንዲመሰክር፣ ወይም ሐሰተኛ ዘገባ፣ ትርጉም ወይም ማመልከቻ እንዲያቀርብ የገፋፋው ወይም ያግባባው እንደሆነ፤

የአደራረጉ ሁኔታና ጠባዩ ስለወንጀል አነሳሽነት በጠቅላላው ክፍል በተደነገገው /አንቀጽ ፴፮/ መሠረት የሚያስቀጣው ካልሆነ በስተቀር ያቀደው ተግባር ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳን በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው የኃይል ሥራ በመሥራት፣ የዛቻ ወይም የማስፈራራት ተግባር በመፈጸም ወይም የማይገባ ጥቅም በመስጠት ወይም በማቅረብ ከሁለት ዓመት በላይ በጽኑ እሥራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ላይ የሐሰት ክስ እንዲቀርብ ወይም ሐሰተኛ ምስክርነት እንዲሰጥ ያደረገ ወይም በምስክር አሰጣጡ ወይም ማስረጃ አሰባሰቡ ላይ ጣልቃ በመግባት ያደናቀፈ እንደሆነ፣ ወይም በሕግ ማስከበር ሥራ በተሰማራ ወይም በመንግሥት ሠራተኛ መደበኛ ሥራ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ያወከ እንደሆነ፣

ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፵፮ በሙግት ጊዜ ማጭበርበር

ማንም ሰው ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ጉዳዮች ሌላ በዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ባለው ሂደት ላይ ቁሳዊ ወይም ኅሊናዊ ጥቅም ለማግኘት፣ በሚጠቅም ወይም በሚጐዳ አኳኋን በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፅእኖ ለማድረግ አቅዶ ፍርድ ቤትን ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያለውን

አካል ለማሳሳት፣ ማስረጃን ለማሰናከል፣ ወይም የፍርዱን ትክክለኛ ሂደት ለማዛባት በማሰብ፡-

ሀ/ የሌላ ሰው የሆነውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሰነድ ወይም ማናቸውንም ኤግዚቢት ወይም የጥፋተኛነት ማስረጃ የደበቀ፣ የሰረቀ፣ ያጠፋ፣ ያበላሸ ወይም በከፊልም ሆነ በሙላው እንዳያገለግል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የሥፍራዎችን፣ የዕቃዎችን ወይም የሰዎችን ሁኔታ የደበቀ፣ ያሻሻለ፣ ያበላሸ፣ ወይም የለወጠ እንደሆነ፤

ወንጀሉ በሌላ ድንጋጌ ከፍተኛ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

አንቀጽ ፬፻፵፯ የፍትህን ሂደት ለማዛባት በተንኮል የሚፈፀም የወሬ መግለፅ ድርጊት

ማንም ሰው ለፍርድ ቤት በሚቀርብ ወይም በፍርድ ቤት እየታየ ባለ ጉዳይ ላይ ተከሣሹን ወይም አባሪውን በማስጠንቀቅም ሆነ በዳኛ፣ በነባሪ፣ በምስክር፣ በልዩ አዋቂ ምስክር ወይም በጠቅላላው በፍርድ ቤቱ ሥራ ረዳት ላይ የተሳሳተ ስሜትን በማሳደር በተሳሳተ መንገድ ውሳኔ እንዲሰጥ ተፅዕኖ ለማድረግ በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የሚያሳስት ወይም ፍሬ ነገሩን የሚያዛባ ወሬ፣ ማስታወሻ፣ ፍሬ አሳብ፣ ትችት፣ ዘገባ ወይም በራሪ ጽሁፍ በማናቸውም መንገድ የገለጸ ወይም ያሰራጨ እንደሆነ፤

ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

BACK



## አንቀጽ ፬፻፴፰ በአንድ ወገን ተከራካሪ ጥቅም ላይ የክህደት ተግባር መፈፀም

፩ ማንኛውም ጠበቃ፣ ነገረ ፈጅ፣ ወይም የሕግ አማካሪ በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ ማናቸውንም ዓይነት ክርክር እንዲከራከር በኦፊሴላዊ መንገድ ወይም በባለጉዳዩ በተወከለበት ጉዳይ የወካዩን ወገን ጥቅም በመሰዋት ወይም በአንድ ጉዳይ የሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳይ አጣምሮ በመሥራት እያወቀ ጉዳዩን ያበላሸበት እንደሆነ፤

በቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈጸመው ከተቃዋሚ ወገን ጋር በመስማማት እንደሆነ የእሥራት ቅጣቱ ከአንድ ዓመት ቀላል እሥራት ያነሰ ሊሆን አይችልም:: ወንጀሉን የፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ ወይም ቁሣዊ ጥቅም ለማግኘት እንደሆነ፤ መቀጮው እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ሊደርስ ይችላል::

ወንጀሉ የተፈጸመው የሞት ቅጣት ወይም የእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት በሚያስቀጣ ወንጀል በተከሠሠ ሰው ላይ ጉዳት በሚያስከትል ሁኔታ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፫ በንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል::

## ምዕራፍ ሦስት

## በወንጀል ፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፬፻፷፱ ተጨማሪ ቅጣቶችን የመከላከልና የመጠበቅ የጥንቃቄ እርምጃዎችን አለማክበር**

ማንም ሰው ከመብት የመሻር ተጨማሪ ቅጣት /አንቀጽ ፻፳፫/ ወይም የጥንቃቄ እርምጃ /ከአንቀጽ ፻፵፩-፻፶፬/ ከተወሰነበት በኋላ እያወቀ በሕግ አግባብ የተወሰነበትን ክልከላ ወይም ግዴታ የጣሰ እንደሆነ፤

በሌላ አንቀጽ ከፍተኛ ቅጣት የሚቀጣ ካልሆነ በስተቀር /አንቀጽ ፬፻፸፰/፤ ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ጥፋቱ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአንድ ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ ፬፻፸ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ማሰናከል**

ማንም ሰው በአንድ ወንጀለኛ ላይ በፍርድ ቤት የተወሰነውን ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ በማናቸውም አኳኋን እንዳይፈጸምበት ያደረገ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ ፬፻፸፩ የእሥረኛ ማምለጥ**

፩ ማንም ሰው በሕግ አግባብ ተይዞ ወይም ታስሮ ካለበት ቦታ ያመለጠ እንደሆነ፤
ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በሰዎች ላይ ዛቻ ወይም የኃይል ተግባር በመፈፀም ወይም በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ እንደሆነ፤ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል፡፡

፫ ጥፋተኛው በመጀመሪያው ወንጀል የተፈረደበት ወይም የሚፈረድበት ሲሆን ስለወንጀሎች መደራረብ ወይም ስለደጋጋሚነት የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ ፬፻፷፪ — እሥረኛ እንዲያመልጥ ማመቻቸትና መርዳት**

፩ ማንም ሰው የመንግሥት ሠራተኛ ሳይሆን /አንቀጽ ፬፻፪/ በሕግ አግባብ የተያዘ ወይም የታሰረ ሰው እንዲያመልጥ በኃይል ድርጊት፣ በማስገደድ፣ በዛቻ፣ በተንኰል፣ በግል ተሰሚነቱ ያለአግባብ በመገልገል ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ መንገድ ያመቻቸ ወይም የረዳ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል።

፪ ቅጣቱ ከሦስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት የሚሆነው:-

ሀ/ ማምለጡ የተፈፀመው፣ የተሞከረው ወይም የተመቻቸው በቡድን የኅብረት ሥራ፣ በጦር መሣሪያ ወይም በማናቸውም ሌላ መሣሪያ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ እንዲያመልጥ እርዳታ የተደረገለት ሰው ሲቪል ወይም የመከላከያ ሠራዊት አባል ቢሆንም ቢያንስ የሃያ ዓመት ፅኑ እሥራት የተፈረደበት ወንጀለኛ እንደሆነ፤

ነው።

፫ ወንጀለኛው ዕቅዱን ለማሣካት ሁከት አንስቶ፣ በሰው ወይም በንብረት ላይ የኃይል ድርጊት ፈፅሞ፣ ወይም ሠራተኛን ወይም ጠባቂን ደልሎ፣ ወይም ማናቸውንም ሌላ ተደራቢ ወንጀል ፈፅሞ እንደሆነ፤ የተደራረቡ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ ቅጣትን ስለማክበድ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚዎች ይሆናሉ /አንቀጽ ፷፫ እና ፷፮/።

<u>አንቀጽ ፬፻፷፫</u> <u>የጦር ምርኮኞችና ወታደራዊ ግዞተኞች ማምለጥና እንዲያመልጡ መርዳት</u>

የአንቀጽ ፬፻፶፯ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተለይ በተዘጋጀ የወታደር ግዞት፣ ቦታ ወይም ሠፈር ውስጥ የሚገኙ የጦር ምርኮኞችን ወይም የወታደር ግዞተኞችን በሚመለከት በፍርድ ውሳኔ በወንጀል ቅጣት የተያዙ ባይሆኑም እንኳ፣ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፬፻፷፩ እና ፬፻፷፪ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ ፬፻፷፬</u> <u>የእስረኞች አመፅ</u>

፩ ማንም ሰው በሕግ አግባብ ተይዞ እንዲቆይ በተደረገበት ጊዜ፦

ሀ/ የእስር ቤቱን አስተዳዳሪ ባለሥልጣን፣ ጠባቂ ወይም የእስር ቤቱን አስተዳደር ወይም ቁጥጥር ለማካሄድ ኃላፊነት የተሰጠውን ማንኛውንም ሰው በኃይል ድርጊት ወይም በዛቻ የሥራ ግዴታውን እንዳያከናውን ወይም የሥራ ግዴታውን የሚቃረን ድርጊት እንዲፈጽም ለማስገደድ፤

ለ/ ከነዚሁ ሰዎች መካከል የሥራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ በአንዱ ላይ አደጋ ለመጣል፤ ወይም

ሐ/ በሰዎች ወይም በንብረት ላይ የኃይል ድርጊት በመፈጸም ለማምለጥ፤

በማሰብ በአመጽ ወይም በሁከት ተካፋይ እንደሆነ፤ ሊወሰንበት ከሚገባው ወይም ተወስኖበት በመፈፀም ላይ ካለው ቅጣት ጋር ተደራቢ በሚሆን ከሦስት ወር

እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ አመፁን ያዘጋጀው ወይም የመራው ሰው:-

ሀ/ የማስገደድ ወይም የኃይል ድርጊት ባልተፈጸመ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት፤

ለ/ የማስገደድ ወይም የኃይል ድርጊት ተፈጽሞ እንደሆነ፤

ከዚህ የበለጠ ቅጣት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፫ በሰዎች ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ደርሶ እንደሆነ ስለወንጀሎች መደራረብ የተደነገጉት የማክበጃ ጠ ቅላላ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ /አንቀጽ ፷፫፣ ፷፯/::

<u>አንቀጽ ፬፻፷፩</u> <u>አካባቢያዊ ክልከላን መጣስ</u>

ማንም ሰው በአንድ ቦታ ወይም አካባቢ ተወስኖ እንዲኖር ወይም በአንድ በተወሰነ ቦታ ከመኖር ወይም ውሎ ከማደር የመከልከል ወይም ከአገር የመውጣት ፍርድ ተወስኖበት ሳለ ከአቅሙ በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖረው ይህን ውሳኔ የጣሰ እንደሆነ፤

አስፈላጊ ሲሆን ተወስኖበት የጣሰውን የጥንቃቄ እርምጃ ከፍ ለማድረግ መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

የቅጣቱ ውሳኔ የሚቀይበት ጊዜ የግል ነፃነትን ከሚቀንሱ የጥንቃቄ እርምጃዎች ጋር አይታሰብም::

BACK



## ርዕስ አምስት

## በሕዝባዊ ምርጫዎችና በድምፅ አሰጣጥ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፬፻፷፯ ለምርጫ የሚደረግ ስብሰባንና የምርጫ ሂደትን ማወክና ማሰናከል

፩ ማንም ሰው በሕግ የተፈቀደ ከምርጫ ጋር የተገናኘ ሕዝባዊ ስብሰባን ወይም በሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ቁጥጥር በአግባቡ የሚደረግ የድምፅ አሰጣጥን ወይም ምርጫን አግባብ በሌለው በማናቸውም መንገድ ያወከ፣ የከለከለ፣ ያደናቀፈ ወይም እንዲቋረጥ ያደረገ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራትና ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ በሰዎች ወይም በንብረት ላይ የኃይል ድርጊት ተፈጽሞ እንደሆነ፤ ወይም የአምባጓሮ ወይም የሁከት ጠባይ ያለው ረብሻ ተነስቶ እንደሆነ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ::

### አንቀጽ ፬፻፷፰ የምርጫ ድምፅ የመስጠትን ወይም የመመረጥን መብት መንካት

፩ ማንም ሰው በዛቻ፣ በማስገደድ፣ በሥልጣኑ ያለአግባብ በመጠቀም ወይም በኃይል ድርጊት፣ በማጭበርበር በተለይም ስምን በመለዋወጥ፣ ማስታወቂያን ወይም መጥሪያን በመደበቅ ወይም በማስቀረት ወይም በማናቸውም ሌላ ብልሀት ወይም ዘዴ:-

ሀ/ ሌላ ሰው በመምረጥ ወይም በመመረጥ መብቱ እንዳይጠቀምበት የከለከለ እንደሆነ፤ ወይም

BACK



ለ/ ይህን በመሰለ ዘዴ ሌላ ሰው መብቱን በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም በዚሁ መብቱ ሳይጠቀምበት ለመቅረት ግዴታ እንዲገባ ያደረገ ወይም ያግባባ እንደሆነ፣

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ማንም ሰው እንደፍላጎቱ ለመጠቀም በተሰጠው መብት መሠረት የመምረጥ መብቱን በአንድ በተወሰነ መንገድ በተጠቀመበት ወይም ሳይጠቀምበት በቀረው ሰው ላይ በደል ወይም ጉዳት ያደረሰበት እንደሆነ፣

ከዚህ በላይ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፷፰</u> <u>በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ</u>

፩ ማንም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለውን ሌላውን ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ፣ ወይም ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

፪ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ማንም ሰው በዚሁ መብቱ እንዲጠቀምበት፣ ወይም በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም ሳይጠቀምበት እንዲቀር ገንዘብ ወይም ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ጥቅም የተቀበለ ወይም ለመቀበል የተስማማ እንደሆነ፣ ከዚህ በላይ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፬፻፷፱ የማይገባ አሠራር

፩ ማንኛውም እጩ ተመራጭ በሕግ ከተፈቀደው ውጭ ለምርጫ ዘመቻ ወጪ የሚሆን ገንዘብ ከማናቸውም ሰው፣ ቡድን ወይም ድርጅት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሰበሰበ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የተወሰነውን የምርጫ ውድድር ሂሣብ ማቋቋሚያ ደንቦች ያላከበረ እንደሆነ ወይም በምርጫ ውድድር ሂሣብ ውስጥ ወጪውን አስቦ አሳንሶ ያመለከተ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

፪ ማንም ሰው ከእጩ ተመራጩ ፈቃድ ሳያገኝ የአንድን እጩ ተመራጭ የምርጫ ወጪ ለመሸፈን ገንዘብ ያሰባሰበ፣ የሰጠ፣ ወይም በማናቸውም መንገድ አስተዋጽኦ ያደረገ እንደሆነ፤

ከላይ የተመለከተው ቅጣት ይፈፀምበታል፡፡

፫ ማንም ሰው በቀጥታ ወይም በሌላ ሰው አማካይነት፡-

ሀ/ በሰው በማስነገር፣ በመጻጻፍ፣ በፖምፍሌት፣ በሚለጠፍ ጽሁፍ ወይም ስዕል፣ ታትሞ በሚወጣ ጽሑፍ፣ በራዲዮ ወይም በማናቸውም ሌላ የሕዝብ መገናኛ ዘዴ በሚሰራጭ ሐሰተኛ ዜና ወይም ወሬ በመታገዝ፤ ወይም

ለ/ በማናቸውም ሌላ የማጭበርበር፣ የማዛባት ወይም ከሐቀኛ አሠራር ውጭ በሆነ መንገድ በመታገዝ፤

አጭበርብሮ የመራጭ ድምጽን ያገኘ ወይም በመራጭ ድምጽ ያለአግባብ የተገለገለ ወይም ድምፁ መራጩ ለመረጠው ሰው እንዳያገለግል ያደረገ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

**አንቀጽ ፬፻፸ በአመዘጋገብ ላይ የሚፈፀም ማጭበርበር**

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ በምርጫ ዝርዝር ወይም በምርጫ መዝገብ ውስጥ በሐሰተኛ ስም ወይም ማዕረግ ወይም በሌለው ችሎታ እንዲመዘገብ ያደረገ ወይም ያለበትን በሕግ የታወቀ ችሎታ ማጣት ሳይገልጽ የተመዘገበ እንደሆነ፤

ለ/ በአንድ ጊዜ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ የምርጫ ዝርዝሮች ወይም መዛግብት ስሙን ያስመዘገበ ወይም ያለአግባብ ብዙ የድምጽ መስጫ ወይም የምርጫ ወረቀቶችን የተቀበለ ወይም እንዲሰጡት ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ያለአግባብ በሕይወት ያሉ፣ የሞቱ፣ የጠፉ፣ ወይም በሕይወት ኖረው የማያውቁ ሰዎችን ያስመዘገበ ወይም በእነርሱ ስም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የተቀበለ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል በእጩ ተመራጭ በተፈጸመ ጊዜ ቅጣቱ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጽኑ እሥራት ወይም ከአሥር ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል::

BACK



## አንቀጽ ፬፻፸፩ በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ የሚፈጸም የማጭበርበር ድርጊት

ማንም ሰው ማናቸውም ዓይነት የታወቀ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ፣ ከምርጫው በፊት፣ በምርጫው ጊዜ፣ ወይም ከምርጫው በኋላ በሚፈጸም በማናቸውም ዓይነት ድርጊት በተለይም:-

ሀ/ የምርጫ መዝገብን፣ የተጠናቀቀ የምርጫ ዝርዝርን፣ ወይም ድምፅ የተሰጠበትን የድምፅ መስጫ ወረቀትን አስመስሎ በመሥራት፣ ሐሰተኛ በማድረግ፣ በመለወጥ፣ በሚያሳስት ዘዴ በላዩ ላይ በማተም፣ ወይም በማስቀረት፣ በማጥፋት ወይም በመውሰድ፤

ለ/ በአንድ የምርጫ ጊዜ ከአንድ ጊዜ በላይ ድምፅ በመስጠት፤

ሐ/ የድምፅ መስጫ ወረቀትን በድምፅ መስጫ ሣጥን ውስጥ በመጨመር ወይም ከምርጫ ሳጥን አውጥቶ በመውሰድ፣ ወይም በማናቸውም መንገድ ያለአግባብ ሕጋዊ መኖሪያ ቦታው ምርጫ ከሚደረግበት አካባቢ ውጭ የሆነውን፣ ችሎታ የሌለውን፣ ችሎታ ያጣውን ሰው ድምፅ እንዲሰጥ፣ ወይም በሞተ ወይም ሕይወት ኖሮት በማያውቅ ሰው ስም ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ወይም ለድምፅ መስጫ እንዳያገለግል የተደረገ፣ወደ ሐሰተኛነት የተለወጠ፣ ወይም በሀሰት የተሰራ የድምፅ መስጫ ወረቀትን እያወቀ በምርጫ ሣጥን ውስጥ በማስገባት ወይም እንዲገባ በመፍቀድ፤ ወይም

መ/ የድምፅ መስጫ ወረቀትን በትክክል ባለመቁጠር ወይም ታስቦ የተሰጠ ድምጽን፣ ድምፅ የተሰጠበትን ወረቀት፣ ስምን ወይም ፊርማን በመተው፣ ወይም ከተጻፈው ፊርማ ወይም ስም ሌላ በማንበብ ወይም በምርጫው ሥነ ሥርዓት ቃለ ጉባኤ ወይም

በኦፊሴላዊ የምርጫ ውጤት ላይ ከእውነተኛው ነገር ውጭ በመመዝገብ፤ ወይም

ሠ/ የምርጫ ውጤትን ወይም ሰነድን በማስቀረት፣ በመደበቅ፣ በመለዋወጥ ወይም በማጥፋት ወይም እነዚህን ለመቀበል ሥልጣን ለሌላቸው ሰዎች ያለአግባብ በመስጠት፤

የምርጫውን ትክክለኛ ውጤት ያሳሳተ እንደሆነ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

## <u>አንቀጽ ፬፻፷፪ የወንጀሎች መደራረብ</u>

የተፈጸመው የማጭበርበር ወይም ወደ ሐሰት የመለወጥ ወንጀል የተሠራው በግዙፍ ወይም በረቀቀ ዘዴ እንደሆነ፤ ይህንኑ ጉዳይ የሚመለከተው የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናል /አንቀጽ ፫፻፴፩፣ ፫፻፴፪/::

## <u>አንቀጽ ፬፻፷፫ የድምፅ አሰጣጥ ምስጢር አጠባበቅን መጣስ</u>

ማንም ሰው:-

ሀ/ አንድ መራጭ ያለውን መብቱን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተገለገለበት ወይም ድምፁን እንደሰጠ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለማወቅ የቻለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የዚህን ዓይነት ጉዳይ በአጋጣሚ ካወቀ በኋላ በቃልም ሆነ በጋዜጣ ወይም በሌላ ዓይነት ዘዴ አስቦ ለሕዝብ የገለጸ ወይም ወሬውን የነዛ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፸፬ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችንና የምርጫ ሣጥኖችን መውሰድና ማጥፋት

፩ ማንም ሰው ድምፅ ተሰጥቶባቸው ያልተቆጠሩ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን የያዘ የምርጫ ሣጥንን ወይም በሳጥኑ ውስጥ የሚገኙትን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን በሙሉ ወይም በከፊል ከቦታው ያነሳ፣ እንዲሰወሩ ያደረገ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም በኃይል ድርጊት እንደሆነ ለአለቆቹ ወይም ለመሪዎቹ ስለቅጣት ማክበድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ /አንቀጽ ፹፬ (መ)/ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

፫ በምርጫ ጣቢያ ላይ ወይም በምርጫ ጣቢያ አባሎች ላይ የሚፈፀም የኃይል ወይም የማስገደድ ድርጊት በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፬፻፷ እስከ ፬፻፷፪ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ያስቀጣል።

## አንቀጽ ፬፻፸፭ ተጨማሪ ቅጣቶች

ምርጫን በሚመለከት የተፈፀመው ወንጀል የእሥራት ቅጣትን ያስወሰነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከሕዝባዊ መብት ለተወሰነ ጊዜ የመታገድን ቅጣት በተደራቢነት ምንጊዜም መወሰን አለበት /አንቀጽ ፻፳፫(ሀ)/።

## አንቀጽ ፬፻፸፮ ቅጣትን የሚያከብዱ ምክንያቶች

በዚህ ርዕስ ውስጥ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱን የፈፀመው የመንግሥት ሠራተኛ ወይም በመምረጫ ወይም በድምጽ መስጫ ጣቢያ በአፊሴል በአባልነት

ወይም በተቆጣጣሪነት የሚሠራ ሰው እንደሆነ፣ ድርጊቱ በሥልጣን ያለአግባብ በመገልገል /አንቀጽ ፬፻፯/፣ ወይም መንግሥታዊ ምስጢርን በመግለጽ /አንቀጽ ፫፻፳፯/፣ ወይም ይህን በመሰለው ወንጀል የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ቅጣቱ እጅግ ቢያንስ የአንድ ወር ቀላል እሥራት ሆኖ የቅጣቱ ጣሪያ ለወንጀሉ በተመደበው ቅጣት ላይ አጋማሹን በመጨመር የሚገኘው ውጤት ነው።

ሁኔታዎቹ በጣም ከባድ ሲሆኑ ወይም ወንጀሉ ተደጋግሞ ሲፈፀም ፍርድ ቤቱ ከእሥራቱ ቅጣት ጋር መቀጮ አጣምሮ ሊፈርድ ይችላል።

## ርዕስ ስድስት
## በሕዝብ ደኅንነት፣ ሰላምና ተረጋግቶ መኖር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች
## ምዕራፍ አንድ
## በሕዝብ ደኅንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች
## ክፍል አንድ
## ሌሎች ወንጀሎች እንዲፈፀሙ የሚያነሳሱ ወይም ሊያነሳሱ የሚችሉ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፬፻፹፯ አደገኛ የሆነ ሥራ ፈትነት

፩ ማንም ሰው ሙሉ አካል እያለው የተወሰነ መኖሪያ ወይም መደበኛ ሥራ ወይም ለኑሮው አስፈላጊ የሆነ መደበኛ ወይም ጉልህ የሆነ የገቢ ምንጭ የሌለው ሆኖ የሥራ ፈትነትን ወይም የመጥፎ አኗኗር አመልን፣ ገንዘብ ለማግኘት ሲል ነቀፌታ ያለበትን መጥፎ ዘዴ አስቦ ልማድ አድርጎ የያዘና በዚሁ ኑሮው ለሕዝብ ደህንነትና ፀጥታ አደገኛ የሆነ እንደሆነ፣

የግል ነጻነትን ከመቀነስ ጋር በሚወሰን የግዴታ ሥራ /አንቀጽ ፻፬/፣ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው የጦር መሣሪያ ወይም በጠባያቸው ወንጀልን ለመፈጸም የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ይዞ የተገኘ እንደሆነ፤ በቀላል እሥራት የሚቀጣ ሲሆን፣ ዛቻን ወይም የማስገደድ ድርጊትን፣ ወይም በግለሰቦች ላይ የኃይል ድርጊት ወይም የእጅ እልፊት የፈጸመ እንደሆነ፤ ስለወንጀሎች መደራረብ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል::

፫ ሁኔታዎች ሲመዛዘኑ ተገቢ ሆኖ በታየ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የነፃነት መቀነስ የጥንቃቄ እርምጃዎችን /አንቀጽ ፻፵፬፣ ፻፵፱/ ከዋናው ቅጣት ጋር አጣምሮ ለመወሰን ይችላል::

<u>አንቀጽ ፬፻፸፰</u> <u>የከፉ አድራጊዎች ማህበርተኛነት</u>

፩ ማንም ሰው ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር በመሆን በሕዝብ ደህንነት ወይም ጤንነት፣ ወይም በሰው ወይም በንብረት ላይ ከባድ ወንጀል ለመፈጸም ወይም ይህንኑ ወንጀል ለማዘጋጀት ያደመ፣ ወይም ሌላ ሰው በዚሁ አድማ እንዲካፈል የገፋፋ እንደሆነና አድማው በተግባር የተገለፀ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

ለዚህ ድንጋጌ ዓላማ "ከባድ ወንጀል" ማለት ቢያንስ በአምስት ዓመት ፅኑ እሥራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው::

፪ ወንጀለኞቹ ብዙ የሆኑ እንደሆነ ወይም የጦር መሣሪያዎችን ወይም ወንጀልን ለመፈጸም የሚያለግሉ ሌሎች መሣሪያዎችን ታጥቀው ወይም ይዘው የተገኙ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቀላል እሥራትና መቀጮ ይሆናል::

፫ በሰው ሕይወት ወይም አካል፣ በሕዝብ ደህንነት ወይም በንብረት ላይ በተፈጸመ ሌላ ከባድ ወንጀል፣ ተከታትለው በተፈጸሙ አንድ ዓይነት በሆኑ ወይም በተለያዩ ከባድ ወንጀሎች፣ ወይም በጦር መሣሪያ፣ በአደንዛዥ ዕጾች ወይም በሰው መነገድን በመሳሰሉት ከባድ ወንጀሎች የወንጀሉ የተለየ አደገኛነት የተገለጸ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ ተደራራቢ ወንጀሎችን መሠረት በማድረግ በሕግ የተደገገውን ከፍተኛ ቅጣት ይወስናል /አንቀጽ ፷፫ እና ፷፮/::

<u>አንቀጽ ፬፻፸፱</u> <u>የከፉ አድራጊዎች መጠጊያና ረዳት መሆን</u>

፩ ማንም ሰው በዚህ ሕግ ስለአባሪነት በተደነገገው መሠረት /አንቀጽ ፴፮/ ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ:-

ሀ/ በሕብረተሰብ፣ በግለሰቦች ወይም በንብረት ላይ ወንጀል ለመፈጸም በተቋቋሙ የከፉ ድርጊት ቡድኖች ወይም ማህበሮች አባላት ሳይገደድ እያወቀ መጠጊያ ወይም ቀለብ የሰጠ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የረዳ፣ ወይም መኖሪያ ወይም መሰብሰቢያ ቦታ የሰጠ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

ለ/ በዛቻ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ሳይገደድ የነዚህን ቡድኖች ወይም ማኀበሮች መኖር፣ ዕቅዳቸውን፣ የሚገኙበትን ቦታ ወይም መሰብሰብያ ቦታቸውን

እያወቀ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ሳያስታውቅ የቀረ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ቡድኑ ወይም ማኅበሩ በጣም አደገኛ እንደሆነ ወይም መጠጊያ መስጠቱ ወይም መርዳቱ የተፈፀመው በልማደኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል::

፫ ማንም ሰው በዚህ ሕግ ስለአባሪነት በተደነገገው መሠረት (አንቀጽ ፴፯) ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጪ ገንዘቡ ወይም ሌላ ንብረቱ:-

ሀ/ በአንቀጽ ፪፻፷፪(፩) ወይም (፪)፣ ፬፻፹፭(፪) ወይም (፫)፣ ፬፻፺፱(፪)፣ ወይም ፭፻፹፫(፫) የተመለከተውን ወንጀል ለመፈጸም፤ ወይም

ለ/ የጦር መሣሪያን በመጠቀም በሚደረግ ግጭት ውስጥ ተሳትፎ የሌለውን ሰው ወይም ሲቪሎችን ለመግደል ወይም በአካሉ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም በንብረት ላይ ከባድ ጉዳት ለማድረስ ወይም መንግሥት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት አንድን ድርጊት እንዲፈጽም ወይም ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማስገደድ ወይም ሕዝብን ለማስፈራራት የተያዘን ዕቅድ ለመተግበር፤

በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚውል እያወቀ በማናቸውም መንገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ገንዘብን ወይም ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ንብረት የሰበሰበ፣ ለድርጊቱ ፈጻሚዎች የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፣

BACK



ንብረቱ ሥራ ላይ ቢውልም ባይውልም ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፬ ማንም ሰው በዚህ ሕግ ስለአባሪነት በተደገገው መሠረት (አንቀጽ ፴፯) ከሚያስቀጣው ሁኔታዎች ውጪ አንድ ቡድን በአንቀጽ ፪፻፷፪ (፩) (፪)፣ ፬፻፹፩(፪) (፫)፣ ፬፻፺፱(፪)፣ ፭፻፹፭(፫) ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፫ የተመለከተውን ወንጀል እንዲፈጽም ወይም የቡድኑ ሕገወጥ አላማ ሥራ ላይ እንዲውል ማናቸውንም አስተዋጽኦ ያደረገ፣ ወይም በተጠቀሰው ወንጀል ላይ ለማሠማራት ሰውን የመለመለ፣ ወይም ድጋፉ ከተጠቀሱት ወንጀሎች አንዱን ለመፈጸም እንደሚያገለግል እያወቀ ለድርጊቱ ፈጻሚ ሀሰተኛ የጉዞ ሰነድ ወይም መታወቂያ ያዘጋጀ ወይም የጦር መሣሪያን ጨምሮ ማንኛውንም ድጋፍ ያደረገ ወይም አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፹</u> <u>ወንጀል እንዲፈፀም በአደባባይ መገፋፋት ወይም ወንጀልን በጅቷል ማለት</u>

ማንም ሰው በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምስል፣ በአካል እንቅስቃሴ ወይም በሌላ አድራጎት በአደባባይ፡-

ሀ/ በሕብረተሰብ፣ በግለሰብ ወይም በንብረት ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ከባድ ወንጀል እንዲፈፀም ሌላውን ሰው የገፋፋ እንደሆነ፤

ለ/ የዚህ ዓይነቱን ወንጀል ወይም አድራጊውን ያሞገሰ ወይም በጅቷል ያለ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ዓላማውን ከተቀጣው ሰው ጋር አንድ በማድረግ፣ የጥፋተኛውን ድርጊት በመደገፍ ወይም

ባለሥልጣኖችን በመንቀፍ የገንዘብ ነክ ቅጣት እንዲከፍል በሕግ አግባብ ለተፈረደበት ሰው ቅጣት ክፍያ የሚሆን የገንዘብ መዋጮ የጠየቀ ወይም የሰበሰበ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፹፩ በጦር መሣሪያ መነገድ

፩ ማንም ሰው መንግሥትን አደጋ ላይ ስለመጣል በተወሰኑት ድንጋጌዎች ከተመለከተው ውጭ /አንቀጽ ፪፻፶፯/:-

ሀ/ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት የጦር መሣሪያዎች፣ ፈንጂዎች፣ ወይም ጥይቶች በመነገድ ዓላማ የሠራ፣ ከውጭ አገር ያስመጣ፣ ወደ ውጭ አገር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ የገዛ፣ የተቀበለ፣ ያስቀመጠ፣ ያከማቸ፣ የደበቀ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም እንዲዘዋወሩ ያደረገ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በመነገድ ዓላማ ሳይሆን ለሚጠረጠሩ ወይም አደገኛ ለሆኑ ሰዎች እያወቀ ማናቸውንም ዓይነት የጦር መሣሪያ የሸጠ፣ ያስረከበ፣ ወይም የሰጠ እንደሆነ፤

የተባሉት ዕቃዎች መወረሳቸው ሳይቀር በመቀጮና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት፣ ወይም ሁኔታው ከባድ በሆነ ጊዜ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በሰው ሕይወት፣ አካል፣ ንብረት፣ በተፈጥሮ ሀብት፣ አካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል የኒውክለር ንጥረ ነገር በይዞታ ስር በማድረግ፣ በመቀበል፣ በመጠቀም፣ ወደ ሌላ ነገር በመለወጥ፣ በማዘዋወር፣ በማሠራጨት፣

BACK



ወይም በማስወገድ፣ በመስረቅ ወይም ንጥረ-ነገሩን አጭበርብሮ እጁ በማስገባት ወይም እጁ እንዲገባ ኃይል፣ ዛቻ ወይም ሌላ ማናቸውንም ድርጊት በመፈጸም ወይም እነዚህ ተግባራትን ለመፈጸም በመዛት የተፈጸመ በሆነ ጊዜ፣

ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ያስቀጣል::

፫ ድርጊቱ የተፈጸመው የጦር መሣሪያ ሲሰራ ተለይቶ እንዲታወቅ የሚያስፈልገው ሥርዓት ስያሜ ወይም የሚመለከተው መንግሥት ሳይፈቅድ ጥፋተኛው የጦር መሣሪያው ወይም ጥይቱ ከተሰራበት ወይም ከሚገጣጠምበት አገር አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ ሳያገኝ ወይም በሕግ መሠረት በመሣሪያው ላይ የመለያ ምልክት ሳይደረግ በሕገ ወጥ የመሣሪያ ንግድ በተገኙ መለዋወጫና ልዩ ልዩ አካላት ተጠቅሞ የጦር መሣሪያን በሠራ ወይም በገጣጠመ ጊዜ፣

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፬ ጥፋተኛው የተጠቀሱትን ተግባሮች የፈፀመው በአፍቅሮ ንዋይ ወይም የሙያ ሥራው በማድረግ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እሥራት ይሆናል::

፭ ስለ መሣሪያ አሠራር፣ አያያዝ ወይም አጠቃቀም የወጡ፣ በደንብ አልፊት የሚያስቀጡ ሕጎች እንደተጠበቁ ናቸው /አንቀጽ ፰፻፰ እና ፰፻፱/::

## ክፍል ሁለት

## የሕዝብ ሁከት የሚያነሳሱ ወይም ሊያነሳሱ የሚችሉ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፬፻፹፪ የተከለከሉ ማኅበሮችና ስብሰባዎች

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ በሕግ፣ በመንግስት ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን በጠቅላላው ወይም ለተወሰነ ጊዜ በተከለከለ ማህበር፣ ቡድን፣ ስብሰባ ወይም ጉባኤ እያወቀ የተካፈለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ እያወቀ ለእንዲህ ያለው ማህበር፣ ቡድን፣ ስብሰባ ወይም ጉባኤ ቤቶችን፣ ቦታዎችን፣ ወይም ግቢዎችን በገንዘብ ወይም ያለገንዘብ እንዲገለገልበት ያደረገ እንደሆነ፤

ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ የወንጀሉ መሪ፣ አደራጅ ወይም አዛዥ የሚቀጣው፤ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል
እሥራት ነው::

### አንቀጽ ፬፻፹፫ ሕቡዕ የሆኑ ማኅበሮች ወይም መሣሪያ የታጠቁ ቡድኖች

ሥራቸው ወይም ስብሰባቸው ሕቡዕ የሆነ ሕገ ወጥ ማኅበሮች፣ ወይም ሕገወጥ የሆኑና መሣሪያ የታጠቁ ቡድኖች ወይም ማኅበሮች፣ በተለይም ለወታደራዊ ሥልጠና ወይም ለዒላማ ተኩስ ወይም ለእስፖርት እንደተቋቋሙ በማስመሰል የሚታወቁ ቡድኖች ወይም ማኅበሮች በአንቀጽ ፬፻፸፱ የተመለከተውን ወንጀል ሲፈፅሙ ተካፋይ የሆነ ሰው፤ በቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

በዚሁ ማኅበር ወይም ቡድን መሪ፣ አደራጅ ወይም ዋነኛ አባል ላይ የሚወሰነው ቅጣት ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት እና ከአንድ ሺህ ብር የማያንስ መቀጮ ይሆናል::

## አንቀጽ ፬፻፹፬ የተከለከሉ ስብሰባዎች

፩ ማንም ሰው በሕዝብ ጎዳና ወይም በሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ላይ በሕግ በተከለከለ ማናቸውም ስብሰባ ላይ በፈቃዱ የተካፈለ እንደሆነ፤

ከሁለት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ የወንጀሉ መሪ፣ አዘጋጅ ወይም አዛዥ የሚቀጣው ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ነው::

፫ መሣሪያ በያዙ ሰዎች በተደረገ ሕገወጥ ስብሰባ አስቦ ተካፋይ የሆነ ማንም ሰው ከሦስት ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፬ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፫ በተመለከተው ሁኔታ ወንጀሉ ሲፈፀም፣ የወንጀሉ መሪ፣ አዘጋጅ ወይም አዛዥ የሆነ፣ ወይም መሳሪያ የያዘ ሰው፤ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፭ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሕግ የተከለከለ ስብሰባን ያደራጀ ወይም የመራ እንደሆነ፤ ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፹፭ በወሬ ሕዝብን ማሸበር

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ ለሕዝብ ደህንነት ወይም ለግለሰቦች ሕይወት፣ ጤና ወይም ንብረት አስጊ የሆነ አደጋ በተለይም የወረራ፣ የሰው ግድያ፣ የእሳት ቃጠሎ፣ የጥፋት ወይም የዘረፋ አደጋ እንደሚደርስ በማስፈራራት፤ ወይም

BACK



ለ/ ስለነዚሁ ሁኔታዎች ወይም በአጠቃላይ ስለሚደርስ ሁከት ወይም በቅርብ ስለሚደርስ ጥፋት ወይም የተፈጥሮ አደጋ የሀሰት ወሬ በመንዛት፤

አስቦ ሕዝብን ያሸበረ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ከፍተኛ ቅጣቶችን የሚወስኑ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሁኔታዎቹ በጣም ከባድ የሆነ ብጥብጥን ወይም ምስቅልቅልን ሊያመጡ የሚችሉ ወይም ያመጡ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

**<u>አንቀጽ ፬፻፹፮</u> <u>የሐሰት ወሬዎችን በማውራት ሕዝብን ማነሳሳት</u>**

ማንም ሰው በአገር ደህንነት ላይ ከሚፈጸሙት ወንጀሎች ውጭ በሆነ አኳኋን /አንቀጽ ፪፻፵፣ ፪፻፶፯/ሠ/፣ እና ፪፻፳፩(፩)/:-

ሀ/ በመንግሥት፣ በሕዝብ ባለሥልጣኖች ወይም በሥራቸው ላይ የሐሰት ወሬዎችን፣ ጥርጣሬዎችን፣ ወይም የሐሰት ሐሜታዎችን የሚፈጥር ወይም የሚነዛ ሰው፤ ከዚህም የተነሳ የሕዝብን አስተሳሰብ ያናወጠ፣ የቀሰቀሰ፣ ወይም ለማናወጥ የሚችል እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በማናቸውም ዓይነት ማሳጣት ወይም ሌላ ዘዴ ጥርጣሬን ያስፋፋ፣ጥላቻን ያነሳሳ ወይም የኃይል ድርጊት ወይም የፖለቲካ፣ የዘር ወይም የኃይማኖት ሁከት የቀሰቀሰ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ፣ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፹፯</u> <u>የማነሳሳት ጠባይ ያላቸው የሐሳብ መግለጫዎች</u>

ማንም ሰው:-

ሀ/ በማናቸውም የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ወይም ስብሰባ ላይ ሕገወጥ ለሆነ ድርጊት የሚያነሳሳ ወይም የዛቻ ጠባይ ያለው ንግግር መግለጫ ወይም ምስል ያዘጋጀ፣ ያስፋፋ፣ ያሰራጨ ወይም ያሰማ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ አግባብ ባለው ባለሥልጣን በሕግ የተሰጡ ትዕዛዞችን ወይም የወጡ ሕጎችን እና ደንቦችን ሕዝብ እንዲቃወም ለማድረግ በግልጽ ያነሳሳ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፹፰</u> <u>ሁከት</u>

፩ ማንም ሰው በሰው ወይም በንብረት ላይ የኀብረት የኃይል ድርጊት በተፈጸመበት ሕገወጥ ስብሰባ በገዛ ፈቃዱ ተካፋይ እንደሆነ፤

ከአንድ ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ የወንጀሉ አደራጅ፣ አነሳሽ ወይም መሪ ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ፤ ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፫ በሰው ወይም በንብረት ላይ በግሉ የኃይል ድርጊት የፈጸመ ማንም ሰው፤ የፈጸመው ወንጀል በተለየ የሕግ ድንጋጌ ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር፣ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፬፻፹፱ ልዩ አስተያየት የሚደረግላቸው ጉዳዮች

የኃይል ድርጊት ሳይፈጽሙ ወይም እንዲፈጸም ሳያነሳሱ ከተከለከለ ስብሰባ፣ የማነሳሳት ጠባይ ካለው የሃሳብ መግለጫ ሰልፍ፣ ሕገ ወጥ ከሆነ ጉባኤ ወይም ከሕብረት ዛቻ በገዛ ፈቃዳቸው ወይም በባለሥልጣን ትዕዛዝ ወጥተው የሄዱ ተካፋዮች አስፈላጊ ሲሆን ተወቅሰው፣ ወይም ተገስጸው /አንቀጽ ፻፳፪/ ከሌላ ቅጣት ነፃ እንዲሆኑ ለመወሰን ይቻላል::

## ምዕራፍ ሁለት

## በሕዝብ ሰላምና ተረጋግቶ መኖር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

## አንቀጽ ፬፻፺ ስብሰባን ወይም ጉባኤን ማወክ

፩ ማንም ሰው በሕግ የተፈቀደውን ማናቸውንም ስብሰባ ወይም ጉባኤ በቃል፣ በዛቻ፣ በኃይል ድርጊት፣ በጉልበት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሕግን በመቃረን የወረረ፣ ያወከ፣ የከለከለ ወይም የበታተነ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የሚመለከተው የባለሥልጣን፣ ኦፊሴላዊ የሆነ የቦርድ ወይም የኮሚሽን ወይም ኦፊሴላዊ የሆነ የምርጫ፣ የሐራጅ ሽያጭ ወይም ሕጋዊ የሆነ ማናቸውንም የሕዝብ ሥራ ለማከናወን የተደረገ ስብሰባን ወይም ጉባኤን እንደሆነ፤ ስብሰባው ወይም

BACK



ጉባኤው የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የሕግ አስፈጻሚነት ወይም የዳኝነት ጠባይ ያለው ቢሆንም፤ ቅጣቱ ከሦስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራትና ከአምስት መቶ ብር የማያንስ መቀጮ ይሆናል::

፫ ጥፋቱ የተፈፀመው በቡድን ወይም የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ መሣሪያ በመያዝ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፬፻፺፭ በራስ ጥፋት ከኃላፊነት ውጭ በመሆን የሚፈጸም የሁከት ተግባር</u>

በራሱ ጥፋት በመስከር ወይም በሌላ ሁኔታ ወደ ፍፁም ኢ-ኃላፊነት ራሱን ያስገባ ሰው ቢያንስ የአንድ ዓመት እሥራት የሚያስቀጣ ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ፤

እንደተፈፀመው ተግባር ከባድነትና እንደ አደገኛነቱ ማደግ ወይም ማነስ በመቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፺፮ የኃይማኖትን ሰላምና ስሜት መንካት</u>

ማንም ሰው አስቦ በአደባባይ:-

ሀ/ የተፈቀደውን ኃይማኖታዊ ሥርዓት፣ ሥነ በዓል ወይም ኃይማኖታዊ ተግባር እንዳይፈጸም የከለከለ፣ ያወከ፣ ወይም ያስተሐቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ለሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት የሚያገለግለውን ቦታ፣ ሥዕል ወይም ዕቃ ያረከሰ እንደሆነ፤

ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፺፫ የሙታንን ሰላምና ክብር መንካት</u>

ማንም ሰው:-

ሀ/ የሬሳን አጀብ ወይም የቀብር ሥነ ሥርዓት ያወከ ወይም ያረከሰ እንደሆነ፤

ለ/ የሞተ ሰው ያረፈበትን ቦታ የደፈረ፣ ያረከሰ፣ የመቃብሩን ሐውልት ወይም ምልክት ያፈረሰ፣ ወይም ያረከሰ ወይም የተቀበረውንም ሆነ ያልተቀበረውን አስከሬን ያረከሰ ወይም አካሉን የቆረጠ እንደሆነ፤

ሐ/ አስከሬንን በአደባባይ ያዋረደ ወይም የመታ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ ሬሳን ወይም ማናቸውንም የሬሳን አካል ክፍል ወይም ቅሪት የወሰደ፣ እንዲጠፉ ያደረገ ወይም የበታተነ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

<u>ርዕስ ሰባት</u>

<u>በሕዝብ፣ በመገናኛዎችና በማጓጓዣዎች ደህንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>በሕዝብ ፀጥታና ደህንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

<u>አንቀጽ ፬፻፺፬ የእሳት ቃጠሎ ማድረስ</u>

፩ ማንም ሰው በሰዎች ወይም በንብረት ላይ የጅምላ አደጋ ለማድረስ አስቦ የራሱን ወይም የሌላውን ሰው ሕንፃ ወይም ማናቸውም ዓይነት ግዙፍ ሥራን፣ ሰብሎችን፣ የግብርና ምርቶችን፣ ደኖችን፣ ዛፎችን፣

BACK



ወይም ማናቸውንም ሌሎች ዕቃዎችን በእሳት የለኮሰ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ ከፍ ያለ አደጋን ያስከተለ ወይም በሰዎች ወይም በንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት የተስፋፋ እንደሆነ፤ በተለይም የተጎዱት የሕዝብ ሕንፃዎች፣ የሕዝብ አገልግሎት ሕንፃዎች፣ ነዎሪዎች ያሉባቸው ወይም ለመኖሪያ የሚያገለግሉ ቤቶች፣ የምግብ፣ የሚቀጣጠል ነገር ወይም የፈንጂ መጋዘኖች፣ ጫካዎች፣ ማዕድኖች፣ የነዳጅ ዘይት ጉድጓዶች ወይም የነዳጅ ማጣሪያዎች፣ መርከቦች፣ አውሮፕላኖች፣ ወይም በተለይ ለአደጋ ምቹ የሆኑ ማናቸውም ሌሎች ዕቃዎች በሚሆኑበት ጊዜ፣

ቅጣቱ ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

## አንቀጽ ፬፻፺፭ የተፈጥሮ አደጋዎችን ማድረስ

ማንም ሰው በሰዎች ወይም በንብረት ላይ አደጋ ለማድረስ አስቦ የውሃ ማጥለቅለቅ ወይም ማስጠም፣ የመሬት መናድ፣ የመፍረስ ወይም ይህን የመሳሰለ ማናቸውም ሌላ አደጋ እንዲደርስ ያደረገ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፬፻፺፬ በተደነገገው መሠረት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፬፻፺፮ ግዙፍ ሥራዎችን ወይም የመጠበቂያ ሥራዎችን መጉዳት

ማንም ሰው በሰዎች ወይም በንብረት ላይ አደጋ ለማድረስ አስቦ ኤሌክትሪክን፣ ወይም ውሃን የሚመለከቱ ህንፃዎችን ወይም የተፈጥሮ ኃይልን ለመከላከል የተሰሩ ስራዎችን

በተለይም ቧንቧዎችን፣ ቦዮችን፣ ማጠራቀሚያዎችን፣ የውሃ ማገጃዎችን፣ መልቀቂያዎችን፣ ወይም ማዕበል ማገጃዎችን ያበላሸ ወይም ያፈረሰ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፬፻፺፩ በተደነገገው መሠረት ይቀጣል።

## <u>አንቀጽ ፬፻፺፪ ማፈንዳት</u>

ማንም ሰው በሰዎች ወይም በንብረት ላይ አደጋ ለማድረስ አስቦ ነዳጅ፣ ባሩድ፣ ዲናሚት ወይም ይህንን የመሳሰለ ማናቸውንም ሌላ አደገኛ ነገር እንዲፈነዳ ያደረገ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፬፻፺፩ በተደነገገው መሠረት ይቀጣል።

## <u>አንቀጽ ፬፻፺፫ በቸልተኛነት የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

ማንም ሰው ከዚህ በላይ ከአንቀጽ ፬፻፺፩ እስከ ፬፻፺፪ ከተመለከቱት ውስጥ ማናቸውንም ወንጀል በቸልተኛነት የፈጸመ እንደሆነ፤

እንደወንጀሉ ከባድነት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

ጥፋተኛው ሰዎችን ወይም ንብረትን ከባድ ለሆነ አደጋ አጋልጦ የተገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ቀላል እሥራት መወሰን አለበት።

## <u>አንቀጽ ፬፻፺፬ በሚፈነዱ፣ በሚቀጣጠሉ ወይም በሚመርዙ ነገሮች አደጋ ማድረስ</u>

፩ ማንም ሰው በሕዝብ ደህንነት ላይ አደጋን ለማድረስ በማቀድ በሚፈነዱ ወይም በቀላሉ በሚቀጣጠሉ ነገሮች ወይም በሚመርዙ ጋዞች የሰውን ሕይወት፣ ጤና ወይም አካል ወይም የሌላውን ሰው ንብረት እያወቀ ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

ጥፋተኛው ለአደጋ ያጋለጠው ንብረትን ብቻ ሲሆንና ያደረሰውም ጉዳት ቀላል ሲሆን ቅጣቱ ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል::

፪ ወንጀሉ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣው ድርጊቱ በሰው ሕይወት ወይም አካል ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም በኢኮኖሚ ላይ ከባድ ጉዳት በሚያደርስ ወይም ሊያደርስ በሚችል ድርጊት በአደባባይ፣ በሕዝብ መገልገያ ቦታ፣ በመንግሥት ተቋም፣ በአገልግሎት መስጫ ተቋም ወይም ሥርዓት ላይ ጉዳት ለማድረስ ታስቦ በተጠቀሱት ተቋማት፣ አገልግሎቶች ወይም ሥርዓቶች ላይ የባዮሎጂካል ኤጀንቶችን፣ መርዝነት ያላቸው ነገሮችን በማፍሰስ፣ በመልቀቅ፣ በማሰራጨት ወይም በሰው ሕይወት ወይም አካል ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ ኃይል ያላቸውን ወይም ለዚሁ ተግባር የተሰሩ ተቀጣጣይና ፈንጂዎችን በማስቀመጥ በመወርወር፣ በማፈንዳት የተፈጸመ በሆነ ጊዜ ይሆናል::

፫ ማንም ሰው በሕዝብ ደህንነት ላይ አደጋን ለማድረስ በማቀድ ሳይሆን ከዚህ በላይ በተገለፀው ሁኔታ የሌላውን ሰው ሕይወት፣ አካል፣ ጤንነት ወይም ንብረት አስቦ ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፬ ማንም ሰው በቸልተኛነት በንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለፀው ሁኔታ የሌላውን ሰው ሕይወት፣ አካል፣ ጤንነት ወይም ንብረት ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፭ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም ንዑስ አንቀጽ (፫) የተፈፀመው ወንጀል ቀላል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ

ፍርድ ቤቱ በቀላል እሥራት ቅጣት ምትክ የግዴታ ሥራን ወይም መቀጮን ለመወሰን ይችላል::

<u>አንቀጽ ፭፻ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ ወይም የሚመርዙ ነገሮችን መሥራት፣ መያዝ፣ መደበቅ፣ ወይም ማጓጓዝ</u>

፩ ማንም ሰው ሕገ ወጥ ለሆነ ዓላማ መታቀዳቸውን እያወቀ የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ ወይም የሚመርዙ ነገሮችን የሠራ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ሌላው ሰው ሕገ ወጥ ለሆነ ዓላማ ሊጠቀምባቸው መሆኑን እያወቀ በንዑስ አንቀጽ(፩) የተመለከቱትን ነገሮች ሠርቶ ለማውጣት የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ወይም መመሪያዎችን ለዚሁ ሰው የሰጠ ማንም ሰው፤

ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፫ ማንኛውም ሰው ሕገ ወጥ ለሆነ ዓላማ መታቀዳቸውን እያወቀ የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ፣ ወይም የሚመርዙ ነገሮችን ወይም እነዚሁኑ ለመሥራት የሚያለግሉ ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ አገር ያስመጣ፣ በእጁ ያስገባ፣ የገዛ፣ ወይም ለሌላ አሳልፎ የሰጠ፣ ከሌላ የተቀበለ፣ ያከማቸ፣ የደበቀ ወይም ያጓጓዘ እንደሆነ፤

ድርጊቱን የፈፀመው በዋጋ ወይም ያለ ዋጋ ቢሆንም፣ ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት፣

ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፩ የሕንፃ ሥራ ደንቦችን መጣስ</u>

፩ ማንም ሰው ማናቸውንም ዓይነት የሕንፃ ሥራ ወይም የሕንፃ ማፍረስ ሥራ ሲቆጣጠር፣ ሲመራ፣ ወይም ሲፈጽም በሕግ የተደነገገውን ወይም በሕንፃ ሥራ ሙያ ወይም ልምድ የሚሠራባቸውን የጥንቃቄ ደንቦችን አስቦ በመጣስ የሕዝብን ደህንነት ወይም የሰዎችን ሕይወት፣ ጤንነት ወይም አካል፣ ወይም የሌላውን ሰው ንብረት አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ፤
ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፫፻፪ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችን ወይም ዕቃዎችን ማንሣት ወይም አለማደራጀት</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ በማናቸውም ድርጅት ወይም ፋብሪካ፣ የማዕድን ቦታ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ የሥራ ቦታ ውስጥ አደጋ እንዳይደርስ ለመከላከል የተቀመጠውን መሣሪያ ያጠፋ፣ ያነሳ፣ ያበላሸ፣ ጠቃሚነቱን ያስቀረ፣ ወይም ከሥራ አገልግሎት ውጭ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሕግ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን ትዕዛዝ መሠረት ለደህንነት ጥበቃ የሚያገለግል የሥራ መሣሪያ የማዘጋጀት ግዴታውን በመተው

BACK



የሌላውን ሰው ደህንነት በአደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ፣ በቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

**አንቀጽ ፭፻፫ በሕዝብ ላይ የሚደርስ ከባድ አደጋን አለማስታወቅ**

ማንም ሰው በራሱ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሳያመጣ ማስታወቅ ወይም የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ እየቻለ ቃጠሎ፣ ፍንዳታ፣ የውሃ ማጥለቅለቅ ወይም የተፈጥሮ የሆነም ሆነ ያልሆነ አደጋ በሰው ሕይወት፣ ጤንነት ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል አደጋን ለባለሥልጣን ወይም የጥበቃ ኃላፊነት ላላቸው አካላት ያላስታወቀ ወይም በማናቸውም ሁኔታ አደጋው እንዳይደርስ ለመከላከል በጊዜው አስፈላጊዎቹን የጥንቃቄ እርምጃዎች ያላደረገ እንደሆነ፣

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

**አንቀጽ ፭፻፬ የተጠበቁ ሁኔታዎች**

የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች ለአገር መከላከያና ለወታደራዊ አገልግሎት የቆሙ የስራ ቦታዎችንና ሥራዎችን መጉዳትን ወይም ማበላሸትን፣ በተለይም ማፍረስን ወይም ማሰናከልን፣ በጉዳት ላይ ማዋልን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን /አንቀጽ ፪፻፵፯/ሀ/፣ ፫፻፳፣ ፫፻፱ እና ፫፻፸፯/ሀ// ተፈፃሚነት አያስቀሩም።

## ምዕራፍ ሁለት

## በማጓጓዣዎችና በመገናኛዎች ነፃነትና ፀጥታ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፭፻፭ ለሕዝብ ጥቅም በተቋቋሙ ግዙፍ ሥራዎችና አገልግሎቶች ላይ ጉዳት ማድረስ**

፩ ማንም ሰው አስበ፡-

BACK



ሀ/ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡትን ወይም ለሕዝብ ጥቅም ሥራ ላይ የዋሉትን የየብስ፣ የውሃ፣ የባህር፣ ወይም የአየር ማመላለሻዎች ወይም መገናኛዎች፣ እነዚህኑ ለማደስ፣ ለመጠገን፣ እንደገና ለመሥራት ወይም አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የሚጠቅሙ የግንባታ ሥራዎችን ጭምር፤ ወይም

ለ/ ለፖስታ፣ ለቴሌግራፍ፣ ለስልክ ግንኙነት ወይም ለቴሌኮሙኒኬሽን በጠቅላላው ወይም የውሃ፣ የመብራት፣ የጋዝ፣ የኃይል ወይም የሙቀት አገልግሎት ለሕዝብ ለማቅረብ ወይም ለማከፋፈል የተቋቋሙት ተቋማት ወይም አገልግሎቶችን፤

በመደበኛ አሠራር የከለከለ፣ ያወከ፣ ወይም ያሰናከለ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራትና በመቀጮ፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በሕግ ወይም በውል ግዴታ ባለበት ሰው እንደሆነ፤ በተለይም ሥራው ወይም ግዴታዎቹ የተቋረጡት ከአቅም በላይ ባልሆነ ኃይል ወይም በሕግ ወይም በውል ከተፈቀዱት ሁኔታዎች ውጭ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከሦስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራትና መቀጮ፤ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል።

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም

BACK



ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፭፻፲፯</u> <u>መገናኛዎችንና ማጓጓዣዎችን በከባድ አደጋ ላይ መጣልና ማበላሸት</u>

፩ ማንም ሰው በመንገድ፣ በባቡር ሐዲድ፣ በውሃ ወይም በአየር ላይ የሚደረግ የሕዝብ ወይም የዕቃ ማጓጓዣ አገልግሎትን ለግጭት፣ ከሐዲድ ለማስወጣት፣ ለስጥመት፣ ወይም በሰዎች ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ለሚያደርስ ለማናቸውም ሌላ አደጋ ለማጋለጥ በተለይም:-

ሀ/ ድልድይን፣ ግድብን፣ የማዕበል ማገጃን፣ የተቋቋመ ግዙፍ ሥራን፣ ወይም የመቆጣጠሪያ፣ የመከላከያ፣ የምልክት ማሳያ፣ ወይም የማመላለሻ መሣሪያን በማበላሸት፣ ከቦታው በማዛወር፣ በማፍረስ ወይም እንዳያገለግል በማድረግ፤

ለ/ በመንገድ፣ በሐዲድ፣ በትልቅ ቦይ/ካናል/ ወይም በማናቸውም ሌላ መገናኛ መንገድ ላይ አደጋን ለማምጣት የሚችለውን ክንውን ወይም ሥራ በማካሄድ ወይም መሰናክልን በማድረግ፤

ሐ/ የሐሰት ትዕዛዝን፣ ምልክትን ወይም ማመላከቻን በመስጠት፤ ወይም

መ/ ግዴታን፣ ደንብን፣ ወይም ለጥንቃቄ አስፈላጊ የሆኑትን ድንጋጌዎች በማናቸውም አኳኋን በመጣስ፤

የሕዝብ ማመላለሻን አስቦ እንዳይሠራ ያደረገ፣ ያሰናከለ፣ ወይም አደጋ ሊደርስበት በሚችል ሁኔታ እንዲገኝ ያደረገ እንደሆነ፤

BACK



ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል በቸልተኛነት ተፈፅሞ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል::

፫ የጽኑ እሥራት ቅጣቱ እስከ አስር ዓመት የሚደርሰው ጥፋተኛው እያወቀ:-

ሀ/ ያለበትን የውል ወይም የሞያ ግዴታ በመጣስ ድርጊቱን የፈፀመ
እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የሌሎችን ሕይወት፣ አካል ወይም ጤንነት አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ ወይም በንብረት ላይ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ፤ ነው::

፬ ወንጀሉ በቸልተኛነት የተፈፀመው የሙያ ተግባርን ወይም የውል ግዴታን በመጣስ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል::

፭ የወንጀል ድርጊቱ ለበረራ ወይም ለባህር ላይ ጉዞ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችን ወይም መሣሪያዎችን በማውደም፣ በማበላሸት ወይም አሰራራቸውን ለማሰናከል ጣልቃ በመግባት የተፈጸመ ሆኖ በበረራ ላይ የሚገኝ አውሮኘላንን ወይም በጉዞ ላይ የሚገኝ መርከብን ለአደጋ የሚያጋልጥ የሆነ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

BACK



፪ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፯ በኮንቲኔንታል ሸልፍ የሚገኝን ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣ አይሮፕላንን ወይም መርከብን ያለአግባብ መያዝ</u>

፩ ማንም ሰው በኃይል፣ በዛቻ ወይም በማናቸውም ሌላ የማስፈራሪያ ዘዴ፣ በተንኮል ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ በኮንቲኔንታል ሸልፍ የሚገኝ ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣ በአገልግሎት ወይም በበረራ ላይ ያለ ወይም በማረፊያው የቆመ አይሮፕላንን፣ በአገልግሎት ወይም በጉዞ ላይ ያለ ወይም በወደቡ የቆመ መርከብን አስቦ የያዘ ወይም በቁጥጥር ሥር ያዋለ እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ለዚህና ለሚቀጥሉት አራት አንቀጾች ዓላማ፣

ሀ/ "በአገልግሎት ላይ ያለ አውሮፕላን" ማለት የአየር ትራንስፖርት ወይም የአውሮፕላን ሠራተኞች ለተወሰነ በረራ ከሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት ጀምሮ አውሮፕላኑ ካረፈ በኋላ እስከ ሃያ አራት ሰዓት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ነው።

ለ/ "በበረራ ላይ ያለ አውሮፕላን" ማለት የአውሮፕላኑ የውጭ በሮች ከተዘጉበት ጊዜ ጀምሮ በሩ እስከሚከፈት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ሲሆን አይሮፕላኑ ተገዶ ያረፈ እንደሆነ ይህ ጊዜ አውሮፕላኑን፣ ሰዎችንና ንብረቱን በሙሉ ለማስለቀቅ የሚወስደውን ጊዜ ይጨምራል።

<u>አንቀጽ ፭፻፰ በኮንቲኔንታል ሽልፍ የሚገኝ ቋሚና የተተከለ ሥፍራን፣ አይሮፕላንን ወይም መርከብን አስጊ ሁኔታ ላይ መጣል</u>

፩ ማንም ሰው በኮንቲኔንታል ሽልፍ በሚገኝ ቋሚና የተተከለ ስፍራ፣ በአገልግሎት ወይም በበረራ ላይ ባለ ወይም በማረፊያ በቆመ አይሮፕላን፣ በአገልግሎት ወይም በጉዞ ላይ ባለ ወይም በወደብ በቆመ መርከብ ውስጥ በሚገኝ ሰው ላይ አስቦ በሕገወጥ መንገድ የኃይል ድርጊት የፈጸመ እንደሆነና፤ ድርጊቱ የሥፍራውን የአውሮፕላኑን ወይም የመርከቡን ደህንነት አደጋ ላይ ለመጣል የሚችል እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ማንም ሰው በኮንቲኔንታል ሽልፍ በሚገኝ ቋሚና የተተከለ ሥፍራ በአገልግሎት ወይም በበረራ ላይ ባለ ወይም በማረፊያው የቆመ አይሮፕላን፣ በአገልግሎት ወይም በጉዞ ላይ ባለ ወይም በወደብ በቆመ መርከብ ውስጥ በሚገኝ ሰው ላይ በቸልተኛነት የኃይል ድርጊት የፈፀመ እንደሆነና፣ ድርጊቱም የሥፍራውን፣ የአውሮፕላኑን ወይም የመርከቡን ደህንነት አደጋ ላይ ለመጣል የሚችል እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፭፻፱ በኮንቲኔንታል ሽልፍ በሚገኝ ቋሚና በተተከለ ሥፍራ፣ አይሮፕላን ወይም መርከብ ላይ አደጋ ማድረስ</u>

፩ ማንም ሰው በኮንቲኔንታል ሽልፍ የሚገኝ ቋሚና የተተከለ ሥፍራን ወይም በአገልግሎት ወይም በበረራ

ላይ ያለ ወይም በማረፊያው የሚገኝ አውሮፕላንን ወይም በአገልግሎት ወይም በጉዞ ላይ ያለ ወይም በወደብ ውስጥ የሚገኝ መርከብን፣ አስቦ በሕገወጥ መንገድ ያወደመ እንደሆነ፣ ወይም ከነዚህ ነገሮች በአንዱ ላይ በአደረሰው ጉዳት ለአገልግሎት፣ ለበረራ ወይም ለጉዞ ብቁ እንዳይሆን ያደረገ እንደሆነ ወይም የአገልግሎት፣ የበረራ ወይም የጉዞ ደህንነቱ ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው በኮንቲኔንታል ሸልፍ የሚገኝ ቋሚና የተተከለ ሥፍራን ወይም በአገልግሎት ወይም በበረራ ላይ ያለ ወይም በማረፊያው የሚገኝ አውሮፕላንን ወይም በአገልግሎት ወይም በጉዞ ላይ ያለ ወይም በወደብ ውስጥ የሚገኝ መርከብን፣ በቸልተኛነት ያወደመ እንደሆነ፣ ወይም ከነዚህ ነገሮች በአንዱ ላይ በቸልተኛነተ ባደረሰው ጉዳት አገልግሎቱ፣ በረራው ወይም ለጉዞ ብቁ እንዳይሆን ያደረገ እንደሆነ ወይም የአገልግሎት፣ የበረራ ወይም የጉዞ ደህንነቱ ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ያስቀጣል::

## አንቀጽ ፭፻፲ ምልክቶችንና የእርዳታ ጥሪዎችን ያለአግባብ ማድረግ

፩ ማንም ሰው በተንኮል ወይም በቂ ምክንያት ሳይኖረው በመገናኛዎች ላይ ሁከት እንዲነሳ ወይም መገናኛ እንዲቋረጥ በማሰብ የአደጋ ምልክትን ወይም

BACK



የተለመደ ወይም በዓለም አቀፍ ስምምነት የታወቀ የእርዳታ ጥያቄን ወይም መልእክትን ያስተላለፈ፣ በደህንነት ወይም በማስጠንቀቂያ መሣሪያ በመጠቀም የማስጠንቀቂያ መልዕክትን ያስተላለፈ ወይም በቴሌኮሙኒኬሽን የአደጋ ማስጠንቀቂያ ያለአግባብ የሠራበት እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ በበረራ ላይ ያለ አውሮኘላንን ወይም በጉዞ ላይ ያለ መርከብን ለአደጋ ለማጋለጥ ሀሰተኛ ማስረጃን በማስተላለፍ የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፫ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኛነት በሆነ ጊዜ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

## አንቀጽ ፭፻፲፩ አደገኛ የሆኑ ነገሮችን ወይም መሣሪያዎችን በሕገወጥ መንገድ ማስቀመጥ ወይም መጫን

፩ ማንም ሰው አደጋ ለማድረስ በማሰብ በየብስ፣ በአየር፣ ወይም በውሃ የሕዝብ ማጓጓዣዎች ላይ የሚቀጣጠሉ፣ የሚፈነዱ፣ ወይም በቀጥታ የሚመርዙ፣ ወይም በመነካካት፣ በመብነን ወይም በመበተንና በመትነን የሚያበላሹ ወይም የሚጎዱ ነገሮችን ወይም መሣሪያዎችን ያስቀመጠ ወይም እንዲቀመጡ ያደረገ፣ የጫነ ወይም ያስጫነ፣ ይዞ የተሣፈረ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው አስቦ:-

(ሀ) በኮንቲኔታል ሽልፍ ቋሚ በሆነና በተተከለ ሥፍራ ደህንነት ላይ አደጋ ለመጣል፤

(ለ) በአገልግሎት ላይ የሚገኝ አውሮኘላንን ለማውደም ወይም ለበረራ ብቁ እንዳይሆን ወይም የበረራ ደህንነቱ ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ፤ ወይም

(ሐ) መርከብን ለማውደም ወይም በጭነቱ ወይም በመርከቡ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም የጉዞውን ደህንነት ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ፤

የሚችል ማናቸውንም መሣሪያ ወይም ዕቃ በማናቸውም ዘዴ በአውሮኘላኑ ወይም በመርከቡ ወይም በኮንቲኔንታል ሽልፍ በሚገኝ ቋሚና የተተከለ ሥፍራ ላይ ያስቀመጠ ወይም እንዲቀመጥ ያስደረገ እንደሆነ፤
ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፫ ማንኛውም ሰው አደጋ ለመጣል ወይም ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ሳይሆን እያወቀ ስለትራፊክ ደህንነት አጠባበቅ የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመጣስ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ድርጊቶች አንዱን የፈፀመ እንደሆነ፤

ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፬ ማንኛውም ሰው በየብስ፣ በአየር ወይም በውሃ የሕዝብ ማጓጓዣዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለበት ሆኖ ሳለ፤ የሥራ

ግዴታውን በቸልተኛነት ሳይወጣ ቀርቶ በነዚሁ ማጓጓዣዎች ወይም በተቋሞቻቸው ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮች ወይም መሣሪያዎች ተቀምጠው ወይም ተጭነው የተገኙ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፫ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ድርጊት በቸልተኝነት ተፈጽሞ ከሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፭፻፲፪ ከባድ ሁኔታ</u>

፩ ከአንቀጽ ፭፻፭ እስከ ፭፻፲፩ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱ ታስቦ ሲፈፀም በሰው ሕይወት፣ አካል ወይም ጤንነት ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ፤
ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ወይም በሞት ያስቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፭፻፲፫ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት</u>

ማናቸውም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፴፬ በተደነገገው መሠረት በዚህ ምዕራፍ ከተመለከቱት ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ፤ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል::

## ርዕስ ስምንት
## በጤና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
## ምዕራፍ አንድ
## የጥበቃ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን መጣስ
## ክፍል አንድ
## በሽታን በማሰራጨትና አካባቢን በመበከል የሚደረጉ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፭፻፲፬ የሰውን በሽታ ማሰራጨት**

፩ ማንም ሰው አስቦ በሰው ላይ ተላላፊ በሽታ ያሰራጨ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤

ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው:-

ሀ/ በጥላቻ፣ በቂመኝነት፣ በክፋት ወይም በወራዳነት መንፈስ በሌላ ሰው ላይ ከባድ ጉዳትን ወይም ሞትን የሚያስከትል በሽታ ያሰራጨ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በዚህ አንቀጽ በፊደል (ሀ) የተመለከተው አሳብ ባይኖርም በሌላ ሰው ላይ ከባድ ጉዳትን ወይም ሞትን የሚያስከትል በሽታ ያሰራጨ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ወረርሽኝ /ኤፒደሚክ/ የሆነ በሽታ ያስተላለፈ እንደሆነ፤

ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት ይቀጣል::

፫ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ቀላል እስራት ወይም መቀጮ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፲፭ የእንስሳት በሽታን ማሰራጨት</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ በቤት እንስሳት፣ በዶሮዎችና ዶሮን በመሳሰሉ ለማዳ አዕዋፋት፣ በሚታደኑ የዱር እንስሳት፣ በዓሣ፣ በንቦች ወይም በሕግ በተጠበቀ የዱር እንስሳት መካከል በሽታን ያሰራጨ እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ጥፋተኛው፡-

ሀ/ ወንጀሉን የፈፀመው በክፋት እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ አስቦ ከፍ ያለ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣

ቅጣቱ ከሦስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል።

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፲፮ የሰብልን ወይም የደንን ተባይ ማራባት</u>

ማንም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኛነት ለእርሻ ሰብል ወይም ለደን ጎጂ የሆነ ተባይ ወይም ረቂቅ የሆነ ሕዋስ /ጀርም/ ያራባ እንደሆነ፣

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፲፭ በተደነገገው ቅጣት መሠረት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፭፻፲፯ ውሃን መበከል</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ ለሰው ወይም ለእንስሳት የሚያገለግለውን የመጠጥ ውሃ ለጤና ጎጂ በሆኑ ነገሮች የበከለ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታና እንደ ጉዳቱ መጠን በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም

BACK



ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው የውሃ ጉድጓዶችን፣ ማጠራቀሚያዎችን፣ ምንጮችን፣ የውሃ ኩሬዎችን፣ ወንዞችን፣ ወይም ሐይቆችን አስቦ በመመረዝ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ቀለል ያለ ሲሆን መቀጮ ይሆናል::

## አንቀጽ ፭፻፲፰ ግጦሽን መበከል

፩ ማንም ሰው የእንስሳትን ሕይወት ወይም ጤና አደጋ ላይ ለመጣል አስቦ መርዛም ወይም ጎጂ በሆኑ ነገሮች ግጦሽን ወይም መስኮችን የበከለ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል::

## አንቀጽ ፭፻፲፱ አካባቢን መበከል

፩ ማንኛውም ሰው አግባብነት ያለውን ሕግ በመተላለፍ በካይ ነገሮችን ወደ አካባቢው የለቀቀ እንደሆነ፤

ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ብክለቱ በሰዎች ሕይወት ወይም ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ጥፋተኛው በዚህ ድርጊት ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ጥሶ እንደሆነ፤ ስለ ወንጀሎች መደራረብ የተጻፉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ::

**<u>አንቀጽ ፭፻፳</u>** **<u>አደገኛ የሆነ ቆሻሻንና ሌላ ቁስን በአግባቡ ለመያዝ</u>**

ማንም ሰው:-

ሀ/ አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት ያልያዘ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን በሚመለከት መለጠፍ ያለበትን ዝርዝር ያልለጠፈ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ያልተፈቀደ የአደገኛ ቆሻሻ ወይም የአደገኛ ነገር ዝውውር ያካሄደ እንደሆነ፤

ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል::

**<u>አንቀጽ ፭፻፳፩</u>** **<u>የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን የሚፃረሩ ድርጊቶችን መፈፀም</u>**

ማንም ሰው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲደረግበት በሕግ የታዘዘውን ማናቸውንም ፕሮጀክት ከተገቢው አካል

BACK



ፈቃድ ማያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም ይህንኑ በሚመለከት ሐሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ፣

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፭፻፳፪ ጤናን ለመጠበቅና ለመንከባከብ በሕግ የተደነገጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች መጣስ

፩ ማንም ሰው ተላላፊ የሰው በሽታን ለመከላከል፣ ለመግታት ወይም ለማቆም በሕግ የተደነገጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች አስቦ የጣሰ እንደሆነ፣

ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከሦስት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ የእንስሳት በሽታን ወይም የሰብል ወይም የደን ተባይን ወይም የረቂቅ ሕዋስ ሥርጭትን ወይም የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል፣ ለመግታት ወይም ለማቆም የተደነገገ የጥንቃቄ እርምጃ ታስቦ የተጣሰ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል::

፬ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ድርጊት የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሦስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

## አንቀጽ ፭፻፳፫ ችግር ወይም ረሀብ እንዲደርስ ማድረግ

፩ ማንም ሰው አስቦ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በተለይም በመደበቅ፣ ያለአግባብ በማከማቸት፣ በማጥፋት ወይም ለሰው ወይም ለቤት እንስሳት ሕይወት ወይም ጤና አስፈላጊ የሆኑትን የእህልን፣

የምግብን፣ የቀለብን፣ የመድሃኒትን፣ ወይም አስፈላጊ የሆኑትን ሌሎች ነገሮች ማመላለስን ወይም ማከፋፈልን በመከልከል በአገር ውስጥ ከባድ መከራ፣ እጦት፣ ረሀብ፣ ተላላፊ በሽታ፣ የእንስሳት በሽታ ወይም ችግር እንዲደርስ ያደረገ እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ማንም ሰው የዚህ ዓይነቱ ችግር በደረሰ ጊዜ ችግሩን ለመከላከል፣ ለመግታት ወይም ለማስወገድ የሚያስፈልገውን ምግብ፣ መድሃኒት ወይም ማናቸውንም ሌሎች ዕቃዎች ለማቅረብ በአቅራቢነት፣ በአገናኝነት፣ ከዋና አቅራቢ ጋር ተዋዋይ በመሆን፣ በአመላላሽነት፣ በወኪልነት፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ያለበትን ግዴታዎች ወይም ኃላፊነት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳያጋጥመው ያልፈጸመ ወይም ያላከናወነ እንደሆነ፤

በንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ይቀጣል።

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሃያ ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

አንቀጽ ፭፻፹፬ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት

በዚህ ክፍል ከተመለከቱት ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ የሆነ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺ በተደነገገው መሠረት ይቀጣል።

BACK



## ክፍል ሁለት

## በሰውና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን በማምረትና በማሰራጨት የሚደረጉ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፭፻፳፭ መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት፣ መሥራት፣ ማዘዋወር ወይም መጠቀም

፩ ማንም ሰው ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው፡-

ሀ/ መርዛማ ነገሮችን ወይም ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶችን ወይም እጾችን ያበቀለ፣ ያመረተ፣ የሠራ፣ የለዋወጠ ወይም የፈበረከ፤

ለ/ ከላይ በፊደል (ሀ) ከተዘረዘሩት ነገሮች አንዱን ይዞ የተገኘ፤ ወደ አገር ያስገባ፣ ወደ ውጭ አገር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ ያከማቸ፣ የደለለ፣ የገዛ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ያሰራጨ፣ ያዘዋወረ፣ አሳልፎ የሰጠ ወይም ለሌላ ያስገኘ፤

ሐ/ ከዚህ በላይ በፊደል (ሀ) ከተዘረዘሩት ነገሮች አንዱን ለማምረት፣ ለማቀነባበር ወይም ለመፈብረክ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን የሠራ፣ ይዞ የተገኘ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደ ውጭ አገር የላከ፣ ወይም

መ/ በፊደል (ሀ) ለተገለጹት ነገሮች መሥሪያነት፣ ማቀነባበሪያነት፣ ማምረ ቻነት፣ መሸጫነት ወይም ማከፋፈያነት ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሆነበትን ቤቱን፣ ግቢውን ወይም ቦታውን የሰጠ፣ ያከራየ ወይም የፈቀደ፤

BACK



እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራትና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማያንስ ጽኑ እሥራትና ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ የሚሆነው:-

ሀ/ ወንጀሉ የተፈፀመው ለዚሁ ንግድ ወይም በዓለም አቀፍም ሆነ በአገር ደረጃ ወንጀል ለመፈጸም በተደራጀ የቡድን ወይም የማኅበር አባል በሆነ ወይም ይህንኑ ሕገወጥ ድርጊት ሙያው አድርጎ በያዘ ሰው እንደሆነ፤

ለ/ ጥፋተኛው የተከለከለውን ሕገ ወጥ ነገር ወይም ለዚህ ዓይነቱ ነገር መጠቀሚያ ቦታ እያወቀ የሰጠው ወይም የፈቀደው በአፍቅሮ ንዋይ፣ በወራዳነት ወይም አግባብ በሌለው ሌላ ዓላማ እንደሆነ፤ ወይም ተጠቃሚው ሕፃን፣ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት ወይም አእምሮው ያልተስተካከለ ወይም የእጽ ሱስ ያለበት እንደሆነ፤

ሐ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈፀመው ሕፃናትን ወይም አእምሮው ያልተስተካከለ ሰውን ለወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም መጠቀሚያ በማድረግ እንደሆነ፤

መ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በማረሚያ ቤት፣ በትምህርት ቤት ወይም በሌላ ማኅበራዊ አገልግሎት ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ ሕፃናት ወይም ወጣት ተማሪዎች ለትምህርት፣ ለስፖርት ወይም ለሌሎች ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች በሚጠቀሙበት ቦታ እንደሆነ፤ ወይም

BACK


ሠ/ ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም በፈፀመው ተመሳሳይ ወንጀል ምክንያት የጥፋተኛነት ውሣኔ ተላልፎበት የነበረ እንደሆነ፤

ነው::

፫ ማንም ሰው መርዛማ ነገሮች ወይም ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶች ወይም እጾች የተገኙት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) ከተዘረዘሩት የወንጀል ተግባሮች በአንዱ አማካይነት መሆኑን ወይም ከተዘረዘሩት የወንጀል ተግባሮች አንዱን ለመፈጸም የታቀዱ መሆኑን እያወቀ እነዚህን ነገሮች ይዞ የተገኘ፣ ያጓጓዘ፣ ያከማቸ ወይም አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራትና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፬ ማንም ሰው:-

ሀ/ ራሱ ወይም ሌላ ሰው በግል እንዲጠቀምበት በማሰብ፣ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተገለጹት ነገሮች አንዱን ያበቀለ፣ የገዛ፣ የተቀበለ፣ የሠራ፣ ይዞ የተገኘ፣ የሸጠ፣ የሰጠ፤ ወይም

ለ/ ከእነዚህ ነገሮች በአንዱ ያለሐኪም ፈቃድ ወይም በማናቸውም ሌላ ህገወጥ መንገድ የተጠቀመ ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ያደረገ፤

እንደሆነ፤ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከሃምሣ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፭ ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ ነገሮችን ለሕገወጥ ዓላማ ለማዋል በማሰብ የሕክምና ባለሙያን በማጭበርበር

የመድሃኒት ማዘዣ እንዲሰጠው ያደረገ ወይም በሕጋዊም ሆነ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ያገኘውን ማዘዣ ላልተፈቀደለት ሦስተኛ ወገን ያስተላለፈ ሰው፤ ወይም የናርኮቲክ ወይም የሳይኮትሮፒክ ነገሮች ማዘዣ አስቦ በሕገወጥ መንገድ የፃፈ የህክምና ባለሙያ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

፫ በዚህ ሕግ ለመንግሥት ገቢ ሊሆን ስለሚገባው ሀብት /አንቀጽ ፻፵/ እና በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ስለማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት /አንቀጽ ፮፻፹፬/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው።

<u>አንቀጽ ፭፻፳፫</u> <u>ዶፒንግ</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ በተፈጥሮና በስልጠና የተገኘው የአካል ብቃት በጊዜያዊ መልክ በይበልጥ እንዲጨምር በማድረግ በእስፖርት ውድድር ጊዜ አካላዊና ሥነ ልቦናዊ የበላይነት ለማግኘት የሚረዱ በሕግ የተከለከሉና ጉጂ የሆኑ ሰው ሠራሽ ነገሮችን ያመረተ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ የሸጠ፣ በባለሙያነት ያዘዘ፣ ያከፋፈለ፤ ወይም

ለ/ በፊደል (ሀ) በተመለከቱት ነገሮች በሕገወጥ መንገድ የተጠቀመ ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ያደረገ፤

እንደሆነ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ወይም ድርጊቱ ከባድ ጉዳት ባስከተለ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ማንም ሰው በንዑስ አንቀጽ (፩) ለተመለከተው ዓላማ ለማዋል በማሰብ፣ በሕግ የተፈቀደ መድሃኒትን ያለአግባብ ወይም ከተሠራበት ዓላማ ውጭ ያዘዘ፣ የሰጠ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፫ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) ከተጠቀሱት ድርጊቶች አንዱ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት፣ ወይም ከአምስት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፳፯</u> <u>የሚጐዱ ወይም የተበላሹ ዕቃዎችንና ምግቦችን መሥራትና መሸጥ እንዲሁም ጥራታቸውን ማርከስ</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ፡-

ሀ/ ምግቦችን፣ ቀለቦችን፣ በምግብነት የሚያገለግሉ ሌሎች ነገሮችን ለሰው ፍጆታ እንደማይበጅ በማድረግ ወይም ምግቦችን ለመሥራት የሚያገለግሉ ነገሮችን ጎጂ ወይም የተበላሸ ይዘት እንዲኖራቸው በማድረግ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም የሕዝብ ጤናን በሚጎዳ ሁኔታ የምግቦችን ወይም የዕቃዎችን ጥራት ያረከሰ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ጎጂ የሆኑ የዚህ ዓይነት የምርት ውጤቶችን ያከማቸ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ወደ ውጭ የላከ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ የተቀበለ፣ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማያንስ ፅኑ እሥራት የሚሆነው ጥፋተኛው:-

ሀ/ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በመንግሥት የተያዘን ወይም ከመንግሥት በኮንሴሽን የተሰጠን ድርጅት የመቆጣጠር ወይም የመመርመር ልዩ ግዴታ ያለበት ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

ለ/ በሽታን የሚፈውሱ፣ ጤንነትን የሚያበረቱ፣ የምግብ ጠባይ ያላቸው ወይም ቶኒክ የሆኑ መርዝነት የሌላቸውና ያለሐኪም ትዕዛዝ ለመስጠት የሚቻሉ ልዩ ልዩ መድሃኒቶች በመጥፎ አመራረታቸው ወይም በጥራታቸው መርከስ የታወቀ ጉዳት የሚያመጡ መሆናቸው ሲታወቅ ወይም ለማወቅ ሲቻል እነዚህን መድሃኒቶች አስቦ ያመረተ፣ ጥራታቸውን ያረከሰ፣ የሸጠ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤

ነው::

፫ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት፣ ወይም መቀጮ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፭፻፳፰</u> <u>የከብት ድርቆሽና ሌላም መኖ ጉዳት እንዲያደርስ አድርጎ መሥራት፤ ጥራትን ማርከስና መሸጥ</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ የድርቆሽን ወይም የተፈጥሮ መኖን ጥራት ያረከሰ ወይም በቤት እንስሳት ጤና ወይም ሕይወት ላይ ጉዳት ለማድረስ እንዲችል አድርጎ ያመረተ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ይህንኑ ጉዳት የሚያደርስ ድርቆሽ ወይም ሌላ ዓይነት መኖ ከውጭ አገር ያስመጣ፣ ወደ ውጭ አገር የላከ፣ ያከማቸ፣ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፳፱</u> <u>ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች</u>

ጥፋተኛው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፳፯ እና ፭፻፳፰ የተመለከቱትን ወንጀሎች ሞያው አድርጎ የያዘ ሲሆን /አንቀጽ ፺፪/ ወይም ወንጀሉን የፈጸመው ከፍተኛ ብዛት ባላቸው ዕቃዎች ላይ ሲሆንና የደረሰውም ጉዳት ከባድ ሲሆን፣ ቅጣቱ በነዚሁ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተው ከፍተኛ የነፃነት ማሳጣት ቅጣትና ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፴</u> <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት</u>

ማናቸውም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ከአንቀጽ ፭፻፳፭ እስከ ፭፻፳፱ ከተመለከቱ ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ እንደሆነ፤

በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፭፻፴፩</u> <u>በአልኮል ወይም በእስፒርቶ መጠጦች የሌላውን ሰው ጤንነት ለአደጋ ማጋለጥ</u>

፩ ማንኛውም ሰው አስቦ የመጠጦች ዓይነት ወይም ብዛት የሚጎዳ መሆኑን እርግጠኛ የሆነውን ወይም ሊጎዳ የሚችለውን አልኮል ወይም እስፒርቶ ያለባቸውን መጠጦች ለአካለመጠን ላልደረሰ ወጣት ወይም ከልክ

አሳልፎ የጠጣ መሆኑ በግልጽ ለታወቀ ሰው የአልኮል ወይም የእስፒርቶ መጠጥ በማቅረብ ወይም በመስጠት ወይም እንዲቀርብ ወይም እንዲሰጥ በማድረግ የሌላውን ሰው ጤንነት ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ ተደጋግሞ የተፈጸመ እንደሆነ፤ የሙያ ሥራውን መከልከሉ የተጠበቀ ሆኖ ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ያስቀጣል::

፫ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል::

## አንቀጽ ፭፻፴፪ አእምሮን በሚነኩ ድርጊቶች ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ

ማንም ሰው አስቦ በማፍዘዝ /ሒፕኖሲስ/፣ በማንዘፍዘፍ፣ በማደንዘዝ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ የሌላውን ሰው የኅሊና ችሎታ ለጊዜው በማጥፋት ለአደጋ ያጋለጠው እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፴፩ በተደነገገው ቅጣት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፭፻፴፫ በድግምት፣ በጥንቆላ ወይም ይህን በመሣሰሉ ነገሮች በሰው ላይ አደጋ ማድረስ

ማንም ሰው ጠባያቸው ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ወይም ጉዳት እያወቀ ጤንነትን ሊጎዱ የሚችሉ ብናኝ ዱቄቶችን፣ የሥራይ በሽታ የሚያመጡ ቅመሞችን፣ መጠጦችን፣ ወይም ሌሎች እነዚህን የመሳሰሉትን ነገሮች

BACK



ለሌላ ሰው ያዘጋጀ፣ የሰጠ፣ የሸጠ፣ ያከፋፈለ ወይም ያጠጣ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፴፩ በተመለከተው ድንጋጌ ይቀጣል::

አንቀጽ ፭፻፴፩ ከባድ ሁኔታዎች

፩ ጥፋተኛው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፴፪ እና ፭፻፴፫ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱን እንደሙያ ሥራው አድርጎ የያዘ እንደሆነ፤ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው ተበዳዩ ሳይፈቅድ እንደሆነ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሰብ ችሎታን ስለማሳጣት በተለይ የተደነገገው /አንቀጽ ፭፻፵፫/ በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናል::

ምዕራፍ ሁለት

ሕክምናንና ጤና አጠባበቅን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መጣስ

አንቀጽ ፭፻፴፭ በሕክምናና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መሥራት

፩ ማንም ሰው አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተወሰነና ቁጥጥር የሚደረግበት የሙያ ችሎታ ሣይኖረው ወይም አግባብ ባላቸው ደንቦች መሠረት በግልጽ እንዲሠራ ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም ከተፈቀደለት ውጭ በማናቸውም አኳኋን በሽተኞችን ማከም ሙያው አድርጎ የያዘ፣ ወይም ገንዘብ በመቀበል የመረመረ፣ ያከመ፣ ምክር የሰጠ፣ መድኃኒት የሸጠ ወይም ማናቸውንም ዓይነት ሕክምና ነክ ሥራዎችን ያከናወነ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው ሁኔታ እንስሳትን የማከም ተግባር የሚሠራ ሰው በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፫ ማንም ሰው ያመረተው፣ ለሽያጭ ያቀረበው፣ የሸጠው፣ ያከፋፈለው፣ ወይም በአገልግሎት ላይ ያዋለው መድኃኒት ወይም የሕክምና መገልገያ መሣሪያ፦

ሀ/ ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተረጋግጦ አግባብ ባለው አካል ያልተፈቀደ፤

ለ/ የተመሳሰለ ወይም የተከለሰ ወይም በማሸጊያው ላይ አሳሳች ገላጭ ጽሑፍ የተደረገበት፣ የተለጠፈበት ወይም የተከተተበት፤

ሐ/ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበት፤ ወይም

መ/ የተከለከለ፣ የተበላሸ፣ የተጭበረበረ፣ የተበከለ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ የተረጋገጠ፤

እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራትና ከሃያ ሺህ ብር እስከ ሃምሣ ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል።

፬ አስቸኳይ ወይም አስፈላጊ የሆነ ወይም በደግነት ወይም ለሙያ ስነ ምግባር ተገዥ በመሆን አልፎ አልፎ በነፃ የሚሰጥ ምክር፣ እርዳታ ወይም አገልግሎት ወይም

ይህን በመሳሰሉ ሁኔታዎች የተፈጥሮ ወይም የተለመዱ ፍቱንና አደጋ የማያስከትሉ መድሃኒቶችን በመስጠት የሚደረግ እርዳታ አያስቀጣም።

፫ በሚኖሩበት አካባቢ በቂ ልምድ አላቸው በመባል የታወቁ ሰዎች በአካባቢው ልማድ መሠረት በሚያከናውኑት ሕክምና ነክ ሥራዎች ላይ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የለውም። ይህም የሚሆነው እነዚህ ሰዎች ሥራቸውን የሚያከናውኑት በሚኖሩበት አካባቢ ብቻ ሲሆንና ድርጊታቸውም የአካባቢውን ሕብረተሰብ አባላት ሕይወት፣ አካል ወይም ጤንነት አደጋ ላይ የማይጥል ወይም የማይጎዳ እንደሆነ ነው።

<u>አንቀጽ ፭፻፳፯ መርዛማና አደገኛ የሆኑ ነገሮችን ያለአግባብ ማቅረብ</u>

ማንኛውም ሐኪም፣ መድሃኒት ቀማሚ /ፋርማሲስት/፣ የጥርስ ሐኪም፣ የእንስሳት ሐኪም፣ አስታማሚ ወይም መርዛማ በሆኑ በናርኮቲክ ወይም በሳይኮትሮፒክ ነገሮች ወይም በጤና ላይ ከባድ ጉዳት ሊያስከትሉ በሚችሉ ሌሎች ነገሮች ሕክምና ለመስጠት ወይም እነዚህኑ ለማስቀመጥ ወይም ለመሸጥ የተፈቀደለት ማንኛውም ሌላ ሰው፣ መደበኛ የሕክምና አሠራር ከሚፈቅዳቸው ሁኔታዎች ውጭና ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው እነዚህኑ ነገሮች የሠራባቸው፣ ለሕዝብ የሰጠ ወይም የሸጠ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ፣ ወይም ጥፋቱ ከባድ እንደሆነ፤ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው በአፍቅሮ ንዋይ እንደሆነ፤ መቀጮው እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ሊደርስ ይችላል።

**<u>አንቀጽ ፭፻፸፯ የሕክምና እርዳታን ያለምክንያት መከልከል</u>**

፩ ማንኛውም ሐኪም፣ መድሃኒት ቀማሚ /ፋርማሲስት/፣ የጥርስ ሃኪም፣ የእንስሳት ሐኪም፣ አዋላጅ፣ አስታማሚ ወይም ማናቸውንም ሕክምና ለመስጠት ተግባሩ መሆኑ በሕግ የታወቀለት ማንኛውም ሌላ ሰው ተግባሩን በሚቃረን መንገድና በቂ ባልሆነ ምክንያት በምንቸገረኝነት፣ በራስ ወዳድነት፣ ገንዘብን አለመጠን በመፈለግ፣ በጥላቻ፣ በንቀት ወይም በማናቸውም ተመሳሳይ ምክንያት አስፈላጊ የሆነውንና በሞያ ተግባሩ ሊያደርገው የሚገባውን አገልግሎት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ፣

በመቀጮ፣ ወይም ወንጀሉ የተደጋገመ እንደሆነ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ አንድ ሰው በሕይወቱ፣ በአካሉ ወይም በጤናው ላይ ከባድ ጉዳት የሚደርስበት ሆኖ ሳለ እርዳታ ያላደረገ ማንም ሰው የሚቀጣበት የከፍተኛ ቅጣት ድንጋጌ /አንቀጽ /፭፻፸፭(፪)/ እንደተጠበቀ ነው::

## <u>አምስተኛ መጽሐፍ</u>

## <u>በሌሎች ሰዎችና በቤተዘመድ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

## <u>ርዕስ አንድ</u>

## <u>በሰው ሕይወት፣ አካልና ጤንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>በሰው ሕይወት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>የመግደል አደራረግና ዓይነቶች</u>

**<u>አንቀጽ ፭፻፴፰ መርህ</u>**

፩ ማንም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኛነት በማናቸውም ዓይነት መሣሪያ ወይም ዘዴ ሌላውን ሰው የገደለ እንደሆነ ነፍሰ ገዳይ ነው::

አስቦ ወይም በቸልተኛነት ሰውን በመግደል ጥፋተኛ የሆነ ሰው ላይ የሚጣለው ቅጣት እንደአገዳደሉ ቀላልነትና ከባድነት ከዚህ በታች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል::

፪ አስቦ ወይም በቸልተኛነት የገደለ ሁሉ የሚቀጣው ሕጋውያን በሆኑ የፍርድ ሂደቶች እና በውሣኔዎቻቸው መሠረት ብቻ ይሆናል::

አንቀጽ ፭፻፴፱ ከባድ የሰው ግድያ

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ የነበረው አሳብ፣ ወይም ምክንያት፣ ለመግደል የተጠቀመበት መሣሪያ ወይም ዘዴ፣ ያገዳደሉ ሁኔታ ወይም ግድያው የተፈፀመበት ቅጣትን የሚያከብድ ጠቅላላ ምክንያት /አንቀጽ ፹፬/ ወይም ሌላ ምክንያት /አንቀጽ ፹፮/ ሲታይ ገዳዩ በተለይ ጨካኝ፣ ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን በሚገልጽ ሁኔታ፤ ወይም

ለ/ ሰውን ለመግደል ወይም የውንብድና ወንጀልን ለመፈጸም የተደራጀ የወንበዴ ቡድን አባል በመሆን፤ ወይም

ሐ/ ሌላ ወንጀልን ለመፈጸም እንዲመቸው ወይም የተፈጸመ ወንጀል እንዳይገለጽ ለማድረግ ሲል፤

አስቦ ሰውን የገደለ እንደሆነ፤

በእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት ይቀጣል::

፪ ወንጀለኛው የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ተፈርዶበት ቅጣቱን በመፈፀም ላይ ሳለ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ሁኔታ ሰውን የገደለ እንደሆነ ፤

በሞት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፭፻፵</u> <u>ተራ የሆነ የሰው ግድያ</u>

ማንም ሰው አገዳደሉ በአንቀጽ ፭፻፴፱ የተመለከተውን ያህል ከባድ ወይም በአንቀጽ ፭፻፵፩ የተመለከተውን ያህል ቀላል ባልሆነ ሁኔታ አስቦ ሌላ ሰውን የገደለ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፭፻፵፩</u> <u>ቀላል የሆነ የሰው ግድያ</u>

ማንም ሰው፡-

ሀ/ የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን በመተላለፍ /አንቀጽ ፸፭/ ወይም ህጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ /አንቀጽ ፸፱/፤ ወይም

ለ/ ከፍ ባለ ደም በሚያፈላ ምክንያት ወይም ባልጠበቀው ሕሊናን በሚያውክ ድንገተኛ ምክንያት ወይም በከፍተኛ ስሜት ወይም በብርቱ ዝንባሌ የተነሣ ሆኖ፤ በአእምሮ ግምት ይህን ለማድረግ በሚያደርሱና በከፊል ይቅርታን በሚያስጡ ሁኔታዎች፤

አስቦ ሌላ ሰውን የገደለ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፭፻፵፪</u> <u>ሌላ ሰው ራሱን እንዲገድል ማነሣሣትና መርዳት</u>

፩ ማንም ሰው ሌላውን ሰው ራሱን እንዲገድል ያነሣሣ ወይም የረዳ እንደሆነ፡ እራስን የመግደል ሙከራው በተደረገ ጊዜ፡ በቀላል እሥራት፡ እራስን የመግደሉ

ተግባር በተፈፀመ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ራሱን እንዲገድል የተነሣሣው ወይም እርዳታ የተደረገለት ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ወይም በአእምሮ ህመም ወይም በዕድሜ መግፋት የተነሣ ችሎታ ያልነበረው ሰው ሲሆን፤ በአነሳሹ ወይም በረጂው ላይ የሚወሰነው ቅጣት የተነሣሣው ወይም የተረዳው ሰው ራሱን ለመግደል ሞክሮ እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት፤ ራሱን ገድሎ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፵፫</u> <u>በቸልተኛነት ሰውን መግደል</u>

፩ ማንም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ውስጥ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ በቸልተኛነት ሰውን የገደለ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እሥራት ወይም ከሁለት ሺህ እስከ አራት ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል።

፪ የሌላ ሰውን ሕይወት፣ ጤንነት ወይም ደኅንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ህክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው በቸልተኛነት ሰው የገደለ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ቀላል እሥራት እና ከሦስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ ብር ሊደርስ የሚችል መቀጮ ይሆናል።

፫ ጥፋተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ግልጽ የሆነ ደንብ

ወይም መመሪያን ተላልፎ እንደሆነ ወይም የሚያሰክሩ ወይም የሚያፈዙ ንጥረ ነገሮችን ወይም መጠጦችን በመውሰድ እራሱን ከኃላፊነት ነፃ በሚያወጣ ሁኔታ ውስጥ ካስገባ በኋላ ቢሆንም እንኳ፣

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት እና ከብር አሥር ሺህ እስከ አስራ አምስት ሺህ የሚደርስ መቀጮ ይሆናል::

አንቀጽ ፭፻፴፩ ሕፃንን መግደል

፩ አንዲት እናት ለመውለድ ምጥ በተያዘች ጊዜ ወይም የምጥ ስሜትዋ ሳያልፍ አስባ ልጅዋን የገደለች እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት ትቀጣለች::

ወንጀሉ ሲሞከር በሕፃኑ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ያልደረሰ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ ፻፹ መሠረት ቅጣቱን ያቃልላል::

፪ አንዲት እናት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ ልጇን አስባ ወይም በቸልተኛነት የገደለች እንደሆነ፣ ግድያን የሚመለከቱት መደበኛ የሕጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ወንጀል በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ተካፋይ የሆነ ሌላ ሰው የሕጉ ልዩ አስተያየት ሳይደረግለት እንደነገሩ ሁኔታና እንደጥፋቱ መጠን ሰው ስለመግደል በተመለከቱት መደበኛ የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል::

BACK



## ክፍል ሁለት
## በፅንስ ላይ የሚደረግ ወንጀል፤ ፅንስ ማስወረድ

**አንቀጽ ፭፻፵፭ መርህ**

፩ በማናቸውም የእርግዝና ደረጃ የሚገኘውን ጽንስ በአንቀጽ ፭፻፶፩ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ አስቦ ማስወረድ ከዚህ በታች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ያስቀጣል::

፪ ፍርድ ቤት የቅጣቱን ዓይነትና መጠን የሚወስነው የማስወረድ ተግባሩ ታስቦ የተፈፀመው በእናቲቱ ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን መሆኑን፣ ድርጊቱ የተፈፀመው በሦስተኛ ወገን ከሆነ እናቲቱ ፈቅዳ ወይም ሳትፈቅድ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል::

**አንቀጽ ፭፻፵፮ አንዲት ሴት በራሷ ላይ የምትፈፅመው የማስወረድ ድርጊት**

፩ የራሷን ፅንስ አስባ የምታስወርድ ሴት በቀላል እሥራት ትቀጣለች::

፪ የማስወረጃ መሣሪያ በመስጠት ወይም ማናቸውንም ሌላ ድጋፍ በመስጠት አንዲት ሴት የፀነሰችውን ስታስወርድ በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም በአባሪነት ተካፋይ የሆነ ሌላ ሰው በቀላል እሥራት ይቀጣል::

**አንቀጽ ፭፻፵፯ በሌላ ሰው የሚፈፀም የማስወረድ ድርጊት**

፩ በሕግ ከተፈቀደው ውጭ አስቦ በፀነሰች ሴት ላይ የማስወረድ ድርጊት የፈፀመ ወይም የማስወረድ ድርጊት በሚፈፀምበት ጊዜ የረዳ ሰው በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ የማስወረድ ድርጊቱ የተፈፀመው ያረገዘችው ሴት ባልፈቀደችበት ወይም ፈቃዷን ለመስጠት በማትችልበት ጊዜ እንደሆነ፤ ወይም በዛቻ፣ በማስገደድ፣ በማታለል ወይም ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለማወቅ በማትችልበት ጊዜ ፈቃዷን በማግኘት እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እሥራት ይሆናል።

፫ በሕግ ከተፈቀደው ውጭ ለሚፈፀም የጽንስ ማስወረድ ድርጊት ፈቃዷን የሰጠች እርጉዝ ሴት በቀላል እስራት ትቀጣለች።

<u>አንቀጽ ፭፻፵፫ ከባድ ሁኔታዎች</u>

ፅንስ የማስወረድ ተግባር የተፈጸመው በሕግ ከተደነገገው ውጭ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ እንደሚከተለው ይከብዳል፦

፩ ጥፋተኛው ወንጀሉን ያደረገው በአፍቅሮ ንዋይ ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም የዘወትር ተግባሩ በማድረግ እንደሆነ (አንቀጽ ፺፪)፣ በአንቀጽ ፭፻፵፪ ከተመለከተው ቅጣት በተጨማሪ በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተደረገው በቂ የህክምና ሙያ በሌለው ሰው እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቀላል እስራትና መቀጮ ይሆናል።

፫ ወንጀሉን ያደረገው ባለሙያ፣ በተለይም በሀኪም፣ በመድኃኒት ቀማሚ (ፋርማሲስት)፣ አዋላጅ ወይም አስታማሚ እንደሆነና ድርጊቱን የፈጸመውም በሙያ ሥራው ያለአግባብ በመገልገል እንደሆነ፤ ከቀላል እስራትና ከመቀጮ በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛውን ለአንድ ለተወሰነ ጊዜ፤ ወይም ወንጀሉን የደጋገመ

እንደሆነ ለዘወትር ከሙያ ሥራው ያግደዋል /አንቀጽ ፻፳፫/::

## <u>አንቀጽ ፭፻፵፱ እርግዝና በሌላት ሴት ላይ የማስወረድ ድርጊት ለመፈፀም መሞከር</u>

እርግዝና በሌላት በአንዲት ሴት ላይ እርጉዝ ናት በማለት የማስወረድ ድርጊት ሙከራ የተደረገ እንደሆነ፣ ሊደረግ ስለማይቻል ወንጀል የተደነገገው ጠቅላላ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል /አንቀጽ ፳፱/::

## <u>አንቀጽ ፭፻፶ ቅጣትን የሚያቀሉ ሁኔታዎች</u>

ፅንሱ የተቋረጠው ከዚህ በታች በአንቀጽ ፭፻፶፩ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጭ ጥልቅ በሆነ እና በሚቆይ የኑሮ ችግር ምክንያት እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ ፻፹ መሠረት በመሰለው ቅጣቱን ያቃልላል::

## <u>አንቀጽ ፭፻፶፩ ፅንስን ማቋረጥ በሕግ የተፈቀደባቸው ሁኔታዎች</u>

፩ በሕክምና ሙያ በተፈቀደ የጊዜ ገደብ ውስጥ በሕክምና ተቋም ፅንስ ሲቋረጥ በወንጀል የማያስቀጣው:-

ሀ/ በመደፈር ወይም በዘመድ መካከል በተደረገ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ፅንሱ የተገኘ ሲሆን፣

ለ/ የእርግዝናው መቀጠል በእናቲቱም ሆነ በፅንሱ ህይወት ወይም በእናቲቱ ጤንነት ላይ አደጋ የሚያስከትል ሲሆን ወይም የልጁ መወለድ በእናቲቱ ጤንነት ወይም ሕይወት ላይ አደጋ የሚያመጣ ሲሆን፣

ሐ/ ጽንሱ ሊድን የማይችል ከባድ የአካል ጉድለት ያለው (ዲፎርምድ) ሲሆን፤ ወይም

መ/ አንዲት እርጉዝ ሴት የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለባት በመሆኗ ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰች በመሆኗ የሚወለደውን ህፃን ለማሳደግ የህሊናም ሆነ የአካል ዝግጅት የሌላት ሲሆን፤

ነው።

፪ በፍጥነት በሚደረግ የሕክምና ሥራ ካልሆነ በቀር ሊወገድ የማይቻል ከባድና ጊዜ የማይሰጥ አደጋ ሲያጋጥም በዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፭ መሠረት የሚፈፀም የጽንስ ማስወረድ ተግባር አያስቀጣም።

## <u>አንቀጽ ፭፻፵፪ ፅንስ የሚቋረጥበት ስነስርዓትና ስነስርዓቱን መጣስ የሚያስከትለው ቅጣት</u>

፩ ከላይ በአንቀጽ ፭፻፵፩ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት ጽንስ ስለሚቋረጥበት ስነ-ሥርዓት፣ የእርጉዝ ሴቶችን መብት በማይነካ ሁኔታ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአጭር ጊዜ ውስጥ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

፪ በአንቀጽ ፭፻፵፩ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) በተገለጹት ምክንያቶች ጽንስ ለማቋረጥ፣ ሴትየዋ መደፈሯን ወይም ከቤተዘመድ መጸነሷን መግለጿ ብቻ በቂ ይሆናል።

፫ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን መመሪያ የጣሰ ማንኛውም ሰው ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

## ምዕራፍ ሁለት
## በሰው አካልና ጤና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፭፻፶፫ መርህ

፩ ማንም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኛነት በማናቸውም ነገር ወይም ዘዴ የሌላውን ሰው አካል ያጐደለ ወይም ጤንነቱን የጐዳ እንደሆነ በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል::

እነዚህ ድንጋጌዎች ማናቸውንም በሰውነት ላይ የሚፈጸሙትን የእጅ እልፊቶችን፣ መምታትን፣ ማቁሰልን፣ የአካል ማጉደልን፣ ጉዳቶችን ወይም ጥፋቶችን እንዲሁም በሰው የአካል ወይም የአእምሮ ጤንነት ላይ የሚፈጸሙትን ጉዳቶች ሁሉ ያጠቃልላሉ::

፪ ፍርድ ቤቱ ለተበዳዩ የሚከፈለውን የጉዳት ካሣ የሚወስነው የጉዳቱን ከባድነትና የተከራካሪ ወገኖችን ሁኔታ ከግምት ወስጥ በማስገባት በዚሁ ሕግ ስለ ጉዳት ካሣ በተደነገገው ጠቅላላ ድንጋጌ መሠረት ይሆናል /አንቀጽ ፻፩/::

### አንቀጽ ፭፻፶፬ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚደረግ የልዩ አዋቂ ወይም የባለሙያ ምርመራ

ፍርድ ቤቱ ስለ አንድ የአካል ጉዳት ጉዳይ ባህሪ፣ ስለሚያስከትለው ውጤት ወይም ስለከባድነቱ የሚያጠራጥር ነገር ያጋጠመው እንደሆነ ጉዳዩን ለመወሰን በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን በሕክምና ምርመራ የሚያውቅ ባለሙያ እንዲረዳው መጠየቅ ይችላል::

BACK



**አንቀጽ ፭፻፶፭ ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት**

ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ የተጐጂውን ሕይወት በሚያሰጋ ወይም በሰውነቱም ሆነ በአእምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ በሚያተርፍ ሁኔታ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የሌላ ሰውን አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑት ብልቶቹ ወይም ሕዋሳቶቹ አንዱን ያጐደለ፣ እንዳያገለግሉት ያደረገ ወይም በሚያስቀቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ መልኩን ያበላሸ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በማናቸውም ሌላ መንገድ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን በሌላ ሰው ላይ ያደረሰ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታና እንደ ጉዳቱ ከባድነት ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

**አንቀጽ ፭፻፶፮ ታስቦ የሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት**

፩ ማንም ሰው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፶፭ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ አስቦ በሰው አካል ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ድርጊቱ በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚያስቀጣውና ቅጣቱ ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት የሚሆነው:-

ሀ/ ጥፋተኛው ጉዳት ያደረሰው በመርዝ ወይም በገዳይ መሣሪያ ወይም የአካል ጉዳት

ለማድረስ በሚችል በማናቸውም ሌላ መሣሪያ በመጠቀም እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ጥፋተኛው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታን በመተላለፍ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ተጐጂው ደካማ፣ በሽተኛ ወይም ራሱን ለመከላከል የማይችል እንደሆነ፤

ነው::

## አንቀጽ ፭፻፶፯ የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች

፩ ማንም ሰው በሌላ ሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ አስቦ ጉዳት ያደረሰው:-

ሀ/ የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን በመተላለፍ /አንቀጽ ፸፭/ ወይም ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሣለፍ /አንቀጽ ፸፱/ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ከፍ ባለ ደም በሚያፈላ መቀስቀስ ምክንያት፣ ባልጠበቀው ህሊናን በሚያውክ ድንገተኛ ምክንያት፣ ወይም በከፍተኛ ስሜት ወይም ከብርቱ ዝንባሌ የተነሣ ሆኖ ሁኔታዎቹ በአእምሮ ግምት ድርጊቱን ከመፈፀም የሚያደርሱና በከፊል ይቅርታን የሚያሰጡ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ የደረሰው ጉዳት በሕግ የተከለከለ ወይም ጉዳቱ መልካም ጠባይን /ሞራልን/ የሚነካ በሚሆንበት ጊዜ የድርጊቱን ምንነትና ውጤት መገመት በሚችል ተጐጂ ጥያቄ ወይም ፈቃድ መሠረት እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከሁለት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአራት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፪ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) በተመለከተው ሁኔታ ተጐጂው በዕድሜው ወይም በአእምሮው

ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ጥያቄው ወይም አሺታው የሚያስከትለውን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ለመረዳት የማይችል እንደሆነ፣ በጥፋተኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት ከአራት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፭፻፶፰</u> <u>ከጥፋተኛው አሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት</u>

ማንም ሰው ቀላል የአካል ጉዳት ለማድረስ አስቦ፣ በቸልተኛነት ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣

ከስድስት ወር እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፭፻፶፱</u> <u>በቸልተኛነት የሚፈፀሙ የአካል ጉዳቶች</u>

፩ ማንም ሰው በቸልተኛነት በሌላ ሰው አካል ወይም ጠ ንነት ላይ ቀላል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣

ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከብር አንድ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ የደረሰው ጉዳት በአንቀጽ ፭፻፶፭ የተመለከተው ዓይነት ከሆነ ወይም ጉዳት አድራሹ የሌላ ሰውን አካል ወይም ጤንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ህክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራትና ከአንድ ሺህ ብር የማያንስ መቀጮ ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የሚያስቀጣው፣ ጉዳቱ ከባድ ከሆነ በወንጀል ክስ አቅራቢነት፣ ጉዳቱ ቀላል ከሆነ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ነው:: የጉዳቱ መጠን የሚወሰነው በአንቀጽ ፭፻፶፭ እና ፭፻፶፮ በተደነገገው መሠረት ይሆናል::

## አንቀጽ ፭፻፷ የእጅ እልፊት

፩ ማንም ሰው የአካል ጉዳትን ወይም የጤንነት ጉድለትን ሳያደርስ በሌላ ሰው ላይ የእጅ እልፊት ወይም የመጋፋት ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፣

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

ቀላል የሆኑ ሰንበሮች፣ የደም መቋጠር ምልክቶች ወይም በቶሎ የሚያልፍ ሕመም ወይም ሥቃይ እንደ አካል ጉዳት ወይም እንደ ጤና ጉድለት አይቆጠሩም::

፪ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ውጭ የሆኑ ጥፋቶች በዚህ ሕግ ስለደንብ መተላለፍ በአንቀጽ ፰፻፵ በተደነገገው መሠረት ያስቀጣሉ::

፫ ተበዳዩ የተፈፀመበትን የእጅ እልፊት ወዲያውኑ በእጅ እልፊት የመለሰ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሌላ ቅጣት በመወሰን ፈንታ እንዳስፈላጊነቱ አንዱን ወይም ሁለቱንም ወገኖች በመገሰጽ ወይም በማስጠንቀቅ ሊያልፋቸው ይችላል::

## ምዕራፍ ሦስት

## በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በህይወት፣ በአካል እና በጤና ላይ ጉዳት በማድረስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

## አንቀጽ ፭፻፷፩ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴቶች እና ሕፃናት ሕይወት ላይ ጉዳት ማድረስ

፩ ማንም ሰው:-

BACK



ሀ/ የእርጉዝ ሴትን ሆድ በማሸት ወይም በመውለድ ላይ ያለችን ሴት አካል በማርገፍገፍ፤ ወይም

ለ/ አዲስ የተወለደ ህፃንን እትብት እበት ወይም እንደእበት የመሳሰለ ነገር በመቀባት፣ ህፃንን ዐሐይ በመከልከል ወይም ቅቤ በማዋጥ፣ የሕፃንን እንጥል በመቁረጥ፣ ግግ በማውጣት ወይም እንዳይከተብ በማድረግ፤ ወይም

ሐ/ ይህን የመሳሰለና ጉጂነቱ በሕክምና ሙያ የታወቀ ልማዳዊ ድርጊትን በመፈጸም፤

የእርጉዝ ሴት ወይም የሕፃን ሕይወት እንዲያልፍ ያደረገ እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም ከሶስት ወር እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል።

፪ የሴቱትም ወይም የሕፃኑ ሞት የደረሰው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ስለዚሁ ጉዳይ አግባብነት ያለው የዚህ ሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል /አንቀጽ ፭፻፵፫/።

አንቀጽ ፭፻፷፪ በጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴት ወይም፣ በሕፃን አካል ላይ ጉዳት ማድረስ

፩ ማንም ሰው፦

ሀ/ የእርጉዝ ሴትን ሆድ በማሸት ወይም በመውለድ ላይ ያለችን ሴት አካል በማርገፍገፍ፤ ወይም

ለ/ አዲስ የተወለደ ህፃንን እትብት እበት ወይም እንደ እበት የመሳሰለ ነገር በመቀባት፣ ሕፃኑን ዐሐይ በመከልከል ወይም ቅቤ በማዋጥ፣ የሕፃንን እንጥል

BACK



በመቁረጥ፣ ግግ በማውጣት፣ እንዳይከተብ በማድረግ፤ ወይም

ሐ/ ይህን የመሳሰለና ጉጂነቱ በሕክምና ሙያ የታወቀ ልማዳዊ ድርጊት በመፈጸም፤

በእርጉዝ ሴት ወይም በህፃን ላይ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ በአካል ወይም በአእምሮ ጤና ላይ ጉዳት የደረሰው በቸልተኛነት እንደሆነ ስለዚሁ ጉዳይ አግባብነት ያለው የዚህ ሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል /አንቀጽ ፭፻፶፱/::

## አንቀጽ ፭፻፷፫ የፍርድ ቤቱ ልዩ አስተያየት

ፍርድ ቤት ከላይ በአንቀጽ ፭፻፷፩ እና ፭፻፷፪ በተመለከቱት ወንጀሎች ረገድ የአድራጊውን ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የኑሮ ልምድ ወይም የማህበራዊ ኑሮ ደረጃ ከግምት በማስገባት መቀጮ ወይም ነፃነትን የሚያሳጣ ቅጣት በመወሰን ፈንታ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ብቻ በመስጠት ሊያልፈው ይችላል::

## አንቀጽ ፭፻፷፬ በትዳር ጓደኛ ወይም ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረስጋ ግንኙነት በሚኖር ሰው ላይ ጥቃት ማድረስ

ማንም ሰው በትዳር ጓደኛው ወይም ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረስጋ ግንኙነት አብሮት በሚኖር ሰው አካል ወይም የአእምሮ ጤንነት ላይ ከባድ ወይም ቀላል ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ ጥቃት የፈጸመበት እንደሆነ፤

ተገቢነት ያለው የዚህ ሕግ ድንጋጌ (አንቀጽ ፭፻፶፭ እስከ ፭፻፷) ተፈፃሚ ይሆንበታል።

<u>አንቀጽ ፭፻፷፭ ሴትን መግረዝ</u>

ማንም ሰው በየትኛውም የዕድሜ ክልል የምትገኘውን ሴት የገረዘ እንደሆነ፣

ከሶስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማያንስ መቀጮ ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፭፻፷፮ የሴትን ብልት መስፋት</u>

፩ ማንም ሰው የአንዲትን ሴት ብልት የሰፋ እንደሆነ፣ ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ድርጊት የአካል ወይም የጤና ጉዳት ደርሶ እንደሆነ፣ በወንጀል ሕጉ ከፍተኛ ቅጣት የሚጥል ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፷፯ በሌሎች ልማዳዊ ጐጂ ድርጊቶች አማካይነት የሚፈፀም የአካል ጉዳት</u>

ማንም ሰው በዚህ ምዕራፍ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጭ፣ ኢሰብአዊነቱ በታወቀና ጐጂነቱ በሕክምና ሙያ በተረጋገጠ ልማዳዊ ድርጊት አማካይነት በሌላ ሰው ላይ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ወይም ሞት እንዲደርስ ያደረገ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ በአንቀጽ ፭፻፷፭ ወይም ፭፻፷፮ ከተመለከቱት ቅጣቶች አንዱ ተፈፃሚ ይሆንበታል::

__አንቀጽ ፭፻፷፰ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሽታን ማስተላለፍ__

ከላይ በተመለከቱት አንቀጾች ውስጥ ከተገለፁት ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በአንዱ ምክንያት ተበዳዩ በተላላፊ በሽታ የተያዘ እንደሆነ አድራጊው በዚህ ሕግ ተላላፊ በሽታዎችን ስለማባዛት በተደነገገው መሠረት በተደራቢነት ይቀጣል::

__አንቀጽ ፭፻፷፱ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተካፋይ መሆን__

በዚህ ምዕራፍ ከተመለከቱት ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ የሆነ ወላጅ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

__አንቀጽ ፭፻፸ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች እንዳይፈፀሙ ማነሳሳት__

ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንዳይፈፀሙ በይፋም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያነሳሳ ወይም የቀሰቀሰ፣ ይህን ዓይነት ዓላማ ለማስፈፀም ሕዝብን ያደራጀ፣ ለዚህ ዓላማ በተደራጀ እንቅስቃሴ ያሳተፈ፣ ወይም ለዚህ ዓላማ ድጋፍ የሰጠ ማንኛውም ሰው፣

ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማያንስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል::

## ምዕራፍ አራት
## የሰውን ሕይወት፣ አካል ወይም ጤንነት ለአደጋ በማጋለጥ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፭፻፸፫ የሰውን ሕይወት ለአደጋ ማጋለጥ

ማንም ሰው አስቦ ሌላውን ሰው በቅርብ ለሚደርስ የሞት አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ወይም ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

### አንቀጽ ፭፻፸፬ የትራፊክ ደንብን በመጣስ ለአደጋ ማጋለጥ

፩ ማንም አሽከርካሪ ወይም እግረኛ በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብን በመጣስ የሌላውን ሰው ሕይወት፣ አካል፣ ጤና ወይም ንብረት ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

ከአንድ ወር እስከ ከሦስት ዓመት በሚደርሰ ቀላል እሥራት፣ ወይም ከመቶ ብር በማያንስ መቀጮ፣ ወይም በሁለቱም ይቀጣል::

፪ ድርጊቱ በሰው ሕይወት፣ አካል፣ ጤና ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ ለጉዳዩ አግባብ ያለው የዚህ ሕግ ድንጋጌና የተጣሰው የትራፊክ ደንብ ድንጋጌ በተደራራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ::

### አንቀጽ ፭፻፸፭ የሰውን አካል ለአደጋ ማጋለጥ

፩ ማንም ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት ሲል:-

ሀ/ በሕይወቱ ሣለ አካሉን ወይም የአካሉን ክፍል ለሌላ ሰው የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ከሌላ ሰው ወይም ድርጅት ጋር ባደረገው ውል፣ ከሞቱ በኋላ አካሉን ወይም የአካሉን ክፍል ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት ሲል የሌላውን ሰው አካል ወይም የአካል ክፍል በተጎጂው ፈቃድ የወሰደ እንደሆነ ድርጊቱ የተፈፀመው:-

ሀ/ ተጐጂው በሕይወት እያለ ከሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት፤

ለ/ ከተበዳዩ ሞት በኋላ ከሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፤ ይቀጣል::

፫ ማንም ሰው በማስገደድ፣ በማጭበርበር፣ በማታለል ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ሳይፈቅድ የሌላውን አካል ወይም የአካል ክፍል የወሰደ እንደሆነ፤

ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል::

፬ ማንም ሰው ከላይ ባሉት ንዑስ አንቀጾች ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ ሕግን፣ ደንብን ወይም መመሪያን በሚቃረን መንገድ አንድን ሰው በማስገደድ ወይም የተባለው ሰው ሳይፈቅድ ወይም ሳያውቀው በእርሱ አካል ላይ የሳይንስ ወይም የሕክምና ምርመራ፣ ምርምር ወይም ሙከራ ያደረገ፤ ወይም በዚህ ሁኔታ የተገኘውን መረጃ በማናቸውም አይነት መንገድ ለሌላ ሰው የገለፀ ወይም የሰጠ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፫ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) ወይም (፬) ከተዘረዘሩት ድርጊቶች አንዱን የፈፀመ እንደሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፴፬ እና ፺(፫) መሠረት ይቀጣል፡፡

<u>አንቀጽ ፭፻፸፬ ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ ወይም መተው</u>

፩ በጤናው፣ በዕድሜው፣ በሁኔታው ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ራሱን ለመጠበቅ የማይችለውን ሌላ ሰው በማናቸውም ምክንያት ይሁን በጠባቂነት ወይም በሃላፊነት ለማኖር የተቀበለ ማንም ሰው የተባለውን ሰው አስቦ፡-

ሀ/ በሕይወቱ ወይም በጤናው ላይ በቅርቡ መድረሱ ለማይቀር አደጋ ያጋለጠው እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ይህን በመሰለ ሁኔታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ ጥሎት የሄደ እንደሆነ፤

አስፈላጊ ሲሆን ከቤተዘመድ ሥልጣን የመሻሩ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ወይም ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በሕፃን ልጅ ላይ እንደሆነ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

BACK



## አንቀጽ ፭፻፸፭ በአደጋ ላይ የሚገኝ ሰውን አለመርዳት

፩ ማንም ሰው በራሱ ወይም በሦስተኛ ወገኖች ላይ አደጋ በማያደርስ ሁኔታ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊረዳው ሲችል በሕይወቱ፣ በሰውነቱ ወይም በጤንነቱ ላይ ሊደርስ በሚችል ከባድ አደጋ ላይ የሚገኘውን ሌላ ሰው አስቦ ሳይረዳው የቀረ እንደሆነ፣ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው:-

ሀ/ በማናቸውም ሁኔታ ወይም ዘዴ ይሁን በተጐጂው ላይ ጉዳት ያደረሰው እራሱ ተከሣሹ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ ተጐጂውን ለመታደግ ወይም ለመርዳት የሙያ፣ ወይም የውል፣ የሕክምና፣ የባሕር ወይም ሌላ ሕጋዊ ግዴታ ያለበት እንደሆነ፣

ከአንድ ወር እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፭፻፸፮ ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን መጉዳት

፩ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን የሚጠብቅ ወይም በኃላፊነት የሚያሳድግ ማንም ሰው በማናቸውም ምክንያት ወይም ሁኔታ ልጁን የበደለ፣ ችላ ያለ ከአቅሙ በላይ ያሰራ ወይም የመታ እንደሆነ፣

ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

BACK



፪ ወንጀሉ በልጁ ጤንነት፣ ደህንነት፣ ትምህርት ወይም አካላዊ ወይም ስነልቦናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በሚያስከትልበት ጊዜ፣ አስፈላጊ ሲሆን ከቤተዘመድ ሥልጣን የመሻሩ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ያስቀጣል::

፫ ይህ ድንጋጌ ወላጆችና ተመሳሳይ ኃላፊነት ያላቸው ሌሎች ሰዎች ለመልካም አስተዳደግ የሚወስዱትንና ሕግን የማይቃረን የዲሲፕሊን እርምጃን አይመለከትም /አንቀጽ ፷፰/::

## አንቀጽ ፭፻፷፪ አምባጓሮ

፩ ማንም ሰው ጥቃትን ለመመለስ፣ ራሱን ወይም ሌላውን ለመከላከል ወይም ጠበኞችን ለመገላገል ሣይሆን ከሦስት በማያንሱ ሰዎች መካከል በተደረገና በሰው ሕይወት፣ አካል፣ ጤንነት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት በሚያስከትል አምባጓሮ ወይም ጠብ ተካፋይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ሰውን ማቁሰል ወይም መግደል የሚችል የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ ዓይነት መሣሪያ በመያዝ ወይም በመጠቀም በአምባጓሮ ወይም በጠብ ተካፋይ እንደሆነ እና ጉዳት ያልደረሰ እንደሆነ፤

ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፫ በአምባጓሮው ወቅት ከነበረው ሁኔታ የተነሣ በተለይም በጠበኞች መካከል በነበረው ቂም፣ የጠብ ማጫር ወይም የስካር ሁኔታ ወይም የጦር መሣሪያዎችን ፣ ድንጋዮችን ወይም ማቁሰል ወይም

BACK


መግደል የሚችሉ ሌሎች ነገሮችን የያዙ ወይም እነዚሁ ነገሮች የተሰጧቸው በመሆኑ በጠቡ መካከል ሰው የቆሰለ ወይም የተገደለ እንደሆነ፤ ቅጣቱ እስከ ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት ሊደርስ ይችላል።

፬ እንዲህ በሆነ ጊዜም ጉዳት ወይም ሞት ያደረሰ ሰው ሊለይ ወይም ሊታወቅ የቻለ እንደሆነ፤ አግባብነት ባላቸው ሌሎች አንቀጾች በተመለከቱት ቅጣቶች በጣምራ ይቀጣል /አንቀጽ ፷፮/።

<u>አንቀጽ ፭፻፴፫</u> <u>የይዋጣልን ፍልሚያ</u>

፩ ማንም ሰው የተፋላሚዎችን ሕይወት፣ አካል ወይም ጤና አደጋ ላይ ሊጥል በሚችል፣ አስቀድሞ በባህል ወይም በልማድ በተወሰነውና ገዳይ መሣሪያዎችን ባካተተ ፍልሚያ ተካፋይ እንደሆነ፤ የአካል ጉዳት ቢደርስም ባይደርስም በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ የሞት አደጋ እንዳይደርስ አስፈላጊ የሆኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች ተወስደው እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከሁለት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፫ ከተፋላሚዎቹ አንዱ እስከሚሞት ድረስ ፍልሚያው ይቀጥላል ተብሎ እንደሆነና ሌላው ተፋላሚ የሞተ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

፬ ማንኛውም ተፋላሚ የተለዩ ደንቦችን ወይም የይዋጣልን ፍልሚያ ልማዳዊ ደንቦችን አውቆ የጣሰና በዚሁ ያለአግባብ በተፈጸመው ድርጊት ሌላውን ተፋላሚ ያቆሰለ ወይም የገደለ እንደሆነ፤ በዚህ ሕግ ሰውን ስለመጉዳት ወይም ስለመግደል በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

BACK



## አንቀጽ ፭፻፸፱ የይዋጣልን ፍልሚያ እንዲደረግ መጠየቅ፣ ማነሣሣትና መርዳት

፩ ማንም ሰው ሌላውን ሰው ይዋጣልን ብሎ የጠየቀ ወይም እንዲህ አይነቱን ጥያቄ ያስተላለፈ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ፍልሚያው ተካሂዶ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል::

፪ ድርጊቱ በተደጋጋሚ የተፈፀመ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሦስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል::

፫ ከተፋላሚዎቹ አንዱ በገዛ ፈቃዱ ከፍልሚያው የወጣ ወይም ፍልሚያው እንዳይደረግ ያገደ ወይም የከለከለ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ ይህን ሰው ወይም ሁለቱንም ተፋላሚዎች ከቅጣት ነፃ ሊያደርግ ይችላል::

፬ ማንም ሰው በዛቻ፣ በማደፋፈር፣ ንቀቱን በመግለጽ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ አንድ ሰው ከሌላ ሶስተኛ ሰው ጋራ የይዋጣልን ፍልሚያ እንዲያደርግ ያነሣሣ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ፍልሚያው ተካሂዶ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፭ የይዋጣልን ፍልሚያውን ሂደት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ወይም ፍልሚያው የሚያስከትላቸውን መጥፎ ውጤቶች ከወዲሁ ለመግታት የተመረጡ ምስክሮች፣ የፍልሚያውን ውጤት የሚዳኙ ነባሪዎች፣ ሀኪሞች ወይም የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪዎች ተፋላሚዎች እንዲጋጠሙ ካላበረታቱ ወይም ካላነሳሱ በቀር ከዚህ በላይ በተመለከቱት ቅጣቶች አይቀጡም:: አባሪነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችም አይፈፀሙባቸውም::

## ርዕስ ሁለት

## በሰው ነፃነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### ምዕራፍ አንድ

### በሰው የግል ነፃነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፭፻፹ ዛቻ**

ማንም ሰው በሌላ ሰው ላይ ድንጋጤን ወይም ፍርሀትን በሚቀሰቅስ ሁኔታ ከባድ አደጋ ወይም ጉዳት የሚያደርስበት መሆኑን በመግለጽ ያስፈራራው እንደሆነ፣ የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ፍርድ ቤቱ ተፋተኛው ለወደፊቱ በመልካም ጠባይ እንደሚመራ የሚረጋገጫ ቃል እንዲገባና በቂ የሆነ ዋስ እንዲጠራ /አንቀጽ ፻፴፭/ ከማዘዝ የሚያግድ አይደለም::

**አንቀጽ ፭፻፹፩ የመክሰስ ወይም የማዋረድ ዛቻ**

ማንም ሰው በሌላ ሰው ላይ ወይም ከዚሁ ሰው ጋር በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ወይም በወዳጅነት በተሳሰረ ሰው ላይ የክስ አቤቱታ ወይም የወንጀል ክስ፣ ወይም ክብርን ወይም መልካም ስምን የሚነካ ፍሬ ነገር እገልጻለሁ ብሎ በመዛት ሌላው ሰው ለመልካም ሥነ ምግባር ተቃራኒ የሆነ ፍላጐቱን እንዲፈፅምለት ወይም ግዴታ እንዲገባ ያግባባ እንደሆነ፣ የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፹ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

**አንቀጽ ፭፻፹፪ ማስገደድ**

ማንም ሰው ከዚህ በላይ ባለው አንቀጽ በተመለከተው ሁኔታ በሌላ ሰው ላይ ወይም ከእርሱ ጋር በሥጋ ወይም

በጋብቻ ዝምድና ወይም በወዳጅነት በተሳሰረ ሰው ላይ በኃይል ድርጊት ወይም ከባድ አደጋ ለማድረስ በመዛት ወይም ሕገ ወጥ በሆነ ወይም በማይገባ በማናቸውም ሌላ መንገድ በተበዳዩ ነጻነት ጣልቃ በመግባት አንድን ነገር እንዲያደርግ ወይም እንዳያደርግ ወይም አንድ ነገር መደረጉን እንዲፈቅድ ወይም እንዳይፈቅድ ያስገደደ እንደሆነ፣

ከዚህ የበለጠ ከፍተኛ ቅጣት በሚወስን ከባድ ድንጋጌ ተጠያቂ ካልሆነ በቀር ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

## አንቀጽ ፭፻፹፫ የመወሰን ችሎታን ማሳጣት

፩ ማንም ሰው፣ ሌላውን ሰው ያለፈቃዱ በምትሐት፣ በአልኮል ወይም አደንዛዥ ዕፆችን ወይም ቅመሞችን ወይም የሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን በመስጠት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ በማፍዘዝ (በማደንገዝ) የዚህን ሰው የማሰብ ችሎታ ወይም የመወሰን ወይም የማድረግ ነፃነቱን የከለከለ እንደሆነ፣

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደነገሩ ሁኔታ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በተደራቢነት ሊፈፀም ይችላል /አንቀጽ ፭፻፴፪ - ፭፻፴፬/።

## አንቀጽ ፭፻፹፬ የወንጀሎች አንድ መሆን

ዛቻው፣ የኃይል ድርጊቱ፣ ማስገደዱ፣ ወይም የመወሰን ችሎታ ማሳጣቱ የተደረገ እንዲህ ዓይነቱ አድራጎት መሠረታዊ ጠባያቸው የሆነውን እንደ ውንብድና፣ በማስገደድ መጠቀም፣ ማስፈራራት (ብላክሜይል)፣ አስገድዶ መድፈር የመሳሰሉትን ወንጀሎች ለመፈጸም በማቀድ ወይም እነዚህ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ

እንደሆነ ለነዚህ ወንጀሎች አግባብነት ያለው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ ፭፻፹፭</u> <u>ከሕግ ውጭ ይዞ ማስቀመጥ</u>

፩ ማንም ሰው ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ወይም ያለ ሕጋዊ ትእዛዝ ሌላውን ሰው የያዘ፣ ያሰረ ወይም በእስረኛነት ስም ይዞ ያስቀመጠ ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ወዲያና ወዲህ እንዳይሄድ በተወሰነ ቦታ ያገደው ወይም ነፃነቱን ያሳጣው እንደሆነ፤

ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው፡-

ሀ/ በሐሰት የአእምሮ ህመም አለበት ወይም አደገኛ ነው በማለት እንደሆነ፤
ወይም

ለ/ ከሰባት ቀን በላይ ለሆነ ጊዜ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል፡፡

፫ ድርጊቱ የተፈጸመው መንግሥት፣ ዓለም አቀፍ ድርጅት፣ ግለሰብ፣ ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት አንድን ተግባር ካልፈጸመ ወይም ከመፈጸም ካልተቆጠበ በቀር በታጋቹ ሰው ሕይወት፣ አካል ወይም ነጻነት ላይ ከባድ ጉዳት እንደሚደርስ ወይም እስራቱ እንደሚቀጥል በመዛት የሆነ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፬ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተገለፀውን ወንጀል የፈጸመው የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን

እንደሆን በዚህ ሕግ የተመለከተው ልዩ ድንጋጌ አንቀጽ ፬፻፳፫ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፶፰ ሰውን መጥለፍ</u>

ማንም ሰው በኃይል ሌላውን ሰው አፍኖ የወሰደ እንደሆነ፤ ወይም ይህንኑ ድርጊት የፈጸመው በዛቻ፣ በማስገደድ፣ በተንኮል፣ በማታለል ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን የሌላውን ሰው ፈቃድ ካገኘ በኋላ እንደሆነ፤

ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፭፻፶፱ ሴትን መጥለፍ</u>

፩ ማንም ሰው አንዲት ሴትን አገባታለሁ በሚል አሳብ በኃይል የጠለፈ እንደሆነ፣ ወይም ይህንኑ ድርጊት የፈፀመው በማስፈራራት፣ በዛቻ፣ በተንኮል ወይም በማታለል ፈቃደኛ እንድትሆን ካደረገ በኋላ እንደሆነ፣

ከሶስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ የጠለፋ ድርጊቱን ተከትሎ አድራጊው ሴትየዋን አስገድዶ የደፈረ እንደሆነ፤ በዚህ ሕግ ስለአስገድዶ መድፈር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት በተጨማሪ ይቀጣል።

፫ የጠለፋውን ድርጊት ተከትሎ በጠላፊውና በተጠላፊዋ መሀከል ጋብቻ መፈጸሙ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም።

፬ ተበዳይዋ በጠለፋው ድርጊት ለደረሰባት የሕሊናና የማቴሪያል ጉዳት አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ካሣ የመጠየቅ መብቷ የተጠበቀ ነው::

## አንቀጽ ፮፻፳፰ የአእምሮ ሕመምተኛ የሆነችን ወይም የመከላከል አቅም የሌላትን ሴት መጥለፍ

ማንም ሰው ያበደችን፣ የአእምሮ ጉድለት ወይም ዝግመት ያለባትን፣ ሕሊናዋ የሳተችውን ወይም ራሷን ለመከላከል ወይም ጥቃትን ለመመለስ የማትችለውን ወይም ራሷን ለመከላከል እንዳትችል የተደረገችውን ሴት ሁኔታዋን እያወቀ አስቦ የጠለፈ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፮፻፳፱ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን መጥለፍ

፩ ማንም ሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን በኃይል አፍኖ የወሰደ እንደሆነ፤ ወይም ይህንኑ ድርጊት የፈጸመው በዛቻ፣ በማስገደድ፣ በተንኮል፣ በማታለል ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን የልጁን ፈቃድ ካገኘ በኋላ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ያበደን፣ የአእምሮ ጉድለት ወይም ዝግመት ያለበትን፣ ኅሊናው የሳተውን ወይም ራሱን ለመከላከል ወይም ጥቃትን ለመመለስ የማይችለውን ወይም ራሱን ለመከላከል እንዳይችል የተደረገውን ለአካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ሁኔታውን እያወቀ አስቦ የጠለፈ እንደሆነ፤

BACK



ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፫ ማንም ሰው የወላጁን ወይም የአሳዳሪውን የማሳደግ ወይም የመጠበቅ ሕጋዊ መብት ለማሳጣት በማቀድ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የወሰደ፣ የጠለፈ ወይም ያላግባብ ይዞ ያስቀመጠ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፬ ጥፋተኛው ለአካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ በወሰደ በሰላሳ ቀን ውስጥ ለወላጁ ወይም ለአሳዳሪው የመለሰ እንደሆነና በተከታዩ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ወንጀሉን ከሚያከብዱ ሁኔታዎች አንዱም የሌለ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ይሆናል፡፡

__አንቀጽ ፭፻፺__ __ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች__

፩ ዛቻው፣ ማስገደዱ፣ የመወሰን ችሎታን ማሳጣቱ፣ ከሕግ ውጭ ይዞ ማስቀመጡ ወይም መጥለፉ የተፈጸመው፡-

ሀ/ የማይገባ ጥቅም ከተጐጂው ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም ለግልሙትና ወይም ለአመንዝራነት ተግባር ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ ለሆነ ተግባር ለመጠቀም ወይም ለዚሁ ተግባር አሳልፎ ለመስጠት በማሰብ፤ ወይም

ለ/ ተጐጂውን ለመበዝበዝ ወይም ወጆ ለመቀበል፤ ወይም

ሐ/ የተለየ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ እንደሆነ፤

ወንጀሉ የከበደ ሆኖ ቅጣቱም በሚከተሉት ድንጋጌዎች እንደተመለከተው ይሆናል፡፡

፪ ወንጀሉ፡-

ሀ/ ዛቻ ወይም ማስገደድ /አንቀጽ ፭፻፹-፭፻፹፪/ ሲሆን ከሦስት ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት፣

ለ/ የመወሰን ችሎታን ማሳጣት ወይም ከሕግ ውጭ ይዞ ማስቀመጥ /አንቀጽ ፭፻፹፫ እና ፭፻፹፬/ ሲሆን ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት፣

ሐ/ መጥለፍ /አንቀጽ ፭፻፹፮ እና ፭፻፹፯/ ሲሆን ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት፣

መ/ የአእምሮ ሕመምተኛ የሆነችን ወይም ለመከላከል አቅም የሌላትን ሴት መጥለፍ /አንቀጽ ፭፻፹፰/ ሲሆን ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት፣ ወይም

ሠ/ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን መጥለፍ /መስረቅ/ /አንቀጽ ፭፻፹፱/ ሲሆን ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት፣

ያስቀጣል፡፡

<u>አንቀጽ ፭፻፺፩ ህፃንን ማለዋወጥ እና የራስ ያልሆነን ህፃን መውሰድ</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ፡-

BACK



ሀ/ አንድን ህፃን በሌላ ህፃን ያለዋወጠ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ እራሱ ያልወለደውን ህፃን የኔ ነው ግሎ የወሰደ እንደሆነ፣

ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል::

<u>አንቀጽ ፭፻፷፪</u> <u>ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን አለማቅረብ</u>

ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን እንዲጠብቅ አደራ የተቀበለ ማንም ሰው በሕግ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ መሠረት ልጁን እንዲረከብ መብቱ ለሆነው ሰው ወይም ተቋም አላስረክብም ያለ እንደሆነ፣

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፭፻፷፫</u> <u>ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን በሚመለከት ልዩ ሁኔታ</u>

ለአካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ የጠለፈው /አንቀጽ ፭፻፹፱/ ወይም አላቀርብም ያለው /አንቀጽ ፭፻፷፪/ ወላጅ ወይም የጉዲፈቻ አባቱ ወይም እናቱ ወይም ወደ ላይ የሚቆጠር ሌላ ወላጅ እንደሆነና ይህንንም የፈጸመው ጠ ባቂነቱን በማረጋገጥ አሳብ ብቻ ወይም ከፍ ባለ የክብር ስሜት በመነሣሣት እንደሆነ፣

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፭፻፺፬</u> <u>ከባድ ሁኔታዎች</u>

በአንቀጽ ፭፻፺፪ ወይም በአንቀጽ ፭፻፺፫ የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ለአካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አርቆ ለማኖር ወይም ከሚያምንበት ሃይማኖት ወይም ጥልቅ ለሆነው ስሜቱ ባዕድ በሆነ አካባቢ ልጁ እንዲለምድ ለማድረግ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከብር አሥር ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፭፻፺፭</u> <u>በፖለቲካ ምክንያት ሰውን መጥለፍ</u>

፩ ማንም ሰው በፖለቲካ ምክንያት በዛቻ፣ በተንኮል፣ በኃይል ድርጊት ወይም በማስገደድ ሌላውን ሰው ጠልፎ፤ በሕይወቱ፣ በአካሉ፣ ወይም በጤንነቱ ወይም በነፃነቱ ላይ አደጋ እንዲደርስበት ለማድረግ፦

ሀ/ ለአንድ ባለሥልጣን፣ ማህበር፣ ቡድን ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አሳልፎ ለመስጠት ወደ ውጭ አገር እንዲወጣ ያደረገው እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በአገር ውስጥ ለሚገኝ ለአንድ ቡድን ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በአገር ውስጥ ከሕዝብ ተገልሎ እንዲቀመጥ ያደረገው እንደሆነ፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፤

፪ ማንም ሰው ጠለፋውን ያዘዘ ወይም ያደራጀ እንደሆነ፤

ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

BACK



## አንቀጽ ፭፻፺፮ ሰውን አገልጋይ ማድረግ

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ ሌላውን ሰው አስገድዶ በተገዢነት የያዘው፣ የሸጠው፣ ያስተላለፈው፣ በመያዣነት አሳልፎ ለሌላ የሰጠው፣ የገዛው ወይም በማናቸውም ዓይነት ዘዴ የነገደበት፣ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ያዘዋወረው ወይም በጉልበቱ የተገለገለበት እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሥውር አኳኋንም ቢሆን ሰውን በባሪያ መልክ የያዘ ወይም ያስቀመጠ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት እና ከሃምሣ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ የሚገኘውን ሰው በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ወይም በውጭ አገር በመድረሻ ቦታው ለማድረስ ወይም ለማስረከብ በማቀድ አስቦ በየብስ፣ በባሕር ወይም በአየር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ ዝውውሩን የመራ ወይም የረዳ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

፫ ወንጀሉ የተደረገው በሕፃናት፣ በሴቶች፣ በአእምሮ ደካሞች ወይም በበሽተኞች ላይ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ይሆናል::

## አንቀጽ ፭፻፺፯ በሴቶችና በልጆች መነገድ

፩ ማንም ሰው ሴትን ወይም ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን የግዳጅ ሥራ እንድትሠራ (እንዲሠራ)

ለማድረግ በማሰብ በኃይል፣ በዛቻ፣ በተንኰል፣ በማታለል፣ በመጥለፍ ወይም በሴቲቱ ወይም በልጁ ላይ ኃላፊነት ላለው ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም በመስጠት ተበዳይዋን (ተበዳዩን) የመለመለ፣ በእጁ ያስገባ፣ የደበቀ፣ ከቦታ ቦታ ያዘዋወረ፣ ከአገር ያስወጣ፣ ወይም ወደ አገር ያስገባ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከሃምሣ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ ማንም ሰው በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ተባዳይ በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ወይም በውጭ አገር በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለጸው ዓላማ መሠረት አስቦ በየብስ፣ በባህር፣ ወይም በአየር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ ዝውውሩን የመራ ወይም የረዳ እንደሆነ፤

ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፭፻፺፰ በሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክ</u>

፩ ማንም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላከ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራትና ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ በዚህ ድርጊት ምክንያት የተላከችው ኢትዮጵዊት በሰብአዊ መብቷ፣ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት

እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከሃምሣ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፫ ተመሳሳይ ድርጊት በወንዶች ኢትዮጵያውያን ላይ በሚፈጸምበት ጊዜ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ ፭፻፺፱ በዚህ ርዕስ በተመለከቱት ወንጀሎች የሕገወጥ ማኅበርና የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት

፩ በዚህ ርዕስ እንደተደነገገው በሰዎች ነፃነት ላይ ወንጀል የተደረገው፣ ማለት ዛቻው፣ ተንኮሉ፣ ማስገደዱ፣ በግድ ይዞ ማስቀመጡ፣ ጠለፋው፣ በግድ አገልጋይ ማድረጉ፣ የባሪያ ሽያጩ ወይም ዝውውሩ፣ ወይም በሴቶችና በልጆች መነገዱ ወይም በሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላኩ የተፈፀመው በማናቸውም መንገድ በሰዎች ለመነገድ በተቋቋመ ቡድን ወይም ማህበር እንደሆነ፣ ቡድኑ ወይም ማህበሩ ፈርሶ ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

ይህ ቅጣት ጥፋተኞቹ በየግላቸው ለፈፀሙት ወንጀል የሚወሰንባቸውን ቅጣት አያስቀርም።

፪ ወንጀሉን የፈፀመው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ፣ እንደወንጀሉ ዓይነትና ከባድነት በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፮፻ የክትትል ወይም የቁጥጥር ጉድለት

፩ በመንግሥት የግዛት መዋቅር ውስጥ በየደረጃው የሚገኝ ባለሥልጣን በሚያስተዳድረው የግዛት ክልል ውስጥ የባሪያ ዝውውር ብዝበዛ እንዳይከናወን ወይም ከባሪያ ንግድ ጋር የተያያዙ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ

ተከታትሎ ወይም ተቆጣጥሮ ከእርሱ የሚጠበቀውን አስፈላጊ እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ከባድነት በአንቀጽ ፫፻፺፯ - ፫፻፺፱ እስከተደነገገው ከፍተኛ የገንዘብ መቀጮ ድረስ ሊቀጣ ይችላል::

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአስር ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>በሌሎች ሰዎች መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

### <u>አንቀጽ ፮፻፭</u> <u>በሲቪል መብቶች በነፃ መጠቀምን መከልከል</u>

፩ ማንም ሰው በዛቻ፣ በኃይል ድርጊት፣ በማታለል ወይም ሕገ ወጥ በሆነ በሌላ መንገድ:-

ሀ/ ሌላው ሰው በሕገ መንግስቱ ወይም በሌሎች ሕጎች ከተሰጡት የሲቪል መብቶች አንዱን በተለይም የወላጅነት ወይም የሞግዚትነት፣ የመክሰስ ወይም ፍርድ ቤት የመቅረብ መብቱን እንዳይጠቀምበት የከለከለ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ ሌላው ሰው ከእነዚህ መብቶች በአንዱ በተወሰነ አኳኋን እንዲጠቀምበት ያስገደደ እንደሆነ፣

ድርጊቱ በሌላ ግልጽ ድንጋጌ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ የሕዝባዊንና የፖለቲካ ነፃ ተግባር የመንካት ወንጀሎች ይልቁንም ድምፅ የመስጠትንና የመምረጥን መብቶች የመንካት ወንጀሎች ተደርገው እንደሆነ በተለይ ይህንኑ ጉዳይ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚዎች ይሆናሉ /አንቀጽ ፬፻፷፯/::

## <u>አንቀጽ ፭፻፺፬ የመዘዋወር ነፃነት መብትን መድፈር</u>

፩ ማንም ሰው በሕግ ሥልጣን ሳይኖረው ሌላው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ በነፃ እንዳይዘዋወር የከለከለ እንደሆነ፣
በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ጥፋተኛው የመንግሥት ሠራተኛ እንደሆነ፣ በዚህ ሕግ በተመለከተው አግባብ ባለው ድንጋጌ ይቀጣል /አንቀጽ ፬፻፳/።

## <u>አንቀጽ ፭፻፺፭ የሥራ ነፃነት መብትን መጣስ</u>

፩ ማንም ሰው በዛቻ፣ በኃይል ድርጊት፣ በማታለል ወይም በሌላ ህገወጥ መንገድ ሌላውን ሰው:-

ሀ/ አንድ የተወሰነ ሥራ ወይም የሥራ ሁኔታ እንዲቀበል፣ ወይም አሠሪው የሥራ ሁኔታዎችን እንዲቀበል ወይም እንዲያሻሽል በማሰብ ሥራ እንቢ እንዲል ወይም እንዲያቆም ያስገደደ፣ ወይም

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) የተመለከቱትን ለመፈጸም ዓላማው የሆነውን አንድ ቡድን ወይም ማኅበር እንዲቀላቀል ወይም የአንድ ቡድን አባል እንዲሆን ያስገደደ፣ ወይም ከእንዲህ ዓይነቱ ቡድን ወይም ማኅበር እንደፈለገው ወይም በፈለገው ጊዜ እንዳይወጣ የከለከለ እንደሆነ፣

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

BACK



፪ ዛቻውን ወይም የኃይል ድርጊቱን የፈጸመው ሰው ወይም የፈጸሙት ሰዎች የጦር መሣሪያዎችን ወይም ሌሎች መሣሪያዎችን የያዙ እንደሆነ ወይም የመከልከሉ ወይም የማስገደዱ ተግባር የብዙ ሰዎች ስብስብ ድርጊት እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን እሥራት ከመቀጮ ጋር ያጣምራል።

## <u>አንቀጽ ፮፻፸ የግል ቤቶችን ወይም የተከለሉ ቦታዎችን መድፈር</u>

፩ ማንም ሰው ከሕግ ውጭ:-

ሀ/ ሕጋዊ ነዋሪ የሆነው ሰው እየተቃወመ ወደ አንድ ቤት፣ ግቢ፣ ጀልባ ወይም ለመኖሪያ ወደሚያገለግል ማናቸውም ሌላ ቦታ ወይም ከቤቱ ወይም ከመኖሪያው ቦታ ጋር ወደተያያዘና ወደ ተከለለ ቦታ ወይም የአትክልት ቦታ ወይም የግል ይዞታ ወደሆነ ማናቸውም ሌላ ንብረት የገባ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ ሰው ባይኖርበትም ወደ አንድ መሥሪያ ቤት፣ድርጅት፣ ኩባንያ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ማኅበር ሕንፃ፣ ቢሮዎች፣ ግምጃ ቤት /መጋዘን/ ወይም አጥር ግቢ ሳይፈቀድለት በኃይል የገባ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ ሕጋዊ ነዋሪው ሳይቃወመው ወይም ፈቅዶለት ከገባ በኋላ እንዲወጣ ሲጠይቀው ያልወጣ እንደሆነ፣

ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ወንጀሉን ያደረገው እንዲህ ዓይነት ድርጊት እንዲፈጽም ያልተፈቀደለት ወይም ቢፈቀድለትም ሊከተለው የሚገባውን ሕግ፣ ጥንቃቄ ወይም ሥነ ሥርዓት ያልተከተለ የመንግሥት ሠራተኛ እንደሆነ፤ በተለይ የተደነገገው ድንጋጌ /አንቀጽ ፬፻፳፪/ ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ ፮፻፭ ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች

ወንጀሉ የተፈፀመው:-

ሀ/ መሣሪያ በመያዝ፣ በመዛት ወይም በኃይል ድርጊት በመጠቀም ሲሆን፤ ወይም

ለ/ በጋራ በተስማሙ የሰዎች ስብስብ ሲሆን፤ ወይም

ሐ/ በሌላ አኳኋን በሕግ የተፈቀደው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት እስከ ጧቱ ፲፪ ሰዓት ባለው ጊዜ ሲሆን፤ ወይም

መ/ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን መስሎ በመቅረብ ሲሆን፣

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

## አንቀጽ ፮፻፮ የመጻጻፍ ወይም የግንኙነት ግላዊነት መብትን መድፈር

፩ ማንም ሰው በሕግ ሳይፈቀድለት:-

ሀ/ የርሱ ያልሆነውን የሥራ /የመሥሪያ ቤት/ የጉዳይ ማስፈጸሚያ ወይም የግል የሆነ ዝግ ወይም ግልፅ የደብዳቤ /የፖስታ/ ወይም የመጻጻፍ፣ የቴሌግራም፣ የስልክ /የቴሌፎን/፣ የኤሌክትሮኒክ ወይም የቴሌኮሙኒ ኬሽን ወይም በማናቸውም ሌላ

ዘዴ የሚደረግ ግንኙነትን፣ የንግድ ወይም የግል የሆነ የተዘጋ ደብዳቤን ወይም ኤንቬሎፕን ወይም አንድን ጥቅል፣ የታሸገ ጥቅል ዕቃን /ኮሊ/ ወይም ማናቸውንም የተላከ ነገር አስቦ የከፈተ ወይም ውስጡ ያለውን ነገር ያወቀ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ለእርሱ ያልተላከውን እንደዚህ ዓይነቱን ደብዳቤ ወይም የታሸገ ጥቅል /ኮሊ/ በስህተት ወይም በቸልተኛነት በመክፈት አንዳንድ ነገሮችን ከአወቀ በኋላ ለሌላ ሰው ያሳወቀ ወይም ጥቅም ያገኘበት እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው አስቦና ህገወጥ በሆነ መንገድ እንደዚህ ዓይነቱን ደብዳቤ ወይም የሚላክ ዕቃ ወደተላከበት አድራሻ እንዳይደርስ ያቋረጠ ወይም ያስቀረ፣ ወደ ሌላ አድራሻ እንዲደርስ ያደረገ ወይም ያወደመ እንደሆነ፤ ድርጊቱ የበለጠ ቅጣት በሚያስከትል ድንጋጌ የሚያስጠይቅ ካልሆነ በቀር በወንጀል ክስ አቅራቢነት ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፫ በመንግሥት ሠራተኞች ስለሚፈጸሙ የሥራ ምስጢርን ስለመግለጽ፣ በአደራ በተሰጠ ዕቃ ያለአግባብ ስለማዘዝ እና በሥራ ተግባር ስለሚፈጸም የመውሰድና የመሠወር ወንጀሎች የተመለከቱት ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፫፻፺፯፣ ፬፻፲፪ እና ፬፻፲፫/ እንደተጠበቁ ናቸው::

## ርዕስ ሦስት
## በክብር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች
## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፮፻፲፫ መርህ

፩ የጥፋተኛው ወይም የተበዳዩ ማኅበራዊ የኑሮ ደረጃ ወይም ማዕረግ ምንም ቢሆን፤ ከዚህ በታች ባሉት ድንጋጌዎች በተመለከቱት ሁኔታዎች በአንዱ፤ በክብር ወይም በመልካም ዝና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ያስቀጣሉ፡፡

ወንጀሎቹ በተፈጥሮ ሰዎች ወይም ሕጋዊ ሰውነት በተሰጣቸው አካላት ላይ ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡ የተፈጥሮ ሰዎችን በሚመለከት ወንጀሎቹ በሕያዋን፣ በሙታን ወይም የመጥፋት ውሣኔ በተሰጠባቸው ሰዎች ላይ ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡

፪ ፍርድ ቤቱ ለእነዚህ ለተለያዩ ወንጀሎች ቅጣትን የሚወስነው የወንጀሉን ከባድነት፣ የተበዳዩን ሁኔታ፣ የወንጀሉን በሰፊው መታወቅ ወይም መሠራጨት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

### አንቀጽ ፮፻፲፬ ወንጀሉ የሚፈፀምባቸው ዘዴዎች

ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ የሆኑ ክብርን ወይም መልካም ስምን የመጉዳት ወንጀሎች በቃል፣ በድምፅ፣ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በስዕል፣ በምልክት፣ በጥቅሻ ወይም በአካላዊ ሁኔታ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡

BACK



በማናቸውም መንገድ በማስመዝገብ፣ በማብዛት፣ በማስተላለፍ፣ በማስታወቅ ወይም በግልፅ በማሣየት፣ በመጻፍ፣ በሚታይ ወይም በሚሰማ በማናቸውም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ወንጀሉ የሚፈጸምበት ወይም ነገሩ የሚነዛበት ዘዴ፣ ከመደበኛውና ቀጥተኛው የወንጀሉ መፈፀሚያ ዘዴ ጋር በእኩል ይታያል::

## አንቀጽ ፤፻፱ ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው አካል ወንጀሉ ሲፈፀም የሚወሰን ቅጣት

፩ ወንጀሉ የተፈፀመው ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት ሲሆን የሚወሰንበት ቅጣት መቀጮ ይሆናል::

፪ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው አካል ላይ የሚወሰነው ቅጣት፣ ይህንኑ ወንጀል በግሉ ለመፈጸሙ የተረጋገጠበት የዚሁ አካል ሥራ አስኪያጅ፣ ዳይሬክተር፣ አስተዳዳሪ፣ ተቆጣጣሪ፣ እንደራሴ፣ ወኪል ወይም ሌላ አባል እንዳይቀጣ አያግድም::

## አንቀጽ ፤፻፲ ካሣ

፩ ተበዳዩ ለደረሰበት ቁሣዊ ወይም የህሊና በደል የሚሰጠው ካሣ በፍርድ ቤት የሚወሰነው በዚህ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፻፩/ መሠረት የበደሉን ከባድነትና መጠን እንዲሁም የጥፋተኛውንና የተበዳዩን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል::

፪ በፍርድ ቤት የሚታዘዘው የኅሊና /ሞራል/ ካሣ በተለይም ፍርዱን፣ የፍርዱን አንድ ክፍል ወይም የፍርዱን ተፈጻሚ ክፍል /አንቀጽ ፻፶፫/ በማስታወቂያ በማውጣት /በማሳተም/ ለሕዝብ በማሳወቅ የሚደረግ ሲሆን በተመሣሣይ መንፈስ

BACK



መወሰንና በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ከሚያስፈልገው የጥበቃ መጠን መስማማት ይኖርበታል።

## አንቀጽ ፮፻፲፩ ያለመከሰስ መብት

በሕገ መንግሥት የተቋቋሙ የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈፃሚ ወይም የፍርድ ባለሥልጣን አባሎች በተግባራቸው መሠረት እና መደበኛ ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ በሚሰጧቸው ወይም በሚያደርጓቸው በአሠራራቸው /በፎርማቸው/ ትክክለኛ በሆኑ መረጃዎች ወይም ንግግሮች ክብር ነክተዋል በማለት ሊከሰሱ አይቻልም።

## አንቀጽ ፮፻፲፪ የማያስቀጡ ትችቶችና ንግግሮች

እንደ ስም ማጥፋት ወይም ክብር መንካት ተቆጥረውም የማያስቀጡት:-

ሀ/ በግለሰብ ተሰጥኦ፣ የሙያ ተግባር ወይም ማኅበራዊ እንቅስቃሴ፣ የስነ ጥበብ፣ የስነ ጽሁፍ ወይም ሳይንሳዊ ፈጠራ ወይም ሥራ በተገቢና በተለሳለሰ ቃል የሚሰጡ የተጤኑ አስተያየቶች ወይም መሠረት ያላቸው ሂሶች፤ ወይም

ለ/ የተባሉት ነገሮች ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸውና በተግባሩ ውስጥ ሆነው የተነገሩትም ክብርን ለመንካት በማሰብ ሳይሆን ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ በተለይም በምርመራ፣ ሪፖርት በማድረግ ወይም የምስክርነት ቃልን በመቀበል፣ በፍርድ ቤት ወይም በአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ፊት በመከራከር፣ በተፈቀደ የመንግሥት የመረጃ ግልጋሎት ጊዜ በመንግሥት ሠራተኛ፣ በጠበቃ ወይም ነገረ ፈጅ፣ በልዩ ዐዋቂ ወይም ምስክር፣ በጋዜጠኛ ወይም በማንኛውም ሌላ ሰው በቅን ልቦና የሚደረጉ ወይም

ተደግመው የሚነገሩ ንግግሮች፣ መግለጫዎች ወይም አስተያየቶች፤

ናቸው::

## ምዕራፍ ሁለት
## ልዩ ድንጋጌዎች፤ ክብርን መንካት

**አንቀጽ ፮፻፲፫ ስም ማጥፋት እና የሐሰት ሐሜት**

፩ ነገሩ እውነት ሆኖ እና የሌላ ሰውን ክብር ወይም መልካም ስም ለመጉዳት በማሰብ ሌላው ሰው እንደዚህ ያለውን ሥራ ሠርቷል፣ እንደዚህ ያለውን ነገር አድርጓል፣ እንደዚህ ያለ መጥፎ ነገር አለበት በማለት ለሦስተኛ ወገን ያስታወቀ ወይም የገለፀ ማንም ሰው፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በስም ማጥፋት ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

አንድ ሰው በፍርድ መሠረት ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ በትን ወይም በአግባቡ የተቀጣበትን ወይም ይቅርታ ወይም ምህረት ያገኘበትን ወንጀል በመጥቀስ መናገር ወይም መግለፅ ስም እንደማጥፋት ተቆጥሮ ከላይ በተመለከተው ቅጣት መሠረት ያስቀጣል::

፪ የተወራው ወይም የተገለፀው ነገር ሐሰት መሆኑ እየታወቀ ድርጊቱ ተፈፅሞ እንደሆነ፤ ጥፋተኛው የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በሐሰት ሐሜት ከአንድ ወር በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፫ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው በመልካም ስም ላይ ከባድ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ እንደሆነ፤ ተበዳዩ የግል አቤቱታ ሲያቀርብ ቅጣቱ ከሶስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራትና መቀጮ ይሆናል::

BACK



፬ የተነገረው ወይም የተገለፀው ነገር ሐሰት ሆኖ፣ በቸልተኛነት ድርጊቱ ተፈፅሞ እንደሆነ፤ የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል::

፭ በባለሥልጣን ዘንድ ሰውን በሐሰት መወንጀል ወይም መክሰስ በአንቀጽ ፬፻፵፯ መሠረት የሚያስቀጣ በመሆኑ በስም ማጥፋት ወንጀል በተደራቢነት አያስቀጣም::

## አንቀጽ ፮፻፲፬ እውነትንና ከፍ ያሉትን ጥቅሞች ስለመጠበቅ የሚደረገው ልዩነት

፩ ስም በማጥፋት የተከሰሰ ሰው ለመጉዳት በማቀድ አልተናገርሁም፣ ወይም የተናገርሁት ባላምንበትም እንኳ ሌላ ሰው የተናገረውን ወይም ሕዝብ የሚያውቀውን ነው ወይም በጥርጣሬ ወይም ሳይሆን አይቀርም በማለት ነው ብሎ በጠቅላላው ለመከላከል አይችልም::

፪ ጥፋተኛው የተናገረው ወይም የገለፀው እውነት ሆኖ ወይም እውነት መሆኑን ለማወቅ በቂ ምክንያት ኖሮት ድርጊቱን በሚፈፅምበት ጊዜ:-

ሀ/ የሌላውን ሰው ስም ለማጥፋት ወይም ክብር ለመጉዳት ሐሳብ ያልነበረው መሆኑን፤ ወይም

ለ/ ተገቢ ለሆነ ጠቅላላ የሕዝብ ጥቅም ወይም ከፍ ላለ ጥቅም ወይም ሞራላዊ ዓላማ መሆኑን፤

ያስረዳ እንደሆነ በስም ማጥፋት ወንጀል አይቀጣም::

፫ አድራጊው የተከሰሰው በሐሰት ሐሜት /ካለምኒ/ ክስ እንደሆነ ፤ የሕዝብ ጥቅምን ወይም ከፍ ያለ ሌላ

ጥቅምን በመጥቀስ በማናቸውም ሁኔታ ከቅጣት ሊያመልጥ አይችልም::

## አንቀጽ ፮፻፲፭ ስድብና ማዋረድ

ድርጊቱ በደንብ መተላለፍ /አንቀጽ ፳፻፵፬/ መሠረት ካላስቀጣ በቀር ማንም ሰው ተበዳዩን በቀጥታ በመናገር ወይም በአሽሙር በስድብ ክብሩን የነካ ወይም በምልክት ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ያዋረደ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

## አንቀጽ ፮፻፲፮ መቀስቀስ እና አፀፋ መመለስ

፩ በመሳደብ ወይም በማዋረድ የተከሰሰ ሰው ይህን ድርጊቱን በይቅርታ እንዲታለፍ በሚያደርግ በራሱ ላይ ብቻ ሳይሆን በሦስተኛ ወገኖች ላይም እንኳ ቢሰነዘር እጅግ አሳፋሪ፣ አስጸያፊ ወይም አስቀያሚ ትችት፣ ሊሆን በሚችል ተግባር ወይም ድርጊት ተቀስቅሶ ወይም ተገፋፍቶ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ላይወስንበት ይችላል::

፪ ተበዳዩ ለደረሰበት ስድብ ወይም ማዋረድ በእርሱ ላይ በተፈጸመው አደራረግ ዓይነት ወዲያውኑ አፀፋውን የመለሰ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ሁለቱንም ጥፋተኞች ወይም ከሁለቱ አንዱን ብቻ ከቅጣት ነፃ ለማድረግ ይችላል::

## አንቀጽ ፮፻፲፯ ቃልን ማንሣት እና መፀፀት

፩ ነገሩ በፍርድ ቤት እየታየ ባለበት ጊዜ፣ ክብር በመንካት የተከሰሰ ሰው ድርጊቱን የፈፀምሁት ያለአግባብ ነው ሲል ፀፀቱን በጽሁፍ ወይም በቃል

ለፍርድ ቤቱ የገለጸ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ለማቃለል ይችላል /አንቀጽ ፻፹፱/::

፪ ይህም በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው አግባብ ላለው ጉዳይ ሁሉ ያውለው ዘንድ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ያልኩትን አንስቻለሁ አጥፍቻለሁም በማለት ጸጸቱን የገለጸ መሆኑን የሚያሳይ የጽሁፍ ማረጋገጫ ለተበዳይ ሊሰጥ ይገባል::

## አንቀጽ ፮፻፲፰ ወንጀሉን የሚያከብዱ ልዩ ሁኔታዎች

፩ ስም ማጥፋቱ፣ የሐሰት ሐሜቱ /ካለምኒ/፣ ስድቡ ወይም ማዋረዱ የሥራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ የመንግሥት ሠራተኛ ላይ ወይም ከመንግሥት ተግባሩ ጋር በተያያዘ መንገድ ታስቦ ተፈፅሞ እንደሆነ፤ የግል አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ:-

ሀ/ ወንጀሉ ስድብ ወይም ማዋረድ ሲሆን፣ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ፤

ለ/ ወንጀሉ ስም ማጥፋት ሲሆን፣ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራትና በመቀጮ፤ ወይም

ሐ/ ወንጀሉ የሐሰት ሀሜት ሲሆን፣ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ፤ ወይም

መ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በተበዳዩ መልካም ስም ላይ ከባድ ጉዳት ለማድረስ በማቀድ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት እና በመቀጮ፤ ይቀጣል::

፪ በዚህ ሕግ የአገሪቱን ክብር ስለመንካት /አንቀጽ ፪፻፵፬/፣ የውጭ አገር መንግሥትንና በመንግሥታት መካከል የተቋቋሙ ድርጅቶችን ስለማዋረድ /አንቀጽ ፪፻፷፩ እና ፪፻፷፪/፣ የበላይ የወታደር ሹምን ስለመስደብ /አንቀጽ ፪፻፺፯/ እና ፍርድ ቤትን ስለመድፈር /አንቀጽ ፬፻፵፱/ የተመለከቱት ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው::

<u>አንቀጽ ፮፻፲፱ የጠፉ ወይም የሞቱ ሰዎችን ክብር የመንካት ወንጀል ሲፈፀም ክስ የሚቀርብበት ሁኔታ</u>

፩ በዚህ ምዕራፍ መሠረት ከሚያስቀጡት የክብር መንካት ወንጀሎች አንዱ የተፈጸመው በሞተ ወይም መጥፋቱ በተረጋገጠ ሰው ላይ እንደሆነ፤ የግል አቤቱታን ለማቅረብ መብት ያላቸው የሥጋ ወይም የጉዲፈቻ ልጆቹ፣ የትዳር ጓደኛው እነዚህም የሌሉ እንደሆነ፤ የሥጋ ወይም የጉዲፈቻ ወላጆች እንዲሁም ወንድሞችና እህቶች ይሆናሉ::

፪ የግል ክብርን ስለመንካት የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ይርጋ በመደበኛ የይርጋ ድንጋጌዎች ይመራል::

የተጐጂውን ሰው መታሰቢያ ክብር ነክተዋል የተባሉት ነገሮች ወደ ታሪካዊ፣ ኪነ-ጥበባዊ፣ ስነ-ፅሁፋዊ ወይም ሣይንሳዊ ዘርፍ የተዛወሩ ማናቸውም አይነት ህዝባዊ ክንውኖችን የሚመለከቱ እንደሆነ፤ የሚያስወነጅለው ድርጊት በተፈጸመ ጊዜ ተበዳይ ከሞተ ወይም መጥፋቱ ከተረጋገጠ ቢያንስ ሠላሳ ዓመት ካለፈ በኋላ የግል አቤቱታው ተቀባይነት የለውም::

BACK



## ርዕስ አራት

## በመልካም ጠባይ እና በቤተዘመድ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ምዕራፍ አንድ

## በመልካም ጠባይ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ክፍል አንድ

## በግብረ ሥጋ ነፃነትና ንፅህና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፮፻፳** **አስገድዶ መድፈር**

፩ ማንም ሰው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ህሊናዋን እንድትስት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ መከላከል እንዳትችል በማድረግ ከጋብቻ ውጭ አስገድዶ ከአንዲት ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው፦

ሀ/ ዕድሜዋ አሥራ ሦስት ዓመት ሆኖ አሥራ ስምንት ዓመት ባልሞላት ሴት ልጅ ላይ ሲሆን፤ ወይም

ለ/ በጥፋተኛው መሪነት፣ ቁጥጥር ወይም ሥልጣን ሥር በሆነ የመጠሪያ ቤት፣ የመማጠኛ ቦታ፣ የሕክምና፣ የትምህርት፣ የጠባይ ማረሚያ፣ የመታሠሪያ ወይም የተያዙ ሰዎች መቆያ ተቋማት ውስጥ በምትገኝ ወይም በተከሳሹ ጥበቃ ወይም ቁጥጥር ስር በምትገኝ ወይም የእሱ ጥገኛ በሆነች ሴት ላይ ሲሆን፤ ወይም

ሐ/ በዕድሜ መግፋት፣ በአካል ወይም በአእምሮ ሕመም፣ በመንፈስ ድክመት ወይም በማናቸውም

BACK


ሌላ ምክንያት የድርጊቱን ምንነት /ባህርይ/ ወይም ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለይታ ለማወቅ ወይም ለመከላከል በማትችል ሴት ላይ ሲሆን፤ ወይም

መ/ በጭካኔ ወይም በማሰቃየት፣ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ወንዶች ህብረት ሲሆን፤

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እሥራት ይሆናል።

፫ አስገድዶ መድፈሩ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ቅጣቱ የዕድሜ ልክ እስራት ይሆናል።

፬ ከአስገድዶ መድፈሩ ወንጀል ጋር ተያይዞ ተበዳዩዋን ከሕግ ውጭ ይዞ የማስቀመጥ ወይም የመጥለፍ ወንጀል የተደረገ ወይም ተበዳይዋ በወንጀሉ ምክንያት በሽታ የተላለፈባት ሲሆን፣ አግባብነት ያላቸው የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ ፮፻፳፩ <u>አንድን ወንድ አስገድዶ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ማድረግ</u>

አንዲት ሴት አንድን ወንድ አስገድዳ ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈፅም ያደረገች እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ትቀጣለች።

አንቀጽ ፮፻፳፪ በንፅህና ክብር <u>ላይ የሚፈፀም የኃይል ድርጊት</u>

ማንም ሰው ተቃራኒ ጾታ ያለውን ሰው በኃይል፣ በብርቱ ዛቻ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ መቃወም እንዳይችል ካደረገው በኋላ ግብረ ሥጋ ግንኙነት የመሰለን ተግባር ወይም ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ለንጽሕና ክብር ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንዲፈጽም ወይም ለመፈጸም እሺ እንዲል ያስገደደ እንደሆነ፣

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፮፻፳፫ አእምሮአቸውን በሳቱ ወይም የአእምሮ ደካማ በሆኑ ወይም ለመቃወም</u>
<u>በማይችሉ ሰዎች ላይ የሚፈፀም የክብረ ንፅህና ድፍረት በደል</u>

ማንም ሰው የተበዳዩን ችሎታ ማጣት እያወቀ በኃይል ወይም በዛቻም ሳይሆን አእምሮውን ካጣ፣ የአእምሮ ደካማ ወይም ዘገምተኛ ከሆነ፣ ከእብድ ወይም አእምሮውን ከሳተ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት የድርጊቱን ምንነት ወይም ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለይቶ ለማወቅ ከማይችል ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ ወይም ይህን መሰል ወይም ሌላ ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፮፻፳፬ ሆስፒታል ውስጥ በተኙ፣ በተጋዙ ወይም በታሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈፀም የክብረ ንፅህና ድፍረት በደል</u>

ማንም ሰው ሹመቱን፣ ሥልጣኑን ወይም ማዕረጉን በመጠቀም በእርሱ መሪነት፣ ቁጥጥር ወይም ሥልጣን ስር በሚተዳደር ወይም ሆስፒታል፣ መጠሪያ ቤት ወይም ስደተኛ ሰፈር ወይም በማናቸውም የመልካም አስተዳደግ ትምህርት መስጫ፣ ጠባይ ማረሚያ፣ የግዞት ወይም የእሥራት ተቋማት ወይም በታዎች ውስጥ ከሚገኝ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ ወይም ይህን መሰል ወይም ሌላ ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፣

BACK



እንደነገሩ ሁኔታ ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

<u>አንቀጽ ፮፻፳፭ አንድ ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነትዋን ምክንያት በማድረግ የሚፈፀም ድርጊት</u>

ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ ማንም ሰው ባንዲት ሴት ላይ የደረሰውን ከፍ ያለ ቁሣዊ ችግር ወይም የኅሊና ኀዘን ምክንያት በማድረግ ወይም በጠባቂነት፣ በአስተማሪነት፣ በአሳዳሪነት፣ በአሠሪነት ወይም ይህን በመሰለ በማናቸውም ሌላ ግንኙነት ምክንያት ያገኘውን ሥልጣን፣ ኃላፊነት ወይም ችሎታ በመጠቀም ከተባለችው ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ አይነት ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

<u>አንቀጽ ፮፻፳፮ ዕድሜያቸው አስራ ሦስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል</u>

፩ ማንም ሰው ተቃራኒ ጾታ ካላት፣ ዕድሜዋ ከአስራ ሦስት ዓመት በላይ ሆኖ አሥራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ይህችው ልጅ እንዲህ አይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈጽም ያደረገ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ አንዲት ሴት ዕድሜው አስራ ሦስት ዓመት ሆኖ አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ከእርስዋ ጋር

BACK



የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ያደረገች እንደሆነ፣

እስከ ሰባት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ትቀጣለች::

፫ ማንም ሰው ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ጾታ ባለውና ዕድሜው አስራ ሦስት ዓመት ሆኖ አሥራ ስምንት ዓመት ባልሞላው ልጅ ላይ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነውን ማናቸውንም ሌላ አይነት ድርጊት የፈጸመ ወይም ይኸው ልጅ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት እንዲፈጽም የገፋፋ ወይም አስቦ በዚሁ ልጅ ፊት እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፤

ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፬ ተበዳዩ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው በአደራ የተሰጠው ልጅ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ:-

ሀ/ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀውን ወንጀል በሚመለከት ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ይሆናል፤

ለ/ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፀውን ወንጀል በተመለከተ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ይሆናል::

BACK



ሐ/ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተገለፀውን ወንጀል በተመለከተ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

፰ ወንጀሉ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን አስከትሎ እንደሆነ፤ አግባብነት ያለው የዚህ ሕግ ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈፃሚ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፮፻፳፯ በሕፃናት ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል</u>

፩ ማንም ሰው ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ጾታ ካላት፣ ዕድሜዋ አስራ ሦስት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ይህችው ልጅ እንዲህ አይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈጽም ያደረገ እንደሆነ፣

ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት
ይቀጣል::

፪ አንዲት ሴት ዕድሜው አስራ ሦስት ዓመት ያልሞላው ልጅ ከእርስዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ያደረገች እንደሆነ፣

ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ትቀጣለች::

፫ ማንም ሰው ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ጾታ ባለውና ዕድሜው አስራ ሦስት ዓመት ባልሞላው ልጅ ላይ የግብረሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነውን ማናቸውንም ሌላ አይነት ድርጊት የፈጸመ ወይም ይኸው ልጅ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት እንዲፈጽም የገፋፋ ወይም አስበ

በዚሁ ልጅ ፊት እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፣

ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፬ ተበዳዩ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሰራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው በአደራ የተሰጠው ልጅ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ፦

ሀ/ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀውን ወንጀል በሚመለከት፣ ወንጀሉ በሌላ ሰው ከሚፈፀምበት ጊዜ ይልቅ በዚህ ዓይነቱ ሰው ላይ ቀጣቱ ይከብዳል።

ለ/ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፀውን ወንጀል በተመለከተ፣ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ይሆናል።

ሐ/ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተገለፀውን ወንጀል በተመለከተ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ይሆናል።

፭ ድርጊቱ በተጐጂ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ፣ ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፮፻፳፰</u> <u>ወንጀሉን የሚያከብዱ ሌሎች ምክንያቶች</u>

የአስገድዶ መድፈር ወይም የግብረ ሥጋ በደልን የሚመለከት ማናቸውም ሌላ ወንጀል በሚፈጸምበት ጊዜ (አንቀጽ ፮፻፳ - ፮፻፳፯) አግባብነት ያለው ድንጋጌ ከፍ ያለ ቅጣት ካላስቀመጠ በቀር ከአምስት

ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣው:-

ሀ/ ተበዳይዋ ያረገዘች እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በአባለዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ተበዳይ ዋን/ተበዳዩን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ ተበዳይዋ/ተበዳዩ ከደረሰባት/ከደረሰበት ከባድ ኅዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሣ ራሷን/ ራሱን የገደለች/የገደለ እንደሆነ፣

ነው::

## ክፍል ሁለት

## ለተፈጥሮ ባሕርይ ተቃራኒ የሆኑ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶች

### አንቀጽ ፮፻፴፱ ግብረሰዶም እና ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ድርጊቶች

ማንም ሰው ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ፆታ ካለው ከሌላ ሰው ጋር ግብረሰዶም ወይም ለንፅህና ክብር ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነውን ሌላ ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

### አንቀጽ ፮፻፵ ወንጀሉን የሚያከብዱ ጠቅላላ ሁኔታዎች

፩ ጥፋተኛው:-

ሀ/ የሌላውን ሰው የገንዘብ ችግር ወይም የኅሊና ኅዘን፣ ወይም የዚህ ሰው አሣዳሪ፣ ሞግዚት፣ ጠ ባቂ፣ አስተማሪ፣ አሠሪ፣ ወይም ቀጣሪ በመሆኑ ያገኘውን ሀላፊነት፣ ሥልጣን፣ ወይም ችሎታ፣ ወይም በመካከላቸው ያለውን ይህን የመሰለ ሌላ

ግንኙነት ያለአግባብ በመጠቀም ከላይ በአንቀጽ ፮፻፳፱ የተመለከተውን ድርጊት የፈፀመበት ወይም ይኸው ሰው ከእርሱ ጋር የዚህ ዓይነቱን ድርጊት እንዲፈጸም ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በዚህ ሕግ /አንቀጽ ፺፪/ በተደነገገው መሠረት ድርጊቱን ሞያው አድርጎ የያዘ እንደሆነ፣

ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከባድ ሁኔታ ሲያጋጥም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት የሚሆነው:-

ሀ/ ጥፋተኛው በኃይል፣ በዛቻ ወይም በማስገደድ፣ በተንኮል ወይም በማታለል የተጠቀመ ወይም የተጐጂውን መከላከል አለመቻል፣ አቅም ማጣት፣ ወይም የአእምሮ ድክመት/ዝግመት ወይም ሕሊና መሳት ያለአግባብ የተጠቀመ፣ ወይም

ለ/ ጥፋተኛው ተበዳዩን (ተበዳይዋን) ያሰቃየው ወይም የጭካኔ ድርጊት የፈፀመበት (የፈፀመባት)፣ ወይም እንዳለበት የሚያውቀውን የአባለዘር በሽታ ያስተላለፈበት (ያስተላለፈባት) እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ ተጐጂው (ተጐጂዋን) ከጭንቀት፣ ከሀፍረት ወይም ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ ራሱን የገደለ እንደሆነ፣

ነው።

<u>አንቀጽ ፮፻፳፮ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ልጆች ላይ የሚፈጸሙ የግብረሰዶም ጥቃትና ለክብረ ንጽህና ተቃራኒ የሆነ ሌላ ድርጊት</u>

፩ ማንም ሰው ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ባለውና ለአካለመጠን ባልደረሰ ልጅ ላይ የግብረሰዶም ጥቃት የፈፀመ እንደሆነ፣

BACK


ሀ/ የተበዳዩ ዕድሜ አስራ ሦስት ዓመት ሆኖ አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ሲሆን፣ ከሦስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት፤

ለ/ የተበዳዩ ዕድሜ ከአስራ ሦስት ዓመት በታች ሲሆን፣ ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት፤

ይቀጣል።

፪ አንዲት ሴት ለአካለ መጠን ባልደረሰች ልጅ ላይ የግብረሰዶም ጥቃት የፈፀመች እንደሆነ፤ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ትቀጣለች።

፫ ማንም ሰው ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ባለውና ለአካለ መጠን ባልደረሰ ልጅ ላይ ማናቸውንም ዓይነት ሌላ ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፤ በቀላል እስራት ይቀጣል።

፬ ተበዳዩ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሰራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው የተሰጠው ልጅ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ፦

ሀ/ የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌን በተመለከተ፣ ወንጀሉ በሌላ ሰው ከሚፈፀምበት ጊዜ ይልቅ በዚህ ዓይነቱ ሰው ላይ ቅጣቱ ይከብዳል፤

ለ/ የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌን በተመለከተ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ይሆናል፤

ሐ/ የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌን በተመለከተ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እስራት ይሆናል::

፭ ድርጊቱ በተበዳዩ ላይ ሞትን ወይም ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ፣ ወይም ተበዳዩ (ተበዳዩዋ) ከጭንቀት፣ ከሀፍረት ወይም ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ ራሱን (ራስዋን) የገደለ (የገደለች) እንደሆነ፤ ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፮፻፴፪ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ለአካለመጠን ባልደረሱ ልጆች</u>

<u>የንጽሕና ክብር ላይ በሚፈጸም የድፍረት በደል ያለው ተካፋይነት</u>

ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን ለማሣደግ፣ ለማስተማር፣ ለማሰልጠን ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለመንከባከብ የተቋቋመ ድርጅት ሃላፊ፣ ሠራተኛ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው በዚህ ዓይነቱ ድርጅት ውስጥ በሚገኝ ልጅ ላይ፣ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፮፻፳፯ - ፮፻፳፱ እና በአንቀጽ ፮፻፴፩ ከተመለከቱት ድርጊቶች አንዱን የፈፀመ ሲሆንና የድርጅቱ አሠራር ወይም አስተዳደር ለወንጀሉ አፈፃፀም ምቹ ሁኔታን የፈጠረ እንደሆነ፤ ወይም ድርጊቱ የተፈጸመው ድርጅቱ በቂ ጥበቃ ባለማድረጉ እንደሆነ፤

እንደየወንጀሉ ዓይነትና ከባድነት በዚህ ሕግ አንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል::

አንቀጽ <u>፮፻፴፫ በእንስሳት ላይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም</u>

ማንም ሰው በእንስሳት ላይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ እንደሆነ፣

BACK



በቀላል እሥራት ይቀጣል።

## ክፍል ሦስት
## በሌሎች የሥነ-ምግባር ብልሹነት መጠቀም

**አንቀጽ ፮፻፴፬ የሌላውን ሰው የዝሙት ድርጊት የዘወትር መጠቀሚያ ማድረግ**

ማንም ሰው ጥቅም ለማግኘት ሲል የሌላውን ሰው የዝሙት ድርጊት የዘወትር መጠቀሚያው አድርጐ የያዘ፣ ሌላውን ሰው ለዝሙት ድርጊት ያቀረበ ወይም ያቃጠረ፣ ቤቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለዚሁ ተግባር ያዋለ ወይም ያከራየ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የሌላውን ሰው የዝሙት ድርጊት የዘወትር መጠቀሚያ አድርጐ የያዘ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

**አንቀጽ ፮፻፴፭ ሴቶችንና ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት አዳሪነት በማቃጠር መነገድ**

ማንም ሰው ለጥቅም ሲል ወይም የሌላውን ሰው ፍትወተ ሥጋ ለማርካት:-

ሀ/ በፈቃዳቸውም ቢሆን በዝሙት አዳሪነት እንዲሰማሩ በማነሳሳት፣ በማባበል፣ በማቅረብ ወይም በማናቸውም ዘዴ በመገፋፋት ሴቶችን ወይም ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን በማቃጠር የነገደ ወይም ከቦታ ቦታ ያዟዟረ፤ ወይም

ለ/ የተባለውን ሰው ለዝሙት ለማቅረብ በዝሙት አዳሪ ቤት ያስቀመጠ፤

እንደሆነ፤ በተለይ ከሕግ ውጭ በግድ ይዞ የማስቀመጥ ድርጊት አብሮ በተፈጸመ ጊዜ ከበድ ያሉ የቅጣት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከአሥር ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፮፻፴፮</u> <u>ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች</u>

ሞያ ተብሎ በተያዘ ሰዎችን ለዝሙት የማቅረብ ወይም ከቦታ ቦታ የማዟዟር ሥራ፦

ሀ/ ተበዳዩ ለአካለ መጠን ያልደረሰ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ተበዳዩ የወንጀለኛው ሚስት ወይም ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ፣ የጉዲፈቻ ልጅ፣ የሚስቱ፣ የወንድሙ ወይም የእህቱ ልጅ፣ በሞግዚትነት የሚጠብቀው ልጅ ወይም በማናቸውም ምክንያት እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው በአደራ የተሰጠው እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ወንጀለኛው ድርጊቱን የፈፀመው የተበዳዩን የገንዘብ ችግር ወይም የኅሊና ኀዘን ወይም በዚህ ሰው ላይ ያለውን የጠባቂነት፣ የአሠሪነት፣ የአስተማሪነት፣ የአከራይነት ወይም የአበዳሪነት ወይም ይህን የመሰለውን ሌላ ሥልጣኑን ምክንያት በማድረግ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ ወንጀለኛው በተንኮል፣ በማታለል፣ በኃይል፣ በዛቻ ወይም በማስገደድ ተጠቅሞ ወይም በተበዳዩ ላይ ያለውን ሥልጣን ያለአግባብ ተገልግሎ እንደሆነ፤ ወይም

ሠ/ ተበዳዩ ማቃጠርን የሙያ ሥራ አድርጐ ለያዘ ሰው ተላልፎ የተሰጠ እንደሆነ ወይም ወደ ውጭ

አገር ተወስዶ ወይም ወሬው፣ አድራሻው ወይም መኖሪያ ቦታው ሊታወቅ ያልተቻለ እንደሆነ፤ ወይም

ረ/ ተበዳዩ ከኃፍረት፣ ከጭንቀት ወይም ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ ራሱን ለመግደል ተገፋፍቶ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት እና ከሃያ ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፮፻፴፮ ሴቶችንና ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት ለማቅረብ የሚደረጉ ዝግጅቶች</u>

ማንም ሰው ሴቶችን ወይም ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት ሥራ እንዲውሉ ለማቅረብ ወይም ከቦታ ቦታ ለማዟዟር ዝግጅቶችን ያደረገ ወይም ሁኔታዎችን ያመቻቸ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በተለይም ማቃጠርን የሙያ ሥራ አድርጐ የያዘ ሰው ተሳትፎ እንደሆነ ወይም ዝግጅቶቹ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁና በብዙ ተበዳዮች ላይ ሊፈጸሙ ታቅደው እንደሆነ፤ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት፣ እና ጥፋቱ ከባድ ሲሆን ከአምስት መቶ ብር በማያንስ መቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፮፻፴፯ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት</u>

የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ክፍል በተደነገጉት ወንጀሎች ተካፋይ እንደሆነ፣ እንደወንጀሉ ዓይነትና እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺(፫) መሠረት ይቀጣል::

BACK



## ክፍል አራት
## በመልካም ጠባይ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፮፻፴፱ ለመልካም ሥነ ምግባርና ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ብልግናና አሣፋሪ ሥራን በአደባባይ መፈፀም

፩ ማንም ሰው እስቦ ሕዝብ በሚያዘወትርበት ቦታ ወይም በሕዝብ ፊት የግብረ ሥጋ ድርጊትን ወይም ለመልካም ጠባይ ወይም ለመልካም ሥነ ምግባር በብርቱ ተቃራኒ የሆነውን ማናቸውንም ሌላ ጸያፍ ድርጊት የፈጸመ ወይም በአኳኋን ያሳየ እንደሆነ፤

ከሦስት ወር እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት፣ ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው ለአካለመጠን ባልደረሰ ልጅ ፊት ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከስድስት ወር እስከ አምስት ዓመት የሚደረስ ቀላል እሥራት ይሆናል::

### አንቀጽ ፮፻፵ ፀያፍ ወይም የብልግና ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ለሕዝብ መግለፅ

፩ ማንም ሰው:-

ሀ/ ጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ጽሁፎችን፣ ምስሎችን፣ ስዕላዊ መግለጫዎችን /ፖስተሮችን/፣ ፊልሞችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ያዘጋጀ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደ ውጭ አገር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ የተቀበለ፣ የያዘ፣ ለህዝብ ያሳየ፣ ለሽያጭ ወይም ለኪራይ ያቀረበ፣ ያከፋፈለ ፣ ያሰራጨ ወይም በማናቸውም ሌላ

BACK


መንገድ ከቦታ ቦታ ያዟዟረ ወይም በነዚህ ነገሮች የነገደ፣ ወይም

ለ/ እነዚህ ነገሮች እንደምን ወይም ከማን ሊገኙ ወይም ሊዘዋወሩ፣ ሊሠራጩ እንደሚችሉ በማናቸውም ዘዴ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያስታወቀ፣ ያመለከተ ወይም እንዲታወቅ ያደረገ፣

እንደሆነ፣ የተከሰሰባቸው ነገሮች መወረሳቸው ወይም እንዲጠፉ መደረጋቸው ሳይቀር ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀለኛው:-

ሀ/ ይህ ዓይነቱን ንግድ ሙያው አድርጐ የያዘው ወይም የተሠማራበት፣

ለ/ እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጆች አስቦ ያሳየ፣ የሰጠ ወይም ያስረከበ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ ለዚሁ ዓላማ ሲባል አካለመጠን ያልደረሱ ልጆች የግብረስጋ ግንኙነት የፈጸሙ በማስመሰል ያሳየ ወይም ሀፍረተሥጋቸው እንዲታይ ያደረገ እንደሆነ፣

ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቀላል እሥራት እና ከአስር ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፮፻፵፩ ፀያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ማሣየት</u>

ማንም ሰው ጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን በትያትር፣ በሲኒማ፣ በተንቀሳቃሽ

ፊልሞች፣ በሬዲዮ፣ በቪዲዮ፣ በቴሌቪዥን ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ እንዲተላለፍ ያደራጀ፣ ለሕዝብ ያሰማ ወይም እንዲታይ ያደረገ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ የተወሰኑት ቅጣቶች ይፈጸሙበታል::

<u>አንቀጽ ፮፻፵፪</u> <u>የተፈቀዱ ሥራዎች</u>

ወሲብን ወይም ፍትወተ ሥጋን ለመቀስቀስ ያልታሰቡ በባሕሪያቸው በሞላ ስነ ጥበባዊ፣ ስነ ጽሁፋዊ ወይም ሣይንሳዊ የሆኑ ሥራዎች እንደጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶች እንደሆኑ ሊቆጠሩ አይችሉም::

<u>አንቀጽ ፮፻፵፫</u> <u>ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ መግለጫዎችና ማስታወቂያዎች</u>

፩ ማንም ሰው ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ ወይም ከግብረ ገብ ውጭ የሆኑ ነገሮችን፣ ምርቶችን ወይም ሥራዎችን ለሕዝብ እይታ ያቀረበ እንደሆነ፤

ከአንድ ወር በማያንስ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው እነዚህኑ ነገሮች ወዳልጠየቁ ወይም በነዚሁ ላይ የሙያ ዝንባሌ ወደሌላቸው ሰዎች በማናቸውም ዘዴ የላከ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም በቀላል እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፮፻፵፬</u> <u>ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን አደጋ ላይ ከሚጥሉ ሥራዎች መጠበቅ</u>

ማንም ሰው ለጥቅም ወይም ስሜትን ለመቀስቀስ ሲል:-

ሀ/ ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን የግብረ ሥጋ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከልክ በላይ ለመቀስቀስ፣

ለማበላሸት ወይም ለማሳሳት ወይም ለአካለመጠን ባልደረሱ ልጆች ላይ የጭካኔ ወይም የገዳይነት ዝንባሌን ወይም ፀረ ማኅበራዊ የሆኑ ወይም ቤተሰባዊ ኑሮን የሚያናጉ ስሜቶችን ከመጠን በላይ ለማነሣሣት፣ ለመቀስቀስ ወይም ለማሳደር የሚችሉ ጽሁፎችን፣ ምስሎችን ወይም ነገሮችን በንግድ ቤት መስኮት፣ በንግድ ዕቃ ማሳያ ቦታ ወይም ከውጭ ለሕዝብ ሊታይ በሚችል በማናቸውም ሌላ ስፍራ በማስቀመጥ በቪዲዮ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ እንዲታይ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ እንደነዚህ ያሉ ነገሮችን፣ ምስሎችን ወይም ጽሁፎችን ለአካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ እያወቀ ያቀረበ፣ ያዋሰ፣ የሰጠ ወይም የሸጠ እንደሆነ፤

አስፈላጊም ሲሆን የዕቃው መወረስ ሳይቀር ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት እና በመቀጮ ይቀጣል።

__አንቀጽ ፮፻፵፯ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት፣ የወንጀል ተጠያቂነት__

የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ክፍል በተደነገጉት ወንጀሎች ተካፋይ እንደሆነ፣ እንደወንጀሉ ዓይነትና እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺(፫) መሠረት ይቀጣል።

## ምዕራፍ ሁለት

## በቤተዘመድ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ክፍል አንድ

## በጋብቻ ሥርዓት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

__አንቀጽ ፮፻፵፰ ጋብቻን በተንኮል ወይም በማታለል መፈፀም__

፩ ማንም ሰው ጋብቻን በሚፈጽምበት ጊዜ ወይም ለመፈጸም ሲል ጋብቻውን ለማፍረስ ወይም እንዳይጸና ለማድረግ ከሚያስችሉት በሕግ

ከተደነገጉት ምክንያቶች አንዱን የሚያሟላ ፍሬ ነገር አስቦ ከሌላው ተጋቢ የደበቀ እንደሆነ፤

ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው አስቦ ማንነቱን በተመለከተ ሌላውን ሰው በመደበቅ፣ በማሳሳት በማጭበርበር ወይም በማታለል ጋብቻን የፈፀመ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፮፻፵፮ በሕግ የተከለከለ ጋብቻን ማስፈፀም ወይም መፈፀም</u>

፩ ማንም ሰው በሕግ የተከለከውን ጋብቻ አስቦ ያስፈፀመ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ አስቦ በሕግ የተከለከለውን ጋብቻ የፈፀመ ተጋቢ፣ የፈቀደ ሰው ወይም ለዚህ ዓይነቱ ጋብቻ ምስክር የሆነ ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

፫ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከተው ድርጊት የተፈፀመው በቸልተኛነት ሲሆን ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል::

<u>አንቀጽ ፮፻፵፰ ያለዕድሜ ጋብቻ</u>

አግባብ ባለው የቤተሰብ ሕግ ከተፈቀደው ውጭ ማንም ሰው እስቦ ለአካለ መጠን ያለደረሰችውን ልጅ ያገባ እንደሆነ:-

ሀ/ የተበዳይዋ ዕድሜ አስራ ሶስት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ጊዜ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፣ ወይም

ለ/ የተበዳይዋ ዕድሜ ከአስራ ሶስት ዓመት በታች በሆነ ጊዜ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፣

ያስቀጣል::

<u>አንቀጽ ፮፻፵፱ ሕገወጥ ጋብቻ መፈፀምና ማስፈፀም በወንጀል የማያስጠይቅበት ሁኔታ</u>

ጋብቻው ካልፈረሰ በቀር በአንቀጽ ፮፻፵፮ ወይም በአንቀጽ ፮፻፵፯ በተመለከተው ወንጀል ላይ ክስ ሊቀርብ አይችልም::

<u>አንቀጽ ፮፻፶ በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈፀም</u>

፩ ማንም ሰው አስቀድሞ በሕግ በጸና ጋብቻ ታስሮ ሳለ ይኸው ጋብቻ ከመፍረሱ ወይም ከመሻሩ በፊት ሌላ ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ፣

በቀላል እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን በተለይም ጥፋተኛው የራሱን እውነተኛ ሁኔታ በመሰወር ከርሱ ጋራ ሁለተኛውን ጋብቻ የፈጸመውን ሰው አውቆ ያሳሳተ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

፪ ማንም ያላገባ ሰው ሌላው ሰው በጸና ጋብቻ የታሰረ መሆኑን እያወቀ ከዚሁ ሰው ጋር ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፫ ከሁለቱ ጋብቻዎች አንዱ እስከሚፈርስበት ወይም እስከሚሻርበት ጊዜ ድረስ የወንጀሉ ክስ ይርጋ ዘመን መቆጠር ታግዶ ይቆያል::

## አንቀጽ ፮፻፶፩ የተለየ ሁኔታ

በጋብቻ ላይ ጋብቻ የተፈጸመው አግባብ ባለው ሕግ በተለየ ሁኔታ በሀይማኖት ወይም በባህል ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች በሚሰጠው እውቅና መሠረት እንደሆነ፤ ከዚህ በላይ የተመለከተው ቅጣት ተፈጻሚ አይሆንም::

## አንቀጽ ፮፻፶፪ አመንዝራነት

፩ አንድ ባለትዳር በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት በፀና ጋብቻ ታስሮ ሳለ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ እንደሆነ፤

በተበደለው ባለትዳር የግል አቤቱታ አቅራቢነት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

እያወቀ ህጋዊ ጋብቻ ካለው ሰው ጋር ባመነዘረው ሰው ላይም ይኸው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆናል::

አቤት ባይ ያመንዝራነት ተግባሩ እንዲፈጸም የገፋፋ ወይም የተስማማ ወይም ይቅርታ ያደረገ ወይም ከዚሁ ተግባር ጥቅምን ያገኘ እንደሆነ ጥፋተኛው ሰው በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም::

፪ ያመንዝራነቱ ድርጊት የተፈፀመው ባልና ሚስቱ በመካከላቸው በተፈጠረ ጠብ ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ በአንድነት መኖራቸው ቀርቶ በነበረበት ጊዜ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ ፹፫ መሠረት የጥፋተኛውን ቅጣት ሊያቃልል ይችላል።

፫ ጥፋተኛው ሳይፋታ ወይም ሌላው ተጋቢ ጥሎት ሳይሄድ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ውሽማ ያስቀመጠ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሦስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል።

<u>አንቀጽ ፮፻፶፫</u> <u>የአቤት ባዩ መሞት</u>

ተበዳዩ የግል አቤቱታ ሳያቀርብ የሞተ እንደሆነ፤ ጥፋተኛው በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም።

ተበዳዩ የግል አቤቱታ ካቀረበ በኋላ ጥፋተኛው ክስ ቀርቦበት የእሥራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ፤ ተበዳዩ ቢሞትም ባይሞትም የአካባቢ ሁኔታዎቹ፣ በተለይም ጥፋተኛው ቤተሰብን የማስተዳደር ወይም የመደገፍ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ለፍርዱ በቂ ምክንያት ሆኖ ሲገኝ፣ ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን በመግለፅ ቅጣቱ እንዲቀርለት ለማዘዝ ይችላል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በዘመዳሞች መካከል የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወንጀል</u>

<u>አንቀጽ ፮፻፶፬</u> <u>በዘመዳሞች መካከል የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ግንኙነት</u>

ጋብቻቸው በሥጋ ዝምድና ምክንያት አግባብ ባለው ሕግ በተከለከለ ሰዎች መካከል ታስቦ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ግንኙነት፤

ከቤተ ዘመድ ሥልጣን የመሻሩ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ያስቀጣል።

## አንቀጽ ፮፻፵፭ በዘመዳሞች መካከል የሚፈፀም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ የብልግና ድርጊት

የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ሌላ ድርጊት ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ያስቀጣል።

## ክፍል ሦስት

## በክብር መዝገብ ላይ እና የቤተዘመድ ግዴታዎችን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## አንቀጽ ፮፻፵፮ የህፃን መወለድን ወይም ተጥሎ መገኘትን አለማስታወቅ

፩ ሕግ በሚያዘው መሠረት የአንድ ህፃንን መወለድ ለክብር መዝገብ ሹም ያላስታወቀ ማንም ሰው፣ ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

፪ ማንም ሰው የተጣለ ሕፃን አግኝቶ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ሳያስታውቅ የቀረ እንደሆነ፣

በንኡስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል፡

## አንቀጽ ፮፻፵፯ የክብር መዝገብን በሐሰት መለወጥ፣ አስመስሎ ህፃንን ማቅረብ ወይም መለወጥ

፩ ማንም ሰው በሌላ ሰው የክብር መዝገብ ሊመዘገብ የሚገባውን ማናቸውንም ፍሬ ነገር የደበቀ ወይም

BACK



ወደ ሀሰት የለወጠ፣ በተለይም የአንድን ህፃን ማንነት ወይም ልደት በሚመለከት አስቦ ሀሰተኛ መግለጫ የመዘገበ ወይም ያስመዘገበ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ አስቀድሞ ሊታወቅ ይችል የነበረ ከባድ ውጤትን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ሆኖ በተለይም ህፃን አለዋውጦ የማስመዝገቡ ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት የሚመለከት ሲሆን፤

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ያስቀጣል::

## አንቀጽ ፮፻፶፰ የቀለብ መስጠት ግዴታን አለመፈፀም

ማንም ሰው ያለበቂ ምክንያት:-

ሀ/ በሕግ መሠረት ሊሰጥ የሚገባውን ቀለብ ለባለመብቶች፣ የፍቺ ውሣኔ እስከ ሚሰጥበት ጊዜ ድረስ የፍቺ ጥያቄ ላቀረበ የትዳር ጓደኛም ቢሆን፣ አልሰጥም ያለ ወይም መስጠትን ያስተጓጐለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሕግ፣ ወይም በውል በገባው ግዴታ መሠረት ከጋብቻ ውጭ ላስረገዛት ሴት ወይም ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብሮት ለኖረ ሰው ወይም ከጋብቻ ውጭ ለተወለደው ልጅ ሊያሟላ የሚገባውን የገንዘብ ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በመቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፮፻፶፱ የልጅ ማሣደግ ግዴታን አለመፈፀም

፩ ማንም ወላጅ ወይም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ያለው ሌላ ሰው ጥቅምን በመፈለግ ወይም ያለበትን ግዴታ ቸል በማለት:-

ሀ/ በኃላፊነቱ ሥር የሚገኘውን ልጅ በከባድ ሁኔታ ያለ በቂ ጥንቃቄና ክብካቤ የተወ ወይም ለሥነ ልቦናዊ ወይም አካላዊ አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ አካላዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ጉዳት እንደሚያደርስበት ለሚያውቀው ወይም መገመት ለሚችለው ሰው፣ ድርጅት ወይም ተቋም ልጁን ለረጅም ጊዜ የሰጠ እንደሆነ፣

ነገሩ ከባድ ሲሆን ከቤተዘመድ ሥልጣኑ መሻሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

፪ የመቅጣትን ልክ በመተላለፍም ይሁን በመበደል ልጁ አስቀድሞ ሊታወቅ የሚችል ወይም የታቀደ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ፣ አግባብ ያለው የዚህ ሕግ ሌላ ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናል /አንቀጽ ፳፮/፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የወል ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፰፻፳ የወንጀሎች መደራረብ

፩ በጋብቻ ሥርዓት ላይ ከሚፈፀሙት ወንጀሎች አንዱ /አንቀጽ ፰፻፵፫፣ ፰፻፵፱ ወይም ፰፻፶፪/፣ በዝምድና ላይ ከሚፈፀም ወንጀል ጋር /አንቀጽ ፰፻፶፬/ በአንድ ላይ ተጣምሮ ሲገኝ፣ ሁለቱም ድንጋጌዎች በተደራራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፪ በግብረ ሥጋ ነፃነት ላይ የሚፈፀሙት ወንጀሎች /አንቀጽ ፰፻፴ እና ፰፻፴፫ እስከ ፰፻፴፰ እና ፰፻፵፱/፣ በዝምድና ላይ ከሚፈፀም ወንጀል /አንቀጽ

፮፻፶፬/ ጋር ተጣምረው ሲገኙ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፫ ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆኑ ወንጀሎች /ከአንቀጽ ፮፻፳፪ - ፮፻፴፩ እና ፮፻፴፱/፣ በዘመዳሞች መካከል ከሚፈፀም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ ከሆነ ወንጀል /አንቀጽ ፮፻፶፮/ ጋር ተጣምረው በተገኙ ጊዜ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ ፮፻፷፩ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች በወንጀል ተጠያቂነት</u>

፩ የግብረ ሥጋ በደል፣ ለንፅሕና ክብር ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ወይም ተፈጥሮአዊ ያልሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈፀመበት ለአካለመጠን ያልደረሰ ሰው በወንጀሉ ተጠያቂ አይሆንም።

ተስማሚ የሆኑት የመልካም አስተዳደግና የጥበቃ ውሳኔዎች በእርሱ ላይ ሊፈፀሙ ይችላሉ።

፪ በሌሎች ሰዎች ላይ ወንጀሉን የፈፀመው ለአካለመጠን ያልደረሰ ሰው የዚህ ሕግ መደበኛ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል /አንቀጽ ፶፪-፶፮/።

<u>ስድስተኛ መጽሐፍ</u>

<u>በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

<u>ርዕስ አንድ</u>

<u>በንብረት መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

<u>አንቀጽ ፮፻፷፪ መርህ</u>

፩ በሌላ ሰው የንብረትና የኢኮኖሚ መብት ወይም በገንዘብ ሊተመኑ በሚችሉ መብቶች ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት፣ አነስተኛ ከመሆኑ የተነሣ በደንብ

እልፊት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር፣ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ያስቀጣል::

፪ የመንግሥት፣ የሕዝብና የግል ንብረት በዚህ ሕግ ጥበቃ ይደረግለታል::

በዚህ ሕግ መሠረት በንብረት መብት ላይ ጉዳት ደርሷል የሚባለው ወንጀሉ ባይፈፀም ኖሮ ንብረቱ ሊገኝበት ይችል የነበረውን ሁኔታ የሚለውጥ ጉዳት ወይም ብልሽት ደርሶ ከሆነ ነው::

## አንቀጽ ፯፻፳፫ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ወይም ያለአግባብ የመበልፀግ ግምት

፩ ወንጀል አድራጊው ለራሱ ወይም ለሌላ ሦስተኛ ሰው ሕገወጥ የሆነ ጥቅም ለማስገኘት አስቦ የፈፀመው ድርጊት ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ሲሆን ድርጊቱ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት የተፈፀመ ነው ተብሎ ይገመታል::

፪ እንደዚህ ባለ ሁኔታ የታሰበው ብልፅግና ባይገኝም እንኳን ያለአግባብ የመበልፀግ ፍላጐቱና ተግባሩ ተጣምረው መገኘታቸው ከተረጋገጠ ፍፃሜ ያገኘ ወንጀል እንደተደረገ ይቆጠራል::

በዚህ ሁኔታ የተወሰደውን ሀብት የመመለስ ወይም ለደረሰው ጉዳት ካሣ አስቀድሞ የመክፈሉ ጉዳይ በአድራጊው ፈቃደኛነት የተፈፀመ ቢሆንም ወንጀሉን አያስቀረውም:: ነገር ግን ስለቅጣቱ አወሳሰን ፍርድ ቤቱ ይህንን ከግምት ማስገባት ይችላል /አንቀጽ ፹፪/(ሠ)/::

## አንቀጽ ፯፻፳፬ በቤተዘመድ አባሎች መካከል ወንጀል በተደረገ ጊዜ የሚቀርብ ክስ

፩ እንደ ውንብድና፣ መንጠቅ ወይም ማስፈራራት ከመሳሰሉ በኃይል ወይም በማስገደድ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች በስተቀር ሌሎች ወንጀሎች የተደረጉት:-

ሀ/ በወላጅና ተወላጅ፣ በአሣዳጊና በማደጉ ልጅ፣ ባልተለያዩ ባልና ሚስት፣ በጋብቻ ወቅት በአሣዳጊና በእንጀራ ልጅ፣ በእናት ወይም በአባት ወይም በሁለቱም በሚገናኙ ልጆች መካከል ሲሆን፣ ወይም

ለ/ በተበዳዩ ቤት በሚኖሩ ቤተዘመዶች መካከል ሲሆን፣

ክሱ የሚታየው በግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ ይሆናል።

፪ የግል ተበዳዩ የክስ አቤቱታ አለማቅረቡ ከላይ በተጠቀሱት የዝምድና ሐረጐች ያልተሸፈኑ የወንጀሉ ተካፋዩችን ከተጠያቂነት አያድናቸውም /አንቀጽ ፺፩/።

## ምዕራፍ ሁለት

## በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ክፍል አንድ

## በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፮፻፷፭ ስርቆት

፩ ማንም ሰው የማይገባውን ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው ንብረት የሆነውን ተንቀሳቃሽ ዕቃ ወይም ከማይንቀሳቀስ ንብረት የተነጠለን ዕቃ አንስቶ የወሰደ፣ በቀጥታ የራሱ ንብረት ያደረገ ወይም በተዘዋዋሪ ከራሱ ንብረት ጋር እንዲቀላቀል ያደረገ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ አድራጊው ከማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ተንቀሳቃሹን ዕቃ የነጠለው ራሱ እንደሆነና ይሄንን ድርጊት የፈፀመው በተንቀሳቃሹ ወይም በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ እንደሆነ፤ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፮፻፹፱ - ፮፻፺፩ ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈፃሚ ይሆኑበታል።

፫ ማንም ሰው በቀላል አኳኋን የሰረቀው እጅግ አነስተኛ ግምት ያለው የሌላ ሰው ዕቃ ሲሆን፣ ስለደንብ እልፊት በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል /አንቀጽ ፰፻፶፪ እና ፰፻፶፫/።

አንቀጽ ፮፻፷፯ ኃይልን መስረቅ

ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው ንብረት ከሆነ የኃይል ማሰራጫ ወይም ለሌላ ሰው ከተዘረጋ መስመር ላይ ጋዝ፣ እንፋሎት፣ ኤሌክትሪክ ወይም ሌላ ዓይነት ኃይል በመውሰድ የራሱ ያደረገ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

አንቀጽ ፮፻፷፰ የጋራ ንብረት የሆኑትን ዕቃዎች መስረቅ

፩ ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በጋራ ባለንብረትነት፣ በሽርክና ወይም በወራሽነት ምክንያት የጋራ ሀብት የሆነውን ዕቃ የወሰደ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ የጋራ ንብረቱ አላቂ ነገር ሆኖ ተከሳሹ የወሰደው ለራሱ ከሚገባው ድርሻ ያልበለጠ እንደሆነ አያስቀጣውም።

አንቀጽ ፮፻፷፰ በሙታን ላይ የሚፈፀም ስርቆት

ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ከሙታን መቃብር ላይ ወይም ከመቃብር ቤት ውስጥ ወይም ከተቀበረ ወይም ካልተቀበረ አስከሬን ላይ ዕቃ የወሰደ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

አንቀጽ ፮፻፷፱ ከባድ ስርቆት

እንደወንጀሉ ክብደትና በተሰረቀው ዕቃ ዓይነት በወንጀለኛው የኑሮ ደረጃና ሁኔታ እንዲሁም በአሰራረቁ ዓይነት፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት የሚሆነው፣

፩ ወንጀሉ የሚመለከታቸው:-

ሀ/ የተሠረቀው ዕቃ የሀይማኖት ሥርዓት በሚፈፀምበት ሥፍራ ውስጥ የሚገኝ የሃይማኖት ዕቃ ወይም በቤተ መዘክር ውስጥ የተቀመጠ ዕቃ፣ ወይም ለሕዝብ ክፍት በሆነ ህንፃ ውስጥ የተቀመጠ ሳይንሳዊ፣ ኪነጥበባዊ ወይም ታሪካዊ ዋጋ ያለው ዕቃ እንደሆነ፣

ለ/ የተለየ ጠባቂ የሌለው እንስሳ ወይም ሰብል ወይም ለቴሌኮሙኒኬሽን፣ ለኤሌክትሪክ ኃይል፣ ለውሃና ፍሳሽ ወይም ለማናቸውም ሌላ ድርጅት አገልግሎት የሚውል ጠባቂ የሌለው መሣሪያ ወይም ዕቃ ወይም እንዲቀመጥ ወይም እንዲላክ ለዕቃ ማከማቻ፣ ለአንድ ድርጅት ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት

በተለይም ለፖስታ ቤት ወይም ለማመላለሻ ድርጅት የተሰጠ ሸቀጥ ወይም ዕቃ እንደሆነ፤

ነው::

፪ ወንጀሉን የፈፀመው:-

ሀ/ የመከላከያ ሰራዊት አባል ሆኖ ወንጀሉን የፈፀመው በጓደኞቹ ወይም በአለቆቹ ላይ ሲሆን ወይም የተሰረቀው ዕቃ ሠራዊቱን የሚያገለግል ወይም እንዲያ ገለግል የተመደበ ሲሆን፤

ለ/ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም አንድ የንግድና ይህን የመሳሰለ ልዩ ሥራ የሚያከናውን ሰው የባንክ ሠራተኛ፣ ጠበቃ፣ ውል አዋዋይ፣ የወኪልነት ሥልጣን የተሰጠው እንደራሴ ወይም በእንደዚህ ያለ ምክንያት የተሰጠውን ሥልጣን በማከናወን ላይ የሚገኝ የንግድ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ድርጊቱን የፈፀመው በተለይ በተሰጠው ሥልጣን ምክንያት በእጁ በገባው የመንግሥት፣ የህዝብ ወይም የግል ንብረት ላይ ሲሆን፤

ሐ/ ባለሆቴል፣ የቤት አከራይ፣ ዕቃ አመላላሽ፣ ተሸካሚ ወይም ይህን የመሳሰለ ሥራ የሚያካሂድ ሆኖ የተሰረቀው ንብረት የደንበኛው ሲሆን፤

መ/ የቤት ሠራተኛ፣ ሠራተኛ ወይም ሥራ ለማጅ ሆኖ ሥራውን ምክንያት በማድረግ በአሳዳሪው ወይም በአሰሪው ላይ ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ ሲሆን፤

ነው::

፫ አድራጊው፦

ሀ/ በሰዎች ወይም በንብረት ላይ ወንጀል ለመፈፀም የተቋቋመ ቡድን አባል ሲሆን፤

ለ/ ስርቆቱን የፈፀመው በተለይ አደገኛ መሆኑን በሚያሣይ በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ይልቁንም የማጥቂያ ወይም የመከላከያ የጦር መሣሪያ ወይም የቤት መሰርሰሪያ መሣሪያ በመያዝ ሲሆን ወይም ራሱን የመንግሥት ሠራተኛ በማስመሰል ሲሆን፣ ወይም በሌሊት ወይም ቅጥር በመጣስ፣ አጥር በመዝለል፣ በር በመስበር፣ ግድግዳ በመሰርሰር ወይም በቡድን በመሆን ሲሆን፣ ወይም ያልተጠበቀ አደገኛ ሁኔታን፣ የሕዝብ ብጥብጥን ወይም መቅሰፍትን ይልቁንም እንደግርግር፣ ቃጠሎ፣ ጐርፍ፣ ማዕበል የመሳሰለውን ሽፋን በማድረግ ሲሆን፤ ነው::

## አንቀጽ ፮፻፸ ውንብድና

ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ፣ የሌላ ሰው ንብረት የሆነውን ተንቀሳቃሽ ዕቃ ለመውሰድ እንዲያመቸው ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኋላ የገጠመውን ተቃውሞ ውጤታማነት ለማስቀረት ሲል፤ በሌላ ሰው ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ከባድ የሆነ የማንገላታት ተግባር ወይም ከባድ ዛቻ የፈፀመ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ይህን ሰው ለመከላከል እንዳይችል ያደረገው ሲሆን፤

ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

BACK



## አንቀጽ ፮፻፸፩ ከባድ ውንብድና

፩ አድራጊው በአንቀጽ ፮፻፸ የተመለከተውን ወንጀል የፈጸመው:-

ሀ/ በሰዎች ላይ ወይም በንብረት ላይ የኃይል ተግባር ለመፈፀም በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል በመሆን ሲሆን፤ ወይም

ለ/ ተበዳዩን እገድልሀለሁ ብሎ እርግጠኛ የሞት አደጋ እንደሚያደርስበት በመቃጣት፣ ይልቁንም በጦር መሣሪያ ወይም በተለይ አደገኛ በሆነ ሌላ ዓይነት መሣሪያ በማስፈራራት ወይም ስቃይ በሚያደርስ ሁኔታ በማንገላታት ወይም ከባድ የአካል ጉዳት በማድረስ ሲሆን፤ ወይም

ሐ/ በተለይ አደገኛነቱን በሚያሣይ በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ሲሆን፤

ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው ወንጀል ለመፈፀም ከተደራጀ ቡድን ጋር በመሆን ወይም የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሣሪያ በመያዝ፣ የሕዝብ ፀጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነትን የሚያሣይ ዘዴን የተጠቀመ፣ ወይም የተፈፀመው የኃይል ተግባር ዘላቂ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ በሆነ ጊዜ የሞት ፍርድ ለመወሰን ይችላል::

በጦር መሣሪያ አማካይነት በልማደኛነት በቡድን የሚፈፀም ውንብድና የሞት ቅጣትን የሚያስከትል ይሆናል።

አንቀጽ ፮፻፸፪ <u>ዘረፋ</u>

ማንም ሰው ዘረፋ የፈፀመ እንደሆነ በተለይም ድርጊቱ የተፈፀመው፡-

ሀ/ ለሕዝብ ሕይወት፣ ለአገር ኢኮኖሚ ወይም ዕድገት ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጡ ምግቦች፣ ስንቆች፣ የሚታደሉ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎች ወይም ሌሎች ንብረቶች ላይ ሲሆን፤ ወይም

ለ/ በመሬት፣ በባሕር ወይም በአየር በሚመጣ እንደመኪና አደጋ እንደ አይሮፕላን ድንገተኛ የመገደድ ማረፍ ወይም እንደመርከብ መስጠም የመሳሰሉት አደጋዎችን ምክንያት በማድረግ ሲሆን፤

እንደነገሩ ሁኔታ ለተራ ወይም ለከባድ ውንብድና በተደነገጉት ቅጣቶች መሠረት ይቀጣል (አንቀጽ ፮፻፸ ወይም ፮፻፸፩)።

አንቀጽ ፮፻፸፫ <u>የባሕር ውንብድና</u>

ማንም ሰው በባሕር ላይ የውንብድና ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከዚህ በላይ በተመለከቱት የተራ ወይም የከባድ ውንብድና ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል /አንቀጽ ፮፻፸ ወይም ፮፻፸፩/።

አንቀጽ ፮፻፸፬ <u>ልዩ ሁኔታዎች</u>

የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ተቃራኒ በሆነ መልኩ በጦርነት ጊዜ የውንብድና፣ የዘረፋ ወይም የባሕር ውንብድና የሚፈጽሙ ለእነዚህ በተለይ በተወሰኑት ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣሉ /አንቀጽ ፪፻፸፫/።

አንቀጽ ፮፻፸፭ <u>እምነት ማጉደል</u>

፩ ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ፣ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጐት የፈፀመ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ተከሳሹ በእምነት እንዲሸጥ ወይም እንዲገዛ ወይም እንዲለውጥ ወይም ለተወሰነ አገልግሎት እንዲያውል የተሰጠውን ገንዘብ፣ ወይም ዕቃ፣ ወይም ዋጋ ያለው ነገር በተባለው መሠረት ፈጽሞ በምትኩ ያገኘው ገንዘብ፣ ዕቃ፣ ወይም ዋጋ ያለው ነገር የሌላ ሰው እንደሆነ ይቆጠራል::

፫ ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል አሳብ እንዳለው ይቆጠራል::

አንቀጽ ፮፻፸፮ <u>ከባድ የእምነት ማጉደል</u>

፩ ወንጀሉ የተፈፀመው፣ በመንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ንብረት ላይ ከሆነ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ሹም ወይም የሕዝብ ባለአደራ ወይም ተመራጭ እንደሆነ ፤

BACK



ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር አንድ መቶ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፪ ወንጀሉ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት የሚያስቀጣው:-

ሀ/ ወንጀሉን የፈፀመው ሞግዚት ወይም ንብረት ጠባቂ፣ ሒሳብ አጣሪ፣የሕግ ወይም የገንዘብ አማካሪ፣ ወኪል፣ ጠበቃ፣ የንብረት አስተዳዳሪ ወይም በሥራው ወይም በተሰጠው ኃላፊነት ምክንያት ንብረቱ በእጁ የገባ ማንኛውም ሌላ ሰው እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ተከሳሹ በእምነት በተቀበለው ሰነድ ላይ ሰጪውን ባለዕዳ የሚያደርግ ግዴታ አስመስሎ በመጻፍ ወይም የገንዘብ መቀበያ ሰነድ በማስመሰል ወይም በፈራሚው ንብረት ላይ ጉዳት በሚያደርስ በማናቸውም ሌላ አይነት አድራጐት ሠርቶበት እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ወንጀሉን የፈፀመው ስለገንዘብ መሰብሰብ ለሕዝብ ጥሪ የሚያደርግ ሰው ሆኖ ለራሱ ወይም ለአንድ የንግድ ማህበር ወይም ለባንክ ወይም ለሌላ ድርጅት ጥቅም ሲል ገንዘብ ወይም ዋጋ ያላቸውን ነገሮች የሚሰበስብ ሰው እንደሆነ፤ ነው።

አንቀጽ ፮፻፸፮ <u>በመንግሥት ወይም በሕዝብ ንብረት ያለአግባብ መገልገል ወይም ማባከን</u>

፩ ማንም ሰው አስቦ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሳይሆን :-

BACK



ሀ/ በመንግሥት ወይም በሕዝብ ንብረት ያለአግባብ የተገለገለ፣ ያዋሰ፣ የሸጠ፣ ለሌላ ያሳለፈ፣ የለወጠ ወይም በዋስትና ያስያዘ፤ ወይም

ለ/ በአደራ የተሰጡትን ወይም የተረከባቸውን ወይም በሥራው ወይም በሥልጣኑ ምክንያት ሊያዝባቸው ወይም ሊያገኛቸው የሚችለውን ማናቸውንም የመንግሥት ወይም የሕዝብ ንብረት አሳልፎ የሰጠ፣ የጣለ፣ ጉዳት እንዲደርስባቸው ያደረገ፣ ያባከነ ወይም ያበላሸ፤

እንደሆነ እንደነገሩ ከባድነት ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ድርጊቱ በቸልተኛነት የተፈፀመ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት ይሆናል::

አንቀጽ ፯፻፳፰ <u>በሌላ ሰው ሀብት ያለአግባብ መገልገል</u>

ማንም ሰው ራሱን ወይም ሌላውን ሰው ያለአግባብ ለማበልፀግ በማሰብ ሳይሆን የንብረቱ ባለቤት በመብቱ እንዳይጠቀምበት ለማድረግ፣ ለማታለል ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለጊዜው መጠቀሚያ ለማድረግ የሌላውን ሰው ንብረት የወሰደ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

አንቀጽ ፯፻፳፱ <u>አግኝቶ መደበቅ</u>

ማንም ሰው የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ:-

BACK



ሀ/ የሌላ ሰው ንብረት ሆኖ በስህተት፣ ባልታሰበ ድንገተኛ አጋጣሚ ነገር፣ እንደ ውሀ ማዕበልና እንደነፋስ ባለ በተፈጥሮ ጠባዩ በመጣ ኃይል ወይም ከባለሀብቱ ፈቃድ ውጭ በሆነ በማናቸውም ሌላ ዓይነት ሁኔታ ከባለቤቱ እጅ ወጥቶ በእጁ የሚገኘውን ነገር /ዕቃ/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ንብረትነቱ የሌላ ሰው የሆነ እንስሳ ሸሽቶ በመጠጊያው ምክንያት በእጁ ስለገባ የራሱ ያደረገው እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

አንቀጽ ፮፻፹፯ <u>ወድቆ የተገኘውን ንብረት ለራስ ማድረግ</u>

፩ ማንም ሰው አንድ የጠፋ ንብረት አግኝቶ ይህንኑ ለባለሥልጣን ሳያስታውቅ ወይም ባለንብረቱን ለማወቅ አስፈላጊውን ሁሉ ሳያደርግ ንብረቱን ለራሱ ያደረገው እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከብር አምስት ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ወይም እንደነገሩ ከባድነት ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ እንዲሁም የተደበቀ ወይም የተቀበረ ገንዘብ ወይም ሀብት አግኝቶ በሕግ መሠረት ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን አስፈላጊውን ማስታወቂያ ሳይሰጥ ወይም ዕቃው ወይም ገንዘቡ የተገኘበት ንብረት ባለቤት ለሆነው ሰው ሊሰጥ የሚገባውን የክፍያ ድርሻ ሳይሰጥ

ንብረቱን ለራሱ ያደረገ እንደሆነ፤ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ይቀጣል።

አንቀጽ ፮፻፹፩ <u>ባለቤት የሌለውን ዕቃ ወይም የተፈጥሮ ሀብትን መውሰድ</u>

፩ ባለቤት የሌላቸውን ነገሮች፣ የተፈጥሮ ሀብትን የሚመለከተው የንብረትነት ጉዳይ እንዲሁም በየብስ፣ በአየር ወይም በባሕር የሚገኙትን በነፃ ያሉትን የማንም ሰው ንብረት ያልሆኑትን የዱር እንስሳት የመያዝ ጉዳይ ይህንኑ በሚመለከተው በፍትሐብሔርና በመንግሥት ሕግ ድንጋጌዎች የሚመሩ ናቸው /አንቀጽ ፫፻፶፫ ፫፻፵፱፣ ፫፻፶/።

፪ ንብረትነታቸው የመንግሥት በሆነ የታሪክ፣ የአርኪዮሎጂ ወይም የኪነጥበብ ዕቃዎች በማይገባ ለመበልፀግ በማቀድ እነዚህን ዕቃዎች ለራስ ማድረግ ወይም እምነት ማጉደል፣ እንደወንጀሉ ዓይነት ስለስርቆት ወይም ስለ እምነት ማጉደል በሚመለከቱት ድንጋጌዎች የሚያስቀጣ ይሆናል።

አንቀጽ ፮፻፹፪ <u>መሸሸግ</u>

፩ ማንም ሰው ዕቃው የተገኘው ባንድ ንብረት ላይ በተፈፀመ ወንጀል ምክንያት መሆኑን እያወቀ ይህንኑ ዕቃ በመግዛትም ሆነ በተውሶ፣ በስጦታ፣ በመያዣነት የተቀበለ ወይም በማናቸውም ይህን በመሳሰለ አኳኋን የወሰደ፣ የተገለገለ፣ ያስቀመጠ ወይም የደበቀ፣ አሻልፎ የሸጠ ወይም በመሸጥና በመለወጥ ስምምነት ውስጥ አገናኝ ሆኖ የረዳ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል።

፪ የወንጀሉ ተግባር ባስገኘው ፍሬ የመጣ መሆኑን እያወቀ በዚሁ በወንጀል ድርጊት በተገኘው ዕቃ ምትክ በልዋጭ የተገኘውን ወይም በሽያጩ ዋጋ የተገዛውን ሌላ ዓይነት ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ተቀብሎ ከዚህ በላይ በተመለከተው ዓይነት አስቦ የሸሸገ ሰው፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ይቀጣል።

፫ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ድርጊት በቸልተኛነት የተፈፀመ እንደሆነ፤ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል።

፬ በተከሣሹ ላይ የሚወሰነው ቅጣት መጀመሪያ ወንጀሉን ባደረገው ሰው ላይ ከሚወሰነው ቅጣት ግንኙነት የሌለው ነው።

፭ ዋናው ወንጀል አድራጊ በዝምድና ምክንያት እንዳይከሰስ (አንቀጽ ፮፻፷፬) ወይም በወዳጅነት ፍቅር ግንኙነት ምክንያት ቅጣቱ እንዲቃለልለት /አንቀጽ ፹፫/ የተፃፉት ድንጋጌዎች ለዕቃ ሸሻጊ አይፀኑለትም።

አንቀጽ ፮፻፹፫ <u>ከባድ የመሸሸግ ወንጀል</u>

የግል ነፃነትን የማሳጣቱ ቅጣት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ፅኑ እሥራትና መቀጮውም እስከ ብር ሃያ ሺህ ለመድረስ የሚችለው ተከሳሹ፡-

ሀ/ በሰዎች ወይም በንብረት ላይ ወንጀል ለመፈፀም በተቋቋመ ቡድን አባልነት ወንጀሉን የፈፀመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የተሰጠውን የሥራ ወይም የንግድ ፈቃድ በወንጀል የተገኘን ንብረት ለመሸሸግ ተገልግሎበት እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ይህን ንብረት የሸሸገው የውንብድና፣ የዘረፋ፣ የባህር ውንብድና፣ የቅሚያ፣ የማስፈራራት ፍሬ መሆኑን

ወይም ዕቃው የተገኘው ከመከላከያ ሠራዊት ንብረት ወይም በጠቅላላው ከመንግሥት ሀብት ውስጥ መሆኑን እያወቀ እንደሆነ፤ ነው።

አንቀጽ ፮፻፹፬ <u>በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ መርዳት</u>

፩ ማንም ሰው በሙስና፣ በአደንዛዥ ዕጽ ወይም መድኃኒት ዝውውር፣ በሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ ወይም በዚህ ሕግ፣ በአንቀጽ ፪፻፵፫(፪)(፫)፣ ፪፻፷፪(፩) (፪)፣ ፬፻፶፭(፪)፣ ፭፻፮(፫) (፬)፣ ፭፻፯ እስከ ፭፻፱፣ ፭፻፲(፪)፣ ፭፻፲፩(፪)(፫)(፭) ወይም ፭፻፲፪ በተመለከተው ወንጀል ወይም በማናቸውም ተመሣሣይ ከባድ ወንጀል አማካኝነት ያገኘውን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕገ ወጥ አመጣጥ ሰውሮ በጥቅም ወይም በስራ ላይ በማዋል፣ በማዘዋወር ወይም በማስተላለፍ ሕጋዊ አስመስሎ ያቀረበ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከመቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ ማንም ሰው በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች በአንዱ የተገኘ መሆኑን እያወቀ ሕገወጥ የሆነን ገንዘብ ወይም ንብረት፣ የለወጠ፣ ያስተላለፈ፣ የተቀበለ፣ ይዞ የተገኘ ወይም በዚሁ ገንዘብ ወይም ንብረት የተጠቀመበት እንደሆነ፤

ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

፫ ማንም ሰው ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተገለፀው ወንጀል መፈፀሙን እያወቀ ወይም

ለማወቅ የሚያስችለው በቂ ምክንያት እያለው አግባብ ላለው ባለስልጣን ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ፤

ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል::

፬ ማንም ሰው ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተገለፀውን ወንጀል በተመለከተ ፖሊስ ክትትል እያደረገ ወይም በቅርቡ ሊያደርግ መሆኑን፣ ጥቆማ መቅረቡን፣ ወይም በውስጥ ደንብ መሰረት ጉዳዩ ለሚመለከተው ሰራተኛ የተላለፈ መሆኑን አውቆ ወይም ጠርጥሮ በወንጀሉ ለተጠረጠረው ወይም ለሌላ ሰው መረጃ የሰጠ ወይም ወሬ ያቀበለ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል::

፭ ማንም ሰው ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለጸው ወንጀል የተገኘ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ ወንጀሉን የሚፈጽመውን ሰው ለመርዳት ወይም ንብረቱ የተገኘበትን ሕገ ወጥ ምንጭ ለመደበቅ ወይም ለመሰወር በማሰብ ንብረቱ ሕጋዊ እንዲሆን ያደረገ ወይም ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላው ያዘዋወረ እንደሆነ፤ ወይም ዕውነተኛ ባህሪውን፣ ምንጩን፣ የሚገኝበትን ቦታ፣ ግብይቱን፣ እንቅስቃሴውን ወይም ከንብረቱ የሚመነጭ መብትን እንዳይታወቅ ያደረገ ወይም የሠወረ እንደሆነ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል::

፮ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ከላይ ከተመለከቱት ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ ሲሆን ቅጣቱ የሚወሰንበት በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፫ በተደነገገው መሠረት ነው::

፯ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከባድ ወንጀል ማለት:-

ሀ/ ወንጀሉ አስር ዓመት ጽኑ እስራት ወይም ከዚያ በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን፣ ወይም

ለ/ በወንጀሉ አማካይነት የተገኘው የገንዘቡ መጠን ወይም የንብረቱ ዋጋ ቢያንስ ሃምሳ ሺህ ብር ሲሆን ነው::

## ክፍል ሁለት

## በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፮፻፹፭ በከብት መንጋ አማካይነት በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ

፩ ማንም ሰው አስቦ መብት ሳይኖረው በሌላ ሰው መሬት ይዞታ የሚገኘውን ሣር፣ ግጦሽ፣ የእርሻ ስፍራም ሆነ ደን፣ የአትክልት ቦታም ሆነ በማናቸውም ሌላ ዓይነት ሁኔታ በሚገኝ የይዞታ መሬቱ ላይ መንጋዎችን አሰማርቶ ያስጋጠ፣ ወደዚሁ ስፍራ የወሰደ ወይም እንዲዘዋወሩ የለቀቀ እንደሆነ፣

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ሁኔታዎቹ ቀላል በሆኑ ጊዜ በተለይም በሚገባ ባለመጠበቅ እንደሆነ የደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ /አንቀጽ ፰፻፶፩(ለ)/::

### አንቀጽ ፮፻፹፮ በሰው ንብረት ላይ ሁከት ማድረግ

፩ ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ጥቅም ለማግኘት ሲል:-

ሀ/ የሌላ ሰው ይዞታ የሆነውን መሬት ወይም ህንፃ የወረረ ወይም የያዘ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በማናቸውም ሌላ አኳኋን የሌላ ሰው ሰላማዊ ይዞታ በሆነ መሬት ላይ ሁከት ያደረሰ እንደሆነ፣

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በመቀጮ ወይም በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ የሁከት ተግባር የተፈጸመው በኃይል ድርጊት፣ በዛቻ ወይም በብዙ ሰዎች ተባባሪነት ወይም አደገኛ መሣሪያ በያዘ ሰው እንደሆነ፣ በወንጀል ክስ አቀራቢነት ከአምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ያስቀጣል::

አንቀጽ ፮፻፹፯ በሰው ይዞታ ላይ ጉዳት ማድረስ

ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ:-

ሀ/ የሌላውን ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ከዚያው ጋር የተያያዙትን ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ሁኔታ የለወጠ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ የግል ወይም የሕዝብ የሆነውን የውሃዎች አወራረድ የለወጠ እንደሆነ፣

ቢያንስ በሦስት ወር ቀላል እሥራት እና በመቀጮ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

አንቀጽ ፮፻፹፰ የወሰን ምልክቶችን ከሥፍራቸው ማዛወርና ማጥፋት

፩ ማንም ሰው መብት ሳይኖረው በሌላው ሰው የንብረት መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ፣ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣ የሌላውን ሰው የመሬት ወሰን ለመለየት የተተከለውን መከለያ ወይም ይህንን የመሳሰለውን ምልክት ከስፍራው ያነሳ ፣ ያዘዋወረ ወይም በሐሰተኛ

ስፍራ የተከለ፣ ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ፣ ወይም ምልክቱ እንዳይታወቅ ያጠፋ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪ ተግባሩ የተፈፀመው ከዚህ በላይ በተመለከተው አሳብ ያልሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከሦስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ

### አንቀጽ ፮፻፹፱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

ማንም ሰው አስቦ የሌላ ሰው ንብረት የሆነውን ዕቃ፣ መሣሪያ፣ እንስሳ፣ ዛፍ (እፅዋት)፣ ሰብል፣ የግብርና ምርት፣ ደን፣ ቤት፣ የሕንጻ ስራዎች ወይም ማናቸውንም ነገር ወይም በይዞታው ሥር የሚገኘውን መሬት ያፈረሰ ወይም ዋጋ ያሳጣ ወይም እንዳያገለግል ያደረገ እንደሆነ በአንቀጽ ፮፻፹፰ የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

### አንቀጽ ፮፻፺ ከባድ ሁኔታ

፩ ወንጀሉ በወንጀል ክስ አቅራቢነት ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ሊያስቀጣ የሚችለው፦

የሚሰጠው ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ ወይም ይህ የተለየ አሳብ ባይኖረውም ተግባሩ እጅግ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በዛቻ፣ በኃይል ወይም በብዙ ሰዎች ይልቁንም ሁከት፣ የሥራ መዝጋት ወይም የሥራ ማቆም አድማ በተነሳ ጊዜ በሠራተኞች ወይም በአሠሪዎች እንደሆነ፤

ነው::

፪ አድራጊው ያወደመው ወይም ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰበት ንብረት የእምነት አምልኮ የሚደረግበት ዕቃ፣ ታሪካዊ፣ ሳይንሳዊ ወይም ኪነጥበባዊ የሆነ ከፍ ያለ ዋጋ ያለው ዕቃ፣ ወይም የሕዝብ የሆነና በህዝቡ ጠባቂነት በመተማመን ያለጠባቂ የሚኖር ሕንፃ፣ ሐውልት፣ ታሪካዊ የሆነ ሥፍራ ወይም ለሕዝብ አገልግሎት፣ ለአገር ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ የተተከለ የመሣሪያ ተቋም፣ የተዘረጋ የቴሌ ወይም የመብራት ኃይል መስመር ወይም እርሻ እንደሆነ፤

ቅጣቱ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ይሆናል::

፫ ወንጀሉ የተፈጸመው ሰውን ለመግደል፣ በአካሉ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ይዞ ለማቆየት በማስፈራራት፣ ወይም መንግሥት የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካልን፣ ቡድንን ወይም ግለሰብን አንድ ነገር እንዲፈጽም ወይም ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማስገደድ ታስቦ በሆነ ጊዜ፤

ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከተው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል::

**አንቀጽ ፮፻፺፩ ከባድ ዘዴዎች**

አድራጊው የሌላውን ሰው ንብረት ለማፍረስ፣ ለመጉዳት፣ ዋጋ ለማሳጣት ወይም ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆን ለማድረግ፣ በሕዝብ ጸጥታ ላይ አደጋ በሚያደርስ እንደ ፍንዳታ፣ ጎርፍ፣ ፍንዳታ ወይም ቃጠሎ በመሳሰለ ነገር ተገልግሎ እንደሆነ፤ ለነዚህ ጉዳዮች ከባድ ቅጣትን ለመወሰን የተደነገጉት አንቀጾች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ /አንቀጽ ፹፮/፡፡

## ዕራፍ ሦስት

## በንብረት መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ክፍል አንድ

## ማታለልን ያካተቱ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፮፻፺፪ አታላይነት**

፩ ማንም ሰው የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታልሎ የራሱን ወይም የሦስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጎዳ አድራጐት እንዲፈፅም ያደረገው እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም እንደነገሩ ከባድነት እስከ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል፡፡

፪ በወስላታነት የሌላ ሰውን አገልግሎት እንደማግኘት በመሰለ አሰራር ሆኖ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት አነስተኛ የማታለል ተግባር በፈፀመ ሰው ላይ የደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎች ቅጣት ይፈፀምበታል /አንቀጽ ፰፻፵፰ እና ፰፻፶፱/፡፡

አንቀጽ ፯፻፺፫. <u>የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት</u>

፩ ማንም ሰው ቼክ በሚወጣበት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ/ እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት ወይም እንደነገሩ ከባድነት ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ አድራጐቱ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፣ በመቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል::

አንቀጽ ፯፻፺፬ <u>በተጭበረበረ ሁኔታ የአክሲዮን ገበያን ንግድ ማካሄድ</u>

ማንም ሰው በአክሲዮን ገበያ፣ ወይም በሌላ ገበያ አማካይነት የአክሲዮን ወይም የአክሲዮን የገበያን ዋጋ በሚመለከት የሕዝብ አክሲዮኖች ንግድ እንዳለ የሚያስመስል ሐሰተኛ ወይም አሣሣች መልክ ለመፍጠር በማሰብ:-

ሀ/ በአክሲዮን ባለቤትነት ላይ ምንም ጠቃሚ ለውጥ የማያመጣ የአክሲዮን ንግድ ያካሄደ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ አክሲዮኖቹ በተጠየቁት ተቀራራቢ መጠን፣ ተቀራራቢ ጊዜ እና በተቀራራቢ ዋጋ በዚያው ሰው ወይም በሌላ ሰው እንደተገዛ ወይም ለዚያው ሰው ወይም ለሌላ ሰው የማኙ ጥያቄ እንደቀረበ ወይም እንደሚቀርብ እያወቀ አክሲዮኖቹን ለመግዛት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ አክሲዮኖቹ በተጠየቁት ተቀራራቢ መጠን፣ ተቀራራቢ ጊዜ እና ተቀራራቢ ዋጋ በዚያው ሰው ወይም በሌላ ሰው እንደተሸጡ ወይም ለዚያው ሰው ወይም ለሌላ ሰው የሽያጭ ጥያቄ እንደቀረበ ወይም እንደሚቀርብ እያወቀ አክስዮኖችን ለመሸጥ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

አንቀጽ ፯፻፲፩ <u>በአክሲዮኖች ወይም በሸቀጦች መቆመር</u>

ማንም ሰው በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የተመዘገቡ ወይም ያልተመዘገቡ ኩባንያዎች ወይም የሌሎች የንግድ ድርጅቶች አክሲዮኖች ወይም ማናቸውም ዕቃዎች ወይም ሸቀጦች ዋጋቸው ዝቅ ወይም ከፍ ማለቱን ምክንያት በማድረግ ገቢ ወይም ትርፍ ለማግኘት በማሰብ አክሲዮኖቹን ወይም ዕቃዎቹን ወይም ሸቀጦቹን የራስ የማድረግ እውነተኛ ሐሳብ ሳይኖረው እነዚህን ነገሮች የሚሸጥ ወይም የሚገዛ በማስመሰል ማናቸውንም ዓይነት ውል በጽሁፍም ሆነ በቃል ያዘጋጀ ወይም የፈረመ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

አንቀጽ ፯፻፲፪ <u>ከባድ አታላይነት</u>

ከባድ የአታላይነት ወንጀል ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና እስከ ብር ሃምሣ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣው፦

ሀ/ ጥፋተኛው በአንቀጽ ፯፻፴፪(፩) እና (፪)(ሀ) በተገለፀው መሠረት እምነት በሚጣልበት የሥራ ደረጃ ወይም ኃላፊነት ላይ የሚገኝ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ አድራጊው የማህበር፣ የባንክ፣ የንግድ፣ የአክሲዮን ገበያ ወይም የኢንዱስትሪ መሥሪያ ቤት አክሲዮን፣ የዕዳ ሰነድ፣ የቦንድ ወይም ማናቸውንም የዋስትና ሰነድ በማውጣት ከሕዝብ ገንዘብ ለመሰብሰብ ጥሪ ያደረገ ወይም ለራሱ ወይም ለድርጅቱ ወይም አድራጊው የአክሲዮን ባለድርሻ ለሆነበት ድርጅት የሸጠ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በሕዝብ አስተዳደር ወይም በሕዝብ አገልግሎት ላይ እንደሆነ፤

ነው።

አንቀጽ ፮፻፺፯ <u>ሌሎች ወንጀሎች</u>

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ወንጀሎች በቀር ስለአክሲዮኖች፣ ስለዕቃ ሰነዶች፣ ስለቦንዶች ወይም ስለማናቸውም የዋስትና ሰነዶች በሚወጡ አዋጆች ወይም ደንቦች ላይ የተደነገገ ወንጀል ሲኖር ሌላ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ያስቀጣል።

አንቀጽ ፮፻፺፰ <u>ኢንሹራንስ በሚመለከት የሚፈጸም የአታላይነት ድርጊት</u>

፩ ማንም ሰው የማይገባ ብልፅግናን ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፦

ሀ/ ኢንሹራንስ የተገባበትን አደጋ በመፍጠር፤ ወይም

ለ/ በውሉ ውስጥ በተገለፀው ጥቅም ላይ ተጽዕኖ በሚያደርግ አኳኋን የኢንሹ ራንሱን ገንዘብ ልክ፣ የውሉን ዘመን፣ ወይም የኢንሹራንሱ ተጠቃሚዎችን የሚመለከት ፍሬነገር በመደበቅ፣ በማሳሳት፣ በማረጋገጥ ወይም ይህንኑ በሚመለከት ሐሰተኛ መግለጫ በመስጠት አንድ የኢንሹራንስ ማህበርን ያታለለ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በማናቸውም ሌላ መንገድ ከኢንሹራንስ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የአታላይነት ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፣

በቀላል እስራት ወይም ሁኔታዎቹ በይበልጥ ከባድ ሲሆኑ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከብር ሃምሣ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉን የፈጸመው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል::

አንቀጽ ፯፻፴፱ <u>በሐሰተኛ ሰነድ ማታለል</u>

ማናቸውም ዓይነት የማታለል ተግባር የተፈፀመው ወደ ሐሰተኛነት በተለወጠ ሰነድ አማካይነት ሲሆን አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ::

አንቀጽ ፯፻ <u>በሕዝብ እምነት በመጠቀም ማታለል</u>

፩ ማንም ሰው ለራሱ ብልጽግናን ለማግኘት አስቦ መንፈስን እጠራልሃለሁ፣ ጋኔን እስብልሃለሁ፣ ደንቃራ እጥልልሃለሁ፣ እጠንቁልልሃለሁ፣ ዕድልህን እነግርሃለሁ፣ ነገርህን እገልጽልሃለሁ፣ ኮከብህን እቆጥርልሃለሁ፣ ሕልምህን እፈታልሃለሁ፣ የወደፊት ዕድልህን አውቅልሃለሁ፣ ውስጥ እጅህን እነብልሃለሁ፣ ከሞተ ሰው ጋር አነጋግርሃለሁ በማለት ፣ ወይም በሰው እምነት

ያለአግባብ መገልገል በሚያስችል በማናቸውም ሌላ መንገድ ሌላውን ሰው ያታለለ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት አፈጻጸሙ በደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎች የሚያስቀጣው ካልሆነ በቀር /አንቀጽ ፰፻፰፩/ በመቀጮ፣ ወይም የተደጋገመ ወንጀል በፈፀመ ጊዜ በቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ የአታላይነት ተግባር የተፈፀመው በአንቀጽ ፯፻፺፪ በተመለከተው ዓይነት ከሆነ በዚሁ በተጠቀሰው ሕግ የተደነገገው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል::

አንቀጽ ፯፻፮ <u>ሌሎች የማታለል ድርጊቶች</u>

፩ ማንም ሰው ከባድ በሽታ ወይም ጉደለት አለብኝ ወይም ከፍተኛ አካላዊ ወይም ስነልቦናዊ ጉዳት ወይም የገንዘብ ወይም ሌላ ማቴሪያላዊ ኪሳራ ደረሰብኝ በማለት የሀሰት ንግግር በማድረግ ወይም የሰዎችን የሀዘኔታ ስሜት በሚስብ በማናቸውም ሌላ የማታለል ዘዴ በመጠቀም ከግለሰብ ወይም ከሕዝብ ላይ ገንዘብ ወይም ማቴሪያላዊ ነገር የሰበሰበ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከተው ንዑስ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ችግሮች አንዱ በሌላ ሰው ላይ የደረሰ አስመስሎ የተባለውን ሰው ለሕዝብ በማቅረብ በመለመኛነት የተገለገለበት እንደሆነና፤ ይህንኑ ሰው ለመርዳት ነው በማለት ከግለሰቦች ወይም ከሕዝብ ገንዘብ ወይም ማቴሪያላዊ ነገር የሰበሰበ እንደሆነ ፤

BACK



ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

፫ ማንም ሰው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት በማድረስ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፪) ለተመለከተው ዓላማ የተጠቀመበት እንደሆነ፤

ከሶስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል::

በሰው ላይ ጉዳት ስለማድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች (አንቀጽ ፭፻፵፫ እና ፭፻፵፬) በተደራቢነት ተፈፃሚ እንዳይሆኑ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ አያግድም::

፬ ማንም ሰው ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊ፣ ማሕበራዊ ወይም ሰብዓዊ ጉዳዮችን ወይም ማናቸውንም ሌላ ዓላማ ምክንያት በማድረግ በሕግ ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን ተፈቅዶለትም ሆነ ሳይፈቀድለት ከግለሰብ ወይም ከሕዝብ ላይ ገንዘብ ወይም ማናቸውንም ማቴሪያላዊ ነገር ሰብስቦ ይህንኑ ገንዘብ ወይም ማቴሪያላዊ ነገር በሙሉም ሆነ በከፊል ከሰበሰበበት ዓላማ ውጭ ያለአግባብ ያዋለ እንደሆነ፤

ገንዘብ ያለፍቃድ ስለመሰብሰብ የተመለከተው የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከሰላሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፭ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) ወይም (፬) ከተመለከቱት ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ ሲሆን በዚህ ህግ በአንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል::

BACK



## አንቀጽ ፯፻፪ በሌላ ሰው ጥቅም የሥራ አመራር ላይ የተፈፀመ ጉዳት

፩ ማንም ሰው በሕግ ወይም በውል ግዴታ የሌላን ሰው የንብረት ጥቅም እንዲጠብቅ ወይም ሥራውን እንዲመራ በሕግ ወይም በውል ግዴታ አደራ ተቀብሎ፣ በተሰጠው ኃላፊነት ያለአግባብ በመገልገል ወይም የተጣለበትን ግዴታ ባለመፈፀም በሚጠብቀው የንብረት ጥቅም ላይ ወይም ለሚሰራበት ድርጅት በሚፈጽመው አገልግሎት ላይ አስቦ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ድርጊቱ በቸልተኛነት የተፈፀመ ከሆነ በመቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል::

፫ ተከሳሹ ወንጀሉን የፈፀመው የንብረት ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቀላል እስራት ሆኖ ከብር ሠላሳ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ በተጨማሪ ይወሰንበታል::

## አንቀጽ ፯፻፫ ከባድ ሁኔታ

፩ ወንጀሉ የተፈፀመው:-

ሀ/ በተሰጠው ሥልጣን ሥራውን በማከናወን ላይ በሚገኝ ወይም በተለይ ታማኝነት በተሰጠው ሞግዚት፣ ጠበቃ፣ ውል አዋዋይ፣ የባንክ ሠራተኛ፣ የንብረት አስተዳዳሪ ወይም ሂሣብ አጣሪ ወይም በሹመት ሥልጣን ባገኘ ወይም የተለየ እምነት የተጣለበት ማንኛውም ሌላ ሰው እንደሆነ ፤ ወይም የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ

ኃላፊነት በተሰጠው በማንኛውም ሌላ ሰው እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በመንግሥት ወይም በሕዝብ ንብረት ላይ እንደሆነ፤

ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና ከብር ሃምሣ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል::

፪ አድራጊው በተሰጠው ሃላፊነት ወይም ተግባር መሠረት ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ከሌላ ሰው ላይ ማናቸውንም ዓይነት ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ሃያ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራትና ከብር መቶ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፫ አድራጊው በተሰጠው ሃላፊነት ወይም ተግባር መሠረት ማድረግ የሚገባውን ለመፈፀም ሲል ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም ከባለጉዳዩ የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር አስር ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፬ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ሹም በመንግሥት ጥቅም ላይ የሚፈፅመውን የተንኮል ሥራ አመራር፣ ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም መቀበል የሚመለከቱት

ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው /አንቀጽ ፬፻፱፣ ፬፻፲ እና ፬፻፲፪/፡፡

## አንቀጽ ፯፻፩ ጥቅም ታገኛለህ በማለት ሌላውን ሰው በመደለል ማነሳሳት

፩ ማንም ሰው የንብረት ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የተበዳዩን ግልጽ የሆነ መንፈስ ደካማነት፣ በእርሱ ላይ የጣለውን እምነት ወይም በንግድ ሥራ ልምድ የሌለው መሆኑን ምክንያት በማድረግ፣ ተበዳዩ ካለው ንብረት ጋር ያልተመጣጠነ እና ከባድ ኪሣራ የሚያስከትልበት መሆኑን እያወቀ ሠርቼ አተርፋለሁ የሚል እምነት እንዲያድርበት በማድረግ ባለዋጋ ወረቀቶችን ወይም ሸቀጦችን እንዲገዛ፣ እንዲሸጥ ወይም ሌላ ተመሣሣይ ድርጊት እንዲፈፅም ያነሣሣው እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት ሲሆን በመቀጮ ያስቀጣል፡፡

## አንቀጽ ፯፻፪ ችሎታ የሌላቸውን ሰዎች ንብረታቸውን የሚጐዳ ሥራ እንዲፈፅሙ ማነሣሣት

፩ ማንም ሰው በአንቀጽ ፯፻፩ በተገለፀው አሳብ፣ ለአካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ወይም በሕግ ችሎታ የሌለውን ሰው መንፈስ ቀላልነት፣ በበዳዩ ላይ የጣለውን እምነት ወይም ልምድና ችሎታ የሌለው መሆኑን መሠረት በማድረግ፤

ሀ/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ወይም ገንዘብ እንዲሰጠው፣ እንዲያበድረው፣ ለዚሁ ቃል እንዲገባለት፣ የዕዳ አለብኝ መተማመኛ እንዲሰጠው ወይም ሌላ ጥቅም እንዲሰጠው በመደለል ያነሳሳው እንደሆነ፤ ወይም

BACK



ለ/ በጠቅላላው በራሱ ወይም በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳትን ለማድረስ የሚችል ሥራ እንዲፈፅም ወይም ሊፈፅም የሚገባውን ሥራ እንዲተው ያነሳሳው እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ እንዲሁም በተመሣሣይ ዓላማ ይህን የመሰለውን ቃል ወይም የገንዘብ ማስከፈያ ሰነድ ወይም የማረጋገጫ ዋስትና የተቀበለና ለራሱ ያደረገ ወይም ለሌላ ሰው አሳልፎ የሰጠ በዚሁ ዓይነት ይቀጣል::

## ክፍል ሁለት

## በኮምፒዩተር አማካይነት የሚፈፀሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፯፻፮ ያለፈቃድ ወደ ኮምፒዩተር መግባት፣ የኮምፒዩተር አገልግሎትን ያለፈቃድ መውሰድ ወይም መጠቀም

፩ ማንም ሰው ወደ ኮምፒዩተር፣ ኮምፒዩተር ሥርዓት ወይም ኮምፒዩተር መርበብ ያለፈቃድ የገባ እንደሆነ፤

በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው ወደ ኮምፒዩተር፣ ኮምፒዩተር ሥርዓት ወይም መርበብ ያለፈቃድ በመግባት አስቦ ዳታን ወይም ኮምፒዩተር አገልግሎትን የወሰደ ወይም የተጠቀመበት ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ያደረገ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ፣ ወይም ነገሩ በይበልጥ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ሃያ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፫ ወንጀሉ በቸልተኛነት የተፈፀመ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከሁለት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

አንቀጽ ፯፻፯ በዳታ ላይ ጉዳት ማድረስ

፩ ማንም ሰው ያለፈቃድ ወደ ኮምፒዩተር ሥርዓት ወይም ኮምፒዩተር መርበብ ገብቶ በእነዚህ ውስጥ ያለን ማናቸውም ዳታ አስቦ በመጨመር፣ በመለወጥ፣ በመሰረዝ፣ ወይም በማጥፋት ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣

ከሶስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ወንጀሉ የተፈጸመው:-

ሀ/ ለመስረቅ፣ ለማጭበርበር፣ ለማታለል ወይም ለመንጠቅ እንዲቻል ማናቸውንም እቅድ ለማውጣት ወይም ለመተግበር፣ ወይም ገንዘብን፣ ንብረትን፣ የኮምፒዩተር አገልግሎትን ወይም ማናቸውንም ዳታ ያለአግባብ ለመቆጣጠር ወይም ለማግኘት ከሆነ፣ ወይም

ለ/ ከላይ በፊደል (ሀ) የተገለጸው እቅድ ባይኖርም ነገሩ ከባድ ከሆነ፣

ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ሃያ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

፫ ድርጊቱ የተፈፀመው በቸልተኛነት ከሆነ፣ ቅጣቱ ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከሁለት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል::

## አንቀጽ ፯፻፰ <u>የተፈቀደለት ተጠቃሚ የኮምፒዩተር አገልግሎቶችን እንዳያገኝ ማቋረጥ</u>

፩ ማንም ሰው ወደ ኮምፒዩተር፣ ኮምፒዩተር ሥርዓት ወይም ኮምፒዩተር መርበብ ያለፈቃድ በመግባት የተፈቀደለት ተጠቃሚ የኮምፒዩተር አገልግሎቶችን እንዳያገኝ አስቦ ያቋረጠበት እንደሆነ፤

ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

፪ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኛነት ከሆነ ቅጣቱ ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከብር ሁለት ሺህ የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

## አንቀጽ ፯፻፱ <u>የኮምፒዩተር ወንጀሎችን አፈፃፀም ለማመቻቸት የሚከናወኑ ድርጊቶች</u>

ማንም ሰው ከዚህ በላይ በተደነገጉት ሦስት አንቀጾች ከተዘረዘሩት ድርጊቶች አንዱን ለመፈፀም እንዲያግዘው በማሰብ መሣሪያዎችን፣ የምስጢር ኮዶችን ወይም ማለፊያ (መለያ) ቃላትን ወደ አገር ወስጥ ያስገባ፣ ያመረተ፣ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ያከፋፈለ፣ የገዛ፣ የተቀበለ ወይም ይዞ የተገኘ እንደሆነ፤

በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

## እንቀጽ ፯፻፲ <u>ሌሎች ወንጀሎች</u>

በዚህ ክፍል ከተደነገጉት ውጭ ሌላ ወንጀል በኮምፒዩተር አማካይነት የተፈጸመ እንደሆነ፤ አግባብነት ያለው ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ ፯፻፲፩ <u>የወንጀሎች መደራረብ</u>

በኮምፒዩተር አማካይነት የሚፈፀም ማናቸውም ዓይነት ወንጀል በዚህ የወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ሌላ ወንጀል አስከትሎ እንደሆነ፤ ለዚሁ ወንጀል ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## የኅሊናን ወይም የሰውን ችግር መሠረት በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፯፻፲፪ አራጣ

፩ ማንም ሰው የተበዳዩን ችግረኛነት፣ የበታችነቱን፣ ወይም የገንዘብ ችግሩን፣ ወይም መንፈስ ደካማነቱን፣ ወይም ልምድ ወይም ችሎታ የሌለው መሆኑን መሠረት በማድረግ:-

ሀ/ በሕግ ከተፈቀደው ወለድ በላይ ገንዘብ ያበደረው እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ካበደረው ገንዘብ ጋራ በግልፅ ተመጣጣኝነት የሌለውን ንብረት በምትኩ እንዲሰጠው ያደረገው ወይም ቃል ያስገባው እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት፣ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው በተመሣሣይ አሳብ በአራጣ ላይ የተመሠረተ መብት የተቀበለ፣ በመከላከያነት የተጠቀመበት ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፈ እንደሆነ፤ ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት ይቀጣል::

### አንቀጽ ፯፻፲፫ በማስገደድ መጠቀም

ማንም ሰው የማይገባውን የንብረት ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ሲል ገንዘብን ወይም ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ሰነድ ወይም መብት የሚሰጥ ወይም ዕዳ የሚያስቀረውን ወይም ማናቸውንም ይሆን የመሳሰለ ጥቅም ያለበትን ነገር እንዲሰጠው ለማድረግ ከወንበዴነት ወንጀል ውጭ /አንቀጽ ፮፻፸/ የኃይል ወይም ከፍ ያለ

የዛቻ ድርጊት በሌላው ሰው ላይ የፈፀመ ወይም እንዳይከላከል ያደረገ እንደሆነ፤

እጅግ ቢያንስ በሦስት ወር ቀላል እሥራት፣ ወይም እንደ ወንጀሉ ከባድነት ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል::

አንቀጽ ፯፻፲፬ <u>ጥቅም ለማግኘት ማስፈራራት</u>

ማንም ሰው ተበዳዩን ወይም ከዚሁ ሰው ጋራ በዝምድና ወይም በፍቅር ቅርብ ግንኙነት ያለውን ሰው ለመጉዳት የሚችል ወሬ ወይም ነገር እውነትም ቢሆን እንኳን በማናቸውም ዘዴ እገልጻለሁ ወይም አሳውቃለሁ ወይም አጋልጣለሁ በማለት አስፈራርቶ፣ በተበዳዩ ወይም በሌላው ሰው ንብረት ላይ ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ ተበዳዩ ዝም እንዲል ያደረገው እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፯፻፲፫ በተገለጸው ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል::

አንቀጽ ፯፻፲፭ <u>ከባድ ሁኔታ</u>

ቅጣቱ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከአሥር ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ የሚሆነው፤ አራጣ በመቀበል፣ አስገድዶ በመጠቀም ወይም ጥቅም ለማግኘት በማስፈራራት የተከሰሰው ሰው:-

ሀ/ ሕጋዊ ፈቃድ ያገኘበትን ሙያ ወይም ሥራ ያለአግባብ በመሥራት ወንጀሉን የፈፀመው እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ወንጀሉን የፈፀመው ለአካለመጠን ያልደረሰውን ወይም ችሎታ የሌለውን ወይም መንፈስ ደካማ የሆነውን ለመጉዳት እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ አስቀድሞ ውጤቱን እየገመተ ድርጊቱን በመደጋገም በተበዳዩ ላይ የሀብት መራቆት እንዲደርስበት ወይም ተበዳዩ እራሱን እንዲገድል ገፋፍቶት እንደሆነ፣ ነው::

## ርዕስ ሁለት

## በንግድና በኢኮኖሚ ጉዳይ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፯፻፲፮ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት

፩ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፬ በተደነገገው መሰረት በዚህ ርዕስ ስር ከተመለከቱት ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ እንደወንጀሉ ዓይነት በአንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል::

፪ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ሁኔታ ወንጀል በሚፈፀምበት ጊዜ በድርጅቱ የሥራ አመራር ውስጥ ባለው የሥራ ድርሻ የተነሣ በወንጀሉ ተካፋይ የሆነ ሥራ አስኪያጅ፣ ነገረፈጅ፣ አባል፣ አስተዳዳሪ ወይም የቁጥጥር ወይም የሂሣብ አጣሪ አካል አባል አግባብነት ባላቸው የዚህ ርዕስ ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል::

፫ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የአንቀጽ ፻፴፫ ድንጋጌን ተፈፃሚነት አያስቀረውም::

## ምዕራፍ አንድ

## ግዙፍነት በሌላቸው መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፯፻፲፯ በሌላ ሰው መልካም ስም ላይ ጉዳት ማድረስ

፩ ማንም ሰው በተንኰል ወይም ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ሐሰት መሆኑን የሚያውቀውን ንግግር ወይም መጥፎ አሳብ በመግለጽ ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ

BACK



ሁኔታ የሌላውን ሰው መልካም ስም በከፍተኛ ደረጃ የጐዳ ወይም ጥርጣሬ ውስጥ ያጣለ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

፪ የሐሰት ሐሜት ክስን የሚመለከተው የዚህ ሕግ ድንጋጌ /አንቀጽ ፯፻፲፫(፫)/ ከዚህ አንቀጽ ጋር በተደራቢነት ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም።

አንቀጽ ፯፻፲፰ ጉዳትን የሚያደርሱ ሐሰተኛ መግለጫዎች

ማንም ሰው መሥራች፣ አባል፣ አስተዳዳሪ፣ የሥራ መሪ፣ ነገረፈጅ፣ የአመራር ቦርድ፣ የኦዲት ቦርድ አባል ወይም አጣሪ በመሆን የአንድን ድርጅት፣ የንግድ ማኅበር ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር ልዩ ልዩ ጉዳይ የሚያውቅ ሆኖ ሳለ፣ ሕዝብ እንዲያውቀው በሚደረግ ማስታወቂያ ወይም ለጠቅላላ ጉባኤ በሚቀርብ ሪፖርት ወይም አሳብ ላይ ጉጂ እና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ አስቦ የሰጠ ወይም እንዲሰጥ ያደረገ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

አንቀጽ ፯፻፲፱ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር

ማንም ሰው በማጭበርበር ወይም የንግድ ሥራ የሚጠይቀውን ቅን ልቦና በሚቃረን ማናቸውም ሌላ አሠራር በሌላ ሰው ላይ አስቦ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የፈፀመበት፤ በተለይም፦

ሀ/ ከተፎካካሪዎቹ የተሻለ ጥቅም ለማግኘት ሲል የሌላውን ሰው መልካም ስም፣ ዕቃዎች ወይም

አሠራሮች፣ እንቅስቃሴዎች ወይም ንግድ በማጣጣል፣ ወይም ስለራሱ ምርቶች፣ አሠራር፣ እንቅስቃሴ ወይም ንግድ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የሐሰት መግለጫ በመስጠት፤ ወይም

ለ/ የራሱን ዕቃዎች፣ አሠራሮች ወይም ምርቶች ወይም ንግድ ከሌላው ጋር የሚያምታቱ ርምጃዎችን በመውሰድ፤ ወይም

ሐ/ ስለእራሱ ልዩ ሁኔታ ወይም ችሎታ በሌሎች ላይ እምነት ለማሳደር ሲል እውነት ያልሆነ ወይም ሐሰተኛ ዘዴ፣ መለያ ምልክት፣ ምልክት ወይም ሙያዊ መጠሪያ በመጠቀም፤ ወይም

መ/ ተገቢ ተግባራቸውን ወይም የሥራ ግዴታውቻቸውን እንዳይወጡ ለማድረግ ወይም የአሠሪያቸውን የአመራረት፣ የአደረጃጀት ወይም የአሠራር ምስጢር እንዲያገኙ ወይም እንዲገልጹ ለመገፋፋት ሲል ለንግድ ተወዳዳሪው ሠራተኞች፣ ወኪሎች ወይም ረዳቶች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም በመስጠት ወይም በማቅረብ፤ ወይም

ሠ/ ለቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ በማናቸውም ሌላ መንገድ እነዚህን የተገኙ ወይም የተገለፁ ምስጢሮችን በመግለፅ ወይም በነሱ በመጠቀም፤

እንደሆነ፤ የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፯፻፳ ምልክቶችን፣ የመገኛ ምንጭ ማስታወቅን፣ ዲዛይኖችን ወይም ሞዴሎችን መጣስ

፩ ማንም ሰው አስቦ:-

ሀ/ ሕዝብን በሚያሳስት መልክ የንግድ፣ የኢንዱስትሪ ወይም የግብርና ይሁን በሌላው ሰው ምርት ወይም ዕቃ ወይም የነዚሁ መጠቅለያ ወይም ማሸጊያ ላይ የሚደረጉትን ምልክቶች፣ መለያ ምልክቶች ወይም የመገኛ ምንጭ ማስታወቂያዎችን የጣሰ፣ ወይም አስመስሎ ያቀረበ፤ ወይም

ለ/ ወደ ሐሰት የተለወጠ፣ የተቀዳ፣መስሎ የቀረበ ወይም ያላግባቡ የተለጠፈ መሆኑን የሚያውቀውን ምልክት ያለበትን ምርት ወይም ዕቃ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ወደአገር ውስጥ ያስገባ፣ ወደ ውጭ የላከ፣ ያከፋፈለ ወይም ለገበያ ያቀረበ፤ ወይም

ሐ/ በይዞታው ስር ያሉትን ይህ ምልክት ያለባቸውን ምርቶች ወይም ዕቃዎች መገኛ ምንጭን ለመግለፅ እምቢ ያለ፤

እንደሆነ፤ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪ ማንም ሰው በአግባቡ በተመዘገቡና በብሔራዊ ወይም ዓለምአቀፋዊ ሕጐች ወይም ስምምነቶች በተጠበቁ የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች፣ በተለይም ኢንዱስትሪያዊ ንድፎች ወይም ዓይነቶች፣ የፓቴንት ፈጠራዎች ወይም አሠራሮች ረገድም ከላይ በተገለፀው ዓይነት ሕገወጥ አድራጐት የፈጸመ እንደሆነ፤ በተመሳሳይ ቅጣት ይቀጣል።

፫ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ድርጊት የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል።

**አንቀጽ ፯፻፳፩ <u>የድርሰት፣ የኪነጥበብ ወይም የአእምሮ ሥራ ፈጠራ መብቶችን መጣስ</u>**

፩ ማንም ሰው አስቦ የድርሰት፣ የኪነጥበብ ወይም የአእምሮ ሥራ ፈጠራ መብቶችን በሚመለከት የተደነገገውን ሕግ የጣሰ እንደሆነ:-

ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ ድርጊቱ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ያስቀጣል::

**አንቀጽ ፯፻፳፪ <u>የግል አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>**

የዚህ ምዕራፍ ወንጀሎች የሚያስቀጡት በግል አቤቱታ አቅራቢነት በሚሆንበት ጊዜ፣ የግል አቤቱታ የማቅረብ መብት ያላቸው በወንጀሉ የተጐዱ ሰዎች ወይም የሙያ ማህበሮቻቸው ናቸው::

**አንቀጽ ፯፻፳፫ <u>ከባድ ሁኔታዎች</u>**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱ የተፈጸመው አታላይነትን ለመፈጸም እንዲያመች ታስቦ እንደሆነ፤ ለአታላይነት የተመለከተው ቅጣት በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናል::

**አንቀጽ ፯፻፳፬ <u>ተጨማሪ እርምጃዎች</u>**

ከወንጀል ቅጣቱ እና በፍትሐብሔር ከሚደረገው ማናቸውም ጥያቄ በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ የወንጀሉ አካል የሆኑ ነገሮችን፣ ዕቃዎችን ወይም ሥራዎችን እንዲሁም ከሽያጩ ወይም ከትወናው የተገኘው ገንዘብ እንዲወረስ ያዝዛል::

ፍርድ ቤቱ ፍርዱ ለሕዝብ እንዲገለፅ ያደርጋል::

BACK



## ምዕራፍ ሁለት

## ዕዳን ለማስከፈል በሚደረግ ክስ አቀራረብ፣ በፍርድ አፈፃፀም እና በአከሳሰር ጉዳይ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፯፻፳፭ በማጭበርበር ዕዳ ለመክፈል አለመቻል

ማንም ሰው መክፈል የማይችለው ዕዳ ያለበት መሆኑን አስቦ የደበቀና ግዴታውን ለመፈፀም አለመቻሉን ወይም ፈቃደኛ አለመሆኑን እያወቀ ውል የተዋዋለ እንደሆነ፤

የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከሃምሣ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም በቀላል እሥራት ይቀጣል::

### አንቀጽ ፯፻፳፮ አላግባብ መክሰር

፩ ማንኛውም በንግድ ሥራ የተሠማራ ባለዕዳ ንግዱን በሚያከናውንበት ጊዜ ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ወይም ሂሳብ ባለመያዝ፣ ያልተመጣጠነ ወጪ በማድረግ ወይም አተርፍበታለሁ በሚል አደገኛ ግምት ብዙ ዕቃዎችን በመግዛት፣ በማጠራቀም ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ወይም ባግባቡ ንግዱን ባለማካሄድ አስቦ በገዛ እጁ ዕዳውን ለመክፈል በማይችልበት ሁኔታ እንዲገኝ ያደረገ ወይም ይህን ሁኔታውን ያባባሰ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ድርጊቱን የፈፀመው በቸልተኛነት ሲሆን፤ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፫ በንግድ መዝገብ ላይ ባልተመዘገበ ባለዕዳ ላይ ክስ የሚቀርበው በባለገንዘቡ የግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ ይሆናል:: የግል አቤቱታውም፣ ባለዕዳው ሀብት

BACK



የሌለው መሆኑ እንዲታወቅለት ካመለከተበት ጊዜ ጀምሮ ባለው ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል::

፬ ከዚህ በላይ የተደነገጉትን ሥራዎች እንዲፈፅም አነሳስቶ የባለዕዳውን መንፈስ ቀላልነት ወይም ቸልተኛት ተጠቅሞ ወደዚሁ መንገድ የመራ ወይም አራጣ በመቀበል የተጠቀመበት ባለገንዘብ በባለዕዳው ላይ ክስ ማቅረብ አይችልም::

አንቀጽ ፯፻፳፯ በማጭበርበር ኪሣራ እንዲደርስ ማድረግ

፩ መክሰሩ በፍርድ የተወሰነበት ማንኛውም ባለዕዳ:-

ሀ/ ግዙፍነት ባለው መልኩ የሀብቱ ክፍል የሆነውን አንድ የተወሰነ ንብረት ለሌላ ሰው በማስተላለፍም ይሁን በማጥፋት፣ በማበላሸት፣ ዋጋው እንዲቀንስ ወይም ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆን በማድረግ፣ ወይም

ለ/ በልብወለድ ፈጠራ፣ በተለይም ከንብረቱ አንዳንዶቹን በመቀነስም ይሁን በመሰወር፣ የሌለበትን ዕዳ ወይም የገንዘብ ጥያቄ በማመን ወይም አለብኝ ብሎ በመቀበል ወይም ዕዳ ሳይኖርበት ዕዳ አለብህ ብሎ ሦስተኛ ወገን እንዲጠይቀው በማነሳሳት፣ ወይም በማናቸውም ሌላ የማስመሰል ዘዴ በተለይም ትክክለኛ ባልሆነ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ፣ ወደሐሰት የተለወጠ መዛግፍ ወይም ሐሰተኛ የሂሳብ ሚዛን ተጠቅሞ በእርግጥ ካለው ሀብት ያነሰ ሀብት እንዳለው በማስመሰል፣ ከእርሱ ላይ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸውን ባለገንዘቦች ለመጉዳት፣

አስቦ ንብረቱ ከእጁ እንዲወጣ ወይም እንዲባክን ያደረገ እንደሆነ፣ ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ የተፈፀመው ወንጀል ከፍያለ ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ወይም ድርጊቱ የተፈፀመው በመከላከያ ሠራዊት ወይም በመንግሥት ድርጅት ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ላይ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከስምንት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይሆናል::

፫ ማንኛውም ሦስተኛ ወገን ገንዘብ ጠያቂዎችን ለመጉዳት እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፣ ከሦስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፬ አድራጊው ወንጀሉን ለመፈፀም የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም ድርጊት ፈፅሞ የተገኘ እንደሆነ፣ ስለማታለል የተመለከተው ድንጋጌ በተደራራቢነት ተፈፃሚ ይሆናል::

አንቀጽ ፯፻፳፫ <u>በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚፈፀም የማጭበርበር ድርጊት</u>

፩ በፍርድ አፈፃፀም የተከሰሰ ባለዕዳ ንብረት የሌለው መሆኑ በጽሁፍ ከታወቀ በኋላ የገንዘብ ጠያቂዎቹን ጥቅም ለመጉዳት በማሰብ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፯፻፳፯ በተመለከተው መሠረት በግዙፍ አድራጎት ወይም በልብወለድ ፈጠራ ንብረቱ እንዲቀንስ ያደረገ እንደሆነ፣

በቀላል እሥራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪ በገንዘብ ጠያቂዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት የፈጸመ ማንኛውም ሦስተኛ ወገን በቀላል እሥራት ይቀጣል::

አንቀጽ ፮፻፸፱ <u>በመያዣነት ወይም በሕግ አግባብ የተያዘን ንብረት ያለአግባብ መውሰድ ወይም ማጥፋት</u>

፩ ማንኛውም ባለዕዳ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በገንዘብ ጠያቂው ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ገንዘብ ጠያቂው በመያዣነት፣ በሪም ወይም በአላባ የያዘውን የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት የወሰደ፣ ለሌላ ያስተላለፈ፣ የጐዳ፣ ዋጋው እንዲቀንስ ወይም እንዳያገለግል ያደረገ እንደሆነ፤

ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ገንዘብ ጠያቂዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ይህን ዓይነት ድርጊት የፈጸመ ማንኛውም ሦስተኛ ወገን ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከሃምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

አንቀጽ ፮፻፹ <u>በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተያዘን ንብረት ያለአግባብ መውሰድ ወይም ማጥፋት</u>

፩ ማንም ሰው ገንዘብ ጠያቂዎቹን ለመጉዳት ሲል በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረውን ወይም የተያዘውን፣ በኪሣራ ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበውን ወይም የይዞታ መብት በተሰጠበት መዘርዝር ውስጥ ተቆጥሮ የተገፈውን ዕቃ ያለአግባብ የወሰደ፣ ያላግባብ ሥራ ላይ ያዋለ፣ ያጠፋ፣ ያበላሸ፣ ዋጋው እንዲቀንስ ወይም ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆን ያደረገ እንደሆነ፤

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

BACK


፪ ገንዘብ ጠያቂዎችን ለመጉዳት እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት የፈጸመ ሦስተኛ ወገን በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል::

፫ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚያስቀጡት ድርጊቶች የተፈፀሙት ገንዘብ ጠያቂዎችን ብቻ ለመጉዳት እንደሆነ፣ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፴፱ ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ አይሆንም::

አንቀጽ ፯፻፴፩ <u>በገንዘብ ጠያቂዎች መካከል ተገቢ ያልሆነ አድልዎ ማድረግ</u>

መክሠሩ በፍርድ የታወቀ ወይም ሀብት ስለማጣቱ ሕጋዊ ማረጋገጫ ያቀረበ ማንኛውም ባለዕዳ ዕዳውን በሙሉ ሊከፍል የማይችል መሆኑን እያወቀ በማናቸውም ዘዴ፣ በተለይም:-

ሀ/ የመክፈያው ጊዜ ያልደረሰውን ዕዳ በመክፈል ወይም የመክፈያ ጊዜያቸው ሲደርስ ዕዳዎችን ከጥሬ ገንዘብ ወይም ከተለመደው የዕዳ መክፈያ ሰነዶች ውጭ በሆነ መንገድ በመክፈል፣ ወይም

ለ/ እንዲሰጥ ሳይገደድ በገዛ ፈቃዱ ዕዳውን እንደሚከፍል የሚያረጋግጥ ዋስትና ወይም መያዣ በመስጠት፣ ወይም

ሐ/ በማናቸውም ሌላ ተመሣሣይ መንገድ የተወሰኑ ገንዘብ ጠያቂዎችን በመጥቀም፣

ሌሎቹን የጐዳ እንደሆነ፣ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

BACK



አንቀጽ ፮፻፴፪ <u>የድምፅ ብልጫን ለማግኘት መደለያ መስጠት</u>

፩ ማንም ባለዕዳ ከገንዘብ ጠያቂዎቹ የአንዱን የድምፅ ድጋፍ ወይም ከፍርድ ቤት የስምምነት ማፅደቂያን ለማግኘት ሲል፡-

ሀ/ ለዚያ ገንዘብ ጠያቂ ወይም በጠቅላላው ስብሰባ ላይ ተወካዩ ለሆነው፤ ወይም

ለ/ በመክሰር የሒሳብ ማጣራት አስተዳደር ወይም የሒሳብ አጣሪ አባል ለሆነ ሰው፤

የተወሰነ ጥቅም የሰጠ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፤

ከሦስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

፪ ባለዕዳውን ለመጥቀም ሲል እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት የፈጸመ ሦስተኛ ወገን ወይም ይህን ዓይነቱን ጥቅም ለዚህ ሦስተኛ ወገን እንዲሰጥ ወይም ቃል እንዲገባ ያደረገ ማንኛውም ሌላ ሰው፤ በተመሳሳይ ቅጣት ይቀጣል፡፡

አንቀጽ ፮፻፴፫ <u>ስምምነትን በማጭበርበር ማግኘት</u>

፩ ማንኛውም ባለዕዳ የስምምነት ጊዜ ማራዘሚያ ቀጠሮ ወይም የስምምነት ማጽደቂያ ከፍርድ ቤት ለማግኘት ሲል በማናቸውም ዘዴ በተለይም ትክክለኛ ባልሆነ ወይም በተጭበረበረ ሒሳብ አያያዝ ወይም የሒሳብ ሰነድ፣ መጻጻፎች ወይም የሒሳብ ሚዛን አማካይነት ስላለበት የገንዘብ ሁኔታ ገንዘብ ጠያቂዎቹን፣ ስለመክሠር ምርመራ የሚያደርግ ዳኛን ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣንን ያሳሳተ እንደሆነ፡

በቀላል እሥራት ይቀጣል::

፪ ባለዕዳውን ለመጥቀም ሲል እንደዚህ አይነቱን ድርጊት የፈፀመ ሦስተኛ ወገን በተመሳሳይ ቅጣት ይቀጣል::

<u>ሦስተኛ ታላቅ ክፍል</u>

<u>የደንብ መተላለፍ ሕግ</u>

<u>ሰባተኛ መጽሐፍ</u>

<u>ጠቅላላ ክፍል</u>

<u>ርዕስ አንድ</u>

<u>ቅጣትን የሚመለከቱ ደንቦች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>የሕጉ ተፈፃሚነት ወሰን</u>

አንቀጽ ፲፻፹፩ <u>ወደ ወንጀል ሕግ ጠቅላላ መርሆች መምራት</u>

በዚህ መጽሐፍ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በቀር የነገሩን ዓይነት እንዲሁም የሕጉን መንፈስና ግብ በመመልከት የወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል መሠረታዊ መርሆችና ደንቦች በደንብ መተላለፍ ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ /አንቀጽ ፫ ፓራግራፍ (፪)/::

አንቀጽ ፲፻፹፪ <u>ደንብ መተላለፍ</u>

አንድ ሰው ደንብ ተላልፏል የሚባለው ሥልጣን ያለው አካል ባወጣው ሕግ የተመለከተውንና አንድ ነገር እንዳይፈፀም የሚያገዘውን ወይም የሚከለክለውን ድንጋጌ የተላለፈ ወይም በወንጀል የማያስቀጣ ቀላል ጥፋት የፈፀመ ሲሆንና የዚህ ዓይነቱ ሕግ መጣስ ወይም ቀላል ጥፋት ቀጥለው በተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚያስቀጣ ሲሆን ነው /አንቀጽ ፲፻፷፯ እስከ ፲፻፸፪/::

አንቀጽ ፯፻፴፬ <u>ሕጉ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ጥፋቶች</u>

፩ በህጋዊነት መርህ እንደተመለከተው /አንቀጽ ፪ ከ(፩) እስከ (፬)/ በዚህ የደንብ መተላለፍ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ የተደነገጉት

፪ ጥፋቶች ብቻ ያስቀጣሉ።

ሊያስቀጡ የሚችሉትም በዚህ ሕግ ውስጥ በግልፅ በተመለከቱት ቅጣቶች ብቻ ይሆናል። እነዚህም ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት ለተፈፀመው ድርጊት የበለጠ ቅጣት የሚደነግጉ አንቀጾች በሌሉ ጊዜ ብቻ ነው።

አንድ ድርጊት የሚያስቀጣው በወንጀል ሕግ ወይም በደንብ መተላለፍ ሕግ በአንደኛው ብቻ እንጂ በሁለቱም አይደለም /አንቀጽ ፪(፫)/።

፫ የደንብ መተላለፍ ተግባሮች የሚያስቀጡት፣ በተፈፀሙበት ጊዜ ጸንተው ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት እንጂ ከድርጊቱ በኋላ የወጣን ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲፈፀም በማድረግ አይሆንም /አንቀጽ ፭/።

ይህ የደንብ መተላለፍ ሕግ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሕጉ ለተመለከተው ለማናቸውም የደንብ መተላለፍ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ ፯፻፴፭ <u>ሕጉ በእኩልነት ተፈፃሚ መሆኑ</u>

ደንብ መተላለፍን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ልዩነት ሳያደርጉ በጥፋተኞች ላይ ሁሉ በእኩልነት ተፈፃሚ ይሆናሉ /አንቀጽ ፬/።

አንቀጽ ፯፻፴፮ <u>ቦታን በሚመለከት የሕጉ ተፈፃሚነት</u>

፩ የደንብ መተላለፍ ተግባሮች ተፈፅመዋል የሚባልበት ቦታ ደንብ ተላላፊው ማድረግ ያልነበረበትን ያደረገበት ወይም ማድረግ የነበረበትን ያላደረገበት ቦታ ነው /አንቀጽ ፳፭/።

እነዚህም ተግባሮች የሚመሩት በግዛት መርህ መሠረት ነው/አንቀጽ ፲፩/::

፪ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ሰው የፈፀማቸው የደንብ መተላለፍ ተግባሮች ክስ የሚታየው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ነው:: በዚህ ጊዜም ክሱን በውክልና የማየትም /አንቀጽ ፲፪/ ሆነ ተከሣሹን አሣልፎ የመስጠት /አንቀጽ ፳፩/ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆኑም::

፫ በውጭ አገር ኢትዮጵያዊ የሚፈፅማቸው ወይም በኢትዮጵያዊ ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች በኢትዮጵያ ውስጥ አያስቀጡም /አንቀጽ ፲፫/::

የማይደፈር መብት የተሰጠው ኢትዮጵያዊ እነዚህን የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች በውጭ አገር ሳለ ቢፈፅም በኢትዮጵያ ውስጥ አይከሰስባቸውም /አንቀጽ ፲፬/::

፬ በኢትዮጵያ ወታደራዊ ሕግ የተደነገጉትን ደንብ ብቻ መተላለፍ ጥፋቱ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ አገር የተፈጸመ ቢሆንም ክሱ የሚታየው የኢትዮጵያን ሕግ በመከተል በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ነው /አንቀጽ ፫፻፲፪/::

ይሁን እንጂ አድራጊው በዚሁ ጥፋቱ በውጭ አገር ፍርድ ቤቶች ተቀጥቶበት ከሆነ ፍርድ ቤቱ አዲስ ቅጣት እንዲቀር ለማድረግ ይችላል::

አንቀጽ ፫፻፴፱ <u>በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ</u>

የደንብ መተላለፍ ክስ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በሚታይበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ በውጭ አገር ፍርድ ቤት በተከሣሹ ላይ የተላለፈው የደንብ መተላለፍና የወንጀል የጥፋተኛነት ወይም የቅጣት ውሣኔ ከግምት ውስጥ አይገባም /አንቀጽ ፳፪/::

## ምዕራፍ ሁለት

## የወንጀል ተጠያቂነት

### አንቀጽ ፯፻፵ የማያስቀጡ ድርጊቶችና የሚቀጡ ሰዎች

፩ የደንብ መተላለፍ ተግባርን ለመፈፀም የሚደረጉ የመዘጋጀትና የሙከራ ድርጊቶች አያስቀጡም::

፪ እንዲሁም ለደንብ መተላለፍ የሚደረገው ማነሣሣት፣ አባሪነት እና ወንጀል ከፈፀመ በኋላ ወንጀል አድራጊውን መርዳት አያስቀጣም:: የሚቀጡት ደንብ ተላላፊው ወይም ደንብ ተላላፊዎቹ ብቻ ናቸው /አንቀጽ ፴፪/::

፫ ደንብ መተላለለፍን በሚመለከት የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት አይቀጣም፤ የሚቀጣው የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፴፪ መሰረት ሕግን፣ ደንብን ወይም መመሪያን በዋና ደንብ ተላላፊነት በሚጥስበት ጊዜ ብቻ ነው::

፬ ደንብ መተላለፍን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በወንጀል ሕግ መንፈስ /አንቀጽ ፶፪-፶፭/ በወጣት ጥፋተኞች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ::

፭ በመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች አማካይነት በሚፈፀሙ ወንጀሎች ተካፋይ ስለመሆን በወንጀል ሕግ የተመለከቱት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፵፮ - ፵፯/ በደንብ መተላለፍ ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ::

### አንቀጽ ፯፻፵፩ የማያስቀጡ ሁኔታዎች

፩ ስለወንጀል ኃላፊነትና ኢ-ኃላፊነት የተመለከቱት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች (ከአንቀጽ ፵፰ - ፶) በደንብ መተላለፍ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፪ በቸልተኛነት የተፈፀመ ድርጊት አያስቀጣም ተብሎ በሕጉ በግልፅ ከተደነገገባቸው ሁኔታዎች በቀር አስቦ ወይም በቸልተኛነት /ከአንቀጽ ፶፯-፶፱/ ደንብ የተላለፈ ማንኛውም ሰው በደንብ መተላለፍ ድንጋጌ ውስጥ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

፫ የደንብ ተላላፊ ኃላፊነትና ተቀጪነት ምንጊዜም ቢሆን በተናጠል ይሆናል /አንቀጽ ፵፩ እና ፲፫/።

## አንቀጽ ፯፻፸፪ ጉዳዩን ለማጣራት የሚወሰዱ እርምጃዎች

መደበኛ ወንጀሎችን በሚመለከት የሚወሰኑት የልዩ አዋቂ ምስክርነት እና የምርመራ እርምጃዎች /አንቀጽ ፶፩ እና ፶፪/ እንዲደረጉ በፍርድ ቤት የሚታዘዘው የጥፋተኛው ሃላፊነት በሌላ መንገድ ሊወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው።

## አንቀጽ ፯፻፸፫ የማያስቀጡና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች

፩ በሕግ የታዘዙ ወይም የተፈቀዱ ድርጊቶችን /አንቀጽ ፷፰/፣ የሞያ ሥራ ግዴታን /አንቀጽ ፷፱/፣ የተጐጂውን ፈቃድ /አንቀጽ ፸/፣ ፍፁም የሆነ መገደድን /አንቀጽ ፸፩/፣ አስፈላጊ ሁኔታን /አንቀጽ ፸፭/ እና ሕጋዊ መከላከልን /አንቀጽ ፸፰/ የሚመለከቱ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ለደንብ መተላለፍም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ሊቋቋሙት በሚችል መገደድ ወይም የአስፈላጊነት ሁኔታ ወይም የሕጋዊ መከላከል መጠንን በማሳለፍ ጊዜ ጥፋተኛው ይቀጣል፤ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ በሕግ በተፈቀደው ወሰን /አንቀጽ ፯፻፷፯/ መሠረት ቅጣቱን ሊያቃልልለት ይገባል።

፪ ከበላይ ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ታዛዡ በተሰጠው ሥልጣን ውስጥ የሚሠራን የበላይ አለቃ ትዕዛዝ

ተቀብሎ ከዚሁ ትዕዛዝ ሳይወጣ የደንብ መተላለፍ ድርጊትን የፈፀመ እንደሆነ አይቀጣም:: ትዕዛዝ የሰጠ ው ሰው ለዚያው ድርጊት ኃላፊ ይሆናል /አንቀጽ ፸፫/::

ታዛዡ ከተቀበለው ትዕዛዝ በማለፍ አስቦ ለፈፀመው ድርጊት ኃላፊ ይሆናል::

አንቀጽ ፳፻፶፬ <u>ስሕተት</u>

፩ ደንብ የተላለፈ ማንም ሰው ሕግ አለማወቅን ወይም የማድረግ መብት አለ ብሎ መሳሳትን /አንቀጽ ፹፩/ እንደመከላከያ ምክንያት አድርጎ ሊያቀርብ አይችልም::

፪ አድራጊው ድርጊቱን የፈፀመው በጭራሽ አለማወቁን ወይም አለመፍቀዱን በሚያሳይ በተረጋገጠ የሁኔታ መሳሳት እንደሆነ በደንብ መተላለፍ ተጠያቂ አይሆንም /አንቀጽ፹/::

አንቀጽ ፳፻፶፭ <u>ቅጣትን የሚያቃልሉ እና የሚያከብዱ ሁኔታዎች</u>

፩ በደንብ መተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው በወንጀል ሕጉ /አንቀጽ ፹፪ እና ፹፫/ በተመለከቱት የማቅለያ ሁኔታዎች ድርጊቱን ፈጽሞ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት /አንቀጽ ፳፻፷፯/ እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣቱን ለማቅለል ወይም በሌላ ዓይነት ቅጣት ለመለወጥ ይችላል::

፪ ጥፋተኛው በወንጀል ሕግ በተመለከቱት የማክበጃ ሁኔታዎች /አንቀጽ ፹፬ እና ፹፭/ ድርጊቱን የፈጸመ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች በተመለከተው /አንቀጽ ፳፻፷፯ እስከ ፳፻፸/ መሠረት ቅጣቱን ያከብዳል::

፫ የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ሁኔታዎች ተጣምረው ሲገኙ፤ ፍርድ ቤቱ ሁለቱንም በሚገባ በማመዛዘን ቅጣቱን ይወስናል /አንቀጽ ፻፹፱/::

## ርዕስ ሁለት

## ቅጣቶችን የሚመለከቱ ደንቦች

## ምዕራፍ አንድ

## ተፈፃሚነት ያላቸው ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች

## ክፍል አንድ

## ዋና ቅጣቶች

### አንቀጽ ፩፻፶፮ መደበኛ የሆኑ የወንጀል ቅጣቶች ተፈፃሚ አለመሆናቸው

፩ ደንብ መተላለፍ ምንጊዜም ቢሆን ለወንጀሎች በተወሰኑት በፅኑ እሥራት ወይም በቀላል እሥራት አያስቀጣም:: ደንብ መተላለፍ ከወንጀል የሚለየው በሚያስከትለው የተለየ ቅጣት ነው::

፪ ደንብ ተላላፊዎች ወታደሮች ወይም ወጣት ጥፋተኞች ሲሆኑ የሚፈጸመው የተለየ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በደንብ መተላለፍ ረገድ የሚፈጸሙ ቅጣቶች ከዚህ በታች በተመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ የሚገኙት ብቻ ናቸው::

፫ ለኅብረተሰቡ ሲባል የጥበቃ ወይም የሕክምና እርምጃዎች መወሰድ ሲኖርባቸው በተለይም ኃላፊ ሊሆኑ የማይችሉ ሰዎችን /አንቀጽ ፻፵ እና ፻፵፩/ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ አግባብ ላለው የአስተዳደር ባለሥልጣን ያስታውቃል /አንቀጽ ፻፶፬/::

BACK



አንቀጽ ፺፻፵፺ <u>የማረፊያ ቤት እሥራት</u>

፩ የደንብ መተላለፍ ድርጊቶች በተፈፀሙ ጊዜ የሚወሰነው ነፃነትን የማሳጣት ቅጣት የማረፊያ ቤት እሥራት ብቻ ይሆናል::

ደንብ መተላለፍ በተደጋገመ ጊዜ የሚወሰነው ቅጣት እና የሕጉ ልዩ ድንጋጌዎች የሚያስቀምጡት ከፍተኛ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ /አንቀጽ ፺፻፹፱/ የማረፊያ ቤት እሥራቱ የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ቀን እስከ ሦስት ወር ይሆናል::

ፍርድ ቤቱ ቅጣትን የሚወስነው በሕጉ ልዩ ድንጋጌ ውስጥ የተመለከተውን ልዩ ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ጊዜ ሳያልፍ የተቀጪውን የጥፋተኝነት ደረጃ ከግምት በማስገባት ይሆናል /አንቀጽ ፹፰/::

፪ በአመክሮ መለቀቅን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፪፻፩-፪፻፺/ ለማረፊያ ቤት እስራት ተፈጻሚ አይሆኑም::

<u>አንቀጽ ፺፻፵፰ የመደበኛ ማረፊያ ቤት እሥራት አፈፃፀም</u>

፩ መደበኛ የማረፊያ ቤት እሥራት የሚፈፀመው ከፍርድ ቤቶች ወይም ከፖሊስ ጣቢያዎች ጋር በተያያዙ ልዩ የመቆያ ቦታዎች ይሆናል:: የተፈረደባቸው ወንዶችና ሴቶች የሚታሰሩት ለየብቻ ይሆናል::

በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በማረፊያ ቤት እሥራት እንዲቀጣ የተፈረደበት ሰው ወደ ጠባይ ማሻሻያ ወይም ማረሚያ ቤት እንዲላክ፣ በወንጀል ምክንያት በእሥራት ከተቀጡት እሥረኞች ጋርም እንዲቀላቀል ማድረግ አይቻልም /አንቀጽ ፺፻፵፺(፩)/::

BACK



፪ የማረፊያ ቤት እሥራት የተፈረደበት ሰው የግዴታ ሥራ እንዲሠራ አይገደድም፤ የሥራ ዋጋ ለማግኘትም መብት የለውም /አንቀጽ ፻፲፩/።

የማረፊያ ቤት የእሥራት ቦታው ፀጥታና አጠቃላይ ደኅንነት እስካልተነካ ድረስ የማረፊያ ቤት እሥራት የሚፈፅም ሰው ከውጭ የሚመጣለትን ምግብ፣ ደብዳቤና ጠያቂዎችን ለመቀበል ይችላል።

<u>አንቀጽ ፻፶፩ በመኖሪያ ቤት ወይም በድርጅት ውስጥ የሚፈፀም የማረፊያ ቤት እሥራት</u>

፩ የጥፋተኛው ግላዊ ወይም የቦታው ሁኔታ የሚፈቅድ ሲሆን፣ የተፈረደበት ሰው በቤቱ፣ በታማኝ ሰው ቤት ወይም ለዚሁ ዓላማ በሚውሉ ዓለማዊ ወይም መንፈሳዊ ተቋሞች ውስጥ የማረፊያ ቤት እሥራቱን ከበቂ ቁጥጥር ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ጋር እንዲፈፅም ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል።

፪ ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ከሚያጋጥምበት ጊዜ በተጨማሪ ተቀጪው ከታሰረበት ቤት እንዲወጣ የሚፈቀድለት ሀይማኖታዊ ተግባሮችን ለማከናወን፣ በሐኪም ለመመርመር፣ አስፈላጊ የሆነ ህክምናን ለማግኘት ወይም ወደ ፍርድ ቤት ለመቅረብ እንዲችል ለዚሁ ጉዳይ ለሚበቃ ጊዜ ብቻ እንዲወጣ ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል።

ከቤቱ እንዳይወጣ የተፈረደበት ሰው ምግቡን የሚችለው ራሱ ነው።

## አንቀጽ ፫፻፺ ስለወታደሮች እና ወጣት ጥፋተኞች የተለየ የቅጣት አፈፃፀም

፩ ወታደራዊ ግዴታቸውን ባለመፈፀማቸው ምክንያት በወታደሮች ላይ የሚፈረደው የማረፊያ ቤት እሥራት የሚወሰነው /አንቀጽ ፫፻፴፪/ በወታደራዊ ደንብ መሠረት ሆኖ የሚፈፀመው በወታደራዊ ዲስፕሊንና ቁጥጥር ሥር በመሆን ለዚሁ ዓላማ በሚውሉ ቦታዎች ይሆናል።

፪ የማረፊያ ቤት እሥራት የተፈረደባቸው ወጣት ጥፋተኞች ቅጣቱን የሚፈፅሙት ስለእነርሱ በተለይ በተደነገጉት ሁኔታዎች መሠረት በትምህርት ቤት ወይም በቤት በሚደረገው የማረፊያ ቤት እሥራት /አንቀጽ ፻፷፩/ ወይም ይህም የማይቻል ቢሆን ፍርድ ቤቱ በመረጠው ተቋም፣ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ታማኝ ሰው ጥበቃ ስር ሆኖ ነው።

የሚወሰነው የማረፊያ ቤት እሥራት ተከፋፍሎ በተለያዩ ጊዜያቶች እንዲፈፀም ለማድረግ ይቻላል። ሆኖም የእያንዳንዱ ቀን የማረፊያ ቤት እሥራት ጊዜ ከሦስት ሰዓት ሊያንስ፣ ጠቅላላው የማረፊያ ቤት እሥራት ጊዜ ደግሞ ከአሥራ አምስት ቀን ሊበልጥ አይችልም።

## አንቀጽ ፫፻፺፩ በማረፊያ ቤት እሥራት ፈንታ የግዴታ ሥራን መወሰን

፩ የማረፊያ ቤት እሥራት ቅጣት ለመወሰን በሚቻልበት ጊዜ የነገሩ ሁኔታዎች ወይም የፍርዱ አፈፃፀም ሁኔታዎች ተገቢ ሆነው ሲገኙ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ሠርቶ ከሚያገኘው ገቢ እየቀነሰ ለመንግሥት ገቢ ከማድረግ ጋር ለተመሣሣይ ጊዜ በሚቆይበት ነፃነትን በሚቀንስ ወይም በማይቀንስ የግዴታ ሥራ ለመለወጥ ይችላል /አንቀጽ ፻፫ እና ፻፬/።

የጊዜውን ርዝመትና የተቀናሽ ገንዘቡን መጠን ፍርድ ቤቱ በፍርዱ ላይ በትክክል ይወስናል።

፪ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በግዳጅ ላይ ባሉ ወታደሮች ወይም በወጣት ጥፋተኞች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

## አንቀጽ ፫፻፶፪ መቀጮ፣ መደበኛ ሁኔታ

፩ ጥፋተኛው ደጋጋሚ ካልሆነ /አንቀጽ ፫፻፷፱/ ወይም የሕጉ ልዩ ድንጋጌ የበለጠ ቅጣት ካልወሰነ በቀር በደንብ ተላላፊ ላይ የሚጣል መቀጮ ከአንድ ብር እስከ ሦስት መቶ ብር ለመድረስ ይችላል።

ጥፋቱ በተደጋገመ ጊዜ የሚደረገው የቅጣት ማክበድ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ደንብ ተላላፊው ጥፋቱን የፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ እንደሆነ፣ መቀጮው እስከ አምስት መቶ ብር ለመድረስ ይችላል።

መቀጮውን በሚወስንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ የጥፋተኛውን የገቢ ሁኔታ፣ የጥፋቱን ክብደት እና የጥፋተኝነት ደረጃውን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል /አንቀጽ ፺/።

፪ ሁኔታዎቹ ሲታዩ መጣመርን ተገቢ ያደረጉት እንደሆነ፣ በተለይም ጥፋተኛው ጥፋቱን የፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ እንደሆነ /አንቀጽ ፺፩ እና ፺፪/ ወይም የሕጉ ልዩ ድንጋጌ እነዚህን ቅጣቶች በአማራጭ ያስቀመጠ እንደሆነ መቀጮ ከማረፊያ ቤት እስራት ጋር ሊጣመር ይችላል።

፫ ለተፈረደበት ሰው፣ ቢያስፈልግም ከፋፍሎ በየጊዜው ሰዳውን እንዲከፍል በመፍቀድ ፍርድ ቤቱ እስከ ሦስት ወር ለመድረስ በሚችል የመክፈያ ጊዜ ሊወስንለት ይችላል። ሁኔታዎቹ በቂ ምክንያት ያስገኙ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የመክፈያ ጊዜውን እስከ አንድ ዓመት ሊያራዝመው ይችላል /አንቀጽ ፺፫/።

መቀጮ የተወሰነበት ደንብ ተላላፊ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ሥራ በመሥራት መቀጮውን እንዲከፍል ሊፈቀድለት ይችላል /አንቀጽ ፺፭/::

፬ የሕግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት በሚመለከት ቅጣቱ መቀጮ ብቻ ይሆናል:: የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፪፻፳፰ እና ፪፻፸ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ መቀጮው ከአስር ብር እስከ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር ሊደርስ ይችላል::

## አንቀጽ ፪፻፺፫ <u>መቀጮ በግዴታ ሥራ የሚለወጥበት ሁኔታ</u>

፩ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መቀጮው ያልተከፈለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሙሉውን ወይም ያልተከፈለውን ቀሪ መቀጮ ከሚያገኘው ገቢ ተቀናሽ በማድረግ ለመንግሥት ገቢ ከማድረግ ጋራ ነፃነትን በሚቀንስ ወይም በማይቀንስ የግዴታ ሥራ እንዲለወጥ ያዝዛል::

፪ ፍርድ ቤቱም አግባብ ባለው የዚህ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች መሠረት የግዴታ ሥራው የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል /አንቀጽ ፺፮ እና ፺፫/::

## አንቀጽ ፪፻፺፬ <u>በወታደሮችና በወጣት ጥፋተኞች ላይ የሚጣለውን መቀጮ ማስገባት፤</u>

፩ አንድ ወታደር መደበኛውን ሕግ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ፤ በእርሱ ላይ የተጣለውን መቀጮ ወይም ያልተከፈለውን ቀሪ መቀጮ ለማስገባት ፍርድ ቤቱ ለተወሰነ ጊዜ ያህል ከወታደሩ ደመወዝ እንዲቀነስ ለማዘዝ ይችላል::

ተቀጪው ካልተስማማ በቀር ይህ ተቀናሽ ከደመወዙ ሩብ ሊበልጥ አይችልም:: ቅጣቱም በፍርድ ቤት የሚወሰነው አግባብ ካለው ከተፈረደበት ወታደር አዛዥ ጋር በመመካከር ነው::

፪ ደንብ ተላላፊው ወጣት ጥፋተኛ ሲሆን ፍርድቤቱ የጥፋቱን ክብደት፣ የጥፋተኛውን የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም የቅጣቱን አስጠንቃቂነት ልዩ ግምት ውስጥ በማስገባት መቀጮውን በተገቢው ወሰን ውስጥ ይወስናል።

ወጣት ጥፋተኛው መቀጮውን ያልከፈለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በነገሩ ሁኔታ ተገቢ መስሉ በታየው መሠረት መቀጮውን ለወጣቶች ወደሚወሰን የማረፊያ ቤት እሥራት ይለውጠዋል።

አንቀጽ ፯፻፶፮ <u>የጉዳትና የሞራል ካሣ</u>

የነገሩ ሁኔታዎች ተገቢ ሆነው ሲገኙ ተጉጂው በደንብ መተላለፍ ለደረሰበት ጉዳት የሞራል ወይም የማቴሪያል ካሣ የመጠየቅ መብቱ እንደተጠበቀ ነው /አንቀጽ ፻፩ እና ፻፪/።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ተጨማሪ ቅጣቶች</u>

አንቀጽ ፯፻፶፯ <u>ማስጠንቀቂያና ወቀሳ</u>

፩ ከማረፊያ ቤት እሥራት፣ ከግዴታ ሥራ ወይም ከመቀጮ በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ በቃል ወይም በፅሁፍ ጥፋተኛውን ሊያስጠነቅቀው፣ ሊወቅሰው፣ ሊገስፀው ወይም ተበዳዩን ይቅርታ እንዲጠይቅ ሊያደርገው ይችላል /አንቀጽ ፻፳፪/።

፪ ፍርድ ቤቱ የተፈጸመው ጥፋት እጅግ ቀላል መሆኑን የገመተ እንደሆነ ወይም ጥፋቱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያለው ሆኖ ባገኘው ጊዜ በዋና ቅጣቶች ፈንታ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተውን ቅጣት ሊወስን ይችላል።

አንቀጽ ፯፻፶፰ <u>ከመብት የመሻር ቅጣት ተፈፃሚ አለመሆኑ</u>

፩ ከሕዝባዊ ወይም ከቤተዘመድ፣ የመንግሥት ሥራ ወይም የሙያ ሥራ ከመሥራት ወይም ከመሳሰሉት መብቶች መሻር /አንቀጽ ፻፳፫/ በደንብ መተላለፍ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

፪ እንዲሁም ወታደራዊ ማዕረግን ዝቅ ማድረግ ወይም ከመከላከያ ሠራዊት ባልደረባነት ማስወገድ /አንቀጽ ፻፳፯/ በደንብ ተላላፊ ወታደር ላይ ተፈጻሚ አይሆንም::

## ክፍል ሦስት

## የጥንቃቄ እርምጃዎች

### አንቀጽ ፲፻፶፫ የመልካም ጠባይ ዋስትና

፩ የመልካም ጠባይ ዋስትና ሊታዘዝ የሚቻለው የደንብ መተላለፍ ድርጊት በሕዝብ ደኅንነት ወይም ጸጥታ ላይ ወይም በሰዎች ወይም በንብረቶች ደህንነት ላይ ተደጋግሞ ሲፈፀምና ይደጋገማል ተብሎ ሲታመንበት ብቻ ነው /አንቀጽ ፻፴፬/::
ከአንድ ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ ዋስትና እንዲሰጥ ማድረግ አይቻልም::

፪ ጥፋተኛው ዋስትና ለመስጠት እየቻለ እንቢ ያለ እንደሆነ የተባለውን ዋስትና እስከሚያቀርብ ድረስ ከአሥራ አምስት ቀን ለማይበልጥ ጊዜ በመደበኛ ማረፊያ ቤት /አንቀጽ ፲፻፵፰/ ወይም ጥፋተኛው ወታደር ሲሆን በወታደር የማረፊያ ቤት እሥራት /አንቀጽ ፲፻፶/ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ያዝዛል::

ይህንንም ጊዜ ለማራዘም አይቻልም::

### አንቀጽ ፲፻፶፬ መውረስ እና ለመንግሥት ገቢ ማድረግ

፩ ለሕዝብ ደኅንነት፣ ጸጥታ፣ ጤና፣ ወይም መልካም አኗኗር አደገኛ የሆኑ ወይም የደንብ መተላለፍ ጥፋትን ለመፈጸም እንዲያመቹ/እንዲረዱ ወይም ሊፈጸምባቸው የታቀዱ ወይም የተፈጸመባቸው አደገኛ ዕቃዎችና መሣሪያዎች እንዲወረሱ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ከዋና ቅጣቶች በተጨማሪ የሕጉን ጠቅላላ ድንጋጌዎች በመከተል

፪ የተባሉት ዕቃዎች እንዲወረሱ ለመፍረድ ይችላል /አንቀጽ ፻፵/::

የህዝብን ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እነዚህን አደገኛ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ለጥንቃቄ ሲባል አስቀድሞ መውረስ ይቻላል /አንቀጽ ፻፵፩/::

፫ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ እነዚሁ ዕቃዎች ወይም መሣሪያዎች ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ለመወሰን ይችላል /አንቀጽ ፻/::

## አንቀጽ ፫፻፳ ድርጅቶችን መከልከል እና የሥራ ፈቃድን ማገድ

ከሥራ ፈቃድ አጠቃቀም ወይም ከድርጅት አስተዳደር ጋር ግንኙነት ያለው የደንብ መተላለፍ ጥፋት ተደጋግሞ በተፈጸመ ጊዜ የሥራ ፈቃድ ወረቀትን መልሶ መውሰድ /አንቀጽ ፻፵፪/ ወይም ድርጅትን መዝጋት ወይም ተግባሩን ማገድ /አንቀጽ ፻፵፫/ በሙሉም ሆነ በከፊል ለመወሰን የሚቻለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው::

የእነዚህ የጥንቃቄ ውሣኔዎች ጊዜ በማናቸውም ሁኔታ ከስድስት ወር የበለጠ ሊሆን አይችልም:: ፍርድ ቤቱ እያንዳንዱ ሁኔታ የሚቆይበትን ጊዜና የነገሩን ወሰን በትክክል ይወስናል::

## አንቀጽ ፫፻፳፩ መውረስና ማገድ ተፈፃሚ የሚሆኑባቸው ዋና ዋና ሁኔታዎች

ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን የመውረስ፣ ወይም ለመንግሥት ገቢ የማድረግ፣ ፈቃድን መልሶ የመውሰድ፣ ድርጅትን እንዳይሰራ የማገድ ወይም የመዝጋት እርምጃዎች የሚወሰኑት በተለይ:-

ሀ/ ገንዘብን ወይም አስተዳደርን /አንቀጽ ፫፻፹፬ - ፫፻፺፭/፤

ለ/ የመገናኛ ብዙኃንን እና ማስታወቂያን /አንቀጽ ፫፻፱ እና ፫፻፲፪/፤

ሐ/ የጦር መሣሪያንና ጥይቶችን፣ እሳትን፣ የሚፈነዱ ወይም አደገኛ የሆኑ ነገሮችን መቆጣጠርን /አንቀጽ ፫፻፫ እና ፫፻፳፱/፤

መ/ ሆቴሎችና መዝናኛ ቦታዎችን መቆጣጠርን /አንቀጽ ፫፻፳ እና ፫፻፳፩/፤

ሠ/ የሕዝብ ጤና ጥበቃ መቆጣጠርን፣ በተለይም እንደመርዛማ ወይም አደንዛዥ ንጥረ ነገሮችን፣ መድኃኒቶችን፣ አልኮሎችን፣ መጠጦችን፣ ምግቦችን ወይም በአጠቃላይ ዕቃዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማዘጋጀትን ወይም መነገድን /አንቀጽ ፫፻፲፫ እና ፫፻፵፩ - ፫፻፵፱/፤

በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይሆናል::

አንቀጽ ፯፻፳፪ <u>የግል ነፃነትን መከልከልና መቀነስ</u>

፩ መከልከሉ ተገቢ መስሎ ሲታየው በተለይም ጥፋተኛው ደጋጋሚ የሆነ ወይም መደጋገሙ አይቀርም ተብሎ የተገመተ እንደሆነ፤ የደንብ መተላለፍ ተግባሮችን ለመፈጸም ወደሚያመቹ ወይም ወደሚገፋፉ አንዳንድ ቦታዎች እንዳይደርስ ፍርድ ቤቱ ለመወሰን ይችላል /አንቀጽ ፻፵፭/::

ክልከላው የሚቆይበት ጊዜ በፍርዱ ላይ የሚወሰን ሲሆን፣ በምንም ሁኔታ ከስድስት ወር ሊበልጥ አይችልም::

፪ ባንድ በተወሰነ ቦታ ከመኖር ወይም ውሎ ከማደር መከልከል፣ ባንድ ቦታ ወይም አካባቢ ተወስኖ የመኖር ግዴታ፣ በቁጥጥር ሥር እንዲጠበቅ ማድረግ፣

ኦፊሴላዊ ሰነዶችን መውሰድ፣ በአገር እንዳይኖር ወይም ካገር እንዲወጣ ማድረግና የመሳሰሉት የግል ነፃነትን የሚቀንሱ ሌሎች እርምጃዎች /አንቀጽ ፻፵፯-፻፶/ በደንብ ተላላፊ ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም::

## ክፍል አራት

## የማሳወቅ እርምጃዎች

**አንቀጽ ፯፻፹፫ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማስታወቅና ፍርድን ለሕዝብ መግለፅ**

፩ ማስታወቁ ተገቢ መስሎ በታየበት ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማስታወቅ ይኖርበታል /አንቀጽ ፻፶፩/::

፪ እንዲሁም የሕዝብ ወይም የግል ጥቅሞች በሚያስገድዱበት ጊዜ ፍርዱ ለሕዝብ ይገለጻል /አንቀጽ ፻፶፫/::

**አንቀጽ ፯፻፹፬ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ መመዝገብ**

፩ ፍርድ ቤቶች የተከሳሹን ያለፈ ታሪክ ጠንቅቀው ማወቅ ይችሉ ዘንድ በደንብ መተላለፍ ረገድ የሚሰጡት የመጨረሻ ቅጣቶች የዚህ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን በመከተል በወንጀለኞች መዝገብ ላይ እንዲመዘገቡ ፍርድ ቤቱ ይወስናል /አንቀጽ ፻፶፬/::

፪ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ የተመዘገቡ ነገሮችን ለሌላ ሰው መግለጽ ስለወንጀሎች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የሚመራ ይሆናል /አንቀጽ ፻፶፬/::

## ምዕራፍ ሁለት

## የቅጣት አፈፃፀም

**አንቀጽ ፯፻፹፭ ቅጣትን ማገድ እና በአመክሮ መፍታት የማይቻል መሆኑ**

የደንብ መተላለፍ ድርጊቶች ከጠባያቸው ልዩነት የተነሣ ላሠራሩ ቀናነት ቅጣቱ አንድ ዓይነትና ቀላል ሆኖ በፍጥነት እንዲፈጸም አስፈላጊ ስለሆነ ቅጣት ሳይወሰን

ወይም ሳይፈፀም ታግዶ እንዲቆይ ስለማድረግ እንዲሁም በአመክሮ ስለመፍታት የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለደንብ መተላለፍ ተፈጻሚ አይሆኑም /ከአንቀጽ ፻፺ እስከ ፱፻/::

አንቀጽ ፯፻፹፮ <u>ቅጣትን ማቅለል</u>

፩ ቅጣት የሚያቀሉ ተገቢ ምክንያቶች የተገኙ እንደሆነ (አንቀጽ ፯፻፷፫(፩)) በማረፊያ ቤት እስራት ፈንታ ጥፋተኛው የግዴታ ሥራ እንዲሠራ ወይም መቀጮ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ሊፈርድ ይችላል:: ፍርድ ቤቱ በሕግ ከተወሰነው ከአነስተኛው መደበኛ ቅጣት ሳይወርድ መወሰን አለበት::

ርዝመቱና መጠኑ የሚወሰነው በአድራጊው የጥፋተኛነት ደረጃ ነው::

፪ ጥፋቱ ቀላል በሆነ ጊዜ የተደረገው በደል አነስተኛ ሆኖ ሲታይና በተለይም የደንብ መተላለፍ ተግባሩ የመጀመሪያ ጥፋት ወይም ባለመጠንቀቅ የተደረገ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ወቀሳን፣ ተግሣጽን ወይም ለወደፊት የሚሆነውን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ብቻ ለማለፍ ይችላል::

አንቀጽ ፯፻፹፯ <u>መደበኛ የሆነ የቅጣት ማክበጃ</u>

ቅጣትን የሚያከብዱ ጠቅላላ ምክንያቶች ያጋጠሙ እንደሆነ /አንቀጽ ፯፻፷፫(፪) ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን የሚያከብደው በሕጉ ከተወሰነው ባለማለፍ ነው /አንቀጽ ፯፻፷፯/::

አንቀጽ ፯፻፹፰ <u>ጥፋት ሲደራረብ ቅጣትን ማክበድ</u>

፩ ግዙፍ የሆኑ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ለእያንዳንዳቸው የተወሰነው ቅጣት ተደምሮ ይፈረዳል:: የቅጣቶቹ ድምር በአንቀጽ ፯፻፷፯ ወይም

በአንቀጽ ፯፻፶፪ ከተደነገገው መደበኛ ከፍተኛ ቅጣት መብለጥ ይችላል:: ሆኖም የማረፊያ ቤት እሥራቱ ቅጣት ከአንድ ዓመት፣ መቀጮውም ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር ለመብለጥ አይችልም::

የሕግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት በተመለከተ መቀጮው ከአምስት ሺህ ብር አይበልጥም::

፪ በአንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎች በተጣሱ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የጠቅላላ ውሳኔዎችን አሳብ በመከተል ቅጣቱን ለማክበድ ይችላል /አንቀጽ ፻፹፯/::

አንቀጽ ፯፻፷፱ <u>በደጋጋሚነት ጊዜ ቅጣትን ማክበድ</u>

፩ አዲሱ የደንብ መተላለፍ ጥፋት በተፈፀመበት ጊዜ ስላለፈው ስለማናቸውም ዓይነት የደንብ መተላለፍ ጥፋት የተፈረደው ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከተፈጸመበት ወይም በይቅርታ ወይም በይርጋ ቀሪ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ አንድ ዓመት ካለፈ እንደደጋጋሚ አያስቆጥርም::

፪ የጥፋት መደጋገም ተደርጓል በሚባልበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ስለ አዲሱ የደንብ መተላለፍ ተግባር በተጻፈው በመደበኛው ከፍተኛ ቅጣት አይወሰንም:: የነገሩ ሁኔታዎችና የጥፋተኝነቱ ደረጃ በቂ ምክንያት ባስገኘ ጊዜ ,በተለይም ያንኑ ጥፋት በልማደኛነት የደጋገመ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ስለ ልዩ ልዩ ቅጣቶች የተጻፈውን መደበኛ የደንብ መተላለፍ ከፍተኛ ቅጣት እስከ አጠፌታ ለማድረስ ይችላል /አንቀጽ ፯፻፸፯ እና ፯፻፶፪/::

አንቀጽ ፯፻፸ <u>መደራረብና መደጋገም</u>

ደጋጋሚነትና የወንጀሎች መደራረብና ተጣምረው በተገኙ ጊዜ ቅጣቱ ከዚህ በላይ በተጻፉት ሁለት አንቀጾች መሠረት ይወሰናል:: ሆኖም የማረፊያ ቤት እሥራቱ

ከሁለት ዓመት፤ መቀጮውም ግለሰቦችን በተመለከተ ከሁለት ሺህ አራት መቶ ብር፤ የሕግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት በተመለከተ ከአሥር ሺህ ብር ሊበልጥ አይችልም።

## ምዕራፍ ሦስት

## ክስ የሚቀርብባቸው፣ ክስና ቅጣት የሚታገድባቸውና ቀሪ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች

### አንቀጽ ፯፻፹፩ የክስ አቀራረብ

፩ ይህን የደንብ መተላለፍ ሕግ ወይም ልዩ ሕጎችን ወይም ደንቦችን በመተላለፍ ምክንያት ክስ የሚቀርበው በሚከተሉት መርሆች መሠረት ነው።

ሀ/ የደንብ መተላለፍ ተግባር የተፈጸመው በሰው አካል ሙሉነት፣ የነፃነት ክብር ወይም በግል ሀብት ላይ ሲሆን፤ ክሱ መቅረብ የሚችለው፣ ተበዳዩ ራሱ ወይም በፍትሐብሔር መደበኛ ደንቦች መሠረት የተፈቀደለትና ችሎታ የተሰጠው እንደራሴው ወይም ስለተበዳዩ መብት ያለው ሰው የግል አቤቱታ ሲያቀርብ ነው።

ለ/ በአስተዳደር ወይም በአስፈፃሚ ክፍል ባለሥልጣኖች የወጣውን ሕግ፣ ትእዛዝ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ የሚፈጸም ማናቸውም የደንብ መተላላፍ ጥፋት የሚያስከስሰውና የሚያስቀጣው የክፍሉ መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት የግል አቤቱታ ሲያቀርብ ብቻ ነው።

ሐ/ በሌሎች የደንብ መተላለፍ ነገሮች ሁሉ ክሱን የሚያቀርበው የዐቃቤ ሕግ በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ነው።

፪ ወታደራዊ ብቻ ለሆኑት የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ተፈፃሚ የሚሆኑት የመከላከያ ሠራዊት የዲስፒሊን ደንቦች ናቸው።

## አንቀጽ ፰፻፷፪ የግል አቤቱታ የሚቀርብባቸው ሁኔታዎች

የደንብ መተላለፍ ክስ እንዲታይ የግል አቤቱታ ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑ በሕግ የተደነገገ እንደሆነ (አንቀጽ ፰፻፷፩) አቤቱታ ስለሚቀርብበት ሁኔታና ጊዜ እንዲሁም አቤቱታ ስለማቅረብ መብት የተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ (አንቀጽ ፪፻፲፩-፪፻፲፫)፡፡

## አንቀጽ ፰፻፷፫ የይርጋ ዘመን

ማናቸውም ዓይነት የደንብ መተላለፍ ድርጊት ቢሆን ክስ ሳይቀርብበት አንድ ዓመት ካለፈ፤ የተፈረደውም ቅጣት ተፈፃሚ ሳይሆን ሁለት ዓመት ካለፈ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የይርጋ ዘመን መጀመርን፣ መታገድን፣ መቋረጥንና ፍፁም ማብቂያውን መጨረሻውን የሚመለከቱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች /አንቀጽ ፪፻፲፱ እስከ ፪፻፳፪ እና ፪፻፳፭-፪፻፳፯/ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ ፰፻፷፬ ይቅርታና ምሕረት

የደንብ መተላለፍ ቅጣቶች በወንጀል ሕጉ ላይ በተደነገጉት ጠቅላላ ሁኔታዎች መሠረት በይቅርታ ወይም በምሕረት ቀሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ይቻላል /አንቀጽ ፪፻፳፱ እስከ ፪፻፴፩/፡፡

## አንቀጽ ፰፻፷፭ መሰየም

ቅጣት የተፈረደበት ሰው፤ ቅጣቱ በሙሉ ወይም በከፊል ከተፈጸመ ወይም በይርጋ ከታገደ ወይም በይቅርታ ከተሰረዘ ከአንድ ዓመት በኋላ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ንፁህ ስሙ ይመለስለታል፡፡

# ስምንተኛ መጽሐፍ

## ልዩ ክፍል

## ርዕስ አንድ

## በሕዝባዊና በማህበራዊ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ፯፻፹፯ በዚህ ርዕስ ሥር በግልጽ ያልተሸፈኑ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶችን የሚመለከት ጠቅላላ ድንጋጌ**

ማንም ሰው በዚህ ርዕስ በተለይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ:-

ሀ/ የመንግሥቱን ተዓማኒነት፣ ገንዘብን፣ ብልጽግናንና ሕዝባዊ እምነትን፤ ወይም

ለ/ ሕዝባዊ ስርዓትን፣ ሰላምን፣ ዕርጋታን፣ ደህንነትን፣ ጠ ጋንነትንና መልካም ሥነ-ምግባርን፤ ወይም

ሐ/ የየብስ፣ የአየር፣ የጅረትና የባህር ትራንስፖርት እንዲሁም የፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን መገናኛ ደንበኛ ሥርዓትን፣ ደህንነትን ወይም ነፃነትን፤ ወይም

መ/ በጠቅላላው የመንግሥት የቀረጥና የግብር ገቢን፣ ጉምሩክን፣ ኢኮኖሚን፣ ምግብን፣ ጤናን፣ የደን ጥበቃን ወይም የፖሊሲ ጉዳይን፤

በሚመለከት ለመጠበቅ፣ በመልካም ሁኔታ ለመያዝ ወይም እንደገና ለማቋቋም አግባብ ባለው ባለሥልጣን የወጣውን ሕግ፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ፣ መመሪያ ወይም የጥንቃቄ እርምጃ የጣሰ እንደሆነ፤

ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ ወይም በልዩ ሕግ ግልፅ ድንጋጌ የማያስቀጣ ሲሆን ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በሚወሰን መቀጮ ወይም የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል/ አንቀጽ ፫፻፵፫ እና ፫፻፶፪/::

## አንቀጽ ፫፻፷፫ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በደንብ መተላለፍ ቅጣት ያለው ተካፋይነት

፩ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ ወይም ድርጅቱን በመሣሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በደንብ ተላላፊነት /አንቀጽ ፴፪ እና ፴፬/ ሕግን፣ ደንብን ወይም መመሪያን በመጣስ በዚህ ርዕስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንዱን በሚተላለፍበት ጊዜ፣ ቀጣሪው ድርጅት እንደ ደንብ ተላላፊ ተቆጥሮ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፪ እና ፫፻፶፭ - ፫፻፷ በተመለከተው መሠረት ይቀጣል::

፪ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው ሁኔታ የደንብ መተላለፍ ጥፋት በሚፈፀም ጊዜ በድርጅቱ የሥራ አመራር ውስጥ ባለው የሥራ ድርሻ የተነሣ በደንብ መተላለፍ ጥፋቱ ተካፋይ የሆነ የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ ርዕስ ስር በተመለከቱት አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል::

BACK



## ምዕራፍ አንድ

## በመንግሥትና በሕዝብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ተግባሮች

### ክፍል አንድ

### በመንግሥትና በሕዝብ አመኔታ ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ተግባሮች

**አንቀጽ ፯፻፸፫ ሕጋዊ ገንዘብን አለመቀበል**

ማንም ሰው በሕግ የተወሰነ ዋጋ ያለውን በማዕድን ወይም በወረቀት የተሠራውን የአገር ገንዘብ በቂ ምክንያት ሳይኖረው አልቀበልም ያለ እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

**አንቀጽ ፯፻፸፬ ሐሰተኛ ገንዘብ በእጅ መኖሩን አለማስታወቅ**

ማንም ሰው በማዕድን ወይም በወረቀት የተሠራውን የሀሰት ወይም ወደ ሐሰተኛነት የተለወጠውን ገንዘብ እውነተኛ መስሎት ከተቀበለ በኋላ ይህ ገንዘብ ሐሰተኛ መሆኑን ወይም ወደ ሐሰተኛነት የተለወጠ መሆኑን እንዳወቀ ወዲያውኑ የአካባቢው ሁኔታ በሚፈቅድለት መጠን፣ የሚያውቅ ቢሆን የመጣበትን ስፍራ፣ አለዚያም ይህ የሐሰት ወይም ወደ ሐሰተኛነት የተለወጠ ገንዘብ በእጁ መኖሩን ጉዳዩ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ሳያስታውቅ ወይም ገንዘቡን ሳያስረክብ የቀረ እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

**አንቀጽ ፯፻፸፭ ሕገ-ወጥ በሆኑ መስፈሪያዎችና ሚዛኖች መገልገል**

ማንም ሰው በወንጀል ሕግ ከተወሰነው ውጭ /አንቀጽ ፫፻፷፩/:-

ሀ/ ከሌሎች ጋራ በሚያደርገው የንግድ ግንኙነት ውስጥ በሕግ ተመርምሮ ያልተፈቀደውን ወይም ለዚሁ ጉዳይ ከተሰጠው ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ጋራ ተስማሚ ያልሆነውን የመስፈሪያ ወይም የሚዛን መሣሪያ ሲሰራበት የተገኘ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በጠቅላላ አድራጐት ስለ ሕጋዊ መስፈሪያዎችና ሚዛኖች ትክክለኛነት ማረጋገጫ መውጊያ ስለ ሚዛኖችና መስፈሪያዎች መመርመርና መገልገል ጉዳይ የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፣

የመወረሱ ቅጣት የተጠበቀ ሆኖ በማረፊያ ቤት እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፹፮ ጊዜያቸው ባለፈ ወይም ወደሐሰት በተለወጡ የመመላለሻ ወረቀቶች መገልገል</u>

ማንም ሰው እንደእውነተኛ ወይም ዋጋ እንዳለው አድርጐ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም ጊዜው ባለፈበት ወይም በተሠራበት የሕዝብ መመላለሻ ወረቀት ወይም ትኬት የተገለገለ እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፫፻፹፯ የማዕረግ ስምና የምስክር ወረቀትን በማጭበርበር መቀበልና መገልገል</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕግ ከተደነገገው ውጭ በሆነ አድራጐት የማይገባውን የገንዘብ ወይም የሕሊና ጥቅም ለማግኘት በማቀድ /አንቀጽ ፫፻፹፫/:-

ሀ/ የችሎታ የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎማ ወይም የትምህርት ማዕረግ ወረቀት ወይም ሥራ ለማግኘት

ሲል በፈተና፣ በውድድር ወይም በምዝገባ ላይ የማጭበርበር ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የሌለውን ወይም መብቱ የማይፈቅድለትን ዲፕሎም የትምህርት ምስክር ወረቀት ወይም የማዕረግ ስም ያለው አስመስሎ ያቀረበ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፹፫ ከሕግ ውጭ የሲቪል ኒሻኖችና የማዕረግ ምልክቶችን መሥራት፣በነዚህ መነገድና እነዚህን ነገሮች ማድረግ**

ማንም ሰው፡-

ሀ/ ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው የሲቪል ኒሻኖችን፣ ሜዳዮችን ወይም የማዕረግ ምልክቶችን የሠራ ወይም ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ ወይም በአደራ ያስቀመጠ ወይም ያስተላለፈ ወይም ለሕዝብ የሸጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤

ለ/ በእንደዚህ ያለው ሥራ ወደ ሐሰተኛነት በተለወጡ ኒሻኖች ወይም ሜዳዩች ወይም ሊገለገልባቸው መብት ሳይኖረው በኒሻኖች ወይም በመለያ ምልክቶች የተገለገለ ወይም ያደረገ እንደሆነ፤

የመወረሱ ቅጣት ሳይቀር በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በቀረጥና በግብር ገቢዎች፣ በፋይናንስ እና በአስተዳደር ጉዳዩች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

**አንቀጽ ፫፻፹፬ የቀረጥና የግብር ሕጎችን መጣስ**

ማንም ሰው በዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፫፻፵፫ - ፫፻፵፭ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፡-

ሀ/ የመንግስትን ገቢ በተለይም ቀረጥን፣ ግብርን፣ ጉምሩክን፣ ፖስታና ቴሌኮ ሙኒኬሽንን፣ የአደንና ዓሣ ማጥመድ መብቶችን፣ በመሬት ወይም ከርሠ-ምድር ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠ ቀምን ወይም ማናቸውም ሌሎች ተመሣሣይ መብቶችን ወይም የገቢ ምንጮችን፣ ወይም

ለ/ ቴምብርን፣ የሚለጠፉ ማስታወቂያዎችን፣ ቀረጥን፣ የመዝገብ ማስገቢያን፣ የስም ማዛወሪያንና ይህን መሰል ጠባይ ያላቸውን የገንዘብ ማስከፈያን፤

በሚመለከት አግባብ ባለው ባለሥልጣን የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፯፻፹፭ በወርቅ፣ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ምንዛሪ ህገወጥ ሥራ መሥራትን አስመልክቶ የወጣ ሕግን መጣስ</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፫፻፵፮ ከተመለከተው ሁኔታ ውጭ፣ በተወሰነ ሁኔታ፣ በገደብ፣ በቁጥጥር ወይም በልዩ ጥበቃ፣ ንግድ ወይም የምንዛሬ ስራ የሚካሄድበትን የአገር ወይም የውጭ አገር ሀብት የሆነውን ወርቅ ወይም ማናቸውንም ዓይነት ጥሬ ገንዘብ አስመልክቶ የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፯፻፹፮ ስለከበሩ ማዕድኖች አጠባበቅ የወጡ ሕጎችን መጣስ</u>

ማንም ሰው በዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፫፻፵፯ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ ስለከበሩ ማዕድኖች አጠባበቅ፣ ቁጥጥር፣ ባለቤት መሆን፣ ግዥ ወይም ሽያጭ የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፯፻፲፯ የሚተላለፉ ሰነዶችን፣ አክሲዮኖችን ወይም የግዴታ ወረቀቶችን የሚመለከቱ ሕጎችን መጣስ

ማንም ሰው እንደ ቼክ፣ የሐዋላ ወረቀት የመሳሰሉ የሚተላለፉ ሰነዶችን እንዲሁም የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ኩባንያዎች አክስዮኖችን ወይም የግዴታ ወረቀቶችን የሚመለከት ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፯፻፲፰ ቁጠባና ባንኮችን የሚመለከቱ ሕጎችን መጣስ

ማንም ሰው የባንክ ተቋማትን ወይም ኩባንያዎችን፣ አበዳሪ የሆኑ ተቋሞች፣ ኩባንያዎች ወይም ፈንዶችን ወይም ሕዝቡ ገንዘቦችን ወይም ተቀማጮችን እንዲያስቀምጥ ወይም የባንክ ወይም የስቶክ ኤክስቼንጅ ሥራ ውስጥ እንዲሳተፍ ጥሪ የሚያደርጉ የመንግሥት ወይም የግል ድርጅቶችን መቋቋም፣ መከፈት፣ አስተዳደር እና ቁጥጥር የሚመለከተውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፯፻፲፱ ሎተሪዎችንና ውርርዶችን የሚመለከቱ ሕጎችን መጣስ

፩ ማንም ሰው፡-

ሀ/ አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ ሳያገኝ ትርፍ ለማግኘት ሲል ሎተሪዎችን፣ እንደሙያ የተያዙ የውርርድ ጨዋታዎችን በይፋ ያቋቋመ፤ ወይም

ለ/ ትርፍ ለማግኘት ሲል ያለ ፍቃድ በአደባባይ ወይም ለሕዝብ ክፍት በሆነ ቦታ፣ ወይም ለመሰብሰቢያ በተዘጋጀ ክበብ የቁማር ጨዋታን ወይም ውርርዶችን ወይም በመንግሥት የተከለከሉ ማናቸውንም ሌሎች የዕድል ጨዋታዎችን አቋቁሞ የነገደ ወይም፤ እንደዚህ ባለ ጨዋታ ወይም ውርርድ የተሳተፈ፤ ወይም

ሐ/ በማናቸውም ሌላ መንገድ አግባብነት ያለውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ፤

እንደሆነ፣ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

፪ ለሕዝብ ጥቅም ወይም ለበጎ አድራጎት ዓላማ ሲባል በሕግ አግባብ የሚቋቋሙ ሎተሪዎች እና ውርርዶች የሚያስቀጡ አይደሉም።

## አንቀጽ ፯፻፹፯ <u>የዋጋ ቁጥጥርን የሚመለከቱ ሕጎችን መጣስ</u>

ማንም ሰው:-

ሀ/ በሞኖፖል የተያዙ ወይም ያልተያዙ ብረታ ብረቶችን፣ ሸቀጣ ሸቀጦችን፣ ምርቶችን ወይም ማናቸውም ዓይነት ዕቃዎችን በመንግሥት ተወስኖ በአግባቡ ታትሞ ከወጣ የዋጋ ዝርዝር አስበልጦ የሸጠ ፡ ወይም

ለ/ በሕግ ከታዘዘው ወይም ከተፈቀደው በተለይም ለንብረት መገልገያ ሊገዛ ወይም ለማናቸውም ዓይነት

ሌላ ኪራይ ከተወሰነው ዋጋ በላይ ያስከፈለ ወይም የጠየቀ፤ ወይም

ሐ/ በማናቸውም ሌላ መንገድ የዋጋ ተመን የሚመለከተውን አግባብነት ያለውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ፤

እንደሆነ፣ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፫፻፺፩ የንግድና የሙያ ሥራዎችን ስለማቋቋም፣ ማካሄድና መቆጣጠር የወጡ ሕጎችን መጣስ

ማንም ሰው በዚህ የወንጀል ሕግ ወይም ለተለዩ የሙያ ወይም የንግድ ሥራዎች በተደነገጉ ሕጎች መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ የኢንዱስትሪ እና የንግድ ድርጅቶችን፣ እደጥበባትን፣ ባለሙያዎችን፣ ጊዜያዊ ወይም ወቅታዊ ሥራዎችን ወይም የሙያ ማኅበራትን እና ማናቸውም ዓይነት ማኅበሮችን ስለመፍቀድ፣ ስለሚያስፈልገው ችሎታ፣ ስለመመዝገብ፣ ሥራቸውን ስለማካሄድ ወይም ስለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፤
በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## ምዕራፍ ሦስት

## ወታደራዊ ግዴታዎችን መጣስ እና በመከላከያ ሠራዊት እንዲሁም በፖሊስ ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

## አንቀጽ ፫፻፺፪ ወታደራዊ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶችን መወሰን

ወታደራዊ ወንጀሎችን በሚመለከት፡ በዚህ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ውስጥ /አንቀጽ ፪፻፹፬-፫፻፳፭/ ከተደነገጉት

ሁኔታዎች ውጭ፣ ወታደራዊ ግዴታዎችን መጣስ እና በወታደራዊ ዲሲፕሊን ላይ የሚፈጸሙ ጥፋቶች፣ አግባብ ያለው የመከላከያ ሠራዊት ባለሥልጣን በሚያወጣው ትዕዛዝና ደንብ ይወሰናሉ::

## <u>አንቀጽ ፯፻፺፫ ወታደራዊ የዲስፕሊን ቅጣቶች</u>

፩ በወታደራዊ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ማንኛውም ማዕረግ ያለው የመከላከያ ሰራዊት አባል ወይም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የሚሠራ ማንኛውም ሌላ ሰው፣ የጦር ምርኮኛ ወይም ግዞተኛ አግባብ ባለው የመከላከያ ሠራዊት ደንብ ውስጥ በተመለከተው የዲሲፕሊን ቅጣቶች ይቀጣል::

፪ ለነሱ በተለይ ከተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች በቀር /አንቀጽ ፫፻፲፱ እና ፯፻፶፩/ እነዚህ ሰዎች መደበኛ የሆኑ ወንጀሎችን የፈጸሙ እንደሆነ፤ በመደበኛ ድንጋጌዎች ውስጥ በተመለከቱት መደበኛ ቅጣቶች ይቀጣሉ::

## <u>አንቀጽ ፯፻፺፬ በመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

በመከላከያ ሠራዊት አባል ወይም በመከላከያ ሠራዊት ወይም በእነዚሁ ተቀጽላ አገልግሎቶች ላይ፣ የሚደረግ ማናቸውም ጥፋት እንዲሁም የእነዚህን ጥቅም በሚመለከት አግባብ ባለው ወታደራዊ ባለሥልጣን የሚወጡ ደንቦችን፣ ትዕዛዞችን ወይም የጥንቃቄ እርምጃዎችን መጣስ በወንጀል የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር፣ በደንብ መተላለፍ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ያስቀጣል::

## <u>አንቀጽ ፯፻፺፭ ደንቡ ለፖሊስ ሠራዊት ተፈፃሚ መሆኑ</u>

፩ ከዚህ በላይ የተመለከቱት መርሆች፣ ስለፖሊስ ግዴታዎችና በግዳጅ ላይ እያሉ ስለሚገባቸው

BACK



ደህንነት በተደነገጉ ደንቦች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ቅጣቶችን በሚመለከትም ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፪ የፖሊስ አባላት እንደ መንግሥት ሠራተኛ ሆነው የሚያከናውኑትን ሥራ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው::

## ምዕራፍ አራት

## በመንግሥት የሥራ ግዴታዎች እና በመንግሥት መሥሪያ ቤት

## /ባለሥልጣን/ ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

### ክፍል አንድ

### በመንግሥት የሥራ ግዴታዎች ላይ የሚደረጉ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

**አንቀጽ ፯፻፺፯ በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል**

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፬፻፯ ከሚያስቀጣው ውጭ፣ ከተሰጠው ሥልጣን በላይ አሳልፎ የሠራ ወይም በሥልጣኑ አላግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

**አንቀጽ ፯፻፺፰ የማስገደድ መብትን ከመጠኑ ማሳለፍ**

በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፳፪ - ፬፻፳፬ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ ቤትን የመበርበር፣ ዕቃን የመያዝ ወይም የመውረስ፣ የማሸግ ወይም እሽግን የማንሣት፣ አካልን የመፈተሽ ወይም የመመርመር፣ ሰውን የመያዝ፣ የማሰር፣ በቁጥጥር ስር የማድረግ፣ የምርመራ ቃልን የመቀበል ወይም ይህን የመሰለ

BACK



ማናቸውም ሌላ ተግባር እንዲፈጽም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ ይህንን ሥልጣኑን በተለይም የሚያበሳጭ፣ የሚያሳዝን፣ መልካም ሥርዓትን ያልተከተለ ወይም ትክክል ያልሆነ ዘዴን በመጠቀም ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፬፻፳፰ ሐቀኛነትን ማጓደል

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፲፩ - ፬፻፲፱ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ ሐቀኝነት የጐደለውን ድርጊት ለመፈጸም ሲል በተሰጠው ሥልጣን ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፬፻፳፱ የአድልዎ እርዳታ መስጠት

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፰፣ ፬፻፱ እና ፬፻፲፬ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ፣ ለግል ጥቅሙ ሲል ከእርሱ ዘንድ ጉዳይ ያለውን ወይም በእርሱ ሥልጣን ስር ያለውን ሰው በአድልዎ የረዳ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፰፻ በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚሰጡትን ኦፊሴላዊ ወረቀቶች በግዴለሽነት መስጠት

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ፡-

ሀ/ የተለመደውን የአንድን ሰው ማንነት ማረጋገጫ ዘዴ ሁሉ ተጠቅሞ የተባለውን ሰው ማንነት እና

BACK



የተባለውን ሰነድ ወይም ኦፊሴላዊ ወረቀት የመቀበል መብቱን አስቀድሞ ሳያረጋግጥ ላልታወቀ ሰው የይለፍ ወረቀት/ፓስፖርት፣ መታወቂያ ደብተር፣ ፈቃድ፣ የወንጀለኞች ሪከርድ ግልባጭ፣ የመልካም ጠባይ ምስክር ወረቀት ወይም የድህነት ማስረጃ ወይም በጠቅላላው የአንድን ሰው ማንነት የሚገልፅ ሰነድን ወይም ኦፊሴላዊ የምስክር ወረቀትን የሰጠ፤ ወይም

ለ/ ሌላው ሰው የሰነዱ ባለቤት አለመሆኑን ወይም በሰነዱ የመጠቀም መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ በእንደዚህ ዓይነቱ ሰነድ ወይም ኦፊሴየላዊ ማስረጃ እንዲጠቀምበት የፈቀደለት፤

እንደሆነ፤ በመቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል፡፡

## አንቀጽ ፫፻፩ አነስተኛ የሆኑ ጉዳዮች፤ የሥነ ሥርዓት /የዲሲፕሊን/ ቅጣቶች

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የመንግሥት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ አነስተኛ የሆነ የደንብ መተላለፍ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነና ፍርድ ቤቱም ለዚህ ጥፋት የዲስፕሊን እርምጃ መውሰድ ብቻ በቂ መስሎ ሲታየው በዚህ ሕግ የተመለከተውን ቅጣት በመተው ለዚህ ውሣኔ የበቃበትን ምክንያት ገልጸ ተገቢ መስሎ የታየውን የዲስፕሊን /አስተዳደራዊ/ ቅጣት እንዲወስንበት ደንብ ተላላፊው ወደሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል አለቃ ያስተላልፈዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በመንግሥት መሥሪያ ቤት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

## አንቀጽ ፫፻፪ ኦፊሴላዊ ማስታወቂያዎችን መጉዳት

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፴፪ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ፣ በአደባባይ የተለጠፈውን

ኦፊሴላዊ ማስታወቂያ ወይም መግለጫ /ፕላካርድስ/ ከስፍራው ያነሣ፣ የቀደደ፣ ያበላሸ፣ የሰረዘ፣ የደለዘ፣ አስቦ የጐዳ ወይም ያቆሸሸ እንደሆነ፤

ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

**አንቀጽ ፰፻፫ አስገዳጅ የሆኑ ኦፊሴላዊ መግለጫዎችን ወይም የሚመዘገቡ ነገሮችን አለመስጠት ወይም አለማስመዝገብ**

፩ ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፩፻፶፩ ወይም በሌላ ልዩ ሕግ ድንጋጌ መሠረት ከሚያስቀጡት ውጭ፣ መስጠት ወይም ማስመዝገብ የሚገባውን ማናቸውንም ዓይነት ኦፊሴላዊ መግለጫ ወይም ተመዝጋቢ ነገር በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ሳይሰጥ ወይም ሳያስመዘግብ የቀረ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

፪ ጤናን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ስለሚሰጡ የሙያ መግለጫዎች የሚመለከተው ልዩ ድንጋጌ /አንቀጽ ፰፻፶፰/ እንደተጠበቀ ነው።

**አንቀጽ ፰፻፩ ተገቢ ያልሆነ ማስታወቂያ**

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፩፻፶፰ እና ፩፻፺፩ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ የአንድ የመንግሥት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ተግባሮችን፣ ውይይቶችን ወይም ውሳኔዎችን መግለፅ የሚከለክለውን ኦፊሴላዊ ሕግ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፬፻፵፭ በሌለው ሥልጣን መገልገል</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፸፪ ከሚያስቀጡ ሁኔታዎች ውጭ፣ በሕግ አግባብ ያጣውን ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፈውን ወይም በፍርድ ለጊዜው የታገደበትን ወይም እስከ ጭራሹ የተከለከለውን ሥልጣን እንዳለ በማድረግ አውቆ የተገለገለበት እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፵፮ ባለሥልጣንን የመርዳት እንቢታ</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፸ ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ የሥራ ግዴታውን እያከናወነ ያለ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ላንድ ለተወሰነ ዓላማ በተለይም የሕዝብ ሰላም መናወፅን፣ የወንጀል መፈፀምን ወይም የወንጀለኛ ማምለጥን ለመከላከል የሚረዳውን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን እርዳታ ወይም ድጋፍ እንዲሰጠው ሲጠራው ወይም ሲጠይቀው ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሳያጋጥመው ወይም የተጠየቀውን እርዳታ ቢሰጥ በራሱ ወይም በንብረቱ ላይ የሚደርስበት አደጋ ሳይኖር እምቢ ያለ እንደሆነ፤
ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፬፻፵፯ ትዕዛዝን አለመፈፀም</u>

፩ ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፸ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ:-

ሀ/ ስሙን ወይም ማንነቱን እንዲነግር፣ ሥራውን / ሙያውን፣ መኖሪያ ስፍራውን፣ አድራሻውን

ወይም የግል ሁኔታውን የሚመለከት ማናቸውንም ሌላ ዝርዝር ጉዳይ እንዲገልጽ፤ ወይም

ለ/ እንዲቆም ወይም እንዲንቀሳቀስ እንዲሄድ፣ የሕዝብ መተላለፊያ መንገድን እንዲለቅ፣ የያዛቸውን ሰነዶች፣ የጉዞ ዕቃዎች ወይም አጠራጣሪ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች እንዲያስፈትሽ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም ሌላ ትዕዛዝ እንዲፈጽም፤

የሥራ ግዴታውን በሚያከናውን አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በአግባቡ ሲጠየቅ ወይም ሲታዘዝ እንቢተኛ የሆነ እንደሆነ፤

ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

፪ ማንም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /፩/ በፊደል (ሀ) ውስጥ የተመለከተውን ጉዳይ አስመልክቶ ያልሆነ መረጃ የሰጠ እንደሆነ፤ በተመሳሳይ ቅጣት ይቀጣል::

## ምዕራፍ አምስት

## በሕዝብ ደኅንነት፣ ሰላምና ተረጋግቶ መኖር ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

## ክፍል አንድ

## በሕዝብ ደኅንነት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

### አንቀጽ ፫፻፫ የጦር መሣሪያዎችንና ጥይቶችን መቆጣጠር

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፹፩ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ:-

ሀ/ የተኩስ መሣሪያዎች ወይም ሌሎች የጦር መሣሪያዎችና ጥይቶች መሥራትን መፈብረክን፣ መኖራቸውን ማስታወቅን፣ መያዝን፣ ማስረከብን፣መቆጣጠርን፣ በነሱ መነገድን ወይም መገልገልን የሚመለከት ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ፤ ወይም

ለ/ ላልተፈቀደለት ሰው በተለይም ለአካለመጠን ላልደረሰ ልጅ እያወቀ የጦር መሣሪያዎችን ወይም ጥይቶችን የሸጠ ወይም ያስረከበ ወይም ተገቢውን ቁጥጥር ሳያደርግ እንዲጠቀምበት የፈቀደ፤

እንደሆነ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

**<u>አንቀጽ ፰፻፱ የተከለከለ የጦር መሣሪያን መያዝና በዚሁ መገልገል</u>**

ማንም ሰው እንዲኖረው ወይም እንዲይዝ ያልተፈቀደለትን የጦር መሣሪያ በአደባባይ ወይም ሕዝብ በሚገኝበት ስፍራ ይዞ የተገኘ ወይም ቢፈቀድለትም በተከለከለበት ጊዜ ወይም ሥፍራ በመሣሪያ የተገለገለ እንደሆነ፤

እስከ አንድ መቶ ብር በሚደርስ መቀጮ ወይም እስከ ስምንት ቀን በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

**<u>አንቀጽ ፰፻፲ የውጭ አገር ዜጎችን መቆጣጠር</u>**

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፪፻፵፫ መሠረት ከሚያስቀጣው ውጭ፣ የውጭ አገር ዜጎች መተላለፍን /ትራንዚትን/ አገር ውስጥ መግባት ማስታወቅን፣ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ መኖርን ወይም ቁጥጥርን የሚመለከተውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፡

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፲፩ ያለፈቃድ ስምን መለወጥ ወይም በሌላ ስም መጠራት

፩ ማንም ሰው ማንነቱን ለመደበቅ ወይም አግባብ ካለው ባለሥልጣን ቁጥጥር ለማምለጥ በማሰብ በሕገ-ወጥ መንገድ የፈጠራ ስም ለራሱ የሰጠ፣ እውነተኛ ስሙን የለወጠ ወይም በዚያው ላይ ሌላ ስም የጨመረ ወይም በሌላ ሰው ስም የተጠቀመ እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

፪ ሕጋዊ የሆነው የሙያ፣ የስነ-ጽሁፍ ወይም ይህን የመሰለው የፈጠራ ስም ወይም በልማድ የሚታወቀው የቅጽል ስም አጠቃቀም በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚያስቀጣ አይደለም::

## ክፍል ሁለት

## በሕዝብ ሰላም፣ ፀጥታና ሥርዓት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

## አንቀጽ ፫፻፲፪ መገናኛ ብዙኃንንና ማስታወቂያን ስለመጠበቅ የወጣውን ሕግ መጣስ

ማንም ሰው የታተሙ ሰነዶችን፣ የሕዝብ ማስታወቂያዎችን፣ በአደባባይ የሚለጠፉ ጽሑፎችንና ስዕሎችን ወይም በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔት ወይም በሌላ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፍ መልዕክትን ስለማሳተም፣ ስለማሳወቅ፣ ስለማከማቸት፣ ስለመሸጥ፣ ስለማሰራጨት ወይም ስለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፫፻፲፫ አስደንጋጭ መግለጫዎች፣ ወሬዎች ወይም ማስታወቂያዎች

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፹፭ እና ፬፻፹፮ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ የሕዝብን መልካም አኗኗር ወይም ጸጥታ ለማናጋት የታቀዱ ወይም

ለማናጋት የሚችሉ ሐሰተኛ ፣ የተጋነኑ ወይም የተዛቡ ወሬዎችን የገለጸ፣ ያሰራጨ፣ ለባለሥልጣን ያስታወቀ ወይም ያመለከተ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፭፻፲፬ ሐሰተኛ የአደጋ ምልክት መስጠት

ማንም ሰው አላስፈላጊ የእርዳታ ጥሪዎችን አውቆ በማድረግ ወይም ሐሰተኛ መልክቶችን በማስተላለፍ፡-

ሀ/ የአገልግሎት መሥሪያ ቤቶችን ወይም የርዳታ መምሪያዎችን፣ የመጓጓዣ፣ የሕክምና ወይም ከአደጋ የሚታደጉ አገልግሎቶችን፣ ፖሊስን፣ የእሳት አደጋ መከላከያን ወይም ሌላ ተመሣሣይ አገልግሎቶችን፤ ወይም

ለ/ ሐኪሞችን ወይም የሕክምና ሥራ የሚያከናውኑ ሰዎችን፤

ለዚሁ ጥሪ እንዲንቀሳቀሱ ያደረገ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፭፻፲፭ የሌሎችን ሥራ፣ ሰላምና ዕረፍት ማወክ

፩ ማንም ሰው በተለይም አምባጓሮ ወይም ጸብ በማንሣት፣ በጩኸት፣ በዘፈን፣ በግርግርና በጫጫታ፣ የጩኸት ድምፅ በሚሰጡ ምልክቶች፣ በመጥሪያዎች ወይም በደወሎች፣ በሚጮሁ መኪናዎች፣ መሣሪያዎች ወይም ሌሎች ድምፅ ሰጪ ዕቃዎች ያለአግባብ በመገልገል የሌሎች ሰዎችን ሥራ፣ ዕረፍት ወይም ሰላም ያወከ እንደሆነ፤

ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪ ጨኸቱ ወይም ሁከቱ የተፈጸመው በፖሊስ ደንብ ወይም በልማድ በተወሰነው መሠረት በሌሊት የሆነ እንደሆነ፣ ወይም በሆስፒታሎች፣ በትምህርት ቤቶች ወይም ይህን በመሣሰሉ ተቋሞች አቅራቢያ እንደሆነ፣ ወይም ደግሞ በአጠቃላይ ታስቦ በክፋት ወይም በተንኮል መንፈስ በመነሣሣት የሆነ እንደሆነ፤

ፍርድ ቤቱ መቀጮ ወይም አንድ ወር ለመድረስ የሚችል የማረፊያ ቤት እስራት ሊወስን ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ ፰፻፲፮</u> <u>ሃይማኖትን የመስደብና የማዋረድ ንግግር</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፺፪ እና ፬፻፺፫ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ፣ ሕዝብ ሊመለከትና ሊሰማ በሚችልበት ቦታ በምልክት ወይም በንግግር ሃይማኖትን፣ የሃይማኖት ሥርዓትን፣ ምልክቶችን ወይም የሃይማኖት አገልጋዮችን የሚያናንቅ ሁኔታን ያሳየ፣ የሰደበ፣ ያዋረደ ወይም የሌላውን ሰው ስሜት ወይም እምልኮ በሚነካ አኳኋን የተናገረ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል፡፡

<u>አንቀጽ ፰፻፲፯</u> <u>የበዓል ቀናቶችን መጠበቅ</u>

ማንም ሰው የግዴታ እንዲከበሩ በሕግ የተወሰኑትን የበዓላት አከባበር ስለመጠበቅ የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከስምንት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል፡፡

<u>አንቀጽ ፰፻፲፰</u> <u>አልኮል የሚያደርሰውን አደጋ መከላከል</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕግ ከተመለከተው ውጭ:-

BACK



ሀ/ አልኮልና እስፒርቶ ያለባቸውን መጠጦች በፋብሪካ ስለ መሥራትና በነዚሁ ስለመነገድ የወጣውን የመቆጣጠር ሕግ፣ ትዕዛዝ ወይም ደንብ የተላለፈ እንደሆነ፤

ለ/ በሕግ ከተፈቀደው ጊዜ ውጭ በሆነ ሰዓት ለሕዝብ ከተከፈቱት የንግድ ቤቶች ውስጥ የአልኮል መጠ ጦችን የሸጠ፣ የገዛ፣ የጠጣ እንደሆነ፤

ሐ/ እነዚሁኑ አልኮል ያለባቸውን መጠጦች ለአካለመጠ ን ላልደረሱ አዕምሮአቸው ትክክለኛ ባለመሆኑ በሙሉ ኃላፊነት ለማይጠየቁ ወይም በጣም መስከራቸውና አደገኛ መሆናቸው በግልጽ ለሚታዩ ሰዎች ከመጠን ባለፈ ብዛት ለሕዝብ ክፍት በሆኑ ቦታዎች የሸጠ፣ የሰጠ ወይም ያቀረበ፣ እንዲሰጣቸው ወይም እንዲሸጥላቸው ያደረገ እንደሆነ፤

መ/ በሕዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ ወይም ለሕዝብ በተከፈተና ሕዝብ የሚያየው ስፍራ አስቦ ሌላው ሰው እንዲሰክር ያግባባ፣ ሌላውን ሰው ያሰከረ ወይም እራሱ የሰከረ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፰፻፲፱ ሰክሮ ወይም አእምሮ የሚያናውጥ ነገር ቀምሶ ሕዝብን ማወክ

ማንም ሰው በሕዝብ አደባባይ የሚያስነቅፍና የሚያስነውር ሥራ የፈጸመ የማስፈራራት ንግግርን የተናገረ እንደሆነ፤

በአስተዳደር ክፍል በኩል ሊፈጸሙበት የሚገባቸው የጸጥታ አጠባበቅ የጥንቃቄ ቅጣቶች የሚፈጸሙበት መሆናቸው ሳይቀር ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ

መቀጮ ወይም ከስምንት ቀን በማይበልጥ በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፹፭የምግብና የመጠጥ ቤቶችን መጠበቅና መቆጣጠር</u>

የማናቸውም መጠጥ ቤት፣ ምግብ ቤት፣ መኝታ ቤት ወይም ሆቴል ባለቤት፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ባለይዞታ ወይም ጠባቂ የሆነ ማንኛውም ሰው ስለእነዚሁ ንግድ ቤቶች የወጣውን ማናቸውንም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፤ በተለይም

ሀ/ በንግዱ የመጠቀም መብትን፣ የንግዱን አካሄድ ሥርዓትና ንግዱ ለኅብረተሰቡ ለሚሰጠው አገልገሎት ማረጋገጫ፤ ወይም

ለ/ ንግዱ ስለሚከፈትበት ወይም ስለሚዘጋበት ሰዓት ወይም ስለማናቸውም ሌላ ቁጥጥር፤ የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፹፮ የቲያትር ቤቶችንና የሕዝብ መደሰቻ ሥፍራዎችን መጠበቅ</u>

የማናቸውም ሲኒማ ቤት፣ ቲያትር ቤት ወይም የማናቸውም ሌላ ዓይነት የሕዝብ መዝናኛ ቤት ባለንብረት፣ አደራጅ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ባለይዞታ፣ መሪ /ዳይሬክተር/ ወይም ወኪል ሲኒማ ቤቶችን፣ ቲያትር ቤቶችን ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት የሕዝብ መዝናኛ ቤቶችን በሚመለከት የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፤ በተለይም

ሀ/ ሥራውን ስለማቋቋም ወይም ለሕዝብ ስለማሳየት ፈቃድ የማግኘት ወይም በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፰፻፹፯

ከተመለከተው ውጭ የደኅንነታቸውንና የሥራ አመራራቸውን ስለሚመለከት፤ ወይም

ለ/ ስለመልካም ሥነ ምግባር፣ ስለ ሕዝብ ሥርዓት ጥቅም ወይም ሕፃናትንና አካለመጠን ያልደረሱ ወጣቶችን ስለመጠበቅ፣ ስለተቋቋመው የምርመራና በቅድሚያ ማረጋገጫዎችን ስለመስጠት ጉዳይ፤ ወይም

ሐ/ ለሕዝብ መዝናኛ ወይም እንደ ቲያትር፣ ሲኒማ ፊልም ትርዒቶችን ማሳያ ቦታዎች ስለሚከፈቱበት፣ ስለሚዘጉበት ወይም ትርዒቶች ስለሚታዩባቸው ሰዓቶች ወይም እነዚሁ ቦታዎች ወይም ተቋሞች ስለመቆጣጠር፤

የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፤ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፰፻፰፪ እንስሳትን በሚያሰቅቅ ሁኔታ ማንገላታት</u>

ማንም ሰው፡-

ሀ/ የሕዝብ መሰብሰቢያ በሆነ አደባባይ ለሕዝብ በተከፈተ ቤት ወይም ለሕዝብ በሚታይ ስፍራ በእንስሳት ላይ ማናቸውም ተገቢና መብታዊ የሆነ ምክንያት ሳይኖረው የጨካኝነትን ተግባር የፈጸመ፣ በመጥፎ ሁኔታ ያጉላላ ወይም ያሠቃየ ወይም አስቃቂ የሆነ የጭካኔ ሥራ የፈጸመ እንደሆነ፤

ለ/ እንስሳዎች በጭካኔ የሚሰቃዩበት፣ አካላቸውን በመቁረጥ የሚጐድልበት ወይም በጭካኔ የሚገደሉበት ሁኔታ የሚታይበትን አዘጋጆች ለሕዝብ ለማሳየት እንስሳት እርስ በርሳቸው እንዲዋጉ ያደረገ ወይም ከተያዙ እንስሳት ጋር የሚደረግ ውጊያ ያዘጋጀ ወይም በተያዙ እንስሳት ላይ ዒላማ የተኮሰ ወይም የዚሁ ዓይነት ሥራ የሚታይበትን ያደራጀ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

## ክፍል ሦስት

## በሕዝብ ፀጥታ ላይ የሚፈፀም ደንብ መተላለፍ

### አንቀጽ ፰፻፴፫ የሰዎችን ሰላማዊ ኑሮ መንካት

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ ከተደነገገው ሁኔታ ውጭ:-

ሀ/ ክፉ ወይም አደገኛ የሆነ ውሻ ወይም ሌላ ዓይነት አውሬን በማነሣሣት፤

ለ/ በሰው ቤት ላይ ድንጋይ በመወርወር ወይም ጠንካራና ስለታም የሆኑ ዕቃዎችን በሰው ላይ በመጣል ወይም ለማቁሰል፣ ለመጉዳት ወይም አደጋ ለማድረስ የሚችል ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ነገር በመጣል ወይም በመወርወር፤

ሐ/ ለፖሊስ ሳያስታውቅና ሳያስፈቅድ ወይም ለሕዝብ ማስጠንቀቂያ የሚሆን ተገቢ ምልክት ሳያደርግ ወጥመድ በመዘርጋት ወይም የማስጠንቀቂያ መሣሪያ ወይም አደገኛ የሆነ ማናቸውንም ሌላ መሣሪያ በማናቸውም ቦታ ላይ በማስቀመጥ፤

ሌላውን ሰው ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

### አንቀጽ ፰፻፴፬ በአደገኞች ሰዎች ወይም በእንስሳት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር አለማድረግ

ማንም ሰው:-

ሀ/ በእብድነት የታሰሩትን፣ በሙሉ ኃላፊነት ሊጠየቁ የማይችሉትን፣ በአልኮል መጠጥ ወይም በሚያፈዙ ነገሮች የተመረዙትን በሽተኞች ወይም በአደገኛነታቸው ምክንያት ለነዚሁ በተዘጋጀው የጥበቃ ቤት የታሰሩትን እንዲሁም ክፉት፣ አደገኛነት፣ ተናካሽነት ወይም ተዋጊነት ያላቸውን እንስሳዎች ወይም አውሬዎችን ስለመጠበቅና የአኗኗራቸውን ደንብ ስለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፤

ለ/ የዚህ ዓይነት ሰዎች ወይም እንስሶች ከሚጠበቁበት ቦታ የጠፉ ወይም ያመለጡ መሆናቸውን አስቦ ለባለስልጣኖች ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ፤

ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም አንድ ወር ለመድረስ በሚችል የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፹፭ የሰዓት እላፊ እና በሌሊት መዘዋወርን መቆጣጠር</u>

ማንም ሰው ስለ ሌሊት ሰዓት እላፊ፣ በሌሊት መዘዋወርን ስለመከልከል ወይም ስለመወሰን አግባብ ባለው ባለሥልጣን የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ ያላከበረ እንደሆነ፤

ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፹፮ የሕንፃ ሥራዎችን መቆጣጠር</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፭፻፩ ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ:-

ሀ/ የሕዝብ ወይም የግል የሆኑትን ማናቸውንም ሕንፃዎች ስለመሥራት፣ በጥንቃቄ ስለመያዝ፣ ስለማደስ፣ ስለመጠገን ወይም ስለማፍረስ፤ ወይም

ለ/ የሕዝብ መሰባሰቢያ ቦታዎችን፣ አዳራሾችን፣ ለቴአትር ትወናና ለመዝናኛ ወይም ለመሰብሰቢያ የሚያገለግሉ ቦታዎችን ወይም ለነዚህ ቦታዎች የተገጠሙ መሣሪያዎችን ወይም የመኖሪያ፣ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ሕንፃዎችን ደኅንነት ስለመጠበቅ፤

የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፰፻፹፯ <u>መንገዶችና የሕዝብ መሰባሰቢያ ሥፍራዎችን መቆጣጠር</u>

ማንም ሰው የሕዝብ ደኅንነትን በተለይም:-

ሀ/ አግባብ ያላቸው ደንቦችን ባለማክበር ወይም አስፈላጊ የሆኑ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳይወስድ ዕቃዎችን፣ ቆሻሻን፣ ጥራጊን ወይም የማይናቅ አደጋ ሊያደርሱ ወይም እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውም ዓይነት ሌሎች ነገሮችን በሕዝብ መተላለፊያ፣ መሰብሰቢያ ወይም ለሕዝብ ክፍት በሆነ ቦታ ላይ በማስቀመጥ፣ በማንጠልጠል፣ በማራገፍ ወይም በመጣል፤ ወይም

ለ/ እነዚህኑ የጣላቸውን ወይም ያስቀመጣቸውን ነገሮች ወይም በእንደዚህ ዓይነት ቦታ ላይ ያደረጋቸውን ቁፋሮዎች፣ ግንባታዎች ወይም ሥራዎች መኖራቸውን የሚያመለክቱ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ወይም ብርሃን ከማድረግ ቸል በማለት ወይም ደግሞ አስገዳጅ ሁኔታ ሳይኖር ወይም ያለበቂ ምክንያት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል

የተተከሉትን መብራቶች በማንሣት ወይም በሚያበረክቱት አገልግሎት ጣልቃ በመግባት፤

የሕዝብ ደኅንነትን ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፰፻፷፰</u> <u>የመገናኛ ደኅንነትን አደጋ ላይ መጣል</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፭፻፭-፭፻፲፫ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ፣ ስለእግረኞች፣ እንስሳት ወይም ማናቸውም ዓይነት ተሽከርካሪ የመዘዋወር ፈቃድ፣ ሁኔታ እና ቁጥጥር እንዲሁም የተሽከርካሪን መኖር ማስታወቅ፣ አያያዝ፣ እድሳት እና አጠቃቀም የሚመለከተውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፰፻፷፱</u> <u>እሳት፣ ፈንጂዎችንና አደገኛ ንጥረ ነገሮችን መቆጣጠር</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፬፻፺፬-፭፻ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ:-

ሀ/ ቃጠሎን ወይም የእሳት አደጋን ስለመቆጣጠርና በተለይም የኤሌክትሪክ ወይም ይህን መሰል ሌላ መስመርን ስለመዘርጋት፣ የጭስ ማውጫን፣ ምድጃዎችን፣ የውሀ ማፍሊያዎችን ወይም በእሳት የሚያገለግሉ ሌሎች መሣሪያዎችን አደጋ እንዳያደርሱ የመለያየትና የመሸፈን፣ በአግባቡ የመያዝና የመጠገን ግዴታን የሚመለከት ሕግን፣ ደንብን ወይም መመሪያን የጣሰ እንደሆነ ፤ ወይም

BACK



ለ/ ዲናሚቶች፣ ቦምቦች፣ አዳፍኔዎች፣ የፈንጠዝያ ርችቶች በተወሰኑ ቦታዎች እንዳይፈነዱ የሚከለክለውን ወይም ይህን የመሳሰሉ ተኩሶች በሚደረጉበት ጊዜ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚያስገድደውን ወይም የተቀጣጠሉ የነበልባል አኤሮስታቶች መወርወርን ወይም ፈንጂ ወይም ተቀጣጣይ ነገሮችን ይህን በመሰለ መንገድ መጠቀምን የእሳት አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉትን እነዚሁኑ ነገሮች ተገቢ ባልሆነ ስፍራ መጣልን የሚከለክል ሕግን፣ ደንብን ወይም መመሪያን የጣሰ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ዘይቶችንና የነዳጅ ዘይቶችን እንዲሁም የነዚህን ውጤቶችን፣ ባሩድና ማናቸውንም ፈንጅ፣ ተቀጣጣይ፣ መርዛማ፣ ቦርቧሪ/አሰልሳይ ወይም አደገኛ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ስለመፈብረክ ወይም ማዘጋጀት፣ መያዝ፣ አያያዝ፣ ማጓጓዝ፣ መግዛት፣ እጥቅም ላይ ስለማዋል የወጣ ሕግን፣ ደንብን ወይም መመሪያን የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

## ምዕራፍ ስድስት

## በሕዝብ ጤና እና በፅዳት ጥበቃ ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

### አንቀጽ ፰፻፴፴ የሕዝብ ጤናና ጤናማነትን መቆጣጠር

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፭፻፲፬-፭፻፳፬ መሠረት ከሚያስቀጡት ውጭ:-

ሀ/ ስለውሃና ለውሃ አገልግሎት ስለተቋቋሙ መስመሮች ወይም መሰል ግዙፍ ሥራዎች የሕዝብ መሰባሰቢያ ቦታዎችና ተቋሞች፣ ቤቶችና መኖሪያዎች፣ ፋብሪካዎች ወይም የማምረቻ ተቋሞች እንዲሁም

ስለኢንዱስትሪና ስለንግድ ማከናወኛ ግቢዎች ንጽሕና፣ ጤናማነትና ጽዳት አጠባበቅ፤ ወይም

ለ/ በሽታዎችን በተለይም የአእምሮ እና ተላላፊ በሽታዎችን፣ ወረርሽኝን እና የእንስሳት በሽታዎችን ስለመከላከል፣ መኖራቸውን ስለማሳወቅ፣ ለመከላከል የሚረዱ ሕክም ናዎችን ስለማድረግ ወይም ስለመቆጣጠር፤

ሐ/ የአካባቢ ብክለትን ስለመከላከል፣ ስለመግታት፣ ስለማቆም ወይም በጠቅላላው ስለመቆጣጠር፤

የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፯፻፴፩ መርዛማና አደንዛዥ ንጥረ ነገሮችንና መድኃኒቶችን መቆጣጠር

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፭፻፳፭ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ:-

ሀ/ ያለሕጋዊ ፈቃድ ወይም ግልጽ የሀኪም ትዕዛዝ ሳይኖረው ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ፣ መርዛማ፣ ጤናን የሚጐዱ ወይም ለጤንነት አደገኛ የሆኑ ዕጾችን፣ ንጥረ ነገሮችን፣ መድኃኒቶችን ወይም ምርቶችን ያበቀለ፣ ያመረተ፣ ያዘጋጀ፣ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ያስረከበ ወይም የሰጠ፤ ወይም

ለ/ እነዚህን ያለፈቃድ መስጠት አይቻልም የሚል ግልጽ ክልከላ ባይኖርም እንደነዚህ ያሉ መድኃኒቶችን፣ ንጥረ ነገሮችን ወይም ምርቶችን በሕግ የተደነገጉ ደንቦችን ወይም ልማድ የሚጠ ይቀውን የተለመደ የአሠራር ደንቦችን ባለመከተል

ኃላፊነት ለሌላቸው፣ ለአካለመጠን ላልደረሱ፣ ለታመሙ ወይም እነዚህ ነገሮች በግልጽ እንደሚጐዷቸው ወይም እንደማይስማሟቸው ለታወቁ ሰዎች እያወቀ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም ያስረከበ፤ ወይም

ሐ/ የሥራ ወይም የሙያ ደንቦች፣ ልማድ ወይም የተፈጥሮ ዕውቀት የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ሳያደርግ በተለይም የመሳሳት ወይም የመደናገር ስጋት ሲኖር እንደነዚህ ያሉ መድኃኒቶችን ንጥረ ነገሮችን ወይም ምርቶችን ያስቀመጠ ወይም የሸጠ ያደለ፤ ወይም

መ/ ማስጠንቀቅ ግዴታው ወይም የሚቻለው ሆኖ ሳለ እነዚሁ የሚያስከትሉትን ለእሱ የታወቀውን የመመረዝ ወይም የመጉዳት አደጋ ለሌሎች ሰዎች ሳያስጠነቅቅ የቀረ፤

እንደሆነ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፭፻፴፬ ሌላው ሰው ኀሊናውን እንዲስት ወይም እንዲፈዝ ማድረግ</u>

፩ ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ /አንቀጽ ፭፻፴፪ እና ፭፻፴፫/ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ የሙያ ሁኔታው እንዲህ እንዲያደርግ ሳይፈቅድለት ወይም ተቀባይነት ያላቸውን አጠቃላይ የሕክምና ወይም የመድኃኒት አሰጣጥ /አደራረግ ልምዶችን በመጣስ/ በሚቃረን መልኩ ሌላውን ሰው የማሰብ ወይም በነፃ የመወሰን ችሎታን ለሚያሳጣ/ለሚያጠፋ ወይም ለሚለውጥ ለሕክምና ምርመራ መለማመጃ ወይም ማናቸውም ዓይነት የሕክምና ወይም ልማዳዊ አሠራር የዳረገው እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

፪ የሕክምና ሙከራዎች ወይም ለሕክምና የሚውሉ የሰውን ድርጊት በሰመመን የመቆጣጠር ተግባር በአግባቡ የተፈቀዱና ለማዝናናት ብቻ የሚደረጉ ሃሳብን የማስተላለፍ፣ መልእክትን ከርቀት የመላክ ድርጊቶች የሚያስቀጡ አይደሉም::

<u>አንቀጽ ፰፻፴፫ ምግቦችን፣ መጠጦችንና ሌሎች ሸቀጦችን መቆጣጠር</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፭፻፳፪ እና ፭፻፳፫ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ:-

ሀ/ ምግቦችን፣ ሥጋን፣ ወተትን፣ የአልኮል ወይም አልኮል ያልሆኑ መጠጦችን፣ የንግድ ዕቃዎችንና የእንስሳት መኖዎችን ስለማስቀመጥ፣ ስለ መሸጥ፣ ስለማጓጓዝ፣ በጥሩ ሁኔታ ስለማኖርና አያያዛቸውን ስለመቆጣጠር፤ የተሰጠውን ፈቃድ፤ ወይም

ለ/ የመገበያያ ቤቶችን መክፈትና መዘጋት፣ ሥራ አካሄድና ቁጥጥርን፤

የሚመለከት ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፴፬ የሕክምናና የመፈወስ ሙያዎችንና ሆስፒታሎችን መቆጣጠር</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፭፻፴፭ እና ፭፻፴፮ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ:-

ሀ/ የሕክምና፣ የመድኃኒት ቅመማና ዕደላ የእንስሳት ሕክምና ሙያዎች እና የማሸት ወይም የተፈጥሮ

ኃይሎችን በመጠቀም የሚደረግ ሕክምና /ፊዚኦቴራፒ/ እና መገጣጠሚያዎችን በመነካካት የሚደረግ ህክምናን /ካይሮፕራክቲስ/ ጨምሮ ተቀጽላ የሕክምና ሙያዎችን ለመሥራት ስለመፍቀድ እና ስለማከናወን፤ ወይም

ለ/ የመድኃኒት ቅመሞችን ወይም መድኃኒቶችን ስለመሸጥ ወይም ስለማደል፤ ወይም

ሐ/ ተመላላሽ ታካሚዎች ወይም በሆስፒታል ተኝተው የሚታከሙ በሽተኞች የሚስተና ገዱበትን ማናቸውም ዓይነት የህክምና ቦታ ወይም ተቋም ስለመክፈት፣ ለሚመለከተው ስለማስታወቅ፣ ሥራውን ስለመምራትና ስለማካሄድ፤

የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፭፻፴፭ የማስታወቅ ግዴታን አለመፈፀም

በሕግ አንዳንድ ጉዳዮችን የማሳወቅ ግዴታ ኖሮባቸው በተለይም የተላላፊ በሽታ፣ የዕፅ ሱሰኝነት፣ የእንስሳት በሽታ፣ የወንጀል ባህሪ ያላቸው ወይም በኅብረተሰቡ በጠቅላላው አደገኛ የሆኑ ድርጊቶች መዛመትን ወይም ስርጭትን ለመከላከል የሚጠቅሙ ጉዳዮችን አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያላሳወቁ ሐኪሞች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ መድኃኒት ቀማሚዎች፣ አዋላጆች፣ የእንስሳት ሐኪሞች እንዲሁም በሽተኞችን እንዲያስታምሙ በአግባቡ የተፈቀደላቸው ሰዎች ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ነገሩ ከበድ ያለ እንደሆነ ወይም በደጋጋሚነት ጊዜ በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣሉ።

## አንቀጽ ፭፻፴፮ የማከምን ተግባር አለመፈፀም

ሐኪሞች፣ መድኃኒት ቀማሚዎች፣ የእንስሳት ሀኪሞች፣ አዋላጆች ወይም የህክምና ሙያ እንዲያከናውን የተፈቀደለት ማንኛውም ሌላ ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፭፻፴፮ እና ፭፻፸፭ መሠረት ከሚያስቀጣው ውጭ፣ በሆነ

አኳኋን እርዳታቸው በሚያስፈልገው ሰው ላይ ጉዳት ወይም አደጋ የሚደርስበት ሆኖ ሳለ በቂ ምክንያት ሳይኖራቸው የማከም ወይም የሚያስፈልገውን መድኃኒት የማዘዝ፣ የመስጠት ወይም የማስታመም ተግባራቸውን ሳይፈጽሙ የቀሩ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣሉ::

<u>አንቀጽ ፰፻፴፯ አስከሬን ስለመቅበርና ስለማቃጠል የወጣውን ደንብ መጣስ</u>

ማንም ሰው ሙታንን ስለማሣየት፣ ስለመቅበርና ስለማቃጠል የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

<u>ርዕስ ሁለት</u>

<u>በሰዎችና በንብረቶች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

<u>አንቀጽ ፰፻፴፰ በዚህ ርዕስ ሥር ባልተሸፈኑ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ያለውን ተካፋይነት የሚመለከት ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ ወይም በሌላ የተለየ ሕግ ድንጋጌ መሠረት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር፣ ማንም ሰው በዚህ የደንብ መተላለፍ ሕግ ልዩ ድንጋጌዎች ውስጥ ከተመለከተው ውጭ ሰዎችን ወይም ንብረትን ለመጠበቅ የወጣውን ሕግ፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ፣ መመሪያ ወይም የጥንቃቄ እርምጃ የጣሰ እንደሆነ፤

በዚህ የደንብ መተላለፍ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች መሠረት በሚወሰን መቀጮ ወይም የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

**<u>አንቀጽ ፰፻፵፱ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ርዕስ ሥር በተመለከቱት የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ያለው ተካፋይነት</u>**

፩ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሃላፊ ወይም ሠራተኛ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ ወይም ድርጅቱን በመሣሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በደንብ ተላላፊነት /አንቀጽ ፴፪ እና ፴፱/ ሕግን፣ ደንብን ወይም መመሪያን በመጣስ በዚህ ርዕስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንዱን በሚተላለፍበት ጊዜ፣ ቀጣሪው ድርጅት እንደ ደንብ ተላላፊ ተቆጥሮ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፺፪ እና ፯፻፷፰ - ፯፻፸ በተመለከተው መሠረት ይቀጣል::

፪ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው ሁኔታ የደንብ መተላለፍ ጥፋት በሚፈፀም ጊዜ በድርጅቱ የሥራ አመራር ውስጥ ባለው የሥራ ድርሻ የተነሣ በደንብ መተላለፍ ጥፋቱ ተካፋይ የሆነ የድርጀቱ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ ርዕስ ስር በተመለከቱት አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል::

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>በሰዎች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ለሰውነት ጥበቃ የወጡ ደንቦችን መተላለፍ</u>

**<u>አንቀጽ ፰፻፶ የእጅ እልፊትና ቀላል የኃይል ድርጊት</u>**

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፭፻፷(፩) መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ:-

ሀ/ ሌላውን ሰው ሳይመታ ወይም ሳያቆስል የእጅ እልፊት ወይም ቀላል የኃይል ድርጊት የፈጸመበት እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሌላ ሰው ላይ ቆሻሻ፣ የሚያውክ ወይም የሚቀነቅን ወይም የሚያቆሽሽ ጠጣር ነገር ወይም ፈሳሽ የጣለበት ወይም ያፈሰሰበት ወይም የወረወረበት እንደሆነ፤

ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስምንት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፰፻፵፩ አስከሬን ወይም ቁስለኛን አለማስታወቅ

ማንም ሰው:-

ሀ/ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ሳያስታውቅ ሞቶ የተወለደን ወይም ሞቶ የተወለደ ነው የተባለውን ሕፃን ወይም ሌላ የሰው ሬሳን የደበቀ፣ የቀበረ፣ ውሃ ውስጥ የጣለ፣ ያቃጠለ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁናቴ እንዲጠፋ ያደረገ ወይም ሬሳን አግኝቶ ለተባለው ባለሥልጣን ሳያስታውቅ የቀረ፤ ወይም

ለ/ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ ምክንያት ሌላውን ሰው አቁስሎ ወይም ገድሎ ይህንኑ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ሳያስታውቅ የቀረ፤

እንደሆነ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፰፻፵፪ በግል ነፃነት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፭፻፹፭ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ ፣ ለአካለመጠን ያልደረሰ

BACK



ልጅን፣ ኃላፊነት የሌለበትን ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለበትን ሰው ወይም በሕግ ወይም በሌላ መንገድ በእርሱ ጥበቃ ስር የሆነውን ሰው በመንግሥት ወይም በግል ተቋም ውስጥ እንዲገባ ወይም በቁጥጥር እንዲውል ወይም የተባለውን ሰው ከደንብ ውጭ ወይም በሕግ ከተቀመጡት የጥንቃቄ እርምጃዎች ተቃራኒ በሆነ መልኩ በእንደዚህ ዓይነቱ ተቋም ውስጥ እንዲገባ ወይም ቁጥጥር ስር እንዲውል ያደረገ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፵፫</u> <u>የግል ምስጢር የመጠበቅ መብትን መንካት</u>

ማንም ሰው የፈፀመው ጥፋት ቀላል በመሆኑ ወይም በቸልተኛነት የተደረገ በመሆኑ ምክንያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፬፻፮ የተመለከተውን ቅጣት የማያስወስንበት ሆኖ ሲገኝ የሌላውን የግል ሕይወቱንና የኑሮውን ወይም በደብዳቤ የሚላላከውን የግል ምስጠ ሩን የገለፀበት እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፵፬</u> <u>በክብር ላይ የሚፈጸሙ ቀላል ጥፋቶች</u>

በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፮፻፲፰ መሠረት መቀጣት የማይገባቸው ቀላል የስድብ ወይም የማዋረድ ድርጊቶች በተፈጸሙ ጊዜ በተለይም ስድቡ ወይም ማዋረዱ ያልተሰራጨ ወይም ሦስተኛ ወገኖችን ወይም ተበዳዩን ያልገባው ሲሆን፣ ተበዳዩ አፀፋውን በሚመልስበት ወይም ጥፋተኛው በተናገረው ተጸጽቶ ይቅርታ በሚጠ ይቅበት ጊዜ ከቅጣት ነፃ ስለማድረግ የተመለከቱት አጠ ቃላይ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፍርድ ቤቱ እስከ አንድ መቶ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ

ወይም እስከ ስምንት ቀን ለመድረስ የሚችል የማረፊያ ቤት እስራት ሊወስን ይችላል::

## ክፍል ሁለት

## በመልካም ጠባይ /ሞራሊቲ/ ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

### አንቀጽ ፰፻፵፰ በመልካም ሥነ ምግባርና መልካም ጠባይ /ሞራሊቲ/ ላይ የሚፈፀሙ ጥፋቶች

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፮፻፴፱ - ፮፻፵፭ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ በአደባባይ ወይም ሕዝብ በሚያየው ቦታ መልካም ሥነ-ምግባርን ወይም መልካም ጠባይን የሚነካ ድርጊት አስቦ የፈጸመ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

### አንቀጽ ፰፻፵፱ አስነዋሪ የዝሙት ጥያቄ እና የብልግና ተግባር

ማንም ሰው በመንገድ፣ በአደባባይ ወይም ለሕዝብ ክፍት በሆነ ሥፍራ:-

ሀ/ መልካም ስነ-ምግባርን ወይም መልካም ጠባይን በሚቃረን መንገድ፣ ያልፈለገውን ወይም ያልጠየቀውን ሰው በድሪያ መልክ በመነካካት ያበሳጨው፤ ወይም

ለ/ ተገቢ ባልሆነ ጥያቄ ሌላው ሰው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም ለመልካም ስነ-ምግባር ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ወይም በኅብረተሰቡ የተወገዙ ማናቸውንም ዓይነት የብልሹነት ድርጊት እንዲፈጽም የገፋፋ፤ ወይም

BACK


ሐ/ በዝሙት ወይም በኅብረተሰቡ በተወገዙ ይህን መሰል ድርጊቶች በመሠማራት የጐረቤቶቹን ወይም የአካባቢውን ነዋሪዎች ያወከ፣

እንደሆነ፣ በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

አንቀጽ ፰፻፵፯ ለብልግና ተግባር የሚያነሳሳ ማስታወቂያና መግለጫ ማውጣት

ማንም ሰው የብልግና ተግባርን ለማበረታታት ወይም የሌላውን ሰው ፍትወተ ሥጋ ለማርካት ሲል ዝሙት የፈለገ ሰው በእንደዚህ ዓይነት ቦታ ራሱን ሊያስደስት ይችላል ብሎ በማናቸውም ዘዴ በይፋ ያስታወቀ እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

አንቀጽ ፰፻፵፰ የማስወረጃ ዘዴዎችን ማስተዋወቅ

ማንም ሰው በሕግ ከተፈቀደው ውጭ ፅንስን ለማስወረድ የታቀዱ ዘዴዎችን ወይም ምርቶችን ያስተዋወቀ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የማስወረድ አገልግሎት እሰጣለሁ ብሎ በይፋ ያስተዋወቀ እንደሆነ፣

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

ምዕራፍ አራት

በንብረት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

ክፍል አንድ

ብሔራዊ ሀብቶችን መጠበቅ

አንቀጽ ፰፻፵፱ ታሪካዊ፣ ኪነ-ጥበባዊ እና የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅ

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ:-

ሀ/ ታሪካዊ፣ የጥንታዊ ቅሪት /አርኪኦሎጅካዊ/ ወይም ኪነ-ጥበባዊ ሀብቶችን፣ የተፈጥሮ መስህብነት

ያላቸውን የተጠበቁ ስፍራዎች፣ ምንጮች ወይም ማናቸውም ዓይነት ብሔራዊ ሀብቶች ስለመጠበቅ፤ ወይም

ለ/ ብሔራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ታሪካዊ፣ የጥንታዊ ቅሪት /አርኪኦሎጂካል/፣ መልክአምድራዊ ወይም ተፈጥሮአዊ ሀብቶች መገኘታቸውን መግለጽን ግዴታ ስለመሆኑ፤ ወይም በቅርሶች ወይም በውድ ወይም በተከለከሉ ማናቸውም ዓይነት ነገሮች ስለመነገድ ወይም እነዚህኑ ወደውጭ ስለመላክ ወይም ወደአገር ውስጥ ስለማስገባት፣ ስለመከልከል፣ ስለመወሰን፣ ወይም ስለመቆጣጠር፤ ወይም

ሐ/ ታሪካዊ ወይም ጥንተ-ቅሪታዊ ሀውልቶችን፣ ተፈጥሮአዊ መስህብ ያለው ስፍራን ወይም በተለይ የተጠበቀ ቦታን ዋጋ ስለመጉዳት፣ ስለማበላሸት፣ ወይም ጉዳት ላይ ስለመጣል፤

የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፭፻፲፱</u> <u>እፅዋትንና እንስሳትን መጠበቅ</u>

ማንም ሰው ብሔራዊ ዕፅዋትንና ደንን፣ እንስሳትንና የዱር አራዊትን ስለመጠበቅ የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ሌሎች ንብረቶችን መጠበቅ</u>

<u>አንቀጽ ፭፻፳</u> <u>የመንግሥት እና የግል ንብረቶችን መጠበቅ</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፮፻፹፭ - ፮፻፻፹፯ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ የመንግሥት ወይም የግል ንብረትን ለመጠበቅ የወጣ ሕግን፣ ደንብን ወይም መመሪያን የተላለፈ በተለይም:-

BACK



ሀ/ በሚገባ ሳይፈቀድለት በመንግሥት ወይም በግል ይዞታ ስር ከሆነ መሬት ላይ አፈር፣ ድንጋይ፣ እንጨት፣ አሸዋ ወይም ከመሬት ላይ የሚገኝ ሌላ ነገር፣ ሣር፣ በመደዳ የተተከሉ ዕፅዋቶችን፣ አትክልት ወይም ፍራፍሬ ወይም ሌላ ነገር የወሰደ፤ ወይም

ለ/ በማናቸውም ወቅት ቢሆን ሳይፈቀድለት ወይም መብት ሳይኖረው በታጠረ ወይም በተዘራ መሬት ወይም አዝመራ ወይም ፍሬ በያዘ መሬት መካከል የገባ ወይም ያለፈ ወይም በእንደዚህ ዓይነቱ ቦታ ላይ የቀንድ ወይም የጋማ ከብቶቹን እንዲያልፉ የነዳበት፣ የለቀቀ ወይም አሰማርቶ ያስጋጠ፤ ወይም

ሐ/ በተከለከለ የአደን ወይም የዓሣ ማጥመጃ ስፍራ ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ የገባ፤

እንደሆነ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

## አንቀጽ ፰፻፶፪ ቀላል ስርቆት

፩ ማንም ሰው በችግር ወይም በፍላጐት ተነሣስቶ ወይም ሕሊና በማጣት ባለአነስተኛ ዋጋ የሆነውን የሌላ ሰው ንብረት ወዲያውኑ ሊበላው ወይም ሊገለገልበት የወሰደ እንደሆነ፤

ከሃምሳ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

ጥፋተኛው ስርቆቱን የፈፀመው በአግባቡ በተረጋገጠ ችግር ወይም እጦት ወይም ተገፋፍቶ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ላይወስንበት ይችላል::

፪ ወደላይ በሚቆጠር ወላጅ፣ ወደታች በሚቆጠር ልጅ ወይም ባልተፋታ የትዳር ጓደኛ ላይ የተፈጸመ ቀላል ስርቆት የሚያስቀጣ አይሆንም::

፫ የተሰረቀው ነገር ባለአነስተኛ ዋጋ መሆን አለመሆን፤ ለስርቆት ወንጀል መኖር መሠረታዊ ነገር የሆነው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና የማግኘት አሳብ /አንቀጽ ፮፻፷፭/ ለቀላል ስርቆት ተቀባይነት ይኑረው አይኑረው የሚለው መመዘን ያለበት እንደነገሩ ሁኔታ፣ በአካባቢው ልማድ መሠረት እና የተሰረቀውን ነገር በማየት ይሆናል::

<u>አንቀጽ ፰፻፶፫</u> <u>እሸት መቅጠፍና ከማሣ መቃረም</u>

ማንም ሰው በዓመቱ በማናቸውም ወቅት:-

ሀ/ እስፍራው ላይ ለመብላት የሌላ ሰው ንብረት የሆነውን ፍራፍሬ፣ የእህል እሸት፣ አትክልት እና ሌሎች የእርሻ ወይም አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ያለፍቃድ የቀጠፈ ወይም የለቀመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሌላ ሰው ይዞታ ስር ካሉ እርሻዎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ቦታዎች ወይም ሰብላቸው በሙሉ ካልተነሣባቸው ማሳዎች በጀንበር መውጫና መጥለቂያ መካከል ባለው ሰዓት፤ እህሎችን፣ ፍራፍሬዎችንና ይህን የመሳሰሉ ሌሎች ነገሮችን የቃረመ፣ የሰበሰበ ወይም የለቀመ እንደሆነ፤

ከዚህ በላይ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፶፬</u> <u>አጠራጣሪ የሆኑትን አንዳንድ ዕቃዎች ያለምክንያት መያዝ</u>

ማንም ሰው ከየት እንዳመጣቸው ወይም ለምን አገልግሎት እንደሚጠቀምባቸው በበቂ ምክንያት ለማስረዳት የማይቻለው ሆኖ ቁልፎችን፣ መክፈቻዎችን፣ የቁልፍ ማንጠልጠያ ቀለበቶችን፣ ጉጠቶችን፣ ልዩ ልዩ ምሣሮችን፣ መሣሪያዎችን፣ ባለዋጋ የሆኑ ሰነዶችን ወይም ሌሎች ዕቃዎችን ይዞ የተገኘ እንደሆነ፡

ከአንድ መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፮፻፶፭ ንብረቶችን መሰወርና አግባብ ላለው ባለሥልጣን አለማስታወቅ

ማንም ሰው፦

ሀ/ ሌላ ሰው የረሳውን ወይም የጠፋበትን ዋጋ ያለው ዕቃ ወይም መሬት ተቀብሮ የተገኘን ዕቃ /አንቀጽ ፮፻፵/ አግኝቶ፤ ወይም

ለ/ በስርቆት ወይም በንብረት ላይ በተፈፀመ ሌላ ወንጀል የተገኘውን ማናቸውም ዓይነት ዕቃ ሳያውቅ ከሌላ ሰው ካገኘ ወይም ከተቀበለ በኋላ ንብረቱ የወንጀል ውጤት መሆኑን ጠርጥሮ፣ አውቆ ወይም አረጋግጦ፤

ሁኔታዎችና ሌሎች የአካባቢ ምክንያቶች እንዲያስታውቅ እንደፈቀዱለት ወዲያውኑ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፮፻፶፮ የሌላ ሰውን ንብረት ማበላሸት ወይም ዋጋው እንዲቀንስ ማድረግ

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፮፻፹፱ እና ፮፻፺(፩) መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ በጥሩ ሁኔታ የመያዝ ኃላፊነት ያለበትን የሌላውን ሰው ቤት፣ ህንፃ ወይም ግድግዳ በበቂ ሁኔታ ባለመያዝ ወይም ባለመጠገን፣ በሌላ ሰው መሬት ላይ የግንባታ ሥራዎችን በማድረግ፣ መግቢያ መውጫ በማሳጣት፣ አንዳንድ ማቴሪያሎችን ወይም ዕቃዎችን በመጣል፣ የውሃ ወይም

የሌላ ፍሳሽ መፍሰሻ ቦዮችን አቅጣጫ በመቀየር ወይም በተገቢ ሁኔታ ባለመያዝ፣ ተሽከርካሪዎችን ወይም ጉታች የጭነት ወይም የግልቢያ እንስሳዎችን በመጥፎ ሁኔታ ወይም ከተገቢው ፍጥነት በላይ በመንዳት ወይም አብዝቶ በመጫን፣ የጦር መሣሪያዎችን ወይም ሌሎች መሣሪያዎችን አጠቃቀም ሳያውቅ ወይም በግዴለሽነት በመጠቀም ወይም በቸልተኛነት የሌላውን ሰው ንብረት ያበላሸ ወይም ዋጋው እንዲቀንስ ያደረገ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፰፻፶፪</u> <u>በሕዝብ ሀውልቶች ላይ ጉዳት ማድረስ</u>

ማንም ሰው ከባድ ጉዳት ሲደርስ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፮፻፺፯(፪) መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ፣ ለሕዝብ አገልግሎት ወይም መደሰቻ ተብሎ የተሠራውን ሐውልት፣ ህንፃ ወይም የተቀረፀ የመታሰቢያ ምስል ወይም ይህን መስል ሌላ ሥራን ያበላሸ ወይም ያቆሸሸ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>በንብረት ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች በጠቅላላው</u>

<u>አንቀጽ ፰፻፶፫</u> <u>የሌላውን ሰው ጥቅም በተንኰል መጉዳት</u>

ማንም ሰው ሕገ-ወጥ ብልጽግናን ለማግኘት በማቀድ ሳይሆን በክፋት፣ ለመጉዳት በማሰብ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ተነሳስቶ የማጭበርበር ወይም የማሳሳት ዘዴ በመጠቀም አንድ ሰው የራሱን ወይም የሌላ ሦስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጐዳ ድርጊት እንዲፈጽም ያደረገ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፯፻፺፱</u> <u>ወስላታነት</u>

ማንም ሰው መክፈል እንደማይችል እያወቀ ለሕዝብ አገልግሎት በሚሰጡ ምግብ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ሆቴሎች ወይም መኝታ ቤቶችና በመሳሰሉት የንግድ ተቋማት ገብቶ ምግቦችን፣ መጠጦችን፣ መኝታን ወይም ማናቸውም ዓይነት ጥቅሞችን ያዘዘ ወይም ያገኘ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፯፻፯</u> <u>ሌሎች ጥቅሞችን በማጭበርበር ማግኘት</u>

ማንም ሰው በክፍያ ብቻ የሚገኙ ጥቅሞች መሆናቸውን እያወቀ በማጭበርበር ያለክፍያ ጥቅሙን ያገኘ እንደሆነ፤ በተለይም:-

ሀ/ በየብስ፣ በአየር ወይም በውሀ ላይ የሚመላለሱ ማናቸውም ዓይነት በሕዝብ ወይም በግል የመጓጓዣ ዘዴዎች የተገለገለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ወደ ትርዒት፣ መዝናኛ፣ ተውኔት፣ ኤግዚቢሽን ወይም ለትርፍ ወደ ተዘጋጀ ማናቸውም ተመሳሳይ ዝግጅት ውስጥ የገባ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ሳንቲም በማስገባት በሚሠሩ አቶማቲክ ማሽኖች በመገልገል እቃዎችን፣ ያገኘ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::

<u>አንቀጽ ፯፻፯፩</u> <u>አውቃለሁ ባይነት</u>

ማንም ሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፯፻ መሠረት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ:-

ሀ/ የሌላውን ሰው በነገሮች ቶሎ የማመን ዝንባሌ ተጠ ቅሞ በማናቸውም ዓይነት ሁኔታ በሚደረግ

የአውቅልሃለሁ ጥንቆላ፣ መናፍስትን በመጥራት፣ የተሸሸገ ገንዘብ የሚገኝበትን ዘዴ ማመላከት ወይም ይህን በመሰለ ማናቸውም ሁኔታ ገንዘብ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በማስተዋወቅ ወይም በሌላ መንገድ ጥቅም ለማግኘት እንደዚህ ዓይነት ሥራዎችን ወይም አገልግሎቶችን እንደሚሰጥ በይፋ ያቀረበ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፰፻፷፪ ያለፈቃድ ገንዘብ መሰብሰብ</u>

ማንም ሰው በሕግ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን ሳይፈቀድለት በአደባባይ እየዞረ ገንዘብ የሰበሰበ ወይም የጠየቀ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል።

ገንዘብ መሰብሰቡ የተፈጸመው ሀይማኖታዊ ሥርዓት በሚፈጸምባቸው ሕንፃዎች ውስጥ ወይም በግለሰብ፣ በሙያ፣ በስፖርት ወይም ሌሎች ክለቦች፣ በልዩ ልዩ ማኅበሮች ወይም ክበቦች አካባቢና በተለይም የገንዘብ ማሰባሰቡ የተደረገው ለበጐ አድራጐት ወይም ለሥራቸው ማስኬጃ እንደሆነ፤ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም።

## ምዕራፍ አራት

## በኢኮኖሚ፣ ንግድና የባሕር አስተዳደር ጉዳዮች ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

<u>አንቀጽ ፰፻፷፫ የንግድና የሂሳብ መዛግብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መተላለፍ</u>

ማንም ሰው ከሕግ፣ ከደንብ ወይም ከመተዳደሪያ ደንብ የመነጨ ግዴታን በመተላለፍ በየጊዜውና በሥነ-ሥርዓት የንግድና የሂሳብ መዛግብትን ሳይዝ የቀረ ወይም ለመያዝ ችላ ያለ ወይም ከሥራው ጋር የተገናኙ መጻጻፎችን፣ ፋክቱሮችን ወይም ሌሎችን የንግድ

BACK


ሰነዶችን በሕግ እስከተወሰነው ጊዜ ድረስ ሳያቆይ የቀረ ወይም ለማቆየት ችላ ያለ እንደሆነ፤

በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል።

<u>አንቀጽ ፯፻፸፩ በግዴታ የፍርድ አፈጻጸም ሥርዓት ላይ እምቢተኛ መሆን</u>

ማንም ባለዕዳ ወይም ሦስተኛ ወገን በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፯፻፷፰ - ፯፻፸ መሠረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ፣ የመክሰስ ወይም ሂሳብ የማጣራት ሥልጣን ያለው አካል የሰጠውን ግልጽና ሕጋዊ ትዕዛዝ ለመፈጸም እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ፤ በተለይም እምቢተኛነቱ የሚመለከተው:-

ሀ/ በይዞታው የማይገኝ ቢሆንም እንኳ የራሱ ጠቅላላ ንብረት አካል የሆነውንና የሚፈለገውን ዕቃ፣ ብድር፣ የዕዳ ጥያቄ፣ ያለበትን ዕቃ፣ የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ መያዣ ወይም ይህን የመሳሰለ ማናቸውም ሌላ ግዴታ የማስታወቅ፣ የመግለጽ ወይም የማቅረብ ግዴታን ሲሆን፤ ወይም

ለ/ ቃሉ እንዲሰማ ወይም በሌሎች ፊት እንዲቀርብ፣ ስብሰባ እንዲካፈል፣ በድምፅ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፍ ወይም የዕዳ አከፋፈል ወይም የግዴታ የፍርድ አፈጻጸም ሥርዓትን በሚመለከት የሕግ ድንጋጌ የታዘዘውን ማናቸውም ሌላ ድርጊት እንዲፈጽም የደረሰውን ደንበኛ ጥሪ የመመለስ ግዴታን ሲሆን፤

በመቀጮ ወይም ከስምንት ቀን በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል።

## አንቀጽ ፯፻፯፮ ስለንግድ መርከቦች የወጡትን ደንቦች መጣስ

ማንም ሰው:-

ሀ/ የመርከቡ ካፒቴን፣ መኮንን ወይም ሠራተኛ ያለበትን እንደምልክት የመስጠት፣ መርከብን የመጐብኘት፣ የመመርመር፣ የመቆጣጠርና የመሳሰለውን የደኅንነት እርምጃ የመውሰድ ግዴታ፤ ወይም

ለ/ የመርከቡን የባህር መዝገቦች፣ መዝገቦች ወይም የሌሎች ሰነዶችን አያያዝ፤ ወይም

ሐ/ በባሕር ወይም በወደብ ላይ ጭነትን፣ ፖስታን ወይም መንገደኞችን ማጓጓዝን፣ ማሳፈርና ማውረድን፣ መጫንና ማራገፍን ወይም መንቀሳቀስን፤ ወይም

መ/ ጽዳት ወይም ጤና አጠባበቅን፤

በሚመለከት የወጡ የንግድ መርከብ ሕጎችን፣ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ፤

የወንጀል ሕጉ ወይም ይህን የሚመለከት ልዩ ሕግ ሌላ ድንጋጌ ተፈፃሚ ካልሆነ በቀር፤ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል::